NEW YORK TIMES BESTSELLER

# እውነተኛው የCIA ምስጢር

(እውነተኛ ታሪክ)




# SEE NO EVIL

## ROBERT BAER

ትርጉም ፡- ማጊ

# እውነተኛው የCIA ምስጢር

(እውነተኛ ታሪክ)

# SEE NO EVIL

## The True Story Of a Ground Soldier In The CIA's War On Terrorism

ትርጉም ፡ - ሚግ

t.me/OLDBOOKSPDF

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ ዕትም ሐምሌ - 2002

የሁለተኛ ዕትም ነሀሴ - 2002

ሦስተኛ ዕትም መስከረም - 2003

አራተኛ ዕትም ሐምሌ - 2003

አምስተኛ ዕትም ሐምሌ - 2008

ዋና አከፋፋይ

ዩኒቲ መጻሕፍት መደብር

ስልክ:- 0912 02 87 94

:- 0911 66 99 46

t.me/OLDBOOKSPDF

# መቅድም

ሀያላን ሀገራት የሀገራቸውን ምስጢርና ደህንነት ለመጠበቅ ሲሉ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ ረቂቅ የስለላና ደህንነት ሰዎችን ጊዜው ባፈራው ሳይንስና ቴክኖሎጂ በማሰልጠን፣ በማስታጠቅና በማደራጀት በህቡዕ ለአደን እንዲሰማሩላቸው የተደራጁ ተቋማትን እስከመመስረት ያስገደዳቸው ምክንያት ስንፈትሽ መረጃን ለመቃረምና ያሉበትንም ሁኔታ ከሌላው ጋር በንፅፅር ለመፈተሽ ብሎም የሀገርን ሉዓላዊ ጥሰት እንዳይደፍር ጋሻ ለመሆን ነው:: ከነዚህ ሀገራትም መሀከል የሁለተኛውንና የአንደኛው የዓለም ጦርነት የመጨረሻ ተዋናዮች የሆኑት ሩሲያና አሜሪካ KGBንና CIA'ን የመሳሰሉ የስለላ ድርጅቶች እንዲሁም ሁሌም ቢሆን በስጋት ለምትናጠውና ለደህንነቷ ስትል በ1948 የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃትን ተከትሎ እንደ ሀገር የተመሰረተችውና የበሬ ግንባር የምታህለው እስራኤል 'MOSSAD' የተሰኘውን ተቋም አቋቁማለች::

ሌሎች ሀገራትም በተመሳሳይ የራሳቸውን የረቀቁ የስለላ ተቋማትን ያደራጁ ሲሆን በተለይም የዮናይትድ ስቴትስ የማዕከላዊ የስለላ ድርጅት በተለምዶ አጠራር CIA የተመሰረተበትን 60ኛ ዓመቱን እንደማስቆጠሩ መጠን ድርጅቱ በዚህ ዕድሜው አስደናቂና ብዙም ግዜም አወዛጋቢነት ያልተለያቸውን ታሪኮችን አስተናግዷል:: ሀገሪቷም በየዓመቱ ከፍተኛ በጀት ለስለላ ተግባራት እየመደበች በአብዛኛው በሲቪል ምሁራን የተገነባውን የሀገሪቱን ከፍተኛ የስለላ ተቋም ማለትም CIA'ን ታጠናክራለች::

የቀድሞውም ሆነ የአሁኑ የአሜሪካ የመረጃ ባለሙያዎች ጃፓን ሳትጠበቅ በአሜሪካ የፐርል ሀርቦር ወደብ እ.ኤ.አ ታህሳስ 7/1941 የፈፀመችው ድንገተኛ የቦንብ ጥቃት ለአሜሪካ ማዕከላዊ የስለላ ድርጅት ማለትም ለCIA መፈጠር ምክንያት መሆኑን በመስማማት ይናገራሉ:: በዚህ መነሻነትም ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ሩዝቬልት በጀርመንና በጃፓን በተያዙ አካባቢዎች የስለላ ሥራ እንዲያከናውኑ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኃላ ቀደም ሲል የነበረውንና በአብዛኛው ጦር መኮንኖች የተደራጀውን የስትራቴጂያዊ አገልግሎቶች ቢሮ የተባለውና (oss) በሚለው ምህፃረቃል የሚታወቀውን ድርጅት አቋቋሙ:: በመስጠቅም የዮናይትድ ስቴትስ ም/ቤት ያሳለፈውንና ፕሬዚዳንት ትሩማን ያፀደቁትን የብሔራዊ ፀጥታ ጉዳይ ሕግ ተከትሎም እ.ኤ.አ መስከረም 18/1947 CIA ተወለደ:: ድርጅቱም በተመሰረተበት የመጀመሪያ ጊዜያት በጦርነቱ ወቅት የአሰራር ልምዳቸውን ይዘው በመጡ የ oss አንጋፋ ሰራተኞች በብዛት ተካተውበት ነበር::

oss የአሜሪካ የጦር ኃይል አንዱ ክንፍ ሲሆን በዋንኝነት የሚሰራውም የተለያዩ ሀገራትን የጦር ኃይል ጥራትና ብዛት እንዲሁም ያላቸውን የጦር መሳሪያ አይነት የሚሰልል ነበር:: እናም ይህ ተቋም በውስጠ ታዋቂነት እስከ 2004 ድረስ የቀጠለ ሲሆን በ2004 CIA



t.me/OLDBOOKSPDF

ባደረገው የማሻሻያ ለውጥ /ተሀድሶ ምክንያት ሙሉ በሙሉ በሲቪል የሰለጠና የደህንነት ባለሙያዎች እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላም ከ CIA ጋር በጥምረት በመሆን ቀደም ሲል ከነበረው የጦርነት ስልቶችና የጦር መሳሪያዎችን ከመሰለል ውጭ እንደ አሸባሪነት፣ የውጭ ሀገራት ፖሊሲን መፈተሽ፣ አንዳንድ ስጋት የሆኑ አለምአቀፍና ሀገር አቀፍ ተቋማት ላይ የመረጃ ስለላ ማድረግ እንዲሁም የስነህዝብ ፖሊሲ አውጪዎችን ማማከር የመሳሰሉትን አካቶ ጠንካራ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ጊዜ አሜሪካውያን እንደደህንነት ጋሻቸው የሚያዩት CIA በአንድ ዋና ዳይሬክተርና በአራት ዋና ዋና ቢሮዎች ተደራጅቶ የሚመራ ሲሆን የበላይ ጠባቂውም የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ነው፡፡ በተቋሙ ላይ በተለይም የሽብርተኝነት ተግባር በአዲስ መልክና ቅርፅ እየተስፋፋ ከመጣበት ከ 1990 ዎቹ ጀምሮ በርካታ ጥቃቶችና የመረጃ ስርቆቶች እንዲሁም የቢሮክራቶች ተልፍልፍ ማነቆዎች የተነሳ የታሰመውን ግብ እንዳይመታ ዕንቅፋት ሆኖበታል፡፡ ለዚህም እንደአብነት ተጠቃሽ የሚሆነው ቦብ ቤር ነው፡፡

ቦብ ቤር ብቻውን አይደለም እንጂ! በድህረ-ቀዝቃዛ ጦርነቱ ጊዜ በ CIA በቆየባቸው አስገራሚ ታሪክ እየተረሳ ይሆን ይሆናል፡፡ ግና አሜሪካ መከላከያ በሚያስፈልጋት በዚያ ተቀውጢ ወቅት ከጥቃት ሊታደጋት ያልተቻለው የዚያ ተቋም ታሪክ ሕዋስነቱ ዛሬም አብሮት አለ፡፡ ቤርን ይገጥሙት የነበሩት ቢሮክራቶች፣ ልፍስፍነት፣ የኋይት ሃውስ ባለስልጣናቱ ግዴለሽነት በጡረታ ለተገለሉትና በደርዘን ለሚቆጠሩ ውጤታማ ለነበሩት ዛሬም ቢሆን ተቋሙን በመለወጥ ረገድ ሚናያላቸው ለሚያስመስሉ ልዩ የ CIA ሰራተኞች ሳይቀር እውነታነት አለው፡፡ ከእነዚሁ የ CIA ሰራተኞች አብዛኞቹን በቅርብ ጊዜያት የማግኘቱ ዕድል ገጥሞኛል እናም ሰራተኞቹ እንደ ቤር ሁሉ በውጫር የሚቆራቆሩና የሚማትቱ በብስጭትና ተስፋ መቁረጥ ስሜት የተሞሉ ሆነው አግኝቼአቸዋለሁ፡፡ እንደቤር ሁሉ የተሰማቸውን ግዳጅ በርትዕና ውጤታማ በሆነ መልክ እንዲወጡት እንደማይደረግም ተረድቼአለሁ፡፡

ይን ሁሉ ስል ታዲያ የአሜሪካውን መረጃ ማዕከል ስረ-መሠረት መዳሰሴ ነው፣ ይህ መጽሐፍ እየተፃፈ ባለበት የመስከረም አስራአንዱ ጥቃት ከደረሰ ከሶስት ወር በኋላ እንኳን ቢሆን የመረጃው ማህበረሰብ ጥቃቱ እንደምን ገቡን ሊመታ እንደቻለ፣ ጥቃ ፈፃሚዎቹ የት እንደሰለጠኑ፣ የማን መልዕክተኛ እንደሆኑና መሳዩን ጥቃት ዳግም ያድር እያድርሱ ሊነግረን አልቻለም፡፡ የቡሽ አስተዳደር በተደጋጋሚ ሲኮንን እንደሚደመጠ የጥቃቱ ፈፃሚዎች አሳማ ቢን ላደንና የአልቃይዳ መረቡ ይሁን? ወይንስ ቦብ ( እንደሚናገረው ከነዚህ በተጨማሪ አንድ ሌላ የመካከለኛው ምስራቅ ሽብርተኛ ቡ በጥቃቱ ተካፋይ ሆኗል?! በርግጠኝነት የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ግና ገሃድ እየፈ ያሉት እውነታዎች የቤርን ግምት የሚያጠነክሩና የሚያስምሩ ስለመሆናቸው አበ አስገነዝባለሁ፡፡ አሜሪካ ላይ ያነጣጠሩት የእነዚያ ጥቃቶች ጠንሳሽ ከአፍጋኒስ ዋሻዎችና ጉድባዎች በአንደኛው የመሸገ አንድ ሰው ብቻ አለመሆኑንም ለማስገን እወዳለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በሌላም መልኩ ይህንን 'ሲና ኢቭል' የተሰኘን መጽሐፍ የስለላ ስራን እንደሚያሳይ አንድ ትዕይንትም መውሰድ ይቻላል፡፡ ቤር ግዳጁን እየተወጣ በነበረባቸው ጊዜያት ሁሉ የአለቆቹ ቂልነትና አጥርቶ መወሰን አለመቻል ያተረፉለትን ብስጭት እናጤናለን እንደ አንድ ጎረምሳ ሁሉ የበረዶ ተንሸራታች ስፖርተኛ የነበረ ቢሆንም አስተሳሰቡ፣ እምቅ ችሎታውና ሞገደኝነቱ ተዳምረው በህይወቱ ላይ ስር-ነቀል ለውጥ ማድረግ አስችለውታል፡፡ ስለሽብርተኞቹም ዓለም ጥልቅ ግንዛቤ እንዲወስድም አርገውታል፡፡ ቤር ሁሌም ቢሆን በስውር የሚፈፅማቸውን ተልዕኮዎች በአግባቡ ተወጥቶአል፡፡ በራሱ ፍላጎት ለግዳጅ በተሰማራባቸው ሊባኖስ፣ ታጃኪስታን ጀርመንና ሰሜናዊ ኢራቅ የተደቀኑበትን አደጋዎች ማለፍም ችሏል፡፡ በኋይት ሃውስ ላይ ሊያንዣብቡ የሚችሉትን አደጋዎች መኖራቸውን ጠቁሟል፡፡ ከዚህ የተነሳ የሽብርተኞች ጥቃቶች በማናቸውም ጊዜና ስፍራ ሊፈፀሙ ስለመቻላቸውም እርግጠኛ ሆኗል፡፡

ቤር CIA ውስጥ ግዳጁን ይፈፅም በነበረባቸው ቀደምት ጊዜያት ይወስዳቸው ስለነበሩት ስልጠናዎች ብቃትና ስለአሰልጣኞቹ እውቀት ያወጋናል፡፡ 'ስለላ በእርግጥ ከአንድ መጽሐፍ የምትማረው፣ ከስልጠና ፊልም የምትቀዳው አሊያም ከክፍል ውስጥ ገለፃ የምትካነው ጥበብ ብቻ አይደለም፡ 'በይበልጥ ልትካነው የምትችለው አንድ ሰው የአዕምሮህን ጓዳ አሻግሮ ሲያይልህና ሆነኸው ስትገኝ ብቻ ነው፡፡' ቤር የባህር ማዶ ግዳጁን በመውጣት ላይ በነበረባቸው ጊዜያት በስሩ የሚገኙትን አንዳንድ ምልምሎች ለስራው የማይመጥኑ ሆነው አግኝቶአቸዋል፡፡ አልፎ አልፎም ቢሆን ምርጥ ችሎታቸውን የሚለግሱ የስራ ባልደረቦቹም በትጋት ግዳጃቸውን እንዲወጡ የሚያሪጉ አለቆች ገጥመውታል፡፡ እርግጥ ነው እንደ አንድ ሰላይ ሁሉ አስቀድሞ ስልጠና ወስዷል፡፡ ስልጠናውን የወሰደው ግን ፈቃደኛ በመሆኑ ነበር፡፡ ያም ስለላን ሳታነብ አታስበው የሚል ውጤታማ ትምህርት አስተምሮት አልፏል፡፡ ቤር የሽብርተኞችን መረብ ለመበጣጠስ ዶሴዎችን በማገላበጥና እየነቀሰ በማንበብ ከመዓልት እስከውድቅት ሌሊት እንደምን ራሱን ያጠምድ እንደነበር ያወጋናል፡፡ እያደዘም ያንን ማድረግ ያልቻሉ የሥራ ባልደረቦቹ ሙከራቸው ስለምን እንደሚከሽፍ በዚህ መጽሐፍ ያትትልናል፡፡ እኛም የቤር ታሪክን ተመርኩዘን አንድ ጥሩ የ CIA መረጃ ሰራተኛ እንደምን ግዳጁን እንደሚወጣ እንመለከታለን፡፡

የዚህ እውነተኛ ታሪክ ዳራ ዛሬ በውጤታማነቱ የምንታመንበት ድርጅት ላይ ያለውን የገነፈለ ቁጣ የሚገልፅ ሰው ታሪክ ነው፡፡ ታሪኩ ስለ ቤር ትምህርት፣ እድገትና፣ ነፃነት ይገልፃል፡፡ ቤር CIA ውስጥ ባገኘው የስልጠና ድጋፍ እንደምን ራሱን በመረጃ ዘርፍ እንዲካን እንዳደረገውም የታሪኩ ፍሰት ያትትልናል፡፡ ጥያቄው ግን እንደ CIA ባለና አንድነቱ በሂደት በተናጋውና በተሸረሸረው ድርጅት ውስጥ አንድ ሰው ለውጥ ሊያመጣ ይችላልን? የሚል ነው፡፡

ስለሆም 'ይህ ሲና ኢቭል' የተሰኘ መጽሐፍ 'አንድ አይነድ አንድ አይፈርድ' የሚል ምላሹን ይሰጠናል፡፡ ይህ የአንድ ሰው የህይወት ተሞክሮ በተቋሙ አመራር ቦታ ላይ ያሉ ግለሰቦች ላይ ተፅእኖ ለማድረግ አልተፃፉም፡፡ ይልቁኑ ዛሬም ተቋሙ ትክክለኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

እመራር እስካገኘና ከአለፈው ስህተቱ እስከተማረ ድረስ መፃዒ ተስፋ ሊኖረው መቻሉን የሚያመላክት ዳራ ነው እንጂ!

CIA ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚችሉ ትልቅ ሀገራዊ ራዕይ የሰነቁና አዲስ የአስተዳደር ሰዎች እስካገኘ ድረስ ሌሎች ቦብ ቤርን የመሰሉ ሰዎችን ማፍራቱ የማይቀር መሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነው፡፡ እናም ታዲያ ያ መሆን ያለበት ግን ዳግም የሽብርተኞች ክንድ ሳያርፍብን ነው፡፡

ሴይሙር ኤም.ኸርሽ (ኤክስፐርት)

ዋሽንግተን ዲሲ



t.me/OLDBOOKSPDF

# መግቢያ

በ1994 ዓ.ም ማለቂያ ግድም ኑሮዬን ጢያራ/አውሮፕላን ውስጥ ያረግኩበት ጊዜ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ ....... ከአንድ ሰዓት በኋላ አማን ጆርዳን እደርሳለሁ፡፡ አልጋ አንድ ሆቴል እይዛለሁ ፈጠን ብዬም ከተለቃለቅኩ በኋላ እራቴን እመገባለሁ፡፡ ሌቱንም በሳጻም ሁሴን ላይ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ከአንድ የኢራቅ ተቃዋሚ አንጃ ጋር ስነጋገር እነጋለሁ፡፡ ....... አልፎ አልፎም ቢሆን ጎኔን አልጋዬ ላይ የማሳርፈው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነበር፡፡ ምንም ያህል ሳላንቀላፋ ወደ ዋሽንግተን የሚጓዘውን አውሮፕላን እይዛለሁ፡፡ ከዛም ላንግሊ ቨርጂኒያ ከሚገኘው የ CIA ጠቅላይ መምሪያ ወዳለው ቢሮዬ እጓዛለሁ፡፡ ይህንኑ ለበርካታ ጊዜያት ደጋግሜዋለሁ፡፡ ይሁንና ተላምጄዋለሁ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለሃያ አራት ዓመታት ወደ መካከለኛው ምስራቅ ተመላልሻለሁ፡፡

አልፎ አልፎም ቢሆን በዚህ ምስጢራዊ ከአገር አገር የሚያዘዋውረው ዲፕሎማሲያዊ ስራ መሃል እረፍት ለመውሰድ ወደ ለንደን እቀናለሁ፡፡ ንፋስ ለመቀበልም ከተማዋ ውስጥ የእግር ጉዞ በማረግበት ጊዜም የምከተለው የተለየ መንገድ አልነበረም፡፡ አንዳንዴም የእግር ጉዞዬ ፍፃሜ የከተማዋ ዕምብርት ወደ ሆነችው "ኤጁዌር" ጎዳና አካባቢ ሆኖ አገኘዋለሁ፡፡ ይህም አካባቢ በአረቦችና በሌሎች የመካከለኛው ምስራቅ ተዋላጆች መኖሪያነቱ የሚታወቅ የማዕከላዊ ለንደን ክፍል ነው፡፡ እዛም ሂጃብ ያጠለቁት ሴቶችንና ጀለቢያ የለበሱ ወንዶችን ሳይ መካከለኛው ምስራቅ ያለሁም መስሎ ተሰምቶኛል፡፡ ግና አካባቢውን ከመካከለኛው ምስራቅ የተለየ የሚያደርጉት ነገሮች መኖራቸውንም ለመቃኘት ችያለሁ፡፡

እዚያ በነበርኩባቸው ጊዜያቶች በአብዛኛው መካከለኛው ምስራቅ ክፍል የሚገኙ መፃህፍት መደብሮች እስላማዊ አክራሪነትን የሚሰብኩና ለአመፅ የሚያነሳሱ በራሪ ፅሁፎች እንዳይሸጡ የሀገራቱ መንግሥታቶች ይከለክሉ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ለንደን ውስጥ ያሉት የአረብኛ መፃህፍት መደብሮች ግን መሰሎችን በራሪ ፅሁፎችን ይሸጣሉ፡፡ በበራሪ ወረቀቶቹ ላይ በደማቅ የሚፃፉት ፅሁፎች አረቦች በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ያላቸውን ጭፍን ጥላቻ የሚገልፁ ስለመሆናቸው ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም፡፡ ፅሁፎቹንም ባላተሙአቸው አሳታሚዎች አመለካከት "ጅሃድ" አሊያም "ቅዱስ ጦርነት" በእስልምና ተከታዮችና በአሜሪካ መሀል መፈንዳቱ ግምታዊ ብቻ ሳይሆን እርግጠኛነትም ነበረው፡፡ እንደነሱ ገለፃም ጦርነቱ ከመታወጁም በላይ ተሰብቋል፡፡ አብዛኛውን የህይወቴ ክፍል መካከለኛው ምስራቅ እንደማሳለፌ መጠን ለአመፅ የሚያነሳሳ ጥላቻ ከእስልምና የዕምነት ዓምድ ያፈነገጠ ስለመሆኑ መናገር እችላለሁ፡፡ ከማን በበለጠ መሰሉ የነውጥ ጥላቻ የሚያስከትለውን ሰብዓዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከበራሪ ጽሁፎቹ ውስጥ አንዳንዱን አንስቼ የተወሰነ ክፍሉን ለመመልከትም ሞክሬያለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እናም የአሳታሚው ወይም የአዘጋጁ ስም ተገልፆ የማገኘው ከስንት አንዴም ነው፡፡ የአሳታሚው አድራሻ እንደማይገለፅም ማየት ችያለሁ፡፡ ግን ከስንት አንዱ ላይ የብሪታኒያ ወይም የጀርመን የሆነ አውሮፓዊ የፖስታ አድራሻ ሰፍሮ አገኛለሁ፡፡ ከዚህም በፀረ - ሽብር እንቅስቃሴው ከጎናችን የተሰለፈችው አውሮፓ የእስላማዊ አክራሪዎች መፈልፈያ መሆኗን ለማወቅ ውስብስብ የመረጃ ስራን እንደማይጠይቅ ተረድቼያለሁ፡፡

ለንደን ውስጥ የሚገኙ የ CIA የስራ ባልደረቦቼን በራሪ ወረቀቶቹን የሚያሳትመው ማን እንደሆነ ያውቁ እንደሆን ብጠይቃቸውም ስለነገሩ የማያውቁ መሆኑን ገልፀውልኛል እንደ እውነቱ ከሆነ ማወቅም አለባቸው አልልም፡፡ የለንደኑ ቢሮአችን አንድን ሰው አረብኛ ተናጋሪ በመሆኑ ብቻ አሊያም በኤጅዌር ጎዳና በመመላለሱ ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም፡፡ የስራ ባልደረቦቼ በራሪ ወረቀቶቹ ይዘው የሚወጡአቸውን መርዘኛ ርዕሰ-ዜናዎች ማንበብ አይችሉ ይሆናል፡፡ በተጨማም CIA በእስልምና አክራሪዎች ላይ በዚያ እስካሉ ድረስ ምርመራ እንዳያካሂድባቸው በብሪታኒያ ባለስልጣናት እግድ ተጥሎበታል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ ታዲያ እዚያ ካሉ አረቦች መረጃን እንደምን መቃረም ይቻል ይሆን???

ባጠቃላይ በአህጉሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረው አለመረጋጋት መሻሻል አላሳየም፡፡ በ1990ዎቹ አጋማሽ CIA በሁሉም አውሮፓ ክፍሎች በነበረበት ሁኔታ መቀጠል ከማይችልበት ደረጃ ደርሶ ነበር፡፡ በቦን፣ ፓሪስ እና ሮም የነበሩት ቢሮዎቻችን ከሶቪየት ጋር ከነበረን ቀዝቃዛ ጦርነት ቅሪትነት የዘለለ ትርጉም አልነበራቸውም ቢሮዎቹ አውሮፓን ያጥለቀለቋትን የመካከለኛ ምስራቅ ተወላጆች ላይ ክትትል የሚያረጉ ሰራተኞች አልነበሯቸውም፡፡ ሰራተኞቹ ቢኖሩም እንኳ ተልዕኮውን የመፈፀም ዝንባሌ፣ ስልጠናና ፈቃደኛነት ይጎላቸው ነበር፡፡

የመካከለኛው ምስራቅ ሁኔታም እየከፋ ሄዷል አልፎ አልፎ አንድ ወይም ሁለት CIA ባለስልጣናት ለእየአንዳንዱ አገር ይመደቡ ነበር፡፡ በዓለም ላይ ያሉ CIA ጣቢያዎች የውጭ ሰላዮችን በመመልመልና የመረጃ ምንጮችን በማነፍነፍ ፋንታ ለዋሽንግተን ወቅታዊ በሆኑት ሰብአዊ መብቶች፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ግሎባላይዜይሽን በአረብ እስራኤል ግጭት ዙሪያ ራሳቸውን አጥምደዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ እንደኔ አይነቱ የቀድሞ ወታደር CIA ሰንደቁን ከማውለብለብ ያለፈ ስራ እየሰራ እንዳይደለ ግንዛቤ ይጨብጣል፡፡

***



t.me/OLDBOOKSPDF

በዛ ያለውን ጊዜያችንን ከመካከለኛው ምስራቅ የምናጠፋ CIA ባልደረቦች የሆንን አብዛኞቻችን ትልቅና አስፈሪ አደጋ ሊደርስ ይችላል የሚል ስጋቱ ነበረን፡፡ ብዙዎቻችን የአረቡ እስም ለአሜሪካ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳላቸው እናውቃለን፡፡ የአሜሪካንን ንፀሀና ጥላሸት የሚቀቡ ጥቂት እንዳልሆኑና የጥፋት ተልዕኮዎች እንዳሉም እንረዳለን፡፡ ይሁንና የመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት በእስም ንግድ ማዕከል እና ፔንታጎን ላይ እንደሚቃጣ ግምቱን በትክክል መሰንዘር የቻለ ሰው መኖሩን እጠራጠራለሁ፡፡ በምን ሊ ብር መለኪያ ጥቃቱ እንደሚደርስ ማመላከት የማይቻል እንደነበር እናገራለሁ፡፡ ቁም ነገሩ ግን ይህ ሳይሆን መፃኢውን ነገር ቀድመን መናገር አለመቻላችን ነው፡፡

እንደተቀሩት የዋሽንግተን ተቋማት ሁሉ CIA'ም ከቴክኖሎጂ ጋር እጅና ጓንት ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር የ CIA ሰራተኞች ሳተላይቶችን፣ ኢንተርኔት፣ የኤሌክትሮኒክስ መጥለፊያ መሳሪያዎችንና የትምህርት ሀትመት ውጤቶችን ሳይቀር በመረጃ ምንጭነት እያነፈንፍን እንጠቀማለን፡፡ ከድንበር ባሻገር በመካሄድ ላይ ስላሉ ነገሮች ያሉንን ግንዛቤዎች እናዳብራለን፡፡ እስላም አክራሪዎችን በተመለከተ ያለውን የመረጃ ክፍተት የአውሮፓና መካከለኛ ምስራቅ ወዳጆቻችን ሊሞሉት እንደሚችሉ አለቆቻችን ያምናሉ፡፡ ይሁንና አንዳንዴ የመረጃ ክፍተቱን ለመሙላት የራሳችንን ሰላዮችና የውጭ መረጃ ምንጮችን መጠቀማችን ውጤቱ እጅግ አስከፊ የሚሆንበትም ጊዜ ነበር፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የደህንነት መኮንኖቻችን ያልተገራና ያልታረመ ፀባይና ኩነቶችን በሚያንፀባርቁበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ አስቀያሚ ዲፕሎማሲያዊ ቀውስ ያስከትላሉ፡፡ ከዚህ ሁሉ የከፋው ደግሞ በዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ዙሪያ ፊታውራሪ ነኝ የምትለዋ አገራችን ለዓለም ያላትን ትውፊትና ሞራላዊ ብቃት ማንፀባረቅ አለመቻሏ ነው፡፡

CIA በከንፋ ብዙ የደህንነት መኮንኖችን ያስጠለለ ድርጅት ብቻ ሳይሆን ከመካከላችንም የበሰሉና የብዙ ዓመት ተሞክሮ ያላቸውን የሚመርጥና ለስልጣንም የሚያበቃ ተቋምም ነበር፡፡ እነዚህም ተለዋዋጭ ባለስልጣናት ገዳቻቸውን እጅግ አደገኛና አስከፊ በሆኑ ስፍራዎችም የተወጡ የቁርጥ ቀን ጉምቱዎች ናቸው፡፡ ይሁንና በ1995 በመረጃ ተንታኝነት እንጂ የባህር ማዶ ተሞክሮ የሌለውን ግለሰብ በዘመቻ መምሪያ ኃላፊነት መሾሙ ብዙም ሳይቆይ እሱም በጡረታ በተገለለ ግለሰብ መተካቱ ይሄም ብዙ ሳይቆይ በቦታው 'ለፖለቲካ ተሳትሮ ምስጋና ይግባውና' በፖርቲ ማዕቀፍነት ከፍተኛ ማዕረግ ላይ የተቆናጠጠውን ሌላ ግለሰብ ሾመውበታል፡፡ እስቲ ይታያችሁ ጭብጦቹ በሙሉ ፊር ሳይዙ የተፈራረቁበት ባለስልጣናት ይሄ ለእኔ ልክ 'ባለቤት እንደሌለውና መሀንዲሶች እንደሚፈራረቁበት የተጀመረ ህንፃ ነው፡፡' የሚመስለኝ በዚህም የመስከረም አስረአንዱን ጥቃት ያቀደውና አውሮፕላን እንዲጠልፉ በማሰማራት በአሜሪካ ምድር ተፈፅሞ የማያውቅ ታላቅ ጥቃት እንዲፈፀም ያቀነባበረው 'ሙሃመድ አታ' በሀምቡርግ መስጊዶች ውስጥ ለጥቃት በመዘጋጀት ላይ እያለ እንኳን አስቀድሞ የሚነግረን የመረጃ ምንጭ አለመኖሩ ሊያስደንቀን አይገባም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

❖❖❖

መጽሐፉ ይህ ባለ አንድ እግር የሆነውን የቀድሞ ወታደር በቀዝቃዛ ጦርነት የነበረውን ግዳጅ በተጨማሪ ይዘከርልናል፡፡ ወታደሩ እንደሶቭየት ሁሉ በራሳቸው ጻፉ መጥፋት ከማይሹ ሽብርተኞች በተቃራኒ ወገን ሆኖ ተፋልሟል፡፡ ይህ ታሪክ አብዛኞቹ አሜሪካውያን መሄድ ስለማይሹባቸው ቦታዎች ይገልፃል፡፡ ብዙሃኑ አሜሪካውያን ከነርሱ ጋር ግንኙነት ባይኖረን እንመርጣለን ስለሚሏቸው ህዝቦችም ያትታል፡፡

ታሪኩ የተወሰደው ከማስታወሻ፣ ከምርመራ ፋይል፣ እና ከእለት ውሎ መመዝገቢያ ነው፡፡ ተደራሲያን ከመንግስት ፋይሎች ውጭ ታይተው የማይታወቁ ዝርዝር መረጃዎች ሊገጥሙት ይችላሉ ይህ ሊሆን የቻለውም አብዛኛው የህይወቴን ክፍል ያሳለፍኩት ማስታወሻ በመውሰድ ስለሆነ በግልፅ ለህዝብ ይፋ የሚሆኑ ባለመሆናቸው ዝርዝር መረጃዎቹ ተሰምተው ባያውቁም አያስገርምም፡፡ እያንዳንዱ የ CIA ሰራተኛ ቅጥር ሲፈፅም ማንኛውንም የጽሁፍ ስራ ከማሳተሙ በፊት ጽሁፉን ተቋሙ ሳንሱር (ቅድመ ምርመራ) እንዲያደርገው ተስማምቶ ይፈርማል፡፡ እኔ ግን ቅድመ-ምርመራው ከመፅሐፉ ያስወጣቸውን ነገሮች ሳይቀር እንዳሉ እንዲታተሙ አድርጌአቸዋለሁ፡፡ በዚህም ስለምን እነዚህን መረጃዎች ተሰምተው እንደማያውቁ አንባቢው ግንዛቤ ይወስዳል ብዬ አስባለሁ፡፡ ዝርዝር መረጃዎቹን ስለ ሽብርተኝነት አስከፊነት፣ ስላሳለፍኩት ህይወት ውጣውረድ፣ በመስከና አንዳዴም በዋሽንግተን ከአለቆቼ ጋር ለስብሰባ በተቀመጥንበት ሳይቀር የነበረውን እሰጣ-ገባ ለአንባቢ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ በማለት የሳንሱር መቀስ ሳያርፍበት እንዳሉ አቅርቤአቸዋለሁ፡፡

በመስክ ለግዳጅ በተሰማራሁባቸው ጊዜያት የፈፀምኩዋቸውን ስህተቶች ቅድመ ምርመራና ምንም አይነት ማስተካከያ ሳላረግ እንዲታተሙ አርጌአለሁ፡፡ አንባቢው በስለላው አለም ከስህተት መማር ምን ያህል ጠቃሚ ነገር እንደሆነ ልብ ማለት ይኖርበታል፡፡ ስራዬ ዋሽንግተን ልዩ ጥቅሞቿን ለማስከበር የምትከተላቸውን ፖሊሲዎችንና መስመሮች እንዳስገነዘበኝ አልደበቅኩም ራሴንም በክሊንተን ዘመቻ ድኅግ ዙሪያ ከሚነዛው አሉባልታ መዘፈቄንም አልሸሸግኩም፡፡ ቢሆንም ይቅርታ የምጠይቅበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ ይቅርታ መጠየቅ ካለብኝም ስለራሴ ደደብነት መሆን ይኖርበታል ሆኖም ህሊናዬ ይቅርታ ስለመጠየቅ የሚደውለው ደውል ካለ ያኔ አስብበታለሁ፡፡ እስካሁን ድረስ ግን አላቃጨለብኝም!



t.me/OLDBOOKSPDF

ራሴን በማጋለጥ ታሪኬን ይፋ ያረግኩበት ምክንያት ለፋብ ምዕተ ዓመት ያገለገልኩትን CIA 'ምን ነካው?' ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሆናል በማለት ነው፡፡ ተቋሙን ከውድቀት ለማንሳት ምን መደረግ ይኖርበታል ለሚለውም ጥያቄ ምላሽ ለማፈላለግም ሞክሬአለሁ፡፡ የመስክረም አስራ አንዱን ጥቃት የአንድ ስህተት ብቻ ሳይሆን እንደሰንሰለት የተያያዙ የብዙ ስህተቶች ድምር ውጤት እንደሆነ አስገንዝባለሁ፡፡ ጀርመናች እንደብሪታንያውያን፣ ፈረንሳዩችና፣ ሳውዲ አረቢያ ሁሉ ጉድ አርገውናል፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው የምንፈልገውን መረጃ አሲያም እንደተቋምነታቸው የመረጃውን ፍሰት አልለቀቁልንምና፡፡ ስህተቶቻችንን አርመን በሽብርተኝነት ላይ ደግም የበላይነት መቀዳጀ ቀላል እንዳልሆነ እናውቀዋለን፡፡ ግን ሊደረግ የሚችል ነው፡፡ እናም ታዲያ ሁሉም ነገር መጀመር ያለበት የ CIA ባለስልጣናት ወደ ትክክለኛው መስመር በማስገባት ሰራተኞቻቸውን በጥራትና በብቃት እንዲመለምሉ በማድረግ የመረጃ ምንጮችን በመስኪዶችና በሌሎችም የሽብርተኞቹ መጠለያ ባረጉዋቸው ስፍራዎች እንዲያነፈንፉ በማድረግ ይሆናል፡፡ ይህም የሽብርተኞችን የጥፋት ጥንስስ ወደ አስፈሪና አስደንጋጭ ሰበር-ዜና ከመቀየርና የአሳዛኝ ፊልም ጻራ ከመሆን ይታደገናል፡፡

ይህ ማስታወሻ አንባቢን ስለላ እንደምን መስራት እንዳለበት ያሳውቃል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ CIA መንገዱን የሳተው የት ነው? እንዴትስ ወደነበረበት እንመልሰው? ለሚሉት ተያያዥ ጥያቄዎች ምላሾችን እንደሚሰጥም እምናለሁ፡፡ ከዚህ በበለጠም መጽሐፉ ተጨማሪ አንድምታ አለው፡፡ በኔ እስተያየት ስለምን የCIA ውድቀት እንዳበሳጨኝ እንደሚያስረዳልኝ እገምታለሁ፡፡ ይህንንም ለማለት የፈለኩት ማንም ለአሜሪካ ደህንነት ተቆርቋሪ ነኝ የሚል ዜጋ በሁኔታው እንደኔው መቆጨትና ለሃገሩ ደህንነት በተጠንቀት ይቁም ለማት ነው፡፡ የCIA'ን ውድቀት እጅ አጣምሮ ማየት ብሄራዊ ሉአላዊነታችንን የምንጠብቅበትን ጋሻ እንደመጣል ማለት ነው፡፡

አሜሪካውያን የ CIA ውድቀት የተፈጠረው በአጋጣሚ አለመሆኑን ሊያጤኑት ይገባል፡፡ CIA በጥቅሉ የተዘፈቀው በፖለቲካዊ ጋሻ አጃግሬነቱ፣ በዋጋቢሶቹ የቤልትዌይ ጦርነቶች፣ በባለስልጣኖቹ መሃል በነበረው ሽኩቻ እና በሌሎችም ምክንያቶች ነበር፡፡ አለማችን የሽብርተኞች ጥቃትና ፍራቻ በሚንጥባት ወቅት የሽብርተኞቹን እንቅስቃሴ መቆጣጠር የነበረበት ይህ አንጋፋ ተቋም የራሱን የቤት ሥራ በማፅዳት ላይ ነበር፡፡ አሜሪካውያን ብዙ ገንዘብ ፈሰስ ያረጉበት ይህ ተቋም ከጭንቀት ሊታደጋቸው አልቻለም፡፡ ርግጥ በምቾት ይኖራሉ ሆኖም በዙሪያቸው ያሉት ውቅያኖሶች ብቸኛ መከላከያቸው ሆነዋል ራስን ማዳን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው አጀንዳ ሆኖ ሳለ ኋይት ሃውስ እና ብሔራዊ ደህንነት ካውንስሉ ራሳቸውን ወደ ንግድ መናሃሪያነት ለውጠዋል፡፡ በሃገር ቤት እና ውጭ ያሉትን የአሜሪካውያን ደህንነት ከማስቀደም ፈንታ የግዙፍ ንግድ ኩባኒያዎችን ጥቅማጥቅሞችን እንደ ግንባር ቀደም አጀንዳነት በመመልከታቸውና በጥቅማ ጥቅም በመታወራቸው ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

CIA'ም ረጅሙን ተስፋ ቢስ ጉዞውን ቀጥሏል፡፡ የዚህ ሁሉ ግዴለሽነት ውጤትም መስከረም 11 ቀን 2001 ዓለምን ሁሉ ጉድ ያሰኘውን ክስተት ፈጥሮአል፡፡ የጥቃቶቹ ዒላማ የዓለም ንግድ ማዕከልንና ፔንታጎንን ይሆናል ብሎ የገመተ ባይኖርም ብሄራዊ ሃብታችንን ጠባብ አእምሮ ለወለደው ጥቅም ማጋበሻ ፖለቲካ ስንል መስዋዕት ማረጋችንን እናውቅ ዘንድ እነዚያን ሁሉ ንጹሀን ደመከልብ መሆን እንዳልነበረባቸው ዛሬም ግንዛቤ የወሰደ አካል የለም ይህም ሁኔታ አበሳጭቶኛል፡፡ ሁላችንንም በመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት የኋይት ሃውስ ብቸኛ የመጀመሪያ ረድፍ መከላከያ የነበሩት የዩናይትድ አየር መንገድ በረራ ቁጥር 93 ተሳፋሪዎች እንጂ ግብር ከፍለን የምንደጉማቸው CIA ፣ FBI በደስተኛና ዜግነት ጉዳይ ቢሮ አሲይም መሰል ተቋማት አለመሆናቸው ሊያበሳጪን ይገባል እላለሁ፡፡

ከጥቃቱ በኋላ ሪፖርተር የሆነው አንድ ወዳጄ አንድ የCIA ከፍተኛ ባለስልጣን "ከመስከረም አስራ አንዱ ትውስታ ባሻገር ያለው አቧራ ሲጠራ አሜሪካውያን ጥቃቱ ለመረጃው ማህበረሰብ ድል እንጂ ሽንፈት እንዳልነበር ማየት ይጀምራሉ" እንዳለው አጫውቶኛል፡፡ ተቋሙ የአለማችንን እሳማ ቢላደኖች ይፋለሙ ዘንድ ከመጀመሪያ ረድፍ ያሰለፋቸው ባለስልጣናቱ የሚያስቡት እንዲያ ከሆነ ከቁጣም በላይ የሆነ ስሜት ይሰማኛል፡፡ ከፊታችን የሚጠብቀንን ሳስብም ውስጤ በፍርሃት ይርዳል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፩

## መጋቢት 15/1995 ላንግሌ ቨርጂኒያ

....... በትዕዛዙ መሠረት ከፍሬድ ቱርኮ ቢሮ ልክ 9:00 ላይ ደረስኩ። ፍሬድ ለእኔ እንግዳ ሰው አይደለም፤ በሚገባ እንተዋወቃለን። በ1980ዎቹ አጋማሽ አካባቢ በCIA የፀረ ሽብር ማዕከል አብረን ሰርተናል፡፡ ፍሬድ በአሁኑ ሰዓት በCIA የደህንነት ክፍል ውስጥ አንድ ኃላፊነት ተሰጥቶት እየሰራ ይገኛል፡፡ ከተለያየንም እጅግ ቆይተናል፤ ከዚህ አንፃር ታዲያ ፍሬድ ወደ ቢሮው እንድመጣ ያደረገው እንደጓደኛ ተገናኝተን እንድንጫወት ነው ብዬ አላስብም፡፡ የሆነ ነገር መኖሩን ልገምት ብችልም ለምን እንደፈለገኝ በትክክል ማወቅ ግን አልተቻለኝም፡፡ ከሰሜናዊ ኢራቅ ተነስቼ ዋሽንግተን ዲሲ እንደገባሁ ነበር በቀጥታ ወደ ፍሬድ ቢሮ ያቀናሁት፤ የተንጨባረረ ፀጉሬን ለመስተካከልና ወራት ያህል በሜዳ ሻንጣ ውስጥ ሲንከባለል የከረመ ገላዬን ለመለቃለቅ እንኳን ጊዜ አልነበረኝም፡፡

የፍሬድን ቢሮ እንኳኩቼ እንደገባሁ እንደ ጅብራ ቆሜ ተገተርኩ፤ እንደጠበኩትም ፍሬድ በተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ ተኮፍሶ በተቀመጠበት ሽቅብ ከተመለከተኝ በኃላ በእጁ ምልክት እያሣየኝ ፊት ለፊት ካለው ወንበር ላይ እንድቀመጥ ጋበዘኝ፡፡ ፍሬድ አልፎ አልፎ ፀጉሩን በጣቶቹ የመፎከት ልማድ እንዳለው አውቅ ነበር፤ ይህን የሚያደርገው ታዲያ አንድ አስጨናቂ ጉዳይ ሲገጥመው እንደነበረ አስታውሳለሁ ይሄው ዛሬ ደግሞ ያንን ልማዱን ሲፈፅም አየሁት፤ ይሄኔ ነው እንግዲህ አንድ ችግር እንዳለ ይበልጥ እየተጠራጠርኩ የመጣሁት፡፡ ይህንኑ እያሰብኩም ፊት ለፊቱ ካለው ወንበር ላይ ተሰየምኩ በመካከላችንም ለአፍታ ያህል ፀጥታ ከሠፈነ በኋላ ፀጥታው በፍሬድ ንግግር ደፈረሰ፡፡

«....... ሁለት የFBI ሰዎች አንተን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ላይኛው ፎቅ ይገኛሉ፡፡» አባባሉ አስደነገጠኝ፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ ከኢራቅ የመጣሁት የFBI ሰዎች እኔን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ፈልገው መሆኑን አላውቅም ነበር፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አንድ ትልቅ ችግር ካልተፈጠረ በስተቀር የFBI ሰዎች ግዳጅ ላይ የሚገኙን የ CIA ኦፊሰሮችን ጠርተው አያናግሩም፡፡

«ስለ ምንድን ነው የFBI'ዎች የሚያናግሩኝ?» አልኩት ፍሬድን በተረጋጋ መንፈስ፡፡

ትክ ብሎ በአርምሞ ሲመለከተኝ ከቆየ በኋላ «ትዕዛዙን ያስተላለፉት ቶኒ ሌክ ናቸው፤ ይህም የሆነው ሳዳም ሁሴንን ለመግደል ሙከራ አድርገሃል ተብለህ በመጠርጠርህ ነው!፡፡ አለኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በእንዳች ነገር እንደተመታ ሰው ሲያጥወለውለኝና ውስጤ ሲተራመስ ይታወቀኛል በቅፅበትም ብዙ ነገሮችን ለማውጠንጠን ሞከርኩ፤ ሁኔታዎችም ተምታቱብኝ፤ «ሳዳም ሁሴንን» የገደልኩም መሰለኝ፡፡ ከሁሉ በላይ ግን የሰዎቹ ጥርጣሬ ገረመኝ፤ የFBI እና የCIA የግንኙነት መስመረ የላላ መሆኑንም ለመታዘብ ቻልኩ ምክንያቱም ጥርጣሬያቸው ሁሉ ሰሜታዊና ምክንያተ ቢስ ነበርና፡፡

«ግራ ከመጋባቴ የተነሳም እየቀለዱ መሆን አለበት!» ብዬ ለመሄድ ስነሳ ፍሬድም ከመቀመጫው እየተነሳ «እየውልህ ....... አንተ ይህንን ከተማ በደንብ እታውቀውም ትንሽ ረጋ በልና አብረን ነው የምንወጣው» አለኝ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለንም ከፍሬድ ቢሮ በስተጀርባ በሚገኘው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተቀምጦ የነበረው «ሮብ ዴቪስ» እኔና ፍሬድን ተቀላቀለን፡፡ ጠበቃው ዴቪስ የሁለታችን ውይይት ሲያዳምጥ የቆየ ቢሆንም ከአዳራሹ መጥቶ የተቀላቀለንም እኔ ልሄድ በመዘጋጀቴ ነበር፡፡

ዴቪስ በፍሬድ ንግግር ጣልቃ በመግባት «ስማኝ .......ቦብ አንተ ለ20 ዓመታት ያክል በግዳጅ ነበር የቆየኸ፤ ዋሽንግተን እጅጉን ተለውጣለች፤ በአሁን ግዜ አታውቃትም፡፡ ፍሬድ ላንተ ብሎ ነው፤ FBI ወይንም ደግሞ CIA በኦፊሰሮቹ ላይ የሚያደርገው ምርመራ ደግሞ በአንተ ብቻ የሚሆን አዲስ ነገር አይደለም፤ እንዲያውም ነጥሮ የወጣ የCIA ህዋስ ያደርግሃለ እንጂ!» በማለት የፍሬድን ቃል አጠነከረው ፍሬድና ዴቪስ ከተናገሯቸው ሁለት ነገሮች ውስጥ አንዱ ትክክል ነው፤ በርግጥም ዋሽንግተን በ20 ዓመታት ውስጥ እጅጉን ተለውጣለች፤ እነርሱ ባይነግሩኝም እኔ ይህንን መረዳት አያዳግተኝም፡፡ የFBI ምርመራ ጠንካራ ህዋስ ያደርግሃል ያሉት የለበጣ ቃላቸው ግን ያልተመቸኝ፤ እጅግ የማይረባና ተልካሻ ነበር፡፡ ምክንያቱም የ CIA አባል የሆነ አንድ ሰው በድርጅቱ ተጠረጠረ ማለት ታማኝነቱ እዚያ ላይ አከተመ ማለት ነው፡፡ ጥርጣሬው ደግሞ መሰረተ ቢስ ቢሆንም እንኳን በCIA ውስጥ ተጠራጥረህ ምርመራ ተደረገብህ ማለት አምስት የትምህርት ዓይነቶችን ተፈትነህ ቢያንስ በአንዱ ወድቀሃል እንደማለት ነው፡፡

ዴቪስ የሚያወራውን ትቼ ወደ ፍሬድ ፊቴን አዞርኩ፡፡ የቀድሞው የምርመራ ኦፊሰርና ፍሬድ ቱርክ ዋሽንግተን ውስጥ ለሚካሄደው አዲስ የፖለቲካ ተሀድሶ እንግዳ ያልሆነና እጅን በበርካታ ጉዳዮች የከተተ ሰው ነው፡፡ ፍሬድ የፀረ-ሽብር ኦፊሰር ሆኖ ይሰራ በነበረበት ጊዜ ከፍትህ ዲፓርትመንት በተደጋጋሚ በሚሰጥር የስልክ ግንኙነት ያደርግ እንደነበር ይወራበታል፡፡ እንደሚናፈሰው ጭምጭምታ ከሆነ ፍሬድ አንድ የመረጃ ምንጭ የሆነ ጆሮ ነበረው፤ ይህም ሰው አለማቀፋዊ ዝናን የተጎናፀፈው የቀድሞው ሽብርተኛው «ካርሎስ ቀበሮ» ከደማስቆ ተነስቶ ወደ ኦማን ከተማ እንዲሁም ካርቱም መቼ እንደገባ የተናገረና በአንድ የ CIA አባል ጥረት ካርቱም ላይ እንዲያዝ ያደረገ ሰው ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ይህ የፍሬድ የመረጃ ምንጭ የነበረው ግለሰብ በመጨረሻ የተገደለ ሲሆን ገዳዩ ማን እንደሆነ ግን አልታወቀም፡፡ የሟቹን ገዳይ በተመለከተ ጣቶች ሁሉ ወደ ፍሬድ የቀሰሩ ቢሆንም ፍሬድ ቱርክ አሸባሪውን ካርሎስ ቀበሮን ለመያዝ ያደረገው ጥረት ሚዛን በመድፋቱ ጉዳዩ ትኩረትን ሳይወስድ ቀርቷል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ፍሬድ «የአሁኗ ዋሽንግተን ለእንተ እንግዳ ነች» ያለበት ምክንያት ምስጢር እየተገለጠልኝ የመጣው አሁን ነው፡፡ በርግጥም ፍሬድ በውስብስቡ የ CIA መረብና የዋሽንግተንን ትኩስ የፖለቲካ አየር እንዴት መተንፈስ እንደሚቻልም የሚያውቅ ብልጣብልጥ ሰው ነው፡፡ ስለሆነ መውጫውንና መግቢያውን የሚያውቀውን ቆቁን መከተል ደግሞ በኢራቅ በርሃዎች ላሳለፈው «ቦብ» ግድ ነበር፡፡

«መጀመሪያ እኔ ልቅደም!» አለኝ ፍሬድ ከክፍሉ ለመውጣት እየተጣደፈ፡፡ «በቃለ መጠይቁ ውስጥ እኔም ዴቪስም እንገኛለን፤ ግን ልብ ማለት ያለብህ ዴቪስ የሚያወራው አንተን ወክሎ ሳይሆን CIA'ን በመወከል ነው፡፡ FBI'ዮች አሁን ሊያናግሩህ ይደውላሉ፤ ጠበቃ እንዲዘጋጅልህም ሊጠይቁህ ይችላሉ፤ ጠበቃ እንደምትፈልግ ከነገርካቸው ነገሮች ሁሉ በመልካም ሁኔታ እንደሚይቀጥል ልትገነዘብ ይገባሃል፡፡ ለማንኛውም ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ እንገናኝ!» አለና ወደ በሩ አመራ፡፡ ሁለቱ የFBI ሰዎች ወዳሉበት ክፍል ገባሁ፡፡ እኔ ስገባ ሁለቱም በአንድነት በመነሳት የእጅ ሰላምታ ካቀረቡልኝ በኋላ ራሳቸውን ለማስተዋወቅ ያህል መታወቂያቸውን አሳይተውኝ ተቀመጥን፡፡ ከሁለቱ ሰዎች አንዱን ማለትም ማይክን ከዚህ በፊት አውቀዋለሁ፤ እንዲያውም በ1986 ዓ.ም በጀርመን ሀገር ቂስባደን ውስጥ አብረን የነበርን ሲሆን ሊባኖስ ውስጥ ያገለግሉ የነበሩና በሒዝቦላህ ታግተው የተፈቱትን 'ላውረንስ ጀንኮ' የሚባሉ የካቶሊክ ቄስን እኔና ማይክ ምርመራ አድርገንባቸው እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

ከማይክ ፊት የሚታየው ገፅታም እሱም እኔን እንደሚያውቀኝ የሚያሳብቅ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ስራ ነውና ማይክ እንደታዘዘው እኔ ላይ ምርመራ ማድረግ ነበረበት፡፡ ሁላችንም ተደላድለን እንደተቀመጥን ማይክ ጥያቄውን ያሾጎደጉድ ጀመረ፡፡ «ሚስተር ቤር ጠበቃ የማቆም መብት እንዳለህ ልገልጽልህ እወዳለሁ፡፡ ፍላጎቱ አለህን?» አለኝ፡፡ ለጊዜው እንደማያስፈልገኝ ገለፅኩለት፡፡ ደግሞም ጠበቃ ለማስቆም የሚያስችለኝ የገንዘብ አቅሙ አልነበረኝም፡፡ ከመርማሪዎችም የሚመጣውን ጥያቄም ለመጋፈጥ ወስኛለሁ፡፡

«ሚስተር ቤር ከአንድ ከባድ የግድያ ሙከራ ጋር የተያያዘ ምርመራ ነው እያደረግንልህ ያለነው፤ ሳዳም ሁሴንን የመግደል ሙከራ.......» ሲል ማይክ ተናገረ፡፡ ለጥያቄው መልስ ሳላልሰጠሁት በመካከላችን ለአፍታ ያህል ዝምታ ሰፈነ፡፡ «ለመሆኑ CIA ስለሚያከብረው ግድያን የሚከለክል ህገ-ደንብ ትዕዛዝ 12333 ምን ያህል ታውቃለህ?» ሲልም አከለበት፡፡ በ1981 ዓ.ም ፕሬዘዳንት ሬገን ስለደነገጉት ህገደንብ ትዕዛዝ 12333 የትኛውም የ CIA ቅጥረኛ ስለሚያውቀው ማይክ ጥያቄውን መጠየቁ አስፈላጊ አልነበረም፡፡ የሆነው ሆኖ ህጉን እንደማውቀው መንገር ነበረብኝና «አዎ በደንብ አውቀዋለሁ!» አልኩት «ሳዳም ሁሴንን ለመግደል ሙከራ አድርገሃል?» በፍፁም!»

«በፍፁም!»

«ሳዳምን እንዲገድል የቀጠርከው ሰውስ ነበር?»

«በጭራሽ!»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እብረህ ከምትሰራቸው የስራ ባልደረቦችህ ሳዳምን ለመግደል የሞከረ እንዳለ ታውቃለህ ወይ?»

«አላውቅም!»

«ሮበርት ፓፐ የሚለውን ስም ተጠቅመህ ታውቃለህ?» ሲልም አከለበት፡፡ መልስ ግን አልሰጠሁትም፡፡ በዚህ ጊዜ ማይክ አይኑን ወደ ጠረጴዛው መሳቢያ እየተመለከተ አንድ ፋይል አወጣና ገፁን ካገላበጠ በኋላ በአመልካች ጣቱ እያመለከተ ሦስት ገፅ የያዘውን ሪፖርት እንዳነብ ነገረኝ፡፡ አነበብኩት፤ ሪፖርቱ በ1995 ዓ.ም አህመድ ቻላቢ በተባለ ኢራቃዊና በሁለት ኢራናውያን መካከል ሰሜናዊ ኢራቅ ውስጥ ተካሂዶ ስለነበረ ስብሰባ የሚያወራ ሲሆን በሪፖርቱም ቻላቢ ሁለቱን ኢራናውያን አሜሪካ ሳዳም እንዲገደል መፈለጓንና ትዕዛዝ ማስተላለፏን እንዳሳመናቸው ይገልፃል፡፡ ቻላቢ ማብራሪያውን ሲቀጥልም የሳዳም ግድያ ለማፋጠን የሃገሪቱ ብሔራዊ ደህንነት ማዕከል ሮበርት ፓፐ በተባለ ግለሰብ የሚመራ ቡድን ያቋቋመ ሲሆን እርሱንም ከኢራን መንግስት ጋር ግንኙነት እንዲፈጥር መፈለጉን ለሁለቱ ኢራናውያን ይገልጻቸዋል፡፡ ቻላቢ ይህንን ሁኔታ ለኢራናውያን እያስረዳ ባለበት ወቅትም በስልክ ጥሪ ስለነበረው ሪፖርቱን ሁለቱ ኢራናውያን እንዲያነቡት በሚያስችል ሁኔታ ጠረጴዛው ላይ ትቶት እንደወጣ፤ ቀሪው ፅሁፍም ቻላቢ ሚስተር ሮበርት ፓፐን የቡድኑ መሪ እንዲሆን ከአሜካው ናሽናል ሴኪዩሪቲ መታዘዙን የሚገልፅ ሐሳብ ያዘለ ነበር፡፡

ስሜቴን መቆጣጠር ስላልቻልኩ ሪፖርቱን ማንበቤን አቆምኩ፡፡ እጅግ በጣም የሚገርምና የሚያስደነግጥ ሪፖርት ነበርና፡፡ በተለይም «ለእኔ»፡፡

አህመድ ቻላቢንን በሚገባ እውቀዋለሁ፡፡ ቻላቢ ከኢራናውያኑ ጋር ውይይት አድርጎ ነበር፡፡ በተባለበት ወቅት እኔም እዛው ሰሜናዊ ኢራቅ ውስጥ ነበርኩኝ የሚያሳዝነው ነገር ቻላቢ ይህንን ሪፖርት የፈጠረው ከምንም ነገር ነበር፤ በጉዳዩ ላይ ከኋይት ሃውስም ሆነ ከአሜሪካ የደህንነት መስሪያ ቤት የተላለፈ ሳዳምን የመግደል ውሳኔ ያልነበረ ሲሆን ቻላቢ ኢራናውያኑን ሳዳም እንዲገደል መወሰኑን ለማሳመን ጥረት ያደርግ የነበረው በራሱ ተነሳሽነት ከምንም ነገር ተነስቶ ነበር፡፡ ቻላቢ ይህንን ቢያደርግ ደግሞ አይገርምም፤ ፀረ-ሳዳም ከሆኑት የኢራቅ አንጃዎች የአንዱ መሪ በመሆኑ ይህንን መሰይ ሴራ በመፍጠር ዓላማውን ማሳካት እንደእርሱ ካለ የአማፂ ቡድን መሪ የሚጠበቅ ነበርና፡፡ ቻላቢ የፈጠረውና ሳዳምን ለመግደል አሜሪካ ወስናለች የተባለው የሪፖርቱ አካል ፍፁም ከዕውነት የራቀ ከመሆኑም ሌላ ሮበርት ፓፐ የተሰኘው ሰውም የፈጠራው አንዱ አካል ነበር፡፡

ይሁንና ጥልፍልፉ አሁን በሚገባ እየተገለጠልኝ መጣ፤ ሰንካላ ዕድልም እዚህ መረብ ውስጥ እንዳስገባኝ ተረዳሁ፡፡ እጅግ የሚያሳዝነኝ ነገር ቢኖር የአሜሪካ የደህንነት መሳሪያ ቤቶች የደህንነት ምንጮች እንደ ሰሃራ በረሐ መድረቃቸው ብቻ ሳይሆን እንደ አህመድ ቻላቢ ዓይነት ሽፍታ የፈጠረውን ስውር ሴራ የአሜሪካ የደህንነት ሰዎችን ያለሐጢያታቸው ገመድ በአንገታቸው እንዲገባ ማድረጉ ነው፡፡ በርግጥ እንደቶኒ ሌክ ዓይነት የአሜሪካ የደህንነት መሳሪያ ቤት ታላላቅ ባለስልጣናት በኢራቅ ውስጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚፈፀመው እያንዳንዱ ሴራ፤ ውሸትና ሽፍጥ ካለማወቃቸው፤ የቻላቢ ሴራ ታዓማኒነት እንዲኖረው ምክንያት መሆኑ እያስደንቅ ይሆናል፤ ይሁንና በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ አንድም የ CIA አባል ክትትል የሌለበት መሆኑ ግን እጅጉን የሚያሳዝንና የሚያሳፍርም ነበር፡፡

ሪፖርቱን እንብቤ እንደጨረስኩ ሁለቱን የFBI ሰዎችን ቀና ብዬ ተመለከትኳቸው፡፡ የሆነው ሆኖ ከእነርሱ መፍትሂ እንደማላገኝ አውቀዋለሁ፤ እንኳን ታች ያሉት የFBI ሰዎች ይቅሩና ቻላቢ የፈጠረውን ይህንን ዓይነቱን ጥልፍልፍ ሴራ ለድርጅቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት እንግዳ መሆናቸው ግልፅ ነበር፡፡

«....... እዚህ ሪፖርት ውስጥ አንድም እውነት አለመኖሩን .......»ስን ማይክ አስረዳኋቸው፡፡ ማይክና ጓደኛው እርስ በእርሳቸው በለሆሳሳ ከተነጋገሩ በኋላ ለጊዜው ጥያቄዎቻቸው በቂ መሆናቸውን ተስማሙበት፡፡

ማይክ እስከበሩ ሸኘኝ፤ ከጥቂት ቆይታዎች በኋላ በአዳራሹ አገኘኝና ለመጀመሪያ ጊዜ ከጓደኛው ተነጥሎ በመምጣት አዋራኝ፡፡ CIA የሚከብረውን ህጉ-ደንብ /ትዕዛዝ 1233/ በድጋሚ ነገረኝ፡፡ በዚህ ህጉ-ደንብ በርካቶች ደስተኛ እንዳልሆኑና የህጉ-ደንቡ ነገርም በእንደነዚህ ዓይነት ድንጋጌዎች ሳቢያ ችግር ላይ መሆኑን ደሰኮረኝ፡፡ ከሁኔታው እንደተረዳሁትም ይህንን ትዕዛዝ መተላለፍ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚያስከትል ነበር ሹክ ያለኝ፡፡ ከማይክ ጋር ከተለያየን በኋላ በትክክል ተረድቼው ከሆነ በእኔ ዓይነቱ ወንጀል የተከሰሰ ሰው ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ የፍርድ ውሳኔው የዕድሜ ልክ እስራት አሊያም የሞት ቅጣት መሆኑን ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፪

## 1962፡ ሎስአንጀለስ ካሊፎርኒያ

....... የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለሁ አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ እናቴ ካሊፎርኒያን ለቅቀን ወደ አውሮፓ ልንሄድ መሆኑን ነገረችኝ፡፡ በወቅቱ እናቴ ከአባቴ ጋር ተለያይታ ስለነበር ሁለታችንም ለብቻችን ነበር የምንኖረው፡፡ ለዘጠኝ ዓመታት ያህል የኖርኩበትን አካባቢ ልለየው በመሆኑ ቅር እንዳለኝ የተረዳችው እናቴ የምንቆየው ለሁለት ወራት ብቻ መሆኑን በመግለፅ ልታፅናናኝ ሞከረች፡፡ የሆነው ሆኖ ሁለት ወራት ያለችኝ ውሸቷን መሆኑን ቆይቼ መረዳቴ አልቀረም ነበር፡፡

አያቴ በስዊዝ ባንክ በኩል የባንክ ሒሳብ ከከፈተልን በኋላ በአውሮፕላን ወደ ዙሪክ አመራን፡፡ እዚያው ዙሪክ ከተማ ውስጥም አንዲት ፊያት መኪና ገዝተን የክረምቱን ወራት በአካባቢው በመዝናናት አሳለፍነው፡፡ በእነዚያ ጊዜያትም ውስጥ በራሴ ጥረት የፈረንሳይኛና የጀርመንኛ ቃላት ማጥናት ጀምሬ ነበር፡፡ ስለ ፖለቲካም ቢሆን ለመውተርተር ያህል ትንሽ ነገር ተምሬያለሁ፡፡ እናቴም በሳንዲያጎ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ትምህርት ታስተምር ስለነበር ምናልባትም የእርሷ የተፅዕኖ በትር ሊሆን ይችላል የፖለቲካ ዕውቀትና ፍላጎት እንዲኖረኝ ምክንያት የሆነው፡፡ በ1962 ዓ.ም በርሊን ውስጥ ተይዘን' በነበርንበት ወቅት ዘመናዊውን የፖለቲካ ቅኝት መማር ጀምሬ ነበር፤ ነገር ግን የእናቴ ፍላጎት የጥንቱን ፖለቲካ እንዳውቅ ነበር፡፡ ከእናቴ ጋር በመሆን ግሪክንና ጣሊያንን ስንጎበኝ ወራትን አስቆጠርን በርካታ ታሪካዊ ቦታዎችንና ገዳማትንም ለመጎብኘት ቻልን፡፡ ሮም ውስጥ 'ካታኮምብን' ስንጎበኝ ቅዝቃዜው አጥንት ድረስ የሚዘልቀውን ጥቂት የበረዷማ ሌትና መዓልቶችን አሳልፈን ነበር፡፡ ታዲያ በነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ ሕይወት በራሷ በርካታ ነገሮችን አስተምራኛለች፡፡ ከዚህም ሌላ እናቴ የጥንቱን የግሪክና የላቲን ቋንቋ እንዳውቅ በማሰብ ኦስትሪያ ውስጥ በሚገኝ አንድ ገዳም ውስጥ ልታስገባኝ አስባ ነበር፡፡ በጥቅሉ በአውሮፓው ጉዞአችን እጅግ በርካታና አዳዲስ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉድኝነቶችን በቀላሉ መልመድ ቻልኩኝ፣ ለአብዛኛው አሜሪካውያን እንግዳ የሆኑትን እንደ ሊባኖስ የቢታ ሸለቆንና የታጂኪስታንን አስደናቂ ተራራዎችም መጎብኘት በመቻሌ እንደ ዕድለኛ የምቆጥረው ነገር ነበር፡፡

ሌላው ቀርቶ በዚህ ጉዟችን ስለ ገንዘብም አጠቃቀም በሚገባ ተምሬበታለሁ፡፡ አያቴ ያስቀመጠልንም የባንክ ሒሳብ ከጊዜ-ወደ ጊዜ እየተሟጠጠ መሄዱንም መረዳት አላዳገተኝም ነበር፡፡ ለዚህም ምስክር ሊሆነኝ የሚችለው ደግሞ እኔና እናቴ የምንከራያቸው ሆቴሎችና የምንመገባቸው ሬስቶራንቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን መምረጣችን ነበር፡፡

....... አንድ ቀን ከጀርመን ተነስተን ወደ ፈረንሳይ ስናቋርጥ በፈረንሳይ ድንበር ኬላ ላይ የጉምሩክ ሰዎች ለፍተሻ አስቆሙን፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ የመኪናችን



t.me/OLDBOOKSPDF

የኢንሹራንስ የጊዜ ገደብ ያለፉበት በመሆኑ ነበር፡፡ ፈታሾቹ ደግሞ ፈረንሳውያን በመሆናቸው ወደ ፈረንሳይ መግባት እንደማንችል ነገሩን፡፡ ጊዜያዊውን ኢንሹራንስ ገዝቶ ለማለፍ የሚያስችል 100 ፍራንክም ስላልነበረን ወደ መጣንበት ለመመለስ ተገደድን፡፡ የሚገርመው ነገር ደግሞ መጀመሪያ አሳልፈውን የነበሩት የጀርመን የድንበር ኬላ ፈታሾች በተመሳሳይ ምክንያት ወደ ጀርመን ተመልሰን ልንገባ እንደማንችል አስረዱን፡፡ ይሁንና ሌሊቱን የምናሳልፍበት ሰፍራ ጀርመናውያኑ ዘቦች ስለሰጡን ሌሊቱን በዚያ አሳልፈን ወደ ፈረንሳይ የሚያስገባውን የድንበር ኬላ ጠባቂ ዘቦች በሌላ ተረኛ ጠባቂዎች እስኪቀየሩ ድረስ ትንሽ ታገስን፡፡ ጠባቂዎቹ በሌሎች ሲተኩም ወደ ተቀያሪዎቹ አመራን፤ ተከታዩን ሌሊትም ከእነኝህ ደጋግ ጥበቃዎች ጋር ካርታ ስንጫወት አደርን፤ ቅርበታችን የመኪናችን ኢንሹራንስ የተመለከተውን ጉዳይ አስረስቶልኝ በሰላም ድንበሩን ተሻገርን፡፡ ከዚያ በኋላ ቀጥታ ያመራነው ስዊዝ ሪዞርት ወደተባለ መዝናኛ ስፍራው የነበረ ሲሆን ከባንክ ሂሳቡ ከተረፈው ሙጣጭ ገንዘብ እናቴ አንድ ቤት በዚያው በመዝናኛ ስፍራው ተከራይታ መኖር ጀመርን፡፡ መደበኛ ትምህርቱን ከረሳሁት እጅግ ብዙ ጊዜ ሆኖኝ ስለነበር አንድ የግል አስተማሪ ተቀጥሮልኝ በተለይም የጀርመንኛ ቋንቋ በደንብ እንዳጠና እናቴ ስለፈለገች እሱን መከታተል ጀመርኩኝ፡፡ የሆነው ሆኖ ትምህርቱ ብዙም ስላልተመቸኝ ሳልገፋበት ቀረሁ፡፡

በሚቀጥለው ክረምት በስዊዘርላንድ ብዙ መቆየታችን የሰለቻት እናቴ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጉምጉምታና የኩባ የሚሳኤል ቀውስ ውዥንብር ታክሎበት ወደ ሞስኮ ማቅናት እንዳለብን ወሰነች፡፡ የሆነው ሆኖ ጊዜ ቀውጢ የነበረበት በመሆኑ ከየትኛውም አካባቢ ወደ ሞስኮ ማቅናት እጅግ ፈታኝ ነበር፡፡ እናም ወደ ሞስኮ ለማቅናት የሚያስችለንን ቪዛ ለማግኘት ከአንድ የሞስኮ የደህንነት አባል ጋል አድርገነው የነበረው እሰጣ ገባ መቼም አይረሳኝም፤ ሰውየው ሰላዮች ስለመሰልነው እጅግ አስጨናቂና መስቀለኛ ጥያቄዎችን ነበር ይጠይቀን የነበረው፡፡ በኋላ ላይ ግን ሰላዮች አለመሆናችንን ሲረዳ ቪዛውን ሰጠን፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አያታችን ትእግስት ተሟጦ ስለነበር ካለንበት ደውሎ እንድንመለስ ይወተውተን ገባ፡፡ የአውሮፕላን ቲኬቱን ቆርጦልን ወደ ቤታችን እንድንመለስ አደረገ፡፡ እናም በኡታህ የሳልት ሊክ ከተማ ውስጥ ከትመን መኖራችንን ቀጠልን፡፡ በሚቀጥለው ዓመት ማለትም በ1964 ዓ.ም ወደ አስፔን ኮሎራዶ አመራን፡፡ አስፔን እጅጉን የምትወደድ ከተማ ሆና ነበር ያገኘኋት፡፡ በተለይ ለምወደው የበረዶ ሸርተቴ ጨዋታ ቀዳሚዋ ከተማ መሆኗ በዚህ ብዙ ደስተኛ እንደምሆን ገምቻለሁ፡፡ እናም በጥቂት ቀናት ውስጥ የበረዶ ሸርተቴ ቡድን አባላት የሆኑ የትምህርት ቤት ጓደኞችን ተዋወቅኩኝ፡፡ ከእነርሱ ጋርም ቀኑን ሙሉ ስራችን የበረዶ ሸርተቴ ስልጠና ሆነ፤ መደባዊ ትምርታችንንም ሙሉ በሙሉ ዘነጋነው ማለት ይቀል ነበር፡፡ በከተማዋ ተራራማ ቦታዎችና የበረዶ ክምር በበዛባቸው ስፍራዎች እየዞርንም ጠንካራ ልምምዳችንን ማድረጉን እንደ መደበኛ ስራችን አድርገን ተያያዝነው፡፡ በእውነቱ የበረዶ ሸርተቴ ውድድር እጅግ የሚያስደስት ጨዋታ ነው፤ በጊዜው የህይወቴ አንድ አካል አድርጌው ነበር ብልም ከዕውነት አልራቅኩም፡፡ እጅግ አስደሳች የነበረው አጋጣሚ ደግሞ አሰልጣኞችን በበረዶ ሸርተቴ ውድድር እጅግ ጠንካራ ከሚባሉት ሰዎች መካከል ቀዳሚዎ መሆኗ ነበር፡፡ አሰልጣኞችን ክሪስታል ኸርቢርቶ የተባለች ኦስትሪያዊ ስትሆን በሴቶች



t.me/OLDBOOKSPDF

የበረዶ ሸርተቴ ውድድር ባለክብር ወሰንተኛ ነች፡፡ ክሪስታል እያንዳንዷን እንቅስቃሴያችንን እየተከታተለች ነበር ለምምዳችንን የምታሰራን፡፡ የበረዶ ሸርተቴ ጨዋታ ጠመዝማዛና መሰናክሎች የበዙበት ጨዋታ በመሆኑ እያንዳንዱን መሰናክልም ከህይወት አጋጣሚዎች ጋር እያገናኘች ነበር በዕናትና በብልጠት እንዲሁም በዕልህ እንድናልፋቸው የምታደርገን፡፡ ለምሳሌ፡- በዘጠና ዲግሪ የምንታጠፍበት ስፍራ ያለ ሲሆን ይህን ስፍራ ክሪስታልና የበረዶ ሸርተቴ ጨዋታ ምጡቅ ባለሙያዎች 'አሪፍ ቅያስ' በማለት ይጠሩታል እዚህ ስፍራ ሲደረስ ሚዛንን ጠብቆ ለመታጠፍ እስጨናቂ ከመሆኑ አንፃርና ይህንን ማለፍ በህይወት ከሚገጥም ጣፋጭ ድል ጋር በማነፃፀርም ይመስላል ለሁለቱ 'አሪፍ' የሚል ስያሜ ያወጡለት፡፡ እስፔን ውስጥ የበረዶ ሸርተቴ እጅግ የሚወደድ የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ ልክ እንደ እግርኳስ ጨዋታ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ይህን ውድድርና መመልከት እጅጉን የሚያስደስታቸውና የሚያዘወትሩትም መዝናኛ ነበር፡፡

☆☆☆

ወቅቱ በተለይም በአውሮፓ የፖለቲካ ትኩሳት ወላፈን የሚጋረፍበት ነበር፡፡ በየሃገራቱ የምረጡኝ ዘመቻዎች የተጧጧፈበትም የነበረ ሲሆን እናቴም ለምርጫ ከሚወዳደሩት ፖለቲከኞች ውስጥ አንዷ ነበረች፡፡ እርትክን ካውንቲ የከሚሽነሮች መቀመጫ አንዱን ወንበር ለመያዝ ትወዳደር ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በጊዜው እጅጉን ውጥረት ላይ ነበረች፡፡ ለነገሩ እኔም በእስፔን ተራሮች ስር ከጓደኞቼ ጋር የበረዶ ሸርተቴ ጨዋታን በመለማመድ ተወጥሬ ነበር፡፡ የእናቴ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በፖለቲካው ውጥረት ተሰቅዞ ስለነበር ለእኔ የምትሰጠኝ ትኩረት ቸለል አለ፡፡ እኔም የበረዶ ሸርተቴ ጨዋታዬን እንጀራዬ ሊሆን እንደሚችልም እራሴን ማሳመን ተያያዝኩት፡፡ በዚህ ዓይነቱም ውድድር የዓለም ሻምፒዮና ለመሆን የተሰፋ ዳቦ ስገምጥም ይታየኛል፡፡ ታዲያ የሰነቅኩት ተስፋ ሊታየኝ የቻለበትም ምክንያት ዝም ብሎ አይደለም የምማርበት የእስፔን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤት በመንፈቁ አጋማሽ ትምርት ቤት የሂድኩባቸውን ስድስት ቀናትና በሥነ-ጥበብ ትምህርት ካገኘሁት የ'D' ውጤት በስተቀር በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ባንዲራ መስቀሌን ወይም 'F' ማግኘቴን ለእናቴ ካረዷት በኋላ ነበር፡፡ እናቴ ይህንን ጉዷን እንደሰማች ካለማመን የተነሳ ማበድ ብቻ ነበር የቀራት፡፡ እኔን አፈላልጋ ለማግኘትም በጣት የሚቆጠሩ አስር ደቂቃዎችን ብቻ ነበር ያባከነችው፡፡ በእናቴ በጥብቅ እየተፈለኩ በነበረበት ወቅትም ፒኖችስ ሬስቶራንት ውስጥ «ሉ» ከምትባለዋ ቺኪ ጋር ቁጭ ብዬ ገተታ ይገፍ ነበር፡፡ እናቴም በማልጠብቃት ቦታ ላይ ስመለከታትም ካለማመኔና ከድንጋጤዬ የተነሳ ባለሁበት ደርቄ ቀረሁ፡፡

«አንተ የውሻ ልጅ በሁሉም የትምርት ዓይነቶች 'F'?' በማለት ስታንባርቅብኝማ እንደኔ ያሉ ጅራሬዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው በዙሪያዬ ስለነበሩ ከምንተፍረቴና ከድንጋጤዬ የተነሳ የልብ ትርታዬ ቀጥ ያለች ነበር የመሰለኝ፡፡ እናቴም ካለማመኗ የተነሳ «በፍፁም ሲሆን ሊቀበለውም አልችልም፡፡» በቃ! «ያንተ ዕጣ ፋንታ ውትድርና መሆን አለበት!» በማለትም ዕሳት በላሰውና በጎረሰው ፊቷ ገረፍ አርጋኝ በመጣችበት ዕብስ አለች፡፡ ሁኔታው እጅጉን ነበር ያስደነገጠኝ ምክንያቱም ከጥቂት ሰዓታት በፊት አስበውና አልመው የነበረው ነገር ማለትም የበረዶ ሸርተቴ ጀብደኛ መሆንን ነበር፤ አሁን ደግሞ እናቴ ወታደርነት እንደሚገባኝ እየነገረችኝ ነው፡፡ እናቴ ደግሞ በሕይወቴ ሳውቃት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀልድ የሚባል ነገር አታውቅም፤ የውትድርና ትምህርት እንዳልገባ ምንም የማታደርግበት ምክንያት የለም፡፡

ከዚያ ግርግር በኋላ ከአስፔን ትምህርት ቤት ወጣሁ፤ ወደ ፈረንሳይም ተመልሰን አቶናን ሰንካላ ዕድል ሆኖ ፓሪስ የደረስነውም የ1968ቱ የተማሪዎች ንቅናቄ አመፅ ከመቼውም ጊዜ በላይ የባሰ በነበረበት ወቅት ነበር፡፡ ሁሉም የመንግስት መስርያ ቤት፤ የንግድ ተቋማት በሙሉ ተዘጋግተው ነበር፡፡ ተማሪዎችም ከየአቅጣጫው እየተመሙ በየአደባባዩ እየዞሩ መፈክራቸውን በዕልህ መንፈስ ያስተጋቡ ነበር፡፡ እኔም አካባቢዬን ለመምሰል ስል መህላቸው በመቀላቀል በታዳሚት ለበርካታ ጊዜ የተገኘሁ ስሆን ሁኔታው አላምር ላላት ለእናቴ ግን ራስ ምታት ሆኖባት ነበር፡፡

በፓሪስ የተማሪዎች ንቅናቄ እንቅስቃሴ እየባሰበት በመምጣቱ የተነሣ ፓሪስን ለቅቀን ወደ ሞስኮ አመራን፡፡ እናም ታዲያ መጀመሪያ ያረፍነው ፕራግ ውስጥ ነበር፡፡ የሚገርመው ነገር ቢኖር እንደ ፓሪሱ አይሁን እንጂ በፕራግም የተማሪዎች ንቅናቄ ሰልፍና አመፅ ተጧጡፎ ነበር የጠበቀን፤ እኛም ታዲያ ሽሽታችንን ወደ ፖላንድ አረግን፡፡ የፖላንድን ድንበር ስናቋርጥ ግን ነገር ሁሉ አልጋ በአልጋ አልሆነልንም ጉዟችንን የሚያደናቅፍ ሁኔታ ገጠመን፡፡ ወደ ሶቪዬት የሚወስደው መንገድና ወደ ቼክ መዲና የሚያቀናው መንገድ በጊዜው ተቀስቅሶና ተቀጣጥሎ በነበረው አመፅ ሳቢያ የቼክ መንግስት የድንበር ኬላዎችን በሙሉ ዘግቶትና በወታደሮች አጥሮ ነበር፡፡

☆☆☆

ቀልድ የማታውቀው እናቴ አስቀድማ እንደዛተችብኝ ኢንዲያን ውስጥ በሚገኝ የኪልቨር የውትድርና ትምህርት ቤት አስገባችኝ፡፡ በጥቅሉ በውትድርና ቤት ስለ መማሪያ ብቻ ማወቅ ይመስለኝ ነበር፤ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ስራዎችን እሰራ የነበረ ሲሆን በትርም ሰዓቱ ደግሞ ትምርቴን አጠና ነበር፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን የትምህርት ቤት ውጤቴም እጅጉን እየተሻሻለ መጣ፡፡ በውጤቴም የተደሰተው የኮሌጁ ዲን አንድ ቀን አስጠርቶኝ የትኛው ኮሌጁ መግባት እንደምፈልግ ጠየቀኝ፡፡ ኮሎራዶ ዩኒቨርሲቲ ብገባ ደስ እንደሚለኝ ነገርኩት፡፡ እሱ የተማረው ኢቪ ሊግ በተሰኘ ኮሌጅ የነበረ ሲሆን ለእኔ ግን ሌሎች ኮሌጆችን እንዳስብ ነበር የመከረኝ፤ ምናልባትም በኮሌጁ ቆይታ ጥሩ ጊዜን ባያሳልፍ ይሆናል ብዬ ከማሰብ ውጭ ሌላ ሀሳብ አልነበረኝም፡፡

«አውሮፓ ውስጥ የተወሰኑ ጊዜያትን እንዳሳለፍክ አውቃለሁ፡፡ ታዲያ እንዴት ነው ዲፕሎማት ወይንም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዓይነት የመሆን ዝንባሌ አላዳበርክም?» አለኝ፡፡ እስከአሁን ድረስ እንደዛ እንዳላሰብኩ ከአሁን ወዲያ ግን እንደማስብበት ነገርኩት፡፡ ሰውየው ያመጣልኝ ሐሳብ እንግዳና አዲስ በመሆኑ አልጠላሁትም፡፡ ብዙም ሳልቆይ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው በጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ፎረን ሰርቪስ የትምህርት ክፍል ደብዳቤ መፃፃፍ ጀመርኩኝ፡፡ ዩኒቨርሲቲውም ለመግቢያ ፈተና ስለተቀበለኝ ወደዚያው አቀናሁ፡፡ በጆርጅ ታውን ውስጥ በሚገኝ አንድ ሬስቶራንት ውስጥ የማታ ስራ በማግኘቴ እሱን እየሰራሁ ቀን ቀን ሌሎች ከትምህርቴ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በመስራት ማሳለፍና በዕረፍት ጊዜዬ ደግሞ ወደ አስፔን እየሄድኩ የለመድኩትን የበረዶ ሸርተቴ በመጫወት እዝናና ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ተዕለታት አንድ ቀን በሞተር ሳይክሌ ስበር ከ20 ዓመታት በፊት የማውቀውን ጓደኛዬን ጆርጅ ቴኔትን አገኘሁት፡፡ የሚገርመው ነገር ቴኔት እኛው ጆርጅ ታውን እንደ እኔ ዕድሉን አግኝቶ ነበር የመጣው፡፡ ቴኔትን ከ20 ዓመታት በፊት ሳውቀው በብሔራዊ የደህንነት መሳሪያ ቤት አንድ ኃላፊነትን ይዞ ነበር፤ በ1997 ዓ.ም ደግሞ የ CIA የአንድ ቅርንጫፍ የቡድን መሪ ሆኖ እንደተመረጠም ጭምጭምታ ሰምቼ ነበር፡፡ ቴኔትን ሳየው በሚገባ አውቄዋለሁ፤ እሱ ያስታውሰኛል ብዬ ግን አላሰብኩም ነበር፡፡ ግምቴ ግን ትክክል አልነበረም፤ ሞቅ ባለ ሰላምታና በናፍቆት ነበር ሰላም ያለኝ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ እናቴ ከአስፔን ወደ ካሊፎርኒያ በመጓዝ አንድ የቆዩ መጽሐፍቶች የሚሸጡትን መደብር ከፍታ መስራቷን ተያይዛዋለች፡፡ የነማርከስና መሰል ሰዎችን መጽሐፍቶች ስብሰባ በመደብሯ ትሸጥ ነበር፤ በህይወት ከሚገኙት ደራሲያን ደግሞ «የሮን ኮቪች» መፅሐፍቶች ይበዙ ነበር፡፡ ሮን ኮቪች ከእናቴ ጋር ቅርበት የነበረውና ለእኔም ጥሩ ስሜት ያለው ጥሩ ሰው ነበር፡፡ ሮን ኮቪች ከእናቴ ጋር ቅርበት የነበረውና ለእኔም ጥሩ ስሜት ያለው ጥሩ ሰው ነበር፡፡ በቬትናም ጦርነት ወቅት ተጎድቶ አካለ ስንኩል የሆነ ሲሆን ቀሪ ህይወቱን በመፃፍ ይኖራል፡፡ ፀረ-ጦርነት አቋም ያለው ኮቪች ሁሌም እቤታችን ሲመጣ ስለ CIA እና FBI በርካታ ነገሮችን እያወጋን ቤታችንን በወጉ ያደምቃት ነበር፡፡

ከጆርጅ ታውን ቆይታዬ በኋላ ያመራሁት ወደፈረንሳይ ነበር፤ እቅዴም የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታዬን ለማዳበር ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ወደ አስፔን ሳደርገው የነበረውን ጉዞዬ ኪሌ በመራቆቱ ምክንያት በሐሳብ ብቻ ቀረ፡፡ እናም ስራ ፍለጋ ወደ ሳንፍራንሲስኮ ማቅናቴ ግድ ሆነብኝ፡፡. ሳንፍራንሲስኮ ከልሸር ውስጥ እያለሁ የማውቀው አንድ ወዳጄን አገኘሁት እሱም ማይክ ኮኬቫ ነበር፡፡ በጊዜው ማይክ የሚወደውን ስራ አግኝቶ ስለነበር ሁለታችንም ለእኔ ነበር ስራ ፍለጋ ስንራወጥ የነበረው፡፡ በኋላ ላይ ግን ማይክ አንድ ሐሳብ አመጣልኝ፡፡ «ለምን በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ለአንተ የሚሆን ቦታ ካለ አናጠያይቅም?» አለኝ፡፡ ቀናነቱ ቢያስደስተኝም ሐሳቡ ግን አልተዋጠልኝም ምክንያቱም ጆርጅ ታውን እያለሁ በፌደራል መንግስት ስራ ሊያስገባ የሚችለውን ፈተና ወስጄ ስለነበርና ፈተናውን ማለፍ መውደቄን ስላሳወቅኩኝ ነው፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ መፈተን እንደሚቻልና አሁን መውሰድ እንደምችልም ማይክ ሊያግባባኝ ጣረ፤ እኔ ግን ብዙም አልተደሰትኩበትም፡፡ በመጨረሻ ላይ ማይክ «እግዲያውማ ለ CIA አመልከት?» በማለት ተሳለቀብኝ፡፡

ማይክ እየቀለደ ቢሆንም እኔ ግን ሃሳቡን ትኩረት ሰጥቼዋለሁ፤ በCIA ፍላጎት ማሳደሬን ግን ለማይክ ወዲያውኑ ትንፍሽ አላልኩም፡፡ ነገሩ የሆነው ወዲህ ነው በ1997 ዓ.ም፡፡ በጊዜው የአሜሪካንን መንግሥትና CIA'ን የተመለከቱ ጉዳዮች ትኩረትን የሚስቡበትና በየጋዜጣው የፊት ገጽ ሽፋንም CIA'ን የተመለከቱ ጉዳዮች በየቀኑ የሚወጡበት ወቅት ነበር፡፡ በአሜሪካ ሴኔትና በተወካዮች ምክር ቤት የሚመራ አንድ ቡድንም ከCIA ጋር የተያያዘ የተደበቀ ምስጢር ለማውጣት ጥድፊያ ላይ የነበረበት ወቅት ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ስለ CIA በጥልቀት የማውቀው ነገር ባይኖርም በCIA ፍቅር ማበዴንና የዚህ ድርጅት አባል የመሆን ፍላጎቴ ሌት ተቀን ማሰቤ የዕለት ተዕለት ተግባሬ ሆኖ ነበር፡፡ በርግጥ በጊዜው የ CIA አባል መሆን «አባሉ ያለ ወንጀሉ ቢገደልም ማንም ተጠያቂ አዳይሆንበ» ብሎ እንደመፈረም የሚቆጠር መሆኑን አልተገነዘብኩም ነበር፡፡ ብቻ ምን አለፋችሁ ከእናቴጋር ዓለምን ስዞር ማደጌ የተደበቁ ነገሮችን አነፈንፎ ማውጣትን ከልክ ያለፈ ፍላጎትን ሳያሳድርብኝ አልቀረም መሰለኝ በCIA ፍቅር ተነደፍኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ለማይክ አንድም ቃል ሳልተነፍስለት ሳንፍራንሲስኮ ለሚገኘው የፌደራል መንግስት ቢሮ ደወልኩ፡፡ ስልኩን ያነሳችውን ኦፕሬተርም የCIA ስልክ ቁጥር እንድትሰጠኝ ጠየኳት፡፡ ካሊፎርኒያ ያሰውንና ዴል የሚገኘውን የCIA'ን ቢሮ ስልክ ቁጥር ሰጠችኝ፡፡ ኦፕሬተሯ ስልኩን ከመስጠቷም በተጨማሪ ለሚገን ወስዳ ለፅሁፍ ፈተና የሚያገለግለኝን የመመዝገቢያ ፎርም ተቀብላ እንደምትልክልኝም ቃል ገባችልኝ.......፡፡ የግል የህይወት ታሪክ መግለጫ ጥያቄዎቹ የሚገርሙና እጅግ በርካቶች ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ እንደውም ግልፅ ስላልነበሩም እየደወልኩኝ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን እጠይቅ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የግል የህይወት ታሪክ መግለጫዎችን ለመሙላት ሁለት ሳምንታትን ወስዶብኝ ነበር፡፡ የጽሁፍ ፈተና የተሰጠው ደግሞ ሳንፍራንሲስኮ በሚገኘው የፌደራል ህንፃ የነበር ሲሆን ከእኔ ጋር የተፈተኑት ሰዎች አብዛኞዎቹ ከእኔ ዕድሜ በላይ የነበሩ በመሆናቸው ሁኔታው አግራሞት አጭሮብኝ ነበር፡፡ እንደውም CIA አባል ለመሆን ዕድሜም ወሳኝ ነገር ይሆን'ዴ ብዬም ከራሴው ጋር ሙግት ገጥሜ ነበር፡፡ እንኚህና መሰል ነገሮች ተደማምረው ፈተናውን እንደማላልፍ ራሴን በአሉታ መንፈስ ሸብብኩት፡፡ በአንድ ሬስቶራንት ውሰጥ ባገኘሁት የሳህን ማጠብ ስራዬ ላይ ሙጥኝ ብዬ ነበር፡፡ ምክንያቱም ተስፋ ከመቁረጤ የተነሳ የወሰድኩትን የፅሁፍ ፈተና እንኳን ዘንግቼው ነበር፡፡

አንድ ቀን ጧት የጽሑፍ ፈተናውን ከወሰድኩኝ ከወር በኋላ ይመስለኛል ስልክ ተደውሎልኝ ለቃለ መጠይቅ እንድዘጋጅ ተነገረኝ፡፡ ጥሪውን የነገረችኝ ሴት ደግሞ ቃለ መጠይቁ የሚደረግበትን ስፍራና ጊዜ ነግራኝ ተለያየን፡፡ ቃለ መጠይቁ የሚደረገው መሀል ከተማው ውስጥ በሚገኘው አንድ ሆቴል ውስጥ ሲሆን የስልክ ጥሪውን ያደረገችልኝ ሴትም በሆቴሉ «ጂም ስኮት» የሚባል ሰው እንዳገኝና እርሱም ሁሉንም ሂደት እንደሚያስረዳኝ ነግራኝ ነበር፡፡ የዛን ቀን ሌሊት ከደስታዬ የተነሳ ስሜቴን መቆጣጠር ተስኖኝ ስለነበር ዕንቅልፍ በዓይኔ ሳይኳል አደረ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ለCIA ለመስራት ከጫፍ ላይ በመድረሴ ሳይሆን ውስጤ ሲፈልገውና ሲሻው የነበረውን እውተኛ ስራ ላገኝ መሆኑ ስለተሰማኝ ነበር፡፡ ብቻ ምን አለፋችሁ ቃለ መጠይቁን በሚገባ ለመወጣት ውስጤን በራስ መተማመን መንፈስ እና በሞራል ገነባሁት ሌሊቱን ሙሉ ስንሳ ስቀመጥ ሰውነቴን ስለቃለቅ አይነጋ የለም ነጋ፣ ወደተባለው ሆቴልም ደረስኩ፡፡ ጨንቆኛል ሆቴሉን ብሳሳትስ ምንድን ነው የማደርገው? ጀምስኮትስ ምን ዓይነት ሰው ይሆን? ምን ዓይነት ጥያቄዎችን ይጠይቀኝ ይሆን? መልሶ ራሴው ላይ እያናጠቡብኝ ይራኮቱብኛል፡፡ በሰዓቱ ከሆቴሉ እንደደረስኩ በቀጥታ ጂም ስኮት ወደያዘው ማረፊያ ቤት አመራሁ፡፡ ለእንግዳ ተቀባዮች መልዕክት አስቀምጦልኝ ስለ ነበር፣ ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ እንድደውልለት መፈለጉን እንግዳ ተቀባዮቹ ነገሩኝ፡፡ ሁኔታው እንግዳ ነገር ነው የሆነብኝ ምክንያቱም እኔን እስከዚያ ደቂቃ እንድጠብቅ የሚያደርግበት ነገር ምን እንደሆነ ግልፅ ስላልሆነልኝ ነበር፡፡ ሐሳቦችን እያወጣሁና እያወረድኩ እንዲሁም እያውጠነጠንኩ ባለበት ቅጽበቶች ሰሳሳው ደቂያ እየተንቀረፈፈችብኝ ሞላች፡፡ ስደውልለትም እንድመጣ ነገረኝ፤ በእንግዳ ተቀባዩ እየተመራሁም ከዕልፍኙ ደረስኩ፡፡ ጅም ስኮት ያረፈበት ክፍል እጅግ ውብ ነው፡፡ ሁሉም ነገር በስርዓት የተቀመጠ ነው፤ የወለሉ ምራኪ ምንጣፍ፣ የአልጋው ሥርዐታማ አነጣጠፍ የሚያስደምም ነው፡፡ ብቻ ምን አለፋችሁ ከሁኔታው እንደተረዳሁት ከሆነ ጂም ስኮት በተከራየው ማረፊያ ክፍል ለአንዲት ቀን እንኳን ያደረበት አይመስልም፡፡ «ምናልባትም ለቃለ መጠይቅ ብቻ» ይሆን እንዴ!? የሚጠቀሙበት ብዬም አሰቤአለሁ፡፡ ጂም ስኮትንም በስም ካወቅኩት ግዜ አንስቶ እንደማስበው ዓይነት ሰው ሆኖ



t.me/OLDBOOKSPDF

አላገኘሁትም፡፡ የCIA አባል ሳይሆን አማተር የኮሌጁ አግር ኳስ ታጫዋች ነበር የሚመስለው፡፡

ከክፍሉ እንደገባሁ ሁለታችንም ወንበር ይዘን ተቀመጥን፡፡ ልቤ በመጠኑም ቢሆን ተምቧ፣ ተምቧ ማለት ጀምራለች፡፡ በአንፃራዊነት የልቤ ምት ስኮትን ከማየቴ በፊት ካለው ጊዜ ጋር ሲነፃፀር ያ ሁሉ የገነባሁት ወኔ ሲከዳኝና ልቤ ሲርድ ይታወቀኛል፡፡

«መቼም ስለ CIA ብዙ ነገር ታውቃለህ ብዬ አስባለሁ፡፡ ቢሆንም ግን ተጨማሪ ነገሮችን መጋገር መልካም ይሆናል በሚል ዕሳቤ ነው ላናግርህ የፈቀድኩት» በማለት ጉሮሮውን በመጠራረግ ንግግሩን ጀመረ፡፡ ስኮት እንዳለው ስለ CIA የማውቀው ነገር ይኖራል፤ ባይኖርም ግን አላውቀም የምል አይመስለኝም፡፡ በመሠረታዊነት CIA በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነበር፡፡ አንደኛ የኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የኢንተሊጀንስ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡ ሌሎች ተመሳሳይ ዳይሬክቶሬት ቢኖሩም ለ CIA ያላቸው ሚና የአጋርነት ነው፡፡ የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ቢኖርም ለCIA ያላቸው ሚና የአጋርነት ነው፡፡ የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ኤክስፐርቶችን፣ የሰነልቦና፣ የፊዚክስ የማህበራዊ ሳይንስና ተመሳሳይ ምሁራን አጠቃሎ የሚይዝ ክፍል ሲሆን ተቀዳሚ ተግባሩም መረጃዎችን እያነፈነፉ ማሰባሰብ፣ መገምገምና ውሳኔዎችን ማሳለፍ ሲሆን፤ በኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ውስጥ የታቀፉት ሰዎች ደግሞ የሰበሰቧቸውን ማስረጃዎች ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት መስጠትና የሎጀስቲክና መሰል ስራዎችን ማከናወን ነው፡፡

ስኮት ስለ CIA ክፍሎች በዚህ አይነት ሁኔታ ከገለፀልኝ በኋላ «በምስራቅ ኤሽያ ጥናት በበርክሌ ዩኒቨርሲቲ የግራጁዬት ስኩል ውስጥ ለመማር ማመልከትህን አውቃለሁ፡፡ ከዚህም እንፃር አንተ በCIA የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት የምትመጥን ይመስለኛል» በማለት አከለበት፡፡ ስኮት እውነቱን ነበር በርግጥም ለበርክሊይ ዩኒቨርሲቲ ለምስራቅ ኤሽያ ጥናት ክፍል አመልክቼ የነበረ ሲሆን ማንዳሪያን የተሠኘ የቻይናዎች ኮርስም መውሰድ ጀመሬ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ዩኒቨርሲቲው እንድማር ቢፈቅድልኝም እንኳ በሁኔታዎች አስገዳጅነት እንደማልገባ አውቅ ነበር፡፡

«እርግጠኛ ነኝ የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬትን እጅጉን ትወደዋለህ» አይደል!? ሲል አከለበት፡፡ ስኮት እጅግ ተግባቢና በጓደኛነት ስሜት ሰዎችን መቅረብ የሚፈልግ ሰው ይመስላል፡፡ ስኮት CIA የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ውስጥ መስራት እንደ ዕድል የሚቆጠር መሆኑን ማብራራቱን ቀጥሎልኛል፡፡ እኔም በቃ! በሀሴት እና በተመስጦ ነበር የማዳምጠው «የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት በቃ! ዩኒቨርሲቲ ማለት ነው፡፡ እጅግ በርካታ ምሁራንና ታላላቅ ሰዎች ያሉበት ነው፡፡ በዩናይትድ ስቴትስ ማዕከላዊ መዲና በሆነችው ዋሽንግተን ዲሲ መኖርም ሌላው ትልቁ ጥቅም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የተለያዩ ሐገራትን፣ ባህል፣ ቋንቋና የኑሮ ዘይቤ ለማወቅም ከየትኛውም መሳሪያ ቤት በተሻለ ሁኔታ የሚመረጥ ነው.......» በማለት ገለፃውን ቀጠለ፡፡ እኔም በጥሞና ከማዳመጤ በተጨማሪ የሚያወራውን ነገር ሁሉ እያመንኩት ስለመምጣቴ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ስኮት የማያቋርጠውን ገለፃውን ቀጥሏል፡፡ ታውቃለህ የኢንተሌጀንስ ዳይሬክቶሬት ከዩኒቨርሲቲ የሚበልጥበት ምክንያት? የትኛውንም አይነት የመገናኛ ብዙሃን፣ መጽሐፍት፣ መጽሔቶች፣



t.me/OLDBOOKSPDF

በራሪ ወረቀቶችንና መሠል መረጃ ምንጮችን በፈለግከበት ዓይነት ቅርፅ ማግኘት የምትችለው በከፊል ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ ግን መረጃን የምታገኘው በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ነው፡፡ ለአፍታ ያህል እንደማሰብ ብሎ የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ከዩኒቨርሲቲ የሚለይበት ሊላም ነገር እንዳለው ሹክ አለኝ፡፡ የአዕምሮዬን ጓዳ የሚበረብር ይመስል ትክ ብሎ ተመለከተኝና እንዲህ አለኝ፡- «የአሜሪካ የፕሬዚዳንት ቢሮ የከፍላችን አካል ነው»፡፡ ከዚያም የተናገረውን ነገር በደንብ እረዳለት ዘንድ ለአፍታ ያህል ገም ካለ በኋላ እንዲ በማለት ቀጠለ «አሜሪካንን ከሚያከል ታላቅ ሀገር ፕሬዚዳንት ጋር ስለ አንድ ውስብስብ ችግር እንደመወያየት በጉዳዩም ፕሬዚዳንት ጋር ስለ አንድ ውስብስብ ችግር እንደመወያየት በጉዳዩም ፕሬዚዳንቱ አንተን ሲያደምጡህ እንደመመልከት ምን ሊያስደስት የሚችል ነገር አለ?» በማለት ጠየቀኝ፡፡ «እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ስራዎችን ከሚሰሩት ታላላቅ ሰዎች መካከል አንዱ አንተ ለመሆን መዘጋጀትህ ሊያኮራህ ይገባል ሲልም አከለ፡፡ ልቢ በሀሴት ሲቃ ድልቅ ድልቅ እያለ ጮቤ ሲረገጥ ይታወቀኛል እንደውም ደረቴንም ከፍቶ የሚወጣም መሰለኝ፡፡ ስኮት ስለ ፕሬዘዳንቱ እያወራኝ ባለበት ቅፅበት እኔ የፕሬዘደንቱን ምስል ከአዕምሮዬ ጓዳ በመከተብ ስለ አንድ ችግር የሆነ መረጃ ስነግራቸውና ሲያደምጡኝ በሀሳብ ነጎድኩኝ፡፡ የስኮት ንግግርም በደሜ መግባቱን የተረዳሁትም ከዚህ በኋላ ነበር፡፡

በመካከላችንም ለአፍታ ያህል ፀጥታ ሰፍና ሁለታችንም በየራሳችን የሐሳብ ባህር ሰመጥን የሆነው ሆኖ ስኮት ጸጥታውን ገሰሰው፡፡ እንዴት ነው ታዲያ.. ስራውን የምትወደውና የምትወጣው አይመስልህም አለኝ፡፡

«እንዴታ! በሚገባ እወደዋለሁ እንጂ!» አልኩት፡፡

ስኮት የማመልከቻ ወረቀቱን ሰብስቦ በአታሼ ቦርሳው ካጨቀ በኋላ በትኩረት ተመለከተኝና እንደው እውነቱን ለመናገር እጅግ አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ ማለትም ያለ ፒ.ኤች.ዲ ወይንም ማስተርስ ዲግሪ አሁን ባለህበት ሁኔታ አሁኑኑ ከባዱን ሃላፊነት አንሰጥህም፡፡ ምናልባት ከበርክሌይ በኋላም ይሆናል፡፡ ለማንኛውም ግን ማመልከቻፀን በቀጥታ አስገባዋለሁ» አለ፡፡ ስኮት ስለ ኢንተለጀንሲ ዳይሬክቶሬት ማብራሪያውን ከሰጠኝ በኋላ ስለሊላው ክፍል የኦፕሬሽ ዳይሬክቶሬት ስለሆነው ማውራቱን ቀጠለ፡፡ እዚህ ዲፓርትመንት ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ ባለስልጣናት የ CIA ቅጥረኞችን በየሃገራቱ የሚያሰማሩ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ቅጥረኞች ታዲያ የውጭ ዜጎች ናቸው፡፡ ማለትም ቅጥረኞቹ የየሀገሩ ዜጎች ከሆኑ የየሀገራቸውን ቋንቋና ባህል በሚገባ ከመረዳታቸውም በተጨማሪ CIA ከሀገራቸው መንግስት የሚፈልገው ጉዳይ ቢኖረው እንኳ መረጃውን በፍጥነትና በተሟላ መልኩ ለማግኘት ስለሚያስችለው ነው፡፡ በሊላ አነጋገር የቅጥረኞቹ ተልዕኮ ምስጢራትን፣ እቅዶችን፣ ዶክመንቶችንና የመሳሰሉትን ጠቃሚ መረጃዎችን መሰረት ብሎም ማቀበል ነው፡፡» ካለ በኋላ ለአፍታ ያህል ዝም አለ፡፡ ስኮት ብዙ ከተናገረ በኋላ ዝም የማለት ባህሪ አለው፤ ምናልባትም የተናገረውን ለማብሰልሰል እንድችል ጊዜ እየሰጠኝም ይሆናል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን ራስህን በኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ውስጥ ከቅጥረኞቹ መረጃዎችን የመሰብሰብ ኃላፊነት እንዳለው ሰው ቁጠረውና፤ ልትሠራው የምትችለውን ሥራ በምሳሌ ላስረዳህ» ሲል ቀጠለ ስኮት ለአፈታ ያህል ትንፋሹን ከሰበሰበ በኋላ

«....... ጊዜው 1941 ዓ.ም ነው እንበል፡፡ ጃፓኖች የፐርል ሃርቦርን ጥቃት ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡ የአሜሪካ ጦር ስለሁኔታው ፍንጭ የለውም፡፡ የሆነው ሆኖ እጅግ ጥቂት መረጃዎች ከወደ CIA ተገኝተዋል፡፡ ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት መረጃዎች ሙሉ መሆን መቻል አለባቸው፡፡ ስለዚህ የጃፓን ጦር በሃርቦር ሊያደርግ ያቀደውን የጥቃት መረጃ ለማግኘት CIA ወደ ቶኪዮ ልኮሀል እንበል፡፡ እዚያ ከአንተ ጋር በመገናኘት መረጃውን የሚያቀብልህ ጃፓናዊ የ CIA ቅጥረኛ ይጠብቅሃል፡፡ ይህ ምን ዓይነት አደጋ እንዳለው መረዳት የሚከብድህ አይመስለኝም ምክንያቱም ቅጥረኛው CIA'ን በመክዳት ለሀገሩ መንግስት አሳልፎ ሊሰጥህ እንደሚችልም ማመን ግድ ነው፡፡ በCIA ውስጥ መሥራትን አደገኛ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንዱ ደግሞ ይሄው ነው፡፡ ዕድለኛ መሆን ከቻልክ ቅጥረኛው CIA'ን አይከዳም፡፡ ....... ለማንኛውም ቅጥረኛው CIA'ን አልከዳም እንበል፡፡ እንደ ሰላይ የምትገናኙት በምስጢራዊ ቋንቋ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ሰውየው መረጃውን ሊሰጥህ ሲፈልግ ይደውልልሃል፡፡ ስልኩን ስታነሳው የተሳሳተ ቁጥር ላይ መደወሉን ከገለፀከለት በኋላ ይቅርታ ጠይቆህ ይዘጋዋል፡፡ ይህ በCIA ቋንቋ ሲተረጎም «አንድ ቦታ ተገናኝተን መረጃውን ውሰድ» ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ «በተመሳሳይም ሌሎችን የድርጅቱን ምስጢራዊ መገናኛ ስልቶች በመጠቀም ትገናኛላችሁ፡፡ በመጨረሻም መረጃውን ይሰጥሃል፡፡» አለና ስኮት በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ከተቀመጠበትም ተነስቶ ወደ ፍሪጁ በመሄድ ሁለት ቀዝቃዛ ኮካ ይዞ መጣ፤ ለእኔና ለእርሱ መሆኑ ነው፡፡ እንደገናም ቁጭ አለና ትረካውን ቀጠለ፡፡ «ስራው ይህን ያህል አስቸጋሪ ነው፡፡ በCIA ውስጥ ትንሽ ስህተት መስራት ራስን በገመድ ውስጥ ማስገባት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ቅጥረኛው በፈፀመው ስህተት እዚያው ቶኪዮ ውስጥ በቁጥጥር ስር ብትውል እስር ቤት መወርወር እንደትምህረት የሚቆጠርልህ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም እስቲ አስበው ....... የጠለፍከው የእንዷትን ሉዓላዊ ሀገር መረጃ ነው፡፡ ይህ መረጃ ለሃገሪቱ የህልውና ጉዳይ መሆኑን ልብ በል፡፡ ጃፓን ፐርል ሃርቦር ላይ ልታደርሰው ያወጣችው ዕቅድ ቢሰረቅ በቀላሉ ለሽንፈት መዳረጓ ግልፅ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ያህል መረጃ ስትዘርፍ ብትያዝ ዕጣፋንታህ ቀላል ይሆናል ብለህ ታስባለህ? በፍፁም! ....... ልብ ማለት ያለብህ ላስፈራራህ ፈልጌ አይደለም፡፡ .......ግን እውነታውን ማወቅ ለጥንቃቄ ጠቃሚ መሆኑ ስለሚታመን ነው፡፡ ብቻ በኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ክፍል ይህን ዓይነቱን ከባድ ኃላፊነት ይዞ መስራት እንደነገርኩህ አደጋም ጭምር እንደተጋረጠበት፤ በአንፃሩ ግን በድል ስትወጣው ደግሞ የሚያስገኘው ክብርና ዝና እንዲሁም ደስታህ በእጅግ ከፍተኛ መሆኑንም ከወዲሁ ላስረግጥህ ፈልጌ ነው፡፡» አለና ሐሳቡን ያጠቃለለ በሚመስል ሁናቴ ገታ አለና ወንበሩ ላይ ተደላድሎ ተቀመጠ፡፡

በመጨረሻም «ለመሆኑ ግን በኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ውስጥ የመስራት ፍላጎትህ ምን ያህል ነው በማለት ጠየቀኝ፡፡ ንግግሩ ሳያስደነግጠኝ አልቀረም መሰለኝ ሐቄ ሁሉ ተበታተነብኝ፡፡

✡✡✡



t.me/OLDBOOKSPDF

ፕያቴውንም ወጂያውኑ ልመልሰለት አልተቻለኝም ከፍሉንም የፀጥታ ድባብ ረበበው፡፡ ወቅቱን በትክክል አስታውሰዋለሁ በወርሃ መጋቢት 1976 ዓ.ም ለተጨማሪ ቃለ መጠይቅ ወደ ዋሽንግተን ተጠራሁ፡፡ በዋርጌት የሆሊዴይ ሆቴሌ ውስጥ ቦታ ተይዞልኝ ስለነበር እዚያው ባረፍኩበት ሆቴል ውስጥም እጅግ በርካታ፣ መስቀልኛ እና ፈታኝ ቃለመጠይቆች ተደረጉልኝ፡፡ ሁሉም ቃለመጠይቆች የተደረጉልኝ ካረፍኩበት ሆቴል ውስጥ መሆኑና ለምን በCIA ህንፃ ውስጥ ይህንን ማድረግ እንዳልፈለጉ አስደንቆኛል፡፡

✲✲✲

በቆይታዬም ከተዋወኳቸው ሰዎች መካከል እጅግ የወደድኩት ቢኖር ዶን ግሬግን ነበር፡፡ ዶን በጊዜው የደህንነት አማካሪ የነበረ ሲሆን ትልቁ ቡሽ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በመሆን በተመረጡበት ወቅትም የደቡብ ኮሪያ አምባሳደር ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ ከዶን ጋር አብረን ባወጋናቸው ጊዜያት ውስጥ ደስ የሚሉ አውዶ አርስቶች ላይ ትኩረት ሰጥተን ተነጋግረን ነበር፡፡ በተለይም ከውልደቴና ካደኩበት አካባቢ ተለይቶ በሰው ነገር መኖር ምን ያህል አስቸጋሪ እና ፈታኝ እንደሆነ በውጭ ሃገራት የነበረውን የቆይታ ተሞክሮዎችን እያነሳ ያጫወተኝን መቼም አይረሳኝም፡፡ ዶን ስለ እኔ ማወቅ ይፈልግ የነበረው ነገርም በርካታ ነበር፤ በተለይም አውሮፓ በነበርኩበት ወቅት ያሳለፍኳቸውን ቁም ነገሮች በተመለከተ አጥብቆ ይጠይቀኝ ነበር፡፡ በተለይም በአውሮፓ ቆይታዬ ጓደኞችን አፍርቼ መሆኑንና አለመሆኑን ማወቅ በጣም ጓጉቶ ነበር፡፡ ከሁኔታው እንደተረዳሁትም ከሆነ በCIA የኦፕሬሽ ዳይሬክቶሬት ሆኖ ለመስራት የውጭ ሐገራት ቆይታና ልምድ ወሳኝ መሆኑን ነበር፡፡ በCIA ለመመልመሌና ለመመረጤ ቅድመ ዝግጅቱን ያወቅኩት ወደ መጨረሻው ምዕራፍ ወደ ሆነው የህክምና ምርመራ ስሸጋገር ነበር፡፡ ቦታውም ካረፍኩበት የሆሊዴይ ሬስቶራንት ጎን ካሉት ህንፃዎች በአንዱ ነበር፡፡ የህክምናውን ምርመራ የማደርግበት ጊዜ ሲደርስም ወደ ስፍራው አመራሁ፡፡ በህንፃው ውስጥ ከሚገኘው ክፍል በአንዱ እንደዘለቅኩኝም ስኮት እንደማገኘው የነገረኝን ሐኪም ማለትም ዶክተር ጃርሜንን አገኘሁት ዶክተር ጃርሜን ዕድሜው 35 አካባቢ የሚገመት ጎልማሳ ሲሆን በሩን እንኳኩቼ እንደገባሁም እጅግ በሚያስደስት ትህትና ነበር የተቀበለኝ፡፡ ዶክተር ጃርሜን በነጭ ሸሚዙ ላይ ያሰረውን ከራቫትና ከበረዶ የነጣ ጋውኑ ከተከለ ሰውነቱ ጋር ተዳምሮ ግርማዋገስን አላብሶታል፡፡ ይሁንና ከቢሮ ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠውን ትልቅ የሒሳብ መሣሪያ ለተመለከተ ደግሞ አካውንታንት እንጅ ሐኪም አይመስልም ነበር፡፡ ብዙም ሳንቆይ ወደ ምርመራው ክፍል አመራን፡፡ የምርመራ ክፍሉ አልጋና እየተጣጠፉ የሚዘረጉ ወንበሮችና አስትሬቸሮች ይበዙበታል፡፡ በተለይም ከፕላስቲክ የተሰሩ ታጣፊ አልጋዎች ብዙ ናቸው፡፡ እናም ከእነኚህ አልጋዎች በአንዱ ላይ ተጋድሜ ምርመራውን እንደማደርግም ገምቼያለሁ፡፡ ዶክተር ጃርሜን ከሚተጣጠፈው ወንበር በአንዱ ላይ እንድጋደም ካደረገኝ በኋላ የተለያዩ መሣሪያዎቹን አዘጋጅቶ ምርመራውን ቀጠለ፡፡

የቀኝ አውራጣቴ ከብረት ኤሌክትሮድ፣ ደረቴ ከመተንፈሻ ቱቦ እንዲሁም የቀኝ ክንዴ ከሙቀት መጠን መቆጣጠርያ መሣሪያው ጋር ተያይዘዋል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«የልብ ምት፣ የአተነፋፈስ ስርዓትህና ተመሳሳይ ነገሮች በጤነኛ መልክ ሂደታቸውን ይቀጥሉ ዘንድ ለጥያቄዎቹ እውነተኛ መልሶችን መስጠት ይኖርብሀል» አለኝ ሐኪሙ፡፡ ከዚያም ጥያቄዎቹን ማዥጎድጎድ ጀመረ፡፡ «አደንዛዥ ዕፆችን ትጠቀም ነበር .......? በስርቆት ተሳትፈሀ ታውቃለህ .......? ከውጭ መንግስት ጋር ግንኙነት ነበረሀ? ወዘተ ....... » የሚሉ ጥያቄዎችን አከታትሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም «አዎ ....... አይደለም» በማለት ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ሰጠሁኝ፡፡

ምርመራው በአጭሩ አራት ሰዓታትን ወሰደ፡፡ ዶክተሩ ተመሣሣይ ጥያቄዎችን ለሦስት ጊዜ አከታትሎ ከጠየቀኝ በኋላ ትቶኝ ወደ ሌላኛው ክፍል ሄደ ከአስር ደቂያዎች በኋላም ተመልሶ መጣ፤ የምርመራውን ውጤት በተመለከተ ልለፍ አሊያም ልውደቅ አሁን እርግጠኛ መሆን እንደማልቻለም ነገረኝ፡፡ የምርመራ ውጤቱን ለአማካሪው መስጠት እንዳለበትና የመጨረሻው ውጤት የሚገለፀውም ከአንድ ሳምንት ቆይታ በኋላ መሆኑን ነግሮኝ በዚሁ ተለያየን፡፡ ከስኮት ጋር ስንገናኝ አላስችል ብሎኝ የህክምና ምርመራው ውጤት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል ብዬ ስጠይቀው በድል አድራጊነት ስሜት አውራጣቱን ወደ ላይ ቀስሮ «አልፈሐል »አለኝ፡፡

✡✡✡

....... ለጊዜው ምክንያቱን ባላውቅም ጥሩ ሙድ ውስጥ ነበርኩ፡፡ ይሁንና ይህ ስሜቴ የዘለቀው በሀሳብ ፈረስ ወደ ፍራንሲስኮ እስካስገርኩበትና ከአፓርትመንታችን በር ስር የተኛችውን የጓደኛዬን ውሻ እስካየሁበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር፡፡ ከጓደኛዬ ማይክ ክፍል ከወጣሁ በኋላ ያመራሁት ወደ በርክሌይ የተማሪዎች ህብረት የማስታወቂያ ቦርድ ነበር፡፡ እዚያ አካባቢ ጥቂት ተማሪዎችን ውርውር ሲሉ ከመመልከቴ ውጭ ያገኘሁት አዲስ ነገር ባለመኖሩ ወደ ክፍሌ ተመለስኩ፡፡

ቀሽንግተን ካደረኩት ቃለ መጠይቅ ከስድስት ሳምንታት በኋላ አንድ ቀን ጧት የአፓርታማዬ በር ደውል አቃጨለ፡፡ በአፓርታማው ውስጥ የነበርኩት እኔ ብቻ ስለነበርኩኝ በሩን መክፈት ግድ ይለኝ ነበርና ለመክፈት ሄድኩኝ፡፡ በሩን ስከፍተው ዕድሜያቸው በግምት ወደ ስልሳዎቹ የሚጠጉና ግራጫ ፀጉር የወረራቸው አዛውንት እንደ ጅብራ በሩ ላይ ተገትረዋል፡፡ ሰውዬው በአንድ እጃቸው መካከለኛ መጠን ያለው ሳምሶናይት ቦርሳ (አታሼ ቦርሳ) በሌላኛው እጃቸው ደግሞ የቦታ መጠቆሚያ ካርታ ይዘዋል ለጊዜው ግለሰቡ በየቤቱ እየዞሩ የሚሰብኩ ክርስቲያን የኢቫንግሊካል ሚሽነሪ እማኝ ነበር የመሰሉኝ፡፡ ግለሰቡ በጠዋቱ ስለረበሹኝ ይቅርታ ከጠየቁኝ በኋላ በበርክሌይ ከሚገኙት ጓደኞቼ የአንዱን ስም ጠሩልኝ፡፡ እሱን ፈልገው እንደመጡም ነገሩኝ አጋጣሚው ገረመኝ አዛውንቱም የጠሩት የጓደኛዬ ስም ለCIA ካስገባሁት የማመልከቻ ቅፅ ላይ በአደጋ ጊዜ ተጠሪዬ ከሆኑት በአራተኛ ረድፍ ስሙን የሞላሁት ጓደኛዬ ነበር፡፡ ለሽማግሌው የጓደኛዬን አድራሻ ልሰጣቸው ካሰብኩኝ በኋላ በጭንቅላቴ ውስጥ ሌላ ሐሳብ ብልጭ በማለቱ ተውኩት አዛውንቱም የ CIA የምርመራ ቡድን አባልመሆናቸውንም ጠረጠርኩ፡፡ ግለሰቡን በዚህ ሁኔታ ማለትም የተሳሳተ መረጃ ይዘው ወደዚህ አፓርታማ መምጣታቸውን እያስረዳኋቸው ወደ በሩ ስሸኛቸውም ለፈጠሩት ስህተት ደጋግመው ይቅርታ ይጠይቁኝ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

✡✡✡

በወርሀ ሐምሌ ዕለተ ሰኞ ማልዶ ላይ፣ ያለውትሮዬ ድብን ያለ ዕንቅልፍ ላይ ነበርኩ፡፡ ይሁንና በተደጋጋሚ ሲያንጫርርብኝ የነበረው ስልክ ከጣፈጠው ዕንቅልፌ ቀስቅሶኝ አነሳሁት፡፡ የስኮትን ድምፅ በቀጭኑ ሽቦ ለመለየት የተጫጫነኝ የጠዋት ድብርት አላገደኝም ነበር፡፡

«በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ዋሽንግተን መገኘት ትችላለህ? የኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት አንድ ክፍት የስራ ቦታ አዘጋጅቶልሃል» አለኝ፡፡ ከCIA ጋር ግንኙነት ካቆምኩ ሶስት ወራት አልፎኛል፡፡ አሁን የኔ ትኩረት በርክሌይ ውስጥ የማጠናው ማንዳሪን የተባለ የቻይንኛን ቋንቋ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ ስኮት ሥራ ተገኝቶልሃል ያለው ነገር በጥቂቱም ቢሆን ልቤን ሰልቦታል፡፡

ስኮት በስልኩ ሲያወራ ትግስት ያለው አይመስልም፡፡ «በሁለት ሳምንታት ውስጥ ዋሽንግተን መገኘት ይኖርብሐል! ፡፡ እለበለዚያ «ሁሉም ነገር ከንቱ ይሆናል» ብሎ የሚተፋቸውን ቃላቶች አጠነከራቸው፡፡ «እርግጠኛ ነህ ለስራው የምመጥንና የማስፈልገው ሰው እኔ መሆኔ ታምኖበታል?» አልኩት ስኮትን፡፡ «ሊያውም ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ያህል ነዋ!» ሲል መለሰልኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፫

## ነሀሴ 1977 ቨርጂኒያ-ታይድዎተ ....... ቦታ

ምንም እንኳን ከሲ-46 አውሮፕላን በር ላይ በፍርሐት ተሸብቤ ቁጢጥ ብልም ውሽንፍሩ ምንም ዓይነት ነገር እንዳይ አላስቻለኝም ከታች ያለው ዕይታዬ ደግሞ እንደ እሀያ ሆድ የከበደው ቁልል ደመና ፀሐይ ግባት ጋር ተዳምሮ መጨረሻው የማይታወቅ ዋሻ አስመስሎታል፡፡ ወደ ሞተሩም አቅጣጫ ወደ ታች አንገቴን አስግጌ ለመቃኘት ሰሞከር ከጢያራው ሞተር ሽቅብ የሚነሳው ትንታግ ልክ እንደ ጦሮ አውሎንፋስ ከበሩ መንጥቆ ሊያወጣኝ ነበር፡፡

ከሦስት ሰዓታት ላልበለጠ ጊዜያት በአውሮፕላኑ ማኮብኮቢያው ቆይተናል ቆይታችንም ምን ለመጠበቅ እንደነበር እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው አሁን ደግሞ ይኸው የፓራሹታችንን ቀበቶ እንድናጠብቅ ቀጠን ያለ ትዕዛዝ ተሰጥቶን በሚያቃጥለውና እንደ ዕሳት ወላፈን በሚጋረፈው በጢያራው የወበቅ ትንታግ እየታጀልን ነው፡፡ የተናዳፊ ትንኞች ንክሻ ደግሞ ኩሪያ ሰራሹን የወታደር መለዮዬን ዘልቆ ይሰማኛል ከመመረሬም የተነሳ ወደ ሰሜን ንፋቀ ክበብ ዝለል ብባል ደስታውን አልችለውም ነበር፡፡

የፓራሹት ዝላይ አሰልጣኛችን ማለትም ሬድ ብለን የምንጠራው 'ዊንቲድ' በበሩ በኩል ፊቱን ወደ ውጭ አውጥቶአል፡፡ በአስተውሀሎትም ታች ያለውን የመሬት ርቀት እየቃኘ እንደነበር ለመገመት ብዙ አልተቸገርንም ቀሪዎቹ የቡድኔ አባላት ቀደም ብለው ዘለዋል ቅደም ብዬ ያልኩት ላይቀርልኝ ፊራ-ተባ እያልኩ አንተ ቅድም አንተ እድም በማለቴ ነው፡፡ እናም አሁን በግምት መሬት ለመንካት ሳይቃረቡ አይቀርም፡፡ ሬድ ተነጣጥለን እንድንዘል የሚያረገን ሆን ብሎ ነው፡፡ ምክንያቱም «በውጊያ ወቅት ሁሉንም እንዳናጣቸው ያሉህን ሰዎች እንዴ እንዲዘሉ ማድረግ የለብህም ሲል በመደባዊ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ወቅት ትምህርት ቤት ያስተማረንን ትምህርት በአዕምሮዬ ውስጥ ያቃጭል ነበር፡፡ «እንዲህ ማድረጉ ደግሞ ተልዕኮውን ከሚጋረጥበት አደጋ ይታደገዋልና» በትውልድ ስዊድናዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆነው ግርማሞገሱ የሚመች ሬድ CIA ባደረጋቸው ምስጢራዊ ጦርነቶች ሁሉ ተካፍሏል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት ምንም ሰው የእርሱን ያሀል በጠላት ወረዳ ውስጥ ሰለሚደረጉ የውጊያ ዝላዮች አያውቅም ለማት ይከብዳል በጣም ተከናታልና፡፡

ሬድ ቲቤታውያንን እንዴት በአውሮፕላን ዝላይ ከሂማሊያ ሰንሰለታማ ተራሮች ላይ ማረፍ የሚችሉበትን ቴክኒክ እንዳስተማራቸው ይነገርለታል በጊዜው ቲቤታውያኑ ዝላዩን ይፈፅሙ የነበሩት ከሃያ አምስት እና ከሰላሳ ሺህ ጫማ ከሚደርስ ከፍታ ይሁን እንጂ አንዳንዴ ወደ ጎን የሚነፍሰው ኃይለኛ ነፋስ የማረፊያ ክልላቸውን በማዛባት የፓራሹት ዝላያቸውን አስቸጋሪና ዕልሀ አስጨራሽ ያደርግባቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህም ለአሰልጣኙ ሬድ ወደ ኮሎራዶ ሃሌ ወደሚገኘው ካምፕ ለማስፈር አስገድዶታል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እናም በሃሌ ካምፕ ቲቢታውያኑ ከወሰዱት ቴክኒኮች መካከል የፓራሹት ገመዶቻቸው እስከሚበጣጠሱበት የመጨረሻ ሰከንድ ድረስ እንደምን ሚዛናቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ሬድ አስተምሮአቸዋል፡፡ ከትምህርቱም መጨረሻ ለመስከ ልምምድ ወደ ሂማሊያ ሸለቆዎች በመሄድ ዝላዮቻቸውን በሚፈፅሙበት ወቅት የሚጋፋቸውን ነፋስ ለመቋቋም አይነተኛው ዘዴ ልክ እንደ በራሪ ኮከብ ወደ ታች መውዘግዘግ መሆኑን ከወሰዱት ስልጠና ተረድተዋል፡፡

ሬድ መጀመሪያ ያስተማረን በፓራሹት ዝላይ ወቅት ማረፊያው ስጋቱራ ከሆነ ጉድጓድ ውስጥ ማረፍ እንደምንችል ነበር፡፡ የስልጠናውም ቅደም ተከተል በመጀመሪያ በተረከዞቻችን መሬት ከነካን በኋላ ለጥቆ፣ ባታችንን፣ ዳሌያችንን በመጨሻም ጀርባችንን እንዴት በየተራ ከመሬት በማሳረፍ መንከባለል እንዳለብን ከበቂ በላይ ልምድ ወስደናል፡፡ በመጨረሻም የመስክ ስልጠናው ምን ያህል የገባን ስለመሆኑ ሬድ በተናጥል ያረጋግጣል፡፡ «አንድ ጊዜ ዝላዬን ፈፅሜ የሸፈነውን የስጋቱራ ብናኝ ላብ እየጠረግኩ ሳለ ወደ እኔ ሰግደድ ብሎ በመምጣት አስተራረፍህ ፈፅሞ እምስቱን የማረፊያ ነጥቦች አልተጠቀምክም» ሲል እንዳንገባረቀብኝ ትዝ ይለኛል፡፡

ሬድ ትምህርቱን በደንብ እንደገባን ለማወቅ ሲልም አምስቱን ማረፊያ ነጥቦች በመጠቀሙ ከአንድ ዝላይ ነፍሱን ያተረፉ ምልምል ወታደር ያልሆነ ሲቪል ሰው ወደ ማሰልጠኛችን አምጥቶ አስተዋውቆናል፡፡ «አንድ ሌሊት ሳአስ ውስጥ ይመስለኛል ሰውየው በግዳጅ ላይ እንዳለ ፓራሹቱ አልከፍትለህ ይለዋል በዚህን ግዜ በሰዓት ከሃያ እስከ ሰላሳ ማይልስ በሆነ ፍጥነት ወደ መሬት መውዘግዘግ ይጀምራል ያኔም ታዲያ መሬት በሚያርፍበት ጊዜ አምስቱን ነጥቦች በሙሉ ተጠቅሞ ባያርፍ ኖሮ ነፍሱን ባላተረፈም ነበር፡፡ ምንም እንኳን ካረፈበት ተነስቶ ለመራመድ ቢያስነክሰውም ህይወቱን አትርፎለታልና እናም እንዴት እንዳስደነቀን ነው የምንገራችሁ ይሄም መመሪያን መከተልና ባግባቡ መጠቀም ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ላስገንዝባችሁ እወዳለሁ፡፡

✲✲✲

የመጣሁበት የስልጠና ቡድን አርባ በመቶ የምንሆን ከሲቪሎች ስንሆን ስልሳ በመቶ ደግሞ ከቀድሞ ጦር ባለስልጣናት የተውጣጣውን የዲኦ ስልጣኖችን ከፍል ይወክላል ማለት ይቻላል፡፡ በቀጣዮቹ ሁለት አስርተ ዓመታት CIA መረጃን እያነፈነፈ ከመሰብሰብ ስራው በተጨማሪ የተለያዩ ማስታወቂያዎችን በማሰባሰብ ቁጥቁጥ የፖለቲካ ባለስልጣኖቹን ወደሚያስደስትበት ድረጅትነት ሲቀየር እመለከት ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ የCIA እናት የሆነችውን የሎጀስቲክና የስትራቴጂክ ግልጋሎቶች ቢሮ (ኦ.ኤስ.ኤስ) ዳግም ነፍስ ዘራች እንደማለት ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ሁላችንም ጀብደኞች ነን፡፡ የመረጥነው ግን ጀብደኛ የማያረጉንን የዲአይ ዘመቻዎችን ነበር፡፡ እንደ ዕውነቱ ከሆነ ህዝብን የማገልገል ከፍተኛ መሻት አለን፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ የመሰለ ኃያላን ሀገር ደግሞ ታላቅ የመረጃ መረብ አገልግሎት ያስፈልጋታል እኛም ልጆቿ ደግሞ ይህን ታላቅ ፍላጎቷን ለማሟላት ደፋ-ቀና በማለት ላይ ነን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

✿✿✿

...... እምስታችንም በፓራሹት ዝላይ ከታይድምተ ሽርጀኒያ እረፍት ይሁቀ በዑር ከሚሰጡትና አሙቱን ሙሉ ከሚካሂዱት የዲ.ኤ. ስልጠናዎች የመጨረሻ የሆነውን የአራት ወር ወታደራዊ ቀመስ ልምምድ ለማድረግ ነበር፡፡ ልምምዱ በአሜሪካ መንግስት ከሚደጎሙት የስልጠና ልምምዶች ሁሉ ከፍተኛ በጀት የተመደበለት ጠንካራና አድካሚ ልምምድ ነበር፡፡ ይህን ልምምድም ከጨረስን በሁዋላ ቀጣዩ ተልዕኮአችንን የምንፈፅመው ከባህር ማዶ እንደሚሆን ጭምጭምታ ተናፍሶ ነበር፡፡

ይሁንና በዛ ምሽት የተሰጠን የልምምድ ተልዕኮ በሽሽት ላይ ያለን አንድ ሰላይ በጀልባ አሳፍረን ማስመለጥ ነበር፡፡ ከሰላዩ ጋር የምንገናኝበት ቦታ ከማረፊያ በታችና በጎምት ከግማሽ ማይል ርቀት ላይ የሚገኝ ቢሆንም ከዛ አንስቶ እስከ ጀልባዋ ያለው ርቀትም ደግሞ እንደ ማይል አይሞላም፡፡ የሆነ ሆኖ ተልእኮውን ለመወጣት እስራ ሁለት ሰዓታት ይተሩናል፡፡ የምንገናኝበት ስፍራም ሰላዩን በተባለው ሰዓት ካላገኘነው ጥለነው መሄድ እማራጫችን ይሆናል ማለት ነው፡፡ አማራጫችን ያ ከሆነ ታዲያ ወታደር በሄደበት አይመለስምና መናፈሻውን አቋራጭ መንገድ ልናደርገው አስበናል፡፡ «አለን» እኛንና መንገዱን በካርታው መሠረት ፈልጎ ለማግኘት አምስት ደቂቃ ፈጅቶበታል፡፡ ቀድመው የተደረጉ የቅኝት ፎቶግራፎችና የሳተላይት ምስሎች አካባቢውን መቃኘት አስችለውታል፡፡ በዚህም የጎላ ችግር እንዳይገጥመን ምክንያት ሆኖልናል፡፡ «አለን» ሰላዩን ከምናገኝበት ስፍራ ለመድረስ ከሰዓት ያነሰ ጊዜ እንደሚወስድብን ገምቷል፡፡ እኛ ግን ለጥንቃቄ ይጠቅመናል በሚል ፈጥነን ወደ ቦታው ሄደን እዛ ሰላዩን መጠበቅ እንደሚሻል ተስማምተናል፡፡

በርግጥም ጉዞውን በጊዜው መጀመራችን እድለኞች ያሰኘናል፡፡ በደኑ ውስጥ አስር ያርድ ዘልቀን ከገባን በሁዋላ መንገዳችን ላይ የእሾህ፣ የአሜኬላና የበረሐ ቁጥቋጦች ተጋርጠውብን ስለነበር ለክፋም ለደጉም ይጠቅመናል ብለን የያዝነው ቆንጨራም እዚሁ ላይ ቦታውን አገኘ፡፡ «አለን» ቆንጨራውን በመጠቀም መንገዳችንን ማፅዳት ጀመረ፡፡ ይሁንና ከግማሽ ሰዓት በኋላም እጆቹ በመዛሉ የማፅዳት ስራውን መቀጠል ከማይችልበት ደረጃ በመድረሳቸው «ኤሪክ» ቆንጨራውን ተቀብሎ ማፅዳቱን ቀጠለ፡፡ ለቀጣዮቹ ሁለት ሰዓታትም መንገዳችንን የማፅዳቱን ሥራ ተራበተራ ተቀባበልነው፡፡ ግና በአንድ ሰዓት ውስጥ ከመገናኛ ቦታ መድረስ የማይቻል ሆነብን፡፡

ጉዞው አድካሚና አሰልቺ ስለነበር ተዝለፍልፈን ከመሬት ተዘረርን፡፡ ግና ጨለማውን አሻግረን ከፊታችን ገላጣ መሬት መኖሩን ማየታችን ደግሞ የብርታት ምንጫችን ሆኖን ነበር፡፡ ከአስር ደቂቃ በሁዋላ «አለን» ሁላችንንም ከተዘረርንበት ለማንሳት ድጋፍ መሆን ነበረበት ፒተርም የጉዞአችን መሪ ሆኖ ከፊታችን በሚራመድበት ወቅትም ከፊት የሽቦ አጥር ይኖር እንደሆን በማለት በአይበሉባው እየዳኸና በሆዱ እየተሳበ በቀስታ ከጭንቅላቱ በላይ ያነሳው ነበር፡፡

ጉዞአችን በህይወቴ ከገጠመኝ አረንቋዎች ሁሉ ከርፋታም ከሆነው አረንቋ እስኪደርስ ድረስ ምንም እንኳን እሳራችንን ያየን ቢሆንም አረንቋው ግን ከነከርፋቱ፣ ባፋ የሚጠላልፍ የሚያስጥም እሜካላ የበዛበት በመሆኑና ከስፋቱና ጥልቀቱም የተነሳም



t.me/OLDBOOKSPDF

ዙሪያውን ዞረን ማለፍ የማይታሰብ ሆኖብን ነበር፡፡ ይሁንና ልናቋርጠው ወሰንን፡፡ አረንቋውን ስናቋርጥ መንገዳችንን እንዳንስት ፈራን፡፡ «አለን» የያዝነውን ኮምፓስ ተመለከተ፡፡ የኮምፓሱ ጠቋሚ ዘንግ ካረንቋው ሲላኛው ጫፍ ካለው አንድ ዛፍ አቅጣጫውን መቀሰሩንም አየን፡፡ ያንን አቅጣጫ ተከትሎ እግሩን ከአረንቋው ዘፈቀ፡፡ እኛም እስከእንገታችን በከርፋታው አረንቋ ተዘፍቀን ተከተልነው ግዳጅ ነውና፡፡

ከአረንቋው ሲላኛ ጫፍ እንደደረስን አንድ አስደሳች ሐሳብ ወደ አእምሮዬ ሰርጾ ገባ፡፡ ያም እኛን ለመከተል ሲል ይህንን ውሃ የሚያቋርጥ ቂል የለም የሚል ዕሳቤ ነበር፡፡ ሊደሉን የሚያሳድዱን ሰዎች ካሉ ደግሞ የሚመጡት ከፊት ለፊት ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከውሃው እንደወጣን ከመሬት ተዘረርን እቮህማቃቹ ሳሮች አድምተውናል፤ ለተጣዮቹ 15 ደቂቃዎች ዕረፍት መውሰድ እንደሚሻል አሰጠናል፡፡ ዕኩዕ ሌሊቱን ካጋመስነው በኋላ ዙሪያ ገቡን በብዙ ትላልቅ ቋጥኞች ከተከበበ አንድ አነስተኛ ኮረብታ ደረስን፡፡ ፒተር፣ ኮርት ኤሪክና እኔ እዛ ስንቀር አለን ሰላዩን ወዳለንበት ለማምጣት ሄደ ካደጋ ስለመራቃችን እረግጠኞች አልነበርንም፡፡ ምክንያቱም ድንገተኛ ጥቃት የሚጠብቀን ከሆነ ሁላችንም ለአደጋ እራሳችንን አጋልጠን ነበርና፡፡

በ0330 ሰዓት አለን ከሰላዩ ጋር ይመጣል ብለን ወዳሰብንበት አቅጣጫ መጀመያ ወደ ምስራቅ ለጥቆም ወደ ሰሜን ተጓዝን፡፡ መንገዱ ለመኪና ምቹ ከሆነበት ስፍራ እንደደረስን ኤሪክ እና ኮርት አለን ይመጣበታል ብለው ወደሰቡበት ጠባብ ሸለቆ ሲገቡ እኔና ፒተርም ሸለቆውን ይዘው የተከተለን ሰው መኖሩንና አለመኖሩን ለማረጋገጥ ከኮረብታዎቹ ላይ ወጣን፡፡

ከአንድ ሰዓት በኋላ አንድ ለጥቆም ሌላ የሚወሳከፍ ሰው ኮቴ ከቅርብ ርቀት ከሸለቆው ውስጥ ሲመጣ ሰማሁ፡፡ ሰላዩ ሀመምተኛ አሊያም እጅግ ወፍራም መሆኑን የሚገልፅልን ሰው እንዳልነበረ እስታወስኩ ሸለቆውን ወርደን እንደ፷ም እጅሬን ይዘን ሌላ ጊዜም በየተራ እየተሸከምነው ለ10 ደቂቃዎች ተጓዝን፡፡ ከኮረኮንቹ መንገድ በደረስንበት ቅፅበትም ምንም እንኳን የእፎይታ ስሜት ቢሰማኝም የሌቱን ሰዓታት ከኢሸርሰት ተራራ ሞት ቀጠና ያሳለፍኩ ያህል ሆኖ ተሰማኝ፡፡

አሁን ለንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተቃርበናል፡፡ ጎህ መቅደድም ጀምሯል አሁን አሁንስ ግዳጃችንን ለመፈፀም ተቃርበናል የሆነው ሆኖ ግን ጀልባዋን ማግኘት ይኖርብናል ጀልባ መቆሚያው ቦታ ላይ ጀልባው መኖሩን ለማረጋገጥ አለን ቀድሞን ሄደ መንገዱ አቅራቢያ ካለ አንድ ቁጥቋጦ ራሳችንን ደብቀን እያደባን እያለ አንድ የመኪና በር በኃይል ሲዘጋ ሰማን፡፡ ለጥቆም ሌላ በር ሲዘጋ አዳመጥን፡፡ ወዲያውም ካለንበት መቶ እርምጃ እርቀት ላይ የመኪና ሞተር የማጓራት ድምጽ ሰማን፡፡

ኤሪክ እና እኔ በሰላዩ ጎንና ጎን ሆነን እየጎተትነው መንገዱን ተሻገርን አሁን የመኪናው ሞተር ድምፅ ጎላ ብሎ ተሰማን፡፡ መኪናውም ወደ እኛ አቅጣጫ በፍጥነት ሲከንፍ ተመለከትን፡፡ የፊት መብራቶቹ ከመንገዱ ጠርዝ ካሉት ቁጥቋጦዎች እንዳረፈ በቁጥቋጦዎቹ ተከልለን ከውሃ ውስጥ ተዘፈቅን፡፡ ቀጥሎም ግራ ያጋባን ክስተት ተከሰተ፡፡ አካባቢው በማስጠንቀቂያ ደውሎች፣ ጩኸቶችና የተኩስ እሩምታዎች እንደካፊያ ዝናብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተርከፈከፉ ሰሚተቻችንም ተደበላለቁብን፡፡ የእጅቦንብ ወደ እኛ አቅጣጫ ውሃ ውስጥ ፈነዳ፡፡ የንበ ጉዳት የማያደርስ ብርሃን የሚፈጥር የንብ መሆኑን ባውቅም ቅሉ በእውነታው ላይ የነበረኝ እምነት እየተሸረሸረ ነበር፡፡

ብዙም ሳይቆይ አንድ የስተን ሰራሽ አሳ ማጥመጃ ጀልባ ጭለማውን ጥሶ ብቅ አለች፡፡ ከጀልባዋ ፊተኛ ክፍል አለን ቆሟል፡፡ አሁን ሰማይና ምድር እየተላተሙ በመሂዳቸው ያለ ችግር ከወደ ዳርቻው ልንታይ እንችላለን፡፡ አውቶማቲክ ጠመንጃ ተኩስ ከየአቅጣጫው መሰማት ተጀመረ፡፡ ጀልባዋም ባህሩ ዳር የበተሉትን ቁጢማዎች ተገን አድርጋ ወደ ዳርቻው ቀረበች፡፡ ሰላዩ ፒተር እና እኔን እየጎተተ ውስጥ ለውስጥ ወደ ጀልባው አቅጣጫ ተጓዘ፡፡ ጀልባዋ ጋር እንደደረስንም ወደ ጀልባዋ ተንጠልጥለን እንሳፈር ዘንድ አለን እንድ ገመድ ቢጤ አቀበለን፡፡

መጀመሪያ ሰላዩ ይግባ ሲልም እንባረቀብን ሰላዩንም ባለጀልባውና አለን ጎትተው ከጀልባዋ አሳፈሩት፡፡ እኔና ፒተርም በጎን በኩል ተንጠላጥለን ከጀልባዋ ተሳፈርን፡፡ ኢሪክና ኮርት ግን በአካባቢው አይታዩም ባለጀልባውም የጀልባዋን አፍንጫ አዙር ወደ ሚፈልገው አቅጣጫ አከነፋት ለነገሩ የፈለገውን አግኝቶአል፡፡

☼☼☼

በወርሃ ሚያዚያ የአንድ ልማታዊ ባለሀብት የእርሻ ማሳ በሚመስል የCIA ዋነኛ ማሰልጠኛ ገብተን ስልጠና መውሰድ ጀምረናል በዚያም የሰውን ልጅ እንደቅጠል የሚያረግፉቸውን አደገኛ መሳሪያዎች ፈታትቶ የመገጣጠም ልምምድ አድርገናል፡፡ እንደ ኤም-16 ወይም ኤኬ-47 ወይም ስተርሊንግ መትረየስን ፈታትቶ መገጣጠምን ካወቅን በኋላ ለኢላማ ተኩስ ወደ መስክ ይዘነው እንወጣ ነበር፡፡ ይሁንና የልምምዱ መቋጫ ያ አልነበረም፡፡ የተጠቀምንበትን ጠመንጃ ፈታተን ከጥቅም ውጭ እናደርገው ነበር፡፡ ከመሳሪያው ጋር ያለን ትውውቅ መጥለቁን ለመፈተሽ ስንልም በምሽት ሳይቀር ከሚሽከረከር መኪና ላይ ሆነን ከርቀት ያለን ኢላማን ለመምታት እንሞክር ነበር፡፡ በየጊዜው ለ40 ደቂቃ የምናረገውን የሰውነት እንቅስቃሴ ተከትሎ በልዩ ልዩ ጦር መሳሪያዎች ልምምድ እናደርጋለን፡፡ ያም በገሀዱ ዓለም ሲፈጥር የሚችልን የጦር ድንጋጤና መረበሽን ሊቀንስልን እንደሚችል እናምናለን፡፡

በቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታትም የኮምፓስ አጠቃቀም ትምህርት ወሰድናል በዚሆ ሁሉም ሰው ቁጥር ከተሰጠፈበት ዘንግ ፊት ይቆማል፡፡ ከዚያም ዘንጉን አልፎ ካለው ደ ከገባ በኋላ ኮምፓሱን በመጠቀም ጉዞውን ይቀጥላል የጉዞው አላማም ከደኑ በስተጀር ከተተከሉትና ተመሳሳይ ቁጥር ከተሰጠፈባቸው ዘንጎች መድረስ ነበር፡፡ ነገሩን ቀን ተ በሩጫ ከተካንነው በኋላ ማታ ማታ ደግሞ በፈጣን እርምጃ ደግመን እንፈፅመው ነበር ቀን ያቋረጥነውን አረንቋም እንዲሁም በምሽት እንድናቋርጠው እንገደድ ነበር፡፡ ቅደ ተከተሉን መጀመሪያ በብርሃን ከዚያም በጨለማ ልምምዱን እንድንፈፅም ስልጠናው ፡ ይለን ነበር፡፡

ሦስት ተከታታይ ሳምንታትን የሀላይ ልምምድ በማድረግ አሳለፍን በመጨረ የጥፋት ልምምዶችን ለመፈፀም ወደ ደቡባዊ ካሮሊና ተዛወርን፡፡ ለሁለት ቀናትም የቦ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጫፍ እንቃቀል አጠናን ይኸውም በእንቃቀሉ ጊዜ ከፍ አርገን ይዘን ከነቀልነው እጃችንን ሊገንጣጥለው እንደሚችል አሳውቆናል፡፡ የቦንቡ ጫፍ እንቃቀል ከገባን በኋላ አንድ ምሽት በተግባር ተለማመድነው፡፡ ለጥቆም ነገሮችን በቦምብ ማጋየት ጀመርን ከነዚህም ውስጥ መኪናች፣ አውቶብሶች፣ በናፍጣ የሚሰሩ ጀነሬተሮች ነዳጅ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች፣ እና አጥሮች ይገኙበታል፡፡ አንድ የተማሪዎች ሰርቪስ የሆነን አውቶብስ ሃያ ፓውንድ ክብደት ባለው አሜሪካ ሰራሽ ሲ-4 ቦምብ አጋይተን ደብዛውን አጥፍተናል፡፡ ለንፅፅር ለንልም ቼክ ሴሚቲክስ የተባለውን ፈንጂ እና ሌሎች የባህር ማዶ ፕላስቲክ ፈንጂዎች በተግባራዊ ልምምዳችን ተጠቅመንባቸዋል፡፡

ማንም ቢሆን ቅኝቶቹን በገሃዱ ዓለም ማየት አይፈልግም፡፡ የኛው ግን ለየት ይላል፡፡ ሦስት ከረጢት ሙሉ የነዳጅና ማዳበሪያ ውህድ አንድን አውቶብስ ለማጋየት ተጠቅመናል፡፡ ይኸው ኤ.ኤን.ኤፍ.ኦ የተሰኘ ውህድ የሚያደርሰው ጉዳት ሲ-4 ፈንጂ ከሚያደርሰው የላቀ ነው፡፡ እናም አውቶብሱ የቀረለት ነገር ቢኖር በፍንዳታው ወቅት በሙቶዎች የሚቆጠሩ ያርዶች ርቀት ላይ ተስፈንጥሮ ያረፈው ሻንሲው ብቻ ነበር፡፡ ሚታይል ናይትሬት ስለተባለ የፈንጂ ውህድም ትምህርት ወስደናል፡፡ አንድ ሰው የዚህን ፈንጂ ውህድ ጠብታ በመዶሻ ቢመታው ያለማጋነን መዶሻው ብትንትኑ ይወጣል ይህን ደግሞ በሙያው የተካኑ ብቻ ይበልጥ ይረዱታል ብዬ እስባለሁ ኢ.ሴል ስለተባለ በሰዓት የሚፈነዳ የቦምብ ትምህርትም ወስደናል ፀረ አውሮፕላን ቦምቦችን በከንደምና አልሙኒየም ጥቅሎች ይዘን እደምን ጥቅም ላይ ልናውላቸው እንደምንችል ተምረናል፡፡ አንድን ሽጉጥ ከአንድ ኢፖክሲ እና ግራፋይት ውህድ ውስጥ ጨምሮ እንደምን በአውሮፕላን ማዘዋወር እንደሚቻል ግንዛቤ ጨብጠናል፡፡ በትምህርቱ ፍፃሜም ከፍተኛ የአሸባሪነት ክህሎት ተክነናል ማለት ይቻላል፡፡

አሪዞና ውስጥ የበረሃና ተራራ ልምምድ አርገናል፡፡ ልምምዱ ከኮምፓስ ትምህርቱ ጋር የሚያመሳስለው ብዙ ባህሪያት ነበሩት፡፡ ከነዚህም በምሽት መቃኘትንና ጦር መግሪያ መጠቀም ይጠቀሳሉ፡፡ ልዩነታቸውም በዚህኛው ልምምድ ወቅት አንድን መርዘኛ ዕባብ ሜፉ ሹል በሆነ ዘንግ ተጠቅመን ማጥመድና እንዴት አብስለን መመገብ እንዳለብን ነበር፡፡ ከሁለት ሳምንታት በኋላም ሄሊኮፕተር እንደምን ማብረር እንደሚቻልና አንድን አውሮፕላን አስፒን ውስጥ ካለው ጓሮዬ በምታክል ስንዝር መሬት ላይ እንዴት አሳርፈን ማስነሳት እንደምንችል ተምረናል፡፡ ካርታ ላይ ያሉት ምልክቶችና ምድር ላይ ያሉ ምልክቶች ፈፅሞ አይመሳሰሉም፡፡ ነገሩ የከፋ የሚሆነው ደግሞ እየሩ ዳመናማ ውሽንፍር በሚሆንበት ጊዜ ነው ከዚህ በኋላ የሁለት ሳምንታት ቆይታችንን አትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ ከሚንሳፈፉ ጀልባዎች አርገናል፡፡ ይህም በህይወት ውስጥ ጥቃቅን ሊባሉ የሚችሉ በምሽት የሰጠሙ ባህር ሰርጓጅ መርከብ ያለበትን እንደመጠቆም ያሉ ክህሎቶችን ተምረናል፡፡

ለአስር ቀናት ያህል ግዳጅ ተጥሎብን ከባልደርቦቼ ጋር ከፍሎሪዳ ዕልፍ ደሴቶች አሳለፍን ደሴቲቷ በአስቸጋሪ አረንቋና ደን የተሞላች ብትሆንም ለአራት ቀናት ያህል በአረንቋው ውስጥ ስንዘዋወር አረንቋው ከጫማችን ይገባ ስለነበር የአረንቋው ክሎሮፊል ይዘት ቆዳችንን ወደ አረንጓዴነት ለውጦት ነበር፡፡ ሌሎች አራት ቀናትን ያሳለፍነው ደግሞ ስራስሮችን በመመገብ ስለነበር ልብሶቻችንን ከጥቅም ውጭ አድርጎብን ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀጣዩ ልምምዳችን ባዶ ከሆነችው ከሜክሲኮ ባህር ሰላጤ በአንድ ማይል ርቀት ላይ ከምትገኘው ከዚህች ደሴት የተደበቀን ጦር መሣሪያ ቆፍሮ ማውጣት ነበር፡፡ ሁኔታው ያህያዋን ሙታን ሌት ተራፊዎች የሆንን አስመስሎናል፡፡ የመሳሪያው ሳጥን የተቀባውን ከምትገኘው ከዚህች ደሴት የተደበቀን ጦር መሣሪያ ቆፍሮ ማውጣት ነበር፡፡ የመሳሪያው ሳጥን የተቀባውን ያህያዋን ሙታን ሌት ተራፊዎች የሆንን አስመስሎናል፡፡ ያለውን ኤም-16 ጠመንጃ አወጣነው፡፡ መከላከያ ግራሶ ከጠረግን በኋላ ውስጡ ያለውን ኤም-16 ጠመንጃ አወጣነው፡፡ ወዲያውኑም እንዷት ፈጣን ጀልባ ወደ ደሴቲቱ ስትቃረብ ተመለከትን ባለጀልባው ጀልባዋን ከአሸዋማው የውሃ ዳርቻ አስካፈናጠጣት ድረስ አላየንም ነበር፡፡ እንዳየንም የጀልባዋን አፍንጫ አዙር ወደ ባህሩ በፍጥነት አከነፋት፡፡ እንደዕውነቱ ከሆነ ለዘመቻ የተሰማራሁበት ግዳጂ የተደበቀ መሳሪያን ቆፍሮ የማውጣት ግዳጅ መሆኑን አላውቅም ነበር፡፡ ይሁንና አሜሪካ ከፍታው በነበረው ፀረ-ዕፅ ዘመቻ የበኩሌን ድርሻ ተወጥቻለሁ ለማለት እችላለሁ፡፡

☼☼☼

ወታደራዊ ስልጠናውን እየወሰድኩ በነበረበት ወቅትም የአንድ መረጃ ሰራተኛ ስራ የተደበቀ መሣሪያን ቆፍሮ ማውጣት ብቻ አለመሆኑን ተረድቼአለሁ፡፡ ስልጠናው በሁለተኛው አለም ጦርነት በትክክለኛው የውጊያ አውድ ተካፋይ ከነበረው አ.ኤስ.ኤስ ወደ ዲ.ኦ የተሸጋገረ ስልጠና ነው፡፡ እርግጥ ነው የዲ.ኦ ስራ ሰላዮችን ማሰማራት እንጂ በጦር ግንባር የመጀመሪያውን መከላከያ መስመር ማበጀት አይደለም፡፡ እስከማውቀው ድረስ ዲ.ኦ ስልጠናውን ይሰጥ የነበረው ቡድናዊ አሰራርን ከአዲሶቹ መረጃ ሰራተኞቹ አዕምሮ ለማስረፅ ነው፡፡ ይህም የምንሰለጥነው ከጠባቦቹ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሰራተኞች ጋር ለመስራት እንዳልሆነ ይገልፃል፡፡

ይህ ገለፃ የዋሆቹን ዋሽንግተናውያን ክብር የሚነካ እንዳይሆን እሰጋለሁ፡፡ ከነሱ ለጥቀው ያሉት መረጃ ሰራተኞችም የሀገራትን ሚስጢራት የሚያራቁቱ ቀበኞች መሆናቸውን መናገር እወዳለሁ፡፡ በፌደራል መንግስቱ ከተቋቋሙት ተቋማት ሁሉ የውጭ ህግጋትን የሚጥሰው ዲ.ኦ. ብቻ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ህግ-ህግ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ዲ.ኦ የመረጃ ሰራተኞቹ እንዲፈፅሙላት የሚሻው ትልቁ ነገር ከሆነ አንድ የምስራቅ አውሮፓ መናገሻ ከተማ ከባላንጣዎቹ በተቃራኒ ሆነው ፈንጂ እንዲያፈነዱና ቃታ እንዲስቡ ነው፡፡ እንደ ላንግሌንና ዋሽንግተን ውስጥ ባሉ የአስተዳደር ሰዎቹ ላይ የፖለቲካ እርምት በጥልቀት ከመወሰዱ በፊት መሣሪያዎችን ወደ ውጭ መላኩ በCIA ላይ ችግር እንደሚፈጥር ባለስልጣናቱ አለማወቃቸው ራስምታት ሆኖባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል በኢራን፣ ቺሊ እና ኮንጎ CIA በመንግስት ግልበጣ ሴራ ውስጥ ስለመሳተፏ ሀገራቱ ይከሳሉ፡ ከዚህም አንፃር የተሻለ የሚሆነው በምስጢር ስራዎቹን ማካሄድና ግብ ግብ መግጠሙን ለሌሎች መተው ይሆናል በጥይት መታኮሱ ጥሩ ዜናን መስማት እንደማያስችል ተቋሙ ማወቅ ይኖርበታል፡፡

ሌላው ከዲ.ኦ ቆይታዬ የተገነዘብኩት ነገር ዲ.ኦ እንደሌሎች የሙያተኛ ወንጀለኛ ድርጅቶች ሁሉ የሚጠቀምባቸው የሚስጥር ኮዶች ያሉት መሆኑን ነው፡፡ ሁሉም ዲ.ኦ ውስጥ ያሉት ከሽንት ቤት ወረቀት ማዘገር እስከ ግብኘ ወረቀቶች ያሉ ወረቀቶች በልዩ ልዩ ዶክመንቶች ተከፋፍለው ይያዛሉ፡፡ ድርጅቱ የሚፈፅማቸው ሁሉም አይነት ግንኙነቶች ምስጢር ይደረጋሉ፡፡ የመረጃ ሰራተኞቹ እውነተኛ ስማቸውን አይጠቀሙም



t.me/OLDBOOKSPDF

በዛ ፋንታ ለሁሉም ምስጢራዊ ስም ይሰጣቸዋል ሲላው ቀርቶ ቦታዎች ሳይቀሩ ሊላ ስም ይወጣላቸዋል፡፡ CIA ሀሰተኛ የቦታ ስሞችን ተጠቅሞ (ልማታዊ የዕርሻ መስክ) የተሰኘ ማሰልጠኛውን እንደምን ካርታው ላይ እንዳስፈረው ላይ በጣም ደንግጫለሁ ያም CIA በሁለት ትይዩ በሆኑ ዓለማት እንዳለ እርጌ እንድቆጥረው አርጎኛል፡፡

ኮንፒተሮች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ መረጃዎችን በአህዛዊ መልኩ መያዝ ጉዳት እንዳለው CIA ወዲያውኑ ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም እጅግ አስፈላጊ መረጃዎችን በጨርቅ ሪባኖች ላይ በታይፕ እንዲተየቡ ማድረጉን ቀጥሎበታል፡፡ መረጃዎቹ በእጅ ፅሁፍ ሳይቀር እንዲገለበጡ ያደርጋል ዝነኞቹ የዲ.አ ባለ ሰማያዊ መስመር የመረጃ ሪፖርቶች መሰሉን ስም ያገኙት ወረቀቱ ላይ በፈዛዛ ቀለም ወደጎን ከተሰመረው ሰማያዊ መስመር ነው በመልዕክተኛም ወደ ዋሽንግተን ይላካሉ፡፡ የሚመለከተው ባለስልጣንም ከመልዕክተኛው ወረቀቱን ተቀብሎ ሲያነብ መልዕክተኛው ቆሞ ይመለከተዋል፡፡ ባለስልጣኑም ንባቡን እንደጨረሰም ወረቀቱን ለመልዕክተኛው ያቀብለዋል፡፡ መልዕክተኛውም ወደ ተላከበት ወረቀቱን ይዞ ይመለሳል፡፡

የምስጢራዊው ዓለም አካል የሆንኩት የመጀመሪያ ስልጠናዬን ለመውሰድ ዋሽንግተን ከመግባቴ በፊት ነው፡፡ ሳንፍራንሲስኮን ለመልቀቅ በመዘጋጀት ላይ እያለሁ ጂም ስኮት ደውሎ አውሮፕላን ማረፊያው የሚጠብቀኝ ሰው እንደሌለ ነገረኝ «እየሀ ያን ማድረጉ አደጋ አለው» ሲልም ተናገረ «ደህንነቱ አስተማማኝ ከሆነ ቤት ከስራው ጋር ትውውቅ በምታረግበት ሁለት ሳምንታት ታርፋለህ፡፡»

«ለምን ሆቴል አይሆንም»

«ያማ! ቢዛ አደጋ አለው»

ወዲያውኑ ሐሳቡን ከአእምሮዬ አወጣሁት፡፡ በራሴው አገር ደህንነቱ አስተማማኝ በሆነ ቤት እንድኖር ያረገኝን ስራ መጀመሩ አስደሳች ነገር ሆኖ ታየኝ፡፡

ከዋሽንግተን ብሔራዊ አየር ማረፊያ ታክሲ ይዤ የቤይሌይ መስቀልያ መንገዶች ወዳሉበት ወደ ሰጠኝ አድራሻ አመራሁ፡፡ ከመስቀልያዎቹ መንገዶች እንደደረስኩም ከአንድ አዲስ የአፓርትመንት ህንፃ ገባሁ፡፡ ፀጉሩ ግራጫማ የሆነ ሌላ ምልምል አስቀድሞ ከአፓርትመንቱ መኖር መጀመሩንም አወቅኩ፡፡ ሀንክ መሆኑን ብቻ ገለፆ ተዋወቀኝ እኔም መልሼ እውነተኛ ስሙን ጠየቅኩት፡፡ አዝናለሁ፡፡ ልነግርህ አልችልም ስኮት አትንገረው ብሎኛል፡፡ አለኝ

በማግስቱ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ አንድ የደስ ደስ ያለው ሰው አያቴን መሆን የሚችሉ አንድ ሴት አስከትሎ መጣ፡፡ ሁለቱ ሰዎች የመጡት ሽፋን ሰጭ ከተሰኘው የዲ.አ ስራ ክፍል ነበር፡፡ ይህ የስራ ክፍል የሐሰተኛ መታወቂያዎችን እውነተኛ አስመስሎ ይሰራል፡፡ የሐሰት ስልክ መስመሮችን ይዘረጋል፡፡ በአለም ዙሪያ ተበትነው ያሉ የCIA መረጃ ሠራተኞችን ትክክለኛ ማንነት ለመደበቅ ከሌሎች መንግስታዊ ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሴትየዋ ሃንክ እና እኔን መታወቂያችንን እንድናሳያት ጠየቀችን የመንጃ ፈቃዶቻችንን፣ የዱቤ ካርዶቻችንንና የክለብ አባልነት መታወቂያዎቻችን ጨምሮ ስማችን የሰፈሩባቸውን ወረቀቶች ሁሉ ተረከበችን፡፡

«ከእንግዲህ እነዚህ ወረቀቶች አያስፈልጋችሁም በማለት በሁለት የተለያዩ ፖስታዎች ከተተቻቸው በፖስታዎቹ ላይም የመጀመሪያ ስሞቻችንን አስፍራ አሸገቻቸው፡፡

ስለማንነቱ ማረጋገጫ ሳይኖረኝ የምኖረውን ኑሮን እያሰብኩት እያለ ሰውየው ለኔና ሃንክ ፎቶግራፎቻችን የተለጠፉባቸው መታወቂያ ወረቀቶች ሰጠን መታወቂያዎቻችንም ሲቪል የውትድርና ሰራተኛ መሆናችንን ይገልፃሉ፡፡ የራሴን መታወቂያ ትኩር ብዬ ተመለከትኩትና ከላዩ የተለጠፈው ምስል የራሴ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሆንኩ፡፡ ፎቶግራፉን ለተቋሙ ያስገባሁት ከማመልከቻ ወረቀቴ ጋር መሆኑን አሁን ትዝ አለኝ፡፡ መታወቂያው ላይ የተፃፈው ስም ግን ሮበርት ኤንጻኮት የሚል ነበር፡፡

«የሆነ ሰው ስህተት የሰራ ይመስለኛል፡፡» ስል መታወቂያውን ለሰውየው እየመለስኩለት ተናገርኩት፡፡ ሰውየውም በመገረም ተመለከተኝ፡፡ የሐሰት ስም እንደሚሰጡህ አልነገሩህም?»

የለም ማንም አልነገረኝም፡፡

ለጥቆም እኔና ሃንክ ከዚያች ቀን ጀምሮ ቢያንስ ከሃገር እስክንወጣ ድረስ በሃሰት ማንነት መኖር እንደምንጀምር አስረግጦ ነገረን፡፡ በጣት የሚቆጠሩ የCIA ኦፊሰሮች ብቻ ዕውነተኛ ስሞቻችንን እንደሚያውቁም አከለበት፡፡

«ቤተሰቦቼን የማገኛቸው እንዴት ነው?» ስል ጠየቅኩት፡፡

ፈገግ ብሎ የዋሽንግተን ዲሲ ፖስታ ሳጥን ቁጥር በቢጫ ቀለም የተተየበበትን ካርድ አቀበለኝ፡፡ በሳምንት አንዴ ደብዳቤዎችህን እንቀበልልሃለን መፃፍ የምትፈልጋቸውን ደብዳቤዎችህን ሁሉ መፃፍ ትችላለህ ሆኖም ከዚህም ሆነ ከሌላ CIA ከሚሰጥህ መጠለያ ሆነህ ወደነሱ መደወል አትችልም፡፡ እነሱም ወዳንተ መደወል አይችሉም፡፡

አሁን አትደውል ከሚለው ህግ ጋር የተዋወቅኩ መሰለኝ ለጥቆም የአፓርታመንቱን ስልክ እንደማይሰራና መቋረጡንም ተረዳሁ፡፡

ጥንዶቹ የማዕከላዊ ሽፋን ሰጭ ሰራተኛ ከተቀረው አለም ያቆራረጡኝ መሰሎ ተሰማኝ፡፡ የCIA ሽፋን ሁሌም ቢሆን የሚያፈናፍን አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ ታሪክ ትዝ ብሎኛልና ነገሩ ወዲህ ነው፡፡ በባህረ ሰላጤው ጦርነት ጊዜ ወደ ዋሽንግተን የተመለሰ አንድ መረጃ ሰራተኛ ሮዝሊን ከሚገኘው ቂስት ፓርክ ሆቴል ያረፉትን አረብ ሰልጣኞቹን በማሰብ ወደዛው ያቀናል፡፡ ከተማዋ ውስጥ አሳልፈውት በነበረው በዛ የመጀመሪያ ለሊታቸው ከአረቦቹ አንዱ ብቸኝነት ይሰማውና ከዚያ በፊት አሜሪካ መጥቶ እያውቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለነበር የእንግሊዝኛ ችሎታውም ብዙም ስላልነበር የስልክ ማውጫ ደብተሩን ገልጾ የአስቸኳይ እደጋ ጥሪ ቁጥር የሆነውን 911 ይደውላል፡፡ የስልክ ጥሪውን ለተቀበለው ሰውም ሴት እንደሚፈልግ ይነግረዋል ፈጣኑ ስልክ ተቀባይም የሚፈልጋት ሴት እስክትመጣ ድረስ ከሆቴሉ ፊት ለፊት ቆሞ እንዲጠብቅ ይነግረዋል ዓረቡም እንደተባለው ከሆቴሉ ሲወጣ ፓርክ ውስጥ የቆመች ሴት ያያል፡፡ ያላወቀው ነገር ግን አምስት የአርሊንግተን ፖሊሶች ቁጥቋጦ ውስጥ መደበቃቸውን ነበር፡፡

በመጨረሻም አረቡ እጅ ከፍንጅ እንደተያዘ ወደሆቴሉ መልሰው ስለማንነቱ ሲጠይቁት ዋሽንግተን የመጣው በአሜሪካ መንግስት የሚሰጠውን ስልጠና ለመከታተል እንደሆነ ሲነግርለት ከሚችለው የመረጃ ሠራተኛ እንዲያገናኙት ለመናቸው፡፡ ለጥቆም አረቡ የተናገረው ትክክል መሆኑን የመረጃ ሰራተኛው አረጋገጠ፡፡ አረቡ ስህተት ሊፈፅም የቻለው ቋንቋ ባለመቻሉ መሆኑንም አስረዳ፡፡ በዚህም ፖሊስ ገጠመኙን ችላ እንደሚልለት ተስፋ አድርጎ ነበር፡፡ በምትኩ ግን ፖሊስ መረጃ ሰራተኛውን መታወቂያ ወረቀቱን እንዲያሳየው ስለጠየቀው የመረጃ ሠራተኛውም የማዕላዊ ሽፋን ሰጭ የሰጠውን የሀሰት መታወቂያ ያሳያል፡፡ መታወቂያውም ለአንደኛው ፖስስ አጠራጣሪ ይሆንበታል፡፡ ዝምታን CIA ከሚጠቀምባቸው ክዶች አንድ ስለነበር በዛ ሴትም ተጠቅሞበታል፡፡ የተቋሙን ስልክ የሚመልሰው ኦፕሬተርም የተገለፁለትን የስም አድራሻ ፈፅሞ እንደማያውቀው ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ፖሊሱ ሌላ ካቲና በማውጣት ላይ እያለ የመረጃ ሰራተኛው ሽፋኑን ጥሶ መውጣት ካለበት ይህ የተሻለ ጊዜ እንደሆነ አሰበ፡፡ .......ፖሊሱ ለባልደረባው አንድ የስልክ ጥሪ ወደ CIA እንዲያደርግ ፈቀደለት፡፡

«የ CIA ሰራተኞችን ቅጥር ማረጋገጥ አንችልም፡፡» የሚል ምላሽ የ CIA'ው ደህንነት ኃላፊ ለፖሊሱ ምላሽ ሰጠው፡፡ በምላሹ የተናደደውና ቀድሞ የባህር ኃይል ባልደረባ የነበረው መረጃ ሰራተኛ ስልኩን ከፖሊሱ ነጥቆ «አንተ የውሻ ልጅ የተረገመ ኮምፒተርህ ላይ ስሜን የማትፈልገው ከሆነ ከእስር እንደተፈታሁ አንገትህን ነው የምቀነጥስልህ ሲል እንባረቀበት፡፡

ሆኖም ጥቂት የስልክ ጥሪዎች ለችግሩ መፍትሄ አስገኙ፡፡ ብዙዎቹ መረጃ ሰራተኛ የሚሰጣቸውን ሽፋን በትክክለኛው ሰዓት አናገኝ ይሆን የሚል ስጋት አላቸው፡፡ አሜሪካ ውስጥ የሽፋኑ ምስጢር ተገለጠ ማለት ደግሞ አንድ ለሊት ዘብጥያ ማሳለፍ ሊሆን ይችላል፡፡ በባህር ማዶ ከሆነ ግን ትርጓሜው ከዚህ እጅግ የከፋ ነው የሚሆነው፡፡

የማዕከላዊ ሽፋን ሰራተኛ ሀንክንና እኔን ተሰናብተው ከሄዱ በኋላ ሁለት ጥቁር ሱፍ የለበሱ የደህንነት ቢሮ ሰዎች ወደ አፓርትመንታችን መጡ፡፡ እኔም የደህንነት ቢሮውን በቀጣይነት ለ21 ዓመታት ደህና አድርጌ ላውቀው ችያለሁ ቢሮው ውሸትን እንደመለያ ማሽን ለምርመራ ይጠቀማል፡፡ ከደህንነት ዕዳት ስራዎች እስከ ውስጥ ስልኮች መቆጣጠር ያሉትን ስራዎች ይፈፅማል፡፡ ላንግሌ ያሉት ደህንነታቸው አስተማማኝ የሆኑ ቤቶች ለሊት መዘጋታቸውን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም ቢሮው ሰው በላው የተባለ ልዩ ሰራተኛ አለው የዚህ ልዩ ሰራተኛ ስራም አደገኛ ሰዎችን ማስወገድ ነው፡፡ የማስወገድ ስራውንም ከፈፀመ በኋላ መርዶውን ለአለቆቹ ያረዳል ለጥቆም ሌሎች ሁለት የቢሮው ሰራተኞች ከተወገደው ሰራተኛ መኖሪያ በመዝለቅ ማንኛውንም መረጃ ያነፍንፋሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ኮምፒውተሩን ይመረምራሉ ዲስኩ ውስጥ ወይም ላይ ያስቀመጣቸውን ንብረቶች ሁሉ ይፈትሻሉ፡፡ ተያያዥነት የሌላቸውን የቤተሰብ ፎቶዎች ሳይቀር ይመረምራሉ፡፡ ከዛም የሚቹን ራሳ እንደ የደህንነት ቡድን ከቤቱ ያወጣውና ያስወግደዋል፡፡

የደህንነት ሰዎቹ አንድ ጫማ ከፍታ ያላቸው ፎርሞችን ከአታቺ ቦርሳቸው አውጥተው ለእና ለሃክ አደሉን, ፎርሞቹንም እንብበን እንድንፈርምባቸውም ጠየቁን የመጀመሪያው ምስጢራዊ ስምምነት ደሞዛችንን በየሁለት ሳምንቱ እንደሚከፍሉንና በምላሹም ያለ CIA ይሁንታ ምንም አይነት መፅሐፍ፣ መጣጥፍ፣ የፊልም ስክሪፕት፣ መጻፍ እንደማንችልና በቴሌቪዥን መታየት እንደሌለብን ይገልፃል፡፡ እውነት ነው ይህ ዘዴ የ CIA የመረጃውን አለም ሚስጥር ጠብቆ ለማቆየት ያስችላል ግና ህይወትህን ሁሉ ተቋሙ ውስጥ ካሳለፍክ በኋላ ግን መጻፍ ወይም መናገር ሊፈቀድልህ ይገባል፡፡

ሌላው የፈረምነው ውል ስራችንን የሚያደናቅፍ ስለሚሆን ለእናቶቻችን፣ ለሚስቶቻችን ለጓደኞቻችን ለማንም የ CIA ሰራተኛ መሆናችንን መናገር እንደሌለብን የሚገልፅ ውል ነበር፡፡ የምናውቀው ሰው CIA'ን በሮችን ዘልቀን ስንገባ ማየቱን ቢነግረን እንኳ ከ CIA ጋር ያለንን ግንኙነት ሽምጥጥ አርገን መካድ ይኖርብናል፡፡ የዲእ ባለስልጣናት ማንነታችሁን ፈጽሞ አታሳውቁ ሁሉን ነገር ሽምጥጣችሁ ካዱ ስለራሳቹህ ለራሳችሁ ጥብቅና ቁሙ የሚል መመሪያ የሰጡንን ተግባራዊ እንድናረገው ይሻሉ፡፡ይሁንና አንዳንድ የመረጃ ሰራተኞች መጀመሪያ ላይ ከሚስቶቻቸው ስራቸውን ቢደብቋቸውም ኋላ ግን አብዛኞቹ እንደሚነግሯቸው ማወቅ ችያለሁ፡፡

በሞገድ ማፈን፣ ሳተላይቶችን መጠቀም፣ ፎቶግራፍና በኒውክለር ቦምብ ዙሪያ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ሚስጥራዊ የመረጃ ቃላት ለማንም ትንፍሽ እንዳንል የሚያዝ ውልም ፈርመናል እንድ ምስጢራዊ ቃል የራሱ የሆነ የጥንቃቄ መመሪያ ያለው ከፍተኛ ምስጢራዊ የአፈታት ስርዓት አለው፡፡ አንድ ወቅት ላይ አንድ ስለ ከፍተኛ ምስጢራዊ ቃላት አፈታት የሚያትት ጽሑፍ ባነበብኩበት ወቅት «ሳቲሪያሲስ» የሚል ቃል ገጥሞኛል ምስጢራዊውን የቃላት መፍቻ በስራ ላይ ባለህበት ሁኔታ ማስታወሱ ለእኔ አስቸጋሪ ነበር ምክንያቱም ተመሳሳይ የሚመስሉ የቃሉ ፍቺዎች ብዙ ነበርና ስለዚህ በቀላሉ ለመረዳት ያዳግቱ ነበር «ሳቲሪያሲስ» ምን ማለት ነው ስልም እጠገቤ የነበሩትን የደህንነት ሰዎች ጠየቅኳቸው፡፡

ከሁለቱ የደህንነት ሰዎች አንደኛው ሆን ብሎ እኔን ሊያሳጣኝ በለሆሳስ 'ሳቲሪሰት' ማለት ከብዙ ሴቶች ጋር ግንኙነት መፈፀም የሚወድ ሴሰኛ ማለት ነው፡፡ እናም አንድ የመረጃ ሰራተኛ በዚህ መሰል ነገር ተጠምዶ ቢገኝ ቆለጦቹን ልንቆርጥለት እንደሚገባ ሕጉ ያዘናል» አለኝ፡፡ ነገሩ ሁሉ አስቂኝ ቢሆንም ወሲብ በአስተዳደር ላይ ላሉቱ ቱባ ባለስልጣኖች የራስ ምታት እንደሆነባቸው አውቃለሁ፡፡ CIA የመረጃ ሰራተኞቹ ወዳጅ ጠላት ሳይለዩ ካገኙት ጋር መዳራታቸውን አይቀበለውም ምክንያቱም ማንኛውም የውጭ ዜጋ ማጣራት እስኪካሄድበት ድረስ በጠላትነት ስለሚፈረጅ ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የ CIA' ሰራተኛ ከአንድ የውጭ ዜጋ ጋር የቅርብና የዘለቀ ጉድኝት ካለው ለአለቆቹ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ እዚህ ላይ ግን «የቅርብና የዘለቀ» ስለሚለው ሐረግ ፍቺ ማንም ርግጠኛ አለመሆኑ ለ CIA' አስቸጋሪ እንደሚሆንበት ግልፅ ነው፡፡ ትርጉሙ አንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

የፍቅር ሌሊት? ወይም ለፍቅር ጓደኛ ግጥም መፃፍ? የደህንነት ሰዎቹ የነገሩን ነገር አልነበረም፡፡ ከስምንት ዓመታት በኋላ ካርቱም ውስጥ እስታዬ የነበረ ሚልተን ቢየርደን ሲሔረት ዋጋ ያለው ፍቺ ሰጥቶኛል፡፡ እንደሚልተን አባባል «የቅርብና የዘለቀ» ጉድኝነት ማለት ከወዳጅህ አልጋ ስር ቀንድ ነብሳ ጫማ ማስቀመጥ እንደማለት ነው፡፡

በየስድስት ወራት CIA ባህር ማዶ ያሰማራቸውን የመረጃ ሰራተኞቹን ....... በተባለ ኮድ «የቅርብና የዘለቀ» ጉድኝነት እንዳላቸው ወይም እንደሌላቸው የሚገልጽ ሪፖርት ለአለቆቻቸው ያስተላልፋሉ ነገሩ ሲበዛ ውጥረት የሞላበት ነው፡፡ አንድ የደህንነት ሰው የምትመሳጠረውን «የቅርብና የዘለቀ» ጉድኝነትን ከተጠራጠረና ለብሔራዊ ደህንነት ስጋት ይሆናል ብሎ ካመነ ለሥራ ከተሰማራህበት ሐገር ወደ ዋሽንግተን ሊመልስህ ይችላል፡፡ በመስቀለኛ ጥያቄም እየጣደፉህም ምርመራ ያረጉብሃል ነገሩ እውነት ሆኖ ከተገኘም ለዓመታት በጥበቃ ስር ወደምትቆይበት እስቸጋሪ ስፍራ ትላካለህ፡፡ በሌላም በኩል አንድ የደህንነት ሰራተኛ ስለግንኙነትህ ሪፖርት ሳታደርግ ግንኙነት ማድረግህን ከደረሰበት ውጤቱ የከፋ ይሆናል፡፡

ከዚህ ጋር በተገናኘ ከሰማሁዋቸው ታሪኮች ሁሉ ያስገረመኝ ነገር ቢኖር ከእናቱና እህቱ ጋር ስለሚተኛ አንዱ የሂንዱ እማኝ የሆነ የመረጃ ሠራተኛ የሰማሁት ታሪክ ያልተለመደ ሆኖ ብኛል፡፡ ነገሩ ሊደረስበት የቻለው በማያቋርጥ መስቀለኛ ጥያቄዎች ምርመራ ከተካሄደበት በሁዋላ ነበር፡፡ ለግዳይ የተመደበው ጨካኝ ሰው ሊገለው በነበረበት ሁኔታ ሠራተኛው የመጀመሪያ ደረጃ መብቶቹ እንዲከበሩለት ጠየቀ፡፡ ነገሩ ከሀገዳውያን የጠደብ ከፍፍል ጋር የተያያዘ መሆኑን አስረዳ፡፡ ዋሽንግተን አካባቢ የራሱ መደብ አባል የሆነችን ሴት ማግኘት ባለመቻሉ ነገሩን መፈፀሙን ተናገረ፡፡ በመጨረሻም ነገሩ ወደ አጠቃላይ ካውንስል ቢሮ ቢመራም ሰራተኛው እንዲረሸን ተበይኖበታል፡፡ ሁኔታው አስገራሚ ቢሆንም መሰሎቹ ነገሮች CIA ምስጢራዊነቱን ለመጠበቅ ሲል የሚጨነቅባቸው ነገሮች ናቸው፡፡

ለሁለት ሳምንታት ያህል ከአንድ ደህንነቱ ከተጠበቀ ቪላ ቤት ውስጥ ልክ እንደ አንድ ባለስልጣን ጥበቃ እየተደረገልኝ ፎርሞች ላይ ፊርማዬን እንዳኖር ካረጉኝና የመምሪያው ኃላፊዎች ለመኖር ያህል ስለሚያደርጎቸው ጥንቃቄዎችና ጥረቶች ሳዳምጥ ከቆየሁ በኋላ የዘመቻ አፈጻፀም ትምህርት ለመቅሰም ወደ «ልማታዊ የእርሻ መስክ» ወደ ተሰኘው ማሰልጠኛ እንደምዛወር ስሰማ ደስታዬ ወሰን አልነበረውም፡፡ ምንም እንኳን ነገሩ ሁሉ ከአንድ እስር ቤት ወደሌላው የመሸጋገርን ያህል ቢሆንም ልዛወርበት ያለው ስፍራ የአንድ ከለብ ባህሪያሉት ከመሆኑም ባሻገር ዳግም ልምምድ ማድረግ የሚያስችለኝ ቦታ ነበርና

«ልማታዊ የዕርሻ መስኩ በእያሌ መጽሐፍ ብዙ የተባለለትና የተገለፀለት ከአየር ላይ በተወሰዱ የቴሌቪዥን ጥናታዊ ፊልሞች የታየ ቢሆንም ያለበትን ስፍራና የሽፋን ስሙን ከመናገር እንድቆጠብ CIA ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል በመሆኑም አሁን ለተደራሲያን መናገር የምችለው ነገር ቢኖር «የእርሻ መስኩ የሚገኘው ቨርጂኒያ ታይድዎተር ውስጥ ከ ....... እንደሆነ ነው፡፡ ይህ «የእርሻ መስክ» ጥብቅ የጦር ሰፈር መሆኑን ነው የሚገመተው እናም በፊተኛው በር ቀርበህ ዘቦቹን ብትጠይቃቸው ቢጫ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፓውዛቸውን እንቦግብገውብህ በሮቹን ከርችመው የሚሰጡህ ምላሽ የተከለለ የወታደር ሰፈር መሆኑን ነው፡፡ የውጭው በር ታልፎ ወደ ውስጥ ሲዘለቅ ደግሞ «የዕርሻ መስኩ» በከፊልም ቢሆን የአንድ ክለብ ገፅታን ይላበሳል፡፡ የቴኒስ ሜዳዎች ፣ የቤት ውስጥ መዋኛ ገንዳዎች፣ አሳ ማጥመጃ ጀልባዎች፣ እያሌ ቡና ቤቶችና መዝናኛዎች እንድን እንግዳ ለመቀበልና ያለ ከልካይ ለማስተናገድ ዝግጁዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎቹም የየራሳቸው መኝታ ክፍሎች አሉዋቸው፡፡ ባጠቃላይ ስፍራው የቅንጦት ሆቴል ዓይነት ባይሆንም ለባለአራት ኮከብነት የማያሳጣ ነበር፡፡

በሌላ ዕይታ የተመለከትነው እንደሆነ የዕርሻው መስክ አንድ አነስተኛ የገጠር ኮሌጅ ሊመስል ይችላል፡፡ ግና በርግጠኝነት እውነታው ይህ ሳይሆን ልዩና ስውር የማሰልጠኛ ቦታ መሆኑን ነው፡፡ ግቢው መግባታችን ከተረጋገጠ በኋላ ያን ዕለት ማታ ድል ያለ ድግስ ያለን መሆኑን ተገልፆልናል፡፡ ይህም የተዘጋጀው ማንነቱ ባልተገለፁልን አንድ የውጭ መንግሥት ነበር፡፡ ነገሩኝ የዛን አገር ስም አሁን ማስታወስ ባልችልም መናገሻ ከተማው ዊልተን መሆኑን መናገር እችላለሁ፡፡ አስተማሪዎቹ የአካባቢውን ባለስልጣናትን መስለው ሲታዩ ተማሪዎቹም አሜሪካውያን ጎብኚዎችን መስለው ተውነዋል፡፡ የኛ ስራ አገር ቤት መኖራችንን መሸሸግ ሲሆን አላማውም ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደምን መሳተፍ እንደምንችልና CIA መታወቅ የለባቸውም ያላቸውን ምስጢሮች መደበቅ እንዳለብን ማስተማር ነው፡፡

ከትወናው በኋላ ወደ አንድ አጭር ከርፋፋና ራስ በራ ወደሆነው መምህር ጋ አልኩ.......፡፡ ሁኔታው ላስተዋለው ከጥቂት አስርተ አመታት በፊት ከጡረታ የተገለለ ያስመስለዋል፡፡ ሲጎነጭለት ከነበረው ማርቲኒ ወደብርጭቆው ሲቀዳ በቀላሉ የሚቀርቡት ሰው መሆኑን ተረዳሁ፡፡

እጄን ዘርግቼ «እንዴት ነው?» ስል ጠየኩት እጆቹን ከኪሱ ሳያወጣ ትክ ብሎ አየኝ፡፡

«አሜሪካዊ ነኝ እዚህ ገና መምጣቴ ነው» ስል አሁንም እንደጠጣ እንደፈገግኩ ተናገርኩ፡፡

«ይገርማል!» ሲል ወዳጃዊነት በተለየው ቅላጼ ተናገረ፡፡ «እዚህ ብዙ አሜሪካውያን አይገጥሙንም፡፡ ምን እየሰራህ ነው»፡፡

«የምሰራው ለአንድ የአሜሪካ ነዳጅ አውጪ ድርጅት ነው፡፡ እናንተ ባላችሁበት ኣካባቢ ነዳጅ ፍለጋ ልንሰማራ ፈልገናል፡፡»

«የስነ ምድር ጠቢብ ነህ»

«የለም፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ደህና ምን አልባት ያ ከአገራችን ከርስ ምድር ያቆየነው ነዳጅ እንደሌለ ላለማወቅህ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡» ሲል ተናግሮና ፊቱን አዙሮ ባለሁበት ጥሎኝ ሔደ፡፡

ክፍሉ እንደተመለስኩ ስለፌዘኛዋ አገር የሚገልፀውን መጽሐፍ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ አገሪቷ ምንም ዓይነት ሃይድሮ ካርቦን እንደሌላት አንብቤ ተረዳሁ፡፡ በማግስቱ ተማሪዎቹ ካዳራሹ እንደተሰበሰቡ የቤት ስራውን ያልሰራ ብቸኛ ተማሪ እኔ ብቻ ስላለመሆኔ እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡

ሰዓቱ በግምት ስምንት ተኩል ግድም አንድ ቁመቱ 6ጫማ ከ3 ኢንች የሆነ ወጠምሻ ጎረምሳ ወደ አዳራሹ ገበ፡፡ ሆን ብሎም ወደመድረኩ አመራ የፊቱ ገፅታ አብዛኛውን የህይወት ዘመኑን ያሳለፈው በበረሐ መሆኑን ያሳብቅበታል፡፡

«ጆ ሊይንች እባላለሁ፡፡ የዚህ ትምህርት መምህራችሁ ነኝ፡፡ ከእናንተ መሀል በትላንት ማታው ስብሰባ የተገኘ ተማሪ ማን ነው?»

አዳራሹ በፀጥታ ተዋጠ እጁን ያነሳ ተማሪ አልነበረም፡፡

ሊንች ወደ ክፍሉ መሃል ሰገደድ በማለት እኔ ከተቀመጥኩበት ዴስክ አጠገብ ቆመ፡፡ ጥቁሩን ሰሌዳዎች ላስተዋላቸው ማይካ የሆኑት ዴስኮቹ እና ጽሁፍ አልባው ግድግዳዎች ደግም ወደ ጆርጂታውን ዩኒቨርስቲ የተመለስኩ መሰሎ እንዲሰማኝ አርገውኛል፡፡ ሆኖም ይህ ሰው በህይወቴ ገጥመውኝ ከነበሩት ፕሮፌሰሮች ከአንዳቸውም ጋር አይመሳሰልም፡፡

«ዛሬ እዚህ ለምን እንደተገኘን የሚነግረኝ ሰው አለ» ድምፁ በአዳራሹ ውስጥ አስተጋባ፡፡

እኔ እንደማላውቅ አውቃለሁ፡፡ እንዲት ጠና ያለች ሴት እጃን ማንሳቷ ከሀሳብ አናጠበኝ፡፡ ለጊዜውም ቢሆን CIA ውስጥወዳለች እንድ ባለስልጣንነት ራሷን የቀየረች መስላለች፡-

«እዚህ የተገኘነው እንደምንም መረጃ ሰብሳቢዎች መሆን እንደምንችል ለመማር ነው፡፡» አለች

ሊንች ሌላው ቀርቶ ስለምላሿ እንኳን አላመሰገናትም፡፡ ክፍሉን በዓይኑ ከማተረ በኋላ ዳግም ወደነበረበት የመድረኩ ጀርባ ተመለሰ፡፡

ሊንች ከመብገኑ የተነሳ ፊቱ ቲማቲም መስለ ራሱንም ለማረጋጋት እየሞከረ ሁለተኛው የስብሰባ ሐሳብ ግልፅ የሆነላችሁ አልመሰለኝም፡፡ እስቲ ከናንተ ቢያንስ አንድ ስልክ ቁጥር ያለው?»



t.me/OLDBOOKSPDF

ከተማሪዎቹ ግማሽ የሚሆኑቱ እጃቸውን ወደላይ አነሱ። ሊንች አሁን በጣም ከመናደዱ የተነሳ ራሱን መቆጣጠር አቃተው። ፊቱን ፊት መደዳ ከተቀመጡት ተማሪዎች ወደ አንደኛው መለሰ። የቢሮ ቁጥር ነው?»

ተማሪው አዎንታዊነቱን ለመግለፅ ራሱን ከፍና ዝቅ አደረገ።

«እናስ ስልኩን ያነሳችው ፀሐፊዋ ማነህ? ብትልህ ምን ትላታለህ? መማሪያ መጸሀፍህ ላይ እንዳነበብከው ዊልተን ዩናይትድ ስቴት ጠላት ናት ኢሚሪገውያንና የመንግሥት ባለስልጣናት ቀጠሮ ያልተያዘበት ግንኙነት ማድረግ አይችሉም። ትላታለህ?»

ሊንች ክፍሉን በአይኖቹ አማተረ

እዚህ ምን እያደረጋችሁ ነው ወደሚለው ጥያቄ ልመለስና የአሜሪካን መንግስት እናንተን ወደ አዳኝ ተኩላነት ለመቀየርና ለመግራት በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ፈሰስ አርጎባችኋል። ትላንት ማታ ግልገሎቹን ከመንጋው ትለያላችሁ የሚል ግምት ነበረኝ እነዚህ ግልገሎች ብዙ ሚስጢራትን የሚያውቁ ሰዎች ናቸው። ወደ ክህደት መንገድ ትወስዷቸዋላችሁ። ለነርሱ ውድ የሆነውን ነገር ሁሉ ሀገራቸውንም ጭምር እንዲከዱት ታደርጉዋቸዋላችሁ። በአንፃሩ ግን የእናት ሀገራችሁን ምስጢር ትደብቋቸዋላችሁ የሚል ግምቱ ነበረኝ እንዴት ነው ያ ሁሉ ስልጠና ውሃ በላውን?»

«CIA ውስጥ የገባችሁት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሆናችሁ በየኮክቴል ግብዣው ነፃ መጠጥ ለመጠጣት የተንበሸበሸ የዕረፍት ጊዜ በአውሮፓ ለማሳለፍ ከሆነ ካሁኑ ወደዋናው መመሪያ ሄዳችሁ ወንበር ብትፈልጉ ጥሩ ይመስለኛል፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር CIA እኔን በሰላይነት ወደ አለም ለመላክ የወሰነውን ውሳኔ ቁርጠኝነት የተረዳሁት፡፡ በተቋሙ ገንዘብ በበረዶ የመንሸራተት ስፖርት የማሳልፋቸው ጊዜያትም ስዊዘላንድ ውስጥ እንደሚጠብቁኝ አሰብኩ፡፡

☆☆☆

በቀጣዩ አምስት ወራት አስተማሪዎቻችን ጥሩ አዳኞች እንዲወጣን የተቻላቸውን ጥረዋል ግረዋል፡፡ ቀን ከሌሊት በመስራት ባለሙያዎቹ ማነፍነፍ መመልመልንና ሰላዮችን ማስማራት በጥቅሉ የተካኑዋቸውን የስለላ ጥበባት በዊልተን ከምትተዳደረው ምናባዊ አገር ሳንወጣ ተማርናቸው፡፡ አንድ ሰው በካምፑ ውስጥ ተቀባይነት አጣ ማለት ደግሞ ግለሰቡ ለመረጃ ሰራተኝነቱ ማረጋገጫ አልተሰጠውም እንደማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማረጋገጫ ሳያገኝ ግዳጁን ለመፈፀም ወደ ባህር ማዶ አያቀናም ማለት ነው፡፡ በቋሚነት ከ CIA መምሪያ ጽ/ቤቶች እንዲሰራ ይደረጋል ከዛም በገዛ ፈቃዱ ስራውን መልቀቁን የሚሻል ሆኖ ያገኘዋል፡፡

ከሁሉ አስቸጋሪው በነሱ አጠራር «አዳኝ ተኩላ» (ለተልዕኮ ማዘጋጀት) ሲሉ የሚጠሩትን ምልመላ መፈፀሙ ነው፡፡ አንድ ሰላይ አላማ ያደረገውን ግለሰብ CIA ማወቅ የሚፈልጋቸውን ሚስጢራት እንደሚያውቅ ካወቀ ለስራው እንዲመለመል ሊያደርጉት



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚችሉት ደካማ ጎኖች መኖር አለመኖራቸውን በማጣራት ግምቱን ይሰነዝራል፡፡ ሕጉ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀመጥ በሴት በኩል ያለውን ድክመት፣ ያለበትን የገንዘብ ችግር፣ በሀገሩ ላይ ያለውን ጥልቅ ችግር እና የአልኮል ሱሰኝነቱን ለተልዕኮው መልምለው የሚል ይሆናል፡፡ አንዳንዴ ግን CIA የሚመለምላቸው ሰላዮች የሚመለመሉት ለአሜሪካ ባላቸው ፍቅር በመመርኮዝ ብቻ ነው፡፡ ጭንቅላታችን ውስጥ ስርፆ የገባውና ለመመልመል የሚያጋልጡ ደካማ ጎኖች ያሉበትን ሰው ተከታተሉት የሚለውን ትምህርት በጥና እግራጭነት በመያዝ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ በመቶሺዎች የሚቆጠሩ የዶላር ቼክ ስለገንዘብ ግድ ሰጥቶት ከማያውቅ ሰው ፊት ማሳየት ሰላዩን ከችግር ውስጥ ከመክተት ያለፈ ፋይዳ የለውም፡፡

ከእ በኋላ የገቡ ተማፆች (ተመልማዮች) ካልተመለመሉ የሚፈጠረውን አሳዛኝ ውጤት በማስረጃ ተደግፎ እንዲያውቁት ተደርገዋል ታሪኩ የተፈፀመው አፍጋኒስታን ካቡል ውስጥ ነው፡፡ የመረጃ ሰራተኛው አንድን የሶቭየት ዲፕሎማት መመልመል ይፈልጋል፡፡ ጊዜው ደርሶም የመረጃ ሰራተኛው የተመልማዩን ደካማ ጎኖች ማወቅ ሳይችል ይቀራል፡፡ በዛፋንታ ሰራተኛው ለሶቭየቱ ዲፕሎማት አሜሪካና ሶቭየት ቢቀራረቡ ውጤቱ ጥሩ እንደሚሆን ያስረዳዋል፡፡ ዲፕሎማቱ በሐሳቡ ከተስማማለት በኋላ ሐሳብ መለዋወጥ ትችላላችሁ በሚል ምትኩ ከሆነ ሌላ የመረጃ ሰራተኛ ጋር ያስተዋውቀዋል፡፡

ነገሩን የከፋ ያደረገው የመረጃ ሰራተኛው ሁኔታውን በዛ መልኩ ሪፖርት አለማረጉ ነበር፡፡ ሪፖርቱ የሶቭየቱን ሰው እንደመለመለውና ምትኩ የሆነው ቦብ....... ከእርሱ የሚሰማውን መረጃ እንደሚያቀብለው ይገልፃል፡፡ ቦብ የሶቭየቱን ዲፕሎማት ብቻውን ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ ሬስቶራንት ባገኘበት ወቅት ልዩ ልዩ ዶክመንቶችን ይጠይቀዋል፡፡ በሁኔታው የተበሳጨው የሶቭየቱ ሰው ጠረጴዛውን በጡቻ ይደቃል፡፡ መጮሁም ቃጣው፣ በሬስቶራንቱ ያለው ተመጋቢም ሁኔታው ግልፅ ይሆንለታል ወሬውም በአንዴ በካቡል ናኘ፡፡፡ ....... ቦብም ወደ ሃገር ቤት ተመልሶ ከእርሻው መስክ እንዲያስተምር ተደረገ፡፡ ግዳጁም እንዳበቃለትና ቤንች መሆኑ የገባውና በሌሎች ችግሮች መጠበሱ የማያጠራጥረው ቦብ ሚስቱና ልጆቹ ቤቱ ውስጥ በነበሩበት ሁኔታ አንድ የገና ጠዋት ከቤቱ በረንዳ በራሱ ጥይት ነፍሱን ማጥፋቱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነበር፡፡

✿✿✿

ሌላም ጊዜ ዲኦ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ስልጠና ስንጀምር ትኩረትና ክብደት እንድንሰጠው የተነገረን ነገር ነበር፡፡ ይኸውም ካስማራችሁት ሰላይ ህይወት በላይ ዋጋ ያለው ነገር የለም የሚል አስተምህሮት ነበር፡፡ አንድ የሚስጥር አገልግሎት ሰራተኛ ለፕሬዝዳንቱ የጥይት ቀለህ እንደሚወስድለት ሁሉ የመረጃ ሰራተኞችም ያስማሩትን የሰላይ ህይወት ከአደጋ ለመታደግ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መዋሸት፣ ማታለል፣ መስረቅ ወይም የከፋ ነገር ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ እጅግ ጥቂት ከስለላ ስራ ውጭ ያሉ ሰዎች በአንድ የመረጃ ሰራተኛና ሰላይ መሃል ስላለው ትስስር የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው ሁኔታው ግን ቀዝቀዝ ባሉና አሉታዊ ቃላቶች ሲገለፅ አንድ የኢኦ ሰው


t.me/OLDBOOKSPDF

'ሚመለምላቸውን ሰላዮች ሕይወት ከአደጋ መጠበቅ ካልቻለ ለCIA የዚያ ሰው ባላደነት ነከትሞለቃል እንደማለት ነው፡፡

አንዳንዴ ተመልማዮቹ ሰላዮች በመረጃ ምንጭነት ከሚጠቀሙባቸው ሰዎች ኣንዱ ሊያፈነግጥና መላው የስለላ መረብ ሊበጣጠስ ይችላል፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ሰላዮቹ የመረጃ ሰራተኞቹን ለመገናኘት ከተቀጣጠሩ በኋላ በስፍራው ሳይገኙ ይቀራሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የመረጃ ሰራተኞቹ ተመልማዮቹን በትክክል እንዲመለመሉና ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያረጉባቸው ዲ.አ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮች ፈሰስ ያደርጋል፡፡ ቆይታችንን ከእርሻው መስከ ባረግንበት ወቅት የዕረፍት ጊዜያችንን የምናሳልፈው ባብዛኛው ወደ ሪችመንድ ቨርጂኒያ በባዶ እግራችን በመሮጥና የመኪና ቅኝት በማድረግ ነበር፡፡ ቅኝቱንም አንዳንዴ አስተማሪዎቻችንን ተከትለን ሌላ ጊዜም እነርሱን ከኋላ አርገን እንፈፅማለን፡፡ ነገሩ ሁሉ አሁን አሁን ሳስበው ልክ የድመትና አይጥ ጨዋታ አይነት ነበር፡፡ የውስጥ ዘመቻዎች አፈፃፀም በሚል ዋሽንግተን ዲሲ ለሚሰጠን ትምህርትም መንደርደሪያ ሆኖናል፡፡

ትምህርቱ የታቀደው ሞስኮና ፔኪንግ ለሚሄዱ የመረጃ ሰራተኞች ነበር፡፡ ሐሳቡ መረጃ ሰራተኞችን በማስማራት ከሁለት እስከ ሶስት መቶ አባላት ያሉትን የቁጥጥር ቡድን መረብ መበጣጠስ እንደሚያስችል የታመነበት ነበር፡፡ እናም በዚህ ረገድ ትምርቱን ከሰጡን ሰዎች አንዷ የነበረችውን ማርታን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ግራጫማ ፀጉር ያላት ማርታ ሰላሳ አመቷ ሲሆን ራሷን የኬጂቢሉ (የራሺያ የስለላ መረብ) መዋቅር አካል ያደረገን ሰላይ ጋር ሞስኮ ውስጥ ከተገናኘች በኋላ በሶቭየቶች እጅ ወድቃ በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥም ከሶቪየት እንድትወጣ ተደርጋለች፡፡ ማርታ የውስጥ ዘመቻዎች አፈፃፀም የተሰኘውን ይህን ኮርስ እንድትሰጥ የተደረገውም በአንድ ወቅት በተግባር ያሳየችው በመሆኑና አሰቀያሚውን የኬጂቢ' (የራሺያን የስለላ መረብ) ምርመራ አልፋ የመጣች ንቁ ሴት በመሆኗ ነበር፡፡ እንደ እውነታው ከሆነ የቁጥጥር መረቦችን ለመበጣጠስ የሚቻለው በክፍል ውስጥ ገለፃ አሊያም በመጽሐፍ ንባብ አለመሆኑ ከቀሰምነው የመስክ ትምህርት በሚገባ አውቀናል፡፡

በመጀመሪያው ቀን ራሷን ካስተዋወቀችን በኋላ በቶሎ ነበር የለቀቀችን፡፡ «ወደየቤቶቻችሁ ሂዱ፤ ያሉባችሁን ቢሎች አወራርዱ፤ አይናችሁ ያማረውን ልባችሁ የፈቀደውን አድርጉ፡፡ ለሚቀጥሉት ስድስት ሳምንታት ግን የእኔ ናችሁ፡፡» ነበር ያለችን፡፡

ማርታ እንዳለችውም ለቀጣዮቹ ስድስት ሳምንታት ከዋሽንግተን ጎዳናዎች አልራቅንም ነበር፡፡ በየመንገዱ የተቀመጡ ጥቅሎችን አልፈናቸዋል በየግድግዳው ላይ የተደረጉ የጠመኔ ምልክቶች (ለሰላዮች የሚተው ምልክቶች ናቸው) ደብዛዞች ስለነበሩ ችላ ብለናቸዋል፡፡ የዚህ ሁሉ ውጤትም የቱጥጥር መረቡን ለመበጣጠስ የተከተልነውን መንገድ አራዝሞብናል፡፡ ሽፋን የሚሰጡን ቡድኖች ለእኛ ጥሩ ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አንዳንዴ «የዶልፊን ቁጥጥር» የሚሉትን ዘዴ ይጠቀሙ ስለነበር ወዲያው ታይተውን ወዲያው ይጠፉብን ነበር፡፡ ሰዎቹ ለሁለት ወይም ሦስት ቀናት ከእኛ አካባቢ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይጠቀም፡፡ ከዚያም በቀጣዩ ቀን ከነርሱ እንዳቸውንም እናይም እንደውም መናፍስቶችን ይመስሉን ነበር፡፡

በሌላ ጊዜያቶች ደግሞ የፏፏቴ ቁጥጥር የሚሉትን ዘዴ ይጠቀሙ ነበር፡፡ ዘዴውም እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ የሚቆጣጠረው ከኋላ ሳይሆን ከፊት መከታተልን ነበር፡፡ አንድ ጥሩ የፏፏቴ ቁጥጥር ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በሙቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችንና አውቶሞቢሎችን በማሰማራት ነው፡፡ አንድ ተቆጣጣሪ ኢላማውን (ጥንቸል ይባላል) ካለፈው በኋላ ወደ መጀመሪያው መስቀልያ መንገድ ያቀለቁላል፡፡ ከዚያም ከአንድ ካሚዮን ላይ ይላፈራል ካሚዩኑንም ይዞ ጥንቸሉን ይቀድማል ይህም ጥንቸሉ ፍሰቱን ዳግም እንዲቀላቀል ያስችለዋል ማለት ነው፡፡ እናም ስዚህ ሁሉ የህቡዕ ተልዕኮ የውስጥ ተቆጣጣሪው እንዳይታወቅ አልባሳቱን በመቀያየር ዱካውን ያጠፋል ማለት ነው፡፡

ይህ ልምምድ ከዕለት ዕለት ያለማቋረጥ ተካሄደ፡፡ ቡድኖቹና ዘዴዎቹ በዘፈቀደ ይፈራረቁብን ነበር፡፡ የዚህ አላማም በሁኔታው እንድንሰላች እና ስህተት እንድንሰራ ነበር፡፡ ተጨማሪ ስራ እንደማይሰጡን እየገመትን ባለንበት ቅፅበት ነገርየውን ያጧጡፉታል፡፡ አንድ ሌሊት ነገሩ እንዳንገሸገሸኝ ሲያውቁ አንድ ቡድን የመኪናዬን ቁልፍ ሰብሮ ማስታወሻዎቼን እንዲሰርቅ አርገዋል ከምሄድበትም ስፍራ የቁጥጥር ቡድኖች እንደሚቆዩኝ ባውቅም ቅሉ እዛም መሳዩን ስህተት ላለመፈፀምም የንቃት ደውል ሆኖልኝ ነበር፡፡

የትምህርቱ ስልጠና አንድ የቁጥጥር መረብ እንዴምን እንደምንበጣጥሰው ብቻ ሳይሆን መኖር እለመኖሩን እንደምን እደምናውቅ ተክነንበታል፡፡ በከተማ ውስጥ በእግር ጉዞ ላይ አሊያም የገጠር ውስጥ እየነዳህ በእንቅስቃሴ ላይ በምትገኝበት፣ በማንኛውም ሰዓት ከእይታ ልትሰወር ትችላለህ፡፡ በዚያ ጊዜም በአንዱ የገጠር መንደር መንገድ ላይ ሆነክ በከተማው ውስጥ ባሉ ህንፃዎች መሃል ማድረግ የምትችለውን ማድረግ ይኖርብሃል፡፡ ለመወሰን ያሉህ ጊዜዎች ሽርፍራፊ ሰከንዶች ብቻ ናቸው፡፡ በዚህ ሁሉ ማለፍም የእንተን ዝግጁነትና ቀራጥነት ግድ ይላል፡፡

✡✡✡

የእርሻ መሰከ ቦታ ስልጠና ፍፃሜ አካባቢ ማንኛችን እዳለፍንና ማንኛችን እንደወደቅን ታወቀ፡፡ አንድ ምሽት ሊንች በብስጭት ከነበርንበት የተማሪዎች መዝናኛ ማዕከል ዘልቆ እጠገባችን ተሰየመ፡፡

«እምስቱም ወራት ለኔ ሲኦል ውስጥ የማሳለፍን ያህል ነበሩ፡፡ ማንኛችሁ ናችሁ ለመስከ ስራው ዝግጁ ሆንናል የምትሉ?»

ምላሽ የሰጠው ሰው እልነበረም

«እዚህ ያን ያህል ዕውቀት በመጨበጣችሁ ደስተኛ ነኝ» ሲልም ሊንች አከለበት፡፡ ወደዚህ ሙያ ስትመጡ ከህሎታችሁ መሬትን የመጫር ያህል ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«አንድ ነገር ማወቅ ካለባችሁ ያ ነገር ባላንጣችሁ እደጅ እያደባባችሁ እንደሚቆያችሁ ነው፡፡ ደግሞም እንደናንተ ሁሉ የሚያንቀሳቅስ ሃብትና ትዕግስት እንዳለው ማወቅ አለባችሁ፡፡ የምትሄዱት ወደ ፓሪስ ሆነ ሞስኮ ግድ የለኝም የትም ሄዳችሁ የት በሚሊዮን የሚቆጠሩ አይኖች ስህተት ስትሰሩ ለማየት እንደሚጠብቁአችሁ እወቁ፡፡»

«ባህር ማዶ ሳለሁ በየማለዳው ስነቃ ምን እንደማደርግ ታውቃላችሁ? ኪሴን እፈትሻለሁ፣ ባለፈው ምሽት ሳነበው የነበረውን መጽሐፍ ገጾች እርገበግባለሁ ሻንጣዬንም አንድ በአንድ እበረብራለሁ፣ የአልጋዬን ስር በአይኖቼ እማትራለሁ ሲበዛ ጭንቀታም ሰው ነኝ የሰላዩን መታወቂያ ወይም ማንነቱን የሚገልፅ ማንኛውንም ነገር ማግኘት ይኖርብኛል ቤቱን ጥዬ በምወጣበት በማናቸውም ሰዓት ተቃራኒዬ ለፍተሻ ከቤቴ እንደሚገባ ማወቅ አለብኝ፡፡»

ሊንች ተጨማሪ ቢራ አዘዘ ሌሎች ሁለት ተማሪዎች ንግግሩን ለማዳመጥ ወደ እኛ ወንበር ስበው ተቀላቀሉን፡፡

«ሌላ ነገር እንድነግራችሁ ይፈቀድልኝ ነገሩ የስነምግባር ጉዳይ ባይሆንም መጽሐፍቱ ላይ የሰፈረውን ህግ የምትከተሉ ከሆነ የሆነ ቦታ ህጉን መጣሳችሁ አይቀርም፡፡

ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ከሰላያችሁ ጋር ያላችሁን ጉዳይ ቋጭችሁ እንበል፡፡የድካም ስሜትም ደቋቁሷችኋል፡፡ እናም ከአልጋችሁ ውጪ የሚታያችሁ ነገር የለም፡፡ ሰላያችሁን ለማስናበት በመሰናዳት ላይ እያላችሁ በመኪናችሁ የኋላ ማሳያ መስታወት (ስፖኪዮ) ቦግ ብለው የበሩ ሁለት የፊት መብራቶችን ታያላችሁ፡፡ እስከዛች ሰዓት በመንገዱ መኪና እንዳልነበረም ታስታውሳላችሁ እናስ ነገሩ አጋጣሚ ይመስላችኋል? ርግጠኛ መሆን አትችሉም ርግጠኛ ለመሆን ሌሎች አስር ደቂቃዎችን ትጠብቃላችሁ ከአስር ደቂቃም በኋላም መኪናው አለመንቀሳቀሱን ትቃኛላችሁ ቀጥሎስ ምን ታደርጋላችሁ?»

«እዛው አካባቢ ከክትትል ነፃ መሆኔን እስካረጋግጥ እየነዳሁ እቆያለሁ፡፡» ሲል አንደኛው ተማሪ መልስ ሰጠ፡፡

«ምናልባት ልክ ትሆናለህ፡፡ ሆኖም በሌሊት ያለ ዓላማ መንዳት፡፡ በአካባቢው ላለን የቁጥጥር ቡድን የመረጃ ሰራተኝነትህን ሊያሳብቅብህ ይችላል፡፡ ያም ቀይ ሙዳ ስጋ ለቀበሮ እንደመስጠት ይሆናል ወዲያውኑ ደህንነቶች መንገዱን ያጥለቀልቁታል፡፡ አሁን መረጃ ሰራተኞችን ያለው አማራጭ ከበባውን መጣስ ይሆናል፡፡ ያን ለማድረግም ህግን መጣስ ይኖርበታል፡፡

«ምን ማድረግ እንዳለብኝ እኔ አውቃለሁ» ስል አቋረጥኩት፡፡ «ሰላዩ ከመኪናዋ ወለል እንዲጋደም አደረገዋለሁ ወደቤት ነድቼም ከመኪናዬ መጠለያ ቤት እንዲወርድ እነግረዋለሁ ለሰዓታት የሚያንቀላፋበት ቦታንም አዘጋጅለታለሁ በማግስቱም በተመሳሳይ መልኩ ከቤት ይዤው እወጣለሁ በአነዳዴም እርጋታን እላበሳለሁ የሚከታተለን ደህንነት አለመኖሩን ሳውቅ የሆነ ቦታ ከመንገድ ወጣ አርጌ አወርደዋለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሊንች ከጠረጴዛው ተንጠራርቶ እጄን ዘርግቶ ብራቮ! ብሎ ጨበጠኝ፡፡ «ትክክል ነህ» አለኝ፡፡

«ወይ እንደዚህ ቢሆንስ» ሲል ቀጠለ በዛ የማንኙነት ጠዋት ሻንጣ ከመኪናችሁ የእቃ ኮፈን እየከተታችሁ ነው እንበል ሚሊዮን ጥንድ አይኖች ከከተማው ውጭ ለሆነ ጉዞ እየተዘጋጃችሁ መሆናችሁን ይገምታሉ፡፡ ስለሆነም እዛው እዛው በመንዳት ፋንታ ከሰላዩ ጋር ከከተማው ወደ ሚያስወጣው መንገድ ትነዳላችሁ በዚህ ጊዜ ደህንነቱ እንደተገመተው ከተማውን ለቃችሁ እየወጣችሁ በመሆናችሁ ክትትሉን ያቆማል፡፡ ከዚህ በኋላ ከደረሳችሁበት የመጀመሪያ ከተማ አውቶብስ ፈርማታ ሰላዩን ታወርዱታላችሁ ይሁንና ሰላዩ ደስተኛ አይሆንም ቢያንስ ግን ዘብጥያ ከመውረድ መዳኑን ያውቃል፡፡»

ሊንች እየመከረን ያለው የዓመታት ተሞክሮውን በማስረጃነት በማስደገፍ ነበር፡፡ አንድ ዕውነታው ከሆነም ፍፁም ትክክል ነበር፡፡ በግዳጅ ላይ በተሰማራሁባቸው ዓመታትም ያወቅኩት ነገር ቢኖር ስለላ ከአንድ መጽሐፍ የምትማረው፣ ከስልጠና ፊልም የምትቀዳው፣ አሊያም ከክፍል ውስጥ ገለፃ የምትካነው ጥበብ ብቻ አይደለም፡፡ ልትካነው የምትችለው አንድ ሰው ትክሻህን አሻግሮ ሲያይልህና ሆነኸው ስትገኝ ብቻ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፩

## ነሐሴ 1970 ማድሪስ፣ ህንድ

የጉዞ ቲኬቴ እንደሚያስረዳው፡- ለሰባት ሰዓታት ወደ ፍራክፈርት ለዓምስት ሰዓታት እንደገና ስጨፍር ወዳነጋሁበት ቴህራን፣ ተጨማሪ ሁለት ሰዓታት ወደ ኒውዴልሂና አንድ ሌላ ማረፊያ ጣቢያ በመጨረሻም ማድራስ ከተማ ለመግባት ለአስራሰባት ሰዓታት ተጉዣለሁ፡፡ ወደ ሌላኛው የዓለም ክፍል መምጣቴ ቢታወቀኝም ከአውሮፕላን ወርጄ ከበሰበሰ የአክልት ክምርና ከፈነዳ ቱቦ የሚወጣው ትንፋግ እስኪያጥንኝ ድረስ CIA ምን ያህል አርቆ እንደላከኝ አላስተዋልኩም ነበር፡፡ የማድራስን አውሮፕላን ማረፊያ ለይቶ ለማወቅ የተወሰነ ጊዜ ፈጅቶብኝ ነበር፡፡

አውሮፕላን ማረፊያው ውስጥ በዘፈቀደ የተንጠለጠሉት አየር መቅዘፊያዎች ሞቃቱን አየር ከመቅዘፍ በዘለለ የፈየዱት ነገር አልነበረም ከፊቴ ላብ እየተንቆረቆረ ነበርና፡፡ ሁለት ሻንጣ አውራጆች ለአንድ ሻንጣ ሲራኮቱ ሌሎች ሦስት ደግሞ ሻንጣዬን ለመሸከም ደጋግመው ይወተውቱኝ ነበር፡፡ ሻንጣዬን እኔው ራሴ ለማዘል ማቀዴን ብገልፅላቸውም ሰምተው እንዳልሰሙ ውትወታቸውን አላቆሙም፡፡ በቀጣይ አንድ እጁ የተጎዳና አንድ እግሩ ሽባ የሆነ የእኔ ብጤ ወለሉ ላይ በደህናዎቹ እጅና እግሩ ከወዲያ ወዲህ እየተንከላወሰ ይጨቀጭቀኝ ገባ፡፡ ወዲያው ወዲያው ከኋላዬ እየተከተለ እግሬን አፈፍ ያደርገዋል በፍጥነት መራመዴም ሆነ በአንገቱ ዙሪያ የተጠቀለለው ድሪቶ ውስጥ የምዶለው ሩፒ (የህንድ ገንዘብ) ብዛት የእኔ ብጤውን እኔን ከመከታተል የሚያስታግሱት አልነበሩም፡፡ ያስማቋረጥ ተከተለኝ በአካባቢውም ያለሁት ብቸኛው ነጭ እኔ ብቻ ነበርኩ፡፡

በመጨረሻም እንደምንም አፈግፍጌ ለአንዱ ሻንጣ አውራጅ ጭብጥ ሙሉ ሩፒ ሰጠው በሁለት ደቂቃ ውስጥ ኮተቴን ፈልጎ አስረከበኝ፡፡ «ማድረስ ፓሪስ አይደለችም» ነበር ያለኝ የህንድ ቅርንጫፍ አለቃዬ ጉዞ ከመጀመሬ በፊት፡፡ «ሁለቱን ዓመታት በአግባቡ ተወጣቸው፣ አትልክስከስ ያን ካደረግህ ለተሻለ ግዳጅ ዝግጁ ትሆናለህ» የሚል መልዕክቱ አሁን ትዝ አለኝ በሌላ አባባል የሙከራ ጊዜ ላይ መሆኔን እያረዳኝ እንደነበር ገብቶኛል፡፡ ምንም እንኳን ከእርሻው የተመረቅሁ ቢሆንም እኔን ለማድራሱ ግዳጅ የመለመለኝ የምስራቁ ዕዝ ቢያንስ በአንድ ቀፋፊ የግዳጅ ቦታ በሚደረግ ጉዞ ተሳትፌ ብቃቴ ስለተረጋገጠ ወስነው ነው ወደዚህ የመጣሁት፡፡ ከዛ መልስ ሊደረግ የታቀደው አረብኛ ተናጋሪ ሰላዮችን ወደ ሰንዓ (የየመን ዋና ከተማ) እንዲሁም ቀሪዎቹን ኩይሳ ብለን ወደ ምንጠራው የCIA



t.me/OLDBOOKSPDF

ትናንሽ ቅርንጫፎች መላክ ነበር። ለነገሩ በጣም አስከፊ የሚባል ስርዓት አልነበረም። ማድራስን የመሳሰሉት የዓለም ከተሞች በስለላ ስራ የተሰማሩባቸውን ሰዎች ለይተው ለማወቅ በቁርጠኝነት ትየተንቀሳቀሱ ነበር። የታመሙ፣ በውጭ አገር መኖር ያስጠላቸው እንዲሁም ጭራሹኑ ስራውን ያልወደዱት ነበሩ። አንዳንዶቹ ከወኪሎቹ ሲገናኙ ተይዘው ወዳገራቸው ተልከዋል። አንድ ሁለቱ ደግሞ አብደዋል። ሌሎቻችን በአስቸጋሪ ሁኔታ እየማሰንን ለውጥ ማምጣት እንችል እንደሆን ተስፋ በማድረግ ላይ ነበርን። ህንድ የተመደቡበትን ተልዕኮ ለመፈፀም ከበርካታ አገሮች የተወሳሰበች ነበረች ለመጀመር ያህል በመጀመሪያ ከእውነተኛ ሰላዮች ጋር ተፋልመህ እንድትሰራ ትዳረጋለህ። የCIA እና ሌሎች የህንድ ጠላቶችን መንጥሮ የማውጣት ኃላፊነት ያለበት የህንድ የስለላ ቢሮ የተቋቋመው በእንግሊዞች በመሆኑ የተደራጀና ጠንካራ ነበር ለማለት ያስደፍራል። የስለላ ቢሮው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ መንጣሪዎችን በአንድ ጊዜ ማሰማራት የሚችል ነበር። በተለይ በእግራቸው የሚንቀሳቀሱት በመንገድ ከሚተረማመሰው በርካታ ወንድ ተመሳሳይ ልብስ ከሚለብሱ ለይቶ ለማወቅ የሚያስቸግሩ ነበሩ። ማንኛዋንም የህንድ ከተማ ባልተነበበተ ሰዓት ሊወሯት ሲላቸው ደግሞ በአፍታ ሊሰወሩ ይቻላቸዋል። ባለ አራት እግሮቹም ቢሆን እንዲህ በቀላሉ ሊታወቁ የሚችሉ አልነበሩም። በጊዜው ህንድ ውስጥ የነበሩ የመኪና ሞዴሎች ሁለት ብቻ በመሆናቸው በስፖኪዮ ለሚመለከት አሽከርካሪ አንዱን ከአንዱ መለየት አይቻልም። ከሞስኮ ወይም ፔኪንስ በተለየ ሁኔታ ህንድ በአለም ላይ ከሚገኙ የስለላ ቦታዎች የበለጠ አስቸጋሪና ውስብስብ ከሚባሉት ውስጥ ያስመድባታል።

እኔ ወደ ህንድ ከማቅናቴ ከዓመታት በፊት በተሞክሮ የሰማሁት የህንድ የስለላ ቢሮ ዴሊሂ ውስጥ አንድ የስለላ መኮንን ከስብሰባ በኋላ ወኪሉን ከመኪና ሊያወርደው ሲል ከኋላው የሚመጡትን የመኪና መብራቶች አስተውሏቸው ስለነበር የተወሰኑ መንገዶችን አቆራርጦ ከቆመ በኋላ ወኪሉን ከመኪናው በወረደ ቅፅበት አስነስቶ እንደበረረና የገጠመው ችግር የተከሰተው መኮንኑ ባለፈበት መንገድ አንድ የደህንነት መኪና ቆሞ ስለነበር ወኪሉን ሲያወርደው ለመመልከት በመቻላቸው ከዚያ በኋላ ነገሮች እንደተመሰቃቀሉና መኮንኑን ጨምሮ ሌሎች በርካታ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው እንደተያዙ መኮንኑና የህንድ ቅርንጫፍ አለቃ የነበረው ሰው ወደአገራቸው እንደተባረሩ በዚህያም ሳያበቃ ለሁለት አመታት CIA በህንድ የሚያከናውናቸው ስለላዎች እንደአቋረጠች ከተሞክሮ ለመገንዘብ ችዬ ነበር፡፡

ወደ መልካም ጎኑ ስንመለስ ደግሞ ህንድ እጅግ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት የመጀመሪያ ተመራጭ ሀገር ነበረች፡፡ በወቅቱ የCIA አላማዎች ያተኮሩት በሶቭየት ላይና በህንድ የኒዩክሊር ፕሮግራም ላይ ነበር፡፡ በ1970ዎቹ ህንድ ከሶቭየት ህብረት ከታንክ እስከ አውሮፕላን ብሎም የባህር ሰርጓጅ የጦር መሳሪያዎች በመሸመት የመጀመሪያ ተርታ ውስጥ ተሰልፋ ስለነበር ሶቭየቶች



t.me/OLDBOOKSPDF

በወቅቱ የነበራቸውን ዘመናዊ መሳሪያዎች ለህንድ በመሸጥ ላይ ስለነበሩ ከሶቭየት የጦር ሰፈር መውጣት የሚችሉ ሚስጥሮችን ለማግኘት ህንድ የመጀመሪያ ተመራጭ ሀገርም ነበረች፡፡ ህንድ ሀገር ለሚገኙት ቢሮዎች ምስጋና ይግባቸውና CIA ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ከተጀመረ መቼና በየትኛው ክልል እንደሚሆን ደፍሮ መተንበይ በሚቻልበት ደረጃ ላይ ነበር፡፡ የዓለም ሃያላን ሀገሮች እንደሚያደርጉት ህንድ በ1974 የኒዩክለር ሙከራ እንዳካሄደች እና ቀጣዩ ሙከራ መቼ እንደሚካሄድ በተለይም ፓኪስታን ውስጥ ሊሆን እንደሚችል ነቅተን እንድንጠብቅ ኋይት ሃውስ አጥብቃ ትፈልግ ነበር፡፡

በሌላ መልኩ የተመለከትን እንደሆን ደግሞ አንድ መኮንን የመጀመሪያ ወኪሉን ለማጥመድ ለሚያደርገው ሙከራ ተመራጭ ሀገር ነበረች፡፡ ከነን አላይንድ እንቅስቃሴ ከመስራቾች አንዷ እንደመሆኗ መጠን ከመላው አለም የሚመጡ በርካታ ተልዕኮዎች የሚካሄዱባት ሀገርም ነበረች፡፡ ድንገት በሂድክበት የኮክቴል ግብዣ ላይ ምን አልባት የሞንጎሊያውን አምባሳደር ወይም የአፍሪካ ናሽናል ኮንግሬስን አምባሰደር ልታገኝ የምትችልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በዋናነት የእኛ ትኩረት የነበረው ግን በሩሲያ ዲፕሎማቶች፣ የጦር መኮንኖች እንዲሁም ቴክኒሺያኖች ላይ ነበር፡፡ ብቻ ምናለፋችሁ የምትፈልጉትን ሰው ለማግኘት የሚጠበቅባችሁ ነገር ቢኖር በራችሁን ከፍታችሁ ቤት ለእምቦሳ ማለት ብቻ ነው፡፡ በቀላሉ ልትቀጥሩት ከቻላችሁ ደግሞ እድለኝነታችሁ ይጎላል፡፡ በመጨረሻም ህንድ ማህበረሰባዊነት የሚታደስባት ሀገር ናት፡፡ ከቤት ሰራተኞች ጋር መተባበር ደረቅ ማርቲኒ ማሰራት፣ ሲጋራ መጠቅለል፣ ክሬኬት ክለብ ውስጥ ያለ ማቋረጥ እንቶ ፈንቶ ከሚቀባጥረው ጋር ተግባብቶ መጫወት እነዚህ ሁሉ ህንድ ውስጥ የሚዳብሩ ክህሎቶች ናቸው፡፡ አንድ የቴኒስ አለማማጅ በሳንቲም ደረጃ መቅጠር ትችላለህ፡፡ አንዳንድ የስለላ መኮንኖች እንዲያውም ፖሎ መጫወት ተምረዋል፡፡ ማድራስ ውስጥ ኑሮ በጣም አሸማቃቂ አልነበረም፡፡

ከኤርፖርቱ ውጣ ውረድ በኋላ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የእኔ ወደምትሆነው ቅጥር ስገባ ቤቱ ነጭ ከድንጋይ የተሰራ ሲሆን አንድ ትልቅ ባናያን ዛፍ እና የጃስሚን ፔርጎላ በመኪና መንገዱ ዳርና ዳር ተሰግስገውበታል፡፡ ከበረንዳው በታች አንድ ምግብ አብሳይ፣ አንድ አስተናጋጅ አንድ የቤት ሰራተኛ፣ የውስጥና የውጭ ፅዳት እና ሌሎች ሁለት አትክልተኞች በጠቅላላ ሰባቱ ሰራተኞቼ ተደርድረው ይጠብቃሉ፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም በባዶ እግራቸው ቢሆኑም ወንዶቹ ነጭ ዩኒፎርም ሴቶቹ ደግሞ ደመቅ ያለ ቋሪያ ለብሰዋል፡፡ ከመኪናዬ ስወርድ ሁሉም ዝቅ ብለው እጅ ነሱኝ፡፡ አስተናጋጄ ቀዝቃዛ የማንጎ ጭማቂ በብር ትሪ ሲያመጣልኝ ህንድ ከአሁን በኋላ አስቀያሚ መኖሪያ መሆኗ ያከትማል ብዬ ለራሴ ወሰንኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

✡ ✡ ✡

ማድራስ ለስለላ ስራዬ ጅማሮ እጅጉን የምትስማማ ሆና ተገኘች፡፡ ሁለት የስለላ ወኪሎችን ለዚያውም ቁልፍ የማይባሉ ብቻ በውርስ ነበር የተቀበልኩት፡፡ ለስብሰባ ለመዘጋጀት፣ ለማነፍነፍ፣ ወደ ማዘገየ ጣቢያዎች ሪፖርት ለማድረግ በቂ ጊዜ ነበረኝ፡፡ እንፍናፊው የስለላ መኮንን ከዋሽንግተን በሺ ማይሎች ርቆ ቢገኝም የሚወድቀውም የሚነሳውም በሚስጢራዊ ሪፖርት ነበር፡፡

ማድራስ የማይቀርልኝን የጀማሪ ስህተት ለመፈፀምም የተሻለች ቦታ ነበረች፡፡ አንድ ሌሊት ከከባድ ዶፍ በኋላ መንገዴን ስቼ ከነስለላ ወኪሌ ባህር ዳርቻ አካባቢ ሁለት ጫማ ያህል የሚጠልቅ ጎርፍ ውስጥ ገባሁ፡፡ ፖሊሶች በማንኛውም ሰዓት ድንገት ሊመጡ እንደሚችሉ በመፍራት ወኪሉን ሱሪውን ከጉልበቱ በላይ አሸብሽቤና ጫማውን በእጁ አሸክሜ ከመኪና ካስወረድኩት በኋላ እስኪሰወር ድረስ በዓይኔ መከተል ግድ ነበረብኝ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሁለተኛው ወኪሌ በቀጠሮው ሰዓት ሊመጣልኝ አልቻለም እንደውም ከዚያም አልፎ ስብሰባው ላይም አልተገኘም ነበር፡፡ የነበሩኝ አማራጮች አንድም እጄን አጣጥፌ እንዲመጣ በተስፋ መጠበቅ አሊያም ሄዶ መፈለግ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ሕጉን ጥሼ ቤቱ ድረስ ሄጄ የፊት በሩን  አንኳንኳሁ፡፡ የማድራስ ደህንነቶች የኒውደልሂዎቹን ያህል ጎበዝ ቢሆኑ ኖሮ ሁለታችንንም አንገታችን ታንቆ ዘብጥያ ከመውረድ አንተርፍም ነበር፡፡ ይሁንና ማድራስ እንደዚህ አይደለችምና ተረፍን፡፡

የአምባሳደር ልጅ የሆነው አዛዥ ክሪስ ድርጅቱን የተቀላቀለው በቀጥታ ከሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ እንደተመረቀ ሲሆን ወደ ህንድ ከመመጣቱ በፊት አፍሪካ ውስጥ ሰርቷል፡፡ እያንዳንዱን ወኪል ከማግኘታችን በፊት ክሪስና እኔ ስለሁኔታው ለመነጋገር እንሰየማለን፡፡ ምን ዓይነት የማውጣጣት መንገድ ለመጠቀም እንዳሰብኩ፣ የምይዛቸው ወረቀቶች የትኞቹ እንደሆኑ፣ ምናልባት ወኪሉ በቀጠሮው ካልተገኘ ተለዋጭ ቀጠሮ ለመቼ እንደሆነ፣ ምን አይነት ጥያቄዎች እንዳዘጋጀሁ እና የመሳሰሉትን ማወቅ ይፈልጋል፡፡ ወኪሉን ካገኘሁት በኋላም ምን እንደተባለና ምን እንደተደረገ አንድ በአንድ እንወያይበታለን፡፡ ከዚያ ያዘጋጀሁትን የሽቦ መልዕክት በወፍራም ቀይ እርሳሱ እያስመረበት ይገመግመዋል፡፡

የሚያስደስተው የማድራስ ውስጥ ኑሮዬ ስራ ብቻ አልነበረም፡፡ ከከተማው በስተደቡብ በባህር ዳርቻ አንድ ቤት ተከራይቼ ነበር፡፡ ቋጥኞች ላይ ተገንብቶ በዘንባባ ዝንጣፊዎች የከበበው ይህ ቤት ከባህሩ ከሃምሳ ሜትር ባልበለጠ ርቀት ላይ ይገኝ ነበር፡፡ ከምዕራባዊው ድብርት ለመላቀቅ አብዛኛዎቹን የሳምቱን መጨረሻዎች የማሳልፈው በባህሩ ዳርቻ በማንበብና በመዋኘት ነበር፡፡ የእኔ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቴኒስን መውደድና ማድራስ ጥሩ የሚባሉ የቴኒስ ሜዳዎች መያዟ አስደሳች ግጥምጥሞሽ ሆነልኝ፡፡

ክሪስ ከአንድ መረጃ አቀባይ ጋር ሲገናኝ እስከታየበት ድረስ ኑሮዬ የተረጋጋና የተደላደለ ድግግሞሽ ነበር፡፡ የህንድ መንግስት ቅሬታ ከማንሳቱ በፊት ኒውዴልሂ የሚገኘው ቢሮአችን ክሪስን ወደአገሩ መለሰው፡፡ ወዳጅነቱን ወይም ቁጥጥሩን በማጣቴ ደስተኛ ባለሆንም በራሴ መሆኔ ኃላፊነት የመሸከም ብቃቴን አሜሪካም ሆነ ኒውዴልሂ ለሚገኙ አለቆቼ ለማሳየት ሞከርኩ፡፡ ሕጉ ሰላይ ያለተቆጣጣሪ ያፈነግጣል የሚል የተቀመጠ ቢሆንም እኔ ግን ያለተቆጣጣሪ መስራት እንደምችል ለማሳመን ቆረጥኩ፡፡

ክሪስ እንደሄደ አንድ በቅርቡ የተቀጠረ አጳኝ (በመኮንኖች ቦርድ እንደሚጠራው) «Access agent» ከህንድ ጦር ጋር ከተመደበ የአረብ ጠጦር መኮንን ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ በኔ አጠራር ሳሚ የተመደበው ከማድራስ የአስር ሰዓት የመኪና ጉዞ እርቆ የሚገኝ የጦር ሰፈር ነው፡፡ በዩናይትድ ስቴትስ በሳሚ አገር የነበረው የሻከሩ ግንኙነት ወደመቋረጡ እየተንደረደረ ስለነበር የሱ ተፈላጊነት ጉልህ ነበር፡፡ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ሙሉ በሙሉ በመቋረጣቸው ከሐገሪቱ መረጃ ለማግኘት የሚጠበቅበት ብቸኛው አካል CIA ሆነ፡፡ በተጨማሪም ሐገሩ ከሶቬት በርካታ የጦር መሳሪያ መግዛቷ ብሎም አብረው የሚመጡ መምሪያ መፅሮችንም ከእኛ እዕምሮ ብዙም የራቁ አልነበሩም፡፡ እርሻው ውስጥ ዘይት አመሳሳሽ መስዬ ልገባ ስል ከገጠመኝ የማያስደስት አቀባበል በኋላ ምንጊዜም ቢሆን የመጀመሪያ ግንኙነቶች የሚሸውዱ መሆናቸውን ተረድቻለሁ፡፡ የሳሚን እጅ ከጨበጥኩ በኋላ ወደ ተለመደው ገተታዬ ዘው ብዬ ገባሁ፡፡ ህንድ ለኑሮ የማትመች ቀሽም አገር ስለመሆኗ፣ ጓደኛ ለማፍራት አሰቸጋሪ ስለመሆኑ እንዲሁም ስለአየሩ ተስማሚነት አነበነብኩ፡፡ ሳሚ ቃል መተንፈስ እንዳይችል ወይም እንዳይሄድ አድርጌ በእንቶፈንቶ ወሬ ጆሮውን ደበደብኩት፡፡ አውርቼ አውርቼ« ሲደክመኝ ወጥመዴን አዘጋጀሁ፡፡ ባህር ዳር ዳርቻ ስላለው ቤቴ አንስቼ ምን ያህል አዝናኝ እንደሆነ እንዲሁም ከዚህ የተጨናነቀ ቦታ ለአንድ ቀን ርቆ ማሳለፍ ምን ያህል አስደሳች ስለመሆኑ አብራራሁለት፡፡

«ወደ ማድራስ ስትመጣ ደውልልኝ፡፡ ቦታውን ትወደዋለህ» አልኩት፡፡ ግብዣው ከልቤ መሆኑን ለማጣራት ለአንድ ወይም ለሁለት ሴኮንዶች ከተመለከተኝ በኋላ «ደስ ይለኛል እደውልልሃለሁ» የሚል ቃል መለሰልኝ፡፡ የአድራሻ ካርዴን ተቀብሎኝ የእርሱን በሰጠኝ ጊዜ ፈገግታዬን ለማፈን ከንፈሬን መንከስ ነበረብኝ፡፡ ተሳካ ይህ ሰው በጣም የሚፈለግና ሊቀጠር የሚገባው



t.me/OLDBOOKSPDF

በመሆኑ እየተሻሻልኩ መሆኔ ተሰማኝ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ልጅን ለቀጠሮ የጠየቅሁ ዕለት የተሰማኝን ያህል ውስጤ በሃሴት ጮቤ ረገጠ፡፡

ከሁለት ሳምንት በኋላ ስደውል የሰጠኝ ምላሽም ስለደወልኩለት መደሰቱን የሚገልፅ አዝማሚያ ነበረው፡፡ ባለመደወሉ ግን ይቅርታ ጠይቆኝ ስልኩን ከመዝጋታችን በፊት አንድ ጠቃሚ ነገር ተነፈሰ፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት በማድራስ እንደሚያልፍ ነገረኝ፡፡ ስለ ባህር ዳርቻ ቤቴ ደግሜ አነሳሁለት፡፡ ትንሽ ካቅማማ በኋላ ጥያቄዬን እንደሚቀበለውና ሚስቱንም ይዟት እንደሚጣ ነገረኝ፡፡ ቢንጎ! አሁን ተቀብዬ እንዳሻኝ ለማሽከርከር ይመቸኛል አልኩ ለራሴ፡፡ ለአንድ ሳምንት ያህል ቤቱን ለሳሚና ለሚስቱ በሚሆን መልኩ ሳዘጋጅ ሰነበትኩ ሁለት ጠርሙስ ብላክ ሌብል ጆኒ ወከር ውስኪ፣ አንድ ሳጥን የካሊፎርኒያ ነጭ ወይን እና ህንድ ውስጥ በማይገኙ የአሜሪካ ምግቦች ቤቱን ሞላሁት፡፡ ሙዚቃ እንዲኖር በሚል የሙዚቃ ማጫወቻዬን ያመጣሁ ሲሆን ከአንድ ቀን በፊት ሁሉም ነገር ዝግጁ ሆኖ እንዲጠብቅ ለምግብ አብሳዬ ትዕዛዝ አስተላለፍኩ፡፡

በዚያች ቃላቅ ቀን ሰማዩ ከዳመና የጠራ ነበር በቢንጋልም አስደሳች ነፋስ ይነፍሳል ቅዝቃዜውም ሊሰማ በሚችል ደረጃ አልነበረም፡፡ ጠዋት ላይ ከዋኘን በኋላ ለአንድ ሰዓት ያህል በባህር ዳርቻው ተቀምጠን በማውራት አሳለፍነው፡፡ ወደቤትም ተመልሰን ምሳ ከበላን በኋላ ባልኮኒው ላይ ቁጭ ብለን ወይን መጠጣት ጀመርን፡፡ ሳሚና ሚስቱ ሙሉ በሙሉ ዘና ብለዋል፡፡ ስለእስልምና፣ ስለ ሳሚ የልጅነት ጊዜ እንዲሁም ስለ ዓይነስውር አባቱ እያወሩ ነበር፡፡

እስከ አስር ሰዓት ድረስ ቆይታችን በመልካም ሁኔታ ሲሄድ ከቆየ በኋላ በድንገት ያልታሰበ ዱብዕዳ ተፈጠረ፡፡ ሰራተኛዬ እያሀ ደርሳ ማማጥ ጀመረች ዘርፋፋ ቀሚሷን ለብሳ ስለምትንቀሳቀስ ነፍሰጡር ስለመሆኗ የማውቀው ነገር አልነበረም ነገሩ ባሏም የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ ቤቱን በፍጥነት ዘጋግተን ሁሉንም ነገር መኪና ላይ ጫንነው፡፡ ሳሚና ሚስቱም ከእኔና ከእያሀ ጋር ወደ ሆስፒታል ካልሄድን ብለው አስጨነቁኝ፡፡

የሳሚ ሚስት ከእያሀ ጋር ስትሆን እኔና እሱ ከሆስፒታሉ ውጭ ያለ ዛፍ ስር አግዳሚ ላይ ቁጭ ብለን አወራን፡፡ በቀላሉ ስለ ሃገሩ ጦር ያወራኝ ጀመር፡፡ በ1967 በተካሄደው የእስራኤል- አረቦች ጦርነት ወቅት የእስራኤልን የግንኙነት መረቦችን ማዳመጥና በቁጥጥር ላይ ተመድቦ የነበረ ሲሆን እስራኤል የU.S.S ነፃነትን አጥቅታ 34 የአሜሪካ መርከበኞችን ስትገድል እንደተከታተለ እስከዚያ ጊዜ ድረስ እስራኤል የአሜሪካ ኩይሳ እንደሆነች የሚነዛውን የአረብ ፕሮፓጋንዳ ሲያምን ቢቆይም የእስራኤል ፓይለቶች የአሜሪካን መርከብ አጋይተው



t.me/OLDBOOKSPDF

የተለዋወጡትን መልዕክት ሲያዳምጥ ግን ምን ያህል እንደተሸወደ ተረዳ። ምስራቁና ምዕራቡ የግንኙነት መረባቸውን ክፍት መተው እንዳለባቸው ያለበለዚያ ግን የመካከለኛው ምስራቅ ሰላም ህልም ብቻ ሆኖ እንደሚቀር አከለበት፡፡ እሱ በማውራት ላይ እያለ እኔ የማስበው ያሰብኩለትን ዜማ አሳምሮ እየዘፈነልኝ እንደሆነ ብቻ ነበር፡፡ በጣም ተፈላጊ ግለሰብ ከማሳመኔም በላይ የሳሚን በአረቡ ዓለምና በአሜሪካ መካከል ውይይት እንዲኖር የመፈለግ ደካማ ጎን ነጥዬ ማውጣት ችያለሁ፡፡ ገርበብ አድረጌ ልገባበት ያሰብኩበትን በር ወለል አድርጎ ከፈተልኝ፡፡

ከሁለት ሳምንታት በኋላ ሳሚ ወደ ማድራስ መልሶ ደወለልኝ፡፡ በዚያን ጊዜ ከስምሪት ጣቢያዎች ማረጋገጫ ማግኘት ችዬ ነበር፡፡ ማረጋገጫውም በሳሚ የኋላ ታሪክ ላይ ጥናት ተካሂዶ ምንም ዓይነት አደናቃፊ ነገር አለመገኘቱን የሚያረጋግጥ ነበር፡፡ በሬ ወለደ ብሎ የሚያወራ አልያም ለCIA ደርቦ እንዲሰራ በሃገሩ የተላከ ሰላይ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለ ሳሚ ቅጥር ጉዳይ አለቆቼ አልወሰኑም፤ እርሱ የእኔ ፈንታ ነበር፡፡ እኔ ግን ግዳዬን መጣል መጀመር እንዳለብኝ ወሰኛለሁ፡፡

ሳሚ ለምሳ ከቤት ውጭ ጋበዘኝ በጉዳዩ ተስማምቼ በቢሮ አልፎ እንዲወስደኝ ሐሳብ አቀረብኩ፡፡ የእርሻው ስልጠና እንዳስተማረኝ የጨዋታው ቦታ በቁጥጥሬ ስር ማድረግ ነበረብኝና ነው፡፡ ሳሚ ቡና እየጠጣና ግድግዳዬን እየተመለከተ ቢሮው ውስጥ ሲንጎራደድ ሆስፒታል ውስጥ ከነበረው በተለየ ቀጥብ መሰለ፡፡ ይሁንና ጥያቄውን የማቀርብበትን ትክክለኛ ሰዓትና መንገዱን እያጠናሁ ስለነበር ለጉዳዩ ብዙ ቁብ አልሰጠሁትም ነበር፡፡

በመጨረሻም የጉሮሮዬን ድምፅ ጠራርጌ «ሳሚ» ብዬ ጀመርኩ፡፡ ምንም እንኳን የአየር መቀዝፈያው አካባቢውን እየቀዘፈው ቢሆንም እያላበኝ ለመሆኑ የፊቴ በላብ መወርዛት ይታወቀኝ ነበር፡፡ «አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ» አልኩኝ፡፡

ሳሚ በአንቆቅልሽ ስሜት ተመለከተኝና በቢሮዬ ጥግ ካለው ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡ እኔ የተቀመጥሁት ከጠረጴዛዬ ፊት ለፊት ነበር፡፡

«የዛሬ ሁለት ሳምንት አካባቢ በሃገሮቻችን መካከል ሊኖር ስለሚገባው ውይይት አስፈላጊነት ተጨዋውተን ነበር በዚህ ጉዳይ ላይ ደግሞ አንተ የሆነ ነገር ልታግዝ እንደምትችል እያሰብኩ ነበር፡፡» ምናልባት እስካሁን ድረስ በCIA መኮንኖች ከተሰጠው መግለጫዎች ሁሉ የላቀውን ማብራሪያ በሚካሄድበት ወቅት ሳሚ አንድ ቃል ሳይተነፍስ ያዳምጥ ነበር፡፡ ነገሮችን እያብራራሁ የሚዘጋጀውን የውይይት መድረክ ከሃገሩ መንግስት መደበቅ እንዳለበት ማውራት



t.me/OLDBOOKSPDF

ስጀምር ሳሚ ኤሌክትሪክ እንደያዘው ከወንበሩ ተስፈንጥሮ ተነስቶ በቁጣ መንቀጥቀጥ ጀመረ፡፡

«እንድሰልልህ እያግባባኸኝ ነው?» አለኝ ዝቅ ባለ ሻካራ ድምፅ ብርጭቆውንም መሬት ላይ ሲያንደባልለው ከአሁን በኋላ አዎንታዊ ምላሽ በምንም መልኩ የማይጠበቅ መሆኑን ተገንዝብያለሁ፡፡

የውይይቱ አስፈላጊነት ከመጀመሪያውም የእሱ ሐሳብ እንደነበር እንስቼ አትተመተምኩ፡፡ ሳሚ በተወሰነ መልኩ ንዴቱ በረድ ቢልለትም አብረን ምሳ ለመብላት ግን ሳንችል ቀረን፡፡ ከዚያ በኋላ ለተወሰኑ ቀናት ብንገናኝም ወደ ቀጠሮዬ ሲመጣ ግን ሰው ተለይቶት አያውቅም ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፰

# 197-,ኒውዴልሂ-ህንድ

ስለከሸፈው ሙከራዬ ወዲኒው ደልሂ ሪፖርት ካደረግሁ ከአንድ ቀን በኋላ ቢል በአስቸኳይ በአካል ተገኝቼ እንዳናግረው አዘዘኝ፡፡

ጨካኙ ቢል አጭር አይሪሻዊ ሲሆን እጅግ የተወደደ እስከዛሬ ከነበሩት የሳቀ ምናልባትም ለወደፊቱም ምትክ የማይገኝለት የጎዳና ላይ የCIA መኮንን ነው፡፡ የመጀመሪያውን ስሜን ኮሪያዊ እንዲሁም ሌሎች በርካታ አሰቸጋሪ ኢላማዎችን ለመቅጠር ችሏል የቀፋፊዎችና አስቸጋሪዎችም ተቀፅላ ነበር፡፡ አንዴ ኮንፈረንስ እንዲያደፈርስ ተመድቦ ከበረዶ በተሰራ ቀስት ከጎዳና በከፍት መስኮት አሳልፎ ማይክራፎኑን ከኮርኒሱ አውርዶ መጣሉ እንደታሪክ ይዘከርለታል፡፡ በንድፍ ሐሳብ ስናየው በረዶው ቀልጦ መንገድ ላይ ይቀራል፡፡ እኔ መስራት አለመስራቱን ሞክሬ አላረጋገጥኩም፡፡ ይሁንና ታሪኩ ከክሪስ ለቅርብ ወዳጁ የተነገረ ነበር፡፡ ሌላኛው አስገራሚ ታሪኩ ደግሞ ቶክዮ እያለ ይለብስ የነበረው ተለዋዋጭ ጃኬቱ እና የቆቡ ጉዳይ ነው፡፡ ጃፓኖች ከትትል ሲያደርጉበት ሲሄድ ይቆይና ድንገት ከእይታ ተሰውሮ ተለዋዋጭ ጃኬቱንና ቆቡን ገልብጦ የጉዞ አቅጣጫውንም ቀይሮ በአሳዳጆቹ መሃል ማለፍ ይችል ነበር፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቢል ቢሮ ስገባ መጀመሪያ ላይ ባላስተውልም በሕንድ የአሜሪካ አምባሳደር ሮበርት ኮህን ትከሻውን ተደግፎ በማየቱ እጅጉን ተደንቄያለሁ፡፡ ቢል ቁንጠኛ መነጽር አድርጎ በቀኝ እጁ ሁለት የፊም መላጫዎች በግራ እጁ ደግሞ ምላጩን ይዞ ነበር፡፡ ቀረብ ብዬ ሳስተውለው ከተፃፈው ወረቀት ውስጥ እየቀደደ ለማይክሮዳት (የፎቶግራፍ ፊልም) ማስቀመጫ የሚሆን ኪስ እያበጀ መሆኑን ለማወቅ ቻልሁ፡፡

«ይህ አዲስ ትውልድ ማይክሮደት ምን እንደሆነ እንኳን አያውቁም» አላቸው ቢል ለአምባሳደሩ ወደ እኔ እየጠቆመ፡፡

ሲጨርስ አምባሳደሩን ቦታ ቀየራቸውና የማይክሮዳቱን የማስቀመጡን ሂደት ያሳያቸው ጀመር፡፡ ጎሂን የፕሪንስተን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ብሎም ዝነኛ አስተማሪ እንደነበሩ የኋላ ታሪካቸው ያሳያል፡፡ ቢልን ከማግኘታቸው በፊት ሰላይ የመሆን ፍላጎት የነበራቸው አይመስለኝም፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ማይክሮዳቶቹን ግን ወደዋቸዋል፡፡ ቢል እንደዚህ ጥልቅ ፍላጎት የሚጋባ ዓይነት ሰው ነበር፡፡

ስለቢል አንድ ሌላ አስደናቂ ነገር ቢኖር ለአላማው ሙትና መቺም ቢሆን ወደ ኋላ አለማፈግፈጉ ነው፡፡ ፔንታጎን ስለ T-72 ታንክ አሰራር ማወቅ በፈለገ ጊዜ ቢል



t.me/OLDBOOKSPDF

ለአንድ ሌሊት ያህል መረጃውን የሚሰጠን የህንድ የታንክ ጥገና ጣቢያ ሰራተኛ ለማግኘት ችሎ እንደነበር ይታወሳል፡፡

ወደ ቢል ቢሮ የሄድኩት በቀጥታ ከማድራስ በአውሮፕላን እንደመጣሁ ነበር፡፡ ወደ ቢሮው ስገባ ተነስቶ በሩን ቆለፈው፡፡

«ደህና ነህ» ብሎ ጠየቀኝ እኔ ደግሞ ሳሚን በጣም ፈጥኜ ለማግባባት ስለመጣሬ ምክንያት እየደረደርኩ ዘላበድኩ፡፡ «የእኔ ጨቅላ የእኔ ጥያቄ ያን አጭበርባሪ ማሳመን ስላልቻልህ አይደለም፡፡ እያልኩ ያለሁት ለምን በድጋሚ ከስሩ ጀምረህ አልሞከርከውም?» ሲልጮኽብኝ፡፡ ድንጋጤዬ ሳይበርድልኝም «አሳት በአንድ ሳምንት ስንት ይከፍልሃል?» ብሎ ጠየቀኝ፡፡

«ወደ 10,000 ዶላር አካባቢ»

«ስልጠናህ ምን ያህል ጨረሰ?»

በእርግጠኝነት ቁጥሩን ባለውቀውም ወደ 250,000 ዶላር አካባቢ ሲጠራ ሰምቻለሁ፡፡

«ጥሩ ሌላውን እኔ ልጨምርልህ፡፡ መኪናህ፡ ድንኳንህ፡ የቤት ኪራይህ፡ የቤትህ ሰራተኞች፡ መብራትህ፡ የአውሮፕላን ቲኬቶችህ እና አንተን ወደ ህንድ ለመላክ የወጣው ወጪ በሙሉ አለ፡፡ በተጨማሪም የቁጥጥር ጣቢያዎች ቁጭ ብለው አንተን የሚያግዙ ሰራተኞችን ደመወዝ አስበው፡፡ ይህ ተዳምሮ በትንሹ ወደ አምስት መቶ ሺህ ዶላር ግምታዊ አሃዝ ያስጠጋናል፡፡ እስከአሁን ባለው ሁኔታ ላገኘኸው ከፍያ ተገቢውን ግዴታ የተወጣህ ይመስልሃል?»

ስለላን በዚህ መልኩ በፍፁም አስቤው ባላውቅም አምስት መቶ ሺህ ዶላር ግን በእርግጥ በጣም ብዙ ብር መሆኑ ተሰማኝ፡፡ አውርተን ስንጨርስ ወደ ኒውዴልሂ መጥቼ ዕዳዬን በተግባር በምከፍልበት ሁኔታ ላይ ተስማማን፡፡ ቢል ከሳሚ ጋር የነበረኝን ተነሳሽነት ወዶታል፡፡ ምናልባትም ከጥቂት ክትትል በኋላ ወደ ተከበረ የስለላ መኮንንነት ሊያሳድገኝ ይችል ይሆናል፡፡

✡✡✡

ከሁለት ወራት በኋላ ወደ ኒውዴልሂ ተዛውሬ አንድ አዲስ አፓርትመንት ተሰጠኝ፡፡ ትልቅ ባለ አራት መኝታ ክፍሎች ያሉት ቢሆንም የማድራሱን የሚወዳደር ግን አልነበረም፡፡ አሁን ያሉኝ አገልጋዮች ሁለት ብቻ ሲሆኑ የባህር ዳርቻ ቤትም የለኝም፡፡

በመጀመሪያው ሳምንት ጉደኛው ቢል የአንድ ቅጥረኛ ፋይል አሸከመኝና «እንካ በዚህ ጥርስህን ሞርድ» አለኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቅጥረኛው ኒውዴልሂ ውስጥ ያለ ጣምራ ሰላይ ሲሆን በጠቃሚ የመረጃ ምንጭነቱ ይታወቃል፡፡ የሚሰራው ለኬጂቢ ቢሆንም ለCIA ደርቦ ለመስራት የተስማማ ነበር፡፡ ለዓመታት በህንድ የሚገኙ የኬጂቢ የስለላ መኮንኖች ሰላዮችን ስም ዝርዝር፣ የአሜሪካዊ ኢላማዎችን ብሎም ህንዳዊ ቅጥረኞችን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ምስጢሮችን ለCIA ሲያቀብል ቆይቷል፡፡ ይሁንና እስካሁን ድረስ በትክክል ለሁለታችንም የሚሰራ ስለመሆኑ እርግጠኛ አልነበርንም፡፡ ኬጂቢ ከኛ መረጃ ለመሰብሰብ የላከብን ሊሆን ይችላልና! ወይም ደግሞ ቅጥረኛው ራሱ ለማን እንደሚሰራ እርግጠኛ ላይሆን ይችላል፡፡ ዛሬ ለእኛ ነገ ደግሞ ለኬጂቢ ሊሰራ የሚችልበት አጋጣሚም አለ፡፡የሁለትዮሽ ሰላይ መሆን ደግሞ ጨፍኖ ቼዝ እንደመጫወት ያህል ነው፡፡

KGB (የሩሲያ የስለላ ድርጅት) CIA ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ እረግጥ ነበር፡፡ ህንድ ለእኛ የልምምድ ቦታ እንደነበረች ሁሉ የእነርሱም ምርጫ ነበረች፡፡ ሶቪየቶች ከመካከላችን አንዱን ለመቅጠር በርካታ ታታሪ ወጣት መኮንኖች ህንድ ውስጥ በማጥለቅለቅ መኖሪያ ቤቶቻችንን ያሰልላሉ፣ ክትትል ያደርጉብናል እልፎ ተርፎም ያለማሰለስ ሊቀጥሩን ሁሉ ይጥራሉ፡፡

እኔ እንዳጣራሁት ከሆነ ከህንድ ወደ ዋሽንግተን መልዕክት አድራሻችንን ጨምሮ በርካታ አባሎቻችን ለእነሱ እንዲሰሩ በማድረግ ስኬቶችን ተጎናፅፏል፡፡ መልዕክት አስተላላፊውን መያዝ ሌላ የሶቭየት መረጃ አቀባይ ቅጥረኞችን ስለሚያሳጣን የነበረው አማራጭ ባለበት ትቶ ሌትና ቀን አታካች በሆነ መልኩ ቁጥጥር ማድረግ ነበር፡፡ መረጃ መለዋወጡ ራሱ በምስጢራዊ ምልክቶች መሆን ጀመረ፡፡ እያንዳንዱ መኮንን መረጃ በሚልክበት ሆነ በሚቀበልበት ጊዜ ሁሉ መረጃውን ወደ ምስጢራዊ ምልክት ምልክቱንም ደግሞ ወደ መረጃ ለመቀየር ይገደዳል፡፡ አንዴ ደግሞ የክትትል ቡድናችን አንድ የኬጂቢ መኮንን ከስቴት ዲፓርትመንት ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት ከፍሉ ውስጥ ከሚሰሩ ሰራተኞቻችን ውስጥ አንዱን ጠዋት አራት ሰዓት አካባቢ ከመኪናው ሲያወርደው ስለተመለከተ ጉዳዩን ለማጣራት የነበሩን አማራጭ ከኬጂቢ አንድ ሰላይ መቅጠር ነበር፡፡

የጥምር ቅጥረኛውን የሚከታተለው መኮንን ፖል የሶቭየት ኢላማዎች ተቆጣጣሪ ሲሆን ስለ ኬጂቢ እጅግ ወሳኝ የሆነ ተንቀሳቃሽ የመረጃ ምንጫችን ነበር፡፡ በ1958 የኬጂቢ የበላይ ዳይሬክተር ማን እንደነበረ ከመናገር ጀምሮ ያለምንም ግድፈት ሌሎች በርካታ የሰለላ ወሬዎችን ማነብነብ ይችላል፡፡

ፖል ቅጥረኛውን እንዲያስተዋውቀኝ ስጠይቀው ከስውር መሳቢያው ስድስት በሁለት ጫማ ያህል የሚደጉሱ ጥራዞች አውጥቶ ሰጠኝ፡፡

«ይህንን በሁለት ሳምንታት ውስጥ እንብበህ መልስ» አለኝ ፖል፡፡

ካጋጠሙኝ ማጣራቶች ሁሉ አታካች የሚባለው ሆነብኝ፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የቅጥረኛው የቀጠሮ ሪፖርቶች ሲሆኑ የተካሄዱ ምልልሶችንም ያጠቃለለ አይነት ነበር፡፡ እያንዳንዱ ሪፖርት የቅጥረኛው ያለፈውን ቀጠሮ በማስታወስ ይጀምርና ከዚያ በኋላ ከማን ጋር እንደተገናኘ፣ የኬጂቢው መኮንን ምን እንዳለው እርሱ ምን እንደመለሰ እና የመሳሰሉትን በጥልቀት ያቀፉል፡፡ አላማው ሪፖርቱን ደጋግሞ በማንበብ ቅጥረኛው



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚዋሸበትን ቦታ ማግኘት ሲሆን የሪፖርቱ ጥልቀት ግን የሚዘለቅ አይነት አልሆነም፡፡ እኔስ ምን ሞኝ ነኝ ወደ ሽምደዳ ቀየርኩት፡፡

ከሳምንት በኋላ ፋይሎችን ተሸክሜ ስመለስ ፖል በማስፈራራት ዓይነት በዓይኑ ገረፍ አረገኝ፡፡ «ቅጥረኛው የአሌግ ኢቫኖቪችን ስም አንድ ጊዜ ብቻ ያነሳበት ምክንያት ለምን እንደሆነ አስተውለሃል?» የሚል ጥያቄ ገና ሳልቀመጥ ጠየቀኝ፡፡ «አሌግ የሚገርም ልጅ መሆኑን እኛ እናውቃለን ቅጥረኛው ይህንን ያላወቀበት ምክንያት ምንድነው?» እንደ እውነቱ ከሆነ የአሌግን ስም ስለማንበቤ እንኳን እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ ፖል ወደ በሩ ሲጠቁመኝ የውጣልኝ ሙድ ስለሆነ እንዳገባቤ ፋይሎችቹን እንደተሸከምኩ መስስ ብዬ ወጣሁ፡፡ ያው እንዴት ይሄን ሁሉ የመረጃ ፋይል በአንድ ሳምንት ውስጥ አጠናቅክ የሚለው ሙድ ስለገባኝ፡፡ እያንዳንዱን በኒውዳልሂ የሚገኝ አሁን አሁን አንድ በአንድ መፈተሽ ጀምሬያለሁ፡፡ ከአንድ ወር በኋላ ሩሲያዊ የኬ.ጂ.ቢ. ሰላይ የቤተሰብ ስም የሆነውን ፓትሮኒምክን አወቅሁ፡፡ እንደውም የጋብቻ ቀናቸውን፣ የሚስቶቻቸውን ስም፣ ብሎም የልደት ቀናቸውን፣ የስራ ዘመናቸውን አንድም ሳይቀር ተገለፀልኝ ፎቷቸውን አጠናሁ፡፡ በሰልፍ ቢቀመጡልኝ ለይቼ ማወቅ እንድችል አድርጌ ነበር ያጠናኋቸው፡፡ ፖል ሌላ እንቆቅልሽ ጨመረብኝ እሱንም በአግባቡ ተወጣሁት ቅጥረኛውን ለመከታተል ኋላፊነቱን ለመውሰድ ዝግጁ ሆንኩ፡፡ ፖልም ቢሆን እኔን መቆጣጠሩና ሲያስፈልገኝም መርዳት ደስታን ፈጠረለት፡፡

በወር ሁለት ጊዜ አብዛኛውን ከእኩለ ሌሊት በኋላ በአልድ ዴልሂ አገኘዋለሁ፡፡ እናም በዚያች ጭር ባለች ሌሊት የሚከታተልህን ሰላይ ከማየትም አልፈህ የለበሰውን ሱፍ አይነት መለየት ትችላለህ፡፡ የስለላ መኪኖች ሊደበቁ የሚችሉበት ቦታም አይኖርም፡፡ ለሁለት ሰዓታት ያህል መኪናዬን እያሽከረከርኩ ቅጥረኛውን ላውጣጣው አልፎ አልፎ ማስታወሻ ለመውሰድ ስል እቆማለሁ፡፡ ከዚያም ወደ ቤቱ ሄጄ ትንሽ እንቅልፍ እተኛና በቀጣዩ ቀን ስለነበረን ግንኙነት በታይፔ እማካኝነት ጥልቅና አታካች የሆነ መረጃ በመተየብ በነበረው የቅጥረኛው ፋይል ላይ እከልበታለሁ፡፡

ታዲያ መረጃውን መተየብ ስራው ተጠናቀቀ ማለት አይደለም፡፡ የቅጥረኛውን ታሪክ ወደ ኋላ ተመልሼ ማመሳከር የሚፈለግብኝ አስፈላጊ ተግባር ነበር፡፡ እንዴ ኦሌግ ኢቫኖ ቪችን እንዲከታተልልኝ ጠይቄው የመኖሪያ አድራሻውንና ታርጋ ቁጥሩን ይዞልኝ መጣ በቀጣዩ ቀንም ንጋት ላይ ወደተሰጠኝ አድራሻ አመራሁ፡፡ መኖሪያ ቤቱ በር ላይ የተሰጠኝ ታርጋ ቁጥር የለጠፈች መኪና መቆሟን አረጋገጥኩ፡፡ በአጋጣሚ ለመሆኑ ለማረጋገጥ አራት ወይም አምስት ጊዜ ያህል ተመላለስኩ፡፡ ሌላ ጊዜ አሌግ ወደ ራሺያ መሄዱን ሲነግረኝ ለማረጋገጥ እውሮፕላን ጣቢያ ውስጥ ያለ ቅጥረኛዬን የኦሌግ ስም በኤርፍሎት የመንገደኞች ዝርዝር ውስጥ መኖሩን እንዲያረጋግጥ አዘዝሁት፡፡ የኦሌግ ስም ዝርዝር ውስጥ አልነበረም፡፡ የህንድ አየር መንገድ ዝርዝር ውስጥም እንዲሁ ሊገኝ አልቻለም፡፡ አማራጮቹም ሁለት ናቸው ቅጥረኛው ዋሽቶኛል ወይም ኦሌግ የሐሰት ፓስፖርት ተጠቅሟል፡፡ የሁለትዮሽ ቅጥረኛን ወይም ጣምራ ሰላይን መቆጣጠር በአደናጋሪ የባቡር ሀዲዶች መካከል ረዥም መንገድ የመሄድ ዓይነት ነው፡፡ በመጨረሻም ሰውዬው ኬ.ጂ.ቢ. እኛ ላይ ያሰማራብን ሰላይ መሆኑን ደረስንበት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እስካሁን ስሰራ የነበረው በሙያዬ አጠራር «building matrices» ተብሎ ይጠራል፡፡ ግምቶችን ማጣራት፣ ደካማ መረጃዎችን ማጉላት እና መልካሙን መንገድ ማስላሰልን ያጠቃልላል፡፡ መረጃዎች የቱንም ያህል ያልተጠናከሩ ቢሆኑ ሊታመኑ የሚችሉ ብቸኛ መንገዶች ስለሆኑ እነሱ ላይ ሙጭጭ ማለት የግድ ይላል፡፡ CIA ውስጥ ዳግም መስራት የፈለግኩትን ለማስፈፀም እጅግ ጠቃሚ ስልጠና ነበር የወሰድኩት፡፡

✿✿✿

የ KGB' ውን ሰላይ ጨምሮ ሌሎች ቅጥረኞች ቢኖሩኝም የአምስት መቶ ሺህ ዶላር እዳዬን መክፈል ለመጀመር እራሴን ችዬ አንድ ቅጥረኛ ለመከታተል እፈልግ ነበር፡፡ እናም አንድ የህንድ ጦር መኮንን ለመከታተል ወሰንኩ፡፡ ምንም እንኳ የህንድ-ፓኪስታን ጦርነት ካበቃ ስምንት ዓመቱ ቢሆንም በማንኛውም ሰዓት ቀጣዩ ጦርነት ሊፈነዳ የሚችልበት አጋጣሚም የሰፋ ነበር፡፡ ምናልባትም ቀጣዩ የኒውክለር ጦርነት ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ የህንድ መኮንን ቢኖረን እንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ቀድሞ ፍንጭ ሊሰጠን ይችላል ብዬ አሰብኩ፡፡

ችግሩ ከመንጋው መሐል ተጠግቶ ታዳኙን ነጥሎ ማውጣቱ ነበር፡፡ የህንድ ጦር አባላት ከሌላው ማህበረሰብ የተነጠሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የውጭ አገር ሰዎች ወደ ሚከፈሉባቸው የኮክቴል ግብዣዎች ወይም ክለቦች መሄድ አይፈቀድላቸውም ከውጭ አገር ዜጋ ጋር ከተገናኙ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋልና፡፡

ወዲያው ግን አንድ ክፍተት ተዘንግቶ መኖሩን አስተዋልኩ ማለትም የህንድ ጦር መኮንኖች አደን እንደሚወዱና በሳምንቱ መጨረሻዎችና በበዓላት ወደ ፑንጃብ አቅንተው ትልቁን የህንድ ድብ ወይም ወፎች ላይ መተኮሳቸውን፡፡ እናም ራሴን አደን ወደ ሚያፈቅር ሰው በመቀየር የተወሰኑትን መኮንኖች የማገኝበትን ዕድል ማመቻቸት እንደምችል አሰብኩ፡፡

ወደ አገሬ ለመዝናናት ስመለስ ለአደን የሚሆነኝ ባለሁለት ጋን እስራ ሁለት ጌጅ ጠመንጃና በርኪታ ገዛሁ፡፡ ለመመሳሰል እንዲያመቸኝም ህንድ አገር የተመረተችና ቀስቶችን በ1942 በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተሰራች ጂፕ መኪና ገዛሁ፡፡ መኪናዋ በጥሩ ሁኔታ ላይ የነበረች ከመሆኗም በተጨማሪ ቀለሟም መጀመሪያ እንደተቀባች ነበር፡፡ ባለቤቱ እንደነገረኝ ከሆነ በ1971 ከፓኪስታን ጋር ከተደረገው ጦርነት በኋላ የተጣለች ነች፡፡ የማስመዝገቡ ሂደት የማያልቅ መስሎ ተሰፋ ቢያስቆርጠኝም የሲቪል ታርጋና የመሳሰሉትን አስለጠፍኩ፡፡ ማንም ነጥሎ ሊያውቀኝ አይችልም ብዬ በወሰንኩ በሳምንቱ መጨረሻ ወደ አደን ቦታው ለመሄድ አመቻቸሁ፡፡

አደኑን ፀሐይዋ ወጥታ አካባቢውን ማሞቅ ስትጀምር ማለትም ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ ጀመርን፡፡ ሳቢሳዎችን ከሚመገቡበት የበቆሎ እገዳ ለማባረር እንዲመቸን መንገዱን እየጠራረግን ግንዱን በቆንጨራ እናጋድማለን፡፡ እኩለ ቀን ላይ ስልሳ የሚሆኑ ሳቢሳዎችን ማደን ቻልን፡፡ እናም ታዲያ ማታ ላይ በእሳቱ ዙሪያ ስንኮለኮል የተወሰኑት ለእራት ተጠበሱ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በአራተኛው ጊዜ የነበረው የአደን ውሎዬ እድሜው በግምት ወደ ሰላሳ አምስት የሚጠጋ አንድ ጎልማሳ አገኘሁ፡፡ ሻለቃ ሲንግህ እንደሚባልና አሁን አደን የምናካሂድበት ቦታ ባለቤት የአክስት ልጅ መሆኑን ገለፀልኝ፡፡ እኔም ወሬውን ለማስቀየር እየጣርሁ አደናችንን ቀጠልን፡፡ ለመከታተል ቀጠሮ መተበልም አልፈለግሁም ተመልሼ ወደ አንቱ የአደን ቦታ ከመጣሁ ላገኘው እንደምችል አውቂያለሁና፡፡

በተጣዩ ቅዳሜ ከሻለቃ ሲንግህ ጋር ለናድን ዋልን፡፡ እንደሌሎቹ የጦሩ አባላት ሁሉ እርሱም ጉደኛ አዳኝ ነበር ወፍ ሲሰት እንኳን አይቼው አላውቅም፡፡ እናም ያን ቀን ማታ በእሳቱ ዙሪያ ተቀምጠን ስለ አሜሪካና ህንድ ለብዙ ሰዓታት ተጫወትን አሜሪካንን ይወዳታል፡፡ እሱ እንደሚያስበው በርዕዮተ ዓለምም ሆነ በጦር መሳሪያ ራዲያ ከአሜሪካ እንደማትበልጥ እየታወቀ ህንድ ከሶቭየት ጋር መወገኗ ስህተት ነው፡፡ ድብቅ ምኞቱ አሜሪካ ውስጥ ኮሌጅ መከታተል እንደሆነም ነገረኝ እኩለ ሌሊት አካባቢ ግን ወደየጎራያችን ተለያየን፡፡

በዚያ መፀው ሲንግህና እኔ አብዛኞቻቹን የሳምንቱን መጨረሻዎች አብረን የምናሳልፍ ወዳጆች ሆንን፡፡ ስንላመድ ህንድ ውስጥ የማይሸጥ የጣሊያን አገር የእደን መሳሪያ በሽልማት ልሰጠው እንዳሰብኩ አጫወትኩት ከሳምንታት በኋላም ሳበረክትለት አቀፈኝ፡፡ በሚቀጥለው ስንገናኝ ግን ሲንግህ ለክፍያ የሚሆን ገንዘብ ይዞ መጣ፡፡ ስጦታ እንደሆነና ገንዘብ መቀበል ከስድብ እንደሚቆጠር ነገሬው ሳልቀበለው ቀረሁ፡፡ ትንሽ ከንገራገረ በኋላ ተስማማ ወጥመዱም ተጠመደ፡፡

ብዙ ጊዜ አብረን በማሳለፋችን ሰዎች ጥርጣሬ እንዳይገባቸው ስለሰጋሁ አደናችንን በአዘቦት ቀናት አደረግን፡፡ ጥንቃብ ድረስ የምንሄድበት ሰፊ ጊዜ ባይኖረንም ከዴልሂ ብዙ ሳንርቅ ጥሩ ሳቢሳዎችን እላጣንም ነበር፡፡

አንድ ቀን ወደ ከተማ ስንመለስ በዋናው መንገድ የሚኖረውን መጨናነቅ ለማስወገድ ጥግ ይዘን በማሽከርከር ላይ ነበርን፡፡ ዋናው መንገድ በምስራቅ ካልካታን ከካቡል በምዕራብ ከአፈጋኒስታን የሚያገናኝ ሲሆን ህንድ ውስጥ በ1600 ማይሎች የተዘረጋ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሲንግህ በድንገት አቁም ብሎ እንባረቀብኝ» መጀመሪያ ላይ መንገዳችን ላይ የሆነ ነገር ያለ ነበር የመሰለኝ መኪናውን እንዳቆምኩ አዲሱን የአደን ጠመንጃ መዞ እስፋልቱን እየሮጠ አቋረጠ ወዲያውንም እንስተኛ ገቢ እመር ብሎ ገባና ከሁለት ደቂቃዎች በኋላ የተኩስ ድምፅ ተሰምቶ ሲንግህ የሞተች ፒኮክ በእጁ አንጠልጥሎ ሲመጣ አየሁ፡፡ ይህ በእንዲህ ሳለ ድንገት ከየት መጡ ሳይባል ዝናር የታጠቁና አውቶማቲክ ጠመንጃ ያነገቱ ስድስት ወታደሮች ከእየአቅጣጫው ብቅ ብቅ አሉ፡፡

ሲንግህ ሰዎቹን ሲያናግራቸው እኔ ከመኪናዬ አልወረድሁም ነበር፡፡ አሁንም አሁንም ግን እየደጋገሙ ወደ መኪናዬ ሲመለከቱ ውስጤ በፍርሃት መራድ ጀመረ፡፡ እንደምጠረጥረው መኪናዬ ከጦሩ የተሰረቀች መሆኗን ከደረሱበት እኔም ሆንኩ ሲንግህ ተያይዘን ዘብጢያ መውረዳችን ነው፡፡ በአንድ በኩል ደግሞ ጥሩነቱ ሲንግህ ከነዩኒፎርሙ ስለነበር ሁሉታችንንም የጦሩ አባላት መስለናቸዋል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻ ሲንግህ ፒኮኳን ለአንዱ ወታደር አቀብሎት እንደምኝ እየፈገገ ወደ መኪናዉ ገባ፡፡

«የሚስ ጋንዲ ግዛት ነበር» አለኝ መንቀሳቀስ እንደጀመርን፡፡

የኢንዲራ ጋንዲን ግዛት አቋርጦ ከመግባቱም በተጨማሪ የሀንድን ብሔራዊ ወፍ በመግደሉ የሰራው ስራ ህገወጥ ነበር፡፡ እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎችን ደግሞ እርሻው ውስጥ አልሰለጠንባቸውም፡፡

ሲንግህን ደጋግሜ እያስተዋልኩት ስመጣ ከመንጋው በቀላሉ የመለየት ፅድሉ የሰፋ መሆን እየገዘፈልኝ መጣ፡፡ አንዱ ጉደኛው ቢልን በአደናችን ሰዓት ይዌው መጣሁ ቢልና ሲንግህም ተመቻቹ፡፡ በኋላም ጥያቄውን የማገኘው ጊዜ መድረሱን ከቢል ጋር ተስማማንበትና ቢልንም በቦታው እንዲገኝ ጋበዝኩት፡፡

ሲንግህ በሩን ከፍቶ ሲገባ ቢልን በማየቱ የሆነ ነገር መኖሩን ጠርጥሯል ይሁንና ፈገግ ማለቱን አላቋረጠም እናም በጓደኝነት መንፈስ ነበርን፡፡ ለሲንግህ ቢራ አመጣሁለት፡፡

ልክ ሳሚን የጀነጀንኩበትን አካሄድ በመድገም ስለረኸርም ጊዜ ጓደኝነታችን መቀባጠር ጀመርኩ፡፡ «ሻለቃ» አለ ቢል ጣልቃ ገብቶ ሌላ ብዙ ነገር ሳንቀባጥር በፀና እኔ ለCIA ነው የምንሰራው አለውና አረፈው፡፡

አሁን የመጀመሪያው ጥይት ስለተተኰሰ መድረኩን ተረከብኩት፡፡ ሲንግህ ለ CIA መስራት ይፈልግ እንደሆነ ጥያቄ ሳቀርብለት ፊቱ አመድ መሰለ፡፡ ወዲያውኑ ከፍሉን ለቆ የሚወጣ መስሎኝም ነበር፡፡ ምናልባትም ከእኔ ጋር የተገናኘ ዕለት ሪፖርት አለማድረጉ ወይም የሰጠሁትን የአደን መሳሪያ መቀበሉ ሳይቆጨው አልቀረም ይሁንና ራሱን አረጋግቶ ቁጭ አለ፡፡ ሰጨርስ ትንሽ አቅማምቶ እንደ ሚያስብበት ነገረኝ፡፡

ሻለቃው ጥያቄውን ሳይቀበለው ቢቀርም አንድ ነገር ግን ጥያቄ አጭሮብኝ አለፈ፡፡ ለቀጣይ ዓመታት ጓደኛሞች ሆነን ቀጠልን፡፡ ጊዜን ጊዜ ሲወልድ መረጃ አቀባይን መቅጠር ፒዛ የማዘዝ ያህል እየቀለለኝ መጣ፡፡ ቁልፉ ጉዳይ የሌሎችን የልብ ትርታ ማድመጥ መቻሉ ላይ ነው፡፡ የገንዘብ ችግር ቁልፉ ጉዳይ ሲሆን ድብቅ አላማዎችና የመሳሰሉት በቀላሉ ሊሰፉ የሚችሉ ቀዳዳዎች ናቸው፡፡ የተወሰኑ ጊዜያት የወሰደብኝ ቢሆንም በስተመጨረሻ ከሰዎች የአእምሮ ጓዳ ጀርባ የሚገሸራሸሩትን ድብቅ አላማዎች ልቅም አድርጎ ለማወቅ ቻልሁ፡፡ ጡረታ ልወጣ አካባቢ እምቢ የተባልኩበት አንዱም አጋጣሚ አልነበረም፡፡

☼ ☼ ☼

ኒው ዴልሂ ውስጥ በተንቀሳቀስኩባቸው ጊዜያት በደህንነት ዓይን ውስጥ አለመግባቴ ጠቅሞኛል፡፡ ከተጠናከረ ክትትል የዘለለ የደረሰብኝ ነገር ባይኖርም ስጋቱ እንዲጨምርብኝ ምክንያት የሆነው ከሲንግህና የመንታ ቅጥረኛው በተጨማሪ ሌሎች



t.me/OLDBOOKSPDF

አምስት መረጃ አቀባዮችን በመከታተሌ ነው፡፡ ሀንድ በመሰለ አስቸጋሪ ቦታ በየሁለት ወይም ሦስት ቀን አንዴ በሌሊት ቢያንስ ከአንድ መረጃ አቀባይ ጋር እገናኝ ነበር፡፡

በነሐሴ ወር አንድ ምሽት እድለኝነቴን የሚፈታተን ነገር ገጠመኝ፡፡ ለአንድ ሳምንት ያህል የወረደው ዶፍ ዝናብ ኒውዶልሂን በጎርፍ ስላጥለቀለቃት መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ እናም እንደኔ ዕሳብ የተወሰነ ገንዘብ ሰጥቼ ቀድሜ በማገኘው ጨለም ያለ ቦታ ከመኪናዬ ለማውረድ ነበር ዕቅዴ፡፡ ልክ ወደተጠሮ ቦታ ስታጠፍ ሰውየው ትይት ቦርሳ ከመሸከሙም ባሻገር ለቀጠሮው ሳይሮጥ አልቀረም መሰለኝ ቁና ቁና ይተነፍስ ነበር፡፡ «የT-72 ማንዋሎች » አለኝ፡፡ መኪናዬ ውስጥ እንደገባ ወደ ቦርሳው እየጠቆመ፡፡

«ምን አልክ?» አልኩት የሰማሁትን ባለማመን ስሜት

እየፈገገ ያለውን ደገመልኝ፡፡

የT-72 ማንዋሎች ማለት ለዓመታት ስንፈልግ የነበርናቸው የሰውቀት ቁልፎች ናቸው፡፡ መረጃ አቀባዩ በሁለት ሰዓታት ውስጥ መመለስ እንዳለባቸው ሲነግረኝማ ይባስ ልቤ መንጠር ጀመረ ማንዋሎቹን የሰጠው ሰርጀንት ከስራ መውጫ ሰዓት በፊት ወደ ቦታው መመለስ አለበት፡፡ ወደ ቢሮ ሄዶ ፎቶ ኮፒ ለማድረግ በቂ ጊዜ ካለመኖሩም በላይ ዴልሂ በዚህ ሰዓት በደህንነት ሰዎች ትጥለቀለቃለች የሆነ ሆኖ እሁንኑ ካላወሰድኳቸው መቼም መልሼ አላገኛቸውምና፡፡

ምርጫው ቀላል ነበር መረጃ አቀባዩን ከመኪናዬ አውርጄ ፈገግ ካልኩለት በኋላ በሁለት ሰዓታት ውስጥ ጊያምካና ክለብ የእንግዳ ማረፊያ ቢሮ ቁጥር 3 ፊት ለፊት እንዲጠብቀኝ ነግሬው ማርሽ አስገባሁ፡፡ ተደናግጦ ተመለከተኝ «ያልኩህ ቦታ ባልኩህ ሰዓት ያለበለዚያ ማንዋሎችህን ዳግም አታያቸውም» ብዬ ሐሳቤን ደገምኩለትና መኪናዬን ሳስወነጭፍ በአቧራ አለበስኩት፡፡

ቢሮ እንዳደረስኩ በተለምዶ «ቴክ ማን ብለን የምንጠራው የቴክኒክ ሰራተኛ እንዲያግዘኝ ጠራሁት፡፡ እኔ ዶክመንቶች ሰጭን እሱ ኮፒ ማድጉን ተያያዘው አስቀድሜ እንደፈራሁት ወረቀት ከማለቁ ትንሽ ቀደም ብሎ ቶነር አለቀብን፡፡ ቶነሩ የተቀመጠበት ቦታ ቁልፍ ሁለታችንም አልነበረንም ነበር እናም ቁልፉን መብሳት ነበረብንና በሳነው፡፡ ስራውን ስንጨርስ ወደ ክለቡ ለመሄድ የቀሩኝ በጣት የሚቆጠሩ ሰባት ደቂቃዎች ብቻ ነበሩ፡፡ የመጀመሪያውን አደባባይ አቋርጬ ስታጠፍ ቆማ የነበረች መኪና መብራት አብርታ ተከተለችኝ፡፡ እልፍ እንዳልኩም ሁለተኛዋ ተቀላቀለችኝ፡፡ ሰዓቴን ሳየው የቀረኝ ስድስት ደቂቃ ብቻ ነው ሌላ ጊዜ ቢሆን ከመኪኖቹ አስክሰወር ድረስ እሽከረከር ነበር፡፡ አሁን ግን ጊዜ የለም፡፡

በጥና መንገድ ከመኪኖቹ ፊት ማሽከርከሬን ቀጠልኩ፡፡ ከመብራቶቹ መብዛት የተነሳ ሁለቱ መኪኖች እየተከተሉኝ ስለመሆናቸው እርግጠኛ መሆን አልቻልኩም ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ከጊዮርካና ከሰብ ግማሽ ርቀት ላይ ትራፊክ ጭንቅንቁ ቀለል የሚልበት አቋራጭ መንገድ ጠመዘዝኩ እንደተጠመዘዝኩም ነዳጅ ሰጠሁ፡፡ መንገዱን ሳጋምሰው ፍጥነቴ ሃምሳ ደርሶ ነበር ማንም በዚያ ፍጥነት እያሽከረከረ ከጓላዬ ከመጣ እየተከታተለኝ ስለመሆኑ እርግጠኛ እሆናለሁ፡፡ በስፖኪው መቆጣጠሪያን ተጥያለሁ «የቸኮላ አደደርሴ» የሚባለው ደርሶብኝ እንደሆነ እንጃ ወደ መንገዱ ስመለከት በላሞች ተጥለቅልቋል፡፡ በዚያች ቅጽበት ፍሬን ብይዝ ላሞቹ መሀል ተሰንቅሬ እካባቢው ወደ ሞት ቀጠና መቀየሩ አይቀሬ ነበር፡፡ ያሉኝ ብቸኛ አማራጭ ተጠማዞ ማለፍ ነበር ችግሩ ታድያ የሀገሮ ትላልቅ ላሞች ባህሪያቸው የሚገመት አለመሆኑ ነው፡፡ አንዳንዱ ሲለግሙ ወደፊት መሮጥ የጀመሩ መስለው ዞረው ወደ ኋላ ሲፈረጥጡ ይችላሉ፡፡ በሃሳቤ ዕጣ እውጥቼ እንደምገባ በሁለት ኢጎች ተጠማዝዤ ወደ መንገዱ ጥግ በማሽከርከር ተረፍኩ፡፡ በቀኝ በኩል ያለው የመኪናዬ ክፍል በመንገዱ ጥግ ወደነበረው የጭቃ ማጥ ውስጥ ተንሸራትቶ አለመገልበጡም ተዓምር ነበር፡፡ መኪናዬ መንዘፍዘፏን እንዳቆመች በስፖኪዮ ስመለከት ላሞቹ ሄደው በምትኩ በትንሹ ሦስት ጥንድ የመኪና መብራቶች ተተክተዋል፡፡ የደህንነት ሰዎች እደሆኑ ጠርጥሬያለሁ፡፡ የሚያስፈራው ነገር ደግሞ እየተጠጉኝ ነበር፡፡

ሁሉንም ዓይነት ሀሳቦች እንደማስኩ ገብቶኛል፡፡ ክትትል ሲበረታ የሚኖረውን የመጨረሻ አማራጭ የአሳዳጄን ጥርጣሬ ማምከን ነው፡፡ የበለጠ ጥርጥር ውስጥ እንዲገባ የሚያደርገው ቢሆንም የተሻለ አማራጭ አልነበረኝም ማንጥሎቹን ለመመለስ የቀረኝ ሦስት ደቂቃ ብቻ ነበር፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻልኩ ግን መረጃ አቀባዬ እንደተናገረው ሰርጀንቱ ተይዞ ወደ እስር ቤት ይወርወርና አጠቃላይ የሰለላ ልፋታችን መቀመቅ ይወርዳል፡፡

የጊዮርካና በሮችን አቋርጬ ስገባ የሚከተሉኝ መኪኖች ቁጥር ወደ አምስት አደገ፡፡ በስፖኪዮዋ ስመለከት አንድ በአንድ ወደ ውስጥ በመዝለቅ ላይ ነበሩ የመጀመሪያዋ መኪና ከኔ አስር ጫማ ያህል ብትርቅ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ምንም መንገድ ባይኖርም እኔ ግን በሁለት የቴኒስ ሜዳዎች መካከል ማሽከርከሬን ገፋሁበት ሊከተሉኝ እንደማይችሉ እውቄያለሁ፡፡ እንዳሰብኩትም እምስቱም መኪኖች ዋናው ሀንፃ ፊት ለፊት ቆመው ሰዎቹ በእግራቸው እየተጓዙ ነው፡፡ ፍሬን ይዤ ማንጥሎቹ ያሉበትን ቦርሳ በቴኒስ ሻንጣ ከትቼ በሁለት ዛፎች መካከል ገሰገስኩ፡፡ ወደ እንግዳ ማረፊያ ቁጥር 3 ስጠጋ የሰው ኮቴ እየቀረበ ሲመጣ ታወቀኝ፡፡ የመረጃ አቀባዬ ጥላ ቆየኝ ባልኩበት ቦታ መኖሩን ሳረጋግጥ ሳልቆም ማንጥሎቹን ከቴኒስ ሻንጣው አውጥቼ ስርቻ ስር ሸንጥኩት፡፡ መረጃ አቀባዩ ቀብ አድርጎት ሲገሰግስ በጨረፍታ ይታየኝ ነበር፡፡

ጉዞዬን ቀጥዬ ጊዮርካና ባር በጀርባ በር በኩል ስገባ ሱፍ ለብሶ ጋዜጣ ከሚያነብ ሀንዳዊ ወጣት በቀር ማንም አልነበረም፡፡ ሄጄም ከጎኑ ተሰየምኩ፡፡ ቃል ሳልተነፍስ እስተናጋጁን ሁለት ደብል ስኮች ያለበረዶ እንዲያመጣልኝ አዘዝኩት፡፡ ሰረኛም ጊዜያት ጓደኞች የነበርን የሚያስመስል ወሬ እስከማስጀምረው ድረስ ቃል ከአፉ የሚወጣ አይመስልም ነበር፡፡

በገባሁበት አቅጣጫ ወደ በሩ ዞር ስል ከአሳዳጆቼ ሁለቱን አየኋቸው፡፡ እኔንና የቴኒስ ሻንጣውን እና ወጣቱን በየተራ እያፈራረቁ ይመለከታሉ፡፡ ፍላጎታቸው በዚያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዓት ያንን ወጣት ለማግኘት የተጣደፍኩበትን ምክንያት ማጣራት መሆኑ ገብቶኛል፡፡ ከጎኔ ያለውን ወጣት ለብቻው አግኝተው ገና ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት መረጃ አቀባዩ ደነመንቶቹን ሰስርጀንቱ ይመልሳል፡፡

ደስ የሚል ጣፋጭ ድል ነበር፡፡ ተጨማሪ ዙር ስኮች ለእኔና ለአዲሱ ጓደኛዬ አዘዝኩ፡፡ ከሦስት ዓመታት የህንድ አገር ቆይታዬ በኋላ የልምምድ ጊዜውን እንዳጠናቀቀ እናጺ ነበርኩ አሁን ግን ራሴን ችዬ መስራት እችላለሁ፡፡ አሁን የምፈልገው ልሂቅ መሆን ነው፡፡ ቻይንኛ ለማጥናት ብጠይቅም የምስራቅ እስያ ቀጠና ምላሽ ከመስጠቱ በፊት የቅርብ ምስራቃዊ ቀጠና የሁለት አመት የአረብኛ ስልጠና እንድወስድ አግባባኝ፡፡ ስለመካከለኛው ምስራቅ ሽራፊ ዕውቀት ባይኖረኝም ግብዣውን ሳላቅማማ ተቀበልሁት፡፡ እስካሁን በሞቃታማው መጥበሻ ዙሪያ ስንከላወስ ቆይቻለሁ፣ አሁን በእሳቱ ላይ የምራመድበት ሰዓት ደርሷል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፯

# ሚያዚያ 18.1983 ቤሩት-ሊባኖስ

ፊቷ አካባቢ የተጠረመሰች የድሮ ሞዴል የሆነች ካዲላክ ክፍት መኪና ቅዱስ ጊዮርጊስ ከሚባለው ሆቴል ባሻገር ባለው መንገድ በዝግታ ሂዳ ቆመች፡፡ ሾፌሩም ሞተሩን ሳያጠፋ በቤሩት ባህር ዳርቻ በኩል የሚዝናኑትን ሰዎች በአርምሞ ይመለከታል፡፡ ማንም ሰው ለክፍት መኪናዋ ትኩረት አልሰጠም ወይም ልብ አላለም፡፡ ሁሉም ሊባኖሳውያን እስከሚያውቁት ድረስ የርስ በእርስ ጦርነቱ አብቅቷል፡፡ በ1982 የፍልስጤም አድፍጦ ተዋጊዎችን ለመደምሰስ ወደ ስፍራው የተንቀሳቀሰው የእስራኤል ጦርም ወደ ደቡብ ቤሩት አቅንተዋል፡፡ እንዲሁም የፍልስጤም አድፍጦ ተዋጊዎች በሚያዚያ 1975 የሊባኖስ የእርስ በእርስ ጦርነቱ ከተጀመረ ጀምሮ በሰሜን በኩል በትሪፓሊና በቢካ ሸለቆ አድርገው ወጥተዋል፤ በአሜሪካ ፊታውራሪነት የሕብረብሔሩን ጦር የተቀላቀሉት የእንግሊዝ የፈረንሳይና የጣሊያን ወታደሮችም ህብር ፈጥረው በስፍራው ቅኝት እያደረጉ ነው፤ የአሜሪካን ባህር ሃይሎች ደግሞ ኤም-16 የፀረ አውሮፕላን ጠመንጃን ጥይት የማይበሳውን ሰደርያቸውን አጥልቀው አውሮፕላን ማረፊያውን በንቃት ይጠብቃሉ፡፡ ሊባኖስ በርግጥ ሰላም የላትም ነገር ግን ለረዥም ጊዜ ከነበረው ሁኔታ የተሻለች ናት፡፡

በሊባኖስ ምድር የሚነፍሰው ነፋሻማ አየርና የጠራው ሰማይ ለመዲናዋ የሰላም ተስፋ የሰነቀ ይመስላል፡፡ በዚያ ቀውጢ ወቅት ማለትም በእስራኤል ወረራ ከተፈፀመባት ከስድስት ወራት በኋላ በጦርነቱ ወደ ፍርስራሽ ተለውጠው የነበሩት መኖሪያ ቤቶችና የመሰረተ ልማት አውታሮች መልሶ ለመገንባት ሁሉም በየፊናቸው ይውተረተራሉ፡፡ ሎደሩ፣ ግሬደሩ፣ ክሬኖች፣ የግንባታ መወጣጫዎች፣ ትላልቅ መቆፈሪያዎች እንዲሁም ውር ውር የሚሉት ሰራተኞች ሌትና ቀን የመልሶ ግንባታውን ሲያጧጡፉ ለተመለከታቸው በፈርኦን ግዜ የነበሩትን የእስራኤል ዜጎች ያስታውሰናል፡፡

ቀትር ላይ ልክ 6፡43 የክፍት መኪናዋ ሹፌር የተልዕኮዋቸውን ቀጠሮ መዳረሱን የሚያመለክት አረንጓዴ ማርቼዲስ መኪና ከፊት ለፊቱ በቅርብ ርቀት እያዘገመ በመምጣት የፊት መብራቱን በረዥሙ ሦስት ግዜ በማብራት ወደ መጣበት እጣምዝዞ ከነፋ፡፡ ሾፌሩም ካዲላኳን የመጀመሪያ ማርሽ በማስገባት በትራፊክ መብራት መጨናነት የተነሳ መኪና ወደ በዛበት ስፍራ አቀና፡፡ ለጥቆም ባለ ሰባት ፎቅ ህንፃ ወዳለው የአሜሪካን ኤምባሲ እየተጠጋ በመጣ ጊዜ ከተጨናነቀው ትራፊክ መሽሎክሎክ የሚችልበትን አጋጣሚ በዓይኑ ቅፅበት ማተረ፡፡ ከዚያም መኪናውን የማቆም ያህል በዝግታ ማሽከርከር ሲጀምር ከኋላ ያሉት አሽከርካሪዎች ጥሩንባቸውን መደብደብ ጀመሩ በዚህን ጊዜ ከፊቱ ጥሎት በሄደ መኪናና በእሱ መኪና መካከል ክፍተት ሲፈጠር ሁለት



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጆቿን ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ከምታሻግር ሴት ጋር ለጥቂት በማለፍ በቅፅበት መንገዱን ቀየረ፡፡

ከዚህ በኋላ ሹፌሩ መኪናውን ነዳጅ በመስጠት ወደ ኤምባሲው የውጭ በር አመራ፡፡ ወደ መግቢያውም ፍጥነት በመጨመር መንገዝ ሲጀምር ጠባቂዎቹ መሳሪያቸውን እንኳን ለማንሳት ጊዜ አላገኙም ነበር፡፡ ጠባቂዎቹም ምን ሊከሰት እንደሚችል ገብቷቸዋል፡፡ ምክንያቱም በቤሩት ለብዙ ጊዜ ሲፈፀም አይተውታልና እናም ማድረግ የሚችሉት ነገር ቢኖር ወደ ምድር ተደፍተው መፀለይ ብቻ ነበር፡፡

ከፍት መኪናውም ከነተሸከመው ቦንብ የሀንፃውን ደረጃዎች በፍጥነት በመውጣት ወደ እንግዳ መቀበያው ማለፍ ጀመረ፡፡ ልክ ከእንግዳ መቀበያው በር ጋር ከቀኑ 7:03 ላይ ሲጋጭ ከተማዋን የሚንጥ ታላቅ ፍንዳታ ሆነ፡፡ ቤሩት ውስጥ ከተከሰተው እንኳን ከፍተኛ ጥፋት የሚባል ነበር፣ ብዙ ማይልስ ርቆ እንኳን ውስጥ ከተከሰተው እንኳን ከፍተኛ ጥፋት የሚባል ነበር፣ ብዙ ማይልስ ርቆ እንኳን የብዙ ሀንፃዎች መስኮቶች ተሰባብረዋል፡፡ ከህንፃው ምድር ቤት መሀል ያለው የአሜሪካ ኤምባሲ ከሙቶ ጫማ ከፍታ በላይ ተበታትነ የጠራው ሰማይም በአቧራ ተሞላ፣ አካባቢው በአንዴ በተሰባበረ የቤሮ ዕቃዎች፣ ግዳዮችና ጉዳተኞች እንዲሁም የተበታተኑ ዶክሜንቶች ብቻ ሆነ፡፡ የዕንግዳ መቀበያው ስፍራ ባንዴ ወደ ፍርስራሽነት ተለወጠ፡፡ የመስታወት መከላከያ ወፍራም የብረት ፍርግርጎች ወደ 27.600 ጫማ በሰኮንድ በመወርወር በባህር ዳርቻው ስራ ላይ በነበሩት ወጣቶች ላይ ጉዳት አደረሰ፡፡ ከሰውየው የተገኘ ነገር ቢኖር የቀሰጡ የሙሰዮ ቁልፎች ብቻ ነበሩ፡፡

አስራ ሰባት አሜሪካውያንን ጨምሮ በድምሩ 66 ሰዎች እስከዛሬ ድረስ በአሜሪካ ላይ ከተቃጣው የሽብር ጥቃት ሁሉ የከፋ ጉዳት ያደረሰ ሆነ፡፡ በተለይ ለ CIA ትልቅ ጉዳት ነበር፡፡ ምክንያቱም ዋና አለቃው፣ ምክትሉና ባለቤቱን ጨምሮ ስድስት ሰራተኛ ተገድለውበታልና፡፡ የሚያዝነው ነገር ቢኖር የምክትሉ ባለቤት ስራ የጀመረችው በዚያኑ ቀን ጠዋት ብቻ ነበር፡፡ የ CIA የመካከለኛው ምስራቅ የሰላ ወኪል የሆነው ቦብ አሚስያ ጨምሮ ተገደሉ፡፡ ቦብ ወደ ኤምባሲው የመጣው ቤሩትን እየጎበኘ በነበረበት ወቅት ነበር፡፡ አንድ እጁ ከባህሩ ዳርቻ እንደ ማይል ርቆ ተንሳፏል፣ የጋብቻ ቀለበቱም እንዲሁ ጣቱ ላይ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት CIA በአንድ ጥቃት ብዙ ሰራተኞች አጥቶ አያውቅም ነበር፡፡ ይሁንና የዚህ ጥቃት ግን በስለላ ድርጅቱ ላይ ለሁለትና ሦስት ሳምንታት ያህል የሀዘን ጥላ አጥሎበት ነበር፡፡

✡✡✡

በሚቀጥሉት ሃያ አራት ሰዓታት የCIA እና የFBI አጣሪዎች ቤሩትን ወረሯት፡፡ ችግሩ ግን የሚጣራ ምንም ዓይነት የተተወ አሻራ አልነበረም ፍንዳታው ሹፌሩን ሙሉ በሙሉ አጥፍቶታልና፡፡ ቦንቡን ያፈነዳው አንድ ተቀጣጣይ ነገር ጨምሮበት እንደሆነ ግምት ቢኖርም እንዳይረጋገጥ እሱም በፍንዳታው ወድሟል ፈንጂዎቹ ተመሳሳይ ናቸው፣ አንድ ባለሙያ እንዲሁም ሊተዋቸው አይችልም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስጥሩ የጠለቀ የሆነው የFBI የምርመራ ኤክስፐርቶች ፈንጂዎቹ እንደተሰሩ ማወቅ አልተቻላቸውም፡፡ ሴምቴክስ ይሁን አርዲሲክስ፣ ሲ-4 ምንም ፍንጭ የላቸውም፡፡ ምንም እንኳን በመጨረሻ ላይ የፔንት ምልክት ቢያገኙም ቅሉ ይህም ቢሆን ብዙ የወታደራዊ ፈንጂዎች የያዙት የፔንትን ቅልቅል ነው፡፡ እሱም ቢሆን በንቡን የሚያፈነዳበት ወቅት ጥቂት ነው የተጨመረበት፡፡ እንደኛው የምርምር ውጤት እስከግማሽ የደረሰ አሲቲሊን በርሜል በመያዝ ፈንጂው በሚፈነዳበት ወቅት ለማቀጣጠል ብቻ ሳይሆን ፈንጂውን ሹፌሩንና ያፈነዳውን ለማጥፋት ታስቦበት እንደገባ ሲያመለክት ሌላው የምርምር ውጤት ደግሞ ከክፍት መኪናዋ ውሰጥ FBI በመጨረሻ የተሽከርካሪውን ሻንሲ ውስጥ የቪን ቁጥር ቢያገኝም ይህንኑም ከዋናው ክሱክሳሱ ጋር ቢያመሳክረውም እንድ ሰው ገዝቶ ሲጠቀምበት ከቆየ በኋላ ወደ ባህረ ሰላጤ ላከው ብንል እንኳን FBI እንዴት ወደ ቤሩት እንደገባ ሲያውቅ አይችልም እንኳንየማን ንብረት ነው የሚለው ይቅርና ስለዚህ ክትትሉ እዚህ ጋር በአራት ነጥብ ተዘጋ፡፡

የሊባኖስ የደህንነት ሰዎች እና CIA ምንም ፍንጭ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ የሊባኖስ አጣሪዎች እንደገመቱት ሾፌሩ የሺአይት ሙስሊም ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች ሙስሊሞች ይልቅ ሺዓቶች ራሳቸውን ለማጥፋትና በሽብርተኝነት ለመስማራት ዝግጁ እንደሆኑና እነዚህ አክራሪዎች መቀመጫቸውም ከቤሩት በስተደቡብ በምትገኘው በቢካ ሸለቆ ነው ቢሉም CIA የደረሰበት ምንም ፍንጭ የለም፡፡

ሦስት ቡድኖች ኃላፊነት እንወስዳለን ቢሉም፡፡ ነገር ግን CIA እነዚህ ድረጅቶች ስለመኖራቸውም እንኳን እርግጠኛ አይደለም ሦስቱም የፈጠራ ወሬዎች ነበሩና፡፡ የሊባኖስ ደህንነቶችም ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ ሰዎችን እሰሩ፡፡ ነገር ግን የለመዱ ተጠርጣሪዎችን ዋና የምርመራው አካል ለማድረግ የታለመ ነበር፡፡ ቦንቡን ያፈነዱት ሰዎች ግን ምንም መረጃ አልተውም፡፡ ምክንያቱም ጊዜ ተወስዶ ታስቦበትና ከፍተኛ ጥንቃቄ ታክሎበት ነውና ድርጊቱን የፈፀሙት፡፡

☼☼☼

እኔ የዚያን ጊዜ በቱኒስ አረብኛ ቋንቋ እያጠናሁ ነበር፡፡ የፍንዳታው ጊዜ በቅፅበት በዓለም ሲያስተጋባ ሁላችንም ተማሪዎችም ሆንም አስተማሪዎቻችን በኤምባሲው ውስጥ የሚሠራ አንድን ሰው እናውቅ ነበር፡፡ ለብዙ አመታት የኤምባሲው ውስጥ ትሰራ የነበረችውን ካሊደያህንም ፈፅሞ አልረሳትም ነበር፡፡

አንዳንድ የፍልስጤም አክራሪ ቡድኖች ከፍንዳታው ጀርባ ሊኖሩ እንደሚችሉ ይህም የጥቂት ሳምንታት ጉዳይ ነው እንጂ አንድ ሰው ተይዞ ይሄንን ሴራ እንደሚያጋልጠው የታወቀ ነበር፡፡ የተሳሳትኩ መሰለኝ፡፡ በህጋዊ መንገድ ጉዳዮ የሚያልቅ አይመስለኝም ወይም ለእኔ በህይወት ዘመኔ ሁሉ እንፈራሁ ሊያደርገኝ ይችላል ነገር ግን ዘሩ አንድ ጊዜ ተዘርቷል፡፡ ፍንዳታው ከመከሰቱ ከጥቂት ወራት በፊት ቤሩትን ጎብኝቻታለሁ፤ የሞቱትንም አለቃውንና ምክትሉን ጨምሮ አንዳንድ ሰዎችን አነጋግሬያለሁ፡፡ በምናቤ ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስባቸው ግን ልቤ በሀዘን ይደቃል፡፡ የቦንብ ጥቃቱን መረጃ የሰጠው እንደሚሰማው ጭምጭምታ ከሆነ ለዓመታት በተሰበሰበው መረጃ እንዲሁም ከሁለት አስር ዓመታት ከተሰጠው መረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የቦንብ ጥቃቱ ከተፈፀመ ከአራት ወራት በኋላ የሁለት ዓመት የአረብኛ ትምህርቱን አጠናቅቄ ወደ ....... ተመደብኩ ከዚያም በጣም ጠቃሚ በሆነች በመካከለኛው ምስራቅ በምትገኝ የመከላከለያ ጣቢያ ተመደብኩ ከዚያም የማቀርባቸው ሪፖርቶች በጣም አጓጊ ሆና በዋሽንግተን ይነበብ ጀመር፡፡ በጣም ጎበዝ የሆነ ወኪልም ነበረኝና እርሱም የተለያዩ ዶክመንቶችንና የመጀመሪያ ደረጃ ስለላ ያዘጋጅልኝ ነበር፡፡ ይህም ቢሆን አልጋ በአልጋ ሆኖልኛል ለማለት ፈልጌ አይደለም፡፡ በጣም አስቸጋሪ ኢሊማዎች ነበሩና ከኔውደልሒ በኋላ ግን የነበረው ቁጥጥር እንደነፋስ ሽውታ ነበር፡፡ እንደገና ወደ ጎዳናው ተመልሶ መውጣት ወኪሎች ማስማራት እንዲሁም አረብኛውን በተግባር ላይ ማዋል ደስ የሚል ስሜት ነበረው፡፡ እናም በግልፅ ማድረግ የምፈልጋቸውን ነገሮች አገኝ ነበር፡፡ ከሁለት ዓመት ልምምድ በኋላ እንኳን ጥሩ ቋንቋ ለመናገር ገና ብዙ ይቀረኛል፡፡ በቋንቋው ያለውምንም ችግር ለመናገር አመታት ያስፈልጋል ይሁንና እግባባበት ነበር፡፡

ነገሮችን ለእዲሱ አለቃዬ ለጆን ነግሬዋለሁ ጆን ማለት ቶሎ የሚቆጣ ቀጭን ሰው፤ በጥንቃቄ የተዘጋጀ ሱፍ ልብስ የሚለብስ እንዲሁም በየቀኑ ቢሮ ሲገባ የሚያምሩ ጫማዎችን የሚጫማ በጥቅሉ ፀዳ ያለ ሰው ነው፡፡ እሱ የሚለብሰው ልክ እንደ ውጪ አገልግሎት ቢሮ ሰራተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ስላይ እንደዚህ መልበስ እንደሊለበት ግንዛቤ የለው አይመስልም፡፡ ጆን ሀላፊነትን መውሰድ የሚፈራና ውሳኔዎችንም በህብረት ነመወሰን የሚጻጻ ነው፡፡

ጆን ስለ ስለላ ስራው ከመጨነቅ ይልት ከዋናው ቢሮ ጋር ያለው ስብሰባ 'መጨረሻው ቀን መቼ እንደሆን ሲጨነቅ ይስተዋላል፡፡ ከላንግይ የአንዳንድ ጉዳዮችን ፡ደት በተመለከተ የሪፖርት ጥያቄ ሲመጣ ጆን ከሳምት በፊት ከማንኛውም መካከለኛ ሥስራቅ ካለ ቢሮ ቀድሞ ስራውን ያቆማል፡፡ የእኔን ሪፖርቶች ዘግይቼ በማቀርብበት ›ቅት ይነጫነጭና ይቆጣም ነበር፡፡ ምንም እንኳን ቢሮው ያለማቋረጥ ገንዘብ ቢሰጠኝም ›ንድ ቀን ግን የሆነ ነገር እንደሚከሰት ግልፅ ነበር፡፡ ይህ የተከሰተው ደግሞ የእንድ ሸባሪ ቤት በምከታተልበት ጊዜ ነበር፡፡

☼☼☼

ዋሺንግተን ዲሲ የመጀመርያ አመት ተማሪ እያለሁ ከወጣት የፍልስጤም ማሪዎች ጋር ጓደኝነት ጀመርኩ፡፡ በተለየ የቀረብኩት እንደኛው ለ CIA እንደምስራ ንም ነገር አያውቅም ነበር፡፡ እሱ በአረብኛ ቋንቋ ሲረዳኝ እኔ ደግሞ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ረዳው ነበር፡፡ በጆርጂታውን በተለያዩ ቡናቤቶች አብረን ተዝናንተናል፡፡ እንዲሁም ነረብን የምግብ ባህል አሰራርን አስተምሮኛል፡፡ ጓደኝነታችንን የበለጠ ያጠነከረው ግን መመረቂያ ወረቀቱን ሲሰራ ስለረዳሁት ነበር፡፡ እኔ የምሄድበት ጊዜ ሲደርስ ግን ረጠረኝ መሰለኝ ገሸሸ ማለት ጀመረ፡፡ ወደ ምሄድባትም ከተማ እዚያ የሚኖር ካሊድ ጊባል ወንድም እንዳለው አድራሻውንና የስልክ ቁጥሩን በተጨማሪም ካሊድ ምንኛውም የደህንነት ችግር ሲረዳኝ እንደሚችል ነገረኝ፡፡

እኔም እንደደረስኩ ወዲያውኑ ለካሊድ ደወልኩለት እሱም ወዲያውኑ እኔን ገኘት ጓጓ ካሊድም ያጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ በፍልስጤም ውስጥ ያለ የአሸባሪ ቡድን ል ነበር፡፡ ሁለታችንም እንደምናውቀው ከ CIA ሰራተኛ ጋር መገናኘት ከፍተኛ ቅጣት



t.me/OLDBOOKSPDF

ያስቀጣዋል፡፡ ነገር ግን ወንድሙ ስለነገረው ኃላፊነቱን በመውሰድ እንገናኝ በመካከለኛው ምስራቅ የተማርኩት ነገር ቢኖር አንደኛው ይህ ነው፡፡ አንድን ሰው ለአንድ ነገር ስራ አትመለምለው ጠቅላላ ቤተሰቡን፣ ዘሩንና ጎሳውን ጨምሮ እንጂ፡፡

አንድ ቀን ከዕኩለ ሌሊት በኋላ በመኪና እየተዘዋወርን መረጃዎችን ለመቃረም እያግባባሁት ሳለ ድንገት በሐሳብ ጭልጥ ብሎ ከሄደበት የሐሳብ ትካዜ በመባነን አቡ ኒዳል የሽብር እንቅስቃሴ እንዳቀደ ሹክ አለኝ፡፡ ይህንንም ሲነግረኝ መንፈሱ መረበሹ ከፊቱ ይነበብበት ነበር፡፡ ካሊድ መረበሹ በጣም ትክክል ነበር፡፡ አቡኒዳል በ CIA የሽብር ጥቃት ቀንደኛ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ጨካኝ ገዳይ ሲሆን በለንደኑ የእስራኤሉን አምባሳደር ላይ የግድያ ሙከራ ያደረገ የነበረና አሁንም አጋጣሚው ቢመቻችለት ከመሞከር ወደ ኋላ የማይል ጨካኝ ሰው ነበር፡፡

ካሊድ ከመኪናው እንዲወጣ ስፈቅድለት የአቡኒዳን አድራሻ ሰጠኝ፡፡ ለጀን አንድም ቃል ሳልተነፍስ በሚቀጥለው ቀን አድራሻውን ለማረጋገጥ በአቅራቢያው ተዘዋወርኩኝ፡፡ ምንም እንኳን ባለ 3 ፎቅ በከተማው የተለመደ አፓርትመንት ህንፃ ቢሆንም በህንፃ መተላለፊያ ላይ መግሪያ ይዞ የቆመ ጠባቂ ከመንገዱ ሆኖ ማየት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ህንፃውን የመንግስት ቢሮ እንደሆነ የሚገልፅ ስለሌለ ያልተለመደ መሆኑ መጥፎ አይደለም ልክ ካሊድ እንዳለው ስለሆነ፡፡

ሁለት ተጓዳኝ ህንፃዎች ከአቡ ኒዳል ቢሮ ጋር ይጋራሉ፡፡ ከሁለቱ አፓርትመንቶች ወደ አንዱ የመግባት እድል ካገኘህ ድምፅ በሌለው መሰርሰሪያ የመሰርሰር ጉዳይ ነው ከዚያም የድምፅ መቅጃ ማስቀመጥ ስራውም በጣም ቀላል ነው የሚሆነው፡፡ በጥቂት ቀዳዳ መሳሪያ በመግጠም ከዚያም ከግድግዳው ጋር ብርጭቆ በማስቀመጥ መስማት ይቻላል፡፡ እናም እኔ ወደ ቢሮ እንደተመለስኩ እቅዴን በማብራራበት ወቅት ጆን በአርምሞ ይመለከተኝ ነበር፡፡ መንግስት ይኼንን የሚያረጋግጥበት ምንም መንገድ የለም ብሎ አካለበኝ፡፡

«መንግስት ምን ሊያደርግ ይችላል፡፡» ብዬ መለስኩለት ምናልባትም በተሳሳተ መልኩ ተረድቶኛል ብዬ በማሰብ፡፡ «አንድ ወኪል እግኝተናል አዋሳኝ ከሆኑት አፓርትመንቶች አንዱን ሊከራይ የሚችል የቴክኒክ ቡድን በማምጣት መሰርሰር፣ ድምፅ የሚያጎላ መሳሪያ በቀዳዳው ላይ መግጠም ከዚያም እጆቻችን በማጣመር መከታተል፡፡

«ቦብ! የፖለቲካ ትኩሳት ባለበት ሁኔታ ተራ የሚባል ሃሳብ የለም፡፡ ይህች አገር ለአሜሪካ በጣም ጠቃሚ ናት እንደዚህ ዓይነት ኃላፊነት በመውሰድ ማንም ራሱን ለአደጋ የሚያጋልጥበት ምክንያት የለም፡፡ በሰላም ሂደቱ ላይ የተሳሳተ እርምጃ በመውሰድ ማንም አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ አይገባም፡፡

በግልፅ አሁን ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ ማየት እንዳለብኝ አስቧል ነገሩን እንደፈለገው ይሁን ብዬ ልተወው አስቢ ነበር እርሱ እኔን ለመለመን ሲሞክር፡፡ «ቀላል በሚባሉ ኢላማዎች ላይ በጥሩ ሁኔታ መስራት ይቻላል፡፡» አለኝ፡፡ የአውስትራሊያ ብሔራዊ ቀን ደርሷል፡፡ ለምን በግብዣው ላይ አትገኝም?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እየቀለድክብኝ» መሰለኝ አልኩት «በአውስትራሊያ ኤምባሲ ግብዣ ላይ በእግዚአብሔር ስም ማንን እንዳገኘ ትጠብቃለህ?» አልኩት፡፡ ጆን ከላይኛው መሳቢያ ውስጥ ዕራፊ ጨርቅ አውጥቶ የፈረደበትን ያንን መከረኛ ጫማውን መጠራረግ ጀመረ ይህንን ሲያደርግ የንግግራችን መቋጫ እንደሆነ ገባኝ፡፡

☼☼☼

ከፍንዳታው ከአራት ቀናት በኋላ ከባህር ኃይል ወታደሮች የጦር ሰፈር ላይ ሆኜ ከቢሮዬ መስኮት በአዲሱ ስራ ላይ ሆኜ ዙሪያ ገቡን እቃኝ ነበር፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ ሰዓቱ ቀትር ላይ ስለነበር ሁሉም የፀሐይዋን ግለት በመሸሽ ወደ የቢቱና ወደ ጥጋ ጥጉ ተከትተዋል፡፡

እዚህ በመካከለኛው ምስራቅ ህይወት ከትላልቅ ግድግዳዎች በስተጀርባ፣ ከእንግዳ ሰዎች እይታ ውጪ በተለይ ከውጪ አገር ዜጎች ውጪ ህይወት ትቀጥላለች፡፡ መካከለኛው ምስራቅ ዕውነታውን ለመሸፈን የታጠረ ቦታም ጭምር ነው ቴሌቪዥንና ጋዜጦች ዕውነተኛ ዜናዎችን አያስተላልፉም፡፡ የሚያስተላልፉት ነገር ቢኖር መንግስት ሊነግራቸው የሚፈልገውን ፕሮፖጋንዳ ብቻ ነው፡፡ የምርመራ ሪፖርቶችንማ ፈፅሞ አያቀርቡም፡፡ ስለፖለቲካም ይሁንና ስለ ማህበረሰብ የሚያወሩ መጸሀፍትን ለማንበብ ለእነሱ ጠቃሚዎች አይደሉም፡፡ የመካከለኛው ምስራቅ ሰዎች ስለራሳቸው ብዙ ካላወሩ ጥሩ ነው፡፡ ስለፖለቲካ ያወራሉ ይሁንና ስለ ሽብርትኝነት እንኳን ለማውራት ግንዛቤ ውስጥ አያስገቡትም፡፡ በእነርሱ ዓይን ሽብርተኝነት የመንግስት ስራ ነው፡፡ ስለዚህ አስተያየት ከመስጠት ይቆጠባሉ ምክንያቱም ዘብጥያ እንደሚወርዱት የውቋታልና፡፡

ምንም እንኳን በመረጃዎቻችን ብንተማመንም በዚህ ረገድ CIA ስለ ኢራን አዲስ የእገታ ዘመቻ ምንም የመረጃ ፍንጭ የለውም፡፡ በባላባከ ምን እየተደረገ እንዳለ ለማወቅ በሳተላይት የተደገፈ ጥቁርና ነጭ ፎቶግራፎች ከዋናው ጽ/ቤት በየጊዜው የሚልኩልን መረጃ በርግጠኝነት የሸኪህ አብደላህ የጦር ሰፈርን የምናይበትን አቅጣጫ ጠቁመውናል፡፡ በጊቢው ውስጥ የቆሙትን መኪኖችና በአካባቢው የሚዘዋወሩትን የሰዎች ጥላ እንዲሁም ወታደራዊ እንቅስቃሴውን መከታተል ይቻላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ከ90 ማይልስ ከፍታ ሆኖ አንዱን የወታደር ልብስ ከሌላው መለየት ያስቸግራል፡፡ ለህገር ውስጥ ዜና ካልሆነ በስተቀር የኢራኑ ፓስዳራን የጦር ሰፈሩን መቆጣጠሩን በፍፁም ልናውቅ አንችልም ነበር፡፡

ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን እንዲሁም ለወደፊቱ በህንፃዎቹ ውስጥ ምን እየተደረገ እንዳለ የፎቶግራፎቹ መረጃዎች ምንም አይናገሩም ወይም በእነዚህ ህንፃዎች ውስጥ ማን እንዳል አይታወቅም፡፡ ይኼንን ለማወቅ ግን የሰው ኃይል ያስፈልጋል እኔም እንዳየሁት ከሆነ አንድ ነገር ለማግኘት ከግድግዳው በስተጀርባ ምን እንዳለ በመገመት እውነቱን ከማድበስበስ መታቀብ እንዳለብን ተገንዝቢያለሁ፡፡ እናም ወደ ሊባኖስ ምድረ ቢካ ሸለቆ ትላልቅ ውሻዎችን ማሳደድ ከፈለጋችሁ ከሰፈር ውጡ፡፡

☼☼☼



t.me/OLDBOOKSPDF

የጆንን በር ሳንኳኳ እሰደነግጥኩት መሰለኝ፤ ምክንያቱም ስለ እቡኒዳል ጉዳዩች ስለተናደድኩበት ግንኙነታችን እንደመሻከር ብሎ ነበርና፡፡ ከዚያን ግዜም ጀምሮ እሱን የተገናኘሁባቸው ጊዜያቶች በጣም ውስን ናቸው፡፡ እሱንም ቢሆን አንዳንድ ነገር ይገፍለት ስገባ ብቻ ነው፡፡

«የእኔ ወደ ሊባኖስ-ቢካ ሸለቆ ጉዞስ እንዴት ነው»? ስል ጠየኩት፡፡ የፈረደበትን የጫማ መወልወያ ጨርቁን እወጣ ጫማውን ካፀዳ በኋላ በመጨረሻ «የእኛ ቦታ አይደለም እንደምታውቀው ቤሩት ይሄንን ነገር አትወደውም፡፡» አለኝ ቀና ብሎ እንኳ ሳያየኝ፡፡

ምናልባት ሊሆን ይችላል ነገር ግን እኔና ጆን ሁለታችንም እንደምናውቀው በቤሩት የሚገኘው የ CIA ቢሮ ምንም ቦታ የለውም፡፡ እስካሁን ድረስ ከጥቃቱ አላገገመምና የቢሮ ሰራተኞች በየሁለት ወሩ ይዘዋወራሉ እንዲሁም ከአዲሱ ኤምባሲ ለአንድ ወይም ለሁለት ወር ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ማንን እያደንኩ እንደሆነ ስለ እኔ ለመጨነቅ ማንም ጊዜ አልነበረውም፡፡

ስለ ሐሳቡ የበለጠ እያሰበበት በመጣ ቁጥር የበለጠ ለመቀበል ያጉረመርም ነበር፡፡ አንድ ነገር ስሰራ ቤሩት ውስጥ ብያዝ ኖሮ እባረር ነበር ይህ ደግሞ የእርሱ ችግር አይሆንም ነበር፡፡ (ርቄ ብባረር ኖሮ ችግሩን ምናልባት ይፈታ ነበር) እንዲያውም በቤካ ሸለቆ የማደርገውን ማነፍነፍ መቀበል ነበረበት ይህም አሜሪካ ከሊባኖስ መንግሥት ጋር ያላትን ግንኙነት እንደማይጠመዝዝ ጆን በመጨሻ ላይ ለአጭር ጊዜ ተስማማ፡፡ ነገር ግን በኪካ ሸለቆ ውሰጥ የምትገኝ በደማስቆና በቤሩት መንገድ ላይ ሺትዋራህ የምትባል ትንሽ ከተማ ከባላባክ አርባ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ብትገኝም በትንሹም ቢሆን በር መክፈት ያስችለኛል ብዬ አሰብኩ እንደውም ማን ያውቃል በለስ ሊቀናኝ ይችል ይሆናል፡፡

በአመታት የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት የሺ ታወራህን የንግድ ማዕከል ማንም አልደፈራትም ነበር፡፡ የሶሪያ ምርጥ ሰዎች የሚገበያዩት እዚያ ነው፤ የተባበሩት መንግስታት ሰራተኞች፣ የእርዳታ ድርጅቶች፣ ከቤሩትና ከደማስቆ የመጡ ዲፕሎማቶች እንዲሁም ይገበያያሉ፡፡ በሺታውራህ ሁሉ አለ ከአሜሪካ የማጽጃ ኬሚካሎች እስከ ስዊዝ ቸኮሌት እዚሁ ይገኛል፡፡ የኩባ ሲጋራ (ቶስካኖ) በለንደን ሱቆች በሚገኝበት ዋጋ እዚህም ይሸጣል፡፡ ማንኛውንም ገንዘብ በሸዋርታን ባንክ ከዙሪክ በተሻለ ዋጋ መመንዘር ይቻላል፡፡ የጦር መሣሪያ መግዛት ከፈለጋችሁ ከሽጉጥ እስከ ሮኬት ላውንቸር ወይም ሌላ የምትፈልጉት የኮንትሮባንድ እቃ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ ፍላጎታችሁ የሐሺሽ ዓይነት ከሆነ በፓርክ ሆቴል ውስጥ የልዩ ልዩ አገልግሎቶች ሰራተኛውን መጠየቅ ብቻ ነው ከእናንተ የሚጠበቁ ከሱቆችዋ ባሻገር ሸዋትራን ከሌሎች ቢካ ከሚገኙት የተለየ የሚያደርጋት ነገር የለም፡፡ እናም እዛ በደረስኩበት ቀን በከተማው ዳርቻ ከሚገኘው ከተወዳጁ የፍልስጤም ነፃ አውጪ ግንባር ጠቅላይ ማዘዣ ጣቢያ ባለፍኩበት ጊዜ ልክ እንደዕቶን የሚጨስ ነገር አስተዋልኩኝና ባቅራቢያ የሚገኘውን ጋሻሊን የሚባልን አረብ ጠየኩት እሱም ኤፍ-16 የተባለው የዕስራኤል የጦር ጀት ተመትቶ እንደወደቀ ነገረኝ ምንም እንኳን እኔ በአግራሞት ብመለከትም እርሱ ግን ያስጨነቀውም አይመስልም፡፡ ተጨማሪ መረጃም ፈልጌ ብጠይቀውም ትክክለኛውን በመስበት ስራ ላይ ነኝ አለኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በእርግጥ የጋሃዛሊ መልስ ትክክለኛ ስሜቱ ነበር፡፡ በቢካ ውስጥ ያሉ የሊባኖሳውያን ጎረቤቶችን የሚያጠቃልል እንደ ሂዝበላህ፣ የጃፓን ቀዩ ጦር፣ ባዕደር ማኒሆፍ፣ ሴንድሮ ሊሚኖሶ፣ ኤፍ.ኤል.ፒ፣ አቡኒዳል፣ ኢሳላ፣ እና ሌሎችም አጥፍቶ ጠፊዎችና ዘር አጥፊ አሸባሪዎች ሁሉ ምንም አልተመዘገቡም፡፡ የእስራኤል አየር ሀይል ወደ ፊት መተከስ እስከቀጠለ ድረስ ሊባኖሳውያን የህይወታቸውን ደህንነት የሚጠብቁበት ጥቂት ገንዘብ ካገኙ ሊበቃቸው ይችላል፡፡ የጋሃዛሊ ፀሐፊዎች ዑ-ኤም.ኤም ከፊል አውቶማቲክ ሽጉጥ በማህደራቸው ውስጥ ይዘዋል እንዲሁም የእርሱ ምክትል ቢሮው የጥይት መከላከያ የተገጠመለት መስኮት ያለው ኤኬ-47፣ በጠረጴዛው ላይ ደግሞ መዕሂቶች አስቀምጧል እናም በመተላለፊያው መንገድ ላይ ሁሉ እሳት ሊጫርበት የሚችል ነው፡፡

በዚያ የመጀመሪያ ቀን ጉብኝቴ ለጊዜውም ቢሆን ወደ ሽትዋራህ እመራሁ ከዚያም በቤሩት ዋናውን መንገድ ይገፔ ወደ ተራራው ማሽከርከሬን ተያያዝኩት ምንም እንኳን ባላባክን ለማየት ጨጋጋማው የአየር ንብርት ቢጋርደኝም በቢካ ሽለቆ ትይዩ ዞሬ አንድ ሬስቶራንት ተቀመጥኩኝና ምግብ አዘዝኩ አስተናጋጁም በሰሃን ምግብ ሲያመጣልኝ ሬስቶራንቱ ተንቀጠቀጠ፣ መስኮቶቹና ማንኪያዎቹም ሳይቀሩ ተንቀጫቀጩ፡፡ አስተናጋጁም ምንም እንዳልሰማ ለማስመሰል ማዶ ማዶውን ያይ ጀመር ይሁንና አውቆ እንደነበር ፊቱን ለማንበብ ችዬ ነበርና፡፡ ከዚያም «የእናንተው ኒውጀርሲ» ብሎ አንሾካሾከኝ፡፡

የዩኤስኤስ ኒውጀርሲ በሊባኖስ ድንበር ላይ የቆመ ያማረ የሁለተኛው አለም ጦርነት የአሜሪካ የጦር መርከብ ነው በየጊዜውም ወደ ቤሩት ተራሮች የጦር መሣሪያ ያቀብላል፡፡ የዋሺንግተን ሀሳብ ኒውጀርሲ ጃፓኖችን በሁለተኛው የአለም ጦርነት እንዳስፈራራቻቸው በተመሳሳይ እስካሁን ድረስ የሐምሌ 17ቱን ስምምነት ለማይቀበሉት ሊባኖሳውያን ማስፈራሪያ እንዲሆን ታስቦ ነበር፡፡

ከምሳ በኋላ የህገሬውን ሰው ለማግኘት ጊዜው እደሆነ ወሰንኩኝ፡፡ ከሽዋትራህ አልፎ ጥቂት ማይልስ በማሽከርከር ወደ ባርሊያስ ወደምትባል መንደር ሄድኩኝ፣ በማዕዘኑ ላይ ወደቆሙት ሁለት ፖሊሶች ተጠጋሁ፡፡ ራሴንም አሜሪካዊ መሆኔን ሳስተዋውቃቸው ከመርከቧ አሁን ገና የወረድኩ መሰሏቸው ወደ ማስና አመለከቱኝ፣ ማስና ለሶሪያ ድንበር የመጨረሻዋ ከተማ ስትሆን የሊባኖሱ ሱሬቲ ጀነራል ቢሮው እዚያ ነው የማስናው ሱሬቲ ህንፃ በ1982 ብዙ ቀጥተኛ ጥቃቶች ስለማስተናገዱ አሁን ድረስ ፈጥጠው እግጥጠው የሚታዩት አሻራዎቹ ያሳብቁበታል፡፡ ቀይ ጣራው ተገነጣጥሎአል፣ ሁሉም መስኮቶች ተሰባብረዋል፣ የጋዮ መኪኖችም በየስፍራው ተጥለው የመኪና ማቆሚያ ስፍራውን አስቀያሚ አድርገውታል፡፡ እምሣ አለቃ አሊ ከፊት ለፊት ፀሐይ እየሞቀና ሲጋራውን እያምቧለቀ በሀሳብ ተመስጧል፡፡ ወደ እርሱም በቀረብኩበት ጊዜ በጣም ተግባቢ ሰው ነለመሆኑ ለመገንዘብ ችያለሁ እኔም ከአሊ ጋር በዝምታ ድባብ መንገዝ ጀመርኩ ዝምታዬንም ለመስበር ስል እንጀር ጠየቁት፡፡ ይህ በአቅራቢያው ያለ መንደርና የጥንት ሮማውያን የንግድ ስፍራ እንደነበር የሚታወቅ ነበር፡፡ ጥቂት ቅሪቶችም ይገኛሉ፤ ይህም ምዕራባውያን እንግዳ ነገር አይሆንም ነገር ግን እንጃር ከጥቂት ለአሜሪካ ጠላት ባልሆኑ ሽባሪ ቡድኖች ካልተያዙት በቢካ ከሚገኙት መንደሮች አንድ ነው፡፡ እሳላ የአርመኖች



t.me/OLDBOOKSPDF

የአሸባሪ ቡድን ሲሆን በሐምሌ 1983 ፓሪስ ስፍራ የመሸገ ነገር ግን ከአሚካ ጋር ምንም አይነት ችግር የሌለበት ነው፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ መሪዎች አሜሪካዊ ዜግነት ያላቸው ነበሩ፡፡ ባለባከ ለእኔ ፅኑ ፍላጎት ከማሳደሩም በላይ በተለየ መልኩም እንድቀርባት ውስጡቴ ገፋፍቶኛል፡፡

አሊ ወደ ቢሮው በማምራት በትንሽ ብርጪቆ ስኳር የበዛበት ሻይ ጋበዘኝ ስለአሜሪካ ማውራትም ፈልጓል፡፡ እንደነገረኝ ከሆነ በሚችጋንና በኒውጀርሲ የሚኖሩ ብዙ እኅቶች እንዳሉትና እርሱም ነገር-ሁኔታዎች ቢመቻቹለት ወደዚያው ለማቅናት ሀሳቡ እንዳለው አጫወተኝ እኔም ስለ አንጃር መጠየቁን ተውኩትና አሊ እንደልቡ እንዲናገር ፈቀድኩለት ይሁንና እሱ ግን ጨዋታውን የማያቆም መስሎ ሲታየኝ ግዜ ለመሄድ ከመቀመጫዬ ተነሳሁና በሚቀጥለው ጊዜ በማስና እንደምንገናኝ ቃል ገባሁለትና ተሰነባበትን እሱም ስራ ላይ መቼ መቼ እንደሚገባ ቀናቶቹን ነገረኝ፡፡

በምመለስበት . ወቅት ለአሊ የአሜሪካንን ቪዛ ለማግኘት የሚቻልበትን የማመልከቻ ቅፅ እና ለጎብኝዎች የሚሆን በራሪ ወረቀቶች አመጣሁለት ይሁንና ቪዛ እንዲሰጠው ልረዳው እንደምችል ቃል አልገባሁለትም ነገር ግን ወረቀቶቹን ስሰጠው ግልፅ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ከአንድ ሰዓት በላይ ስለ አሜሪካ ብቻ ሳይሆን ስለ መካከለኛው ምስራቅም በማውራት አሳለፍን፡፡ አሊ ስለ ባላባክና ስለ ኢራን ምንም ትንፍሽ አላለም እኔም እንዲሁ ምንም አልተናገርኩም እናም ወደ በሩ እየወጣሁ ሳለ አሊ አንድ ወረቀት እጄ ላይ ሰጠኝ የእርሱን ሙሉ ስሙንና የቤት ስልክ ቁጥሩን ፅፎበት ነበር ከዚህ በኋላ ነበር ከሁሴን አልሙሳዊ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው የተገነዘብኩት፡፡ ይህ ሰው የኢራኑ ፓስዳራን ወኪል ሲሆን የሽክ አብደላህን የጦር ሰፈር ተቆጣጥሮ የያዘው ሰው ነበር፡፡

አሊን በየጥቂት ሳምንታት ውስጥ በየጊዜው እጎበኘው ነበር፡፡ እሱም አሜሪካዊ ጓደኛ ማፍራቱን ወዶታል እናም እኅቶቹን ለመጠየቅ ወደ አሜሪካ ለመጓዝም ማሰብ ጀምሯል፡፡ ምን ያህል ልረዳው እንደምችልም ለማየት ዙሪያዬን መዞር ጀምሯል፡፡

እስከ ጥር ወር ድረስ በመካከላችን ያለው ንግግር ምንም እንዳች ፍሬ ነገር አልነበረውም ነበር፡፡ እንዲሁ ከአሊ ጋር ሻይ ከፊታችን አስቀምጠን እናወራለን እናም በባላባክ ውስጥ የፀሀይን ቤተመቅደስ ለመጎብኘት ተጋብዤ እንደነበር ነገርኩት፡፡ በእርግጥ አልተጋበዝኩም ነበር ነገር ግን ስላቀድኩት ግብ ዙሪያ የማወራበት ጊዜ ስለነበር ነው ምንም ዓይነት የደህንነት ችግር እንደሌለም ጠየቅሁት ምንም ቃል ሳይናገር ክንዴን ይዞ ከቢሮው በስተጀርባ እርቀን ሄድን በሁለት የፍርስራሽ ክምር መካከል ሆነን አወራን፡፡

«ሚስተር ቦብ መሄድ አትችልም» አለኝ ከፉኛ አዝኖ፡፡

«ለምን አልሄድም» አልኩት

«ለአሁን የሮማውያንን ቅሪቶች እርሳቸው፡፡»

«ለምድን ነው አሊ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

ተጨማሪ ነገሮችን ማውራት ለእርሱ አስቸጋሪ ሁኔታን እንደሚፈጥርበት ከሁኔታው እንበብቡና ተለሳለስኩበት እሱም፣-

«በፍልስጤም ውስጥ ያለ አንድ አሜሪካዊ ሊያገኙ ነው በመጨረሻም እንዲህ በማለት አንሾካሾከኝ አንድ ወኪል ነው»

እውቃለሁ ማንን? እንዴት? እና መቼ? በማለት ለማስጨነቅ አልፈልግም ከዚህ በላይ ምን ይነግረኛ?

☼☼☼

«ይህ የማይረባ ነገር ነው አለ ጆን፡፡

«ጆን ይህ ሰው ሙሳዊ ነው፣ እርሱ የመጣው ከባለባክ ነው፡፡ አንድ ነገር አግኝቶ ሊሆን ይችላል ይህንን መረጃ ከእጃችን ማጥፋት የለብንም፡፡ በመረጃ ሪፖርታችን መግፍ አለብን፡፡»

«ይኼንን ምናምንቴ እስቲ ተመልከቱት ምንም የተጨበጠ መረጃ እንኳን አልያዘም ይህ የተመሰመሰ የመረጃ ምንጭ አይደለም፡፡ የተወለደበትን ቀን እንኳን አታውቅም ይህን እንደ መረጃ አድርጌ እንዳስተላልፈው አትጠብቅ፡፡ ተመልሰህ ሂድና ስለትውልዱ የምትጠላውን የወረቀት ስራ ሰርተህ ና ወደ እኔ ከዚያም የሚሆነውን እናያለን፡፡»

ስለምንም ለማውራት ምንም ነጥብ አልነበረም ፒ ኦ ኤ እዚህ ጋር ምንም ትርጉም ሊሰጠው አይችልም እሲ ወኪል ለመሆን ምንም ፍላጎት የሌለው ነው በየጊዜው አንዳንድ መረጃዎችን ሊሰጠኝ ይችል ነበር ነገር ግን ለዘሩ ለሙሳዊስ በጣም ታማኝ ነበር፡፡ የትኛውም መረጃ የተሳሳተ እንዳልነበርና ራሴንም በኃላፊነት እንዳያስጠይቀኝ የእሲ ማስጠንቀቂያ በኤምባሲ ውስጥ ላለውና ይኼንን መረጃ ለላኪው ጓደኛዬ በዋሽንግተን በኩል ለመንግስት እንዲሰጥ አስተላለፍኩ፡፡ የቆንስላ ጉዳዮች ኃላፊ እንሳውና ከቆንስላ ጉዳዮች ጋር አስቀመጠው፡፡ ይህች የመጀመሪያዋ ወረቀት ነበረች እድጋ የ CIA ትልቅ የእገታ መረጃ የሆነችው፡፡

☼☼☼

ሚያዚያ 16,1984 ጠዋት 4:38 ላይ ሦስተኛ ቡናዬን እየጠጣሁና ሄራልድ ትሪቡን ጋዜጣ እያነበብኩ ሳለሁ፤ ሞቶሮላ ስሪት የሆነችው የራዲዮ መልዕክት መገናኛዬ እንጫረረች ጆን ነበር «በቻልከው ፍጥነት ወደ ቢሮ ተመለስ፡፡» ጆን ሁል ጊዜ ሲናገር የተቆጣ ነው የሚመስለው አሁን ግን በፍፁም መረበሽ ይታይበታል፡፡

እኔም ቢሮ በደረስኩበት ቅፅበት ጆን የታመመ ያህል ፊቱ የገረጣ ሆኗል «ባክሌይ እገታ ተፈጽሞበታል» አለኝ ቴሌ ግራሙን እየሰጠኝ፡፡ በዚያ ጠዋት ቢል ባክሌይ በቤሩት የ CIA ዋና አዛዥ ከሚኖርበት የአፓርተመንት ህንፃ ሲወጣ ጭንቅላቱን በመምታት፣ አስገድደው በመኪና ይዘውት ሄዱ፡፡ ምንም ሰው የመኪናውን ታርጋ ወይም



t.me/OLDBOOKSPDF

የአጋቾችን ማንነት ያወቀ የለም፡፡ የኢስላም ጂሃድ ድርጅት (ኢጃድ) ለኤምባሲው ፍንዳታ እንዲሁም የበክሊይን መታገትንም ኃላፊነቱን ወስዷል፡፡ ነገር ግን ይህ ግለት ምንም ነገር ሊነግረን አይችልም፡፡ እስካሁን ድረስ ስለ ኢጃድ ምንም ነገር አናውቅምና፡፡

ከ1982ቱ የእስራኤል ወረራ ከተፈፀመ ጊዜ ጀምሮ በክሊይ ሲታገት የመጀመሪያው አሜሪካዊ አይደለም፡፡ እነ-ዴቪድ ዶጂ፣ ፍራንክ ሬጀር የኤሌክትሪካል ኢንጂነር የሆኑ አሜሪካዊ ፕሮፌሰር በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ በቤሩት ውስጥ ይሰሩ የነበሩ አንዳንድ በየካቲት 1984 ታግተው ነበር፡፡ የ CNN ቢሮ ዋና ኃላፊ ጀርሚ ሌቪን ከወር በፊት ተይዘው ተወስደው ነበር፡፡ ነገር ግን ተራዜንች ነበሩ ይህ ልክ እንደቤተሰብ አባላት በሚስጥር የታጨቁ ናቸው፡፡

«ወደ ቢካ ሸለቆ ተመልሼ አሊን ማግኘት አለብኝ ጆን ስለው ልክ አዕምሮውን እንደሳተ ሰው ጆን» በአርምሞ ተመለከተኝ፡፡

«እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ የለብንም በማለት ሳያቋርጠኝ አነበንብኩ ሶሪያ እንዴት ቢካን እንደምታስተዳድር በአይኔ ራሴ አይቻለሁ፡፡ በራሷ ስልጣን እስካለ ድረስ በአንድ የውጪ ዜጋ ላይ ምንም አይነት እርምጃ እንዲወሰድ አትፈቅድም፡፡ በክሊይ እና ሌሎችም በቤሩት ታግተዋል፤ ሶሪያ ምንም ጦር በዚያ የላትም፡፡ ጆን ሊታሳውቀኝ ይገባ ነበር፡፡» ስል አንባረቅኩበት፡፡

«እርሳው እርሱን» አለ ጆን እያቋረጠኝ «ወደ ዋሽንግተን እጠራለሁ ብጠይቃቸው እንኳን ያለምንም ማመንታት ይነግሩኛል፡፡»

አካባቢውን ቃኘሁና ወደ በሩ አመራሁ ትክክል ነበር፡፡ ዋናው ቢሮ ይኼንን ሊፈቅዱ አይችሉም፡፡ ማንኛውንም እንቅስቃሴ በሊባኖስ ያለውን በተቻለ መንገድ መዝጋት ነበር የሚፈለገው፡፡

ለሚቀጥሉት ሰባት ወራት ስለ በክሊይ አንዳች ፍንጭ አልተገኘም፡፡ እርሱ ስለመታገቱ ብቻ አይደለም ነገር ግን በሊባኖስ ውስጥ ስለመኖሩ እርግጠኛ አልነበርንም፡፡ CIA ወደ እያንዳንዱ መንግስትና የግለሰብ ምንጮች ሁሉ ሄዷል ነገር ግን ማንም ሰው ምንም አይናገርም በሀሜት መልክ እንኳን አይሰማም፡፡ እንደ እኔ እንደ እኔ ከሆነ ባላባክ ፍለጋ ለመጀመር ጥሩ ስፍራ ይመስለኛል እናም ስለ እገታው የበለጠ ባወቅሁኝ ቁጥር የበለጠውን በነፃነት መውጣት መግባት እችላለሁ በመጨረሻ ለማየት ያለኝ ፍላጎት የተሻለን ነገር ያመጣልኛል ብዬም አሰብኩ፡፡

በመጀመሪ ያደረኩት ነገር ቢኖር ....... ን ለማግኘት ማመቻቸት ነበር እርሱ የ ...... አሜሪካ ነው፡፡ ከፊሉ የቤተሰቡ አባል በቢካ ውስጥ ከሻኢቲ ጎረቤቶቻቸው ጋር ግሳዊስን ጨምሮ በሰላም ይኖራሉ፡፡ በራስ መተማመን ተሰማኝ በ ....... ሁኔታ ፓስፖርን ኒነኩኝ እንኳን የሚያስቡ አይመስለኝም፡፡ ምን ለማድረግ እንደምፈልግ ስነግረው ...... 'ተባለውን የሊላኛውን ዘመዱን ስም ጠራው እሱም የሊባኖስ የጦር ካፒቴት ሲሆን ኮለታችንም በሹዋትራን ተገናኘተን በካፒቴት መኪና ወደ ባላባክ ሄድኩኝ፡፡ ካፒቴት እኔ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማን እንደሆንኩ ወይም ባለባክን ለምን መነብኘት እንደምፈልግ ምንም ፍንጭ የለውም ነበር፡፡

ወደ ባለባክ በመኪና ማሽከርከር ወደ ሲኦል እንደመውረድ ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ከከተማው ውጪ ከመሆኑም በላይ አስፈሪና አስጊ የሆነ ሞት ሞት የሚሸቱ የግድግዳ ላይ ፅሁፎችና ምስሎች ከፍርስራሽ ህንፃዎችዋ ላይ ተስለዋልና ያው ተጠንቀቁ ነገር ነው፡፡ ለአብነት ያህል፡- የሚቃጠል የአሜሪካ ባንዲራ፤ የኢራኑ አያቶላህ ሆሚኒ በቴህራን ወደ አሜሪካ ኤምባሲ የተቃውሞ ሰልፍ ሲመሩ በደም የተበከለ የአሜሪካን ባንዲራ ....... ጽሁፎቻቸውንም የተመለከትን እንደሆነ በባለባክ የተሰቀሉት ጽሁፎች በአረብኛና በፋርስ ቋንቋዎች ሞት ለአሜሪ የሚል ነጋሪት የሚጎስሙ ናቸው ይህንን እየቃኘሁ ሳለሁ ካፒቴኑ ድንገት ከጓደኛው ቤት ምሳ እንድበላ እስተያየቱን ጠየቀኝ እኔም መስማማቴን በመግለጽ ላይ ሳለሁ ልክ ከሁሴን እል መሳዊ እንት ቤት ፊት ለፊት ነበርን፡፡

ወደ ውስጥ ስንዘልቅ በወለል ላይ የተቀመጡት በጣም ብዙ እንግዶች በሳሎን በኩል ስንገባ ሁሉም እኔን በጠላትነት ስሜት ተመለከቱኝ፡፡ ከወራት በኋላ ያዩት የመጀመሪያው ምዕራባዊ እኔ ሳልሆን አልቀርም፡፡ አንዳንድ ሲኒ ሻይ ከጠጣን በኋላ በሰሃን ላይ ባሮ ሽንኩርት ባቄላ እና ዳቦ (ፉል) መጣልን፡፡

እስከ አሁን ድረስ ነገሮች ሁሉ በመልካም እይሄዱ ነበር ከእንግዶቹ አንዱ በእኔ ላይ የተለየ ፍላጎት እስኪያድርበት ድረስ የተንዥረገገ ጺሙን እየሞዠረቀና እንዲሁም በክንዱ ላይ ያስነቀሰውን «ሰማዕታትን እናከብራለን» የሚለውን ንቅሳቱን እያሳየኝ ለጥቂት ሰኮንዶች በእኔ ላይ ካፈጠጠ በኋላ «ወደ ባላባክ ምን አመጣህ» ብሎ ጠየቀኝ፡፡ የተለመደ ውሸት ከምደጋግም ሌላ ትልቅ ውሸት መዋሸት እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡

«በዜግነቴ ቤልጂማዊ ነኝ፡፡ የምሰራው ለአንድ የእርዳታ ድርጅት ነው፡፡» ብዬ መለስኩለት ጣቶቼንም እቆላልፌ ዝም አልኩኝ ፈረንሳይኛ ወይም የፍላሚን ቋንቋ የሚናገር ሰለሌለ ግራ ቀኙን በማማተር ተኮፈስኩኝ እኔ ግን የፍላሚሽ ቋንቋ ቀርቶ ፊደሉን እይቼ አላውቀም የፈረንሳይኛ ቋንቋዬም ቢሆን የተሰባበረ ነበር፡፡

«ጌታዬ ስሞትን መጠየቅ እችላለሁ?» ባለ ሪዛሙ ንግግሩን በመቀጠል ጠየቀኝ

«ሚስተርሬሚ»

«ይህ የቤተሰብ ስምህ ነው?»

«አይደለም ማርቲን ነው» አልኩኝ ከማቆሜ በፊት፡፡

«ሬሚ ማርቲንኮኛክ በሊባኖስ ስለማይሸጥ ነው፡፡ ደግነቱ ምግብ ቀርቦልሃል ብላ እንግዲህ!» ከዚያም ወደ ፀሐይ ቤተ-መቅደስ ወሰደኝ እዚያም ከደረስን በኋላ በተዘጋው በአሮጌው በሮማውያኑ ባላባክ ስናንኳኳ ተከፈተልን በዚያ ውስጥም ሁለት ካኪ ዩኒፎርም የለበሱ ኢራናውያን ፓስዳራን ወታደሮች ነበሩ፡፡ ቦታውን ለእኛ የሚያስጎበኙበት ወቅትም



t.me/OLDBOOKSPDF

እነዚሁ ወታደሮች ደስተኞች አልነበሩም፡፡ እኛም በመኪናችን ወደ ከተማ እየወጣን ሳለ በየኮረብታዎች ላይ ስላሉት አጥር ግቢዎች ካፒቴኑን እልፎ እልፎ በምጠይቅበት ወቅት እንደማውቀው የሻይካህ አብዱላሂ የጦር ሰፈር ነው፡፡ በማለት መኪናውን በግድግዳው ዙሪያ አቆማት በዚህም አጋጣሚ ሁሉንም ህንፃ ለመቃኘት እድል አገኘሁ፡፡ ከሳተላይት የተነሳው ፎቶግራፍና አሁን እያየሁት ያለበት ሁኔታ ምን ያህል ልዩነት እንዳላቸውና እንደሚራራቁ አስደንቆኛል በተለይ አንዱ ህንፃ ትኩረቴን ስቦታል፡፡ ሁለት የፓኪስታን ወታደሮች የመግቢያ በሩን ይጠብቃሉ የመስኮቶቹን ውስጠኛ ክፍል ካርቶን ወይም ብርድልብስ ሸፍኖታል፡፡ በግድግዳው ላይ በእንጨት የተሰራ ምልክት ለተጋቡ ሰራተኞች ብቻ የተለየ ሰፍራ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ከዓመታት በኋላ እንኳን በክሊይ ውስጥ አይኑን ተሸፍኖ ከሞተር ማቀዝቀዣ ጋር ሌሎች አምስት ምዕራባውያን ታጋቾችን ጨምሮ ውስጥ መኖሩን አላወኩም ነበር፡፡ በተጨማሪም ይኸው ህንፃ ኤምባሲውን ላፈነዱት ሰዎች ዋነኛ መገናኛ ቁልፍ ሰፍራ መሆኑንም አላወኩም ነበር ነገር ግን በዕውነት እነዚህን ነገሮች ሁሉ ማወቁ አላስደነገጠኝም ነበር አግራሞትን አጫረብኝ እንጂ በመካከለኛው ምስራቅ እያንዳንዱ ነገር የተያያዘ ነው፡፡ አንዱን ክር ከመዘዝክ ሌሎች ብዙ ነገሮች ተከትለው ይወጣሉ አንዷን ነገር ስበህ ካወጣህ ሌሎች ብዙ ነገሮች ገሃድ ይወጣሉ፤ ይህም እያንዳንዱ ነገር በውጤታማነት ሊያስኬዱ ይችላል፡፡

ነገር ግን ይኼንን ለመስራት የደህንነት ሰው ያስፈልጋል አንድ ሰፍራ ሆነው የሚሰሩ፣ ወኪል፣ የወኪሉ ተቀባይ፣ የገሃዲዎች መረብ እንዲሁም ጉዳዩን ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ ሰራተኛ፣ የአየር ቅኝት ፎቶግራፍ ብቻውን የተሸፈኑትን መስኮቶችና የሚጠበቁትን በሮች በሼኪ አብደላህ የጦር ሰፈር ውስጥ ነገሩን ገሃድ ሊያደርጉት አይችሉም፡፡ በዚያን ቀን የሰዎች አይን በምድር ላይ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ሊሆኑ አይችሉም በባላባክ ውስጥ በመጨረሻ የስለላ ስራ ወደ ህዝቡ ሁሉ ሰርጿል፡፡ እንደማስበው በCIA ውስጥ የአባቶቻችን የተነሳሽነት መንፈስ ነበር በድርጅቱ ውስጥ የነበረው፡፡ አሁን ግን በተቃራኒው እንደመንጋ ዝም ብሎ መጓዝ ይመስላል በመካከለኛው ምስራቅ ጥፋትን አምጥቷል በመጨረሻም በአሜሪካ ምድር በራሷ ላይ ሊሆን ይችላል፡፡

☼☼☼

በግልፅ ለመናገር የባላባክ ጉብኝቴ በፊት የነበረውን ግምቴን ሁሉ ከንቱ ያስቀረ ነበር፡፡ ስለ ባለባክ እንደ አንድ ትልቅ ክፍታ እንዳስብና ይኼንን እውቀት ከሳተላይት ፎቶግራፎች ወይም ከመፅሐፍት ሊገኝ የማይችል ነገር ግን አደገኛና ባክሊይን ወይም ሌሎችን ሊረዳ የማይችል ነው፡፡

ከአጭር ጊዜ በኋላ ወደ ካርቱም ሱዳን ተዘዋወርኩ ጅን ስለ ባለባክ ጉዞዬ ምንም አላወቀም ነበር የሰጠኋቸው ምክንያቶችን ብቻ እንጂ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፺

## ጥር 1996 ፤ ሳንግሴይ - ቨርጂኒያ

ስድስተኛ ፎቅ የሚገኘው ኮሪደር የመልሶ ግንባታ የሚካሄድበት ስፍራን መስሏል። ሳጥኖች፣ ቁሳቁሶችን ጥቅል የስልክ ገመዶች እዚህም እዝያ የፍርስራሽ ክምርና የተመሰቃቀሉ ቁሳቁሶች ተከማችተውበታል ከኮሪደሩም ግራና ቀኝ ያሉ ቢሮዎች በቀለም ቀቢዎች በኤሌክትሪክና በቴሌ ቴክኒሻኖች ተጨናንቀዋል የግንባታ ሰራተኞች ወለሉን ይፈረካክሳሉ አናጺዎች ደግሞ የቢሮ መከፋፈያ ቦርዶችን እየቆረጡ በመጣል በምትካቸው አዲሶቹን ይገጥማሉ። የአዲሱ ፀረ ሽብርተኝነት ዘመቻ ሃላፊ ቢሮ የት እንደሆነ የሚያውቅ ሰው ባለመኖሩ ቢሮውን ፍለጋ ከክፍል ክፍል መዞር ግድ ነበረብኝ ይሁንና ቢሮው ካልተመሰቃቀሉት ክፍሎች ውስጥ አንዱ እንደሚሆን ገምቼ ነበር።

ቢሮውን ከፍቶ ለሚገባ ባለጉዳይ አየሩ ላይ ረበ የሚታየው የትምባሆ ጭስ አየር በረራዎችን የሚያስተጓጉል የወረደ ደመና መስሎ ሊታየው ይችል ይሆናል። ከሌሎቹ የCIA ባለስልጣናት በተለየ መልኩ የ«ዲዊ ክላሪጅ» ቢሮ የቢሮ ጠረጴዛ አልነበረውም። ከዚያ ይልቅ ክፍሉ መሃል ላይ ግማሽ ደርዘን ወንበሮች የከበቡት ክብ ጠረጴዛ ይገኛል። የዲዊ ቢሮው ከሌላው ለየት ማለቱ ወኪሎች ክፍሉ ውስጥ እንደልባቸው ዘና ብለው እየተንጎራደዱ ማውራት እንዲችሉ ያመቻቸ ይመስላል። ምክንያቱም ወኪሎቹ የተሻሉ ሃሳቦችን እንደሚያፈልቁ ተገንዝቧልና።

ዲዊ ምናልባት ስለቢሮው ማሽብረቅ አልተጨነቀበት ይሆን ይሆናል። ይሁን እና ከአብዛኛዎቹ የCIA ባለስልጣናት በተለየ መልኩ ስራው ከኋይት ሀውስ ጋር በቀጥታ ያገናኘዋል፡፡ የላቲን አሜሪካ ምድብ አዛዥ እንደመሆኑ መጠን የሮናልድ ሬገን ውድ ሃገርን ከጥቃት ለመታደግ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም፡፡ በ1985 ለኢራን በመርከብ ይጓጓዝ የነበረን ጦር መሳሪያ አነፍንፎ የደረሰበት ንቁ ሰላይ መሆኑ እንደአንድ ጀብዱ ተመዝግቦለታል፡፡ በጥቅሉ ዲዊ ኋይት ሃውስ የሚፈልገውን ዓይነት ንቁ ሰላይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በ1985 አቡ ኒዳል በቪየትናም እና ሮም አየር ማረፊያዎች ላይ ጥቃት ካደረሰ በኃላ ኋይት ሃውስ ዲዊን የአዲሱና ኃያሉ የCIA ፀረ-ሽብር ቡድን ሃላፊ አርጉ መሾሙም ማንንም አላስገረመም።

ዲዊ በሩ ላይ መቆሜን እንዳየ ወደውስጥ እንድገባና ክቡ ጠረጴዛ ጋር እንድቀመጥ ጋበዘኝ። ፈፅሞ ድብብቆሽ የማይመቸው ግልፅ ሰው ስለመሆኑ ሰምቼያለሁ።

«ሚስተር ዲዊ» በፀረ ሽብር ዘመቻው መሳተፍ እፈልጋለሁ የሚሰጠኝንም ማንኛውም ግዳጅ ለመወጣትም ዝግጁ ነኝ።» አልኩት ገና ለመቀመጥ ሳዘግም።

እውነታው ግን በሽብር ዙሪያ በሚካሄዱ ዘመቻዎች መሳተፍ መፈለጌ ሳይሆን በአለቆች ቢሮክራትነት መሰላቸቴ ነበር፡--ሲቢያዎች ከሲቢያ ተቃዋሚ ተወካይ ጋር ግንኙነት



t.me/OLDBOOKSPDF

ማድረጌን ካወቁ በኃላ እኔን ለመግደል ማሴር በመጀመራቸው ከአራት ወር ቆይታ በኃላ የCIA ዋና መምሪያ ከካርቱም እንድወጣ እንዳደረገኝና፤፤ ከዚያም ብዙም እንቅስቃሴ ከማይታይበት የአፍሪካ ምድብ ውስጥ ስራ እንደሰጠኝ፡፡ በተጨማሪም የቢል በክሊደን ፍሲጋቤ ከንቱ መቅረቱን ያም ጆንን እንዳበሳጨው እግረ መንገዴን ለ ዲዊ ነገርኩት፡፡

«ያ የተረገመ አሁንም አልተገኘም ነው የምትለኝ?» ሲል ዲዊ ጠየቀኝ ጥያቄውን ከመመለሴ በፊትም «የአረብኛ ቋንቋ ችሎታህ ምን ያህል ነው?» ሲልም አከለበት፡፡

የዐረብኛ ችሎታዬ ከዐረብኛ ትምህርት ቤት ከወጣሁበት ጊዜ በበለጠ መካከለኛው ምስራቅ ውስጥ ባሳለፍኳቸው ሶስት ዓመታት ተሻሽሏል አልኩት፡፡

«በማንኛውም ጊዜ ወደ ማንኛውም ቦታ ሂድ ብትባል ፍቃደኛ ትሆናለህ?»

«ከፈለግክ ዛሬውኑ ከላከኝ አውሮፕላን ቲኬት ለመቁረጥ ዝግጁ ነኝ፡፡» አልኩት፡፡

ዲዊም ማወቅ የፈለገው ይሄንን ነበር፡፡ እናም የእኔን መረጃ ያጨቀውን ዶሴ መክፈትም ሆነ ማገላበጥ አላስፈለገውም፡፡ ይሁንና ሁናቴውን እየሰራሁበት ላለው የምስራቅ ምድብ ማሳወቅ እችል እንደሆነ ጠየቅኩት

«እንዳትሞክረው» ሲል ቢሲጋራው ጭስ እጦልቆ አየኝ፡፡ ከሁለት ሳምንት በኋላም አዲሱን የዲዊ ድርጅትን ተቀላቀልኩ ማለትም ፀረ ሽብር ማዕከልን ወይም CTC' ን፡፡

☼☼☼

ዲዊ በማካሄድ ላይ በነበረው ፀረ-ሽብር ጦርነት እንደ አንድ እግረኛ ጦር አባል በተሳተፍኩባቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ጦርነቱ ምንያህል ፈታኝ መሆኑን ማወቅ ችያለሁ፡፡ የሽብርተኝነትን እስከፊ ገፅታ በቢካ ሽለቆ ተገኝቼ አይቻለሁ፡፡ በሁኔታው ተገርሜአለሁ ደንግጫለሁም፡፡ ከኤምባሲው የቦንብ ፍንዳታ ጀርባ ያለው ማነው የሚል ግላዊ ጥያቄዬን እንዳነሳም አስገድዶኛል፡፡ ለሁሉም ግን ቁልፉ ያለው በፀረ-ሽብር ማዕከል ነው፡፡ ከዚህም በላይ ዲዊ በሽብርተኞች ላይ መስሎ የታየውን እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ስልጣን ከCIA' ዳይሬክተር 'ቢል ኬዚ' ተሰጥቶታል ለሚወስደው ዕርምጃም የሚበቃውን ያህል በጀትም ተበጅቶለታል የዳይሬክቶሬት ኢንተለጀንሲንና የዳይሬክቶሬት ኦፕሬሽንን በመረጃ መረብነት በመጠቀምም የፀረ-ሽብር ማዕከልን ማጠናከር እስችሎታል፡፡ በአባሪነትም ጥቂት የሱስእንጀለስ አልሞ ተኳሾችን መልምሎ ቀጥሯል፡፡ እናም በነዚህ በሰለጡ ወታደሮችም በተመረጡ ቦታዎች በማስማራት ሽብርተኞችን በቁጥጥሩ ስር ለማዋልም ቋምጧል፡፡

ስራዬን በጀመርኩባት ቀን የፀረ-ሽብሩ ማዕከል የቢሮ ውስጥ ስራዎች በቅልጥፍና እየተከወኑ ስለመሆናቸው በአይኔ አስተውያለሁ፡፡ ሁሉም ሰራተኞች በትጋት በክፍሉ ውስጥ እንደ ጉንዳን ይርመሰመሳሉ፣ ያለማቋረጥ ስልኮች ይንጫረራሉ፣ የህትመት ማሣሪያዎችም ይንቻቻሉ፣ ዶሴዎችም እዚህም እዚያም ይከፋፈታሉ ይዘጋሉ፣ ከግድግዳው የተሰየመው ቲቪ ደግሞ የቀኑን ሰበር ዜና እና የተለያዩ ጉዳዮችን በመዳሰስ ጆሮአችሁን አውሱኝ አይናችሁንም



t.me/OLDBOOKSPDF

አትንፈጉኝ ይላሉ፣ በሙቶዎች የሚቆጠሩት ትጉህን ሰራተኞች ደግሞ አይኖቻቸውን ከምፒውተር ላይ ተክለው መረጃዎቻቸውን ይበረብራሉ ግራ ከመጋባቱ የተነሳ ፈዝዤ ቀረሁ። እጎንጎክ አትብሉኝና ባጠቃላይ ከፍሉ የጦር-ቀጠና ማዘዣ መሰሏል።

ለነገሩ ነገርየው ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ነበር። ዲዊም የአውሮፓውን የፀረ-ሽብር ቡድን በጣምራ በመምራቱ ውጤታማነቱ በቀጣይም ድልን እንደሚያጎናፅፈው ከወዲሁ ተስፋ ተጥሎበታል። እናም በስሩ ከሚተዳደሩ ቢሮዎች አንዱ ሚያዚያ 15 ከተሰኘው የፍልስጤማውያን ሽብርተኛ ቡድን ውስጥ የራሱን ሰላይ አስርጓል። እናም ይህ ራሱን ሚያዚያ 15 ብሎ የሚጠራው የሽብርተኛ ቡድን ብዙውን ጊዜ የአውሮፕላን ውስጥ ቦምብ ፍንዳታዎችን በመፈፀም ይታወቃል። እናም ሰርጎ ገቡ ለእኛም ሆነ ለሌሎች ልክ እንደ አንድ የወርቅ ማዕድን ማውጫ ስፍራ ሆኖልን ነበር። ለምሳሌ ለሳኪው ወገን ሁለት ያህል ጥቃቶች እንዳይፈፀም ማድረግ የሚያስችል መረጃዎችን አቀብሏል። ይህም ሰዳዊ ሰላዩን ሳለማጣት የሚችለውን እንዲፈፅም አድርጎታል። አለቃውም ሰርጎ ገቡን በአሜሪካ ኢምባሲ ላይ ጥቃት እንዲፈፅም ባዘዘው ጊዜም ዳዊ በአሜሪካ ኢምባሲ ጊቢ ውስጥ በቆሙት አንዲት መኪና ላይ የቦምብ ጥቃቱ እንዲፈፀም አዟል። እናም በዚህ ጥቃት የሞተ ሰው ባይኖርም ጥቃቱ አለቅየውን ሰርጎ ገቡ ቢያንስ ሙከራ እንዳካሄደ እንዲያምን አድርጎታል። በሰርጎ ገቡ ማመኑንም ሰርጎ ገቡ የማያቋርጥ የመረጃ ምንጫችን መሆን አስችሎታል።

ምንም እንኳን የፀረ-ሽብር ማዕከሉ በዘመን-አፋራሽ ቴክኖሎጂ የታጨቀና የታገዘ ቢሆንም ዕውነታው ግን ዲዊ በመስክ የሚመድበው ሰው ማጣቱን እዛ ላይ ያለውን ክፍተት ያሳያል። 'ቢል ኬዚ' ቃል የገባለትን ነገሮች ወደጉን በመተው ባህር ማዶ ያሉት የCIA ቢሮዎች ጥያቄዎቻቸውን ዋናው መምሪያ ለሚገኙ የየአካባቢዎቻቸው አለቆች ይመራሉ። አለቆቹም ጥያቄዎቻቸውን በማያሻማ መልኩ ከመለሱላቸው በኋላም የዲዊን ጦር መስበቅ አይፈቅዱም ነበር። ሁኔታውን ላስተዋለ እጅግ የተወሳሰበና አደገኛ ነበር። ዘመቻዎቹ ተበላሹም ተሳኩ ውጤታቸው ወዳጅ የሆኑ የውጭ መንግስታትን ማስከፋት ሆነ ባስ ሲልም በዘመቻው ተሳታፊ የነበረን ሹም ከስልጣኑ ያወርዱትና ወደ ሀገር ቤት ይልኩታል። ካለኛቸው ደግሞ ሹሙን ሊገድሉት ይችላሉ። ምንም እንኳን 'ዲዊ' ዘመቻውን ለማካሄድ የፕሬዚዳንት ሬገን ፍቃድ ቢኖረውም በስሩ የተኮለኮሉት ሹማምንቶች ግን ወታደሮችን ወደ ግንባር ለማዝመት ፈቃደኞች አልነበሩም ቢሮክራትነታቸውም መቼ በዚህ ብቻ ያበቃል ፓሪስ የሚገኘውን የቁጥጥር ቡድን በአንድ የተጠረጠረ ሰላይ ላይ የመኖሪያ አፓርትመንቱ በዓይኑ ቁራኛ እንዲጠብቅልን ብንጠይቅም በምላሹም ቡድኑ ፓሪስ የሚገኘው የአገሬው መረጃ ቡድን ነገሩን ሲደርስበት ስለሚችል ትዕዛዙን እንደማይፈፅምልን ገልፆልናል።

ቦን የሚገኘው ሌላው ቡድንም ወደ ምዕራብ ጀርመን በሚፈልሱ የመካከለኛው ምስራቅ ተወላጆች ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉ ጥቂት ዓረቦች እንዲመለምልልን ብንጠይቅም ቡድኑ ያንን ማድረግ የሚችሉ በቂ መረጃ ሰራተኞች እንደሌሉት አሳውቆናል።

በሌላ ጊዜም ቢሆን ቤይሩት የሚገኘው ቢሮአችን ወደ ሊባኖስ 167 ነይ ያለን አንድ ሰላዮችን እንዲያገናኘው ጥያቄ ብናቀርብም ያገኘነው ምላሽ ግን በአካባቢው ባለው የደህንነት ችግር ምክንያት ትዕዛዙ ተፈፃሚ ሲሆን እንደማይችል የሚገለፅ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

እናም ሳስበው ጥረታችንና ድካማችን ሁሉ አሸባሪዎችን መዋጋት ሳይሆን ስንክሳሩን ቢሮክራሲዎችንን መዋጋት የነበረ ስመሆኑ አስረጅ ነበር። እናም 'ዲዊ' ናላው ከመዞሩና ነገር ሁኔታዎች በሙሉ ከመምታታታቸው የተነሳ የትኛው ሰው ለየትኛው ቦታ እንደሚመጥን ለመመልመል ተስኖት ሁሉ ነበር ወይም አልቻለ ነበር። ይሁንና ከስድስት ወራት በኋላ ማግኘት የቻለውም ሁለት አረብኛ ተናጋሪ ሰራተኞችን ሲሆን ከእነሱም አንዱ እኔ ስሆን ሌላኛው ደግሞ ትርጉሜና ቢሮአችንን ለመምራት በማትናቱ ከሰላዮቻችን ጋር ከያሉበት የስራ ምድብ የመገናኘቱና የማቀናጀቱ ስራ የእኔ ኃላፊነት ነበር። ይሄም ስማገያ በመቶ የሚሆኑት የCIA ሰላዮች አረብኛ ተናጋሪ በመሆናቸው ሥራው አስቸጋሪ ሆኖ አላገኘሁትም።

አንድ ጊዜ ሊባኖስ ውስጥ የታገቱ ሰዎችን በማፈላለግ ላይ ከነበረ አንድ ትርጉሜ ቢሮ ውስጥ እንድሰራ ታዝዤ በነበረበት ወቅት ከትርጉሜና ቢሮው ሰራተኞች መካከል መካከለኛው ምሥራቅ በመስራት እንደኔ ረዥም ልምድ ያካበተ ሰራተኛ እንዳልነበረ አስታውሳለሁ። እንደው የትርጉሜና ቢሮው ኃላፊ ከሊባኖስ በቀር መካከለኛው ምስራቅን ረግጦ እንደማያውቅ አጫውቶኛል። ብቻ ምን አለፋችሁ ያለተሞክሮ ነበር በየቦታው ይመደቡ የነበሩት።

የሌሎችም የትርጉሜና ቢሮዎቻችን የተመለከትናቸው እንደሆነ ከዚህ የከፋ ሆኖ ነው ያገኘኋቸው። ምክንያቱም ከወኪሎቻቸው ጋር ተገናኝተው የማያውቁ ከመሆኑም በላይ ተሞክሮም ያልነበራቸውና የችግሩ ወላፈን ያልጠበሳቸው ከስንት አንዴ ካልሆነ በስተቀር ከዋሽንግተን ወጥተው የማያውቁ ነበሩ ትርጉሜና ቢሮዎችን እንዲመሯቸው ይደረጉ የነበሩት። ነገርየውን ሳስተውለው እንዴት ነው! ለብዙ ዓመታት የአንድ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር ሆኖ የሰራን ዶክተር በአንድ ጀንበር የአንድ ቀዶ ጥገና ቡድን መሪ እንደማድረግ ያህል ነበር፡፡

☼☼☼

ምንም እንኳን ኋይት ሀውስ ታጋቾችን የማስለቀቅ ኃላፊነት ለ ዲዊ የሰጠው ቢሆንም እሱም በዐረ-ሽብር ዘመቻው ለሚሳተፉ ወታደሮች የማዕረግ ሹመት እንዲሰጥ መወትወቱን ተያይዞታል፡፡ ከጀርመን ከተመለስኩ ከአንድ ሳምንት በኋላ አንድ ጠዋት ላይ ዲዊ ወደ ቢሮው አስጠርቶኝ «ግምትህ ጥሩ ነው» አለኝ ስለምኑ ስለው «ታጋቾቹን ነፃ ማውጣት እንደምችል የነገርከኝን እረሳኸው እንዴ?!» አለኝ፡፡ በማስከተልም ኧረ ለመሆኑ ሀሳቡ በምን መንገድ ሊመጣልህ ቻለ? በብዙ ምክንያቶች የተነሳ ግልፅ ምላሽ ልሰጠው አልቻልኩም፡፡ በ1986 መጨረሻ ታጋቾቹን የያዛቸው ማን ነው የሚለው ሀሳብ በራሱ በመረጃ ማህበረሰቡ ዘንድ ከፍፍልን ፈጥሮ እንደነበረ አስታውሳለሁ፡፡ CIA ጉዳዩን እስላማዊ የጅሃድ ድርጅት ታጋቾቹን ስለመያዙ ቢናገረም ቅሉ ስለ ድርጅቱ ግን በቂ መረጃ አልነበረውም። በእርግጥ ድርጅቱ በሶሪያና ኢራን እንደሚንቀሳቀስ ቢያውቅም በሁለቱ ሀገራት ይደገፋል የሚል ዕምነቱ ግን አልነበረውም። ሌሎች ዋሽንግተን ውስጥ ያሉ በተለይም ፔንታጎን ውስጥ ያሉ የመረጃ ተንታኞች ደግሞ በዚህ ሃሳብ አይስማሙም። እንደውም ይህ እስላማዊ ጅሃድ የኢራናዊው ፓስድራን አሻንጉሊት ከመሆን ያለፉ ድርጅት አይደለም በማለት ያጣጥሉታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የCIA አቋም በጠንካራ መረጃ ላይ የተመሰረተ ባይሆንም ስር ከመስደዱ በፊት ችል የሚባል አልነበረም። በበከሴይ ላይ አፈና ከተፈፀመ ዓመት በኋላ እንኳን CIA በከሴይን ወይም ሌሎቹን ታጋቾች የዕስልምና ጀሃድ አራማጆች የት እንዳደረሷቸው ፈፅሞ ማወቅ አልተቻለውም። ማለትም እንደ በከሴይ፣ የCNN ጋዜጠኛውን ጄራሚንና ካህናቶቹን በንጃሚንና፣ ላውረንስ ማርቲን ጄንኮ'ን ያገተው በደቡብ ሊባኖስ የሚንቀሳቀሰውና ኢማድሙኢዝ ሙግህኒያ የተባለው ወጣት የሺዓ ሙስሊም አራማጅ መሆኑን የሚገልፅ መረጃ አልደረሰ እቀብላን ነበር። እንደሱም እንደ መረጃው መሰረት ከሆነማ ከ 1982 ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ መግህኒያህ የፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅት ሲቀመንበር ያሲን አረፋት ተቀጣሪ እንደነበር አልጀራውያኑ ገልፀውልናል። ሆኖም እንደመረጃ ምንጫችን ከሆነ ግለሰቡ ከፍሊስጤም ነፃአውጭ ድርጅት ራሱን አግሎ በራሱ መንቀሳቀስ እንደጀመረና የአሜሪካ ታጋቾቹን ለመልቀቅ በታህሳስ 12,1983 በአሜሪካ እና ፈረንሳይ ኢምባሲዎች ለደረሰው የምብ ፍንዳታ ተጠያቂ የሆኑና በኩዌት እስር ቤት የሚማቅቁትን 17 እስረኞችን መልቀቅ እንደሚሻ ነው የገለፀው። ምክንያቱም ከእስራሰባቱ አንዱ የሆነው ሙስጠፋ ሳድር አል-ዲን የመግህኒያ ሚስት ወንድም መሆኑንም መረጃ አቀባዮቹ አብራርተውልን ነበርና። እናም ታዲያ ይሄን ሁሉ በምናብ ፈረስ ስጋልብ የነበረው ከዲዊ ቢሮ በር ላይ ቆሜ መሆኑን ሳስተውል ለራሴም ገርሞኛል ምክንያቱም ምን ያህል በሀሳብ የጊሊዮሽ እንደሄድኩ አላወኩም ነበርና ዲዊም ከሀሳቤ ስላሳናጠበኝ ሳላመሰግነው አላልፍም። እናም በመጨረሻ ላይ ከሀሳቤ እንደተመለስኩ እንዲህ አልኩ «መግህኒያ'ን በሀሳብ መረብ እናጠምደዋለን ማለቴ ቤተሰቦቹን» አልኩት። ዲዊ የተናገርኩት አልገባውም መሰለኝ ምን አልክ?! አለኝ በመገረም። «ይኼውልህ» ዲዊ አልኩት። «ስት ነገሮች እውነት መሆናቸውን ዕንመን።» ታጋቾቹ በመግህኒያ እጅ ናቸው እንበል፣ ሙግህኒያ እንደአብዛኞቹ የመካከለኛው ምስራቅ ተወላጆች ቤተሰቦቹን ይወዳል ብለን እናስብ፣ ከዚያም ድረጅቱ የታገቱበት ሰዎችን ለማስለቀቅ የታዘዘውን ሊፈፅም እንደሚችል እንመን እናም ይህ ሁሉ እውነት ከሆነ የሙግህኒያ ቤተሰቦችን ይዘን ታጋቾቹን ለማስለቀቅ ልንጠቀምባቸው እንችላለን አልኩት።

ዲዊም በሀሳቤ ከመስማማቱ የተነሳ በል «የኢማድን ቤተሰቦች ፈልገህ አምጣልኝ።» በማለት አሳሰበኝ። ነገርየውን በቶሎ ብጀምረው የተሻለ በሆነ ነበር። ይሁንና ዱዊ ጉዳዩን ለእሊናር ወይም ኢን.ኢስ.ሲ ውስጥ ለሚሰራ ሌላ ሰው አጋርቶ ሊያበላሸው እንደሚችል ገምቼያለው። ይሁንና ኋላ ላይ ጉዳዩ በመድበሰበሱና ባለመነሳቱ እኔም ችላ ብየው ነበር። ግምቴ ርግጥ ቢሆንም ግን የኢራን አማፅያን ወሬ በናኘ ጊዜም ናርዝ ሀሳቤን የኋይት ሀውስ ልዩ የኢ-ሜይል የመገናኛ ዘዴ በሆነው PROF በመጠቀም በበተናቸው መልዕክቶቹ እንዳሰራጨው ኋላ ላይ ለማወቅ ችያለሁ።

☆☆☆

ዲዊ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ታጋቾቹ ሲያናግረኝ ወደ እኔ መጣ......። በቀጣዩ ቀንም በውይይታችን ውጤታማነት መተማመን አደረብኝ። እኛም ታዲያ በመጨረሻ ላይ ስላነሳሁት ስለዚህ ዘመቻችን ዲዊ ለኋይት ሀውስ ይንገር አይንገር የማውቀው ነገር የለም። ነገር ከሆነም ኋይት ሀውስ ለጉዳዩ ትኩረት ስለመስጠቱ አጠራጣሪ ይሆንብኛል። ምክንያቱም



t.me/OLDBOOKSPDF

ኀይት ሀውስ ጉዳዮችን ስለማድበስበስና ስለሚወስዱ እርምጃዎች በቢሮክራሲው ሳንካ መጠላለፍ የተነሳ ማ-ለማ ግድ የለውም። ይሁንና የታጋቾቹን መለቀቅ ግን አጥብቆ ይፈልገዋል።

በ1986 ሚያዚያ ወር አንድ ጠዋት ዲዊ ቢሮዬ 'የአንድ ሰላይን' ዶሴ ይዞ በመምጣት ይህን እንብበው ብሎኝ ጠረጴዛዬ ላይ እየወረወረው 'አንተና ኬቭ የተረፋት የዕረፍት ጉዞ ታደርጋላችሁ' አለኝ። ጆርጅኬቭ ማለት ደግሞ ስለ ኢራን አብጠርጥሮ የሚያውቅ አለ የተባለ የCIA ምሁር ነበር። ፐርሺያኛና አረብኛ አቀላጥፎ የሚናገረው ኬቭ ለበርካታ ዓመታት በመካከለኛው ምስራቅ በመስራቱ ምናልባትም CIA አለኝ ከሚለው ሰራተኛው አንዱ ነው። እናም እጅግ ተፈላጊ ከመሆኑም የተነሳ ከተገለለበት ጡረታ ተመልሶ CIA'ን እንዲቀላቀል ተደርጓል። ይህም የሆነው በመካከለኛው ምስራቅ ያሉ የCIA ኤክስፐርቶች በፍጥነት በመመናመናቸው እየሳሳ በመሄዱና አዳዲሶቹን የማሰልጠን ዕቅድ ባለመኖሩ ነበር። ዲዊ ከቢሮዬ ወጥቶ ሲሄድ ከዶሴው ጀርባ የተፃፈውን የሰላዩን ስም ——— እንደሚል አየሁ እናም የስሙ የመጀመሪያ ሁለት ፊደላት ስውየው ኢራናዊ ወይም መረጃውን የሚያስተላልፈው ከኢራን ስለመሆኑ ይናገራሉ። ከዶሴው ውስጥ ያለው የመጀመሪያ ሰነድም የሰላዩ ዕውነተኛ ስሙ ማኑሸር ጉርባኒፋር መሆኑን ይገልፃል። ይሁንና ስሙ ለእኔ ምንመም ትርጉም ባይሰጠኝም ከሰነዱ በስተግራ በኩል 'አስቸኳይ ማሳሰቢያ' የሚል ሀረግ ሰፍሮበታል ይህም ዳይሬክቶሬት ኦፐሬሽን ውስጥ ላለን ሰዎች ከአንድ ሰላይ እንድንርቅ የሚያሳስብ መልዕክት ነበር። እናም ታዲያ ይህንን ማሳሰቢያ ዲ.ኦ የሚያስተላልፈው አንድ ሰላይ CIA'ን አሊያም ኋይት ሀውስን በሀፍረት ሊያሸማቅቅ የሚችል የፈጠራ ዜና በመገናኛ ብዙኃን ካሰራጨ በኋላ ነበር። እናም እኔ ካስቸኳይ ማሳሰቢያው ባለፉ ቀሪውን የዶሴውን ክፍል ማንበብ አላስፈለገኝም። እንደ የመረጃ ሰራተኛ አንዱ ፈጠራ ካስተላለፉ በኋላ ከሱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት መፍጠር አያስፈልግም እናም የጎርባኒፋር ዶሴን ፈፅሞ ከማላነባቸውና ከተቆለሉት ሌሎች ፋይሎች ላይ ደረብኩት።

ዲዊም ከሁለት ሳምንት በኋላ መጣና እንዴት ነው?! አነበብከው? ሲለኝ እንዳላነበብኩት ስነግረው ፋይሉን ይዞ ከቢሮዬ ወጣ። ብዙም ሳይቆይ ከፀረ-ሽብር ቡዱኑ ወጥቼ ወደ ቤይሩት እንድጓዝ ተደረገ። ዲዊ ምንም አማራጭ አልነበረውም ምክንያቱም የምስራቃዊ ምድብ ከእኔ በስተቀር ለግዳጅ የሚያሰማራው ሰው አልነበረውም። ግዳጁ አደገኛ ብቻ ሳይሆን መጥፎ ሊባል የሚችል ቢሆንም ስለሽብርተኛ መማሪያው ብቸኛው ቦታ በመስክ መሰማራት መሆኑን ባለፈው የሕይወት ተሞክሮዬ ጠንቅቄ ስለማውቅ ይህ ግድ አልሰጠኝም ነበር።

'ጆርጅ ኬቭ' ዲዊ ለዕረፍት በሚል ወደ ቴህራን እንዲሄድ ያቀረበለትን ሀሳብ ተቀብሎ በተጓዘበት ወቅት የኢራን አማፅያን ዜና እየናኘ ስለነበር ለመክሰስ ተቃርቦ ነበር። ዲዊም ቢሆን ከክሱ ቻርጅ አላመለጠም ይሁንና የስራው ኃላፊነትና ያስመዘገባቸው ውጤቶች ሚዛን በመድፋታቸው በይቅርታ ታልፎአል። እኔም የጎርባኒፋርን ዶሴ ባነብ ኖሮ ወደ ቴህራን ባልተላኩ በኢራን ዐመፅ ጠንሳሽነትም በተከሰስኩም ነበር። ምክንያቱም ያን ወቅት ትዕዛዞችን ላለመቀበል ራሴን ያሳመንኩበትም ወቅት ነበርና።

☼☼☼



t.me/OLDBOOKSPDF

እልፍ አልፎም ቢሆን የሆኑ ሰዎች ለምን በኢራን አማፅያን ጉዳይ ውስጥ እጃቸውን ሊከቱ እንደቻሉ አስባለሁ። አሁን አሁንማ ሳስበው ኢራናውያኑ ኋይት ሀውስ ውስጥ የሚያጃጅሏቸው ሰዎች ማግኘታቸው ግልፅ ሆኖልኛል። እኔን የሚገርመኝ ነገር አንድን ታጋች ለማስለቀቂያ የሚሆን መሳሪያ አጭቆ ኢራን የሚያርፈው አውሮፕላን ኢራን ገና ከማረፉ እነሱ በደርዘን የሚቆጠሩ ሌሎች ዜጎችን ያግታሉ። እኔማ ሁኔታው ከዚያም የከፋ እንደሚሆን ተረድቼያለሁ። ዕቅዱ የከሸፈው ግን ኋይት ሀውስ በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆነውን የዲፕሎማቲክ ግንኙነት መስመር በአጭበርባሪነቱ የታወቀውን ጎርባኒፈርን እንዲቆጣጠረው ሲፈቅድ ነው። እናም ነገሩን ሳስበው አንድን የመንገድ ጋዜጣ አዟሪ በአክስዮን ግዢ ስራ ላይ የማስማራት ያህል ነው። መታሰብ የነበረባቸው ሁለት ነገሮች እሱ እላለሁ። በመጀመሪያ ደረጃ በ1983 በቤይሩት ባሕርተኞች መኖሪያ ሰፈር ከደረሱት የቦምብ ጥቃቶች በኋላ ስለወታደራዊ ጥቃት መከላከል ዘመቻ ጉዳይ የታሰበበት ነገር አልነበረም። ፔንታጎንም በወረራ ጥበብ ያልተካኑ ወታደሮችን የሚያሰማራበት ምክንያት አልገባኝም። የፀረ-ሽብር ቡድኑ አካል የሆነው የ'ዴልታ ፎርስ' ቡድንም ወደ ስፍራው እንዲላክ ፔንታጎን አልተስማማም። ይህም የሆነው የዴልታ ፎርስ ቡድን አባል አንድን ታጋች ሀያ አራት ሰዓት በአይነ-ቁራኛ እንዲከታተል ካልታዘዘ በቀር ቡድኑ ሊሰማራ ባለመቻሉ ነው። ይህም ቢሆን ሊሟላ የሚችል ቅድመ ሁኔታ አልነበረም። እናም በእነዚህና በመሳሰሉት ቢሮክራሲዎች የቀረው መፍትሔ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት እንዲሆን አርጎታል። ግራም-ነፈስ ቀኝ ችግሩ የተፈጠረው ብሄራዊ የደህንነት አባል የሆነና ከኢራን ጋር ግንኙነት ያለው ሰው በመታጣቱ ነበር።...... የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በስዊዘርላንድ በኩል ያደረገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አልተሳካም ምክንያቱም የስዊዘርላንድና ኢራን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በታጋቾቹ ጉዳይ እንዲመክሩ ከማድረግ ባለፉ ያስገኘው መፍትሔ አልነበረምና። CIA ራሱ ከቴህራን ጋር ግንኙነት አለመኖሩ ችግሩን አስከፊ አድርጎታል። ስለሆነም በ1979 የኢራኑ አብዮት ሲከሽፍ ለዋሽንግተን ፓለቲካ ምስጋና ይግባውና CIA ያየውም ሆነ የሰማው ነገር አለመኖሩ ሊያስደንቀን አይገባም።

እናም ወታደራዊ ዘመቻም ዲፕሎማሲያዊ ጥረቱም ባለመሳካታቸው ኃይት ሀውስ ከእስራኤል መስማማት በኃላ ጎርባኒፈርን ከኢራን ጋር የመገናኛ መንገድ አድርጎ ሊጠቀምበት ወሰኗል። እኔን ግን አግራሞት ያጫረብኝ ይህ አጭበርባሪ የሰራውን መስስ ብሎ ካየ በኃላ ኋይት ሀውስ ትውልደ-አሜሪካዊ የሆነ ኢራናዊውን አልበርት ሃኪምን በሽምጋይነት ለመጠቀም መወሰኑ ነበር። ሽምጋያችንም ከኢራን ጋር የሚያገናኘን ሁለተኛው የግንኙነት መስመር ሆኖአል። እናም እንደ ጎርባኒፋር ሁሉ ሃኪም ጉዳዩ ውስጥ እጁን የከተተው ለገንዘብ ጥቅም ሲል ነበር። ይሁንና ከማንኛውም ሽምጋይ በተሻለ በቀጥታ ታጋቾቹ ወዳሉበት የኢራናውያኑ ፓስድራ ቡድን ወደሚገኝበት ቦታ ማምራት መቻሉም ከጎርባኒፋር የተለየ ያደርገዋል። በተጨማሪም ይኸው ሃኪም የፓስድራ ባለሥልጣን የሆነውንና የኢራን ፓርላማ አፈጉባኤ የሆኑት አሊአክበር ሃሺሚ ራፍሳንጃኒ እህት ልጅ አሊ ሃሺም ባህራሚኒን በቀጥታ መገናኘት የሚችል መሆኑ ሃኪምን ከሌሎቹ ሽምጋዮች ይለየዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፰

# ሚያዚያ 1986 ፤ ዋሽንግተን-ዲሲ

ወደ ቤይሩት ከመሳኬ በፊት በሽብርተኝነት ላይ የተጣበበ የአጭር ጊዜ ስልጠና ለራሴ ለመስጠት ችዬ ነበር። ለዚያ ደግሞ ከሲ.ቲ.ሲ የተሻለ በ CIA ውስጥ አልነበረም። በሽብርተኝነት ላይ CIA ውስጥ የተጠራቀሙ ፋይሎችንና ኮንፒዩተር ውስጥ የታጨቁ መረጃዎችን ያለገደብ የማሰስ መብቱ ነበረኝ። ምንአለፋችሁ መዋዕለ-ሕፃናት ውስጥ በነፃነት እንደተለቀቀ ህፃን ሆኜ ነበር።

በመጀመሪያ ትኩረቴን የሳበው የኤምባሲው ፍንዳታ ጉዳይ ሆነ። አሁንማ ምስጢሩ ውስጤን አብሰልስሎታል ማለት እችላለሁ። ክምሩን ዶሴ አብጠርጥሬ ለመቃኘትና ለመቃረም አስፍስፌያለሁ ከዛም ስለጉዳዩ በጥልቀት ማብራራት እችላለሁ ብያለሁ ይሁንና መጨረሻ ላይ ያገኘሁት መረጃ የሁለት ዓመት እድሜ ያለው ነበር። ለዚህ ደግሞ ሁለት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የኤምባሲው ፍንዳታ በሊባኖስ የCIA'ን ተሰሚነት የቀነሰው በመሆኑ ኤምባሲው ወደ ምስራቅ ቤይሩት ከተዛወረ በኋላ አብዛኞቹን ሙስሊም መረጃ አቀባዮቹን ማጣቱና ክርስቲያኖችን ከሙስሊሞች የሚለየውን አረንጓዴ ቀጠና ማቋረጥ የሚችሉት በጣም ጥቂቶቹ ብቻ መሆናቸው በመሆኑም አረንጓዴው ቀጠና ስያሜውን ያገኘው በተከለከሉት መንገዶች ከሚበቅሉት አረንጓዴ ዛፎች ነው።

ከአሁን በኋላ የቱባውን ክፍል መምዘዝ እንደሚታሰበው ቀላል እንዳልሆነ ተገንዝቢያለሁ። የሊባኖሱ ፕሬዚዳንት አሚን ጁማይል በፍንዳታው ተጠርጥረው የተያዙትን በሙሉ እንደዋዛ ከእስር ፈተዋቸዋል። ተገደው ያደረጉት ስለመሆኑ ጥርጣሬ አለን። የሆነ ሆኖ ተጠርጣሪዎቻችንን በመላው መካከለኛው ምስራቅ ተበታትነው እንደመገኘታቸው ከዜሮ ከመጀመር አንድንም። በእጃችን የቀረ ነገር ቢኖር በፍንዳታው ማግስት በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ የተዘረዘረው የሶስቱ ተጠርጣሪዎች ስም ዝርዝር ብቻ ነው። ልዩነቱ ከተጠርጣሪዎች አንደኛው (IJO-Islamic Jihad Organization) አባል መሆኑ ነው። አሁን ጥርጣሬያችንን የሚያገላ አንድ ሰው በውስጡ ይዟል። ኢማድ ሙግህኒያህ ይባላል። መጀመር ካስፈለገ ከእሱ የተሻለ አማራጭ አይገኝም።

ኢማድ ሙግህኒያህ በጣም አነጋጋሪ ሰው ነበር። ፓስፖርቱ ላይ በተፃፈው መሰረት በ1962 ታይር ዲባ ተብላ በምትጠራ የደቡባዊ ሊባኖስ ጉስቋላ መንደር የተወለደ መሆኑ ቢጠቀስም እርግጠኛ የሚኮንበት መረጃ ግን አልነበረም። በርካታ ሺአዎች ህገወጥ ስራ መስራት ሲፈልጉ በትውልድ ቀዬነት የሚያስመዘግቡት ስፍራ ነበር። ሙግህኒያህ ያደገው ምንም ወራጅ ውሃ በሌለበት በደቡባዊው የድሆች መንደር መሆኑን እናውቃለን። አባቱ አትክልት ሻጭ ስለነበሩ ይኖሩ የነበረው ከቤሩት አውሮፕላን ማረፍያ ብዙም የማይርቅ ቦታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ነበር። በእርስ በርስ ጦርነቱ ወቅት ስፍራው የአረንጓዴው ቀጠና ዋና መተላለፊያ ነበር። በታዳጊነቱ በጥይትና ፈንጂ ፍንዳታ ሲባንን ስለማደጉ ምንም ጥርጥር የለውም። የሚባርቁ ጥይቶች ቤታቸውን በተደጋጋሚ ወንፊት ያደርጉት ነበርና።

ይህ ሁሉ መረጃ ከቅጥረኞቻችን የተቀበልነው እንጂ የትኛውም የCIA መኮንን 'አይን አል ዲልባህ' ድረስ ዘልቆ ገብቶ የሚያረጋግጥበት እድል አልነበረንም። 'አይን አል ዲልባህ' የተከለከለ ቦታ ነው። እዚያ ሁሉም እርስ በርሱ ይተዋወቃል። እንግር የጣለው ፀጉረ ልውጥ ማንነቱን በትክክል ማብራራት ካልቻለ በሰላም በመጣበት መንገድ የሚመለሰው ዕድለኛ ከሆነ ብቻ ነው። የሊባኖስ ባለስልጣናት እንኳን ያችን ቦታ መርገጥ አይችሉምና።

ሙግህኒያህ በያሲር አረፋት የሚመራውን ኃይል-17'ን የተቀላቀለው ገና በ14 ወይም በ15 ዓመቱ ነበር። ከዚያ በፊትም ቢሆን አረንጓዴውን ቀጠና እያቋረጠ ከክርስቲያኖች ጋር የሚበጣበጥ ነውጠኛ ነበር። ቤይሩት በሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርስቲ ለአንድ አመት ያህል ትምህርት መከታተሉ ይነገራል። ወይም አንድ የሆነ ሰው ደረጃውን ከፍ ለማድረግ እያስወራለት ነው። እናም ይህ ነውጠኛ ከአንድ የሩቅ ሙስሊም ዘመድ በስተቀር የጠለቀ የእስልምና መሰረት አልነበረውም።

እዚህ ድረስ የምናውቅ ቢሆንም ከምንፈልገው መረጃ አንፃር ግን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። ከ1982ቱ የእስራኤል ወረራ ባድማ ተነስቶ እንዴት አንደ ምስኪን አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሃብታምና በመሳሪያ የተደራጀ የአሸባሪዎች ድርጅት ሊመሰርት ይቻለዋል?? በርካታ የውጭ አገር ሰዎችን ሲያግት የነበረው ሰው በእርግጥ ይህ ነውን?? በአፕሪል 1983 የአሜሪካን ኤምባሲ በቦምብ አጋይቶ ፍንጭ ሳይተው የተሰወረውስ?? ፋይሉችን የበለጠ ባገላበጥኩ ቁጥር ሙግህኒያህ ብቻውን እንደሚሰራ አልጀርያውያን ያስቀመጡት ግምት ስህተት መሆኑን እያመንኩ መጣሁ።

ሲ.ቲ.ሲ ውስጥም ሆነ ሽርፍራፊ መረጃዎችን አገኘሰሁ ብዬ ባሰብኩበት ቦታ ሁሉ ለሁለት ወራት ያለሚቋረጥ እንደፍልፈል ቆፈርኩ። ዘወትር ጠዋት 12 ሰዓት ከመሆኑ በፊት ቢስክሌትን ጉዳና 123 በሚገኘው የCIA ቢሮ በር ፊት ለፊት አቆማለሁ። አንዳንዴ እንዲፈትሹኝ ለማድረግ የጠባቂዎችን ማረፊያ ቢሮ ማንኳኳት ይጠበቅብኝ ነበር።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ሰው ሁሉ ጥርግርግ ብሎ ከቢሮው ሲወጣ እኔ ግን ለአንድ ወይም ሁለት ተጨማሪ ሰዓታት እነባለሁ። ጠረጴዛዬላይ የተበታተነው የፋይል ክምር በራሱ በሳቅ ያንከተክታል።

ሙግህኒያህ በቤይሩቱ ኤምባሲ ፍንዳታ ውስጥ ስለነበረው ሚና ፍንጭ ማግኘት አልተቻለኝም። የመካከለኛው ምስራቅን ድሮች በመቀጣጠል እንዳጠናሁት በእርግጥ ሙግህኒያህ በፍንዳታው እጁ ካለበት የኢራን መንግስት ከጀርባው ስለመኖሩ ተጠራጥሪያለሁ።

ለምሳሌ ያህል ዴቪድ ዶጅ የተጠለፈው በፓስዳራን እንደነበር እረግጠኞች ነን። በሌላ በኩል አንድ ሌላ የፓስዳራን መኮንን ቢሮ ውስጥ በ1983 የውጭ አገር ዜጎችን ለመጥለፍ እቅዶ እንደነበር ደርሰንበታል። ስለዚህ የአሁኖቹ አጋቾች ከበፊቶቹ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው መጠርጠር ሙግህኒያህን ከመጠርጠር እኩል ተቀባይነት ይኖረዋል። መጨረሻ ላይም የቢል



t.me/OLDBOOKSPDF

በክሴይ ሞት ይታወሳል። በሐምሌ 1985 አካባቢ ነው የሞተው። ቀኑን በእርግጠኛነት ባላስታውሰውም ይህ ፅሁፍ በዝግጅት ላይ በነበረበት ወቅት የኢራን መከላከያ ሚኒስቴር የነበሩት አሊ ሳልች ሻምክሃኒ ሊባኖስ ውስጥ የውጭ አገር ሰዎች በእንገዝህላልነት ለአንታ መጋለጣቸውን ጠቅሰው ለበቀል መነሳሳታቸውን አሳውቀው ነበር። እንደተነገረን ከሆነ ሻምክሃኒ ሌሎች የታመሙ ታጋቾችን ካሉ በአስቸኳይ ህክምና እንዲካሄድላቸው ለፓስዳራን ትዕዛዝ አስተላልፈዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሂዝቦላ እስረኛ የነበረው ሊባኖሳዊ አይሁድ የውስጥ ደዌ ሐኪም ኤሊሃላክ ፈረንሳዊውን የሀO ታጋች ሚሼል ሴውራትን እንዲመረምረው ተደርጓል፡፡ የሃላክ ጥረት ግን ሴውራትን በቀጣዩ አመት በካንሰር ከመሞት ሊታደገው አልቻለም። ለነገሩ ሃላክ ራሱንም አላዳነም። ሀO እርሱን የሚተካ ዶክተር እንዳገኘ በስቅላት ከዚህች ዓለም አሰናበተው።

በመጨረሻ የሚነሳው አጓጊው የCNN'ን ጋዜጠኛው ጀረሚ ሌቪን ጉዳይ ይሆናል። ሀO ሌቪኒን የያዘው ማርች 7/1984 ቤይሩት ውስጥ ነበር፡፡ እስከሚቀጥለው አመት የፍቅረኞች ቀን ድረስ ስለእርሱ የተሰማ ምንም ወሬ አልነበረም፡፡ ያን ቀን ግን ባላባክ ውስጥ በሚገኘው የሶሪያ የፍተሻ ጣቢያ ድንገት ብቅ አለ፡፡ ሌቪን እንደተናገረው ንጋት ላይ ሲነቃ ሰንሰለቱ ላልቶ በማግኘቱ ሁለት ብርዱልብሶች ቀጣጥሎ ከታጎረበት ሕንፃ በመስኮት ወርዶ ነው ያመለጠው፡፡ እንደገለፃው ከሆነ ታስሮ የነበረበት ቦታ የሼክ አብደላ ምሽግ ውስጥ ነው፡፡ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ የጠለፈው ሀO ቢሆንም እስሮ ያቆየው ግን የኢራን ፓስዳራን ነበር ማለት ነው።

ይህንን ሁሉ በማወጣና በማወርድበት አንድ ጠዋት የሲቲሲ ምክትል ኃላፊ ፍሬድ ቱርኮ ወደቢሮው ጠርቶኝ «ጀንኮ ወጥቷል» አለኝ። ሊሊቱን እንቅልፍ በአይኑ እንዳልዞረ ሰው የድካም ስሜት ተጫጭኖታል። «ወደ ወስቤዳን እየሄደ ነው። ድረስበትና አናግረው»። በማለት ቀጠን ያለ ትዕዛዝ ሰጠኝ።

አባት ላውረንስ ማርቲን ጀንኮ ጥር 8/1985 ቤይሩት ውስጥ ታግተው የነበሩ አሜሪካዊ ቄስ ናቸው። እንደሌቪን ሁሉ እሳቸውም ሐምሌ 26 1986 ድንገት እስከሚለቀቁ ድረስ ስለቆይታቸው የሚታወቅ ነገር አልነበረም። የካቶሊክ ቄስ የነበሩት ሬቨረንድ ቤንጃሚን ዌይር ቀደም ብሎ ተለቆ የበረ ቢሆንም ከ FBI'ም ሆነ ከCIA ጋር ለማውራት ፈቃደኛ አልነበሩም። ጀንኮ ከሌቪን በኋላ የተፈጠረውን ክፍተት ይሞሉልናል ብለን ተስፋ አድረገናል። ስለዚህ ቢስክሌቶን ቤት ለማድረስ የሚበቃ ጊዜ አልነበረኝም። ፍሬድ በአንደኛዋ የሲቲሲ ዋገን ቤቱ ተወስጄ ልብሶቼን እንድሸክፍ ካስደረገ በኋላ ወደ ቅዱስ አንድሪው የጦር ሰፈር ገስገስን እናም እዚያ ስንደርስ ወደሃያ የሚጠጉ ረዳት መርማሪዎች ተዘጋጅተው እየጠበቁኝ ነበር። ሲ-141 ቡድኑ ወደ ዌስባደን ለመንቀሳቀስ በተቃረበበት ሰዓት አንድ የአየር ኃይል ሻለቃ ለስቴት ዲፓርትመንቱ የፀረ-ሽብር ዘመቻ መሪ አምባሳደር ቦብ ኦክሌይ በረራችን ሊዘገይ እንደሚችል አሳውቀው። አትላንቲክ ውቅያኖስ በአውሎነፋስ በመታመሱ አስቀድመው ለተነሱና ነዳጅ የጨረሱ በረራዎች ብቻ እንዲፈቀድላቸው ተደርጓል። የበረራችን አጣዳፊነት ኤፍ.ኤ.ኤን ስለማያስጨንቀው የነበረን አማራጭ ቁጭ ብለ መጠባበቅ ሆነ።

ኦክሌይ ወደኋይት ሃውስ ስልክ ደውሎ ኦሊኖርገዝን አናግሮ ሲመለስ በፈገግታ ተውጦ «እንሂድ» አለን። በኋላ ላይ ስለጉዳዩ እንደሚከተለው አብራራልን። ኖርዝ ወደኤፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኦሎ ጋላሬ ደውሎ የፕሬዚዳንቱን ስም በመጥራት ባስቸኳይ የበረራ ፈቃድ እንዲሰጠን ትዕዛዝ አስተላለፈ:: በ[illegible]ሽብር ዘመቻ ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰራተኛ ኀይት ሃውስ ውስጥ የሚፈራ ግለሰብ ቀኝ እጅ እንዳለው ያወቅሁት ያኔ ነው::

ጀንኮ እንዳሰብነው የወርቅ ገንቦ አልሆኑልንም:: የማስታወስ አቅማቸው ከፍተኛ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያሳለፉት አይናቸው ተሸፍኖ ወደ ግድግዳ ዞሮ በመታሰር ነበር:: አልፎ አልፎ ከጠባቂዎቹ ጋር የተመላለሷቸው ቃላትም ብዙም ቁምነገር ጠብ የሚላቸው አልሆኑም:: የሙግህኒያህም ሆነ የሌላ ሰው የሚያስታውሱት ፊት አልነበረምና::

ጉዳችን በከንቱ እንደተደረገ መቁጠር በጀመርኩበት ሰዓት ነበር ጀንኮ ስለጁራሚ ሌቪን ድንገት ማውራት የጀመሩት:: ጠባቂዎቹ ሌቪን ማምለጡን እንዳወቁ ንዴትና ፀፀት በተቀላቀለበት ስሜት ቀሪዎቹን ታጋቾች በታችኛው ቤቃ በኋላ ላይም ሶርያውያን ወደማይደርሱባቸው ደቡባዊ ቤይሩት እንደወሰዷቸው ተናገሩ:: ከዚህ የተረዳነው ነገር ቢኖር ሌቪን በእርግጥም አምልጦ የወጣ መሆኑንና አጋጆቹ ከሶሪያዊያን መጋፈጥ እንደማይፈልጉ ነበር::

በሳተላይ የተነሱ የሼክ አብደላን ምሽግ ፎቶዎች ለጀንኮ ስናሳያቸው ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን መዘርገፍ ጀመሩ:: አጋቾቹ ጀንኮ ይጠቀሙበት የነበረውን መታጠቢያ ቤት ሽንቁር ሙሉ በሙሉ ባለመድፈናቸው ስህተት ሰርተውልናል:: በቀዳዳ እያሾለኩ በተደጋጋሚ 'ክሃኪ' ተብለው የሚጠሩ የኢራን ወታደሮች ከጦሩ ቀጠና እነርሱ ወደታሰሩበት ህንፃ ምግብ ሲያመላልሱ ለመመልከት ችለዋል:: ጀንኮ ከፎቶዎቹ መርጠው የሼክ አብደላን ምሽጉች ለመጠቆም ቻሉ:: ያገቡ መከንኖች የሚኖሩበትን ህንፃም ነጥለው አወጡት:: ህንፃውን እኔም በ1984 ኦክቶበር ላይ በጠባቂዎች ታጅቤ ቢቃን በጎበኘሁበት ወቅት ለማየት ችዬ ነበር::

☼☼☼

መካከለኛው ምስራቅ ውስጥ እንደነበሩ ሌሎች በርካታ ጉዳዩች ሁሉ የሙግህኒያህ ታሪክም እየተወሳሰበ መሄዱ አልቀረም:: በስተመጨረሻ የገጠመኝ ግን ከነጭራሹ ቅጥ አምባሩ የጠፋ ነገር ሆነብኝ::

ሴፕቴምበር 30/1985 ራሱን የእስልምና ነፃ አውጪ ድረጅት ብሎ የሚጠራ ቡድን አራት የሶቭየት ዲፕሎማቶችን ቤይሩት ውስጥ ሲያግት ከመካከላቸው አንደኛው በፅኑ ስለተጐዳ ለሞተ ተዳረገ:: ሶርያ ትሪፓሊ ውስጥ የሚገኙ አክራሪዎችን ማጥቃቷን እንድታቆም ያቀረቡት ጥያቄ የሶሪያ ሙስሊም ወንድማማቾች ቡድን አባላት ስለመሆናቸው ፍንጭ ሰጠን::

ብዙም ሳይቆይ ስሁዱር ሰላማህ የሚባል ያልታወቀ ፍልስጤማዉ ተይዞ እገታውን እንዲያምን ተደርጎ በህይወት በሚገኙት ሶስት የሶቭየት ዲፕሎማቶች ተቀየረ:: (ሳላማህ ያመነው ወዶ እንዳልሆነና እንዲያውም መርማሪዎቹ ምላሱን ለማለዘብ ቆለጡን እንደቆረጡት ሐሜት አለ)::

ምን ማመን እንዳለብን ግራ ገባን:: የሳላማህ ታሪክ ቤይሩት ውስጥ እንደአፈታሪክ የሚነገር ሆኗል:: እውነታው ሲወጣ ግን ከልብወለድ የበለጠ የማይታመን ነበር:: ሶቭየቶችን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለማስለቀቅ በተደረገው ድርድር ኢማድ ሙግህኒያህ ከያሲር አራፋት ጋር በመገናኘት ነገሮችን አመቻችቷል። በምትኩ ሶቭየቶች እጋቾቹን እንደማይበቀሏቸው ከአራፋት ጠይቆ ማረጋገጫ አግኝቷል። አብዱ ኢያድ የተባለ የፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅት የደህንነት መሪ ለሙግህኒያህ በባንክ 200,000 የአሜሪካን ዶላር እንዲያስገባለትና ነገሮችን እንዲያሳልስ በያሲር አራፋት ተመርጦ ነበር። ሶቭየቶች ለቃላቸው አድረው ሙግህኒያህንም ሆነ የእስላም ነፃ አውጪ ድረጅትን አይከታተሉም እነሱም በተራቸው ማንንም አያግቱም።

ይህም ታዲያ ሙግህኒያህ በአዲስ አይን እንዲታይ አደረገው። አዎ በአንድ ወቅት የአራፋት ሃይል 17 አባል ነበር። አልጀሪያውያን ከአራፋት ጋር ያለውን ወዳጅነት ተቋርጧል ማለታቸው ስህተት መሆን አለበት። ቢያንስ የሚመገበው ከፍልስጤማዉያን ጎንዳ መሆኑን አውቀናል።

የስሁዱር ሰላማህን እውነተኛ ማንነት ባወቅን ጊዜ ታሪኩ እጅጉን አጓጊ እየሆነ መጣ እውነተኛ ስሙ አሊ ዲብ ይባላል። የተወለደው በ1957 ከሊባኖስ ሺአቶች ሲሆን የአራፋትን ቡድን ገና በልጅነቱ ተቀላቅሎ በኋላ ላይ ወደ ስለላ ተዛወረ። በ1975 በእርስ በርስ ጦርነቱ ወቅት የአንድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ተሹሞ የነበረ በመሆኑ የሙግህኒያህ አለቃ ነበር ማለት ነው። ከእስራኤሉ ወረራ በኋላ ዲብ በአለም አቀፍ ሽብር መሳተፍ ጀመረ። ስሙም በ1984 ጣሊያን ላዲስፓሊ ውስጥ ከተያዘ የሂዝቦላህ ሽብርተኛ የአድራሻ ደብተር ውስጥ ተገኝቷል።

የዲብ ጉዳይ ወደሌላ አበድ አል ላቲፍ ሳላህ የተባለ ጆርዳን ውስጥ በ1950 የተወለደ የፋታህ ስራ አስፈፃሚ ጉዳይ ይመራናል። ቤይሩት ከሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርስቲ ከተመረቀ በኋላ የታወቀ የሺአ ፖለቲከኛ ልጅ አገባ። በተመሳሳይ ጊዜ የፋታህን ስለላ ተቀላቀለ። በ1982 ፋታህ ከቤይሩት ሲወጣ ቀርተው ቤይሩት ውስጥ እስራኤልን ከሚዋጉት ወገን ሆነ። አሊ ዲብ (ስሁዱር ሳላማህ) ከሙግህኒያህ ጋር አገናኝ ድልድይ መሆን እስከሚጀምር ድረስ ተደብቆ ቆየ። ከዚያ ዲሴምበር 17,1985 ቆጵሮስ ውስጥ ከጓደኛው ጋር በጠርሙስ ባሩዶችን ይዘው ተያዙ። ጠርሙሱ የአየር ማረፊያውን ኤክስሬይ መፈተሻ ለመሸወድ የተጠቀሙበት ነበር። ልክ TWA-847 ጠላፊዎች ይጠቀሙበት እንደነበረው። ይኼ ሁሉ ሲሆን ሳላህ ከአራፋት ደመወዝ ይቆረጥለት እንደነበር የኃላ ታሪኩ ያስረዳል። በተጨማሪም ቆይተን እንደደረስንበት አራፋት በሳላህ አማካኝነት ለሙግህኒያህ እና ለሂዝቦላህ እርዳታ ይልክ እንደነበረ ታውቋል።

☼☼☼

ታዲያ የአራፋት ጉዳይ ወደ ኤምባሲው ፍንዳታ እንዳነጣጥር አደረገኝ። በፍንዳታው ተጠርጥረው ከተያዙት መካከል አንደኛው ሙሃመድ ናይፍ ጃዳ የተባለ የፋታህ አባል እንደነበረበት አስታወስኩ። ሊታመን የሚችል ታሪክ ያወራ ብቸኛው ታሳሪ ነበር በእርግጥ የፍንዳታውን ምስጢር ለማፍረጥረጥ ጥሩ ሚና ሊጫወት የሚችል ነው።

ከፍንዳታው ጥቂት ወራት አስቀድሞ ጃዳ የተሰኘ ፍልስጤማዊ በኤምባሲው በጥበቃ ሰራተኛነት ተቀጥሮ ነበር። የፋታህ መኮንን መሆኑንና በፍንዳታው ንድፍ ውስጥ እንደነበረበት ያመነው ወዲያውኑ ነበር። በ1982 መፀው ወር የፋታህ አለቃው አዝሚ ሱግሃይር ኤምባሲው ውስጥ ስራ ፈልጉ እንዲቀጠር አዘዘው። ለምን ብሎ ሳይጠይቅ በቀጥታ ኤምባሲው አካባቢ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሉ የባህር ሃይል ሰራተኞች ጋር ጓደኝነት መስርቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ባህር ሃይል ውስጥ ተቀጠረ።

ወዲያውኑም ወደጥበቃ ክፍል ተዛወረ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላም ሁለት የሉግሃይር መኮንኖች የሚጄይ 17ቱን ስምምነት ለማገዝ ደፋ ቀና እያሉ የነበሩትን አምባሳደር ፎን ሃቢብ እንቅስቃሴ በእንክር እንዲከታተል ተነገረው። እሱም ያለማቅማማት ትዕዛዙን ተቀበለ። ከፍንዳታው ሁለት ቀናት በፊት እነዚያ መኮንኖች ሌላ ሃሣብ ይዘው መጡ። የአሁኑ አመጣጣቸው ግን አምባሳደሩን በማስደንገጥ ሙከራ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ለማሳመን ነበር። ማለትም አምባሳደሩ ኤምባሲው ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ መኪና ወደፊትና ወደኋላ በማሽከርከር ምልክት እንዲሰጣቸው ታቀደ። አፕሪል 18,1983 ጠዋት መንገዱ ላይ እንድ ጠባቂ በስህተት አምባሳደሩ ኤምባሲ ውስጥ ስለመኖሩ ይነግረዋል። መንገዱ ባዶ መሆኑን አረጋግጦም ወደ ውጭ ወጥቶ የመርሴዲሷን የፊት መብራት እያበራ ምልክት ሰጣቸው። ከዚያ ቀጥሎ የሚያስታውሰው ነገር ቢኖር ኮብልጭታና ከታላቅ ፍንዳታ በኋላ ፍርስራሽ ወደ እሱ እየመጣ እንደነበረ ብቻ ነው። በእርግጥ የጃዳ መትረፍ የአፈንጂዎቹ ፍላጎት ሳይሆን በተዐምር የሆነ መሆን አለበት። ከCIA የቀረቡለትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሷል። ሊባኖሳዊው በነፍስ ግድያ ተጠርጥሮ መስቃየት ከጀመረ በኋላ ግን ማንም የCIA አባል ሊያናግረው አልቻለም። እንዲያውም በ1986 ጃዳ የት ,እንዳለ እንኳን የምናውቀው ፍንጭ አልነበረም።

ዋና መስሪያ ቤት ውስጥ ያሉትን ፋይሎችንና መረጃዎችን ካገላበጥኩና ስለ ሀO እና ሙግሀኒያህ መቃረም የቻልኩትን መረጃ ከቃረምኩ በኋላ ወደ ቢይሩት መሄድ ነበረብኝ፡፡ እንዳንፋንፍኩት መረጃ ከሆነ ኢራናዊ ወታደሮች ተጠሳፊዎቹን እንደሚቆጣጠሩ፣ ሙግሀኒያህ TWA 847'ን እንደጠለፈና አሁንም ድረስ ከፈታህና አረፋት ጋር በቅርብ እንደሚሰራ እንዲሁም ለቢይሩት ኤምባሲ ፍንዳታ ፋታህ ለተጠያቂነት የቀረበ ስለመሆኑ በመጠኑም ቢሆን እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ቀጣዩ ስራዬም የሚሆነው ነጥቦቹን የማገናኘት ሂደት ይሆናል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፱

## ነሐሴ 1986 ፤ ሳርናካ-ቆጵሮስ

ፓይለቱ ከ40 ደቂቃዎች በላይ ዘግይቶ ነበር የደረሰው። ኤርፓርት ውስጥ በሚገኝ አንድ ካፍቴሪያ ውስጥ ቁጭ ብዬ አሁንም አሁንም የደቂቃ ቆጣሪውን እየተመለከትኩ እጠባበቃለሁ።

የተሳሳተ መረጃ ደርሶኝ እንደሆነ ኒኮሲያ ጋር ደውዬ ለማጣራት ብፈልግም ከዋና መስሪያ ቤቱ የተሰጠኝ ቀጠን ያለ ትዕዛዝ ስለሄሊኮፕር የበረራ ሰዓት በስልክ ማውራት እንደማይቻል ያስጠነቅቃል። ታክሲ ይዤ በቀጥታ ኒኮሲያ ዘንድ ለመሄድና ምን እንደተፈጠረ ለማጣራትም ዳድቶኝ ነበር።

በንግድ በረራ ደግሞ ወደ ቤይሩት መሄድ የማይታሰብ ነው። ምክንያቱም ሂዝቦላህ እያንዳንዱን ገቢና ወጭ ይቆጣጠራል። ሳልታፈን ከአየር ማረፊያው ከወጣሁ በራሱ ዕድለኛነት ነው። 'በላርናካና ጁኒይህ' መካከል በሚገኘው የክርስቲያኖች የአሳ ማጥመጃ ወደብ በኩል እንዲት መርከብ በማታ መልህከቋን ጥላ ነበር ይሁንና ይህን አማራጭ መጠቀም አልችልም ምክንያቱም ሶርያውያንና ሊባኖሳዊ ተባባሪዎቻቸው ለኢሳማ መለማመጃነት መጠቀም ጀምረዋልና።

እንደገና በላርና በለንደን መካከል ያለውን የሰዓት ልዩነት አሰላሁ። አልተሳሳትኩም። የበረራ የትዕዛዝ ወረቀቴንም ተመለከትኩ በግራ በኩል ላይኛው ጥግ የሄሊኮፕተሩን መነሻ ሰዓትና ፓይለቱን የት እንደማገኘው በእርሳስ ፅፌዋለው።

ተነስቼ በድጋሚ ወደ አየር ማረፊያው ልቃኝ ባሰብኩበት ቅፅበት ሾፌሩ እየሮጠ ወደ ካፍቴሪያው መጣ። በእጁ ክኒፕቦርድ ይዟል። ትንፋሽ እያጠረው «ቤር ነህ» ብሎ ጠየቀኝ።

ወደኒኮሲያ የሚወስደው መንገድ በትራፊክ ስለተጨናነቀ ነው የዘገየሁት ይቅርታ ይደረግልኝ አለኝ።

ከተርሚናሉ ፊትለፊት አቁሞት ወደመጣው ቫን ተጣደፍን። ከኤርፓርቱ ጀርባ አካባቢ የነበረ ጠባቂ ቫኑን አይቶ እንድናልፍ ፈቀደልን። ሾፌሩ በሁለት ኤሮፕሌኖች መሃል እየተሽከረከረ ጉዞውን ቀጠለና ወደ ጥግ አዙሮ በሁለት የዩ.ኤስ ብላክ ሃውክ የጦር ሄሊኮፕረሮች መካከል ገባ። እዛም ቅጠልያ ነበልባልማ ቀለም ያለው ዩኒፎርም የለበሱ ኮማንዶዎች እየጠበቁኝ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ወደ ቤይሩት ነው አይደል የምትሄደው?» ሲል የዕዝ ኃላፊው ጠየቀኝና በርሳዬን ተቀብሎ የህይወት አድን ልብስ አቀበለኝ። «በረራችን ለአንድ ሰዓት ነው ሁለት ሄሊኮፕተሮች እንጠቀማለን ምናልባትም አንደኛው ከወደ ሁለተኛው የሚተርፉትን ያነሳል። የምነግራችሁ ነገር ውሃውን ከነካ በኋላ ለመስመጥ ከአንድ ደቂቃ በላይ እንደማይወስድበት ነው። ታዲያ ወደ ውሃው ለመዝለል እንዳትሞክሩ። መዘውሮቹ እየተሽከረከሩ ስለሚሆን በጣጥሰው የተፈጨ ስጋ ያደርጓችኋል። ሁሉም ነገር በፍጥነት የሚወሰን ነው» ካለ በኋላ ጥቅሻውንና ፈገግታውን መገበን።

«ሌላ የረሳሁት ነገር ደግሞ ... መሬት ላይ የምንቆየው ለ20 ሰኮንዶች ብቻ ይሆናል። ከዚያ በላይ አንድ ሴኮንድ እንኳን መጨመር አንችልም። ድንገት እሳት ከተነሳ በፍፁም ለመዝለለ እንዳትሞክሩ እየተምዘገዘገ ወደ ላርናካ መመለስ የሚፈልግ መቼም ማንም አይኖርም?» አይደል እንዴ??

ሁለቱ ሄሊኮፕተሮች ከቦታቸው ተከታትለው ተነሱ። ቀስ እያሉ ወደ ባህሩ በመዞር አፍንጫቸውን አዘቅዝቀው በሁለት ሰኮንድ ውስጥ ፍጥነታቸውን ከ ዜሮ ወደ 440 ማይል በሰዓት ከነፉ ከ2500 ጫማ ከፍታ ትንሽ ዝቅ ብለን ጉን ለጉን መብረራችንም ቀጠልን። ጥርት ያለ ቀን ነበር የሜዲትራኒያንም ባህር ከታች ሆኖ ያንራል።

ለቤይሩት አስር ደቂቃ ያህል ሲቀረን የዕዝ ኃላፊውም የካርጉውን በር ከፍቶ አየር ሲያስገባ ሁላችንም አንድ ኢንች ተኩል በሚወፍረው ከረጢት በመሸፋፈን ላይ ነበርን። ከዚያም ከውሃው ሃያ ጫማ ያህል ከፍታ ወዳለው ቦታ ሄሊኮፕተሮቻችን አዘቀዘቁ በዚህ ከፍታ መሬት ላይ ያለ ሰው ሊያየን ካለመቻሉም በተጨማሪ ሊተኩሱብንም አይችሉም። እንዲያውም አሁን አሁን ሄሊኮፕተሮች ከዚህም ወርደው እንደሚበሩ ሰምቼያለሁ።

ሊባኖስን ማየት የምችልበት ደረጃ ላይ አልነበርኩም ምክንያቱም ወፍራም ጭጋግ ወደቡን ጋርዶታልና። ይሁንና ጭጋጉን ስንጥቀነው ካለፍን በኋላ ከባህር ዳርቻው አናት ላይ እንደምንገኝ አወቅሁ። ሄሊኮፕተሮቹ ወደ ግራ ታጥፈው ወደ ኤምባሲው በቀጥታ የሚሄዱ መስሎኝ ነበር። ይሁንና አንዱ ሌላኛውን እየተከተሉ በጠባቡ ዋሻ ውስጥ ወደፊት ገሰገሱ። አሁንም የምንበረው በሃያ ጫማ ከፍታ በመሆኑ የአካባቢው ሰዎች ከባንኮኒያቸው እንኳን አስገገው መመልከት ችለው ነበር።

ዋሻው እየጠበበ ሲመጣ ሄሊኮፕተሮቹ ወደ ቀኝ ታጥፈው ቀጥ ብለው ወደሰማይ ለአንድ ሰኮንድ በረሩና ወደ ኮረብታ ወጥተው መብረር ጀመሩ። በጀርባችን በኩል ባለአራት ታሪኩ የምስራቅ ቤይሩት ኤምባሲ በሴፕቴምበር 20/1984 የመኪና ውስጥ አጥፍቶ ጠፊው የአስራ አራት ሰዎችን ግዳይ ሰዎች የቀጠፈውን ፍንዳታ ያስታውሷል። ከ17 ወራት በፊት ከሱ ቀድሞም በውሃው በኩል የነበረው የባለ ሰባት ታሪክ ኤምባሲ በፍንዳታው ወደ ፍርስራሽነት ተቀይሮ የነበረ ሲሆን በፍንዳታው የተራረፉት ቋሚዎች ተደጋግሞ በሚገብኘው ጎብኚዎች ተደጋግፈው የሚዳሰሱ አፅሞች ሆነው አሁንም አሉ።

ሁለት ታጣቂዎች 0.50 ካሊበር መትረየስ ደግነው ማማው ላይ ይታያሉ። ሄሊኮፕተሩ ከማረፉ በፊት አንገቱን የሚያወጣ ሞኝ ቢያገኙ አናቱን የሚበረቅሱት ይመስላሉ። እነዚህ ሰዎች አምርረው ነው የሚሰሩት። ከሁለት ወራት በፊት ኤምባሲውን በጣም ተጠግቶ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያበረረን የተባበሩት መንግስታት ሄሊኮፕተር ሲያፈነዱ አብራሪውንም ጉድተውት እንደነበር ይታወሳል። ወርጂ ዞር እንዳልኩ ሁለቱ ብላክሃውኮች ከመቀፀበት ከርቀት ወደ ነጥብነት ተቀይረው ሜዲትራኒያንን እያጋመሱት ነበር። ወደ ቤይሩት ከሃምሳ ጊዜ በላይ ከበረርሁ በኋላ እንኳን የሚሰማኝ ስሜት የገሃነም ጥልቅ ውስጥ የምገኝ ዓይነት ነበር።

የሄሊኮፕተሮቹ መሄድና የተደገነው የ 0.50 ከሊበር መትረየስ ወደ ከተማው ውጥረቱን ረገብ አደረገልኝ።

አዲሱ ባለሁለት ታሪክ የቤይሩቱ ኤምባሲ ቪላ ከፍርስራሹ መቶ ያርድ ያህል የሚርቅ ሲሆን በዓለም ላይ ከፍተኛ ጥበቃ ከሚደረግላቸው ንብረቶች መካከል አንደኛው ነው። ኤምባሲውን የከበበው 40.800 ያርድ ስኩዌር ቦታ የኤሌክትሪክ ኃይል በተለቀቀበት የሽቦ አጥር ምሽግ መሰል ግንቦች፣ ማማዎች፣ የመትረየስ መደገኛዎችና በአሸዋማ ደለሎች የታጠረ ነው። ቪላውን ከሮኬቶች ጥቃት ለመከላከልም አንድ ጫማ ውፈረት ያለው የብረት ፍርግርግም ይገኛል። ጣራው በፀረ-ሮኬቶች ተሞልቷል። ከስድስት መቶ በላይ ጠባቂዎች ያሉት ሲሆን ይህም ቁጥር ኤምባሲውን በወታደር ብዛት ከሃገሪቱ አራተኛ ያደርገዋል።

የጥበቃ አጥሩ ይኸን ያህል እየተጠናከረ እንኳን ባለፉት ሶስት አመታት CIA ሁለት ሃላፊዎች፣ አምስት መኮንኖች እና በርካታ መረጃ አቀባዮቹን አጥቷል። ቤይሩትና ሊባኖስ አስቸጋሪ ቦታዎች ብቻ አልነበሩም። ከጃንዋሪ 1984 ወዲህ 37 የውጭ አገር ዜጐች የታገቱ ሲሆን ከመካከላቸው ስድስቱ ደግሞ ተገድለዋል።

ወደ ቤይሩት በሄድኩበት ወቅት እንኳን ሹብርተኞቹ ኤምባሲው ወደሚገኝበት ምስራቃዊ የክርስቲያኖች ቦታ እየተጠጉ ነበር። የፈረንሳይ ጦር አታሼ ፈረንሳይ ኤምባሲ ውስጥ የተኮሰበት ሳይታወቅ ተነጥሎ ተገድሏል። የፈረንሳይ የስለላ ሰዝ ምክትል ኃላፊ ከሊባኖስ የደህንነት ቢሮ ፊትለፊት በመትረየስ ወንፊት ሆኗል አብሮ ይሰራ የነበረ ሊባኖሳዊ መኮንን እንደጠቆመበት ጥርጥር የለውም። ሌሎች ሶስት የፈረንሳይ ታጣቂዎች በእረፍት ቀናቸው ከሰዓት በኋላ በጥይት ተደብድበዋል። የፈረንሳይና የአሜሪካ መኮንኖች በተመሳሳይ መልኩ ኢላማ ውስጥ በመሆናችን እነዚህን ግድያዎችን እንደቀልድ አንመለከታቸውም።

ብጥብጡን ለመከላከል ወደ ቤታቸው ለመሄድ ካልሆነ በስተቀር ማንም የአሜሪካ መኮንን ከኤምባሲው ቅጥር ውጭ እንዳይወጣ ትዕዛዝ ተላልፏል። ሲንቀሳቀሱ እንኳን ጥይት በማይበሳቸው መኪኖች ሆኖ በበርካታ የታጠቁ ጠባቂዎች ከፊትና ከኋላ አጅበዋቸው ነው። ኤምባሲው ውስጥ የሚኖሩት ደግሞ ኡዚ ደግነው በሚንቀሳቀሱ ፓትሮሎች ይጠበቃሉ። በጣም እርግጠኛ ለመሆን ሲባል የስቴት ዲፓርትመንት መኮንኖች ለዎችን የሚያነጋግሩት ኤምባሲው ውስጥ በብረት አስፈንጣሪ መጋረጃ ተከልለው ነው።

ከግቢው መውጣት የሚችለው አምባሳደሩ ብቻ ሆኖ እሱም ሳይረን በለቀቁ 12 መኪኖች ታጅቦና ጠባቂዎቹም ትራፊኩን ለማቅለል ወደ ሰማይ እየተኮሱ ነው። ዋናዋ መኪናም ብረት ለበስ ስትሆን ጠባቂዋም 0.50 ካሊበር መትረየስን የደገነ እጁን ከቃታው የማይነቀል ነው። የተባበሩት መንግስታቷን ሄሊኮፕተር ከመታት ጠባቂ ይልቅ ይኸኛው በጣም ያመረረ ነው። አምባሳደሩ ሲንቀሳቀስ ማየት ደጋግመው ለተመለከቱት ሊባኖሳውያን እንኳን አስቂኝ ትርዒት ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

በ CIA በኩል በህይወት ለመሰንበት የምንከተለው አካሄድ ለየት ያለ ነው። መሳሪያ መያዛችን ጥርጥር የለውም። ሆኖም 12 ዓመት ዕድሜ በላይ የሆነ ማንኛውም ዜጋ መትረየስ በነገተባት አገር ትናንሽ የጦር መሳሪያዎች የሚያዋጡ አልሆኑም ከሽብርተኞች በተማርነው መሰረት ራሳችንን ቶሎ ቶሎ እንቀያይራለን፤ አካባቢም እንለዋውጣለን እናም ፍፁም እንቅስቃሴያችን በማይገመት መልኩ ነበር። ወደ 30 የሚጠጉ የመኖሪያ አፓርትመንቶችና ከሁለት እጥፍ በላይ መኪኖች የነበሩን ይመስለኛል። መኖርያና መኪና በቀያየርኩ ቁጥር ተንቀሳቃሽ ኢላማ ትሆናለህ። በጣም ፈጥነህ ስትንቀሳቀስ ደግሞ የማይመታ ኢላማ መሆን ትችላለህ። አንድ ሌሊት ኢሽራፍያህ ውስጥ በሚገኝ አፓርትመንት ካሳለፍኩ የሚቀጥለውን ከቤሩት በስተሰሜን 30 ማይል በሚርቅ የባሕር ደርቻ አድራለሁ። አንዳንዴ በቀን ውስጥ ሁለት ወይም ሶስት መኪኖች እንቀያይራለን። የምንጠቀምባቸው መኪኖች ሌላው ሊባኖሳዊ ከሚጠቀምባቸው በምንም የተለዩ አይሆኑም። ቀስ በቀስ የ1964 ሞዴል ማርቼዲስ አረንጓዴ ታክሲ ማሽከርከር ጀመርኩ። ምንአለፋችሁ ያለችግር ልክክ ማለት ቻልሁ። ማንኛውም ሊባኖሳዊ ታክሲዋ ውስጥ ያለው አሜሪካዊ መሆኑን ሳይጠረጥር እጁን ሲያውለበልብልኝ የሚችልበት ደረጃ ደረስሁ።

የሚመስል ነገር ባይሆንም ቤይሩት ውስጥ መስራቴን ወደድሁት። የዕዝ ቢሮዎች ውስጥ በስብሰባ ከመታረክና ነጋ ጠባ ወረቀት ከማገላበጥ የበለጠ እየወደድሁት የመጣሁት በቤይሩት ጉዳናዎች መንቀሳቀሱን ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ስራችንን ባግባቡ ከመስራት እንቅፋት ከሚሆነን ቢሮክራት ከሆነው ከዋሽንግተን ፓለቲካ ለመራቅ መቻሌ ነበር።

... አሁን ስደርስ ያገኘሁት አለቃ ጄሪ የተባለው የቀድሞ የአየር ወለድ መኮንን ሲጋራ የሚያጨስ ሲሆን በስራው ከሁኔታዎች ጋር ራሱን የሚቀያይር ነበር ጄሪ ስለቦታው አደገኛነት ያለው አመለካከት ጤናማ ስለሆነ እንዴ የምሰራውን የማውቅ ሰው መሆኔን ካረጋገጠ በኋላ በነፃነት እንድሰራ ፈቀደልኝ። ስራዬን በአግባቡ እስከሰራሁና መረጃ ባግባቡ እስከሰበሰብኩ ድረስ ቢሮ መገኘቴ የግድ አልነበረም።

ቤይሩት ውስጥ መረጃ አቀባዮችን መቅጠር ከሌላው አለም ለየት ይላል። ለነገሩ ቤይሩት ራሷ ከሌላው አለም በእጅጉ ትለያለች። አንድ ጊዜ ፍልስጤማዊ መረጃ እንዲፈለፍልልን ፈለግንና መርማሪ እንዲላክልን በጠየቅነው መሰረት በርኔ የተሰኘ ቀጫጫ ጥቁር አሜሪካዊ ተላከልን። በርኔ ትላልቅ ፍሬም ያላቸው የፕላስቲክ መነፅሮች የሚያዘወትር ሲሆን ቤይሩትን ገና ከላርናካ በሄሊኮፕተር ሲነሳ ጀምሮ ጠላት።

የበርኔንን ዕቃ ድብቅ ቦታ አስቀመጠን በቀጥታ ከተማውን አቋርጠን ወደ ምርመራው ቦታ ሄድን ደስ የሚል ቀንም ነበር። በርካቶች በባህሩ ዳርቻ እየዋኙና ወዲያ ወዲህ በማለት በመዝናናት ላይ ነበሩ። ከአረንጓዴው ቀጠና የሚሰማው የመሳሪያ ድምፅ ያስወትሮው ፀጥ ረጭ ብሏል። በርኔ ስለቤይሩት የነበረው ስሜት እየተሻሻለ ሲሄድ ይታወቀኛል። በጣምም ዘና ማለት ባይችልም አሁን ቢያንስ ወደ ቤይሩት የላከውን አለቃውን አፍንጫ የመስበሩን ሃሣብ የተወው ይመስለኛል።

ከአሽራፊያህ በፊት ሃዝሚያህ ወደተሰኘው የቤይሩት አቀበታሙ ክልል አቅንተን ነበር። እናም በየጫካው በርካታ ጠመንጃዎች ተደግነው ብናይም ሰፈሩ ግን የመኮንኖች



t.me/OLDBOOKSPDF

መኖርያ በመሆኑ ተረጋግተናል። በርኔ የማውጣጣቱን ስራ ሲነድፍ ለፍልስጤማዊው እንዲያቀርብልኝ የምፈልጋቸውን ጥያቄዎች እየፃፍኩኝ ነበር። ፍልስጤማዊው እንግሊዘኛ አቀላጥፎ የሚናገር ስለነበር እኔ ለአስተርጓሚነት ስለአልተፈለግሁ ከጆርባ ባለው ክፍል ውስጥ ማሸለብ ፈለግሁ።

ጎኔን አሳርፌ ገና አይኔን መክደን ስጀምር መስኮቶችን የሰነጣጠቀ ታላቅ ፍንዳታ ህንፃውን አናወጠው፣ አፍታም ሳይቆይ ሁለተኛው ተደገመ።

በርኔ የመኝታ ቤቱን በር በርግዶ ገብቶ «እሰቀልን» በማለት ጮኸ። ተረጋጋ «የባረቀ ነው ለኛ የሚያሰጋ አይደለም» አልኩት ለማረጋጋት ለነገሩ እውነቱን ነበር፡፡ ወደምዕራብ የተተኮሰ መሆኑን በድምጹ እውቂያለሁ፡፡ «በድምፁ እኮ ወደ የት የተተኮሰ እንደሆነ መለየት ትችል ነበር» ባለማለቱ ስህተት ፈፀምኩ፡፡ ምክንያቱም ምን ያህል ፍርሀት ልቡን እንደሰለበው ከፊቱ ድንጋጤ ማንበብ ችዬ ነበርና፡፡

«አይደለም አንተ እንዳሰብከው አይደለም» ሲል ሳቀብኝ በርኔ ጩኸቱ አደንቁሮሃል በሚል ስሜት፡፡ እውነታው ይህ እንዳልሆነም ገብቶኛል የሞተ አይነት ሆኖ ነበርና፡፡ በደም ስሮቹ የቀዘቀዘ ደም በሚዘዋወሩበት አካል ባለበት ሁኔታ ሳውጣጣው የምችልበት ምንም አይነት መንገድ እንደሌለም ተረዳሁ፡፡

ሁላችንም ብንሆን ቤሩት ውስጥ በቆየንባቸው ጊዜያት የውጭ አገር ዜጎችም ጭምር እንደዚያ አይነት ደንዳና ባህሪ ያዳበርን ይመስለኛል፡፡ ውጊያው የሚካሄደው ሌሳ ቀጠና እንደሆነ ነው ለሁሉም ፩የሚሰማን፡፡ አንዳንዴ እንኳን በምኖርበት አፓርትመንት አካባቢ ከምዕራብ ቤይሩት ሚሊሻዎች 107 ሚ.ሜ የሮኬቶች ጥቃት ይሰነዘርና ብዙ ሳይቆይ ወደያውኑ እረጭ ይላል፡፡ ከደቂቃዎች ልብ የሚያስደልቅ ውጥረት ከነገሰ በኋላ ህይወት ወደነበረችበት ትመለሳለች፡፡ በቃ! ምን አለፋችሁ ቤይሩት እንደዚያ ነች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፳

## መጋቢት 1987 ፣ ቤይሩት-ሊባኖስ

የኤምባሲውን ፍንዳታ ጉዳይ ማንሳት በሮማውያን ዘመን የነበረን በመሬት መንቀጥቀጥ የፈራረሰንና በእሳተ ጎመራ ድብልቅልቁ የወጣን ቲያትሪ ቤት መልሶ የመገንባት ያህል ነበር።

እንዲያውም ከዚያም የከፋ ገፅታ ነበረው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። በክርስቲያኖች ምስራቃዊ ቤይሩት ስንቀመጥ ጭለማ ውስጥ የመስራት ያህል ነበር። በርካታ መረጃ አቀባዮቻችን ወደሚገኙበት ምዕራባዊ ቤይሩት ማቋረጥማ የማይታሰብ ነው። ከዚህ በባሰ ደግሞ ሂዝቦላን ወይም ሌላ የሺዓ እስላማዊ ቡድን ነጥሎ የሚያስቀምጥ መረጃ አቀባይ አልነበረንም። ኢማድ ሙግህኒያህን ወይም የእስላሚክ ጀሀድ ድርጅትን መቅረብ የሚችል ማንም አልነበረም። እንደዚህ መሆኑ ደግሞ መረጃ አቀባዮቻችን እራሳቸው ሚስጥር የሚያውቁ ሳይሆኑ ሚስጥር የሚያውቅ ሰው የሚያውቁ እንዲሆኑ አደረገብን።

ከነበሩኝ ምርጥ ጆሮ ጠቢዎች መካከል አንዱ ማለትም ፋሪድ ብዬ የምጠራው የፍሪላንስ ጋዜጠኛ ነበር። ፋሪድ ክርስቲያን ቢሆንም የስራው ፀባይ አረንጓዴውን ቀጠና እንደልቡ እንዲያቋርጥ እድል ከፍቶለታል። እራሱ በራሱ ፋሪድ ከገዳይ ፈገግታው ጋር በየትኛውም የአለም ክፍል እንደዋዛ ማለፍ የሚችል ብልጣብልጥ ነበር። በመላው ሊባኖስ በርካታ ጓደኞች ያፈራ ሲሆን ከሙግህኒያህ ወይም ሂዝቦላህ በስተቀር ከፈለገው ጋር እንደልቡ ማውራት ይችላል። እኔም ዕቀባውንም ቢሆን ወድጄለታለሁ ምክንያቱም ካስቸጋሪዎቹ ሰዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት የሚያተርፍለት ነገር ቢኖር ክትትል ብቻ ነው የሚሆነው። እንደውም በዚያን ወቅት ሂዝቦላ ግራ የተጋባበት ጊዜም ነበር። ከአመት በፊት ማርች 8,1985 ሙሐመድ ሁሴይን ፋድላላህ ከተሰኙ የሺአ መሪ ህንፃ ስር በፈነዳ የመኪና ላይ ቦምብ ሰማንያ ሰዎች መገደላቸው ሂዝቦላ ወዳያውኑ አፈንጂዎችን አሰልጥኗል በሚል CIA ላይ እጁን እንዲቀስር አድርጎታል። ይሁንና የማይመስል ነገር ነበር። ማንም ስለመኪና ላይ ቦምብ ለሊባኖሳውያን ሊያስተምር የሚችል አይኖርምና። ለነገሩ እዚህ ስነ - አመክንዮ ዋጋ የለውም በሂዝቦላህ ፊት የተጠረጠረ ሁሉ በጅምላ ከመታረድ አይድንምና።

ለፋሪድ የሰጠሁት የመጀመሪያ የቤት ስራ ለሀዐ ቅርብ ናቸው ብለን ስለጠረጠርናቸው ሰዎች የህይወት ታሪክ መረጃ እንዲያሰባስብ ነበር። እኔም በሱ ላይ ሊኖር የሚችለውን ጫና ለማቅለል አረንጓዴው ቀጠና አካባቢ ሲን-አል-ፊል በተሰኘ ሰፈር ቤት ተከራየሁ። ሁሌም



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀድሜ እየተገኘሁ ፋሪድ ከነተወጣጠረ እታቼ ቦርሳው በመኪኖች ስር እየተሽሎከለከ ሲመጣ እጠባበቀው ነበር።

እንደገባ ስስሳ መጠጥ አተረብኩለትና በቦርሳው ያጨቀውን በሙሉ ሶፋ ላይ ይዘረግፈዋል። የምዝገባ ወረቀቶች፣ የፓርቲ አባልነት ዝርዝሮች፣ የቆዩ የጋዜጣ ላይ ዕሁፎች፣ ስለሂዝቦላ ሰላማዊ ሰልፎች የተነሱ ፎቶዎች እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። አብዛኛዎቹ የማይጠቅሙ ቢሆኑም አንድም ቀን እንዲያመጣቸው ከማበረታታት ተቆጥቤ አላውቅም። የሚጠቅመውን ከመካከሉ ፈልጎ ማውጣት የኔ ፋንታ ነበር። ይሁንና ፋሪድ ጠቃሚ ነገር ባመጣ ጊዜ ሁሉ ማበረታቻ ገንዘብ እሰጠዋለሁ ምክንያቱም ቢይሩት ውስጥ ገንዘብ የ CIA ችግር አልነበረም።

ከTWA - 847 ጠላፊዎች መካከል አንዱ የነበረውና የሙግሂኒያህ ቡድን አባል እንደሆነ ስለምንጠረጥረው ሙሐመድ ሃማዳህ ፋሪድ መረጃ እንዲያሰባስብልኝ አድርጌ ነበር። እሱም አራት ሳምንታት ያህል ከወሰደበት በኋላ የደስታ ሲቃ በተቀላቀለበት ድምፅ እንዴት የምዝገባ ጽ/ቤቱን አግኝቶ ተደብቆ በመግባት ተመሳሳይ የኒኬል ቁልፍ አስቀርጾ የሃማዳህ ቤተሰብን መረጃ ማምጣቱን ገለፀልኝ።

ከዘመናት አንዱ ብቻ እንደሚገኝ መረጃ ተጠንቅቄ አነሳሁት። በ1929 አል ሳዋናህ ውስጥ ከተወለዱት የመሐመድ አባት አሊ ሀሰን ሃማዳህ ጀምሮ በ1931 ከሂርባት ውስጥ የተወለዱት እናቱ ፋትማህ አብድ አል ሃሰን ዳቡክ ድረስ የቤተሰቡ ታሪክ ተቀምጧል። የሂዝቦላህ አደገኛ መሪ የሆነውን የመሐመድ ታላቅ ወንድም አብድ አል ሃዲ ሃማዳህን ጨምሮ በህይወት ያሉ ወንድምና እህቶቹ በሙሉ ተዘርዝረዋል።

ኑሮውን በፀረ-ሽብር ላይ ያልመሰረተ ግለሰብ ስለምን የአንድ ቅጥረኛን ህይወት ለቀላል መረጃ ብሎ አደጋ ላይ ይጥላል የሚል ወቀሳ ሊሰነዝርብኝ ይችላል። እኔ ግን ይህ መረጃ እንደቁልፍ ሆኖ ሊያገለግለኝ እንደሚችል አውቃለሁ። መረጃዎቹም አድራሻ፣ ስልክ ቁጥሮችንና የጋብቻ ትስስሮችን ይጠቅሙናል ሌሎች ቅጥረኞቻችን የሚያቀብሉንን መረጃ ለማመሳከርም ይጠቅሙናል። እኔም ሆንኩ ሌላ መርማሪ ፓሊስ አንድ ወቅት ሙሃመድ ሃማዳህን በቅርብ የሚያውቅ ቅጥረኛ ማግኘታችን አይቀርም። እንግዲህ ያኔ ነው የነበረንን መረጃ ነቅሰን የምናውቀውን ማረጋገጥ የምንችለው። ለምሳሌ የሃማዳህ መረጃ እንደሚያመለክተን ከሆነ የሙሃመድ እህት የሆነችው ሰሚራ የተወለደችው ፌብርዋሪ 13,1969 ሲሆን እስካሁንም ሳታገባ ቡርጅ አለ በርጅናህ ውስጥ በሚገኘው የሃማዳህ ቤት ውስጥ ነው የምትገኘው እናም ቅጥረኛው ስለ እርሷ የሚያውቀው ነገር ከሌለ የሚያወራው ነገር ሁሉ ውሸት መሆን ይገባናል ምናልባት ያለውን ያህል ሳታገባ ቡርጅ አል በርጅናህ ውስጥ በሚገኘው የሃማዳህ ቤት ውስጥ ነው የምትገኘው እናም ቅጥረኛው ስለ እርሷ የሚያውቀው ነገር ከሌለ የሚያወራው ነገር ሁሉ ውሸት መሆኑ ይገባል ምናልባትም ያለውን ያህል ለሙሃመድ ቅርብ ላይሆን ይችላል ወይም እኛን ግራ ለማጋባት የተላከብን ተኩላም ይሆናል ማለት ነው። መረጃ ደግሞ ዕውቀት ገንዘብ ጉልበትና ራስን መጠበቂያም ማማ ነው ማለት ነው። በኋላ ላይ ታዲያ ሙሃመድ ሃማዳህ ጃንዋሪ 13,1987 ፍራንክፈርት አየር ማረፊያ በከፍተኛ ደረጃ ተቀጣጣይ የሆነውን ሜታይል ናይትሬት በጠርሙስ ይዞ ሊያልፍ ሲል መያዙ አልቀረለትም ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፋሪድ እንደያውም የአንድ ሽብርተኛን ጉዳይ ለመፍታት ጠቅሞናል። ጥር 25,1986 አራት ሊባኖሳዊ አሸባሪዎች ከባግዳድ የተነሳን የኢራት አውሮፕላን ጠልፈው ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ በመከስከስ አብራሪዎቹን ጨምሮ መንገደኞቹን በሙሉ ጨረሷቸው። ኢራቃውያን እንደነገሩን ከጠላፊዎቹ አንደኛው ሪባል ካህሊል ጃሉል የተባለ በደቡባዊ ክፍል የሚገኝ ሺአ ነበር። ታሪኩን ለማረጋገጥ ስንጥር ፋሪድ የጃሉል ቤተሰብ ቡርጅ አል በረንጅህ ውስጥ የምዝገባ ቁጥር 117 መመዝገቡን የሚገልፅ መረጃ አገኘን። ከካህሊል ጃሉሉ ልጆች ዝርዝር ውስጥ በፌብርዋሪ 10,1967 የተወለደው ሪባል ካህሊል ጃሉል ስም ይገኛል። የፋሪድ የወሬ ምንጭ ባገኘለት መረጃ መሰረት ሂዝቦላን መስጊድ ግድግዳ ላይ የተቀረው የሪባል ጃሉል የምስል ፓስተር አገኘለት። በመጨረሻም ፋሪድ ሪባል በአንድ ወቅት የተጠቀመበትን ፓስፓርት ቅጅ ለማግኘት ቻለ። ስሙ የተለየ ቢሆንም ሮቶው ግን ሂዝቦላህ ውስጥ ከተገኘው ፓስተር ጋር ተመሳሳይ ነበር። ዞረን ዞረን ግን አንዲት ተጨማሪ መረጃ ወደካዝናችን አስገባን ማለት ነው።

✡✡✡

እንደልማዳችን ፋሪድ አግሩን እንደነቀለ ስልኩን እንጠልፋለን። ቤይሩት ውስጥ የማንኛውም ሰው ስልክ ይጠለፋል። በየትኛውም መንገድ ብትሄድ የስልክ ሽቦዎች ተጠላልፈው ታገኛለህ። ከዚህ ውስጥ ግማሹ በስተጀርባው አላማ ያዘለ ነው። ለምሳሌ ቤይሩት ውስጥ ወደሚገኘው እድሜ ጠገብ የንግድ ማዕከል ሃምራ ስትገባ አንድም የስልክ መስመር ባታገኝ የስልክ ካምፓኒው መጥቶ እንዲያስገባ መጠበቅ የለብህም። የስልክ ኩባንያው ሙሉ በሙሉ ተበትኗል። ያልህ አማራጭ የሚሰራ መስመር ፈልገህ መህጋዊም ሆነ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ሙጭጭ ማለት ነው። ከሃምራ ሆቴሎች አንድ መስመር መስረቅ ትችላለህ። የስልክ ዕዳ መጥቶባቸው ስለማያውቅ መሰረታቸውን ሊያውቁ አይችሉም። እንደዚህ ፍሪላንስ ስልክ በተንበሸበሸበት አገር ስልክ መጥለፍ በጣም ቀላል ነው።

እኔም ታዲያ የተጠለፉ የስልክ ቅጅዎችን በማሰስ የሪባል ጃሉልን ዱካ ለማግኘት መጣር ጀመርኩ። ጥረቴም ተሳክቶ በአብድ አል ሃዲ ሀማዳህ በተባለው የ TWA ጠላፊ ወንድምና በጂሃድ ጃሉል መካከል የተካሄደ የስልክ ጥሪ አገኘሁ። የጃሉሉ ቤተሰብ በጣም ሰፊ በመሆኑ ሪባልና ጂሃድ ስለመዛመዳቸው እርግጠኛ አልነበረኩም። የጃሉልን የምዝገባ መረጃዎች ሳገላብጥ ግን ጂሃድ ካህሊል ጃሉሉ የሪባል ታላቅ ወንድም መሆኑን አረጋገጥኩ። በተጨማሪም ሚያዚያ 16,1986 የተደረገ መሳጭ የስልክ ምልልስም አገኘሁ። በሊባኖስ ፓሊስ ውስጥ የሚሰራ ሙሃመድ ሙራድ የተባለ የሂዝቦላ አባል ወደ ሀ0 ቢሮ ይደውልና ሙግህኒያህን ማግኘት ይችል እንደሆን ሲጠይቅ እንደሌለ ሲነገረው በየተራ አብድ አል ሃዲ ሃማዳህ፣ ጂሃድ ጃሉሉ እና ዙሃይር ጃሉሉን ለማግኘት ይጠይቃል። ዙሃይ 204 የሪባል ሌላኛው ወንድም መሆኑን ከምዝገባ ዶክመንቶቹ አረጋገጥኩ። አሁን በእ ቢሆን ከኢራቁ የአውሮፕላን ጠለፋ ጋር ሙግህኒያህን የሚያያይዘው ነገር እንዳለ ገብቶኛል። ሙራድ በበኩሉ ዘግየት ብሎ ቤይሩት ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ውስጥ አራት አሜሪካዊ ፕሮፌሰሮችን እንዲታፈኑ አድርጓል።

በዚህ አላበቃሁም አንድ ሌላ መረጃ አቀባዬ እንደነገረኝ ከሆነ የጃሉል ቤተሰብ የሚኖረው ከሙግህኒያህ በአጉራባች አይን አል ዲልባህ በተሰኘ ሰፈር መሆኑን ነበር።


t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲያውም ከካንዲ መጋዝን በላይ ከሙግህኒያህ ቤት ብዙም ሳይርቅ የሚገኘውን የአፓርትመንታቸውን የውጭ ንድፍ ለማግኘት ቻልኩ። ስለጂሃድ ተጨማሪ በርካታ ነገሮችን አጣራን ማለትም የመኪናውን ታርጋ፣ ስልክ ቁጥሩን ብሎም የሽጉጡን አይነት የቤተሰቡን ታሪክም አባቱ ስካራም እንደነበሩ ጂሃድ ኩሽና ውስጥ መሳሪያ ሲወለውል ባርቆበት በድንገት እናቱን እንደገደላት ጭምር አጣራን።

ፋሪድ የሚሰበሰበውን አይነት መረጃ የሚያቀብሉ ሌሎች አምስት ቅጥረኞች ነበሩኝ። ቀስበቀስ የሙግህኒያህን ቡድን አደረጃጀት አስቀመጥኩ። ብዙ ጊዜዬን አጠፋ የነበረው ሰውን ከሰው ለማገናኘት ስጥር እና አሳሳች መረጃዎችን ስሰርዝና በመረጃ መቀነቴ ላይ ስደርት ነበር። የጥልፍልፎቹ ንድፍ የቦይንግ 747 ሞተርን የሽቦ ቅጥልጥሎሽ መስሉ ነበር። እናም ታዲያ ዝርዝር ጉዳዮችን ሳጠና ሙግህኒያህ እንዴት የቡድኑን ምስጢር ጠብቆ እንዲቆይ እንዳስቻለው አመለከተኝ። እያንዳንዱ ግለሰብ በደም የተሳሰረ፣ ፋታህ ውስጥ አብሮ የተዋጋ ወይም ከአይን አል ዲልባህ አካባቢ የተሰባሰበ ነው። የአይን አል ዲልባህ ወሮበላዎች የሚል ስያሜ መስጠት ጀምረን የነበረ ቢሆንም ህዐ እንደዚያ ለመፈረካከስ አስቸጋሪ ቡድን የሆነው በተመሳሳይ ሁኔታ መሆኑን ስናስብ ግን ነገሩ ግራ አጋባን።

☼☼☼

በቅጥልጥሉ ጥናት ከሙግህኒያህ ጉን አብሮ መነሳት የጀመረ አንድ ሌላ ስም ሁሴይን ካህሊል ነበር። ራሱ ካህሊል የቀድሞውን የኤ.ቢ.ሲ ባልደረባ ቻርለስ ግላስን በመጥለፍ ሂደት እስከተሳተፈበት ጊዜ ግን የጎላ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር።

ግላስ ወደ ሊባኖስ በጥር 1987 ሲመጣ ለመፅሃፍ ስራ የሚሆን ምርምር ለማካሄድ ነበር። ከሊባኖሳዊት እናት የተወለደ በመሆኑ ከየትኛውም አሜሪካዊ ሪፓርተር በተሻለ አካባቢውን የሚያውቀው ሲሆን በጠለፋው መሃከል በካሜራ የTWA-847 ካፒቴንን ቃለ መጠይቅ በማድረጉ መጠነኛ ዝናን ማትረፍ ችሏል። ይሁንና ሊባኖስን አብጠርጥሮ ባለማወቁ ጉዞውን ከማስተዋወቅ ባለመቆጠቡ ስህተት ሰራ። የግላስን ሲደንን የመንበኘት ጭምጭምታ ኢራናውያን እንደሰሙ አንድ የፓስዳራን መኮንን ወደ ሁሴይን ካህሊን ቤት በመሄድ ግላስን እንዲያግተው አዘዘው። ምንም እንኳን አገታው መቼና እንዴት የሚጠለፍበት መኪና ታርጋ ሳይቀር መረጃው አስቀድሞ ቢደርሰንም ከግላስ ጋር መገናኘት የምንችልበት ምንም ዓይነት መንገድ አልነበረንም። አየር ማረፊያው አጠገብ ሲታገት እጃችንን አጣጥፈን ከመመልከት በዘለለ ለእርዳት እጃችንን መዘርጋት አልቻልንም።

ምንም እንኳን ፈረሱ ከጋጣው ያመለጠ ቢሆንም ፋሪድ ስለካህሊል የሚችለውን ሁሉ እንዲያጣራ አደረግሁ። የቤተሰቡን የምዝገባ ወረቀቶች ለማምጣት አንድ ሳምንት ያህል አልፈጀበትም ነበር። የካህሊል ሙሉ ስም ሁሴይን አሊ ሁሴይን ጃዋድ ካህሊል ሲሆን አባቱ አሊ እናቱ ሰሚራ ካህሊል ይሰኛሉ። በአንድ ወቅት የሊባኖስ የፓርላማ አባል ሆኖ ሊመረጥ ከሚችለው ነባር የሂዝቦላ አባል እህት ጋር በጋብቻ ተሳስሯል። ሌላ ቅጥረኛም በርከት ያሉ በካህሊል ፎቶዎችን አመጣልኝ።

እስካሁን የተገኘው መረጃ አጥጋቢ ቢሆንም የቀድሞ የፋታህ አባል ለነበረ መረጃ አቀባዬ የካህሊልን ስም ስሰጠው ግን ታሪኩ ልብ ወደ ሚሰቅል ደረጃ ተሸጋገረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እዚህ ላይ ሰሚር ብዬ የምጠራው መረጃ አቀባዬ የቀድሞ የሊባኖስ ሚሊሺያ መኮንን ሲሆን በ1975 ከውጊያ በኋላ በሆቴል እንዲሰራ በፋታህ ተቀጠረ። በ1982 አረፋት ከቤይሩት ከወጡ በኋላ ሳሚር ለፋታህ መስራቱን ቢያቆምም ከተወሰኑ ቀሪ ምስጢራዊ አባላት ጋር የነበረው ግንኙነት እንደቀጠለ ነበር።

ሰሚርና እኔ የተገናኘነው በክርስቲያኖች ምስራቃዊ ቤይሩት አሽራፊያህ ውስጥ በቀድሞ ውሽማው አፓርትመንት ውስጥ ነበር። ሲመጣ አንድ ወይም ሁለት ወታደሮች ከጉኑ አይታጡም። ሙስሊም በመሆኑ ክርስቲያኖች አንድ ቀን ሊያፍኑት እንደሚሞክሩ ይጠራጠራል። ከወታደሮቹ ጋር የተላመደን ቢሆንም ወገባቸውን በዝናር ታጥቀው አፓርትመንቱን በመሳሪያ በተጠንቀቅ ሲጠብቁ ማየቱ ግን ያናድዳል።

ከግላስ መታገት በኋላ በነበረን የመጀመሪያ ግንኙነት አጋማሽ ላይ ምንም ቃል ሳልተነፍስ ለሰሚር ሶስት ፎቶዎች አቀበልኩት። ሁለቱ የግራ ክንፍ አባላት ፍልስጤማውያን ሲሆኑ ስለእነርሱ የሚያስጨንቀኝ አንዳች ነገር አልነበረም። ሶስተኛው ግን ካህሊል ሲሆን መስጊድ ውስጥ ከበርካታ አማኞች ጋር እየሰገደ የሚያሳይ ነበር።

ሰሚር ወዲያው የካህሊልን ፎቶ መልሶ ሰጠኝና «ይኸውና ሁሴን ካህሊሊ» አለ አመልካች ጣቱን ካህሊሊ ላይ እንደቀሰረ፡፡ «በ60ዎቹ መጨረሻ ፋታህ ውስጥ ነበር፡፡ ይመስለኛል በ1971 ነው የተቀላቀለው፡፡ ለሁለት ዓመታት ያህል አብረን ሰርተናል»፡፡

«አሁንስ»?

«በ1982 ካህሊል እስራኤሎችን ቀድሞ ከቤይሩት ወጥቷል የደህንነት አዛዥ በመሆንም ከ ሁሴይን አል ሙሳዊ ጋር እንደተፈራረመና የሺህ አብደላ ምሽጉች ሲማረኩም ጦሩን የመራው እሱ እንደነበረም ሰምቼያለሁ። ከዚያ በኋላ ምን እንደገጠመው አላውቅም ለማጣራት እሞክራለሁ አለኝ።

ያን ቀን ከሰዓት በኋላ ስለካህሊል የሚታወቀውን ሁሉ እንዲላክልኝ ወደ ዕዝ ጣቢያዎች መልዕክት አስተላለፍኩ የተመለሰለኝም የሚያስገርም ነበር። በደረሰኝ ባለ አምስት ገፅ ሪፓርት መሰራት በ1985 የሼክ አብደላን ምሽጎች በበላይነት ያስጠብቅ የነበረው ሊባኖሳዊ ካህሊል ሲሆን የሀዐ ታጋቾች ተይዘው የነበረውም በተመሳሳይ ወቅት እዚያው ቦታ እንደነበር የሚገልፅ ነበር። ሆኖም የመረጃው ታማኝነት የሚስተባበል አይነት አልነበረም።

በቀጣዩ ቀጠሮችን ሰሚር በምዕራብ በኩል ሺአዎች እርስ በርሳቸው ውጊያ ስለመጀመራቸው ማጉረምረም ጀመረ። በመጨረሻ ራሴን መቆጣጠር አቅቶኝ «ስለካህሊል የሰማኸው አዲስ ነገር አለ»? አልኩት።

«እ... የ እርሱን ጉዳይ ልረሳው ተቃርቤ ነበር። ከታይር የመጣ አንድ የበፊት ወዳጄን አግኝቼው ነበር»

«ካህሊል ታይር ውስጥ ነበር?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እዎ ለሁለት አመታት ያህል በፋታህ የተማሪዎች ህዋስ ውስጥ ከተፈጠረ መሰንጣጠቅ በኋላ ካህሊል በኃይል-17 ቀጣሪነት ወደ ታይር ተዘዋወረ፡፡ «እርግጠኛ ነኝ ይሰራለት የነበረውን እለታ ስም ስምተኸው እታውቅም፡፡» «አዝሚ ሱግሃይር» ይባላል፡፡

ተነስቼ ሰሚርን ላቅፈው ዳድቶኝ ነበር፡፡ ሱግሃይር የተለመደ ስም አልነበረም፡፡ ጃዳን ኤምባሲ ውስጥ እንዲሰራ ከቀጠረው ሱግሃይር ጋር አንድ መሆን አለባቸው፡፡ ግምቴ ትክክል ከሆነ የአለም ሻምፒዮናን ሪከርድ የመስበርን ያህል ይሰማኛል፡፡ ከጃዳ በተጨማሪ አንድ ሌላ ሰው ከፍንዳታው ጋር ማያያዝ ችያለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ ከፍንዳታውና ከዕገታው ጋር በቀጥታ የተያያዘ አንድ ብቸኛ ሰው ለማግኘትም ችያለሁ፡፡ በድንገት ካህሊል ከሙግህኒያ በብዙ እጥፍ የተሻለ ተፈላጊ ሰው መሆኑን፡፡

ወደ ማዘዣ ቢሮዎች ተመልሼ ስለ ሱግሃይር የሚታወቀውን ሁሉ ሰበሰብኩ፡፡ በርካታ መረጃ ነበር፡፡ ከእኔ በፊት ቤይሩት የነበሩት ሰዎች ስራቸውን በአግባቡ ነበር የተወጡት፡፡ በማስረጃዎቹ መሰረት ሱግሃይር በ1944 ፍልስጤም ውስጥ ተወለደ፣ በ1969 የፋታህን ኃይል-17 ተቀላቀለ፣ በ1970 እና በ1971 የያስር አረፋትን ጦር ዳግፎ ዮርዳኖሳውያንን ወግቷል፣ ከዚያም ፋታህ ሽብር ለማካሄድ የሚጠቀምበት ልብወለድ ድርጅት የብላክ ሴፕተምበርን አባል ሆነ፣ በ1973 አቡ ኢያድ የደህንነት ቢሮ ኃላፊ አድርገው ሾሙት፣ በእያንዳንዱ የብላክ ሴፕቴምበር የሽብር ጥቃት ውስጥ ተሳታፊ ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡ በሙኒክ ኦለምፒክ የተካሄደው የጅምላ ግድያም በዚህ ስር የሚጠቃለል ነበር፡፡

ሊቢያ ውስጥ ለበርካታ ዓመታት ከቆየ በኋላ ታይር ውስጥ የፋታህ ኮማንደር ሆኖ በ1979 ተሰየመ፣ ከዚያ በኋላ ሁሴይን ካህሊል በእርሱ ስር ሆኖ መስራት ጀመረ፣ በ1982 የእስራኤሉ ወረራ ወቅት ፋታህ ሱግሃይር እንደተገደለ የሚገልፅ ሀሰተኛ ዜና አሰራጨ፡፡ በእርግጥ ቤይሩት ውስጥ ከእስራኤሎች ጋር የሚደረገውን ፍትጊያ ሲመራ ቆይቷል፡፡ ካህሊል ልሂቅ ሽብርተኛና የእግር ዱካ እየተከተለ የሰልጠና ብልህ ሰው ነበር፡፡ ይሁንና እየቆየ የከነከነኝ አንድ ፍንጭ ይቀረኛል፡፡ ጃዳ ከተለቀቀ በኋላ የት ደረሰ? ጊዜ የሚወስድ ነገር መሆኑ እየገባኝ በድጋሚ ማዘዣ ጣቢያዎችን መረጃ ጠየቅሁ፡፡ ከሁለት ቀናት በኋላ ተስፋ ካደረግሁት የተሻለ መልስ መጣልኝ፡፡ ጃዳ በባህረ ሰላጤው ያደፈጠው የፋታህ ህዋስ ኃላፊ በሆኑት አኒስ አብደላህ ሃሰን (አቡ አሊ) አማካኝነት ወደ ዱባይ እንደተወሰደ፡፡ በቀጣዩ ቀን የአቡ አሊን የስልክ ወሬ ለማግኘት የስልክ ቅጅዎችን መበርበር ያዝኩ፡፡ ተስፋ ልቆርጥ በተቃረብኩበት ሰዓት ላይ ከ UO ቢሮ ለአቡ አሊ ወደ ዱባይ የተደረጉ ሶስት ጥሪዎችን አገኘሁ፡፡ በዚህም ሳያበቃ እንደመረጃዎቹ ከሆነ አቡ አሊ አብደ አል ላቲፍ ሳላህ ለተሰኘ የሙግህኒያህ ረዳትና UO ውስጥ የያሲር አረፋት ተወካይ እንደሚሰራ ተገልፆል፡፡

ይህ ሁሉ መረጃ ተአማኒና የማይጣራስ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ልነግራችሁ የምፈልገው አንድ ነገር አለ፡፡ ማስረጃ በስለላ አለም ውስጥ ብዙም የሚሻሻልበት ዕድል የለውም፡፡ ምክንያቱም የአሰባሰቡ ሂደት ቀድመው በነበሩና ስራው በአግባቡ እንዲሰራ በሚፈልጉ መኮንኖች አማካኝነት ከታሪኩ በእየእንዳንዱ መቀልበሻ ከእማኞች፣ የተጠለፉ ስልኮች ብሎም ለሰው በማይነገሩ ሰዓታትና መንገዶች በተደረጉ ምርምሮች አማካኝነት የተጠናከሩ ናቸውና፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እናም አንድ ሚዛናዊ ሰው ሊወስድ የሚችለው ብቸኛ ማጠቃለያ ቢኖር ያሲር አረፋት አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት አንድ የፋታህ ሀዋስ ሚያዚያ 18,1983 ቤይሩት የሚገኘውን የአሜሪካ ኤምባሲ አጋይቶቷል። ሙግህኒያህና ካህሊል ያሰጥርጥር ተሳታፊ ነበሩበት። ያልተመለሰ አንድ ወሳኝ ጥቃቄ ቢኖር ትዕዛዙን ማን አስተላለፈው? የሚል ነበር።

✡✡✡

ወደሚቀጥለው ደረጃ ስመሸጋገር «በትክክል መኪናውን ወደ ኤምባሲው ቅጥር የነዳው ማን ነበር?» ከሚለው ጀምሮ ሌሎች በርካታ የመረጃ ክፍተቶች መሞላት አለባቸው። ይህንን ማወቅ ከቻልን ወዳፈነዱት ሰዎች ማንነት ሊያመራን ይችላል።

በጥቅምት 1987 ጉዳዩን በእንጥልጥል የሚያስተው ሁኔታ ተፈጠረ። ከሰዓት በኋላ ጠረጴዛዬ ላይ ባቀረቀርኩበት ሰዓት የኤምባሲያችን ጠባቂ መጥቶ ሚስተር ወከር ሊያናግረኝ እንደሚፈልግ ገለፀልኝ። ሚስተር ወከር የCIA መኮንኖችን ሊያናግር ለሚመጣ ድንገተኛ ሰው የሚሰጥ የምስጢር ስም ነበር።

ለማንኛውም ሰው እንደማደርገው መረጃ አቀባዩ አድርጌ ልቀጥረው እንደምችል አይነት መቅረብ ይጠበቅብኛል። ያ ደግሞ ለሌላ ሰው መረጃ ከሚያቀብሉ ሊባኖሳዊ ጠባቂዎች ነጥቶ ማቆየትን ይጠይቃል እናም ታዲያ ሚስተር ወከር ተፈትሾ ወደ ኤምባሲው እንዲገባ ከማድረግ ይልቅ እኔ በሌላ አቋራጭ ወደ ውጭ ወጣሁ።

ይጠብቀኝ የነበረው ሰው ዕድሜው ሰላሳ አምስት የሚጠጋ ቢሆንም እናቱ ላይ ያለው መላጣ ግን ከዚያ በላይ የኖረ ያስመስልበታል። የለበሰው ቲሸርት ቀለሙ የለቀቀና የነተበ ነበር። ነጣላ ጫማው ሙስሊም ስለመሆኑ ያሳብቅበታል። የሊባኖስ ክርስቲያኖች ግን በአብዛኛው የሚለብሱት የአውሮፓውያን ልብስና የሚጫሙትም ጫማዎች እንደዚያው ነበር።

ብረት ነክ ነገሮችን በማያሳልፈው የፍተሻ በር ካሳላፍኩት በኋላ አሸዋ የተሞሉ ጆንያዎች በተደረደሩበት ምሽግ አሳልፌ በጀርባ በር በኩል አስቀድሜ መኪና ወዳቆምኩበት ቦታ ይገፍው ወጣሁ።

በባህር ዳርቻው አካባቢ ባለው ቀለበት መንገድ መንዳት እንደጀመርን ሚስተር ወከርን የዜግነት መታወቂያውን እንዲያሳየኝ ጠየቅሁት። ከቲሸርቱ አውጥቶ መታወቂያውን ሲያሳየኝ መኪናዬ ከመንገድ ልትወጣ ምንም ያህል አልቀራትም ነበር። ከሙግህኒያህ ቤተሰብ ጋር ተመሳሳይ የቤተሰብ ስም ነው ያለው። ሃሰን ብዬ የምጠራው ይህ ሰው ከአሸባሪው ሙግህኒያህ ጋር ያለውን ግንኙነት ስጠይቀው «የአክስቴ ልጅ ነው» በሚል መለሰልኝ። አላማዬ በፍጥነት ግንኙነታችንን ወደተጠናከረ ደረጃ ወደማሸጋገሩ አደገ። የሀዐ አሸባሪ የአክስት ልጅ እንደመሆኑ መጠን ሃሰን በክርስቲያኖች ምስራቃዊ ቤይሩት የነበረው ቆይታ ለስላሳ ለኮንዶች ያህል ብቻ ነበር። እርሱን ለማውረድ ለአደጋ የማያጋልጠንና በሚቀጥለው ቀጠሮ በቀላሉ ላገኘው የምችልበትን ቦታ ለማሳወቅ ወደምንገናኝበት ቦታ ለመምጣት ወደምስራቂዊው ቤይሩት ብዙ ሳይገባ ፋሪድን አገኝበት ወደነበረው ሲን አልፊል አመራሁ።


t.me/OLDBOOKSPDF

መንገድ ላይ ሳለንም ማውራታችንን ቀጥለን ነበር። ስለእርሱ ሁሉንም ነገር ማወቅ ስለፈለግኩ የት እንደሚኖር! ማግባት አለማግባቱን! ስንት ልጆች እንዳሉት እና ሌላም ሌላም ሂዝቦላና IJO ውስጥ በቅርብ የሚያውቀው እነማንን እንደሆነ ማወቅም ፈልጊያለሁ፡፡ እናም ሁለቱም ውስጥ አባል አለመሆኑን እየነገረኝ በነበረበት ሰዓት ቢያንስ ወዳእንዳቸው በአባልነት እንዲመዘገብ የማድረግ ሃሣቤ መላወስ ጀምሮ ነበር፡፡

ከአረንጓዴው ቀጠና በስተምስራቅ ለምን እንደመጣ ቢጠየቅ ምን መመለስ እንዳለበትም ተነጋገርን፡፡ ያለበቂ ምክንያት ሲን አልፈል ፒዛ ገዝቼ ልመለስ ነው ብሎ ያቀረበውን ሀሳብ አጣጥዬበት ከዚህ ይልቅ በምስራቁ ክፍል ለሚገኝ ጀርመናዊ ተመራማሪ የእስልምና መፅሃፍትን እየገዛሁለት ነው የሚለውን ሀሳብ እንዲመልስላቸው ተስማማን፡፡ ምናባዊው ጀርመናዊ ወደ ምዕራቡ ክፍል የሚሄድበት አጋጣሚ ስለማይኖር እውነታው የሚጣራበት ዕድል አይኖርም፡፡ ያን ያህል የሚያስጋ ሽፋን ባይሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ የተከሰተልኝ ሀሳብ ነበር፡፡ ከዚያን በኋላ ለሃሰን ከቢሮዬ ጋር ግንኙነት የሌለውን ተለዋጭ ስልክ ቁጥር ሰጠሁት፡፡

በመጨረሻ ሃሰንን የማወርድበት ቦታ ስደርስ CIA'ን ለመቀላቀል ምን እንዳነሳሳው ጠየቅሁት፡፡

«የንፁሃን ደም ሲፈስ ዝም ብዬ መመልከት አልችልም፡፡ ሂዝቦላ እየሰራ ያለው ስህተት ነው፡፡»

«ግንኮ አደጋ አለበት» አልኩት፡፡ «ልጆች አሉህ? ከተያዝክ ልትገደል ትችላለህ» አውቃለሁ፡፡ አላህ ግን ይጠብቀኛል፡፡»

☼☼☼

ሃሰን ሂዝቦላን ተቀላቅሎ በአንደኛው ቢሯቸው ስራ ስለተቀጠረ ከ CIA መረጃ አቀባዮች መካከል በጠቃሚነታቸው ቀዳሚውን ስፍራ ያዘ፡፡

አገር ቤት ያሉ መርማሪዎች በየጊዜው ጥያቄያቸውን ያዥጎደጉዱልኝ ጀመር ሼክ እንትና ስለ እነሼክ እንትና ምን ያስባል?፣ ሂዝቦላህ ለአላማው ማስፈፀሚያ ስንት እያወጣ ነው?፣ ወደ ሊባኖስ ፖለቲካ መግባት የሚፈልጉት መቼ ነው?... የመሳሰሉትን፡፡ እኔ የመሰጠኝ ነጥብ ግን የኢማድ ሙግህኒያህንና የIJO ግንኙነት ነበር፡፡

በዚህ ነጥብ የተሻለ ለመስራት IJO ውስጥ መቀጠር የግድ ስለሚል በጉዳዩ ላይ ሃሰን እስከጫፍ ጉዳዩን እንዲያጣራልኝ ጠየቅሁት። እንደሚጠበቀው የመጀመሪያው ትዓዛዜ በ ሚያዚያ 18,1983'ቱ ፍንዳታ ዙሪያ ያጠነጠነ ነበር። ሃሰንና እኔም ረዥም ጊዜ ወስደን ተነጋገርንበት። በፖለቲካው የጠለቀ መሆኑን ስለማውቅ የአሜሪካ መንግስት ማን እንዳፈነዳው ምንም አይነት ፍንጭ እንደሌለው አመንኩለት። ከመካከለኛው ምስራቅ የሚሰጠን መልስ የ 17 አሜሪካውያንን ህይወት ስለቀጠፈው ፍንዳታ CIA ምንም ፍንጭ እንደሌለው መናገራችን ተቀባይነት እንደሌለው ነው፡፡ ይሁንና ሀሰን እንደዛ አላለም፡፡ «የተሻለ ፍንጭ ካጣን


t.me/OLDBOOKSPDF

ለምን ከኢማድ አንጀምርም?» ሲል በዚያች ቅፅበት እንደማገኘውም ቅጥረኛ ሃሰንም የምፈልገውን ዓይነት መልስ ስለሰጠኝ የመጨረሻ ተመቸኝ፡፡

ሃሰን ለሙግሀኒያህ ቅርብ የሆኑ ኢማም በሚያስተዳድሩት መስጊድ መስገድ ጀመረ በየሳምንቱ አርብ ሳያቋርጥ ከመሄዱም በተጨማሪ አንድ የጥናት ቡድን ተቀላቀለ፡፡ ጥሩ ፀሐፊ ሆኖ በመገኘቱ ለኢማሙ ትራክት ያዘጋጅላቸው ጀመር፡፡ ኢማሙ ሃሰን ለ ሀዐ ሽብርተኛ ራሱን አሳልፎ የሰጠ መሆኑን እያወቁ ሲመጡ በእምነቱ የፀና አድርገው ተቀበሉት፡፡

አንድ ቀን ኢማሙና እሱ ብቻቸውን ባሉበት ሁኔታ የፍንዳታውን ጉዳይ የማንሻው ሰዓት አሁን እንደሆነ ስለተሰማው በተስማማነው መሰረት ሐሰን አለሳልሶ ነበር የጀመረው፡፡ ይሁንና በቀጥታ አጥፍቶ ጠፊው ማን እንደነበር በመጠየቅ ፋንታ ለረዥም ጊዜያት ኢማሙን ሲያገለግል የነበረና አሁን የሌለ ወጣትን ስም በማንሳት ጀመረ፡፡ ድምፁን በሃዘኔታ ምፀት ዝቅ አድርጎ ወጣቱ የዩ.ኤስ ኤምባሲን ለማፈንዳት መኪናውን የነዳው ሾፌር ስለመሆኑ ጭምጭምታ ስለመስማቱ አወጋቸው፡፡

«ከየት ነው ይኸን የሰማኸው?» ጠየቁ ኢማሙ፡፡

ሃሰን አደናጋሪ በሆነ ሁኔታ ሀዐ ውስጥ ካለው የአክስቱ ልጅ መስማቱን ገለፀላቸው ኢማሙ የአክስቱን ልጅ አግኝተው ሊያረጋግጡ እንዳማይሞክሩ ያውቃልና፡፡

«አይደለም» አሉ ኢማሙ እጃቸውን በማወራጨት.. የአሜሪካንን የስለላ ጎጆ ያጋየው የተቀደሰው ወጣት እሱ አይደለም»፡፡

ሃሰን ግን እርግጠኛ ስለመሆኑ ማውራቱን ቀጠለ፡፡

«አይደለም ተሳስተሃል» ኢማሙ ሃላፊነታቸው ያን ያህል ሲደፈር ማየት አልፈለጉም፡፡ «ወንድም ሃሱና ነበር፡፡ ብለው በስሱ ተነፈሱ፡፡»

«ማን?»

«ሙሃመድ ሃሱና»

✡✡✡

የአፈንጂውን ስም ስንሰማ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜያችን ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ ታሪኩ ከአነሳሱ እንደገና መጣራት ስለ አለበት በርኔ ወደ ቤይሩት ተመልሶ እንዲመጣ ጋበዝኩት፡፡ አላማዬም ሃሰንን እንዲያውጣጣልኝ ነበር እናም ከሁለት ቀናት በኋላ በብላክሃውክ ከች አለ፡፡

ለምን እንደሆነ አላውቅም በርኔን ከመጀመሪያ ቆይታው የበለጠ ዝጋታም ሆኖ ነበር ያገኘሁት አረንጓዴው ቀጠና አካባቢ የሚካሄደው ውጊያ ዛሬ ፍፁም ጋብ ብሏል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉም ነገር በሰላም ከቀጠለ የሃሰን ጉዳይ ከምሳ ሰዓት በፊት ሊያልቅ ይችላል ብዬ ገምቼያለሁ፡፡

ወደ ሲን እልፊል ጉዳና ቁልቁል መውረድ እስከምንጅምር ድረስ እገር እግን ነበር፡፡ ከመረጥነው ቦታ ልንደርስ ሶስት ህንፃ ያህል ሲቀረን ከ 0.50 ካሊበር መትረየስ የተወነጨፈ አረር ከላያችን የተንጠለጠለ የአምቡላንሱን እንፖል ቦርቅሶ መኪናችንን ላይ በታተነው፡፡ ከመኪናችን ጣራ ሽቦዎች ሲንጣጡና ሲኮማተሩ ይሰማን ነበር፡፡ በርኔን ተመለከትሁት ፊቱ ላይ የሚነበበው ስሜት «ህይወቴን እደጋ ላይ በመጣሉ ገድየው ልሩጥ ወይስ ከዚያ በፊት ልሩጥ?» የሚል ይመስላል፡፡

የሁለተኛው አረር ፍንዳታ ግን ከመንገዱ በታች የሚገኘውን ህንፃ ሰርሰሮ ገባ፡፡ በርኔ ወደ እግሬ እየጠቆመ «እነዚህ እግሮች ያንተ ናቸው መሰለኝ ምን ትጠብቃለህ ነጻጅ መስጫውን ስጠው እንጂ ... እዚህ ድረስ መጥተው ማነህ? ... ወዴት ነህ? እስኪሉህ ትጠብቃለህ እንዴ?? በማለት እንባረቀብኝ፡፡ ወደ ጉዳያችንም በተደናገጠ ሙድ እየሄድን ሳለ በርኔ ሙዱ ተሰርቆ ሲቀዣበር ሃሰን መኪናው ውስጥ አለመኖሩ ትዝ ሲለኝ ዕጢዬ ዱብ አለ! በቃ በመኪና እሱን ፍለጋ ከቦታ ቦታ ስማትር ከ10 ደቂቃ በኋላ በሲን እልፈል እውራ ጎዳና እየተንጠራዘዘ ሃሰን ብቅ አለ፡፡ አሁን እፎይ አልኩ ተኩሱ ጋብ ቢልም አካባቢው ግን ፀጥ -ረጭ ብሏል፡፡

ሃሰን ማጣራት ተደርጕበትም የተናገረው ሁሉ እውነትነቱ ተረጋገጠ፡፡ ማጣራቱ ጅማሮ እንጅ ሙሉበሙሉ የምንተማመንበት አልነበረም፡፡ ኢማሙ ሃሰንን ዋሽተውት ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ስለ አጥፍቶ ጠፊው የሚያውቁት ነገር ባለመኖሩ አለማወቃቸውን ለመሸፈን የፈጠሩት ሽፋንም ይሆናል፡፡ ኢማሙ ላይ ማጣራት ማካሄድ ስለማልችል አማራጩ ወደመረጃ ሰብስቤ መመለስ ነበር፡፡

ሃሱና ሊባኖስ ውስጥ የተለመደ ስም አልነበረም፡፡ እንደዚያ መሆኑ ደግሞ ነገር አቅልሏል፡፡ ሁሉንም ቅጥረኞቼን በሃሱና ቤተሰብ ዙሪያ መረጃ እንዲያሰባስቡልኝ አሰማራኋቸው፡፡

ሰሚር አንድ ሻለቃ በሃሱና ስም እንደሚያውቅና ከቤቱ የተሰወሩ ስለመኖራቸው እንደ ሚያጣራ ቃል ገባ፡፡ ከሳምንት በኋላ ሙሃመድ ተብሎ የሚጠራ የሻለቃ ሃሱና ወንድም ኢራን ውስጥ ኢራቅን ሲዋጋ መሞቱን የሚገልፅ ዜና ይዞ መጣ፡፡

«ኢራን?» አልኩኝ በመደነቅ፡፡ «እንዴት ሊሆን ይችላል? ሊባኖሳውያን በቀላሉ ተታለው ኢራንን ሊወጉ አይሄዱም፡፡» አልኩት፡፡

«አጣራለሁ» አለ ሳሚር፡፡

በቀጣዩ ስንገናኝ የሻለቃ ሁሱና ቤተሰብ የስም ብቻ ሙስሊም መሆናቸውን ከእነሱ አፍ መስማቱን ነገረኝ፡፡ ቁራን የሚያነቡት ወይም መስጊድ የሚሄዱት በጣም አልፎ አልፎ ቢሆንም ሙሃመድ ሀሱና ግን የተለየ ነበር፡፡ አባታቸው ጠጪና ረባሽ የነበረ ሲሆን ሙሃመድ በዚህ እጅጉን ይማረር እንደነበር በእምነቱ ለመፅናት በነበረው ፍላጐት



t.me/OLDBOOKSPDF

የሺእ እስልምናን ከተቀላቀለ በኋላ በ1983 መጀመሪያ አካባቢ ድንገት ወደኢራን ሄዶ ከኢራቅ ጋር በነበረው ጦርነት እንደሚሳተፍ ለቤተሰቡ እንደ አሳወቀ እና ከዚያ በኋላ ስለ እሱ ምንም ዓይነት ወሬ ሰምተው የማያውቁ መሆኑን በመጨረሻ ከኢራን ኢምባሲ ሙሃመድ በውጊያ መካከል መሞቱን የሚያረዳ ደብዳቤ እንደ ደረሳቸው ነው የሚያውቁት፡፡ ደብዳቤው ውስጥም የተረፉት ጥቂት መሆናቸውንና ኢራን ውስጥ በሚሊዮች መቃብር እስከሬኑ በክብር ማረፉ ተገልፆል፡፡ ደብዳቤው በሙሃመድ መቃብር ላይ የተፃፈውን ጥቅስም ጨምሮ እንደያዙ እና ከዚህ የበለጠ ስለወንድማቸው ሞት የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ጭምር ነበር የተናገሩት፡፡

ፋሪድ ደግሞ በሙሃመድ ሃሱና ዙሪያ የሚቻለውን ሁሉ ቆፍሮ አቅርቦልኛል፡፡ ሃሱና ፓስፖርት የነበረው ቢሆንም ከሃገር ወጥቶ ስለማወቁ የሚገልፅ ምንም ዓይነት ምልክት እንደሌለበት ሲዶን ውስጥ በተገኘ የቤተሰቡ የምዝገባ ታሪክ መሰረት የሃሱና ቤተሰብ መኖሪያ ሂዝቦላ በሚቆጣጠረው አየር ማረፊያ አካባቢ አውዛይ ተብሎ በሚጠራ ሰፍራ እንደነበረ የሚገልፅ ነበር ያቀረበልኝ መረጃ፡፡

ምንም እንኳን ፍርድ ቤት ሊገትር የሚችል መረጃ ማጠናከር ባልችልም በየቀኑ ግን የዕውነትን ጭራ ለመያዝ እየተቃረብኩ ነበር፡፡ ስለሃሱና የማውቀውን ሁሉ በዝርዝር አስቀመጥኩ፡፡ በፍንዳታው ዙሪያ ከምፅፋቸው ዝርዝር የስለላ ሪፓርቶች የመጀመሪያው መሆኑን ነው፡፡

ከቀናት በኋላ የበላይ ኃላፊዎቹ ብዙ የደከምኩበትን ሪፓርት መሰራጨት እንደሌለበት ወሽመጤን የሚበጥስ ቀጠን ያለ ትዕዛዝ ላኩልኝ፡፡ «መረጃው አጥጋቢ ቢሆንም ከታሪክነት የዘለለ ጠቀሜታ የለውም» የሚል ነበር የፃፉልኝ፡፡ በቀላል አማርኛ «የብሔራዊ ደህንነት አባላት ከአሁን በኋላ ኢምባሲውን ስላፈነዳው አካል ማንነት የማወቅ ግድ የለባቸውም፡፡»

☼☼☼

በሂደት ግን ዋሽንግተን በጉዳዩ ላይ ፍላጐት ማጣቷን እየተረዳሁ መጣሁ፡፡ CIA ስለፀረ ሽብርተኝነት ለመማር ቤይሩትን መሰል ቦታዎችን ረግጠው በማያውቁ ሰዎች እጅ እየወደቀ እንደነበርም ለማስተዋል ቻልኩ፡፡ የኢምባሲው ፍንዳታ ለእነሱ የቀድሞ ታሪክ ብቻ ሳይሆን በስራ እለም የፈለጉትን እንዳያሳኩ የሚያግዳቸው ሆኖ አግኝተውታል፡፡ የኤጀንሲውን አስቀያሚ ጊዜያት የሚያስታውስ ዜና በማውራት ለምን ወደ አላስፈላጊ አታካራ እንደሚገቡ አላውቅም፡፡ እኔ ደግሞ ስራዬን የምመለከተው ከተለየየ አቅጣጫ ነበር፡፡ ከነማን ጋር ስንታገል እንደቆየን ማወቅ ካልቻልን በየትኛውም ሰዓት እስከ አፍንጫቸው ታጥቀው ብቅ ሊሉብን እንደሚችሉ ደመነፍሴ ሹክ ብሎኝ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሙግህኒያህ ከአገር ከወጣ የተቆረጠበት የእስር በፍርድ ቤት ማዘዣ እንደፀና ነበር፡፡ እናም ወንድ የሆነ እስከሚፈፅመው በመጠባበቅ ላይ ነበርኩ፡፡ እኔ ግን ማነፍነፌን በመቀል ከዚህ በኋላ ያገኘሁትን ሰው ጂን ብዬ ሰየምኩት ጂን እንደሙግህኒያህ ሁሉ ህይወቱን በአረንጓዴው ቀጠና አካባቢ ሲዋጋ ያሳለፈ ሲሆን



t.me/OLDBOOKSPDF

ዕድሜው 32 ግድም ነበር፡፡ ብቸኛው ልዩነት እርሱ ሲግርከና ሲገድል የነበረው ሙስሊሞችን መሆኑ ነበር፡፡

ጂን ዶሚኖስ ተብሎ በሚጠራ ናይትክለብ ውስጥ እየጠበቀኝ ነበር፡፡ «አንድ ቀን ራሱ ለመስራት በጣም የሚከብደውን ስራ ሲያጋጥመው CIA ወደ እኔ ሊመጣ እንደሚችል አውቅ ነበር» አለኝ እየጨበጠኝ፡፡

በአርምሞ አካባቢውን ቃኘሁት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ቢያልፍም ዶሚኖስ ገና በመሙላት ላይ ነበር፡፡ የጦር መሳሪያ ደላሎች፣ የኮሎምቢያ ናርኮቲክ ዕፅ አዘዋዋሪዎች፣ ክርስቲያን የጦር መሪዎች፣ ህገወጥ ንግዱን የሚያጧጡፉት እዚህ ነው የሚሰበሰቡት ዶሚኖሲ ከእነአስራሩም ጭልምልም ያለ ሲሆን ሆን ተብሎ ወሬዎች እንዲዋጡ ሙዚቃው ጆሮ የሚያደነቁር ተደርጐ ነው የሚለቀቀው፡፡

ወደ ጂን ዞሬ «በምዕራቡ ክፍል ጊዜዬን የማያባክኑ መስመሮች መዘርጋት እፈልጋለሁ» አልኩት፡፡

«የስለላ ስራ አልሰራም መረጃ ከፈለግህ የሊባኖስ ሀይሎችን አናግራቸው፡፡» የሚል አጭር መልስ ሰጠኝ፡፡

የሊባኖስ ሃይሎች ማለት ቀንደኛ የክርስቲያን ሚሊሺያዎች ናቸው፡፡ ሁለታችንም የስለላ ስራቸው እንደማይረባ እናውቃለን፡፡

«መረጃ አይደለም የፈለግሁት፡፡ ግዳጅ ማስፈፀም ነው የምፈልገው» አልኩት፡፡ ጂን ፈገግ ብሎ «በመጨረሻ ሶሪያ መስመሩን አልፋ ገባች ማለት ነው፡፡» አለ

«አይደለም በደቡባዊው ክልል የሚገኝ አንድ ሰው ማጥመድ እፈልጋለሁ፡፡»

«ግድያ ነው?»

«አይደለም፡፡ ከነነፍሱ ነው የምፈልገው»

«ማነው?»

«ሰዎቹን አገናኘኝና እንነጋገራለን»

ጂን ዙክ ውስጥ የሚገኝ የቪዲዮ ቤት ስም ፃፈልኝና «ነገ ጠዋት አራት ሰዓት ላይ» አለኝ፡፡

... ስደርስ ሬንጅ ሮቨር መኪናው ውስጥ ቪድዮ ቤቱ ፊትለፊት ተቀምጦ ነበር፡፡ ወጥቶ እንድከተለው ምልክት ሰጥቶኝ መጋዘኑን አቋርጠን በጀርባ በር ወጥተን በምስጢር በር በኩል ወደ መኖሪያ አፓርትመንት ገባን መብራት ጠፍቶ ስለነበር አምስቱን ደረጃዎች ወጣን፡፡ ከዚያም የሊባኖሱ ጦር ካፒቴን በሩን ከፈተልንና ገባን ሌላ መኮንንም ሶፋ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀምጦ ነበር፡፡ መመገቢያው ክፍል ጠረጴዛ ላይ ደግሞ ሊባኖስ ጦር ውስጥ ያልተለመደ M-16 ከእቅርቦ የሚያሳይ መነፅሩና ድምፅ ማፈኛው ተቀምጦ ይታያል፡፡

የካፒቴኑ ግራ እጅ የታጠፈ የዳክዬ እግር ይመስላል፡፡ ስገምት በፍንዳታ ነው እንደዚያ የተኮማተረው፡፡ ከጂን ጋር ለመነጋገር ከቤቱ ወደ አንደኛው ጥግ ሲሄዱ አንደኛው እግሩ ከሌላኛው እንደሚያጥርም አስተዋልኩ፡፡

«ካፒቴኑ የምትለውን ለመስማት ዝግጁ ነው» አለኝ ጂን ወደኔ ተመልሶ እንደመጣ፡፡ በምዕራቡ ክፍል መስመር መዘርጋት እንደምፈልግ መናገር ስጀምር ጂን እንዳደረገው ካፒቴኑም ፈገግ አለ፡፡

«ኢላማዬ ሶርያዊ አይደለም፡፡ ሂዝቦላ ነው፡፡ አንድ የእስላሚክ ጂሃድ አባል መያዝ እፈልጋለሁ» አልኩ፡፡

ያለምንም ማንገራገር «እርሳው» አለኝ ካፒቴኑ፡፡ እንግሊዝኛ ሲያወራ በአሜሪካውያን ቅላጼ ቢሆንም ስሙን ለመግለፅ ግን አልፈለገም፡፡ «ልታገኘው የምትፈልግ ከሆነ በደቡባዊ ክልል ጠለፋ የሚያካሂድልህ አንድም ሰው አታገኝም፡፡»

ጂንና ካፒቴኑ በድጋሚ ተነጋገሩ በግላቸው እወሩ፡፡

«ይህንን ስራ ሊሞክርልህ የሚችል አንድ ግለሰብ አለ፡፡ በጣም የተቀናጀበር ከመሆኑ የተነሣ እኛ ከእርሱ ጋር ከሰራን ቆይተናል»

«የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል?» ብዬ ጠየቅኩ፡፡ የምፈልገውን ከአረንጓዴው ቀጠና አሳልፎ ያመጣዋል ወይስ ይቀራል እኔ'ኮ የምከፍለው ሲሳካለት ብቻ ይሆናል»

ካፒቴኑ በድጋሚ ሊያገኘው ይችል እንደሆነ ለመሞከር ተስማማ፡፡ ወደ ውጭ እንደወጣን ሁለቱ መኮንኖች እነማን እንደሆኑ ጂንን ጠየቅኩት፡፡ ሁለቱም ከሊባኖስ ጦር በፈቃዳቸው የለቀቁ ሲሆኑ አሁን በቢቃ ሸለቆ የሚንቀሳቀሰው ፀረ-ሶርያ ኀይላ ቡድን አባላት መሆናቸውን ገለፀልኝ፡፡ በሶሪያውያን ላይ በርካታ የተሳኩ ጥቃቶች ያካሂዱ ቢሆንም ሁሌም አባሎቻቸውን በማጣት ላይ ናቸው፡፡ «በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ውስጥ የሚቀራቸው አንድም ተዋጊ አይኖርም» አለኝ ጂን፡፡

ከአንድ ሳምንት በኋላ ምሽት ላይ ባብዳ ወደሚሰኘው ከደቡባዊ ክፍል ከሚዋሰነው የክርስቲያኖች መንደር ወሰደኝ፡፡ እስከሚጨልም በጂን ሬንጅሮቨር ውስጥ ከቆየን በኋላ ቀስ ብለን ቁልቁለቱ እያሽከረከርን ወረድን፡፡ አረንጓዴውን ቀጠና እየቀረብነው በመጣን ቁጥር ህንፃዎቹ በአውሎንፋስ የተመቱ የጠጠር ክምሮች ይመስሉ ጀመር፡፡ ባብዳንን ከደቡባዊው ክፍል የሚለያት የመጨረሻዎቹ ህንፃዎች ወደጉቶነት መቀየራቸው ብቻ ነበር፡፡

የሊባኖስ ጦር በሚጠብቅባቸው ሶስት የፍተሻ ጣቢያዎች አለፍን ሁሉም ጂንን ስለሚያውቁት እጃቸውን ያውለበልቡለታል በመጨረሻ አራት በአምስት የሆነ ገደል ላይ ደረስን፡፡ የመኪናዋን ድምፅ ሲሰሙ ሁለት ጠባቂዎች ተፈናጥረው በመውጣት መጪ



t.me/OLDBOOKSPDF

አለመሆናችንን አረጋገጡ፡፡ እኛም መኪናዋን እነርሱ ጋር ትተናት በእግራችን ጉዟችንን ቀጠልን፡፡

አሁን የምንገኘው የማንም ባልሆነ መሬት ላይ ነው ከሂዝቦላ ምሽግ መቶ ከንድ ያህል ብንርቅ ነው፡፡ ይህ ሙግሂኒያህ በ 1970 ዎቹ ለፋታህ የተዋጋበት ቦታ መሆኑን እንዳውቀው ባይፈቀድልኝም የሊባኖስ ጦር ለሂዝቦላ የጦር መሳሪያ የሚያቀብልበትን መንገድ ነበር የተከተልነው፡፡ በዓመቱ መጀመሪያ አካባቢ በሂዝቦላና በተቀናቃኙ አማል መካከል ግጭት ሲከሰት ሶሪያ አማልን እየደገፈች ነው በሚል ወሬ ብቻ የሊባኖስ ጦር ሂዝቦላን እየደገፈ ነበር፡፡ ፅንፈኛ የክርስቲያኖች ፅንፈኛ ሙስሊሞችን ሊደግፉ የሚችሉበት ብቸኛ ቦታ ቢኖር ሊባኖስ መሆን አለበት፡፡

በከፍታ ቦታ ሳር ላይ ተቀምጠን በሮኬት ፍንዳታ ታጅበን ለሃያ ደቂቃዎች ያህል ጠበቅን፡፡ ጂን የጦር መሳሪያ አለመያዙን ባስተውልም ሂዝቦላ ካመረረብን ሽጉጥ ምን ሊሰራልን ይችል ይሆን? ብዬ ራሴንም ጠይቄያለሁ፡፡

በጨለማው ውስጥ የሰው ጥላ ቢከብደኝም ቀስ በቀስ ጥላው እየቀረበ ሲመጣ ጺሙን በአግባቡ ወደተስተካከለው ሰውነት ተቀየረ፡፡ ፓሎ ጂንስ፡ ሸሚዝና የካውቦይ ጫማ ተጫምቷል፡፡ ስሙን ኢሳም ብዬ ሰይሜዋለሁ፡፡

ኢሳምና ጂን ተቃቀፉ ጂን ሰውዬውን ስለስድስቱም ልጆቹ ስማቸውን እየጠራ ጠየቀው፡፡ ለአምስት ደቂቃዎች ያህል ካወሩ በኋላ ለምን እንደፈለግነው ጂን መናገር ጀመር፡፡ የሆነ ያልሆነውን እየቀባጠርን ቆየን፡፡ አይን አል ዲልባህ ውስጥ የሚኖር አንድ ሰው ተይዞ እንዲመጣልኝ እንደምፈልግ በቀጥታ ለኢሳም ነገርኩት፡፡

«ስለ አይን አል ዲልባህ የምታውቀው ነገር አለ?» ሲል ጠየቀኝ፡፡ ይመስለኛል ተገርሟል፡፡ ሊገምተኝ የፈለገ ይመስላል፡፡

ጥያቄውን ወደ ጐን ትቼ «ኢማድ ሙግሀኒያህን ነው የምፈልገው» አልኩት፡፡ አሁን አይኑ ሲበለጠጥ ተመለከትኩኝ ወደ ጂን ዞሮ «የምሩን ነው?» ብሎ ጠየቀው፡፡ ጂን በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ፡፡

ኢሳም ወደ እኔ ዞሮ «ሁለት ሺህ ዶላር ከከፈልከኝ እገድለዋለሁ፡፡ በቅድሚያ አንድሺውን እፈልጋለሁ» አለኝ፡፡

የለም «ከነነፍሱ ነው የምፈልገው»

«እንግዲያውስ ሌላ ሰው ፈልግ»

በፀጥታው ውስጥ የተኩስ ድምፅ በቅርብ ርቀት ይሰማን ጀመር፡፡

«ለማንኛዋም አል ዲልባህ ውስጥ የፈለግሽውን መስራት እንደምትችል በምን እርግጠኛ መሆን እችላለሁ?» ስል ጥያቄ አቀረብኩለት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ኢሳም ሳቀ፡፡ «ሚስተር ጂን ስለእኔ ማንነት አልነገረህም ማለት ነው! የእናንተው የኒውጀርሲ ባህር ሃይሎች የገደሉት ተደምሮ እኔ ከገደልኩት የሰው ቁጥር አይስተካከልም፡፡»

«ኢሳም በአንድ ጊዜ አስራ አንድ የመኪና ቦምቦችን ጠምዶ አፈንድቷል» አለ ጂን በማብራራት አይነት፡፡

ለአንድ አንባቢ ይህ የሚያስደነፋ ጀግንነት ሳይመስል ቢችልም ሊባኖስ ውስጥ ለሚገኝ ሽብርተኛ ግን በአንድ ኦሎምፒክ ሶስት ወርቅ የመውሰድ ያህል ነው፡፡

አሁን ተኩስ ባናታችን ማፏጨት ጀምሯል አሁንስ መሄድ አለብን አልኩ ለኢሳም በሚቀጥለው ሳምንት እንደምንገናኝ ነገርኩት፡፡ በመሃሉ ስለሙግኒያህ የሚቻለውን ያህል እንዲያጣራልኝ ነገርኩት፡፡ የሚኖርበትን ቦታ፣ የመኪናዎቹን መግለጫ፣ የቅርብ ወዳጆቹን ዝርዝር እንዲሁም የቤቱን ፎቶ እንደምፈልግ ነገርኩት፡፡ ኢሳም ቃል ከመተንፈሱ በፊት አስር አዲስ የመቶ ዶላር ኖቶች ኪሱ ውስጥ ሸጎጥ አደረግኩለት ገንዘብ ችግር እንደማይሆንብኝ ለማሳወቅ ያህል፡፡

ሙግህኒያህ ይህ ነው የሚባል ቦታ እንደማይኖር አውቃለሁ፡፡ CIA እና ሌሎች በርካታ ተከታታዩች ባሉበት ዛሬ ያደረበት ቦታ ነገ አይደግምም ብሎም በገባበት በር ተመልሶ አይወጣም ከውስጥ ልብሶቹ በበለጠ መኪኖቹን ይቀያይራል፡፡ ነገር ግን ኢሳምን ማመን ከመጀመሬ በፊት ምን ማምጣት እንደሚችል ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡

✡✡✡

በቀጣዩ ሳምንት በቀጠሮው ቦታ ከእኛ ቀድሞ ተገኘ በርካታ ዕሁፎችና በኢንቨሎፕም ፎቶዎችን አጭቋል፡፡

«ባለፈው ሳምንት ሙግህኒያህ ለሁለት ሌሊቶች ያደረበት ቦታ ይኸውልህ» አለኝ አንድ ፎቶ እያቀበለኝ ባለሁለት ታሪኩ ኃይማኖታዊ ግንብ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡

«ምንድነው ይኼ?» ስል ጠየቅኩት

«የሙግህኒያ እያት የምትኖረው እዚህ ነው፡፡ በየተወሰኑ ሳምንታት እዚህ ያድራል፡፡ ነገር ግን መቼ እንደሚመጣ አስቀድሞ አይናገርም፡፡ በአብዛኛው ብቻውን ድንገት ከተፍ ይላል፡፡»

«እንዴት አወቅህ?»

«ያክስቴ ልጅ እዛ ት/ቤት ውስጥ ትሰራለች፡፡ ሲመጣና ሲሄድ አይታዋለች፡፡ የምትኖረው አይን አል ዲልባሕ ውስጥ በመሆኑ ቤተሰቡን ከልጅነቷ ጀምራ ነው የምታውቀው» በቀጣዩ ቀን ኢሳም የሰጠኝን መረጃዎች አገላበጥኳቸው፡፡ ኢሳም የአይን አል ዲል ባሁን ጋንግ አሳምሮ እንደሚያውቀው ጥርጥር አልገባኝም፡፡ ስልክ ቁጥሩ፣ መኪኖቹ፣ አድራሻዎች ሁሉም ተዘርዝረዋል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ኢሳም በቀጣዩም ሆነ ከዚያ ቀጥሎ በነበረን ቀጠሮ ላይ አልተገኘም። በሶስተኛው ቀጠሮ ግን ብቅ አለ። የት እንደነበረ ስጠይቀው መልስ ሊሰጠኝ አልፈቀደም።

«በዚህ ሳምንት ሙግኒያ ወደ ት/ቤቱ ይመጣል። የሆነ ሰው ከቴህራን ሊያናግረው ይመጣል» አለ ኢሳም «ምንአልባትም ሌላ ዕድል ላናገኝ እንችላለን» ሲልም አከለበት።

«እንዴት ነው ታድያ ከዚያ ይዘህ ልታመጣው የምትችለው?» ስል ጠየቅሁት።

«በፊትም ነግሬሃለሁ። ልገድለው እችላለሁ አግቼ የማመጣልህ ከመሰለህ ግን አብደሃል ማለት ነው»።

ኢሳም እንዲያወራ ፈቀድሁለት።

«ከት/ቤቱ ፊትለፊት የመኪና ማቆሚያ አለ የእኔ ዕቅድ በሁለቱም ጥግ መኪኖች አቁመን በአንድ ጊዜ ሁለቱንም ማፈንዳት ነው አንድ ሺህ ኪሎ ሴምቴክስ ችግርህን እንደሚያቃልልህ አውቂያለሁ። »

ኢሳም ትክክል ነበር ሁለት የመኪና ቦምቦች ህንፃውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደፍርስራሽነት ቀይረው ውስጡን ምንም ነገር እንዳይተርፍ ማድረግ ይችላሉ።

«ሙግህኒያህ እዚያ እንደሚኖር እርግጠኛ መሆን ትችላለህ?» ስል ጠየቅሁት።

«የአክስቴ ልጅ ትነግረኛለች»

«ለመጀመር ምን ትፈልጋለህ?»

«ሁለት ሺህ አሁን ከች ታደርጊያለሽ ሙግህያኒህ ከሞተ በኋላ ደግሞ አስር ሺህ» አለኝ። ለመወሰን ብዙ ግዜ አልፈጀብኝም። CIA'ን ስቀላቀል ባዶዬን ነበርኩ አሁን ግን ወደ መረጃ ጆንያነት ተቀይሬያለሁ ኢንባሲውን ያፈነዳውን ሰው በማወቅ ጉጉት ተስከፌ ነበር። ያ ግን ማን መገደል እንዳለበት የመወሰን ስልጣን ተሰጥቶኛል ማለት አይደለም። እሱን ለዋሽንግተን ፓለቲከኞች መተው ነበረብኝና።

ለኢሳም ተመልሶ ተጨማሪ መረጃ እንዲያሰባስብ ነገርኩት። ስለሁኔታው ለበላዮቼ ሪፓርት አላደረግኩም በማለት ተስፋ ሰጥቼው ተሰናበትኩት ከዚያም በኃላም ደግሜ አላየሁትም አሁን ይፀፀተኛል? አዎን። ኢማድ ሙግህኒያህ ከአሳማ ቢን ላደን ጉን ስለመሰለፉ እርግጠኛ ባልሆንም አሜሪካ በእርግጥም ሽብርተኞችን በመዋጋት ላይ ከነበረች ማድረግ የነበረብን ጠቃሚ እርምጃ ኢሳም ያቀረበልኝን ዕቅድ ከአለቆቼ ጋር መክረንበት ተግባራዊ ማድረግ ነበር። የሆነ ሆኖ እንደሌሎቹ ችግሮች ሁሉ ይህንንም አስቀምጠነው አለፍን።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፱

ብዙ ሰዎች ስለ ያሲራ አረፋት ያላወቁት ነገር በተለይም ከ1993 ዓ.ም'ቱ የኦስሎ ስምምነት በኃላ፤ እንዲሁም በ1994 ዓ.ም ከሽሞን ፔሬዝና ይስሃቅ ራቢን ጋር በጋራ የኖቤል ሽልማትን ካገኙ በኃላም ቢሆን ብዙሃኑ ያልተገነዘቡት ሃቅ አራፋት ትግልን የጀመረው አክራሪ እስላም በመሆን እንደ ነበር ነው። ሌላው ቀርቶ 'ጥላ' የተሰኘው የፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅት ሊቀመንበር ከሆነ በኃላ እንኳን ከአክራሪዎቹ የሺአና ሱኒ ሙስሊሞች ጋር ግንኙነቱን ያላቋረጠና የእነኚህ ጎሣዎች አክራሪ አባላትም የፓለቲካ ጥንካሬን ይጨምሩለት የነበረ መሆኑን ነው።

ኢ.ኤ.አ. በ1929 ዓ.ም የተወለዱት አራፋት መሃመድ አብድአል ራወፍ አራፋት አል ቁጽዋ የሚል ሙሉ መጠሪያ ነበራቸው። ቀድሞ አራፋት የተገኙበት እንደጎሣ የሚቆጠር የትስስር ግንድ ሲሆን ይህ ፓለቲካዊ ይዘቱ እጅጉን የሚጎላበት ግንድ በፍልስጤም ጠንካራ ኃይማኖታዊ ምሁራንን በማብቀል የታወቀ ነው። አደገኛ የፓለቲካ ሰዎችንም በማፍራት የታወቀ የጎሣ ቡድን ሲሆን በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት የዚህ ጎሣ ወይንም አንጃ አባላት የነበሩ ግለሰቦች አዶልፍ ሂትለርንም ይደግፉ እንደነበር ይነገራል። አራፋት በፍልስጤም ይወለዱ አንጂ ያደጉት ግብፅ ውስጥ ነው። በካይሮ ዩንቨርስቲ ሲቪል ምህንድስናን አጥንተዋል። በዩኒቨርሲቲው ቆይታቸውም የፍልስጤም ተማሪዎች ሕብረት መሪ የነበሩ ሲሆን ከምረቃ በኃላ ደግሞ በግብፅ ጦር ሰራዊት ውስጥ በሌፍተናንትነት ማእረግ አገለግለዋል ከዚያም 'ሙስሊም ወንድማማቾች' የተሰኘውን የእስልምና ማህበር ተቀላቀሉ። ማሕበሩን ከተቀላቀሉ በኃላ የተለያዩ ንቅናቄዎችን በማስተባበራቸው እዚያው ግብፅ ውስጥ ሁለት ጊዜ ታስረው ተፈትተዋል። ከዚያም ወደ ኩዌት በማቅናት የእስላም ወንድማማች ማህበሩን በተገቢው ሁኔታ ለማደራጀት አሠቡ። የሆነው ሆኖ ኩዌት ጎራ ለለዮና ወጣ ላለ ኢስላማዊ የሃይማኖት እንቅስቃሴ ቦታ የምትሠጥ ሃገር ስላልነበረች አራፋት የ «ኢስላም ወንድማማቾች» ማህበርን በማፍረስ የፋታህ ንቅናቄን መሠረቱ። የፋታህ ንቅናቄ አባላት አብዛኛዎቹም የኢስላም ወንድማማቾች አባላት የነበሩና እንዲሁም በባህረ ሰላጤው የሚኖሩ የፍልስጤም ተወላጆችን ያካተተ ነበር።

አረፋት ፋታህን በዚህ ሁኔታ ካደራጁ በኃላ እ.ኤ.አ ጥር 1,1965 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በእስራኤል ላይ ጥቃትን ሰነዘሩ። አራፌት በእስራኤል ላይ ጥቃት



t.me/OLDBOOKSPDF

መሠንዘራቸው የእስምን በተለይም የአረቡን ዓለም ትኩረት ወዲያውኑ ማግኘት ችለው ነበር። በጊዜው የግብፅ መሪ የነበሩት አብዱል ናስር የአራፋትን ፀረ-ጺዮናዊነት አሊያም አክራሪ ኢስላማዊነት አቋም ለመፈተሽ ሲሉ አራፋትን ወደ ግብፅ ጋብዘዋቸው የነበረ ሲሆን በስተመጨረሻ ግን አራፋት ሊገድሏቸው ከሚፈልጓቸው ሰዎች መካከል አንዱ አብዱል ናስር መሆናቸውን ከፀጥታ ጠበቂዎቻቸው በማረጋገጣቸው የግብዣ ጥሪውን አጠፉት። የአራፋት ፋታህ እንቅስቃሴ እስከ 1970 ድረስ ይህን ያህል ጥንካሬ የተሰተዋለበት አልነበረም። በ1977 ዓ.ም ግን 'ኮሚቴ 77' የሚል አዲስ ስትራቴጂ ተነድፎ የፋታህ አባላትን ቁጥር የመጨመር እንቅስቃሴ ተጧጧፈ። ይህንንም እንቅስቃሴ በዋንኛነት ይመሩ የነበሩት የአራፋት ምክትል አቡ ጂሃድና ሙኒር ሻፊቅ አሳል ነበሩ። በተለይም የሙኒር ሻፊቅ አሳል ዋንኛ ተግባር የሊባኖስና ፍልስጤም ተወላጅ የሆኑ ምልምል አባላትን ከእስልምና ሃይማኖት አንፃር የፋታህን ፓለቲካዊ እምነት ማጥመቅ ነበር። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነበር ኢማድ ሙግኒያህ፣ አሊ ዲብና ሳላህ የፋትህ ንቅናቄ አባላት ሊሆኑ የበቁት። አራፋት በዚህ ዓይነት አዳዲስና ወጣት አባላትን በፋትህ ንቅናቄ ውስጥ ከሰበሰቡ በኃላ የአረቡን ዓለም ኢስላማዊ የፖለቲካ ነበልባል መቀላቀል ጀመሩ። ከሶሪያው ፕሬዚዳንት ሃፊዝ አልአሳድ ጋር እጅና ጓንት የሆነውን የሶሪያን ኢስላማዊ ወንድማማቾች የእምነት ማህበር የጦር መሳሪያ በመርዳት አልአሳድን ከስልጣን የማስወገድ ጥረትም አደረጉ። ይሁንና አሳድ በወቅቱ ለኢስላማዊ ወንድማማቾች ጦርመሳርያ በመርዳት ከስልጣን እንዲወገዱ ሙከራ ያደረገው CIA መስሏቸው የነበረ ቢሆንም በኋላ ላይ ግን ሃላፊነቱ የፋታህ መሆኑን በማረጋገጥ በአራፋት ላይ ብቀላን ለመፈፀም ስትራቴጂያቸውን ነደፉ። እ.ኤ.አ. በ1983 ዓ.ም ሶሪያ ሰይድ ሙራጋ (አቡሙሳ)ና ኒሞር ሳሊህ (አቡ ሳሊህ) የተባሉ ሁለት የፋትህ አባላትን በማሣመን የራሳቸውን ድርጅት እንዲያቋቁሙ አደረገች። በጊዜው በሶሪያ ውስጥ የነበሩት አራፋትንም ከሃገር በማስወጣት ወደ ትሪፓሊና ሊባኖስ እንዲሠደዱ አደረገች። ከአምስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥም ሶሪያ ውስጥ ይደራጅ የነበረው የአቡሙሳና አቡ ሳላህ ጦር ከሶሪያ የጦር ሃይል ጋር በመተባበር ሊባኖስ ውስጥ በነበረው የአራፋት ሃይል ላይ ጥቃት ሰነዘሩ። በወቅቱ አራፋት ሊባኖስ ውስጥ የነበሩ ሲሆን አምስት ያህል የሚሆኑ የግሪክ መርከቦች ከለላ በመስጠት የጥቃቱ ሰለባ ከመሆን አትርፈዋቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ በትሪፓሊ ወደብ ከትመው የነበሩትን 500 ያህል የአራፋት ተከታዮችን የፈረንሳይ ባህር ሃይል ከእስራኤል የአየር ሃይል ጥቃት አትርፈዋቸዋል። በዚህ መሠረትም አራፋት ወደቱኒዝ በማቅናት ከየትኛውም የፍልስጤም ፓለቲካዊ እንቅስቃሴ ተነጥለው እንዲቆዩ ግድ ሆኖባቸዋል። አራፋት ከዚህ አይነቱ የጥቃት ተሞክሮ ያገኙት ትልቅ ልምድ ቢኖር የእስላም ሃይሎች ከተባበሩ የሚመልሳቸው ሃይል እንደሌለ ሲሆን ዳግመኛም እንዲህ ባለው ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት ጥንቃቄ ማድረግ እንሚኖርባቸው ተገንዝበዋል።

✲✲✲



t.me/OLDBOOKSPDF

እ.ኤ.አ. 1972 ዓ.ም የኢራኑ ፕሬዚዳንት የነበሩት አያቶላህ ናኦሚ እና ያሲር አረፋት ኢራቅ ነጃፍ ውስጥ አንድ ስምምነት ተፈራርመው የነበረ ሲሆን ስምምነቱም 'በደቡብ ሊባኖስ በሚገኘው የፋታህ ካምፕ ውስጥ ኢስላማዊ ወታደሮችን እናሰለጥናለን' የሚል ነበር። ከዚያን ጊዜ ወዲህም በኢራን የፓለቲካ አብዮት ያለፉ የኢራን መሪዎች ሁሉ በዚሁ የፋታህ ካምፕ ወታደራዊ ስልጠናን በመውሰድ አልፈዋል። ይህም የአያቶላህን ልጅ አህመድ አያቶላህንና በኢረን የፓስደራን ቀዳሚ ኮማንደር የነበረውን ሙስጠፋ ቻምራን የሚያጠቃልል ነበር። አራፋትና አያቶላህ እ.ኤ.አ. ጥር 19/1979 ዓ.ም ቴህራን ውስጥ ተገናኝተው የነበረ ሲሆን በዚህ ወቅትም እጅግ በርካታ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በመመካከር የሚተጋገዙበትን ስልት የነደፉ ሲሆን በወቅቱም አራፋት ለመላው የፋታህ ንቅናቄ አባላት በሙሉ የኢራንን ፓለቲካዊ አብዮት የመደገፍ የሀሊና ግዴታ እንዳለባቸው አሳስበው ነበር። አራፋትና አያቶላህ በቴህራን ከውይይትም በላይ የሆነ ጊዜን ካሣለፉ ከሁለት ሣምንታት በኋላም ቴህራን ውስጥ ይገኝ የነበረው የዩናይትድስቴትስ ኤምባሲ እንዲዘጋ ተደረገ።

በየካቲት 1980 ዓ.ም የሌባኖስ ዜግነት ያለው የሱኒ ሙስሊም አኒስናካሽ ፓሪስ ውስጥ በስደት ይኖሩ የነበሩ የቀድሞ የኢራን ጠቅላይ ሚኒስቴር ሻፑራ ባክቴሪን የመግደል ሙከራ አደረገ። ይሁንና ናካሽ በፈፀመው የግድያ ሙከራ ስደተኛው ባክቴር ሲያመልጡ ደመከልብ የሆኑ አንዲት ወይዘሮና አንድ ፖሊስ ለህልፈት ተዳረጉ። ናካሽም በቁጥጥር ስር ውሎ ስለነበር የዕድሜ ልክ እስራት ተፈረደበት።

በጊዜው ናካሽ ስደት ላይ የሚገኙትን የቀድሞ የኢራን ፖለቲከኛ ሊገድል የተነሳሳበትን ዓላማና ግቡ ግልፅ ያልነበረ ሲሆን፣ በኋላ ላይ ግን ባክቴርን እንዲገድል ናካሽን የቀጠሩት ያሲር አራፋት መሆናቸው ሲረጋገጥ አራፋትና ኢራን በፓሪስ የሽብርተኞች ቡድን እያጠናከሩ መሆናቸውም ግልፅ እየሆነ መጣ። ከባክቴር የግድያ ሙከራ ጋር ተያያዞም ያሲር አራፋት በመላው ዓለም የኢስላሚስት አሸባሪዎችን መረብ በእጅጉ እያጠናከሩ ስለመሆናቸው እርግጥ እየሆነ መጣ።

በ1982 ዓ.ም የአራፋት ተከታዮች በሙሉ ከቤሩት እንዲባረሩ ሲደረጉ ሁሉም አባላት ወደ ኢራን በመግባት ፓስዳራንን የተቀላቀሉ ሲሆን ሙግኒህያህና ተከታዮቹ እንዲሁም ባልደረቦቹ ከኢራናውያን ጋር ጥብቅ ቁርኝታቸውን የጀመሩትም ከዚያ ወዲህ እንደነበር ይገመታል።

በ"ኃይል 17' ውስጥ የሙግኒያህ አለቃ የነበረው አሊ ዲብ ፊተኞች ኃለኛ ኃለኞች ፊተኛ እንዲሉ ሙግኒያህ አለቃው እርሡ ደግሞ ምክትል ሆኖ መስራት የጀመረውም ያኔ ነበር። የአራፋትና የሙግኒያህን ግንኙነት ለመረዳት ጊዜያትን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚወስድ ግልፅ ነበር። የሆነው ሆኖ ሙግኒያህ አንድ የኩዌትን አውሮፕላን ከጠለፈ በኃላ ትስስራቸው ገሃድ መሆኑ ታውቆ ነበር።

ሙግኒያህ በኩዌት የታሰሩ አስራ ሰባት አሸባሪዎችን ለማስፈታት ሲል የኩዌትን አውሮፕላን ሊጠልፍ መሆኑን ለአራፋት እንዳስረዳቸው መረጃ አግኝተን የነበረ ሲሆን ሙግኒያህ ይህንን ሊያደርግ ያቀደውም የካቲት 23/1988 ዓ.ም ነበር። ምንም እንኳን አራፋት ስለ ሁኔታው ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ የነበረ ቢሆንም ሃሳቡን ግን ደግፈውት ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ በመጋቢት 14/1988 አሊ ዲብ እስረኞቹን ለማስፈታት ከኩዌት መንግስት ጋር ለድርድር እየተዘጋጀ መሆኑን አሳውቆአቸው ነበር። የሆነው ሆኖ የኩዌት በረራ 422 አውሮፕላን ይህ ከመፈፀሙ በፊት በሙግኒያህ ተጠልፎ ነበር። እናም አውሮፕላኑ ከተጠለፈ ከአራት ቀናት በኃላም አሊ ዲብ ከአራፋት ጋር በመገናኘት ከተመካከረ በኃላ እስረኞቹ ካልተለቀቁ የታገቱትን መንገደኞች አንድ በአንድ እንደሚገድሏቸው ለኩዌት መንግስት ግልፅ አደረገ። ብዙም ሳይቆይ ሙግንያህ ሁለት መንገደኞችን ወዲያው ሲገድል አራፋትን ሁኔታው ድንጋጤ ውስጥ ጨመራቸው። ሙግኒያህ አውሮፕላኑን ወደኪዌት ከዚያም ወደ አልጀሪያ እንዲሄድ ካደረገ በኃላ በመጨረሻም አውሮፕላኑ ወደመጣበት ተመልሷል።

የመካከለኛው ምስራቅ ፖለቲካን ወይንም የሽብርተኞች መረብን ሳልተራዳ አንድ ሰው ሁሉም ነገር ቀላል ይመስለዋል። ነገር ግን ሁኔታውን በቅርበት ለሚከታተለው የሽብርተኞች መረብ እጅግ ውስብስብና እጅግ የተጠላለፈ መሆኑ ሲሆን የሚገርመው ነገር ደግሞ ሁሉም የሽብሩ ቱባው ገመድ ተተብትቦ ተተብትቦ የሚደርሠው ከያሲር አረፋት እግር ስር መሆኑ ነው። ከዚያም ወደ ኦሳማ ቢንላደን ሊሄድ የሚችል መሆኑም የማይጠረጠር ሲሆን ውስብስብነቱ የባሰ የሚሆነው ግን ቢላደን ጋር ሲደርስ ነው።

በአንድ ወቅት ያሲር አረፋትን በኃይት ሃውስ "ሮዝ ጋርደን' ስመለከታቸውና በበረሃ ድንኳኖች ውስጥ በምስጢር ከ CIA ሰዎች ጋር ይገናኙ እንደነበረ ስሰማ ይህንን ሁኔታ ኦሳማ ቢላደንም የሚያውቅ አይመስለኝም አልኩ ለራሴ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲

## ነሐሴ 1988፣ ቤሩት-ሊባኖስ

ጓደኛዬ ቹክ ማኪ ጉዞዋን ወደ ፓሪስ ልታደርግ ወደተዘጋጀችው ሄሊኮፕተር ጎትቶ አስገባኝ እንደገና ፓሪስ በመመደቤ ቤሩትን ልለያት ነው፡፡ ይሁንና ትንሽ ቅር ሳይለኝም አለቀረም፡፡

ቹክ እጅግ የምቀርበው ጓደኛዬ ነው፤ ለሁለት ዓመታት ያህል አንድ ቢሮና አንድ ወንበር ተጋርተን ሠርተናል፡፡ ስንዝናናም አንድ ላይ ነው፡፡ ከቅርበታችን የተነሣም እንቀላለዳለን እናም ታድያ ሰዎች ከቹክ ገፅታ አንፃር ሲመለከቱኝ ሲቢጣ ነኝ፡፡ ይህንን በሚያሣብቅ ሁኔታም ቹክ በአንድ እጁ ሳይቀር ያነሣኝ ነበር፡፡ ቢፈልግ ለበርካታ ሠዓታት ተሸክሞኝ ሊቆይም ይችላል እንደ ዕውነቱ ከሆነም እንደ ቹክ የሰማይ ስባሪና ጠንካራ ሰዎችን አይቼ አላውቅም፡፡

ከሄሊኮፕተሯ ገብተን ጉዞ ስንጀምር ቤሩትን ለመጨረሻ ጊዜ አቆልቁዬ ሳያት ከወደቡ አቅራቢያ ዕሳቱ እየጋመ ይንቀለቀላል በዚህ ጊዜ ቤሩት ውስጥ ልሠራው የምችለው ብዙ ነገር እንደነበር ትውስ አለኝ፡፡ ወዲያውኑም ይህንን ሃሳቤን ተውኩና የሃሱናን ፎቶ አውጥቼ ተመለከትኩ፡፡ ሃሱና በቅርብ ቀን አንድ የጭነት መኪና ይዞ ወደ ኢምባሲያችን የገባ አጥፍቶ ጠፊ ነበር፡፡ የሃሱና ጉዳይ ብዙ መጣራት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነበር ምንያረጋል ታዲያ በአለቆቼ ትዕዛዝ ትቼው ወደ ፓሪስ አቀናሁ፡፡ የሆነው ሆኖ የኔን ቦታ ሌላ ባለስልጣን ስለሚይዘው ጉዳዩን በሚገባ ያጣራ ይሆናል፡፡ የኢምባሲውን የቦምብ አደጋ በተመለከተም CIA እስከመጨረሻው ተጉዞ ፋይሉንም እንደሚዘጋው እምነት አለኝ፡፡

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ግን ለቹክ አላወራሁትም ነበር፡፡ ... ጥቂት ከተንቀሣቀስን በኋላ የእኔና የቹክ መለያያ ደረሠ፡፡ ቹክ እንደኔ ወደ ፓሪስ አያቀናም፡፡ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል እዚያው ይቆያል፡፡ እናም መለያየታችን ድንገት ነውና በመለያያችን የመጨረሻ ሰዓት ተቃቅፈን ተሣሥመን ተለያየን፡፡ ጊዜ ብናጣም እንኳን እንደምን እየተደዋወልን መጠያየቅ እንዳለብን ቃል ተገባባን፡፡

እናም ቹክ ተለይቶኝ ጥቂት ሜትሮችን ከተጓዘ በኋላ ጠራሁት፡፡ «እዚህ አካባቢ ለብዙ ጊዜ የምትቆይ ከሆነ ... ነግሬሃለው ሽብርተኞች ነፍስህን ይበሏታል» አልኩት በቀልድ መልክ፡፡ እሱም እየሳቀ «ወንድ ወጣቸው በለኝ እንጂ!!» ብሎኝ በዚያው ተለያየን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ከስድስት ወራት በኃላ ማለትም ታህሳስ 21/1988 ዓ.ም «ፖን ኤኤም 103» አውሮፕላን በስኮትላንድ የሎከርቢ ሰማይ ላይ እንዳለ በመፈንዳት ቁልቁል ወደ ምድር መውዘግዘጉ ተሠማ፡፡ ውዱ ጓደኛዬ ቹክ አውሮፕላኑ ውስጥ መኖሩንም አውቅ ስለነበር ልቤ በድንጋጤ ራደ ለሰዓታትም ፈዝዤ ቀረሁ፡፡

☼☼☼

ከሎከርቢው ፍንዳታ በኃላ የነበሩት ሁኔታዎች በመጠኑም ቢሆን ፍርሃት ውስጥ የከተቱኝ ነበሩ፡፡ አደጋው በርግጥም ከባድ የነበረ ሲሆን ድርጊቱን ሊፈፅመው የሚችለው አካልም ደግሞ በሊባኖስ የከተመና በኢራን የሚረዳ የሽብርተኞች ቡድን እንደሚሆን መገመት እያዳግትም፡፡ ቤሩት ውስጥ ብሆን ኖሮ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ምርመራ እንዲኖር የማደርግበት ዕድል ነበረኝ፡፡ የሆነው ሆኖ ጉዳዩ ዓለም አቀፋዊ የሽብርተኞች መረብን የሚነካካ በመሆኑ በምገኝበት ፓሪስ የሚኖሩ የአረብ ቅጥረኛ ሽብርተኞችን መከታተልም በራሱ አንድ ነገር ነው ብዬ ለራሴ ተፅናናሁ፡፡ እናም ኢራን በሎከርቢው የአውሮፕላን ፍንዳታ እጇ እንዳለበት እርግጥ የሆነው በ1988 መጀመሪያ አካባቢ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳትም ቅፅበታዊ የብቀላ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን በባህረ ሰላጤው አካባቢም አንድ የኢራን 'ኤርባስ' ተመትቶ እንዲወድቅ ተደርጓል፡፡ ይህ ከሆነ ከጥቂት ሰዓታት በኃላ ሙሃመድ አፊዝና ሌሎች ሁለት የፍልስጤም ነፃ አውጭ ድርጅት አመራሮች ደቡብ ሊባኖስ ውስጥ በሚገኝ የስደተኞች ካምፕ ውስጥ አስቸኳይ ስብሰባ አድርገው የነበረ ሲሆን የስብሰባው ተቀዳሚ ዓላማም በአየር ላይ እንዳለ በአሜሪካ ሚሳኤል ለተመታው የኢራን አውሮፕላን (ኤርባስ) የበቀል እርምጃ ይሆን ዘንድ የአሜሪካ አውሮፕላንን የማጋየት ተግባር በሚከናወንበት ሂደት ላይ ነበር፡፡

ምንም እንኳ አሜሪካ የኢራኑ ኤርባስ ተመትቶ የወደቀው በስህተት ነው ብትልም ኢራናውያን ግን ይህንን የሚቀበሉበት አንጀት አልነበራቸውም፡፡ በመሆኑም ዓለም ላይ እጅግ በተቀናጀ ሁኔታ ከተቀናጀው ከፍልስጤም ነፃ አውጭ ድርጅት ጠቅላይ ዕዝ (General Command) ጋር በመተባበር የኢራን ባለስልጣናት የበቀል ጦራቸውን ሰበቁ፡፡ እ.ኤ.አ. የካቲት 21/1990 ዓ.ም አንድ የኦስትሪያ አውሮፕላን አየር ላይ እንዳለ ተመትቶ ወደቀ ለጥቆም ከሁለት አመት በኃላ ማለትም ነሐሴ 16/1992 ዓ.ም ኤል.ኤል በተሠኘ አውሮፕላን ውስጥ የፈነዳ ቦምብ አራት ግለሠቦችን አቆሠለ እናም ለሁለቱም አደጋዎች የኢራን ባለስልጣናት እጃቸውን ባስገቡበት ሁናቴ ጠቅላይ ዕዙ ሃላፊነቱን መውሠዱ ግልፅ ነበር፡፡

የአሁኑ የኢራን ጥቅም ጠባቂ የሆነው ዳልቃሙኒ በ1980ዎቹ አጋማሽ ገደማ በአውሮፓ ውስጥ ይኖር የነበረ ሲሆን በአውሮፓ ማክዶናልድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬስቶራንቶች እየተዝናና በነበረበት ወቅት በእንቲፋዳህ እንቅስቃሴው በርካታ ፍልስጤማውያን ጓደኞቹ መስዋዕት እየሆኑ ነበር፡፡ ዳልቃሙኒ ይህንን ሁኔታ በሚገባ ይረዳ ነበር፡፡ ይሁንና ውስጡ ይብሰለሰል ስለነበር በዚህ የተነሳ ከዕለታት በአንዱ ቀን የእስልምና ንቅናቄን ለመቀላቀል ወሰነ እናም ወሰኖም ሳይውል ሳያድር በኢራን ውስጥ የሚገኘውና በፍልስጤም ነፃ አውጭ ድርጅት ጠቅላይ ዕዝ በሚንቀሳቀሠው አንጃ አባልም ሆነ፡፡ ይሁን እንጂ ዳልቃሙኒ ቡድኑን ከተቀላቀለ በኋላም እንኳን ታማኝ አማኝ መሆኑን የጠቅላይ ዕዙ አለቆች ቢረዱም ቅሉ አሁንም ተጨማሪ ፈተናዎችን መፈተን እንደሚገባቸው አመኑ፡፡ በነሐሴ 31/1997 እንዲሁም ሚያዚያ 26/1998 ባሉት ጊዜያትም በኢራን ባለስልጣናት አጋፋሪነት ዳልቃሙኒ ምዕራብ ጀርመን ውስጥ በሚገኝ የአሜሪካ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ላይ አደጋ እንዲጥል ተደረገ፡፡ አደረገውም፡፡ ምንም እንኳን በአደጋው ጉዳት ባይደርስም ዳልቃሙኒ በርግጥም የጠቅላይ ዕዙ ታማኝ አገልጋይ እንዲሆን የኢራን ባለስልጣናት ተገንዝበው ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ዳልቃሙኒ በሎከርቢ ሰማይ ላይ በፈነዳውና በአውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩ 259 ሰዎችንና ምድር ላይ የነበሩ ከ11 በላይ ሰዎችን በፈጀው አደጋ እጁ እንዳለበት በመጠርጠሩ ከሌሎች በጀርመን ከሚገኙ የጠቅላይ ዕዙ ህዋስ ባልደረቦቹ ጋር በቁጥጥር ስር ሊውል ችሏል፡፡ ዳልቃ ሙኒ አሁን ድረስ በእስር ላይ የሚገኝ ቢሆንም እሱ ይመራው ከነበረውና በአደጋው ከተሳተፉት ቀንደኛ ሽብርተኞቹ የተወሠኑት በማምለጣቸው ምርመራውን አዳጋች አድርጎት ነበር፡፡

የአውሮፕላኑ አደጋ ከደረሰ ከሁለት ቀናት በኋላ በጠቅላይ ዕዙ የባንክ ሒሳብ ቁጥር የተመዘገበ 11 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን ገንዘብ ከስዊዘር ላንድ ወደ ፓሪስ ከዚያም ወደ ሃንጋሪ በተለያዩ የጠቅላይ ዕዙ የባንክ ሒሳብ ቁጥሮች መዘዋወሩ ታወቀ፡፡ የሚገርመው ነገር ደግሞ በፓሪስ ብሄራዊ ባንክ ውስጥ ተቀምጦ የነበረው የጠቅላይ ዕዙ ገንዘብ እስር ላይ በሚገኘው ዳልቃሙኒ ስም የተመዘገበ መሆኑ ነበር፡፡

የሒሳብ ቁጥሩ እንደሚያስረዳውም ከሆነ 500 ሺህ ዶላር የሚሆነው ገንዘብ በአውሮፕላኑ አደጋ ተሳትፎ እንዳለው ለሚጠረጠረው ሙሃመድ አቡ ታሊብ የተከፈለ ነበር፡፡ ከዚህ መነሻነትም 11 ሚሊዮን ዶላር የተዘጋጀው አውሮፕላኑን ለማጋየት ለተጠነሠሠው ሴራ መገልገያ እንዲሆን ታስቦ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም ነበር፡፡ አቡ ታሊብ ከጥቅምት 3/1988 እስከ ጥቅምት 19/1988 ዓ.ም ድረስ በማልታ ደሴት ጉብኝት እንዳደረገና በዚያውም አንዳንድ ቁሳቁሶችን ልብሶችን፣ ፈንጂዎችንና የጦር መሣሪያዎችን ገዝቶ እንደያዘ የተገመተ ቢሆንም አውሮፕላኑን የሚያጋዩ የጦር መሣሪያዎችን የሠበሠቡት ግን ከዳልቃሙኒ የቅርብ ግንኙነት እንዳላቸው የተገመቱት የሊቢያ ዜጎች ሊሆኑ እንደሚችሉም ሌላኛው ጥርጣሬ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

☆☆☆

በCIA በኩል ናቢል የተሠኘው ስም በሐምሌ 1988 በተካሄደው በጠቅላይ ዕዙ በተደረገው ስብሰባ ላይ ለናቢል ማክሁዙሚ (አቡ አቢድ) የተሠጠ ስም መሆኑ ተረጋግጧል:: ናቢልም የዳልቃሙኒ ረዳት እንደሆነ ይታወቃል:: ከዚህም ሌላ ናቢል ማክሁሙዚ ከፓስዳራን ጋር ግንኙነት ያለው ቀንደኛ ሰው ነው:: ኢሪናዊው የፓስዳራን ኪዝ ኦፊሰር ፍሪዲን መህዲ ነዛድም ከናቢል ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳላቸው ሲታመን 'ናቢል ማክሁዙሚ ወደ ጀርመን ተጉዞ ከ ዳልቃሙኒ ጋር ስለቦምብ ጥቃቱ ተወያይቶ ነበር ወይስ አልነበረም?' የሚለው ጥያቄ ግን ለCIA'ም ሆነ ለጀርመኖች እንግዳ ነበር:: በእርግጥ መህዲ ነዛድ በሐምሌ 1988 ጀርመንን መጎብኘቱ ግልፅ ነበር፤ ነገር ግን እዚያ ሄዶ ምን እንደሠራና ከማን ጋር እንደተገናኘ አይታወቅም:: በ1988 መግቢያ አካባቢም ሊቢያን የጎበኘ ሲሆን ምናልባት በዚህ ወቅት ከዳልቃሙኒ ጋር ተገናኝቶ አውሮፕላኑን የማጋየት እቅድና ፕሮግራም ነድፈው ሊሆን እንደሚችል ይገመታል:: ይህ ከሆነ ደግሞ የኢራን፤ ሊቢያና የፍልስጤም ነፃ አውጭ ጠቅላይ ዕዝ ባለስልጣናት የሎከርቢውን ፍንዳታ ለማስፈፀም አይነተኛውን ሚና ተጫውተዋል ከሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ፍንጭ ይታያል:: ሌላው ቀርቶ ጀርመን ራሷ በሎከርቢው ኤ.ኤ.ኤም 103 አውሮፕላን ፍንዳታ እጇ እንደሌለበት እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: ነገር ግን ምንም እንኳን በእነ ዳልቃሙኒ የሚመራው ህዋስ በጀርመን ውስጥ እየተጠናከረ የነበረበት ሁኔታ ቢፈጠርም የጀርመን ወታደራዊ ሃይሉ እንቅስቃሴውን ለመግታት በተለይም ህዋሱ በተደጋጋሚ የሚሞክረውን አደጋ የመጣል አጋጣሚ አክሽፈዋል፤ በእርግጥ ከዚያ አንፃር ስንመለከተው ጀርመን በጉዳዩ ላይ ሃላፊነት የማትወስድበት ዕድል አላት:: ይሁንና በዳልቃሙኒ የሚመራው ህዋስ ዓላማ ምን እንደሆነ ጀርመን አለማወቋና ለማወቅም ጥረት አለማድረጓ እንደ ችግር ሊወሠድባት መቻሉ የማይቀር ነበር::

ጀርመን በጊዜው ከኢራን ጋር የፈጠረችው የኢኮኖሚ ግንኙነትም በጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዳትሠጠው ያደርግ ነበር:: ማለትም ጀርመን ከኢራን የነዳጅ ግዥ ለማከናወን እንዲሁም ሜርሲዴስ መኪናዎቿን ለኢራን ለመሸጥ በከፍተኛ ጥቅም በመተሣሰሯ የተነሣ ኢራንን በየትኛውም አቅጣጫ የምትደግፍበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር:: ሌላው ቀርቶ በጀርመን የጦር ካምፖች የኢራን ወታደሮች እንደሚሠለጥኑም የተደረሠበት ጉዳይ ነበር::

ጀርመን ብቻ ሳትሆን ፈረንሣይም ብትሆን በጊዜው ከአረብ ሃገራቱ የምታገኘው ጥቅም ስለነበራት ከ CIA ጋር መረጃዎችን ለመናበብ ፍላጎትና ጊዜ አልነበራትም:: እ.ኤ.አ በ1991 የአልጀሪያ የእርስ በርስ ጦርነት ከተፈፀመ በኋላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኢስላማዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ተቋቁሟል፡፡ ከፈረንሳይ ህዝብ ቁጥር የሚልቀውን መጠን የያዙት አልጀሪያውያን በሃገራቸው ፓለቲካ ጣልቃ መግባታቸው ስለማይቀር ጉዳዩ ፈረንሳይንም የሚነካ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ፈረንሣይ እንደ ጀርመን ሁሉ ከፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ትስስሮሽ በተገናኘ መልኩ ከአረቡ አገራት ጋር ግንኙነት እንደሚኖራት የታወቀ ነበር፡፡

✡✡✡

የሆነው ሆኖ ወቀሣዎችን ሁሉ በአውሮፓ ሃገራቱ ላይ ሙሉ በሙሉ ማድረግ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም CIA'ም የራሱ ችግር ነበረበት፡፡ በተለይም ከአረብ ሃገራት ጋር የጥቅም ግንኙነት ባላቸው የአውሮፓ ሃገራት የCIA ቅጥረኞች ባለመኖራቸው ትልቁ ችግር ነበር፡፡ የሎክርቢው አውሮፕላን ከፍራንክፈርት ሲነሳ ጠንከር ያለ ፍተሻ ያልተደረገበት መሆኑ ሲረጋገጥ ሀላፊነቱን ጀርመን መውሠድ ነበረባት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ CIA በጀርመን የሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ አንድም ቅጥረኛ የሌለው መሆኑ ከአውሮፕላኑ ፍንዳታ በፊት የሴራ ፍንጮች እንዳያገኝ ምክንያት ሆኗታል፡፡ ይህ ሁኔታ በአንዳንድ የአውሮፓ ሃገራት ዘንድም ተመሣሣይነት ይታይበት ነበር፡፡ የCIA ችግር ደግሞ አዳዲስ ቅጥረኞችን አለማፍራት ብቻ አልነበረም፤ ነባሮቹ ቅጥረኞችም እጅጉን እየተሰላቹና ግድየለሽነትን እያሣዩ መምጣታቸው ነበር፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ የዋሽንግተን መንግስት በCIA ውስጥ ያለው ጣልቃ ገብነትና ችግሮችን ለማስወገድ የሚደረጉ ጥረቶች አዲስ ቅጥረኞችን ፍላጎት እንዲያሳድሩ ካለማድረጉም በተጨማሪ ነባሮቹም ፍላጎት እያጡ እንዲመጡ ማስገደዱ ነበር፡፡ እናም ታድያ ከእነዚህና መሰል ሌሎች CIA ነክ ችግሮች ጋር ወደ ዋሽንግተን መሄድ ነበረብኝ የ ይሁንና ነገሮች ሁሉ ደስ አላሉኝም፡፡ በ1989 መጀመሪያ አካባቢ ቤኪ ከተሠኘች CIA' ን ለቃ CIA አባል የነበረችና የስለላ ስራ አልተመቸኝም በሚል ሙድ ሳንፍራንሲስኮ ከምትኖር ወጣት ሴት ጋር አንድ ቀጠሮ ይዤ ነበር፡፡ እናም ከቤኪ ጋር የተገናኘሁት ከፓሪስ ወጣ ብሎ በሚገኝ አንድ ዕድሜ ጠገብ ሆቴል ውስጥ ነበር፡፡ ታዲያ ወደ ሆቴሉ ስንገባ መጀመሪያ የተቀበለን ነገር ቢኖር ሆቴሉን ያወደው የቡና የወይን ጠጅ ሽታ ነበር፡፡ እናም ቤኪ ወደያዝነው ክፍል የሚመጣ ሙሉ ሰርቪስና ሻይ አዘዘች ወይይታችንን የሚቀላቀለው ጃኮስ እስኪመጣ ድረስም እየተጨዋወትን ቆየን፡፡ ጃኮስ ማለት ደግሞ በጦር መሳሪያ ንግድ ዕንቅስቃሴ ይተዳደር የነበረ ቅጥረኛ ሲሆን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን በንግድ ስራው ደስተኛ አይመስልም ይህንንም ካለባበሱ ለመገመት ችያለሁ፡፡ ከዚህ በፊት ደልዳላ ሠውነት እንደነበረው የሚያስታውቀው ጃኮስ አሁን ግን ስጋው የከዳው ይመስላል፡፡ በትከሻዎቹ ትይዩ ከፍና ዝቅ ብለው የተለጠፉት የሸሚዙ ክሳዶች ግዴለሽነቱን ሲያሳብቁ የሸሚዙ አዝራሮችም በቦታው የሉም፡፡ ጃኮስ እንደደረሠ አንዲት ሴት ልጅ ከእርግዝና ምርመራ ጋር በተያያዘ ወደ ሆስፒታል ይዞ መሄድ እንዳለበትና ከዚያ በኋላ ቢመለስ ጥሩ እንደሆነ ቢናገርም ቤኪ ተቃወመችው፡፡ ቤኪንና ቡናውን ከተመለከተ በኋላም ኮኛክ መውሰድ እንደሚፈልግ አሳወቀ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ጃኮስ ኮኛኩ ከመጣለት በኃላ ይዞት የመጣውን መፅሃፍ እያገለባበጥን በማየት ውይይት ማድረጋችንን ቀጠልን፡፡ ዶክመንቱም ጃኮስ ያደረጋቸውን ድርድሮች ባይዝም ሌሎች ጠቃሚ ነገሮች ነበሩት፡፡ በተለይም አንድ የስዊዘርላንድና ብሪታንያ ውልደት ያለው ግለሠብ በሶቬየት ህብረት የተመረቱ ሚሳኤሎችና ሌሎች መሣሪያዎችን ወደ ኢራን ይልክ እንደነበር ዶክመንቱ ይዘረዝራል፡፡ ጃኮስ ቤኪ በCIA ውስጥ በነበረችበት ጊዜ ቅጥረኛዋ በመሆኑ ይህንን ጠቃሚ መረጃ ለምን እንዳላሣወቀች ግልፅ አልሆነልኝም፡፡ እኔም በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ያልኩት ነገር የለም፤ ለማንኛውም ከዚህ በኃላ ጃኮስ የኔ ቅጥረኛ እንደሚሆን አውቃለሁ፡፡ ጃኮስም ለመሄድ ሲዘጋጅ ቤኪም በቀዘቀዘ መንፈስ ሠላምታ ከሠጠችው በኃላ በሩን እስከሚወጣ ድረስ በአይኗ ሸኘችው፡፡ ሁኔታዋም አልደነቀኝም ነበር ምክንያቱም በቅጥረኞችና በኦፊሰሮቻቸው መካከል በሚደረጉ እንዲ አይነት ስብሰባዎች የተለመደ ክስተት እንደሆነ አውቃለሁና፡፡

የሁለተኛውን ቀጠሮአችንን ያደረኩት ግን ከፓሪስ ርቃ በምትገኝ አንዲት አነስተኛ ከተማ ነበር፡፡ ዓላማዬም በባቡር ወደ ጄኔቭ መሄድና ከዚያም መኪና ተከራይቼ ወደ ፈረንሳይ መመለስና ድንበር አካባቢ በሚገኙ የፈረንሳይ ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን መመርመር ነበር፡፡ ጃኮስና እኔም የተገናኘነው በትንሿ ከተማ በሚገኘው አንደኛ ደረጃ ሬስቶራንት የነበረ ሲሆን የያዝነው የመመገቢያ ክፍልም ፈረንሣውያን ወይዛዝርቶቻቸውን የሚያዝናኑበት ክፍል ነበር፡፡ ጃኮስና እኔ በርግጥ ብቻችን ነን፡፡ በንግግራችንና በሁኔታችን የማንንም ትኩረት በማንወስድበት ሁኔታ መሆናችንም አስደስቶኛል፡፡

አንድ ሁለት ለማለት የጀመርነውም ከአንድ ባህላዊ መጠጥ ሲሆን በመቀጠልም እኔ ከዚህ በፊት የማውቀውን ነጭ ቡርጋንዲ መኮምኮም ቀጠልን፡፡ ሁለተኛውን ብርጭቆ እንዳጋመስኩ ጃኮስ መጋል ጀመረ፤ ደህንነቴንም ከጠየቀኝ በኃላ በቀጥታ ወደ ጨዋታው ዘለቀ፡፡

«በፈጣሪ ታምናለህ?» አለኝ፡፡ መጀመሪያ ጥያቄውን በቀልድ መልክ ያነሳው ቢመስለኝም ከሁኔታው ሳስተውለው ግን የምሩን እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ «በአንድ እጅግ አደገኛ በሽታ ቢያዝ ይሆናል እንዲህ ዓይነት ጥቃቄ ያነሣልኝ» በማለትም አሠብኩና «... አይ... ይሄን ያህል አለምንም!» አልኩት፡፡

«እየፈገገ እጅግ በጣም ጥሩ ነው!» አለኝ፡፡

«እንግዳ ጥያቄ ነው የጠየከኝ፤ አንድ ቅጥረኛ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ሲጠይቀኝ የመጀመሪያዬ ነው!» አልኩት፡፡ ለአፍታ ያህል በሀሳብ ከቆዘመ በኃላ ቤኪ ባለፈው ዓመት ምን ስትሰራ እንደነበር ታውቃለህ?» አለኝ፡፡ እንደማላውቅ ካረጋገጥኩለት በኃላ «እኔን ወደ ክርስትና እምነቷ ለትለውጥ አመቱን ሙሉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና መፅሀፍ ቅዱስ ስትሰብከኝ ነበር የከረመችው ስለ ቢዝነስና



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለማመጣላት ዶክመንቶች ከእኔ ጋር የማውራት አምሮቷ ግን ዝቅተኛ ነበር፡፡» አለኝ፡፡ ስለዚህ ጉዳይም ፓሪስ ከተመለስኩ በኋላ በፓሪስ በሚገኘው ቢሮአችን ለሚሰራው አንጋፋው ፈረንሳዊ የCIA ሰው ነግሬው ነበር፡፡ የሚገርመው ነገር ቢኖር ፓሪስ በሚገኘው የCIA ቢሮ ከሚሠሩ ከሶስት ወይም ከአራት ያላነሡ አባሎቻችን ተልዕኮአቸውን ትተው ቢኪ በምትከታተለው የክርስትና እምነት ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ አንዱ እንዲያውም የአስተዳደር ኦፊሰር የነበረ ሲሆን የስብከት ወረቀቶችን በመበተን ስራ ላይ መወጠር ከጀመረ መሰንባበቱን ሰምቼያለሁ፡፡ ቹክ ይህንን ጉዳይ አስቀድሞ ያውቅ ስለነበር ምንም አልመሠለውም፡፡

ጉዳዩም ከእርሡ ቁጥጥር ውጭ መሆኑንም ሳይረዳ አልቀረም፤ ምንም እንኳ ጉዳዩ በተለይም ከእምነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ እንደ መብት ሊቆጠር ቢችልም በCIA አይን ይህን ዓይነቱን እንቅስቃሴ ማድረግ ግን ትክክል አልመሠለኝም፡፡ የጃክስና የቤኪ ታሪክ ትኩረት የሚሻውና ራሡን የቻለ መፍትሄ የሚያስፈልገው በበርካታዎቹ የCIA ሰዎች ላይ የሚንፀባረቅ ችግር መሆኑ ግልፅ ቢሆንም ወደ ሌላው አዲስ ችግር አዕምሮአችን መወጠር ነበረብን፡፡ በፓሪስ ያገኘነው ሌላ አንድ መረጃ በርግጥም አስደንጋጭ ነበር፡፡

ከፓሪሱ ግዙፍ ወታደራዊ ካምፕ አቅራቢያ በሚገኝ ሰፍራ አንድ የኢራን ቡድን እየተንቀሳቀሰ ነው የሚል ነበር፡፡ እናም በአዲሱ መረጃችን መሰረት በጉዳዩ ላይ ጠልቆ በመግባት በኩልም ጉዳዩን እኔ መከታተል እንዳለብኝም ሳሳውቃቸው ፈረንሳውያኑ ኦፊሰሮቻችን ተሳለቁብኝ ምክንያታቸው ደግሞ መረጃው ተጨባጭነት እንደሌለው በመረዳታቸው ነበር፡፡ ይሁንና እኔ ግን ቅር ተሰኝቼበታለሁ፡፡ ከሁለት ዓመታት በፊት በዚሁ አካባቢ ከትመዋል የተባሉ የኢራን ሽብርተኞች በዲፕሎማቶቻችን ላይ ባደረሱት አደጋ ብዙዎቹን መግደላቸውንና ማቁሠላቸውን ሳስበው ይበልጥ ጭንቅ አለኝ፡፡ ይሁንና እኔ ግን በሚስጥር ከአንድ የፈረንሣይ የቴሌኮሙኒኬሽን ቴክኒሻን ጋር በመተባበር የኢራን ሽብርተኞች ይገኙበታል በሚባለው ሰፍራ ላይ ያነጣጠረ ስልክ የመጥለፍ ተግባርን ማከናወን ቀጠልን፤ ነገር ግን እኔ ብዙም በማልረዳው ሁኔታ ይህ ሙከራ ሳይሣካ ቀረ፡፡

በመሆኑም ሌላ ዘዴ መጠቀም የተሻለ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በወርሃዊ ህዳር 1990 እንደ ጥሩ መረጃ ተገኘ፡፡ ይህም መረጃ ፈረንሣይ ሶስት ያህል የአቡኒዳል ተማሪዎችን በምስጢር እያሠለጠነች መሆኑን ተረዳን፡፡ የፈረንሳይ መንግስትም ለሠልጣኞቹ የሚሆነውን ወጭ እንደሚሸፍነው ተገነዘብን፡፡

አቡኒዳልም በምስጢር በካምፑ ውስጥ የሚገኝበት አጋጣሚ በተደጋጋሚ እንደሚፈጠር መረጃ በመገኘቱም የስልክ መጥለፍ ሂደቱን አጧጧፍነው፡፡ ይሁንና ብዙም አልተሳካልንም ነበር ምክንያቱም በተጠለፈው ስልክ ውስጥ የሰማነው ነገር ቢኖር 'መንግስት ይህ እንዲከሠት አይፈቅድም' የሚል ሐረግ ብቻ ነበር በተደጋጋሚ እንሰማ የነበረው፡፡ እናም ከዚያ በፊትና በኋላ የተነገሩትን ሀገሮች ባውቃቸው ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ይሁንና ፍላጎቴ ከምኞት አላለፈም ነበር፡፡ እናም ፓሪስ የስለላውን ስራ



t.me/OLDBOOKSPDF

እስከነ አካቴው የረሳችበት ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ኦፊሠሮች ከትጥረኞቻቸው ጋር በመገናኘት ጥቅም የሌላቸውን ውይይቶች ማድረግና ምንጫቸው ግልፅ ያልሆነ ሪፓርቶችን ይፅፋሉ፡፡ ሁሉም ሃላፊነቱን የረሣም ይመስላል፡፡ ኦፊሠሮች ዋንኛ ስራቸው ሴሚናሮችንና ስብሰባዎችን መካፈል ብቻ ሆነ፡፡ በዚያው ሰሞን አንድ ቅጻሚም ሁሉም አባል የአሜሪካ ቤዝ ወደ ሆነው ቤልጂዬም ሞንስ ውስጥ ወደ ሚገኘው ሰፍራ አመራ፡፡ ጉዞው ደግሞ ለስራ ሳይሆን ለሽርሽር መሆኑ ያስታውቅ ነበር፡፡

ይህንን ሁኔታ ስመለከትም አንድ ነገር አስታወስኩ፤ የCIA የዘመቻ መምሪያ ሲዳከም ሃላፊነትን የመወጣት ተግባር የሚከውኑት ቅጥረኞች ሳይሆኑ ሳተላይቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ቢቻል ኖሮ ከቅጥረኞች ይልቅ የስለላ ተግባር ሁሉ በሳይተላይቶች ቢሠራ እንዴት ጥሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ የቅጥረኞችን ውሸት፣ አለመታመን፣ ፍርሃትና መረጃ ለሌሎች አሣልፎ የመስጠት ሁኔታን ማስወገድ ነው፤ በሁለተኛ ደረጃም ደግሞ ቅጥረኞችን ለመቅጠርና ለተጓዳኝ ስራዎች የሚወጣውን ወጭም መቀነስ በተቻለ ነበር፡፡ እናም እኔ በፓሪስ የCIA መረብ እየተበጣጠሰ መሄዱን ካጤንኩ ሰንብቼአለሁ፡፡ ስለላ በርግጥም እጅግ አደገኛው የስራ አይነት መሆኑን እየተረዳሁትም መጥቼያለሁ፡፡ CIA በቅጥረኞቹ ላይ የሚያደርገው ቁጥጥር የላላ በመሆኑ ምክንያት ችግሩ ወደባሠ ሁኔታ እያቆለቆለ እንዳለ መገንዘብ ቢቻልም አንድ ሠው መፍትሄ ሊያመጣ እንደማይቻለው አወቅኩ፡፡ እናም እኔ በዚህ ሁኔታ በ CIA ውስጥ የምቆይም አልመሰል አለኝ፡፡ ለማንኛውም ግን ደርሶብኝ ከነበረው የመንፈስ ብቸኛታና መቀዝበር ለጊዜውም ቢሆን ከፓሪስ ውጭ CIA ወደሚገኝበት ሰፍራ ማምራት እንዳለብኝ ራሴን አሳመንኩት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፩

## ጥቅምት 24/1992፤ ዱሻንቤ-ታጃኪስታን

የስልኩን እጀታ ወደ መስኮቱ አወጣሁኝና የCIA ንዑስ ዲፓርትመንቶች ኦፊሠር የሆነው ባልደረባችን እየተካሄደ ያለውን ነገር እንደሠማ በማለት 'አዳምጠው!' አልኩት ከአክቶበርስኪያ ሆቴል ጀርባ የሚሠማውን የታንክ ቃጠሎና ፍንዳታ እንዲሠማ በመፈለግ ምክንያቱም በተከታታይ በስፍራው ከባድ የፈንጅ ድምፆች ይሰሙ ነበርና፡፡ ከሆቴሉ ትንሽ ሜትሮች አለፍ ብሎ የሚገኘው የዱሻንቤ መስጊድም በእሳት ተያይዞ በነበረበት ጊዜም እንድ የሰቆቃ ድምፅ ይሠማ ነበር፡፡ እናም ይሄ ድምፅ መጀመሪያ ዝግ ያለ ቢሆንም እየቆየ ግን እየበረታና ወደጣር ድምፅ እየተለወጠ የመጣ የሚመስል ነበር፡፡

ለ48 ሰዓታት ያህል እንቅስቃሴ ላይ ስለነበርኩኝ እጅግ ተሰላችቼና ተዳክሜ ነበር፡፡ ከሁሉም ድካሜ ይበልጥ አባብሶት የነበረው ሁኔታ ደግሞ ከኪቭ ወደ ዱሻንቤ የሚሄደውን አውሮፕላን ጥበቃ ወደ ዱሻንቤ አውሮፕላን ማቢያ የተመላለስኩበት ጊዜ ነበር፡፡ ወደ ዱሻንቤ የሚመደበው አውሮፕላን በሰዓት እንደሚነሣ ዘወትር በማስታወቂያ ሲነገር ብሠማም ወደ ማቢያው ስሄድ ግን አውሮፕላኑን አላገኝም፡፡ በዚህ ሁኔታ ለአምስት ቀናት ከተመላለስኩ በኋላ በአምስተኛው ቀን የኤርፖርቱ አስተዳደር ወደ ዱሻንቤ የሚደረገው ጉዞ ከስድስት ወራት በፊት መታገዱን በሃዘኔታ ገለፀልኝ፡፡ ለምን በየቀኑ ወደ አውሮፕላን ማቢያው እንደተመላለስኩ ለማሠብ ጊዜ እንኳን አልነበረኝም፤ ከዚህ ይልቅስ ሁኔታውን ያያያዝኩት ከሶቪዮት ህብረት መውደቅ ጋር ነበር፡፡

ያለ ራሺያ ቪዛ ወደ ፍራንክፈርት ተጓዝኩ፤ ከዚያም በአንድ የአሜሪካ አየር ሃይል አውሮፕላን ወደ ዱሻንቤ በረርኩ፡፡ ፓይለቱ አውሮፕላኑን ዝቅ በማድረግ የታጃኪስታን ተራራዎችን አሌክሳንደር ዘግሬት ወደ አፍጋኒስታን ከመሄድ ይልቅ ከደቡብ ወደ ምስራቅ የተጓዘበትን አቅጣጫ እየተመለከትን ወደ ዱሻንቤ አቀናን፡፡ እናም ረጅሙን ምሽት ከሁለት ታጃኪስታን ጥንዶች ጋር በመሆን ቮድካ እየኮመኮምን አሳለፍነው፡፡ በሚቀጥለው ቀን ግን ጠንከር ያለ ጉንፋን ያዘኝና ተኛሁ፡፡ በሶስተኛው ቀን ግን ልክ ከጧቱ 12፡09 ግድም በክፍሌ መስኮት በኩል የገባው ከፍተኛ የአየር መቃወሚያ ድምፅ ከዕንቅልፌ አነቃኝ፡፡ ይሁንና ከእንቅልፌ እንደነቃሁ የት እንዳለሁ ማስታወስ ሁሉ ተስኖኝ ነበር፤ እየቆየሁ ግን አዕምሮዬን ማሰራት ስጀምር ያለሁበትን አገር አወቅሁት፡፡ አዎ! ያለሁት እጅግ ኃላ ቀር፣ ድሃና ከሌሎች የሶቪዮት ሪፐብሊኮች ብቻዋን ተነጥላ በምትገኘው «ታጂኪስታን» ነበር፡፡

አሊጋዬ ላይም እንደተንጋለልኩ ያለሁበት ቦታ ምን እንዳመጣኝ? እንዴት እንደመጣሁ? በምናብ የኃልዮሽ በማጠንጠን ማስላሰሌን ተያያዝኩት...፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ከፓሪስ ቆይታዬ በኋላም ለሶስት ዓመታት ያህልም በሞሮኮ ቆይቻለሁ፡፡ ትላልቅ ቤቶቿ፣ ፀሃያማ አየር ንብረቷ፣ የጎልፍ መጫወቿና በአትላስ ተራራ ጥግጋት የሚገኘው የሸርተቴ መጫዎቻ ስፍራዎቿ ለእኔ ሞሮኮ የማይረሱ የትዝታ አሻራዋን ነበር ጥላልኝ ያለፈችው፡፡ ስራዬም ቢሆን ጥሩ የነበረ ሲሆን በተሠጠኝ ሀላፊነት ውጤታማ በመሆን ረገድም በሞሮኮ ጥሩ ጊዜን አሣልፌአለሁ ማለት እችላለሁ፡፡ 1 የግል ጉዳዮቼን በተመለከተም ቢሆን ሁሉንም ነገር በድብቅ ነበር የማስኬደው፣ መካከለኛው ምስራቅ በነበርኩበት ወቅት ከአንዲት ቆንጆዬ ጋር ተዋውቄ ትዳር መመስረቴንና ሶስት ልጆች ማፍራታችን የሚያውቁም ጥቂት ሠዎች ነበሩ፡፡ እናም እኔና ቤተሠቤ በአብዛኛው የምንኖረው ተለያይተን ነበር፣ ምክንያቱ ደግሞ እኔን የሚከታተሉኝ ጠላቶቼ በመብዛታቸው ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ሊቢያ ውስጥ እኔን ለመግደል ሴራ የጠነሠሡ ሰዎች መኖራቸውን ካረጋገጥኩ በኋላ ልጆቼንና ሚስቴን ፈረንሳይ ውስጥ በሚገኝ አንድ ስፍራ እንዲኖሩ ጥረት አድርጌ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ግን ሁሉም ነገር ከመሆኑ በፊት ከባለቤቴ ጋር በፍቺ የተለያየሁ ሲሆን እኔም በሚገርም አጋጣሚ ታጂኪስታን ውስጥ ራሴን አገኘቼዋለሁ፡፡

☼☼☼

ዋሽንግተን ውስጥ የሚገኘው ዋና መስሪያ ቤታችን በዙሪያችን እየተካሄደ ስላለው ጦርነት ይሰማ አይሰማ የማውቀው ነገር ስላልነበር ደውዬ ጉዳዩን ማሳወቅ ነበረብኝና ዋሽንግተን ወደሚገኘው የCIA ቢሮ በመደወል ዱሻምቤ ውስጥ የምንገኘውን የCIA ሰዎችና የውጪ ዜጎች ከጦርነት ቀጠናው እንዲያስወጡን ተማፀንኩ፡፡ በተለይም የአየር ሃይሉ ባልደረባ ወደሆነው ማክዲል በመደወል C-141 አውሮፕላንን እንዲልክልን ስንግረው በሁኔታው የመጨረሻ ነው የላቀብኝ፡፡ በጦርነት መሃል ስለምንገኝ ሁኔታው አስደንቆት ይሁን ሌላ በምን ምክንያት እንዳላቀው ግን አልገባኝም ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ አውሮፕላኑ ካለንበት ስፍራ ሊደርስ የሚችለው የአውሮፕላኑን የጉዞ ዋጋ መክፈል ከቻላችሁ ነው የሚለው ዜናው አስደንግጦኝ መላ ጠፍቶብኝ ነበር፡፡ ነገር ግን በአሜሪካ መንግስትና በአየር ኃይሉ መካከል ስምምነት ላይ መድረስ በመቻሉ እና የቅድሚያ ክፍያ በመከፈሉ ከጦርነቱ ቀጠና ውስጥ ልንወጣ የምንችልበት ዕድል እንዳለ አመንኩኝ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በታጂኪስታን የአሜሪካ አምባሣደር የሆነው ስታን ኢስኩን ዶሮ በአካባቢው የሚገኙትን አሜሪካውያንን ሰብስቤ በኤምባሲው ቅጥር እንዳስጠልላቸው አዘዘኝ፡፡ ይህን ማድረግ በርግጥ በጣም አስቸጋሪ ነበር፣ ምክንያቱም የጦርነቱ ሁኔታ የሚፈቅድ ካለመሆኑም ባሻገር እያንዳንዱ አሜሪካዊ የት እንዳለ ማወቅ ስለማይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን በከፍተኛ ጥረት በርካታ ሰዎችን ታጂኪስታን ሆቴል አካባቢ እንዲሠባሠቡና ለበረራው እንዲዘጋጁ ማድረግ ቻልን፡፡

...«የመጣሁት ከአሜሪካ መንግስት እናንተን ለመርዳት ነው፡፡»

በማለት ራሴን በማስተዋወቅ ጀመርኩኝ፡፡ ቀጥዬም ስለተፈጠረው አስቸጋሪ ሁኔታ መዘርዘር ጀመርኩኝ፡፡ የሆነው ሆኖ ከእንዳቸውም ፈገግታን አልተቸርኩም፡፡ ... ለማንኛውም አንድ ጥሩ አንድ መጥፎ ዜናዎች አሉኝ፣ ከጥሩው ዜና ብጀምርላችሁ ... ሁላችንንም የውጭ ዜጎች ከዚህ የጦርነት ቀጠና የሚያስወጣን አውሮፕላን ተዘጋጅቷል፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

ስል ማጉተምተም ጀመሩ፡፡ በመቀጠልም ጉርምርምታቸውን እንዲያቆሙ በእጀ ምልክት በመስጠት መጥፎውን ዜና አረዳኋቸው «እንደሚታወቀው አውሮፕላኑን የሚልከልን የአሜሪካ መንግስት ነው፡፡ ወጭውን የሚሸፍነውም እሱ ሲሆን ከዚህ ሰፍራ በሠላም ከወጣን ሁላችንም የአውሮፕላን ትራንስፓርቱን ወጭ ልንከፍል እንገደዳለን» አልኳቸው፡፡ አብዛኛዎቹም በጥላቻ መንፈስ አፍጥጠው ተመለከቱኝ፡፡ ከእነኚህ መካከልም የኢራን ዲፕሎማቶች ይገኙ የነበሩ ሲሆን ጥቂት ካስተዋሉኝ በኋላ «ለመሆኑ ስምህ ማን ነው?» በማለት ጠየቁኝ፡፡ ጥያቄው ቢያስገርመኝም «ሚስተር ቦብ እባላለሁ» በማለት መለስኩላቸው፡፡ በጣም በሚደንቅ ሁኔታ በዚያች ዕለት ምሽት እንድ የኢራን ሬዲዮ ጣቢያ «ሚስተር ቦብ የተባለ አሜሪካዊ በታጃኪስታን ለሚገኙ ድሃ የውጭ ስደተኞች ሕገወጥ የአውሮፕላን ቲኬት እየቸበቸበ ነው!» የሚል እኔን የሚያሳጣ ዜና ሰማሁኝ፡፡ ጉዞ ከማድረጋችን በፊትም በአካባቢው የሚገኙ መረጃዎቻችን ማጥፋትና ከዱሻንቤ የመልቀቃችን ጉዳይ ለማክዲል ማሳወቅ ግድ ነበረብኝና አደረግሁት፡፡

✡✡✡

በአክራሪዎቹና በዱሻምቤ የቀድሞ ነዋሪዎች መካከል ይደረግ የነበረው ጦርነት በነዋሪዎቹ አሸናፊነት በመጠናቀቁ ሰላም በአካባቢው ሊሰፍን ቻለ፡፡ እኛም የዱሻምቤን ሕይወት ፊት ካቆምንበት ቀጠልን፡፡ ስራችንንም እንዲሁ በጊዜው እኔ የዱሻምቤ የCIA አዛዥ ሆኜ ተሹሜ የነበረ ሲሆን በሚደንቅ ሁኔታ የራሺያ ጦር ሰራዊት አባላትና የKGB (የራሺያ የስለላ ድርጅት) ባለስልጣናት አብረን በአንድ ሆቴል ውስጥ እንኖር ነበር፡፡ ታዲያ ሁኔታው ከራሺያ የKGB ባለስልጣናት ጋር የመቀራረብና የመተዋወቅ ዕድልን ፈጠረልኝ፡፡ ምንም እንኳን የCIA እና የKGB ዓላማ የተራራቀና ተቃራኒ ቢሆንም በአንድ አካባቢ መኖራችን በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች እንድንገናኝ አስገድዶናል፡፡

የ CIA ቢሮ በራሺያ ኤምባሲ ውስጥ በሚገኘው ሠፈ የተንጣለለ ግቢ ከመገኘቱ እንዛርም እንድ ዩሪ አብራሞቪች ካሉ ሰዎች ጋር የመገናኘት ዕድል ሊፈጥርልኝ መቻሉ ግድ ነበር፡፡ ዩሪ እንደኔ የተራራ ላይ የበረዶ ሸርተቴ አፍቃሪ ከመሆኑም በተጨማሪ እጅግ ጎበዝ የፓራሹት ጀብደኛ እንደሆነ ይነገርለታል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዩሪ ወደ ክፍሉ አስጠራኝና ቮድካ ጋበዘኝ፡፡ ለቮድካ መጠጥ እንግዳ ስለሆንኩኝ የመጠጡ ሃይል ወደ እንቅልፍ ማምራቱ የማያስደንቅ ነበርና ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ማንቀላፋቴ ግድ ሆነ፡፡ የሆነው ሆኖ ዩሪ ከእንቅልፌ ቀሥቀሠኝና ለአየር ላይ የፓራሹት ዝላይ ልምምድ መውጣት እንዳለብን ነገረኝ፡፡ እኔም ምንም ሳላቅማማ ተከተልኩት፡፡

የራሺያ ሠራዊት ንብረት በሆኑት AN-2 አውሮፕላኖች እኔ፣ ዩሪና ሌሎች የጦሩ ባልደረቦች ወደ አፍጋኒስታን ድንበር ገሠገስን፡፡ በአፍጋኗ ዋና ከተማ ካቡል ሠማይ ላይም እንገፍበብን፡፡ በአውሮፕላኑ ውስጥ ሠማይ ላይ ሆኜም በሀሳብ የትየለሌ ነገሮችን አወጣሁ፣ አወረድኩ፡፡ በተለይም ከKGB የቅርብ ሰዎች ጋር ለዚያውም በራሺያ የአየር ኃይል ቡድን አባላት ጋር የCIA ዋና ሠው መገኘቱ ደነቀኝ ራሴንም «ምን እየሠራሁ ነው?» ብዬም ጠየኩት፡፡ ከዚህ በፊት በፓራሹት የወረድኩት እንዴ ብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑም ታወቀኝ ድፍረቱም ደነቀኝ፡፡ እነኚህን መሣይ ነገሮች እያውጠነጠንኩ ባለሁበት ሁኔታም ዩሪ የመጀመርያው ወራጅ እኔ መሆኔን ነገረኝ፡፡ «እንግዳችን በመሆንህ የመጀመሪያውን ዝላይ በመዝለል ወደ ምድር የምታመራን አንተ ነህ» አለኝ፡፡ ሁኔታው አስፈሪም አስደሣችም ይመስላል፡፡ ከአውሮፕላኑ ላይ ሆነው ቁልቁል ሲመለከቱ የተንጣለለ የገብስ ማሣ የሚመስለው ጥቅጥቅ ደመና ይታያል፡፡ አየር ላይ ስበር የመጀመርያዬ ቢሆንኖር ያለጥርጥር ደመናው የምድር ገፅ ሲመስለኝ እንደሚችል ገመትኩ፡፡ እናም እንዲህ እያሰብኩኝ የመጨረሻዋ የዝላዩ ሰዓት እየደረሰ መጣ፡፡ ፓራሹቱን እንዲሁም ቀበቶዬን ማጠባበቅ ይጠበቅብኝ ነበርና አጠባበቅኩ፡፡ ዩሪና ሌሎች የራሽያ ሠራዊት አባላት የእኔን እርምጃ ተከትለው አብረውኝ ቁልቁል እንደሚወዘገዘጉ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡

☼☼☼

ከዕለታት አንድ ቀን የክፍሌ በር ተንኳኳ፤ ስከፍተውም አንደ የራሺያ ምልምል ወታደር ነበር፣ ወታደሩም ቆፍጠን ባለ አነጋገር «ኮሎኔል ይፈልጉሀል» ካለኝ በኋላ ከእኔ መልስ ሳይጠብቅ በመጣባት ዕብስ አለ፡፡ ወዲያውኑም ግርማ ሞገሳሙ ኮሎኔል ግሪጎር ጨለማ ከወረሰው አቅጣጫ ድንገት ከቆምኩበት ብቅ አለ፡፡ ግሪጎር በዱሻምቤ ከሚገኙት የራሺያ ኮሎኔሎች መካከል እጅግ ልጅ እግር ነው፡፡ ግሪጎር ወዳለሁበት በመቅረብ «የአሜሪካው ወታደራዊ አታሼ አንተነህ?» ብሎ ጠየቀኝ፡፡ «ወታደራዊ አታሼ ነኝ እንኳን ባልልም ክፍተቱን ግን እሞላለሁ ብዬ አስባለሁ» አልኩት፡፡ «በጣም ጥሩ ... ነገ ልክ ከጠዋቱ 3 ሰዓት አንድ መኪና በርህ ላይ ይጠብቅሃል» ብሎኝ ዙሪያ ገባውን ለአፍታ ቃኝቶ በመጣበት ተመለሰ፡፡

በሚቀጥለው ቀን ኮሎኔሉ በነገረኝ ሰዓት አንዲት የራሺያ ወታደራዊ መኪና ከነሾፌሩ መጣልኝ፡፡ ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላም ከዱሻንቤ አርባ ማይል ከሚገኘው የራሺያ ወታደራዊ ካምፕ ደረስን፡፡ ኮሎኔል ግሪጎርና ባለቤቱን እንዲሁም በርካታ የራሺያ ወታደራዊ መሪዎች እስከሚስቶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው አገኘኋቸው እኔም ይሄኔ ነው ፓርቲ መሆኑ የገባኝ፡፡ ቀስ በቀስም እየለመድኩት የመጣሁትን ቮድካም መጨለጥ ጀመርኩ፡፡ ሴቶቹ ምግቡን ለማበሳሰል ጉድጉድ በሚሉበት ሰዓት እኛ ደግሞ ቮድካችንን እየጨለጥን በባህር ስላጠለው ጂብዱ ስለፈፀሙት እንደ ጀኔራል ኖርማን ሸዋርክዝፍ ስላሉ ሰዎች እናወጋ ነበር፡፡

ሁሉም ነገር ሞቅ ሞቅ እያለ ሲመጣና የጨዋታው አውድም እየደራ ሲመጣ ሁለቱ ራሺያውያን ሁለት ድምፅ አልባ ሽጉጦቻቸውን አውጥተው ማሣየት የሚፈልጉትን ነገር ለማሳየት ተዘጋጁ፡፡ አንዱ ሽጉጥ ለየት ያለ ይሁን እንጅ ያው ሽጉጥ ነው የሚመስለው፡፡ የአንደኛው ግን ፍፁም እስክርቢቶ ነበር የሚመስለው፡፡ ሽጉጦቹን አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ሁለቱም ድምፅ አልባ መሆናቸውና ራሺያውያኑ የሚጠቀሙባቸው የቫሃቢስ ወይም ዋሃቢስ ቡድን አክራሪዎችን የሚገድሉበት መሆኑ ነው፡፡ ቫሃቢስ የሚለው ስያሜ ደግሞ የእስላም አክራሪዎችን የሚወክል ስም ሲሆን በ 18ኛው ክፍለ ዘመን መሃመድ ኢብን አብዱል ዋሃብ ከተባሉ የእስልምና ተሃድሶ መሪ የተወሰደ ስም ነው፡፡ መሃመድ ዋሃብ በሳኡዲ አረቢያ በእስልምና ተሃድሶ ወቅት እጅግ ጠንካራ የዕምነት ህግጋትን በመደንገግ የታወቁ ሰው ሲሆኑ የእርሳቸውን ስም ይዞ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚንቀሣቀሰው የቫሃቢስ (ዋሃቢስ) ፓርቲም የእርሳቸውን አቋም በመያዝ በአለም ዙሪያ ይንቀሣቀሣል፡፡ እናም እነኚህ ራሺያውያን ካፕቴኖች የያዟቸው ድምፅ አልባ ሽጉጦችም በታጃኪስታን ውስጥ የሚኖሩ የዋሃቢስ አባሎችን ለመግደል የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ከሁለቱ ካፒቴኖች አንዱ አስክርቢቶ የምትመስለውን ሽጉጥ በመፈታታት ለመፈንዳት ዝግጁ እንድትሆን ካደረጋት በኃላ ዋሃቢሶችን እንዴት ሲጥ እንደምናደርጋቸው ላሣያችሁ ፈልጌ ነው አለና ከእኛ ማዶ ከሚገኘው ኩሬ ውስጥ ወረወራት፡፡ በሚገርም ሁኔታ ከመጠነኛ ጭስ በስተቀር ድምፅ አልነበራትም፡፡ እኔም እስከአሁን ካየኃቸው ድምፅ አልባ መሣሪያዎችም ይህቺኛዋ በጣም አስገራሚ እንደሆነች ገመትኩ፡፡

ጥቂት ከተጨዋወትን በኋላ ሁለት ማይሎች ያህል ርቀት ወዳለው ወታደራዊ ሬንጅ መሄድ ነበረብንና ከራሺያ ሰራቶች ከሆኑ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎቻቸው ጋር ለመተዋወቅ ዕድሉን አስፋልኝ፡፡ በስፍራውም እጅግ የተደራጀ ወታደራዊ ማሰልጠኛ በመሆኑ የተኩስ ልምምድ አደረግን፡፡

☼☼☼

ግሪጎር ስለሆኔታው ጠየቀኝ፡፡ በጣም መደሰቴን ከነገርኩት በኃላ በሚቀጥለው ሳምንት ደግሞ T-72 ታንክን ይዘን የመንዳት ልምምድ ለማድረግ እንድዘጋጅ በጥያቄ ስሜት ነገረኝ፡፡

እንደዕውነቱ ከሆነ በሕይወቴ ታንክ አሽከርክሬ አላውቅም፡፡ እንኳንስ የራሺያ ታንክ ይቅርና የአሜሪካንን ታንክ ነድቼ አላውቅም፡፡ ሁኔታው ትንሽ ቢያስፈራኝም አልችልም ማለት ስለከበደኝ ብቻ በድፍረት በታንኩ መሪ ላይ ተደላድዬ ተቀመጥኩ፡፡ ግሪጎር በተመስጦ ይመለከተኝ ስለነበር የእኔም ጉጉት ጨመረ እኔም በሚገርም ሆኔታም ታንኩን በሚገባ ሁኔታ ነዳሁት፡፡ ጥቂት ከተንቀሳቀስኩ በኋላም የታንክ ተኩስ ልምምድ ማድረግ ቻልኩኝ፡፡ ኮሎኔል ግሪጎር እጅጉን ነበር የኮራብኝ፡፡ የሆነው ሆኖ የእኔን ከራሺያ የምድር ጦር አባላት መላመድ የተመለከቱ የቀድሞዋ ሶቪየት ዋና ባለስልጣናት በፓራሹት መውረድን እንደከለከሉት ሁሉ በተለይም እኔ በተሣተፍኩበት ሁኔታ የትኛውም ዓይነት የታንክ ልምምድ እንዳይደረግ አገዱ፡፡ ሁኔታው ቢያሣዝነኝም የኮሎኔል ግሪጎርን ማዕናኛ ማግኘቴ ግን አስደስቶኝ ነበር፡፡ ኮሎኔሉ የራሺያን ጨለማ ጎን በብርሀን ሊያሳየኝ ሳይወስንም አልቀረም ነበር፡፡

☼☼☼

ግሪጎሬ ሃገሬን የሚያስደስት ነገር እንደሚያሳየኝ እየነገረኝ ነበር፡፡ ማታ ከ11 ሰዓት በኃላ ወደ አየር ማረፊያው አቀናን፡፡

Mi - 8 እና Mi - 24 ሄሊኮፕተሮች እንዲሁም ሌሎች አውሮፕላኖች በየጥጋው ውስጥ ጥላቸው ይታይ ነበር፡፡ ከ IL -76 ካርጎ አውሮፕላኑ 100 ሜማ ያህል ርቀን ድምፅ ሳናሰማ ቁጭ አልን፡፡ ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኃላም የ IL -76 አውሮፕላን



t.me/OLDBOOKSPDF

መብራቶች በሩ፡፡ አንድ ወታደርም ከአውሮፕላኑ አቅራቢያ ሆኖ የመብራቱን አቅጣጫ በዝግታ ዙሪያ ገባውን ለቁጥጥር ያህል አዞረው፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ደግሞ አንዲት Mi-8 ሄሊኮፕተር መጥታ ከIL-76 ጎን አረፈች በመቀጠልም አንድ ሠው ከሄሊኮፕተሯ ላይ ቆሞ ትላልቅ ሻንጣዎችን በIL-76 ካርጎ ከውሮፕላኑ በር በኩል ይወረውራል፡፡ ከ10 ደቂቃ በኋላም ይህ ትዕይንት ተጠናቆ ሄሊኮፕተሯ ተነስታ አፍጋኒስታን አቅጣጫ አመራች፡፡ IL-76 ከርጎ አውሮፕላኑም ብዙም ሳይቆይ ሞተሮቹን አስነስቶ በረረ፡፡

«ሄሮይን» አለኝ ግሪጎር ወደ እኔ በመዞር፡፡ «ይህ ከሳምንታዊ ፕሮግራሞች አንዱ ነው» በማለትም አከለ፡፡ ከዚያም ታሪኩን ሁሉ በዝርዝር ይነግረኝ ጀመር ያኩብ ሳልምቭ የታጂኪስታን የሃገር ውስጥ ሚኒንስትር ሲሆኑ ከራሺያ ጥቂት ጀኔራሎች ጋር በመሆን ጥሬ አፒዮም በራሺያ ወታደራዊ አውሮፕላኖች ከአፍጋኒስታን ወደ ሞስኮ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በዚህ ባየኸው መልኩ ያጓጉዛሉ፡፡ አፒየሙ ሞስኮ ከደረሠ በኋላም በድብቅ ከተዘጋጀ የሞስኮ ላብራቶሪዎች እጋዥነት ወደ ሄሮይን ተለውጦ በጀልባ ወደ ስዊድን ይሄዳል ከዚያም አሜሪካን ለጥቆም ወደ መላው ዓለም ይሠራጫል ማለት ነው፡፡ ይህንን ታሪክ ለአሜሪካው አምባሰደር ኤስኩዴሮ ነገርኩት፡፡ በጣም ተገርሞ ጉዳዩን ለውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ሳሊሞቭ እንደሚነግረው ገለፁልኝ፡፡

ሳሊሞቭ ከፖለቲካ ስውነቱ ይልቅ ጡንቸኝነቱ የሚያመዝን ሠው ነው፡፡ በዱሻንቤ እርሻ ኮሌጅ የቦክስ ስፖርት መምህር የነበረ ሲሆን የአንድ የወንጀለኛ ቡድን አባል ሆኖ ሠውን ከሠው ያስተራርድ የነበረ ወሮበላ የነበረ ሰው ነው፡፡ በታጂኪስታን ፓለቲካ ውስጥ ከታጂኪስታን ከተባረረውና ከጦርነቱ በኋላ ስልጣን ላይ መውጣት ከቻለው ቡድን ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበረውም የታጂኪስተን የሃገር ሚኒስቴር ሆኖ ለመመረጥ አልተቸገረም ነበር፡፡ እኔና አምባሣደራችን ኤስኩዴሮ ከሳሊሞቭ አጠገብ ስንደርስ ስለጉዳዩ መጀመሪያ ማውራት እንዳለብኝ ኤስኩዴሮን አሳመንኩት፡፡

ጉዳዩን በተመለከተም ለሳሊሞቭ በዝርዝር አስረዳው ገባሁ፡፡ ታጂኪስታን በሄሮይን የንግድ እንቅስቃሴ እየተሣተፈች ከሆነች አሜሪካ ልትታገሣት እንደማትችል አስረዳሁት፡፡ ሳሊሞቭ ከሙዝ የማይተናነስ ግዝፈት ያለው እስክርቢቶ በጣቶቹ መሃል እያሽከረከረ ድንጋጤና አግራሞት በተቀላቀለበት ስሜት ያደምጠኛል፡፡ ኤስኩዴሮ ደግሞ በተመስጦ ይመለከተኛል የእኔ ንግግርም ቢያንስ አስር ደቂቃ ያህል ወሰደ፡፡

ከሁለት ሳምንታት በኋላም ሳሊሞቭ መልሡን መለሠልኝ፡፡ በጊዜው ስቴፈን ቤንቹራ ከተባለ በሞስኮ የሚገኝ የፈረንሳይ ፕሬስ ባልደረባ ጋር በቢሮዬ እያወራን ነበረ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ከባድ ፍንዳታ ሰማን፡፡ በእርግጥ ሰዓቱ እንዲህ ዓይነት ፍንዳታ የማይጠበቅበት ከመሆኑ አንፃር ትንሽ ከተደነቅን በኋላ ወሬያችንን ቀጠልን፡፡ ወዲያው ደግሞ የኢምባሲው አስተዳደር ቢሮዬን በርግዶ በመግባት «ቤትህን አጋዩት!» አለኝ፡፡ ቤቱን ከተከራየሁት አንድ ወር ቢሆነኝ ነው፡፡ አንዳንድ ምስጢራዊ የሆኑ የግል ጉዳዮችን በተመለከተ ከሠዎች ጋር ለመገናኘት እጠቀምበታለሁ፡፡ አካባቢው ፀጥ ያለ ስለሆነም ይስማማኛል፡፡ አንድ የአይን ምስክር እንደገለፀው ከሆነ ከቤቱ ባሻገር የተወሠኑ የፖሊስ መኪኖች ቆመው ሁኔታውን ሲከታተሉ የቆዩ ሲሆን አንድ ግለሠብም ወደ ቤቱ የመስኮት



t.me/OLDBOOKSPDF

አቅጣጫ በመሄድ ሁኔታዎችን እጥንቶ እንደተመለሠ ተናግሮ ነበር፡፡ ጉዳዩን ለኮሌኔል ግሪጎር ስነግረው፤ «የእኔ T-72 ታንክ ተጠቅመህ የሳሊሞቭን ቤት አጋየው» አለኝ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ራሺያ በከባድ ሙስና ከመውደቋ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እየመረመርኩ ባለበት ሁኔታ ግሪጎር አንድ ዕለት ወደ ዱሻንቤ ወሠደኝና ከራሺያ የምድር ሃይል ሠራዊት ኮማንደር ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ ሶስታችን እራት እየበላን ባለበት ሁኔታ ኮማንደሩ «በወር አንዴ ብቅ የምትል የCIA C-130 አውሮፕላን እንዳለች አውቃለሁ» አለኝ፡፡ እውነቱን መሆኑን አረጋገጥኩለት፡፡ ቀጠለናም 'ታዲያ ለምን አንድ ቢዝነስ አንሰራም?' በማለት ተናገር፡፡ «ሲጋራ እያሸኩኝ እዚህ ለሚገኙ ወታደሮች እኔ እሸጣለሁ፡፡ ትርፉንም ሃምሳ -ሃምሳ እንካፈላለን» አለኝ፡፡

በሁኔታዎች ሁሉ በጣም ተደነቅኩ፡፡ ማንኛውም እዚህ የሚገኝ ሰው በራሡ የሚተማመን ጠንካራ ካልሆነ ከየትኛውም የማፊያና የወንጀለኛ እንዲሁም ዕፅ አዘዋዋሪዎች አባል መሆኑ የማይቀር መሆኑ ተሰማኝ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ቡድን ውስጥ እንዲገቡ የሚገፋፋ ሰዎች ደግሞ ትላልቅ ስልጣን ያላቸው ሰዎች መሆናቸው ያስገርማል፡፡ አንዳንዶቹማ የተሠረቀ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ለማሸጥም የማያቅማሙ ናቸው፡፡

ወዲያውኑ ግሪጎር ዋሽንግተን መነሳቱን የማትፈልገውን የራሺያን ብሔርተኝነት ጉዳይ አንስቶ ማውራት ጀመረ፡፡

ግርጉር ራሱን ተራማጅ የራሺያ ብሄርተኛ አድርጎ ቢገልፅም እውነታው ግን የራሺያ ብሄርተኛ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ ራሺያ ራሷን በሙስና ከተዘፈቁ ፖለቲከኞቿ፣ በአደንዛዥ ዕፅሱስ ከናወዙ ጀኔራሎቿ ለማፅዳት ታላቁን የጥቅምት አብዮት የመሰለ አብዮት ያስፈልጋታል ብሎም ያምናል፡፡

አንድ ምሽት ሳጥን ሙሉ የጀርመን ቢራ ይዤ ቤቱ ሄድኩ፡፡ ግሪጎር ቮድካ መጠጣት ቢወድም ቢራው ልዩ ጣዕም ስለነበረው ከቢራው መጐንጨት ጀምሯል፡፡ ሳጥኑ ቢራ እንደተጋመሰም በሞቅታ መንፈስ ቦሪስ የልሲን በ1993 ከሞስኮው ኃይት ሃውስ ላይ ለመፈፀም ስላሰቡት ጥቃት ማውራት ጀመረ ጥቃቱ የሩሲያ ሰራዊትን እንዳልነበረ ለማረግ የተቃረበ እንደነበርም ተናገረ፡፡ ታማንስካያ የተባለው ክፍለጦር በኃይት ሃውሱ ላይ ጥቃት እንዲፈፅም ቢታዘዝም በአንድ ግለሰብ ስር ያሉ የጦሩ አባላት ጥቃቱን ለመፈፀም አሻፈረኝ በማለት ታንኮቻቸውን ለማንቀሳቀስ ሳይፈቅዱ ቀሩ፡፡ በአጭሩ ሰዎቹ አመፁ፡፡ በዚህም ምክንያት በጥቃቱ ለመሳተፍ አስበው የነበሩት የጦር አዛዦች ሁሉ ከሰራዊቱ ተባረሩ፡፡ ከህብረተሰቡም ተገለሉ፡፡ ማግኘት የሚገባቸውን የደረጃ እድገትም ሳያገኙ በመቅረታቸውም በሃፍረት ራሳቸውን ከስራ አሰናበቱ፡፡ «የልሲን ሰራዊቱን ከፋፍለውታል» በማለት ግሪጎር በረዥሙ ተነፈሰ፡፡

ከሳምንት በኃላ ወደቤቱ ተመልሼ ስሄድ ግሪጎርን በሞቅታ መንፈስ ሆኖ አገኘሁት፡፡ ለመቀመጥ ስዘጋጅ «መኪናዋን ይዞን እንውጣ» አለኝ መኪናውም ከአፓርትመንቱ ፊት ለፊት የቆመች ቢሆንም ሾፌሩ ዕረፍት ላይ ስለነበር ራሱ መሾፈሩን መርጦአል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ሸፈረ፡፡ «የራሺያ ጦርአዛዦች የሞስኮን ቧልት ማስቆም ቢችሉ ማለቴ የልሲንን ቢያስወግዱ ዋሽንግተን ምን ትል ይሆን?»

ግሪጐርን ተመለከትኩት፡፡ የተናገረው ከልቡ ይመስላል፡፡ ግሪጐር ለአንድ ሙሉ ደቂቃ በፀጥታ ተውጦ ቆየና «ስማኝኝ ሚ/ር ቦብ እኔና ጥቂት የጦሩ አዛዦች ሁኔታውን እንስተን ተነጋግረንበታል፡፡ ሁላችንም አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለነው የሞስኮው አዛዦቻችን ሌላው ቀርቶ ጉብኝተውት በማያውቁት የሩሲያ ጠረፍ ነው፡፡ እኛ ባንኖር ኖሮ እንደነሱማ ከሆነ ሩሲያ ገና ድሮ በተንኮታኮተችም ነበር፡፡ ለነሱ ቁምነገራቸው ያገሪቷን ገንዘብ ወደፊት ሲኖሩ ላቀዱት ኑሮ ወደደቡብ ፈረንሳይ ማሸሻቸው ነው፡፡ አታምነኝ ይሆናል በመጨረሻ ዙር ሁሌም የሚደርሰን የጥይት እሽግ ባዶ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለታንኮቹ የሚሆኑ መገናኛ ራዲዮኖች ማግኘት አልችልም፡፡ ዲቃሎቹ ራዲዮኖቹን ለኛ በመላክ ፋንታ ተልከስክሰው ለሞስኮ ታክስ ኩባንያዎች ይሸጡላቸዋል፡፡ ራሃባችንንም የምናስታግሰው በጓሮአችን ፍሬዎች ነበር፡፡ ባጠቃላይ ሰዎቹ ታላቅ የአገር ክህደት ወንጀል ፈፅመዋል፡፡»

«ግሪጐርን እኛ ስትል ማንን ማለትህ ነው?» ስል ጠየቅኩት፡፡

«አሃ! እንደኔ የሚያስቡትን በመቶዎች ሚቆጠሩ የጦር አዛዦችን ማለቴ ነዋ!! ሁላችንም በግንባር ተሰልፈናል የጦሩን አስር በመቶ እንሆናለን ተዋጊዎቹ ግን እኛው ነን፡፡»

«መሪ አላቹሀ?»

«ይህንን ጉዳይ በበላይነት መምራት የሚችለው አሌክሳንደር ሌቤድ ብቻ ነው፡፡ ቢሆንም ሁኔታውን አላነሳንበትም አሁን ሁኔታው የሚነሳበት ጊዜ አይደለም፡፡»

ሩሲያ አሉዋት ከሚባሉት ጀኔራሎች ስመጥር የሆነው ጀኔራል ሌቤድ ሞልዶቫ የ17ኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ነው ከሁሉም ከቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ክፍለ ጦሮች የተውጣጡ ወታደሮች የተደራጀውን የጄኔራል ሌቢድ ጦር ተቀላቅለዋል፡፡ ይህም የተቀሩትን ክፍለ ጦሮች ማግኘት ካለባቸው የሰው ሃይል በ2 ሶስተኛ ባነሰ የሰው ኃይል እንዲንቀሳቀሱ አርጓቸዋል፡፡

«ሌላ ሰው የለም ነው የምትለኝ? »

«የለም መኮንኖች ማሠልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የሚሰራ ሁላችንንም የሚያውቀን አንድ ጄኔራል አለ ጄኔራል-ይባላል፡፡ ሆኖም ሚ/ር ቦብ ብዙ ጥያቄዎችን ጠይቀሸኛል አሁን ደግሞ እድሉን ስጠኝና አንድ ጥያቄ እንድጠይቅህ ፍቀድልኝ በየልሲን መንግስት ላይ መፈንቅለ መንግስት ብናካሂድ ዩናይትድ ስቴትስ እንዴት ትመለከተዋለች?»

ግሪጐር ሃሳቡን ለመተግበር ፈቃድ እየጠየቀ አልነበረም፡፡ የነገረኝን ሃሳብ ለመምሪያ ፅህፈት ቤቱ ባሳወቅኩ ጊዜም ለግሪጐር እንድነግር የተላኩልኝ መልዕክቶች አስቸኳይ ነበሩ፡፡ መልዕክቶቹም መፈንቅለ መንግስት መካሄድ እንደሌለበት ይገልፃሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀሽንግተን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠውን መንግስት መደገፉን እንደምትቀጥል ይናገራሉ፡፡ ምላሹም የጠበቅኩት ነበር እኔም ጥና መምሪያው ግሪጎርን ማግኘቴን እንድቀጥል ስለፈቀደልኝም ተደስቻለሁ፡፡

ቢሆንም ውለታ ለውለለት ሞክሬአለሁ አንድ ጊዜ በተመሳሳይ መልኩ ስንገናኝ ስለሞቶሮላ የመገናኛ መሳሪያዎች የሚገልፁ በራሪ ወረቀቶች አሳይቶኛል፡፡ ቢሆንም መሳሪያዎቹን የት እንደሚያገኛቸው ለጠቁመው አልቻልኩም በመገናኛ ዘዴዎች አቅርቦት የሚያዘውን ክፍለ ጦር መደገፍ እችል እንደሆነም ጠይቆኛል ለጥያቄውም ከዋናው መምሪያ ያገኘሁት ምላሽም አለወትሮው አጭር ነበር «ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ» የሚል ምላሽ፡፡

ግሪጎር ሩሲያ ተሃድሶ ያስፈልጋታል ብሎ የነገረኝን ነገር መቼስ አሁን ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል ያውቀዋል፤ ይሁንና ነገሩን በጥልቀት መመልከት እችል ዘንድ ወደ ፓሚርስ መሄዴን ፈልጐታል፡፡ ጥቂት የአሜሪካ ኤምባሲ ሰራተኞች የፓሚርስ መናገሻ የሆነችው ኮሮግን በሄሊኮፕተር ከመጐብኘታቸው ባለፈ ወደኮሮግ በመኪና ለጉብኝት የሄደ የአሜሪካ ልዑካን ኖሮ «አያውቅም የወደፊቷን ራሺያ ማየት ከፈለግክ የታጃኪስታንን ድንበር ተከትለህ መንዳት ይኖርብሃል» ሲል ግሪጎር ተናገረ «ሐዚያም በህይወትህ ዓይተህ የማታውቀው ሲያል የሆነ ምድር እዚያ ታያለህ» አለኝ፡፡

ግሪጎር ምን ሊለኝ እንደፈለገ መገመት አላቃተኝም ነበር፡፡ የታጃኪስታን ሶስት ሩብ ቆዳ ስፋትን የሸፈነችው ፓሚርስ በአለም ካሉ ስፍራዎች ሁሉ ስርዓት አልበኝነት የነገሰባት ስፍራ ናት ፓሚርስ በእስላማዊ ደፈጣ ተዋጊዎች የጦር አበጋዞች፣ ሽፍቶች፣ ኮንትሮባንድ ነጋዴዎችንና በራሺያውያን ዘላኖች የምትተዳደር ሃገር ነች፡፡ እናም በዛች ሃገር ብቸኛው የመተዳደሪያ ገቢ ጦር ማሣሪያና ናርኮቲክ ማቀባበልና መሸጥ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ታዲያ የኢራት ፓስድራን ፓሚርስ ውስጥ መሸሸጊያ ማግኘቱ አያስገርምም ቡድኑ ከድንበር ባሻገር ባለችውና አፍጋኒስታን ውስጥ ከምትገኘው ታሎካን የጦር ሰፈሩን ገንብቷል ያም በመካከለኛው እስያ አለመረጋጋትን መፍጠር ያስችለዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ አሜሪካ ሰራሾቹን ስቲንገር ተወንጫፊ ሚሳይሎች እስከመግዛት ደርሷል፡፡ የሚሳይሎቹን አፈሙዝም የታጂክ አከራሪዎች ላይ ደግኗል፡፡ ሩሲያኖችም ድንበሩን ተከትለው በርካታ የጦር ሰፈሮችን አቋቁመዋል፡፡ ያ ማለት ግን በተቀናቃኞቻቸው ላይ የፈጠረው ተፅዕኖ አልነበረ፡፡

አደገኛነቱን ባውቅም ፓሚርስ ውስጥ ለማላለፍ እንድወስን ያረገኝ የራሴ ምክኒያት ነበረኝ ዱሻንቤ ከደረስኩበት ጊዜ አንስቶ በከፍተኞቹ ተራሮች መሃል ባሉት ሸለቆዎች ስላለው የጥንታዊ ስልጣኔ ቅሬታ ሲወራልኝ ሰንበቷል፡፡ ከሸለቆው ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የታላቁን እስክንድር ሚስት የሆንችው ሮዛኔን ያስገኘው ጥንታዊውን የሳማርካንድ መንግስት ዝርያዎች መሆናቸው ተተርኮልኛል፡፡ እናም ሰዎቹ ዛሬ የራሳቸውን መጠሪያ ያግኖቢስ ያረጉ ቢሆንም ላለፉት 25 መቶ ዓመታት በቋንቋቸው ላይ ይሄ ነው የሚባል ለውጥ አልተከሰተም፡፡ ቋንቋቸው የኢራን ቋንቋ ዝርያ ካለውና የሂንዱ አውሮፓውያን ቋንቋ ከሆነው ሶግዲያን ጋር ይቀራረባል፡፡ ያግኖቢሶቹ ዛሬም አኗኗራቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደጥንቱ ነው፡፡ ኤሌትሪክ አይጠቀሙም፡፡ የቧንቧ ውሃም የላቸውም፡፡ የሚወራው እውነት ከሆነም ያግኖቢሶቹ ወደቀድሞው ዕሳት አምልኮአቸው ተመልሰዋል፡፡

ጆሴፍ ስታሊን የነዚህን ህዝቦች ባህል ለማጥፋት ፋይዳ ቢስ ሙከራ አድርጎ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ማለትም ወደ መላው ሶቭየት ግዛት በታትኖአቸው ነበርና፡፡ እናም ቀደም ብሎ የተከሰተውን የአገዛዙን መውደቅ ተከትሎ በሁለተኛው አለም ጦርነት የአ.ኤስ ሰራተኛ የነበሩትና የሃርቫርዱ ፕሮፌሰር ኢራናዊው ተመራማሪ ሪቻርድ ፍራይ ወደኢግኖብ በመጉዋዝ የመጀመሪያው አሜሪካዊ ሆነዋል፡፡ በቀጣዩ ዓመትም በስፍራው የፈነዳው የእርስ በእርስ ግጭት ደግሞ ወደስፍራው መጉዋዝን አስቸጋሪ አርጎታል፡፡ እናም እኔ ወደዚያው በማቅናቴ ጥንታዊውን የሳማርካንድ መንግስት ከጐበኙት ጥቂት አሜሪካውያን መካከል አንዱ ሆኜያለሁ ማለት ነው፡፡ የሸፈንኩትም ጉዞ ፓሚርስን፣ ታጃኪስታን ከአፍጋኒስታንና ቻይና ጋር የሚያዋስናትን ድንበር እንዲሁም የጋርምና የያግኖስን ሸለቆ ያካትታል፡፡ በጉዞም ላይ ፈታኝና ብዙ ስንክሳሮች ገጥመውኝ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታዬ ነበር፡፡

☼☼☼

ላለፉት ሁለት አመታት የቧንቧ ውሃ ሳላይ አሳልፌአለሁ፣ በጭቃ ስኳትን ከርሜአለሁ፣ ከቀለጠ በረዶ በሚወርድ ውሃ ታጥቤአለሁ፣ በወታደራዊ ራሽን ኑሮን ኑሬያታለሁ አሁን ግን የታጃኪስታኑ ኑሮ አንገሽግሾኝ በቃኝ ከምልበት ደረጃ ደርሼአለሁ፡፡ የኖርኩትን ኑሮ ሌላው ተተኪዬ የሚኖርበት ጊዜ ደርሷል ብዬ አስባለሁ፡፡ እናም በወርሃ ጥር ዋና መምሪያው ተተኪዬን ወዳለሁበት እንዲልክልኝ መጨቅጨቁን ስራዬ በማድረግ መማጠን ገባሁ፡፡ ይሁንና ለጥያቄዬ ምላሽ ሳላገኝ ሁለት ወራት ከባከኑ በኋላ ለምሰራበት ምድብ ስራተኛ ጉዳይ አስፈፃሚ ቢሮ ደወልኩኝ አለመታደል ሆኖ በምላሹም ከይቅርታ ጋር እኔን እንዲተካ የታሰበው የሩሲያ ቋንቋ ተናጋሪ ሰው ወደጦር ትምህርት ቤት ሊላክ መሆኑ ተነገረኝ ምንም እንኳን ተተኪዬን በቶሎ ሊልኩልኝ እንደሚችሉ ቢያባብሉኝም ተተኪ የተባለው ሰውዬ ግን የመካከለኛ አስተዳደር ስልጠና ስለነበረው እኔን መተካት ሳይችል ቀረ፡፡ በሶስተኛ አማራጭነት የታጨው ሰውዬ ያቀረበው ሰበብም ከግምት የሚገባ አልነበረም፡፡ ማለትም ሰውየው ዱሻንቤን «ለግዳጅ የሚያበቃ ቦታ አይደለችም» በሚል ሰንካላ ሰበብ ከምድቡ የቀረበለትን ጥያቄ ውድቅ አርጎታል፡፡ ዋና መምሪያውም ተተኪዬን ማግኘቱን እስኪያበስረኝ ጊዜም ራሴን ሙት አርጌ ቆጥሬዋለሁ፡፡ ለዘላለም ሲእል በሆነችው ዱሻንቤ የምቆይ አርግጌ አስቤዋለሁ፡፡ የኋላ የኋላ ግን ተተኪዬ የተገኘልኝ መሆኑ ቢያስደስተኝም ቅሉ ደስታዬ ከኔ ጋር የቆየው የሰውየውን ግለ ታሪክ ማንበብ እስከጀምር ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር፡፡ ሰውየው ቀደም ሲል በጦር አዛዥነት አገልግሏል፡፡ ሩሲያኛም ሆነ የታጂክ ቋንቋን መናገር የማይችል ከመሆኑም በላይ ስላይ መልምሎም ሆነ በስሩ አንድም ሰላይ አስተዳድሮ አያውቅም፡፡ ነገሩ ሁሉ እንደ የመረጃ ተንታኝ ሰራተኛ እኔን እንዲተካ የመላክ ያህል አደገኛ ሆኖ ታየኝ፡፡ ሰውየው ሊያውቅ የሚችለው ብቸኛ ነገር ቢኖር የቦምብ ማፈኛን እንደምን መንቀል እንዳለበት ብቻ ሆኖም ታሰበኝ፡፡ ይሄም ዕውቀቱ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ዋና መምሪያው ዱሻንቤ ያለው ቢሮአችንን ወደ ታሺልዳራ ካዛወረው ብቻ ይሆናል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

CIA ውስጥ ቆይታ ባረኩባቸው በነዚያ ሁሉ አመታት ይሄን ያህል ድንጋጤ ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡ CIA ከሩሲያ ጦር ያሰረገው ሰላይ የለውም፡፡ ታጃኪስታን ውስጥ አንድ ሰላይ የሚመስምልለትን ሰራተኛውን ወደዛው ስለመላኩ ጊዜ ወስዶ አላሰበበትም፡፡ ተተኪዬም እንግሊዝኛ ከማይችለው ግሪጎሪ ጋር መነጋገር አለመቻሉ አላስጨነቀውም CIA ዕውነታው ሩሲያ በማንኛውም ጊዜ በኒውክሊር አረር ተሸካሚ ሚሳይሎቿ የዩናይትድ ስቴትን ግዛት ላይ ጥቃት መፈፀም መቻሏ ሆኖ ሳለ ስለሩስያ የውትድርና እንቅስቃሴ የቀረቡለትን መረጃ አጣጥሏቸዋል፡፡

ለነገሩ ሊያስገርመኝ አይገባም ነበር ምክንያቱም ከዚህ በፊት አፍጋኒስታን ውስጥ የፈነዳውን የእርስበርስ ጦርነት ተከትሎ ድንበር ማቋረጥ ስለጀመረው የስደተኛ ጐርፍ የበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት አለቆቼ አፍጋኒስታን ውስጥ በስፋት የሚነገሩትን የዳሪና የፓሽቱን ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ሰው እንዲልኩልኝ ብጠይቅም ምላሽ አላገኘሁም ነበር፡፡ ይሁንና ምላሽ ባገኝ ኖሮ ስደተኞቹ ተዝቆ የማያልቅ ወርቃማ የመረጃ ምንጭ ሆነው ይሁንና ምላሽ ባገኝ ኖሮ — 

ባገለገሉም ነበር፡፡ ማለትም ከመሃላቸው አንዳንዶቹን መልምለንና አሰልጥነን ወደ አፍጋኒስታን ተመልሰው መረጃን እንዲቃርሙ ባደረግናቸውም ነበር፡፡ ይሁንና በዛ ፋንታ የተሰጠኝ ምላሽ የነዚህን ቋንቋ ተናጋሪዎች የትም ማግኘት እንደምችል ነበር፡፡ CIA ስለአፍጋኒስታን ከእንግዲህ መረጃ የመሰብሰብ ፍላጎት እንደሌለው እንዳውቅ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የጠቀስኳቸው ቋንቋዎች አላስፈላጊነት ተገልፆልኛል፡፡ በዚያ ፈንታ ዋና መምሪያው በቦታው ስለሚፈፀሙ የታዋቂ ጥቃቶች ማብራሪያ የሚያፈላልግ አራት አባላት ያሉት ቡድን ወደስፍራው እንደሚልክ አሳውቆኛል፡፡ ቡድኑን የማልቀበለው መሆኔን መግለጼም በስሜ ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ያለፉ ክስተት ሆኗል፡፡

እናም እኔ CIA'ን የሚያሳስበው ከቶውኑ ምንድን ነው? የሚለውን ሃሳብ በአዕምሮዬ ጓዳ ማብላላት ባለሁበት በዚያች ቅፅበት አንድ ቴሌግራም ደረሰኝ ቴሌግራሙም የሴኔቱ ውጭ ግንኙነቶች ኮሚቴ ሊቀመንበር የሆኑት ክሌይቦርን ፔል ከኔ ጋር ለመወያየት ወደታጂክስታን በመጓዋዝ ላይ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ያሰብኩት ተሳካ ስል ለራሴ ተናገርኩ ፔል የቀድሞ ውጭ ጉዳይ ሰራተኛ የነበረና በተጨማሪም በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅትም ወታደር የነበረ በመሆኑ ስለሩሲያ ጦር የምንነግረውን እንደሚሰማኝ ርግጠኛ ነበርኩ፡፡

እናም ከመድረሱ ቀደም ባሉት ቀናቶች ሃሳቦቼን በካርዶች ላይ አሰፈርኩ፡፡ የሩሲያ አዛዦች የልሲን ላይ መፈንቅለ መንግስት ለመፈፀም ማቀዳቸውን ልንገረው ፈልጌአለሁ፡፡ ደግሞስ ሊፈፀም ስለሚችል መፈንቅለ መንግስት ለመስማት የማይጓጓበት ምክንያት ይኖራልን? ወደዋናው መምሪያ ሲመለስም የሚተካኝን ሰው አስፈላጊነት ለአለቆቼ በደንብ ይነግራቸዋል፡፡ በዱንሻንቤ ወዳለው ቢሮአችን እኔን ተክቶ ከግሪጐር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚቀጥል ሰው እንዲላክም ያረጋል...፡፡

ከሩሲያውያኑ ጉዳይ ያነሰ ክብደት ያለው መስሎ ሊታይ ቢችልም ሚሳይል ከአንድ ትልቅ የመንገደኞች አውሮፕላን በበለጠ በጅምላ ጨራሽ መሣሪያነት ሊያገለግል መቻሉ እውነት ነው፡፡ ከዚህም ጉዳይ በተጨማሪ ለሴናተር ፔል ታጃኪስታንና



t.me/OLDBOOKSPDF

አፍጋኒስታን ውስጥ ስለሚንቀሳቀሱ እስላማዊ አክራሪዎች ያሰባሰብኩዋቸውን መረጃዎች ላቀብለው ወሰኘእለሁ፡፡

ዱሻንቤ ከደረስኩበት ጊዜ እንስቶ በእስልምና ላይ የማደርገውን ጥናቴን ቀጥዬበታለሁ፡፡ ሁልቀን ማለት ይቻላል ቁራን እነባለሁ፡፡ በሌሎች የሙስሊም ምሁራን የተፃፉ መፃህፍቶችን እገላብጣለሁ፡፡ አላማዬ የአረብኛና ፐርሺያኛ ቋንቋ ክህሎቶቼን ከማዳበር ባሻገር እስላማዊ ቅዱስ መፅሃፍቱ ስለቅዱስ ጦርነትና ግድያ ምን ይላሉ ለሚለው ጥያቄዬ መልስ ማፈላለግ ነበር፡፡ እናም ስለፈለግኩት ርዕስ የፈለግኩትን ያህል ማንበብ ብችልም መፅሀፍቶቹ የደረሱበት አንድም ድምዳሜ እልነበረም፡፡

እግር መንገዴን እንድ የታጂክስታን እስላማዊ መሪ ስሆነው አብደላ ኑሪ የቅርብ የሆነ ሰውን ለስራዬ መመልመል ችዬ ነበር፡፡ ኑሪ የሚንቀሳቀሰው ከአፍጋኒስታን ውጭ ሲሆን በሩሲያና የአካባቢው ሽሪኮቿ ላይ የማያባራ ጦርነት ከፍቷል፡፡ ከሰውየው ጋር የምፈፅመው ግንኙነት እስፈላጊ የሚያረገው ሌላው ጉዳይ ሩሲያና ታጃኪስታን አሜሪካ በኑሪ ላይ ለሚያረጉት ውጊያ ድጋፍ እንድታረግላቸው መማፀናቸው ነው፡፡ ኑሪ በመካከለኛው ምስራቅ የቅርብ ሽሪካችን ከሆኑችው ሳኡዲ እረብያ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚደረግላት የሚገልፅ መረጃ እለኝ፡፡ በሳዑዲ ንጉሣውያን ቤተሰብ ጥበቃ ስር የሚገኘው እለማቀፍ እስላማዊ ሊግ ድርጅት ከሳኡዲ ለኑሪ ልዩ ልዩ እርዳታና ጦር መሣሪያዎች በመርከብ እንደሚልክለት ደርሰንበታል፡፡ ኢስላማባድ ፓኪስታን እና ሪያድ ሳውዲ እረብያ ያሉ ቢሮዎቻችን ተፈላጊውን መረጃ ሊሰጡን የማይችሉ ከመሆናቸው አንፃር ከ --- ጋር ያለንን ግንኙነት መቀጠሉ እስፈላጊነት እንድና ሁለት የለውም፡፡

በነገራችን ላይ ሩሲያና ታጃኪስታን በኑሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ጥሩ መሠረት ያለው ነው ማለትም ኑሪ በሐምሌ 1999 በአሳማ ቢን ላደንና የኢራኑ መረጃ ተቋም መሃል የወዳጅነት ውል እንዲፈረም አርጓል በዚህም የኢራኑ መረጃ ማዕከል ሰራተኛና ቢን ላደን ቢያንስ አንድ ጊዜ ተገናኝተዋል፡፡ እናም በግንኙነቱ ወቅት የተፈፀመውን ውል ምንነት ባናውቅም ቢን ላደን ከኢራን ጋር የተቀናጀ የሽብር ጦርነት በአሜሪካ ላይ ለመክፈት ማቀዱን እውቀናል ስለዚህ እኔን የሚተካው ሰው ከ ------ ጋር ግንኙነት ማረግ እስከቻለም ድረስ ቢን ላደን ያወጣው እቅድ እየተተገበረ መሆን አለመሆኑን የምንደርስበት ጉዳይ ይሆናል፡፡

ዳግም ላሰምርበት የምሻው ነገር ቢኖር ደግሞ የመስከረም እስራ አንዱን ጥቃት የመሰለ ማስቀረት የሚቻለው ስለቢላደን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ግንኙነት ካላቸውና እኔ ከመለመልኩትና ከመሳሰሉት ሰዎች ጋር መገናኘት መሰሉ ጥቃት ዳግም እንዳማይደርስ ማረጋገጫ ይሆነናል ምክንያቱም እውነታው ቢንላደን ያገኘውን አጋጣሚዎችን በመጠቀም የሽብር መረቡን የሚያስፋፉ መሆኑ ነው፡፡ ያ እስከሆነም ከመረቡ ጋር ንክኪ ያላቸውን ሰዎች ቁጥራቸው የቱንም ያህል ይሁን የቢንላደንን ዕቅድ ያሳውቁናልና፡፡

ባይገርማችሁ እኔ ይህን ፅሁፍ እየፃፍኩ ባለበት ሰዓት አሜሪካ ቀውጢ ጦርነት ውስጥ ነች የጠላቶቿ ቅጥረኞችንም እንደ አንድ ወራጅ ውሃ መውሰድ ይቻላል፡፡ በሙቶዎች የሚቆጠሩ በተገደሉና በቁጥጥር ስር በዋሉ ቁጥር ሌሎች መቶዎች በነሱ እግር



t.me/OLDBOOKSPDF

ይተካሉ፡፡ ጊዜአችን ልንጨርሳቸው እንችልም፡፡ ከነሱ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመፍጠር ግን የውጥናቸውን ምንነት ልንደርስበት እንችላለን ያም የጦርነታቸውን ዕቅድና አቅጣጫ በትክክል ለማወቅና ነገሮችን በምን መልኩ እንደምን እየተጉዋዙ እንዳለ ለመረዳትና ምን ያህል ወጣቶች ራሳቸውን ሊሰው እንደተዘጋጁ ለማጤንና እንዲሁም ወደመስጊዶች ማሰረግ የምንችላቸው ሰዎች እንዲኖሩን ያደርገን ነበር፡፡ እስካሁን መስጊዶችን ሰርገው የሚገቡ ሰዎች አልነበሩንም፡፡ ያም እስካሁን ግልፅ ያልሆኑልኝና CIA እና መላው መረጃ ማህበረሰብ ግቡን ለመምታት የሚጠቀምባቸው መንገዶች ትክክለኛ አለመሆንን ያሳያል፡፡ እናም ይህም ታጃኪስታን ወዳለው ጦር ግንባር መምጣትን ለደፈሩት ሴናተር የምነግራቸው ጉዳይ ይሆናል፡፡

☆☆☆

ከሊይቦር ፔልን ያሳፈረችው ሲ-20 የአየር ሃይል አውሮፕላን ያረፈችው መጋቢት 31/1994 ከቀትር በኋላ ነበር፡፡ ያን ዕለት ማታ አብረን ራት እስከተመገብንበት ጊዜ ድረስ ሴናተሩን የማናገር እድል አላገኘሁም ነበር፡፡ ፔል ሌቱን ሙሉ በአውሮፕላን ሲጓዝ እንዳደረ መንገደኛ አይመስሉም ምክንያቱም የድካም ስሜት አይነበብባቸውም ነበርና፡፡

ዕራት ከተመገብን በኋላም አምባሳደር ኤስኩዶሮ እኔንና ፔልን አስተዋወቀን በመለጠቅም እኔና ፔል ተያይዘን ወደ ውጭ ወጣን፡፡

በወንጀለኛ ድርጅቱ አባል ሊያረገኝ ስለሞከረው አንድ ምክትል የምድር ጦር አዛዥ ነገርኳቸው፡፡ ፔል ግን በዝምታ ከማዳመጥና ከመራመድ ውጭ ቃል ትንፍሽ አላሉም ሰውየውንም እንዴት እዳጠመድኩት ገልጬ በእድማው ላይ ሊሰነዘር ስለታቀደው ጥቃት ማወቅ መቻሌን አጫወትኳቸው ዕቅዱም በሰራዊቱ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ እንዳሳደረም አወጋሁዋቸው፡፡ ቀስ በቀስም ርዕሴን ወደእስላማዊ አክራሪዎች እንቅስቃሴ ለወጥኩ እኔን የሚተካው ሰው የታጂክ ቋንቋ ተናጋሪ መሆን አስፈላጊነትንና ተያያዥ ነገሮችን በማንሳት ተናገርኩ፡፡

በመሃል «አምባሳደሩ ወደ ፓሚርስ እና ሶግዲያና ስላረከው ጉዞ አጫውተኛል፡፡ በደንብ ልታብራራልኝ ትችላለህ??» አሉኝ፡፡

ቀጣዮቹን 20 ደቂቃዎች በያግኖብ ሸለቆ ስላየሁዋቸው ነገሮች በማውራት አሳለፍኩኝ፡፡ አቀራረቤንም ፔልን እንዲማረኩ አርጓቸዋል ያ ማለት ደግሞ ወደ ሩሲያ እንደማልመለስ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ ነገሩ ሁሉ በመረጃ ፊንታ የጉዞዬን ማስታወሻ ተናገር የተባልኩ አስመስሎኛል፡፡ ይሁንና በጥሞና አዳምጠው ከጨረሱ በኋላ የማበረታታትም ሆነ የአድናቆት መግለጫ እንዲሁም ማሳሰቢያም ሳይሰጡኝ በመጡበት መንገድ ዕብስ አሉ፡፡ ውስጤ ቢንጨረጨርም ምላሹን ከጊዜ በኋላ አገኛለሁ የሚል ተስፋ ነበረኝ ይሁንና ያም አልሆነም፡፡ በጊዜው CIA መጠሪያውን ወደ ማዕከላዊ አስንብኚ ተቋምነት መቀየር ያሻዋል ብዬ አስብ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ምክንያቱም አለቆቻችን ከሚታርሙት መረጃ በተጨማሪ በአካል እቦታው ድረስ እየመጡ ለዕርምጃው የሚያሳዩት ዳተኝነት እሁን ድረስ ሳስበው በጣም ያቃጥለኛል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፲፪

## መጋቢት 3/1995፤ ሳሳሀ አልዲን - ኢራቅ

«ወዲህ ናና የመጣልህን መልዕክት ተመልከት» ሲል ቶም ላይኛው ፎቅ ካለው ክፍል ሆኖ ነገረኝ፡፡

ቶም ሁለተኛ ፎቅ ካለው ቀድሞ በመኝታ ክፍልነት ስንጠቀምበት ከነበረውና አሁን ግን የመልዕክት መቀበያና ማስተላለፊያ ከሆነው ክፍል ሆኖ የጠዋቱን መልዕክት በመቀበል ላይ ነበር፡፡ የአንድ ልዩ ሃይል አዛዥ የሚመስል ግርማ ሞገስ የነበረው ቶም CIA ለመስራት በኮንትራት ነበር የተቀጠረው፡፡ በፀረ-ሽብር ዘመቻውም ረድቶናል ተቋሙ ሰራተኞችን በኮንትራት ማሰራቱ በጊዜው የገጠመውን ችግር የሚያሳይ ሲሆን ችግሩ ምን ይሁን ምን እኔን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም፡፡ አጭሩና ጠቆር ያለ ቆዳ ያለው ቶም ኢራቃዊ በመሆኑ ኮንትራቱን እንዲፈርም ተደርጓል በተጨማሪም በዘርፉ ልምድ ማካበቱንና ታጋሽነቱ ለስራው አሳጭተውታል፡፡ እናም ደረጃዎቹን ስወጣ አስብ የነበረው ዋና መምሪያው በአስቸኳይ ከሰሜን ኢራቅ እንድንወጣ አዞን ይሆን ይሆን እያልኩ ነበር፡፡

ዋና መምሪያው በሰሜናዊ ኢራቅ አንድ ቡድን በነጠላ መሰማራቱ እፎይታን አልሰጠውም በዚህም ምክንያት የኢራቅ ጉዳይ የሚያሳስበው የዋና መምሪያው ሃላፊ አልነበረም መገናኛ ብዙሃን በተቃወሙት የ1991 ዓ. የባህረ-ሰላጤው ጦርነት የሳዳም ሁሴን ተቃራኒ ሆነው የተሰለፉት ጥምር አይነት የሳዳም ሁሴንን ሰራዊት ከኩዌት አስወጥተዋል፡፡ ወራሪው ሃይልንም ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲቀበል አርገውታል፡፡ ግና ሳዳም ሆሴንን ከስልጣን ማስወገድ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ሁኔታው በክልሉ ያለውን የሃይል ክፍተት የሚረዱትን አረብ ወዳጆቻችንን አስከፍቷል፡፡ የኢራቅ ኩርዶችና ብዙሃኑ ሺያዎች ጥምር ክንዳቸውን በመጋቢት 1991 በተዳከመው የሳዳም አገዛዝ ላይ ባነሱ ጊዜም እርዳታችንን ተማፅነው ነበር፡፡ እኛም ሳዳም ሄሊኮፕተሮቻቸውን በተቀናቃኞቻቸው ላይ ሲያዘምቱ ከማየት ባለፈ ያረግነው ነገር አልነበረም፡፡ ሁኔታው ኩርዶችን ወደ ኢራንና ቱርክ በብዛት እንዲጎርፉ ካረገ በሁዋላ ጆርጅ ቡሽ የበረራ ዕገድ በኢራቅ ላይ እንዲጣል አርገዋል ያም ኩርዶች ሰሜናዊ ኢራቅ ያካለለውንና እውቅና የተነፈገውን የኩርድ መንግስት ዳግም ማቋቋም



t.me/OLDBOOKSPDF

አስችሎአቸዋል፡፡ ያንንም ግዛት ኩርዶቹ አገራችን ነው ሲሉ አውጀዋል፡፡ ኩርዶች ማለት ደግሞ የህንድ አውሮፖውያን ዝርያ ያላቸው በመካከለኛው ምስራቅ ካሉ ዝርያዎች አናሳዎቹና የራሳቸው መንግስት የሌላቸው ህዝቦች ነበሩ፡፡

ያላለቀው ጦርነታችንን CIA ከጫፍ እንዲያደርሰው የታቀደ ይመስላል፡፡ እቅዱ የጦርነቱን ስጋት መቅረፍ፣ ሳዳም ሁሴንን ከስልጣን የሚወገዱበትን መንገድ ማፈላለግና የኩርዶች እርስበርስ ጭፍጭፍን ማስቆምን ያጠቃልላል፡፡ ያን ማድረጉ ለዋሽንግተን ባለስልጣኖች ቀሎ ይታያል፡፡ በገሃድ ያለው እውነታ ግን የባለስልጣኖቹን ግምት ውድቅ ያደረገ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ሳዳም ሁሴን እራሳቸው በእኛ ላይ አፈና አሊያም ግድያ እንደማይፈፅሙ ማረጋገጫ ሊሰጠን የሚችል ሰው የለም፡፡ የኩርዶች ጉዳይም ሌላው ጥያቄ የሚያጭር ነገር ነው፡፡

ኩርዶች በ1991'ዱ የባህረ ሰላጤ ጦርነት የሳዳም ጦር ከሰሜናዊ ኢራቅ እንዲወጣ ካደረጉ በኃላ የእኛ የሚሉት አገር ሊኖራቸው ችሏል፡፡ ማዕከላዊ መንግስት ያልነበራቸው በመሆኑም ወደ እርስ በርስ ግጭት አምርተዋል፡፡ ግጭቱም ባብዛኛው ብልጭ ድርግም የሚል ቀላልና የደፈጣ ውጊያን ያጠቃለለ ነበር፡፡ በሂደትም ኩርዶቹ ከባድ መሳሪያዎችን መጠቀም ጀምረዋል፡፡ ለአንድ ወይም ሁለት ቀናት በከባድ መሳሪያ መጠዛጠዙን ስራቸው አድርገውት ነበር፡፡

በየካቲት አጋማሽ ውጊያው አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ በአንድ መኪና ላይ የተጠመደ ቦምብ በህዝብ በተጨናነቀ የገበያ ስፍራ ፈንድቶ ከመቶ በላይ ሰዎችን ገሏል፡፡ ዙሪያዋን ፈንጂ የታጠቀች ሴት ሳላህ አል ዲን ከሚገኘው መኖርያ ህንፃችን አንድ ጥግ የአጥፍቶ መጥፋት ጥቃት ፈፅማለች በወቅቱ ጥቃቱ ከደረሰበት ክፍል ከአንድ የኩርድ ቅጥረኛችን ጋር ግንኙነት በመፈፀም ላይ የነበርን ሲሆን ብዙም ሳይቆይ ከሳላዲን ከአንድ ማይል ባነሰ ርቀት ላይ ከሚገኝ ስፍራ ሁለቱ ዋነኛ ተቀናቃኝ የቱርክ አንጃዎች ውጊያ ገጥመዋል፡፡

ባለፉት ጥቂት ቀናትም ኩርዶቹ ፈፅሞ የመጠፋፋት አዝማሚያ አሳይተዋል፡፡ የሁኔታው መከፋትም ኢራቅን በማሳሰብ ሳዳም ጦራቸውን በሙሉ ከ የካቲት 28 ጀምሮ በተጠንቀቅ እንዲቆም አዘዋል፡፡ ፈቃድ የወሰዱ የሰራዊቱ አባላትም ወደግዳጅ እንዲመለሱ አዝዘው ነበር፡፡ እናም ከባህረ ሰላጤው ጦርነት ማክተም በኃላ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠባባቂ ጦራቸውን ከግንባር አሰልፈዋል፡፡ በቀጣዮም ቀንም ማለትም መጋቢት 1 ኢራን ጦሯን ወደ ኢራቅ ድንበር አስጠግታለች፡፡ ይህ ሁሉ ከቱርክ ጦር ወደኢራቅ ድንበር መጠጋት ጋር ተዳምሮ የዋሽንግተንን ትኩረት ለማግኘት በቂ ነበር፡፡ ቱርኮችም ጥበቃቸውን የቱርክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኩርዶች ደፈጣ ተዋጊዎች በመንደርደሪያነት በሚገለገሉበት ሰሜናዊ ኢራቅ አጠናከረዋል፡፡

ሁኔታው ዋሽንግተንን ቢያስበረግግና ከሰሜናዊ ኢራቅ እንድንወጣ ብታደርግ አይገርመኝም የመጀመሪያዋን ጥይት በሰማን ቁጥር ጓዞችንን ጠቅልለን መሸሽን ለምደነዋል፡፡ ባለስልጣናቱ ለቬየትናም ለላኦስና ኮንጐ የተዋጋናቸውን አስቀያሚ ጦርነቶች መለስ ብሎ ማየትን የተሳናቸው መስለው ታይተውናል፡፡ እኔም ለደህንነታችን ይበጃሉ ያልኳቸውን ዕርምጃዎች ወስጄያለሁ፡፡ ምክንያቱም የነገሮች በፍጥነት መለዋወጥና ፈጣን ዕርምጃ የመውሰድ አስፈላጊነትን ግልፅ አርጎልናል፡፡ እናም የተቀሩት ብቸኛ መከላከያችንም ኩርዳውያን ዘቦቻችን ሆነዋል፡፡ «ከዚህ እንድንወጣ እየገፋፉንኮ ነው አይደል እንዴ?» ስል ከመገናኛው ክፍል በስራ የተጠመደውን ቶምን ጠየቅኩት ሁኔታው በላንግሌይ እና ዋሽንግተን አለቆቻችን ዘንድ ሊፈጥር የሚችለውን ድንገተኛ መረበሽ አይቀሬነት እየታሰበኝ አለቆቻችን ከሰፍራው መራቃችንን ቢሹ እንኳ ግንኙነታችንን መቀጠል ወደሚያስችለን የቱርክ ድንበር እንድንሄድ ከማድረግ ያለፈ ትዕዛዝ እንደማይሰጡን ገምቼአለሁ፡፡ እኛን ወደዋሽንግተን መመለሱ ሳዳም ሁሴንን ከማስወገዱ እቅዳቸው ጫፍ የደረሱት የኢራቅ ተቃዋሚዎችን ሞራል ማላሸቅ እንደሚሆን አውቃለሁ፡፡

ያልተለመደ መገረም ከቶም ፊት አነበብኩ፡፡ «ነገርኩህ እኮ ሲል መለሰልኝ ሁኔታው ያ መሆኑን ላታምን ትችላለህ፡፡»

መልዕክቱ «እስቸኳይ» ነው፡፡ ይላል እኛ ካለንበት ቦታ ለቀን ከመውጣታች ጋር የሚያያዝ ምንም ነገር አልነበረውም፡፡ ቶም እንዳየው ያቀበለኝ የቴሌግራም መልዕክት CIA ውስጥ ቆይታዬን ባረግኩባቸው 19 ዓመታት አይቼ የማላውቀው መልዕክት ሆነብኝ መልዕክቱም የተላከው ከኃይት ሃውስ ሲሆን የተፃፈውም ከፕሬዝዳንቱ ብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ከሆኑት ቶኒ ሌክ ነው፡፡ በ CIA የቴሌግራም መሳኪያ በመጠቀምም ከእጃችን እንዲደርስ ሆኗል፡፡ ቴሌግራሙን ያን ዕለት ጠዋት ለኢራቅ ተቃዋሚ መሪዎች ማስረከብ ይጠበቅብኝ ነበር፡፡

ቴሌግራሙንም ማንበብ እንደጀመርኩ መርዶ ነው ስል ለራሴ አጉተመተምኩ፡፡ «በዚህ ሳምንት መጨረሻ ለመፈፀም ያቀዳችሁት እቅድ ሙሉ ለሙሉ ተሰርዟል፡፡ እቅዱ ፉርሽ ሊሆን የሚችልበት ትልቅ እድል መኖሩን እናምናለን፡፡ በመሆኑም በእቅዱ ለመግፋት የምትወስኑ ከሆነ በራሳቹሁ እንደትወጡት ይሁን!!»

ለጥቆ በሰፈረው ሁለተኛና የመጨረሻው አንቀፅ መልዕክቱን ለሰዎቹ እንዳስረከብኩ ለዋሽንግተን ቴሌግራም እንዳረግ ቀጠን ያለ ትዕዛዝ ተሰጥቶኛል፡፡

ዘጠኝ ከማይሞሉ ማይሎች ርቀት ላይ ከሚገኘው የኢራቅ ጦር ግንባር ርቄ አይደፋሬዎቹን በበረዶ የተሸፈኑት የኩርድ ተራሮችን ከጀርባዬ ትቼ «ተሰርዟል»



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚለው ቃል እየኔን ተከዬ እንደ ጅብራ ተገትሬያለሁ፡፡ ሳዳም ሁሴን ኩዴታ ሊካሄድባቸው የተቃረበ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ እኛን ፍለጋ ጦራቸውን ወደ ሰሜናዊ አቅጣጫ ከመላክ ፋንታ መፈናፈኛ እንዳጣች አንድ እይጥ ራሳቸውን በተከላከሉም ነበር፡፡

እኛም መጫሚያችንን ከማጥለቃችን በፊት የመጀመሪያው T-72 ታንክ ሳሳህ እል ዷን ደርሶ 125 ሚ.ሜ. ቀለሀውን ከቤታችን የፊት በር ባርከፈከፈውም ነበር፡፡

መልዕክቱን በደንብ ለመረዳት ዳግም አነበብኩት፡፡ በሌክ መልዕክት የሰፈረው «እቅድ» የሚል ቃል በሳዳም ሁሴን ላይ ከሠላሣ ስድስት ባነሱ ሰዓታት ውስጥ ሊፈፀም የታቀደውን መፈንቅለ መንግስት ያመለክታል፡፡ ዋሽንግተን እቅዱን ከተጠነሰሰበት ከጥር ወር እንስቶ ከአንድ ወር ለበለጠ ጊዜ ስታብላላው ቆይታለች ያም እቅዱን ወደሌላ ጊዜ እንዲሸጋገር ለማድረግ ወይም ለማስቆም በቂ ጊዜ ሆኖ እግኝታዋለች፡፡ እቅዱን ያረቀቅኩት እያንዳንዱንም ሂደት ከስር ከስሩ ዋሽንግተን ላሉ አለቆቼ ሪፓርት አደርግ የነበርኩት እኔው ነበርኩኝ፡፡ ዎሽንግተን መፈንቅለ መነግስቱ ያለሳንካ እንደማይፈፀም አውቃለች እቅዱ ከመፈፀሙ አስቀድሞ ሃሳቧን እንደምትቀይርም ተረድታለች፡፡ በእውነቱ ሳዳም እቅዱን ለመተግበር በቀሩን ሰዓታት ታንኮቻቸውን በጉዳናዎቻቸው ላይ እንደሚያርመሰምዷቸው እናውቅ ነበር፡፡ ዋሽንግተን ግን በእቅዱ ዙሪያ ያቀረብነውን ሪፓርት ችላ ብላለች መንገዱ አልጋ ባልጋ እንደሆነ ሁሉ ዝግጅቱን በምናረግበት ጊዜ ሁሉ እጇን እጣምራ እይታናለች አሁን መፈንቅለ መንግስቱን የሚፈፅሙት የኢራቅ መኮንኖች እቅዳቸውን ከዳር ለማድረስ በሚንደረደሩበት በዚህ ሰዓት የብሄራዊ ደህንነት አማካሪው ከጉዳዩ እጁን ሰብስቧል፡፡

ቴሌግራሙን ካነበብኩ በኃላ በተከተሉት ደቂቃዎች ግን ለምን ስል ራሴን ደጋግሜ ጠይቄአለሁ፡፡ ለምን እንዲህ ያረጋሉ?? ስለምንስ የዘገየ እርምጃ ይወስዳሉ?? ነገሩ ሁሉ ቶኒ ሌክም ሆኑ CIA ከመፈንቅለ መንግስቱ ራሳቸውን ማራቅ እንደፈለጉ እድርጎ እሳየኝ፡፡ ብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤቱ ሳያውቀው የፈፀምኩት የ CIA ግዳጅ ኖሮኝ እያውቅም፡፡ የሌክ የመካከለኛው ምስራቅ አማካሪ የሆነው ማርቲን ኢንዲክ CIA በሰሜን ኢራቅ የሚንቀሳቀስ ህዋስ እንዲፈጥር አይል እኔም ሕዋሱን እንድመራው አድርጎ ነበር፡፡ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ህዋሱን ከስራ ውጭ የሚያደርግ ትዕዛዝ ሲያስተላልፍም ኢንዲክ ትዕዛዙን በዝምታ አልፎታል፡፡ ኢንዲክ ሌክን ጨምሮ እንደማንኛውም የኢራቅን ጉዳይ የሚከታተል ኤን.ኤስ.ሲ ውስጥ የሚሰራ ሰው በሰሜናዊ ኢራቅ ያለው ህዋስ ስለምን የኢራቅ ተቃዋሚዎች በሳዳም ሁሴን ላይ ለመፈፀም በጠነሰሱት መፈንቅለ መነግስት እቅድ ውስጥ እጁን እንደከተተ ያውቃል፡፡ እቅዱ መተግበሩን ኤን.ኤስ.ሴ ባይፈልገው ኖሮ በአጭሩ እንዲቀጭ ማድረግ የነበረበት ኩዴታው መጠንሰስ በጀመረበት ወርሃ ጥር ነበር፡፡ አሁን አይተግበር የሚል ትዕዛዝ ማስተላለፍ ግን ዳግም ልናገኘው የማንችለውን ሳዳም ሁሴንን ማስወገድ የሚያስችለንን እድል እንድናጣው የሚያደርገን ይሆናል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩን በምስጢራዊው የሳተላይት ስልካችን ተጠቅሜ ለኢንዲክ ባሳውቀውስ ስል አሰብኩኝ፡፡ ግና ስልክ ቁጥሩ ቢኖረኝም ምላሽ ሊሰጠኝ እንደማይችል ገመትኩኝ የኤን ኤስ ሲ ባለስልጣናት በመስክ ካሉ የCIA ህዋሶች የሚደረጉላቸውን የስልክ ጥሪዎች አይቀበሉም፡፡ በተጨማሪም በኔና ኢንዲክ መሃል ያለው ግንኙነት ጥሩ አልነበረም፡፡ ከመንፈቅ በፊት ኤን.ኤስ.ሲም ሆነ ዋሽንግተን ውስጥ ያሉት ባለስልጣናት ያለምንም ደም በሳዳም ሁሴን ላይ ሊፈፀም ስለሚችል መፈንቅለ መንግስት ማሰባቸውን እንዲያቆሙ ነግሬዋለሁ፡፡ ምክንያቱም የኢራቅ ወቅታዊ ሁኔታ ያን መፈፀም እንደማያስችል አስረድቼው ነበር፡፡ ከግንኙነቱ በኃላም ስራዬ ሳንካ ገጥሞታል፡፡ ለታላላቆቹ የዋሽንግተን ህልመኞች ያለምንም ደምጠብታ ሳዳምን ከስልጣን የማስወገዱ ሃሳብ የተስፋ ዳቦ ሆኖባቸዋል፡፡ ግና በሳዳም ዙሪያ ካለው ክበብ ሰዎችን ማስረግ አለመቻላችን እቅዳችንን ከመሬት ማውረድ አላስቻለንም፡፡ አሁንም ከነፃዋ አገር 6/192 ማይሎችና 8 የሰዓት ቀጠናዎችን ርቄ እንደምገኝ ማመን ይኖርብኛል፡፡ ያም ወደዛች ምድር እስካልተመለስኩ የችግሩን መንስኤ ሳውቀው እንደማልችል ግልፅ አርጎልኛል፡፡

«ከዚህ ጋር ተያይዞ የተላከልን ቴሌግራም ይኖር ይሆን?» ስል ቶምን ጠየቅኩት፡፡ ራሱን በአሉታ ወዘወዘ፡፡

የዋሽንግተን ዲሲ እና የዋና መምሪያው ቅርንጫፍ ወደሆነውና የሳዳምን ጉዳይ ወደሚከታተለው ቢሮዬ ስልክ ደወልኩ፡፡

ስልኩን የተቀበለኝም በስራ ላይ የነበረው ሃላፊም «የኢራቅ ጦር በሙሉ ተጠንቀቅ ላይ መሆኑን አታውቅም እንዴ?! ሲል አንባረቀብኝ፡፡

«የሰራዊቱ በተጠንቀቅ መቆሙ የማይጠበቅ ነገር አይደለም» ስል በሚንቀጠቀጥ ድምፅ «መለስኩለት ያ ግን የእቅዳችን አንድ አካል ነበር፡፡ ግን የተቀረውና ምስጢር የሆነው የእቅዳችን ክፍልስ?»

ስለመፈንቅለመንግስቱ ግልፅ የሆነ መረጃ ልሰጠው አልፈለግኩም፡፡ ይህም ስለሱ መረጃ ይኑረው አይኑረው የማውቀው ነገር ስላልነበረ ነው፡፡

«ይህና ከሳዳም ጋር ሌላ ዙር ጦርነት መግጠም የሌክ እቅድ አካል አይደለም፡፡ በደንብ አስቦበታል፡፡ ስለሱም ምንም ነገር ዳግም መስማት አይሻም፡፡»

ስልኩን ዘግቼ አንፀባራቂውን ሁለተኛ ፎቅ ላይ በጦርነት ማስፈፀሚያ ክፍልነት የምንጠቀምበትን መኝታ ክፍላችንን በዓይኖቼ ቃኘሁት፡፡ መስኮቱ በአንድ ብርድ ልብስ ተሸፍኗል፡፡ ከአየር የተነሱ ካርታዎች በየግድግዳው ላይ ተሰቅለዋል፡፡ ኤስ-47 ጠመንጃዎችና ራሽን የያዙ ሳጥኖች የክፍሉን አንድ ጥግ ይዘዋል፡፡ ሳዳም ከየካቲት 28 ጀምሮ ለሰሜናዊ ኢራቅ የተዘረጋውን የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲቋረጥ በመወሰናቸው ኤሌክትሪክ ያልነበረን በመሆኑ ባልኮኒው ላይ ያሉት ኤል



t.me/OLDBOOKSPDF

እስ.ቲ አምፑልና ጀነሬተር በድምፃቸው አካባቢውን ያውካል፡፡ ላለፉት ሁለት ወራት ሚናችን የነበረው የጦርነት ጨዋታ ከሚጫወቱት ልጆች ሚና ያለፉ እንዳልነበረ አስተዋልኩ፡፡

«ለምን ዞር ዞር ብለን አንመጣም?» ንፁህ አየር መውሰድ ፈልጌያለሁ ስል ቶምን ጠየቅኩትና ተያያዝን ወጣን፡፡

ከመኖሪያ ቤታችን ወረድ ብሎ ካለውና የኢራቅ ዋነኛ ተቃዋሚ ከሆነው የኢራቅ ብሄራዊ ኮንግረስ ፅህፈት ቤት ፊት ለፊት ሶስት ሩሲያ ሰራሽ ወታደራዊ ካሚዮኖችና አንድ አነስተኛ የጭነት መኪና ቆሟል፡፡ ሶስት የደንብ ልብስ የለበሱ ወጣቶች እያውካኩና እየሳቁ መኪኖቹ ላይ ፈንጅና ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ይጭናሉ፡፡ ወደ ኢራቅ ግንባር ለመጉዋዝ በመዘጋጀት ላይ እንደነበሩ ያስታውቅባቸዋል፡፡

የሳላህ አል-ዲን ዋነኛ ጉዳና የሰው ዘር አይታይበትም፡፡ የከተማዋ ብቸኛ ሻይ ቤትም ባዶሆኗል ቀኑን ጠመንጃዎቻቸውን ግድግዳ አስደግፈው ሱኳር የበዛበት ሻይ ሲጎነጩ የሚያሳልፉት አዛውንቶች እንደወትሮው ውስጡ አልነበሩም፡፡ ሰዎቹ ነገሮች ኩርድ ውስዋ ሲባባሱ ጊዜ ብቸኛ መጠለያ ወደሚሆኑዋቸው ተራሮች ውስዋ ፈለፈልዋቸው መንደሮች ሄደዋል፡፡ እንደተቀረው የሳላህ አል ዲን ነዋሪ ሁሉ የCIA ሰራተኞነታችንን የሚያውቀው አስተናጋጅ በፍርሃት ካየን በኃላ መጋረጃውን ገልጦ ወደውስጠኛው ክፍል ዘለቀ፡፡ ስለመፈንቅለ መንግስቱ መካሄድ አለመካሄድ የምናውቀው ነገር ባይኖርም አየሩ ላይ የረበበ አንዳች ነገር ስለመኖሩ ግን እርግጠኞች ነበርን፡፡ ይህንን ድባብ ለተቀባዮ ክፍል መስጠት ቀላል ነገር አለመሆኑን ጥርጥር የለውም ስልም ለራሴ ተናገርኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፫

## ጥር 21/1995 ፡ ሰሜናዊ-ኢራቅ

ጥር 21/1995 እኔና ቡድኔ ወደ ሰሜናዊ ኢራቅ በእግራችን በተጓዝንበት ወቅት ፀረ-ሣዳም እንቅስቃሴ ለመፈፀም የወጣን ሰው እናገኛለን የሚል ግምት አልነበረንም፡፡ ቡድኑን በመሪነት ወደአካባቢው ይገፔ የተጉዋዝኩት CIA ሳዳም በሌሎቹ ተጐራባች ሀገራት ላይ የወረራ እቅድ ይኑራቸው አይኑራቸው ለማወቅ ሌላ አማራጭ ስላልነበረው ነው፡፡ እንደዕውነቱ ከሆነ ስፍራው የኢራቅ ወታደራዊ ባለስልጣናትን ተባባሪያችን አርጐ ለመመልመል ምቹ መሆኑን እውቃለሁ፡፡

የመጀመሪያው ግዳጃችን ድንበር አቋርጠን ኩርዶች በመጋቢት 1991 በአደረጉት ህዝባዊ መነሳሳት በቁጥጥራቸው ስር ካዋሏትና ዛኩ ከተሰኘችው ትንሽ ከተማ በመግባት አንድን የኢራቅ ሜጀር ጄነራል ማግኘት ነበር፡፡ ጄኔራሉ የኢራቅን ጦር ከድቶ ወደ ሰሜኑ ግዛት እስከመጣበት 1994 የኢራቅ ፕሬዝዳንት አማካሪ በመሆን አገልግሏል፡፡ ከዚህ አንፃር የሳዳም ስከድ ሚሳይሎች በተለይም ጅምላ ጨራሽ ሚሳይሎች የተደበቁበትን ስፍራ ይነግረናል ብለን ጠብቀናል፡፡

በሹፌሩ በሚሽከረከረው አውቶሞቢል ካረፍንበት መኖሪያ ቤት ከረፋዱ 5 ሰዓት የደረሰው ጄኔራል በቡድናችን ሁኔታ ሳይገረም አልቀረም፡፡ ወደሰሜናዊ ኢራቅ የተሻገርነው ከጭነት ካሚዮኖቹ ላይ ተጭነን የነበር ሲሆን በጉዟችን መጨረሻም እንድናርፍበት የተደረገው ቤትም መብራት ውሃና የቤት ማሞቂያ (ሂተርም) አልነበረውም፡፡ ከቤቱ የደረስንበት ውድቅትም እጅግ ብርዳማ ስለነበር ቅዝቃዜው በኮዳችን የያዝነውን ውሃ ወደበረዶነት ቀይሮታል ፂማችንን ሳንላጭ፣ ሰውነታችንን ሳንታጠብ ብቻ ለቀዝቃዛ አየር የሚሆኑንን ወታደራዊ አልባሳት ደራርበንና አውቶማቲክ ጠመንጃዎችን አንግተን ስንታይ የዩናይትድ ስቴትስ ተወካዮች ሳይሆን አንድ የተሸነፈ ጦር አዝርክርኮና ጥሏቸው የሄዱ ምርኮኛ ወታደሮች እንመስል ነበር፡፡

ሁኔታችን ግራ ያጋባው ጄነራል ከመኪናው ወርዶ ተጠራጣሪ ለጥቆም የያዘውን በትረ-መንግስት በስጦታ መልክ ሰጠኝ፡፡ ጄኔራሉ እዚህ ግባ የማይባል ሙሉ ልብስ ለብሷል፡፡ ርካሽ ቆዳ ጫማዎችንም ተጫምቷል፡፡ ያስረው ክራቫትም ተቆላሟል፡፡ የተንኸረገገው ሪዙ፣ የካሬ ቅርፅ ያላቸው ትከሻዎቹና ቆፍጣናው ዕርምጃዎቹ ግን ወታደርነቱን ሰባቂ ነበሩ፡፡ ጄኔራሉ ከዚህ ቀደም በአንድ ጋዜጣ ላይ ከሳዳም ጐን ከአንድ ምሽግ አጠገብ ተቀምጦ የተነሳውን ፎቶ አይቼው ስለነበር እንዳየሁት ልለየው ችያለሁ፡፡ ሳሎን ገብተን ገና አረፍ ከማለታችን ወጥ ቤቷ ሻይ አቀረበችልን፡፡ ይሁንና ጄነራሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳዩን ለመጀመር አቀበት ሆኖበታል፡፡ ኢራቅን እንዴት እንዳገኘናት፣ እንደተመቸንና እንዳልተመቸን የምንፈልገው ነገር እንዳለም በማከታተል ጠየቀን፡፡

እኔም የመካከለኛው ምሥራቅ ቆይታዬ መሰሉን ትህትና የተላበሰ ጥያቄ እንድላመደው አድርጎኛል፡፡

«ጀኔራል ስለወላኞቹ የሳዳም ጦር መሣሪያዎች መነጋገር እንችል ይሆን?» ስል በመሃል ጠየቅኩት፡፡

ጥያቄዬ ሳያስገርመው አይቀርም መሰለኝ «ስለሱ የማውቀው ነገር የለም መሣሪያዎቹ የት እንደተደበቁ የሚያቁት ሳዳም፣ የሳዳም እማች የሆነው ሁሴን ካሚልና ጥቂት የሳዳም የቅርብ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡» አለኝ

ምንም ሳንነጋገር በእርምጥ ብቻ አንድ ደቂያ ነጎደ፡፡ እኔም ዝምታውን ለመስበር ያህል እኛን ለማግኘት ብሎ ጊዜውን ሰውቶ በመምጣቱ ላመሰግነው ስል ጉሮሮውን በመጠራረግ «የሳዳም በስልጣን መቆየት የአሜሪካ ፍላጎት ነውን?» ሲል ጠየቀኝ፡፡

የፈራነው አልቀረምና ጀኔራሉ በሾርኔ ሊነግረን የፈለገውን ሲብላላ የቆየውን፣ ኢራቅ ውስጥ ከምናደርገው እንቅስቃሴ ጐን የማይጠፋውንና አሜሪካ ሳዳም ከስልጣን እንዳይወርዱ ምስጢራዊ ድጋፍ ታደርጋለች የሚለውን የኃልዮት ጭምጭምታ ነበር፡፡ እንደነገሩ ከሆነ ነገሮየውን በኢራቅ ካገኘኃቸው ሰዎች በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር እንደነገሩ ከሆነ ነገሮችን ሰምቼዋለሁ፡፡ እንደውም ከኢራቃውያን አንዳንዶቹ ሌላው ቀርቶ ሳዳም ሁሴን የCIA ቅጥረኛ ሰላይ መሆናቸውን ያምኑ ነበር፡፡ ኃልዮቱ ግን አብዛኛው ኢራቃዊ ካለውና ዓለምን የሚገዙት የማይታዮ የጨለማው ኃይላት በመሆናቸው ታሪክም ብዙ እጥፋት ያለውና ጥቂቶች የሚያዩት የሴራዎች ቅጥልጣይ ነው ከሚለው እምነት ጋር የተቆራኘ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ከነገሮች ውስብስብነት አኳያ የአንድ አገር የውጭ ፖሊሲ መቀረፅ ያለበት አንድ ምስጢራዊ ሴራን መሰረት አድርጐ መሆን አለበት እንደማለት ነው፡፡ በጎ(ሀ) ልዮቱ መሰረት ሳዳም እና ዩናይትድ ስቴትስ በ1980 ኢራቅ ኢራንን መውረር የሚያስችላትን ምስጢራዊ ውል ፈርመዋል፡፡ የውሉም ብቸኛ አላማ ኢራንን ማፍረክረክ ነበር፡፡ ለጥቆም ጦርነቱ የኢራቅን የባህር ሰላጤው ሃያል ሃገር ሊያደርጋት በመብቃቱ ዩናይትድስቴትስ ኢራቅ ኩዌትን እንድትወር ለማድረግና የኢራቅን ጦር መደምሰስ እንዲያስችላት በማለት ከኩዌት ጋር ምስጢራዊ ውል ተፈራርማለች በዚህም ኢራቅ በተራዋ ኃይሏ እንዲፍረከረክ ተደርጓል፡፡ እናም ኢምፔሪያሊዝም ከዚህ በተሻለ ሊሰራበት የሚችልበት መንገድ የለም የሚለው የኀልዮቱ ድምዳሜ ሆኗል፡፡

ኀልዮቱ ፍቺ ላልተገኘላቸው ምስጢራት ስፊ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በባህረሰላጤው ጦርነት መቋጫ ላይ ስለምን ሳዳምን አድና እንዳልያዘቻቸውና ህዝባዊ መነሳሳቶችን ለማጨናገፍ የሚጠቀሙባቸውን ሄሊኮፕተሮች እንዲቆዩላቸው እንዳደረገች የራሱን ትንታኔ ይሰጣል፡፡ ሸሪኮቿ ከሆኑት ቱርክ እና ዮርዳኖስን ከመሳሰሉ ሃገራት ጋር ሳዳም ስለምን በኮንትሮባንድ የነዳጅ ግብይት እንዲያደርጉ እንደፈቀደችላቸውም ያብራራል፡፡ የቀድሞው ፕሬዝዳንቷ ጆርጅ ቡሽ በ1993 ኩዌትን



t.me/OLDBOOKSPDF

በነበኙበት ወቅት በሳዳም የግድያ ሙከራ ከተደረገባቸው በኋላ ሳዳምን በማሳደድ ፌንታ ፕሬዝዳንት ቢል ክሊንተን ባግዳድ ውስጥ የሚገኙ ባዶ ህንፃዎችን በሁለት ክሩዝ ሚሳይሎች መምታትን ስለምን እንደመረጡ ይተነትናል፡፡

ጎልዮቱ በተጨማሪም በ1993 ነዋሪነታቸው ለንደን የሆነው የቀድሞው ኢራቅ ጠቅላይ ሚኒስቴር ልጅ CIA ሌላው ቀርቶ የጠንሳሾቹን ስም ዝርዝር ለሳዳም አሳልፎ በመስጠት በሳዳም ላይ የተካሄደውን መፈንቅለ መንግስት እንዲከሽፍ አድርጓል ማለታቸውን በመጥቀስ አብዶቱን ይጨምራል፡፡ ይህ ሃሰተኛ ወሬ ከእውነታው ያፈነገጠ ቢሆንም አብዛኞቹ የኢራቅ ወታደራዊ ባለስልጣናት እውነታነቱን አምነው ተቀብለውታል፡፡ እናም እነርሱን የስራችን ተባባሪ እርጐ መመልመሉንም የማይቻል ሊያደርግብን ይችላል፡፡

እናስ ሳዳምን በስልጣን በማቆየት የምናተርፈው ምንድነው? ሳዳም ለደህንነታችን ስጋት ወረራ ሊፈፅሙብን ይችላሉ በሚል በጎረቤት ሀገራት ዘንድ ፍርሃት ያሳደሩ ሰው ናቸው፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ ሳዳምን የባህረሰላጤውን ፀጥታ ለማስከበር ትፈልጋቸዋለች፡፡ የአካባቢው አረብ ሃገራት የሳዳምን ስም በመስማት እናታቸውን እንደሚፈልጉ ቡችሎች ከጉያዋ እንዲሻጡ ትሻለች፡፡ የባህረሰላጤው አረብ ሃገራት ለዚሁ የዩናትድ ስቴትስ ከለላ የሚከፍሉት ክፍያ የንዳጅ ዋጋን አያንረውም፡፡ ይህ ሁሉም ለኢራቃውያኑ ፍፁም የሆነ ትርጉም የሚሰጥ ነገር ነው፡፡

እናም እኛም ይህን የሴራ ጎልዮት ከመጋፈጥ ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበረንም፡፡ «ሳዳም እንዲወገዱ እንፈልጋለን፡፡ በስልጣን እንዲቆዩ ያደረጋቸው የኢራቅ ህዝብ ነው» ስል አስረግጬ ተናገርኩ፡፡

ጄኔራሉ ምላሼን ለአፍታ ካጤነው በኋላ እኔን ከማመን ውጪ ምርጫ እንደሌለው በማወቁም «ወደደጅ እንውጣ» አለኝ

መንገዱን ይዘን ቁልቁል 20 ያርድ እንደተጉዋዝን ጄኔራሉ ፊቱን ወደኔ አዞረ፡፡

«እኔ ወደሰሜን እንድመጣ የተደረግኩበት ምክንያት ሳዳምን የማስወገድ እቅድ ባለው የወታደራዊ ባለስልጣናት ቡድን ተመርጬ ነው» ሲልም የሰማው ሰው ስላለመኖሩ እርግጠኛ ለመሆን አካባቢውን እየቃኘ በሹክሹክታ ተናገረ፡፡ «ሃገራችሁ ከጎናችን እንደምትሰለፍ ለማወቅ እንፈልጋለን፡፡»

ለአንድ ደቂቃ ያህል የተናገረው የገባኝ መሆኑን ለማወቅ በትኩረት ሲያየኝ ቆየ፡፡ ላቋርጠው ባለመፈለጌ የሰጠሁት ምላሽ አልነበረም፡፡

«ሌላም ሁለተኛ ጥያቄ አለን፡፡» ሲልም ንግግሩን ቀጠለ ስልጣኑን እንደተረከብን ዩናይትድ ስቴትስ ዲፕሎማቲካዊ እውቅና ልትሰጠን ይገባል አሊያ ግን ለስልጣን ሹኩቻ ሲባል የእርስ በርስ ጦርነት ይፈነዳል፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

ጄኔራሉ የፈለገውን ለማለት ስልጣኑ ነበረው፡፡ ርግጠኛ መሆኑ ቢበዛበትም የዩናይትድ ስቴትስን ድጋፍ ለማግኘት ግን የሚያበቃው አልነበረም፡፡ ይሁንና «በዚህ ኩዴታ ውስጥ ማን ማን እንደሚሳተፍና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የቀሽንግተን መንግስት በዝርዝር ማወቅ ይፈልጋል፡፡» አልኩት፡፡

ጄኔራሉ እጁን አንስቶ ንግግሬን እንዳቋርጥ በማድረግ «መጀመሪያ ከዋሽንግተን ምላሽ አግኝልኝና ከዛ በኋላ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ መነጋገር እንችላለን፡፡» አለኝ፡፡

ከከተማይቱ ዳርቻ እንደደረስን የመልስ ጉዞአችንን ማድረግ ጀመርን፡፡ ጄነራሉ ከቱርክ ጦር አዛዥ ጋር አንካራ ውስጥ ለመገናኘት ቀጠሮ ነበረው፡፡ ከድንበሩ ባሻገር የቱርክ ሄሊኮፕተር እየጠበቀችው ናት በዚህ ቀጠሮው ለቱርኮቹ ስለመፈንቀለ መንግስቱ ሊነግራቸው አቅዷል፡፡

«ጥያቄዎች እያሉህ ትህትናህ እመዝኖ ሳትጠይቀኝ ቀርተህ ይሆናል፡፡» ሲል የመልስ ጉዟችንን ስናደርግ ተናገረ «አዎን! የምናደርገውን ካልተሳካ ደግሞ የሚጠብቀንን ቅጣት ጭምር እናውቃለን፡፡

«የሳዳምን የደህንነት ጥንካሬ በቅርበት የማውቀው ነው፡፡ በጦርነቱ ወቅት ሳዳም ፊት ቀርቤ ሶስቴ ወታደራዊ ማብራሪያ ሰጥቻለሁ፡፡ ለመሆኑ እኔም ሆንኩ ማንም ሌላ ሰው ከሳዳም ጋር እንደምን እንደምንገናኝ ታውቃለህ? ከባግዳድ ጎዳናዎች ማዕዘን ወደአንዱ ሄደህ እንድትጠባበቅ ይነገርሃል፡፡ ጥበቃው እስከ ሶስት ሰዓት ሁሉ ሊፈጅብህ ይችላል፡፡ ከዛ አንድ መኪና ወዳለህበት መጥቶ ይቆምልሃል፡፡ ገብተህም ከመኪናው ወለል እንድትተኛ ይነገርሃል፡፡ ምንም ነገር ማየት እንዳትችል በብርድ ልብስ ትሸፈናለህ፡፡ መኪናውም እዛው ባግዳድ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ሲዟዟር ይቆያል፡፡ ያኔም የት እንደሆንክ የምታውቀው ነገር አይኖርም፡፡ በመጨረሻም ሳዳም አንተን ወደሚጠባበቁበትና ምናልባትም ለዛ ግንኙነታቸው ብቻ ወደተዘጋጀው ተራ ቤት ትወሰዳለህ ግንኙነታቸሁም ሲቋጭ ባመጣህ መኪና በመጣህበት መልኩ እንደትወሰድ ትደረጋለህ፡፡ በዚህም አካባቢውን መለየት ሳትችል ትቀራለህ፡፡ አዎን! የሳዳም ደህንነት አጥር እጅግ እጅግ ጥብቅ ነው፡፡ ግን ቀዳዳው ምኑ ጋር እንደሆነ እናውቃለን፡፡ እመነኝ የምናደርገውን እናውቃለን፡፡»

ጄኔራሉ ሊሄድ ሲል የመኪናውን መስኮት ዝቅ አርጎ አንድ የመጨረሻ ቃል ተነፈሰ፡፡

«ከዋሽንግተን የምንሻው ግለፅነትን ብቻ ነው፡፡ የሳዳምን መወገድ መፈለግ አለመፈለጋቸውን ማወቅ ይኖርብናል ሌላ የምንፈልገው ነገር የለም፡፡ ከአንካራ በሁለት ወይም በሶስት ቀናት ውስጥ እመለሳለሁ፡፡ ያኔ የጥያቄያችንን መልስ ይዘህ እንደማገኝህ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡»

ቤት እንደገባሁ ጄኔራሉ የነገረኝን ሁሉ ለጠቅላይ መምሪያው አስተላለፍኩ፡፡

☼☼☼



t.me/OLDBOOKSPDF

የጄኔራሉ ዝርዝር መረጃ ያልያዘ መልዕክት ብዙ ርቀት እንደማይጓዝ ባውቅም ከኢራቅ ጦር ከድቶ መውጣቱን ዋሽንግተን በጥልቀት እንደምትመረምረው አውቃለሁ፡፡ ጄኔራሉ ከጦርነቱ መባቻ በኃላ ጦሩን የከዳ የመጀመሪያው ከፍተኛ ማዕረግ ያለው ሰው ባይሆንም ከፍተኛ የፖለቲካ ዕርከን ከተቆናጠጠ ክዩፍሬት ቤተሰብ የተገኘ ሰው ነበር፡፡ ከምንም በላይ ሳዳም ከተገኙባቸውና በስልጣን እንዲቆዩ ካደረጓቸው የሱኒ ሙስሊሞች የተገኘ ሰው መሆኑ ለነገሩ ክብደት ይሰጠዋል፡፡ ሱኒዎች ከኢራቅ ህዝብ 20 በመቶ ቢሆኑም የጦር ሃየሉን መቆጣጠር ችለዋል፡፡ ጠንካራ የደህንነት ኃይልም መስርተዋል፡፡ ምንም ዓይነት ታንክ አውሮፕላን ወይንም ከአንዱ ኩባንያ የበለጠ የመንግስት አካል ለሳዳም ያለው ታማኝነት ፍፁም ከሆነ አንድ የሱኒ ባለስልጣን ይሁንታ ውጭ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡ ያለ ሱኒዎች ድጋፍ ሳዳም ለአንድ ቀን በስልጣን ላይ መቆየት አይችሉም፡፡ ለዚህም ነው የጄኔራሉ መክዳት በሳዳም ጎራ ፍራቻ እንዲነግስ የማድረጉ ምልክቶች እንዲታዩ ያደረገው፡፡

ቀደም ሲል ሳዳም ጦሩ ውስጥ የሚደረጉ መክዳቶችን በቸልታ ሲያልፉ ቢቆዩም ጄኔራሉ ህዳር 8 ጦሩን ከከዳ በኃላ ጄኔራሉን አድኖ የሚገድል ቡድን አቋቁመዋል፡፡ ለከፍተኛ የጄኔራሉ ጎሳ መሪዎች አባላት የጄኔራሉን በሃይማኖት ደረጃ ከህዝቡ መገለል እንዲያውጁ አድርገዋል፡፡ እንዲህ በማድረጋቸውም የጄኔራሉ ተከታዮች በህዝቡ ዘንድ ቦታ እንደሌላቸው ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ዋናው ፍራቻቸው ግን ጄኔራሉ ከጥቅል ስልጣናቸው ቋጠሮውን እንደፈታች አንዲት የነተበች ክር ተደርጐ እንዳይወሰድ ነበር፡፡

የዋሽንግተን መንግስት ግልበጣውን ባይደግፈውም የሳዳም አገዛዝን ፅኑነት ዳግም መፈተሽ እንደሚኖርብን አውቂአለሁ፡፡ የመንግስቱ ፅናት የሆነው የሱኒ መሰረት እየተሸራረፈ ይሆን? የጄኔራሉ ቃል እንዳለ አምኖን መቀበል ባንችልም CIA የጄኔራሉን መረጃ ተአማኒነት የሚያጣሩ ታማኝ የመረጃ ምንጮች ኢራቅ ውሰጥ ሊኖሩት ይገባል፡፡ እነዚህ የመረጃ ምንችጮችም እዛው ኢራቅ ውስጥ ከሚኖሩና ከወታደራዊ ባለስልጣናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሱኒዎች መሆን ይኖርባቸዋል እጅግ በርካታ ህዝብና ከግማሽ ሚሊዮን የበለጡ ጥምር ኃይላት ፀረ-ሳዳም ጦርነት ከከፈቱ ከሶስት ዓመታት በኃላ እንኳን በ1995 CIA ኢራቅ ውሰጥ የጄኔራሉን መረጃ የሚያጠናክር ወይም ቀርሽ የሚያደርግ አንድ የመረጃ ሰራተኛ እንኳ ማግኘት ሳይችል ቀርቷል፡፡

CIA በሃገሪቷ ውሰጥ ብቻም ሳይሆን እንደ ኢራን ዮርዳኖስ ቱርክ እና ሳዑድ አረቢ ባሉ ተጎራባች ሃገሮች ሳይቀር አንድ ሰብዓዊ የመረጃ ምንጭ አልነበረውም እንደተቀሩት የዩናይትድ ስቴትስ አካላት ሁሉ የመረጃ ድረጅቱ በኢራቅ ጉዳይ ላይ አይናማ አልነበረም፡፡ የጄኔራሉ መረጃ ተአማኒነት በሌላ መንገዶች ተጣርቶ በጥንቃቄ ሊመረመር ይገባ ነበር፡፡

የመንግስት ግልበጣውን ከጠነሰሱት ወታደራዊ ባለስልጣናት ፊት ለፊት ተገናኝተን ስለሆኔታው ከአንደበታቸው መስማት ቢኖርብንም ያን ማድረጉ የሚቻለን አይሆንም፡፡ ኢራቅ በCIA አጠራር ክልክል ቀጠና ናት፡፡ CIA ማንኛውንም የመረጃ ሠራተኛ በሳዳም ቁጥጥር ስር ወዳለው ግዛት ማስረግ ባለመቻሉ ከአገሪቱ ጋር የሚፈፅመውን ግንኙነት በሶስተኛ ወገን በኩል መፈፀም ነበረበት፡፡ የኢራቅ ወታደራዊ



t.me/OLDBOOKSPDF

ባለስልጣናት ሰሜናዊውን የኩርዶች ይዞታ ጨምሮ ከኢራቅ ውጭ ወዳለ አገር መሻገር የማይፈቀድላቸው በመሆኑ የግንኙነቱ ስኬት ሊወሰን የሚችለው በሶስተኛው ወገን ጥንካሬ ነው፡፡ አንድ ባለስልጣን ደግሞ መሰሉን ድርጊት ሲፈፅም ቢያዝ በአሲድ መታጠብ እጣ ፈንታው ይሆናል ውጤቱም ነፍሱን አትርፎ ውሎው ከአሰቃቂና አስፈሪ ፊት ጋር ከቤቱ እንዲውል ያደርገዋል ያም ማለት ሳይታይ ወደሃገሪቷ በሚገባና በሚወጣ መልዕክተኛ ግንኙነቱን መፈፀም አለብን ማለት ይሆናል፡፡ መፍትሄው ፍፁም አይደለም ሁኔታው በአንድ ትንፋሹ በሚቆራረጥ የትዕይንት ተራኪ የታጀበ አንድን በመድረክ ጉንና ጉን የሚካሄድ ትወናን የመከታተል ያህል ቢሆንም ያን ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረንም፡፡

☼☼☼

የጄኔራውን እቅድ ለጠቅላይ መምሪያችን ባስተላለፍኩ በሳምንቱ «ይህ እቅድ አይደለም» የሚል ባለሶስት ቃላት ምላሽ ከመምሪያው አገኘሁ፡፡

ምላሹ የተሰጠኝ በኢራቅ ጉዳይ ላይ ከኔ ጋር ከሚሰራ ባለስልጣን መሆኑ ገብቶኛል፡፡ ይህ ባለስልጣን ደግሞ ባህር ማዶ ወጥቶ የሚያውቀው ከ25 ዓመታት በፊት በቬየትናም ጦርነት ጊዜ ለዓመት ብቻ የነበር ሲሆን መካከለኛውን ምስራቅ ረግጦት አያውቅም፡፡ ቢሆንም ቅሉ የጠቅላይ መምሪያው ምላሽ ዱብ እዳ ሆኖብኛል፡፡ ምላሹም ተጨማሪ ማብራሪያ ካለመጠየቁም በላይ ለጉዳዩ ማበረታቻ አልቸረውም፡፡ ያም CIA በኢራቅ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰላዮች እንዳሉትና ያለ እውቅናው ሃገሪቱ ላይ ዝር የምትል ወፍ እንደሌለች ያስመስላል፡፡

በሚቀጥለው ቀን ጄኔራሉን ለማግኘት ውስብስብ ጭቃማ መንገዶችን ይዤ መሃል ሳላህ አል ዲን ውስጥ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቱ አቀናሁ፡፡ በጄኔራሉ መኖሪያ ያሉ እቃዎች አሰዳደር የተበታተኑ ስለነበር ጄኔራሉ ቤተሰቦቹን ይዞ ወደሰሜን ያቀናው መያዝ የሚችለውን እቃ ብቻ ይዞ የነበረ ይመስላል፡፡ ወለሉ ላይ እግሮቻችንን አቆላልፈን ተቀምጥን ባለቤቱ ሻይ ስታቀርብልን ልጆቹ ከበስተኃላችን ካለው በር ሆነው ሁኔታችንን ይከታተሉ ነበር፡፡ የጠቅላይ መምሪያውን ምላሽ ለጄነራሉ መናገሩ ትርጉም የለሽ እንደሚሆን አሰቤያለሁ፡፡ ምላሹን ብነግረው አይረዳኝም፡፡ ካልተረዳኝ ደግሞ ምስጢሩን አያጋራኝም ከምላሹ የተረዳሁት ነገር ቢኖር የዋሽንግተን መንግስት የመንግስት ግልበጣውን ከማጣጣል ይልቅ በመንግስት ግልበጣው የሚሳተፉ የባለስልጣናትን ስም ዝርዝር ጉዳዮች እንዲገለፁለት የሚፈልግ መሆን ነበረበት፡፡

ለጄነራሉ ከጠቅላይ መምሪያው መንግስት ግልበጣውን የተመለከተ ምላሽ እንዳልተሰጠኝ ስነግረው አንዳች አስፈሪ ስሜት ፊቱ ላይ አነበብኩኝ፡፡ ምስጢራዊው ኮሚቴ መልዕክቱ በ24 ሰዓት ውስጥ ምላሽ ያገኛል የሚል እምነት እንደነበረው ነገረኝ፡፡ ምላሹን ፍለጋ መልዕክተኞች በየምሽቱ ድንበር ተሻግረው ይመጡ እንደነበረ አጫወተኝ፡፡ ጄኔራሉ የዋሽንግተን መንግስት በዚህ አንገብጋቢ ጉዳይ ላይ በሰዓታት ልዩነት ምላሽ መስጠት አለመቻል የሚዋጥለት አልሆነም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የንግግራችንን አርዕስት ለመቀየር በማሰብ በስሜት ግዛት ስላለው ሁኔታ ተነጋገርን ከትምህርት ቤታቸው ስለወጡት ልጆቹና ስላለበት የምግብ እጥረት ችግር ተጨዋወትን እናም ከቤቱ ለመውጣት ስነሳ ጄኔራሉ እንድቆይ ምልክት ሰጠኝና «ይህን ወደ ዋሽንግተን አስተላልፈው፡፡»

ጄኔራሉ መከፈት ያልፈለገውን በር መክፈት መፈለት ስለመንግስት ግልበጣው ዝርዝር ጉዳዮች ሊነግረኝ መወሰኑ ታወቀኝ ግምቴ ትክክል ከሆነ ጄኔራሉ ከዚህ በኋላ ማፈግፈግ አይቻለውም እርሱና ግብረ አበሮቹ የሆኑት የምስጢር ኮሚቴው አባላት የ1993 ቱን መንግስት ግልበጣ ከሀደት በመፈፀም እንዲከሽፍ ያደረገው CIA እንዳልሆነ በማመን እጣፈንታቸውን በእጃችን ላይ ያኖራሉ፡፡ የዋሽንግተን መንግስትን ቀልብ ለመሳብ መሰሉን አደጋ ከመጋፈጥ ውጭ ምርጫ እንዳልነበራቸው ሆኖ ታይቶኛል፡፡ ሰዎቹ በፀረ-ሳዳም እንቅስቃሴአቸው ለመግፋት የዋሽንግተንን ይሁንታ ማግኘት እንዳለባቸው አምነዋል፡፡ እናም ልክ ነበርኩ ጄኔራሉ የ CIA'ን ድጋፍ ለማግኘት እንደኩኩ መለኮቱ መዘመር ይጠበቅበታል፡፡

✲✲✲

የመንግስት ግልበጣው የጀርባ አጥንት የሆኑት ሶስቱ የካበተ የውጊያ ልምድ ያላቸው ክፍለ ጦሮች ማለትም 76ኛው ብርጌድ 15ኛው የእግረኛ ክፍለጦርና 5ኛው ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር ነበሩ፡፡ እንደጄኔራሉ ገለፃ ክፍለጦሮቹ ከሳዳም ታማኝ ክፍለ ጦሮች በተለይም የሪፓብሊካን ዘብ ከተሰኘውና ሳዳምን በመንበራቸው ጠብቆ ካቆየው ክፍለ ጦር የሚጥማቸውን መልሶ ማጥቃት መቋቋም የሚያስችላቸውን ጦር መሳሪያ ታጥቀዋል፡፡ እርግጥ ክፍለ ጦሮቹ የተቀናጀውን የሪፐብሊካን ዘብ ክፍለ ጦሮች ጥቃት መቋቋም እንደማይችሉ ቢያስቡም ታማኝ ክፍለ ጦሮቹ ትንጅት ፈጥረው ጥቃት ከመክፈታቸው በፊት ሳዳምን ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡ እቅዱ እንደ መብረቅ አባርቆ እንደነጎድጓድ መክሰት ሲኖርበት መቋጨት ያለበትም ማንም አፀፋዊ እርምጃ መውሰድ ከመጀመሩ በፊት ይሆናል፡፡

ለመንግስት ግልበጣው ስኬት አስተዋፅኦ የሚኖረው ሌላው አራተኛ አካል ከቲክሪት ወጣ ብሎ ካለው ሰፍራ የሚገኘውና ከሳላህ አል ዲን ጦር ትምህርት ቤት ጋር ተያያዞ የተሰራው የታንክ ማሰልጠኛው ኩባንያ ነው፡፡ የማሰልጠኛው አዛዥ መንግስት ግልበጣውን በቁንጮነት ይመራል አዛገዙ የምስጢራዊው ኮሚቴን ትእዛዝ እንዳገኘ ከትምህርት ቤቱ አስራ ሁለት ታንኮችን ከነአጃቢዎቻቸው በመውሰድ 'አውጃህ' ወደሚገኘው የሳዳም መኖሪያ እንዲሰማሩ ያደርጋል፡፡ የሳዳም መኖሪያን በመከበብም ሌሎቹ ሶስቱ ክፍለ ጦሮች ደርሰው መንግስት ግልበጣውን ከመክሸፍ እስኪታደጉት ሽፋን ይሰጣል፡፡

ከቲክሪት በስተምስራቅ የምትገኘው የአውጃህ መንደር የሳዳምን ማጥመጃ ተደርጋ የተወሰደችው ኢራቅ ውስጥ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ሳዳም መሸሸጊያ አርገው እንደሚጠቀሙባት ስለሚታወቅ ነው፡፡ ሳዳም ከተወለዱባት የአውጃህ መንደር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሰላላቸውና ወደስልጣን ከመጡ በኋላም ከመንደሪቷ ዳርቻ በሚገኝ ስፈ መሬት ላይ ዘመናዊ መኖሪያ ቤት የገነቡ ሲሆን የኮሚቴው እቅድ ከአውጃህ ራቅ ካለ ስፍራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምናልባትም ባግዳድ ውኸርንብር በመንዛት ኮሎኔሉ በመንደሪቷ ጎዳናዎች ላይ ታንኮቹን ከማስማራቱ አስቀድሞ ሳዳም ከስፍራው እንዲደርሱ ማድረግ ነበር፡፡ ምንም እንኳ ኮሚቴው ውዥንብሩ ሲነዛ ሳዳም ወደእውጃህ እንደሚያቀኑ በጥሩ መልኩ ቢያመላክትም መፈንቅለ መንግስቱን ሊያከሽፍ ስለሚችል አንድ እድል ግን ጊዜ ወስዶ አሳስበበትም ነበር፡፡ ይኸውም ሳዳም ወደ እውጃህ እንዲቀኑ በሳዳም የደህንነት ሃይል ውስጥ ያለ የመረጃ ምንጭ የመንግስት ግልበጣውን ጠንሳሾች ማንነት ይፋ ሊያደርግ እንደሚችል ነበር፡፡

ለመንግስት ግልበጣው ስኬት ቁልፉ ግልበጣው ምስጢራዊነቱን የመጀመሪያዋ ጥይት እስክትተኮስ የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህም ሳዳም እውጃህ ውስጥ ኢላማ እንደሚሆኑ እንዳይጠረጥሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ያን ለማድረግ ደግሞ የኮሚቴው አባላት ቤተሰቦቻቸው ስለመንግስት ግልበጣው ያላቸው እውቀት ውሱን እንዲሆን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ሁሉም የምስጢራዊው ኮሚቴ አባላት እና የአራቱ ክፍለጦሮች አዛዦች በደም የተሳሰሩ ሲሆን አብዛኞዎቹም የመጀመሪያ የአክስት ልጆች ናቸው፡፡

«ወዲያውኑ ላይከሽፍም በዛሬይቱ ኢራቅ ውስጥ መቆየት የሚችል ብቸኛ ሴራም ያ ነው፡፡» አሉኝ ጄኔራሉ፡፡ ከዚህም በላይ በእውጃው ጥቃት እንደሚሳተፉ የሚጠበቁት አብዛኞቹ ወታደሮች ከሹማር የጎሳ ጥምረት የተውጣጡ ይሆናሉ የተባበሩት መንግስታት በኢራቅ ላይ የጣለውን ማዕቀብ ተከትሎ የታየው የአገሪቱ መዳከም ጥንታዊ የጎሳ ትስስሮሽ ለመንግስት ታማኝ የሆኑ ጎሳዎችን እየተኩ እንዲሄዱ አድርጎአቸዋል፡፡

በኮሚቴው ምልከታ የእቅዱ ምስጢራዊነት እስኪተጠበቀና ሊላ ተቀናቃኝ ሃይል ጣልቃ እስካልገባ የኮሎኔሉ ታንኮች በ20 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ እውጃህ ይገባሉ፡፡ ለጥቆ ባሉት ከ10 እስከ 20 በሚደርሱ ደቂቃዎች ሌሎቹ ክፍለ ጦሮች ደርሰው በሳዳም ላይ ከበባ ይፈፅማሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ሳዳም ያላቸው ምርጫ እጅ መስጠት ይሆናል አሊያም ታንኮቹ የመኖሪያቸውን አጥር ደርምሰው ይገባሉ ከዚያም ሁሉም ነገር ከአንድ ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፍፃሜውን ያገኛል፡፡

☼☼☼

ቀጥለው ባሉት ሁለት ሳምንታት ጄኔራሉ የአራቱን አዛዦችና ምክትሎቻቸውን ስም ዝርዝር ሰጡኝ የቤተሰቡን የትውልድ ሀረግ በዛፍ ግንድ ዝንጣፊ በመሳል ባለስልጣናቱ ያላቸውን የደምትስስር ዝምድና አስረዱኝ፡፡ የወታደራዊው ሽግግር መንግስት ባለስልጣናት የሚሆኑትን ሰዎች ስምም ነገሩኝ፡፡ ስማቸውን ከነገሩኝ ሶስቱ ስለመንግስት ግልበጣውም ሆነ በመንግስት ባለስልጣንነት እንዲያገለግሉ ስለመመረጣቸው እንደማያውቁ አጫወቱኝ፡፡ ሰዎቹ ኮሎኔሉ በእውጃህ ጎዳናዎች ላይ ታንኮቹን እስከሚያሰማራ ስለጉዳዩ እንዲያውቁ እንደማይደረግም አብራራልኝ፡፡ ይህ ሁሉ መረጃውን ለመከፋፈል እና የመንግስት ግልበጣውን ምስጢራዊነት ለመጠበቅ የታቀደ ነው፡፡

ከጄኔራሉ ጋር ከምናደርገው ከእያንዳንዱ ቆይታ በኋላ ለጠቅላይ መምሪያው መልዕክት እስተላልፍ ነበር፡፡ የመንግስት ግልበጣው ቁልፍ ተዋናዮች ስም ዝርዝር ለCIA ጠቅላይ መምሪያ አዛዦች የተላለፈላቸውና እነሱም በመዝገባቸው ያኖሩት ቢሆንም



t.me/OLDBOOKSPDF

መንግስት ግልበጣውን በተመለከተ ግን ማድረግ ስለሚፈልገው ነገር የዋሽንግተን መንግስት አቋሙን አሳሳወቀም፡፡

☼☼☼

የእሰቃዬ ዝምታ ተሰፋ ያስቆረጠው ጄኔራል በወርሃ የካቲት መባቻ ቤታችን መጣ፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ ተገናኝተን በነበረበት ወቅት ግልበጣው በሚካሄድበት ቀን ዩናይትድ ስቴትስ ግልበጣውን መደገፏን ለማሳየት አንድ ተዋጊ አውሮፕላን በባግዳድ አየር ላይ እንዲበር እንድታደርግ ጠይቆኝ ነበር፡፡ በወቅቱ ጥያቄውን ለእሰቃዬ ማስተላለፏ አሳስጨነቀኝም ዋሽንግተን ለመንግስት ግልበጣው ዕውቅና ባልሰጠችበት ሁኔታ አየር ኃይሏ በኢራቅ ክልል እንዲበር ማድረጓ ግን የማይመስል ነገር ነው፡፡

ሻይ ከቀረበልን በኋላ በተለመደው ዝምታችን ተውጠን ቆየን፡፡ ለጥቆም ጄኔራሉ ፊቱን ወደኔ መልሶ እጄን ክንዴ ላይ ጣል አድርጎት፦

«ኩርዶች ሁሉን ነገር እንዳልነበረ ሊያደርጉብን ነው፡፡ ስለዚህ የሰላም ስምምነት እንዲፈራረሙ ብታደርጉ ስምምነቱ ዩናይትድ ስቴትስ የሳዳም መወገድ ቁርጠኛ አቋሟ መሆኑን ሊያሳይላት ይችላል፡፡» አለኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፲፬

## መጋቢት 3/1995፣ ሳሳህ አል-ዲን-ኢራቅ

ጄኔራሉ ያመጣው ሃሳብ ወሳኝ ነበር፡፡ ኩርዶች በመፈንቅለ መንግስቱ ባይሳተፉም እቅዱ በእንጭጩ እንዲቀጭ የማድረግ አቅሙ አላቸው፡፡ በወርሃ የካቲት አጋማሽ የእርስ በርስ ጦርነታቸው መላውን ሰሜናዊ ኢራቅ ያዳረሰ ሲሆን ጦርነቱ ኢራንንና ቱርክን ጣልቃ ለመግባት እንዲዘጋጁ ሲያደርጋቸው ሳዳም ከኩርዶቹ ግዛት ለመዝለቅ የሚያደርጉትን ግስጋሴ ኩርዶቹ መቋቋም እንዲሳናቸው አድርጓቸዋል፡፡

እንደሚታወቀው ደግሞ የኩርዶቹ ጦርነት መሠረት በጊዜ በታሪክና በባሕርያቱ ይለያያል፡፡ ጥንታዊዎቹ ልዩነቶቻቸው ደግሞ በ1995 ዋነኛ ተቀናቃኞች የሆኑትን ሁለቱን የኩርድ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኬ.ዲ.ፒ) እና የኩርድ አርበኞች ህብረት (ፒ.ዩ.ኬ) የተሰኙ አንጃዎችን ወልደዋል፡፡ አንጃዎቹም በአልበገር ባይነት እርስ በዕርሳቸው ተፋልመዋል፡፡ ማንኛውም አንጃ ደግሞ በሰከነ አዕምሮ ሰላም ለማውረድ ሲባል እንደሚወሰነው በመወሰን ፈንታ ጦርነታቸውን ሰብቀውበታል፡፡ ከዚህ ሁሉ የከፋው ደግሞ ሁለቱም ወገኖች ተስፋ በቆረጡ ጊዜ በ1988 በጅምላ ጨራሽ መሣሪያ በሽዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ኩርዶችን የጨፈጨፉትን ሳዳም እና የተናቀውን ጦራቸውን በሰሜኑ ግዛት ጣልቃ እንዲገቡ መጋበዛቸው ነበር፡፡

በኩርዶቹ በኩል ለሳዳም የሚቀርብ ማንኛዋም ግብዣ ደግሞ ለመንግስት ግልበጣው ጠንሳሾች አደጋ አለው፡፡ ምክንያቱም ግዳጁ የተሰጣቸው የኢራቅ ወታደሮች ወደኩርዶቹ ሊሰርጉ መቻላቸው ሳዳም ፊጣንና በማያዳግም መልኩ በአካባቢው የሚታዩ ማንኛቸውንም አለመረጋጋትና የአመፅ ፍንጮችን መጨፍለቅ ያስችላቸዋል፡፡ ጄኔራሉ ከጅምሩ ኮሚቴው የኩርዶቹን ግጭት ጋብ ማለት እንደሚፈልገው ቢነግረኝም አሁን ግን ግጭቱ ከሚያካሂዱት መፈንቅለ መንግስት በላይ አሳሳቢ ሆኖባቸዋል፡፡ ለአንድ ቀንም ቢሆን የኢራቅ ወታደሮች ወደሰሜናዊው ግዛት መመለስ ሳዳምን የማይቀለበስ ድል ባለቤት እንዲሆኑ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ያም ከሆነ ታዲያ ኢራቃውያን የሴራ ኃልዮቱን በመጥቀስ ዩናይትድ ስቴትስ ሳዳም እርምጃ እንዲወስዱ ምስጢራዊ የማስጠንቀቂያ መልዕክት እንዳስተላለፈችላቸው ሆኖ ይሰማቸዋል፡፡ እነሱም አሜሪካውያን የሳዳምን በስልጣን መቆየት ይፈልጉታል የሚል እምነታቸውን ያስረግጥላቸዋል፡፡

እኛም እውነታውንና ለግምቶቹ ሰበብ የሆነውን መንስኤ ወደጎን ትተን ሳዳም ከስልጣን እንዲወርዱ ቢደረጉም ቀሪው የቤት ስራ የሚሆነው የኢራቃውያኑ እንጂ የኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

አለመሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ለዚህም ዋጋ ያላቸው እነሱ እንጂ እኛ ለጉዳዩ ያለን አመለካከት አይደለም ዩናይትድ ስቴትስ የሳዳምን በስልጣን መቆየት በምስጢር እንደምትደግፍ ካመኑ ከሳዳም በተፃራሪ ጎራ ለመሰለፋቸው ትርጉም አይሰጡትም፡፡

☼☼☼

እናም በሁኔታው ተስፋ የቆረጡት ኩርዶች ብቻ ሳይሆኑ እንደማንኛውም ሰው ሁሉ አህመድ ቻላባይንም የሁኔታው ተለዋዋጭነት አሳስቦታል፡፡

ቻላባይ መቀመጫቸውን ሳላህ አል ዲን ውስጥ ያደርጉ ተቃዋሚ ድርጅቶችን በጥላው ስር ያሰባሰበው የኢራቅ ብሄራዊ ኮንግረስ መሪ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ አግኝቼው የነበረው በ1994 ዋሽንግተን ውስጥ የነበር ሲሆን በወቅቱ ፈፅሞ ሳዳምን ከስልጣን የማስወገድ እንቅስቃሴ ላይ ሚና ያለው ሰው አይመስልም ነበር፡፡ በጊዜው የሳቪለሮው ሱፉን ለብሶ 150 ዶላር የሚያወጣ ስሪቱ የኢጣሊያ የሆነ የሃር ከረባት አስሮና ከጥጃ ቆዳ ተሰርተው በእጅ የተሰፉ መጫሚያዎቹን ተጫምቶ ማሪዮት ድልድይ ሲያቋርጥ ሳየው አንድን ስኬታማ የባንክ ሰራተኛ እንጂ በታንክ ላይ ተፈናጦ ወደ ባግዳድ የሚያቀና አርበኛ አይመስል እንደነበረ አስታውሳለሁ፡፡ እናም አጠገቤ ደርሶ ሲጨብጠኝ የዕጅ ሽቶው አፍንጫዬን እንደሰነገው ትዝ ይለኛል፡፡

አንድ ቀን የኢራቅ ተቃዋሚዎች ስኬታማ መሪ እሆናለሁ የሚለው ህልሙ ቻላባይ መስሎ ከሚታየው ጋር ያልተጣጣመ ህልም ሆኖብኛል፡፡ ለዚህም ደግሞ የመጀመሪያው ምክንያቱ የሚሆነው ቻላባይ የሚገኝበት እናላ መደብ የሆነው የሺአ ሙስሊም ኢራቅን አስተዳድሮ የማያውቅ ከመሆኑም በላይ መሰሉን ስኬት በቶሎ መጎናፀፍ አለመቻሉ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያቱ ቤተሰቡ በ1958 የሃሼሚት ንጉሳዊ አገዛዝ መውደቅን ተከትሎ ወደሊባኖስ መሰደዱን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ነበር የ13 ዓመት ልጅ የነበረው ቻላባይ እድገቱን እዚያው በማድረግ የኢራቅ አነጋገር ዘዬውን በሊባኖስ አነጋገር ዘዬ የለወጠው ቻላባይ ይበልጡንም ዩናይትድ ስቴት ውስጥ ከሚገኝ የድህረ ምረቃ ት/ቤት በመግባት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማስትሬት ዲግሪውን በመስራትና ከቺካጎ ዩንቨርስቲ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የዶክትሬት ዲግሪውን በማግኘት የአሜሪካንን ዘይቤ ያለው እንግሊዘኛን መማር ችሏል፡፡ በኢራቅ ውስጥ ስለሚያደርገው የብሄርተኝነት እንቅስቃሴ የቱንም ቢልም ኢራቃውያን ቻላባይን የሚያዩት እንደ አንድ አገር የለሽ ስደተኛ ነው፡፡ በባንከኝነት ህይወቱም መጨረሻ ላይ ዮርዳኖስ ውስጥ ንብረትነቱ የራሱ የሆነውን የፔትራ ባንክ በ1989 የደንበኞቹን ተቀማጭ ገንዘብ የሆነን በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር በማክሰር ድቀት አጋጥሞት እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ለባንኩ ክስረትም ተጠያቂ የሆነው ሰው በርግጠኝነት በማይታወቅበት ሁኔታም ጉዳዩን ያየው የዮርዳኖሱ ችሎት ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ አውሎታል በሚል ቻላባይ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ አሳልፏል፡፡

እናም ቻላባይ በውጭው አለም በወንጀልኝነቱ የሚታወቅ ሲሆን በአገር ቤት ግን ምንም እውቅና አልነበረውም በማስረጃ አይደገፍ እንጂ ድርጊት አቃጅነቱ እንተሳታሽነቱና ተሞክሯቸው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴው በኢራቅ ብሄራዊ ኮንግረስ ውስጥ የሚፈፅማቸው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው አካል ናቸው፡፡ የኮንግረሱ የተሰባሰቡትን ተቃዋሚ ሃይላት



t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ እንደ ፀበኛ ድመቶች መውሰድ ይቻላል፡፡ ከሺአ ሃይማኖት አባቶች፣ ከቤዲዊን ጎሳ አለቆች፣ ከንጉሳዊ ቤተሰቦች፣ ከኮሚኒስቶች፣ ከቀድሞ ወታደራዊ ባለስልጣኖች፣ ከቀድሞ የባስ ፓርቲ ባለስልጣኖች፣ እና ከኩርድ ጎሳ አለቆች የተውጣጡት ተቃዋሚ ሃይላት ለሳዳም እንዳላቸው ጥላቻ ሁሉ እርስ በርስ ይጠላላሉ፡፡ ከዚህም በላይ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ከቻላባይ የበለጠ መሪ መሆን እንደሚችሉ አድርገው ያስባሉ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም የተቃዋሚ ሃይላቱ ቪየና ውስጥ ባደረጉት የ1992 ቱ ስብሰባቸው ቻላባይን የኢራቅ ብሄራዊ ኮንግረስ (አይ.ኤን.ሲ) ፕሬዝዳንት አድርገው የመረጡት ሲሆን ለሁለት አመታትም ይብዛም ይነስም የፕሬዝዳንትነት ሚናውን ሲወጣ ቆይቷል፡፡ ከዚህም አንዱ «የጨዋታው ፍፃሜ» የተሰኘውንና ለ1991 ሕዝባዊ መነሳሳት መሰረት የሆነውን አቋሙ የተንፀባረቀበትን ረቂቅም ዕቅዱ መንደፍ እንዳስቻለውና ይህ ዕቅዱም ሳዳምን ለማስወገድ ከሚደረድሩልን አሰልቺ ዕቅዶች ውስጥ የተለየ ዕቅድ እንደነበረም አስታውሳለሁ፡፡

☼☼☼

ዴቪድ ሊት በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የባህረሰላጤው ጉዳይ አስፈፃሚ ሲሆኑ በአመት አንዴ ወይም ሁለቴ ወደሰሜናዊ ኢራቅ በብላክ ሃውክ በተሰኘው ሄሊኮፕተር ይበራሉ እናም በአንድ ወቅት ላይ ጉብኝታቸው ላይ እንድገኝ ከሌላ ወገን ግብዣ ቀርቦልኛል.... እናም በዚህ ስብሰባ ላይ ለመገኘት በሩን አልፌ ወደ ውስጥ ስገባ እነሱ ስብሰባውን ጨርሰው ሊወጡ ሲሉ አገኘኋቸው ሌላው ቀርቶ ሰላምታ እንኳን አልሰጡኝም እናም እኔ ግራ በተገባ መንፈስ ሆኜ ቻላባይን ስጠይቀው አቶ ሊት ሁለት ስብሰባዎች ነበራቸው የመጀመሪያው ከታሊባን ጋር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከባርዛኒ ጋር ነበር፡፡» አለኝ ጀላል ታላባኒ የኩርድ አርበኞች ሕብረት (ፒ.ዩ.ኬ) መሪ ሲሆን ማሱድ ባርዛኒ ደግሞ የኩርድ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኬ.ዲ.ፒ) መሪ ነው፡፡

እናም «ሊት ኩርዶቹ ግጭቱን ያቁሙ አሊያ ግን አየር ሃይላችን ጣልቃ ይገባል ያሏቸው ይመስልሀል?» ስል ጠየቅኩት፡፡ ነገሩ ሳላህ አል ዲን ውስጥ አስገራሚ ወሬ እንደሚሆን ገብቶኛል፡፡

ቻላባይ በመንከትከት «ሊት ነግረዋቸዋል፡፡ አሜሪካ በኩርዶቹ መሃል ሰላም ለሚያስከብረው ሃይል ክፍያ ለመፈፀም ወስናለች፡፡ ጉዳዩን የምታስፈፅሙትም እናንተው ትሆናላችሁ፡፡ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ለዚሁ ኃይል የሚከፈል መሆኑን ሊት ቃል ገብተዋል፡፡» አለኝ፡፡

«የሚከፈለው የማን ገንዘብ ነው?» ስል ጠየቅኩት፡፡ ይኸውም ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሳያማክረን እንዴት ጣልቃ ይገባል ብዬ በማሰቤ ነበር፡፡

«የእናንተ የCIA' ዎች ገንዘብ ነው» አለኝ፡፡ ቻላባይ በሃሴት ተሞልቷል፡፡ የአሜሪካ መንግስት በራሱ እግር እየተደነቃቀፈ ሲራመድ ከማየት የበለጠ የሚያስደስተው ነገር የሌለ ሰው ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ያንዕለት ማታ ወደዋሽንግተን ብደውልም ስለ ሁለት ሚሊዮን ዶላሩ ጉዳይ የሰማ ሠው አላገኘሁም፡፡ ግን ከደወልኩ ከአንድ ሰዓት በኃላ ከጠቅላይ መምሪያው ተደወለልኝ፡፡ CIA ለጣልቃ ገቡ ሃይል ለመክፈል አለመስማማቱንና ያን ማድረጉ ፍፁም ህገ ወጥ መሆኑ ተነገረኝ፡፡ ጥፋቱ ግን ቀደም ሲል ተፈፅሟል፡፡ ኩርዶቹ በውጭ ጉዳይ መስሪያቤትና CIA መሃል ልዩነት ማድረግ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ሊት ቃል ገብቶላቸዋል፡፡ ዋጋውን ከፋዩም እኔው እሆናለሁ፡፡

☼☼☼

በጥቂት ሳምንታት ውስጥም ሊት ቃል ለገቡላቸው ሁለቱ አንጃዎች ከፍያ የሚሆን ገንዘብ አለመኖሩ ከታወቀ በኃላ ውጊያው ደገሞ አገረሸ፡፡ የታላባኒ ፒ.ዮ.ኬ ተዋጊዎች ጠመንጃዎቻቸውን ለውጊያ ዝግጁ አደረጉ፡፡ ቡድኑ ኬ.ዲ.ፒ ላይ አንድ የመጨረሻ ጥቃት ይከፍት ይሆናል ኢሊያም ያለችውን የመጨረሻ ሳንቲም ተጠቅሞ ለሳዳም ይደውልላቸዋል፡፡ ስለዚህ የሆነ ነገር መደረግ ነበረበት፡፡

«ጊዜ የለንም» ሲል አንድ ምሽት እራት ሰንበላ ቻላባይ ተናገረ፡፡ «ሊት ተቀባይነት አሳጥተዋችኋል፡፡ ከእንግዲህ በኩርዶች በኩል ያላችሁ ተሰሚነት እከትዋለታል፡፡ ለዚህ ሁሉ መፍትሂውም ሳይቀደሙ መቅደም ነው፡፡»

ቻላባይ ልክ ነበር የጀኔራሉ ምስጢራዊ ኮሚቴ ስላቀናበረው መፈንቅለ መንግስት ልነግረው ብፈልግም ብነግረው ይበልጥ ተስፋ እንደሚያስቆርጠው በማወቁ ሳልነግረው ቀረሁ፡፡

«ህዝባዊ ማንሳሳት ባደራጅ የዋሽንግተን መንግስት ምን የሚያደርገው ነገር የኖራል?» ሲል ጠየቀኝ፡፡ «የታላባኒን ጥቃት ማስቆም የሚቻለው በዚያ መልኩ ብቻ ነው፡፡» አለኝ፡፡

ዋሽንግተን ውስጥ በቻላባኒ ህዝባዊ ማንሳሳት ላይ እምነት የሚጥል እንድም ባለስልጣን እንደማይኖር ብሎም ኩርዶቹ እርስ በርስ ቢጨፋጨፉ ግድ የሚሰጠው ሰው እንደማይገኝ አውቃለሁ እንደውም የዋሽንግተን መንግስት ፍላጎት ኩርዶች የጋዜጦች አብይ ዜና እንዳይሆኑ ማድረግ ነበር፡፡ ኢራቅም ከቀዝቃዛው እረንቋ ተዘፍቃ ለረጅም ጊዜ በመቆየቷ የዜና ርዕስ ሳትሆን ቀርታለች ቢሆንም እሁንም አለቆቼ ቻላባይ ስለምን በእቅዱ እንዲገፋበት አይፈቅዱለትም? ብዬ ማሰቤን አላቆምኩም፡፡ የቻላባይ እቅድ ቢያንስ የዋሽንግተን መንግስትን የምስጢራዊው ኮሚቴን የመንግስት ግልበጣ እቅድን ዳግም እንዲያጤነው ይገፋፋው ይሆናል፡፡

እኔም ለምን «እቅድህን ነድፌህ ጥያቄህን አታቀርብም» የሚል ምላሽ ሰጠሁት፡፡

ቻላባይም ያልኩትን ፈፀመ በቀጣዩ ቀንም ህዝባዊ መነሳሳቱ መጋቢት 4 ኮምሽቱ 4 ሰዓት እንደሚቀጣጠል እና ታላባኒ እና ባርዛኒ በሰሜን ግንባር ተሰልፎ ባለው የኢራቅ ጦር ላይ በአነስተኛ መሳሪያ የታገዘ የደፈጣ ጥምር ጥቃት እንደሚከፍት ገልጮ ወደዋሽንግተን መልዕክቱን እንዳስተላልፍለት ጠየቀኝ፡፡ እያደዘም በተባለው እለት



t.me/OLDBOOKSPDF

የኩርዱ አምስተኛ ተዋጊ ክንፍ በኪርኩክ እና ሞውሲል አመፅ እንዲነሳ በማድረግ ኢራቅ ውስጥ ባሉ የመንግስት አገልግሎት ተቋማት ሁሉ ላይ ጥቃት እንደሚከፍት ነገረኝ፡፡ በተመሳሳይ ሰዓትም በደቡብ የሚገኙት የሺአ ተዋጊ ኃይላት በኢራቅ ጦር ላይ ጥቃት ይከፍታሉ፡፡ይህ በተፈፀመ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የኢራቅ ጦር በማመፅ ህዝባዊ መነሳሳቱን እንደሚቀላቀል በመግለፅ ቻላባይ ግምቱን አስቀመጠልኝ፡፡ እቅዱም «የጨዋታው ፍፃሜ» ከተባለው እቅዱ ጋር በጣም ይመሳሰል ነበር፡፡ ባርዛኒም ሆነ ታላባኒ በህዝባዊ መነሳሳቱ ለመሳተፍ መስማማታቸውን ባይገልፁለትም በተለይ የአሜሪካንን ድጋፍ ካገኘ ስለሁኔታው ነግሮ ሊያሳመናቸው እንደሚችል ቻላባይ ገልፆልኛል፡፡

የቻላባይ እቅድ የሚፈፀምበት ቀንና ሰዓትን የያዘ ወደዋሽንግተን የሚላክ መልዕክት ፃፍኩ፡፡ መልዕክቱን የፃፍኩት ረጅም ጊዜ ለጠበቀው «የጨዋታው ፍፃሜ» ለተሰኘው የቻላባይ እቅድ የዋሽንግተን መንግስት አስተያየት ምን እንደነበር እና ይህኛው እቅዱን በተመለከተ አቋርጠው ወይንም ለሌላ ጊዜ አስተላልፈው የሚል ምላሽ እንደሚሰጠው እያወቅኩ ነበር ምን የማልረባው ነኝ!፡፡

☼☼☼

ኩርዶቹ አመፁን እንዲቀላቀሉ የማሳመኑ ጉዳይ ሲነሳ ለቻላባይ አዳጋች የሆነበት ማሱድ ባርዛኒን ማሳመን ነበር፡፡

ባርዛኒ ማለት ደግሞ የኩርዱ አማፂ ሙስጠፋ ባርዛኒ ወይም በአሜሪካኖች ዘንድ ሬድ ሙላህ ተብሎ የሚጠራውና በ1970 ዎቹ አልፎ አልፎ በሳዳም ጦር ላይ የደፈጣ ውጊያ ይከፍት የነበረው ተዋጊ አንጃ መሪ ልጅ ነው፡፡ ሙስጠፋ በ1974 በኢራኑ ሻህ እና ሄነሪ ኪሲንገር የተከፈተበት ዘመቻ ተሰፋ አስቆርጦት ወደ አሜሪካ የተሰደደና እዛም ከነልብ ስብራቱ እሊጋው ላይ እንዳለ ቨርጂኒያ ውስጥ ከሚገኝ ማክሊየን በተባለ ስፍራ ሊያርፍ ችሏል፡፡ ከዚህ አንፃር ታዲያ ማሱድ በCIA'ና በዩናይትድ ስቴትስ ላይ የከፈተው የጥፋት ዘመቻ ያለምክንያት የሆነ አልነበረም፡፡ በአሜሪካ የሚደገፈው የኢራቅ ብሄራዊ ኮንግረስ መቀመጫው በባርዛኒ  ቁጥጥር ስር ባለችው ሳላህ አል ዲን ውስጥ እንዲሆን የፈቀደውም በውዴታው አይደለም፡፡

ነገሩን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ባርዛኒ በወቅቱ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጥሩ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ያለ መሆኑ ነው፡፡ ከብዙ አመት የስደት ኑሮ በኃላ ምንም እንኳ ተሰፋው ገና ያልተጨበጠ ቢሆንም አገሬ የሚለው አገር በማግኘቱ ደስተኛ ነው፡፡ ፕሮቫይድ ኮምፈርት በሚል በአሜሪካ በተካሄደው ዘመቻ የአየር ሃይል ሽፋን እንዲሰጠው ያደረገ ሲሆን ዩናይትድ ስቴስም ለዚህ ዘመቻዋ ባርዛኒን እንዲከፍላት የጠየቀችው ዋጋ የሌለ ከመሆኑም በላይ በውስጥ ጉዳዮቹ ማልታ ከመግባት ተቆጥባለች ይህም ባርዛኒን በ1994 መባቻ መጠነኛ የሆነ የነዳጅ ዘይት ኮንትሮባንድ ንግድ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡

የባህረ ሰላጤው ጦርነት ከመፈንዳቱ ወራት አስቀድሞ የተባበሩት መንግስታት ኢራቅ ወደውጭ በምትልከው ነዳጅ ዘይት ላይ ሙሉ ማእቀብ ጥሎ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ማዕቀቡም ሃገሪቱ ወደውጭ የምትልካቸውን ምርቶች ማለትም ነዳጅ ዘይትን



t.me/OLDBOOKSPDF

ጨምሮ መላክ እንዳትችል አድርጓታል፡፡ እናም ግብረ ሀይሉ ለቁጥጥር ያመቸው ዘንድ መጀመሪያ ላይ ማታ ማታ የማዕቀቡን ተፈፃሚነት የሚቆጣጠሩ ጀልባዎች ባህረ ሰላጤው ላይ ቅኝት ያደረጉ የነበረ ሲሆን ብዙም ሳይቆይ ከኢራቅ ወደ ቱርክ የሚያመራው መንገድ ተከፍቶ አትክልት በሚያጓጉዙ የጭነት ካሚዮኖች ከመጫኛቸው ስር በተበየደላቸው ጋን ነዳጁን ከኪርኩክ ወደቱርክ ማጓጓዝ ጀመሩ፡፡ እንደውም በ1995 የተደረጉ ግምቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ በቀን መቶ ሺህ በርሜል ነዳጅ ዘይት በዚህ መልኩ ወደቱርክ ይሻገር እንደነበረ የሚታወስ ነው፡፡ እናም የጭነት መኪኖቹ ቱርክ ለመድረስ የግድ የኩርዶች ይዞታ የሆነውንና በኬ.ዲ.ፒ ቁጥጥር ስር ያለውን ሰፊ የመሬት ክፍል ማቋረጥ ስለነበረባቸው ባርዛኒ ከእያንዳንዱ ካሚዮን ላይ ድርሻውን ወሰዷል፡፡

በኮንትሮባንድ ይሸጥ የነበረው ዘይት ለሳዳም ህልውናቸው ነበር ማለት ይቻላል ምክንያቱም ሳዳም በዘይቱ ሽያጭ በሚገኘው ረብጣ በስልጣን ያቆዩዋቸውን የደህንነት መስሪያ ቤታቸውንና የሪፐብሊካን ዘብ ጦራቸውን ለመደጎም ተጠቅመውበታልና፡፡ እንደዕውነቱ ከሆነ ነዳጁ እርሱ በያዛቸው ግዛት የማያልፉ በመሆኑ ተጠቃሚ ካልሆነው ታላባኒ በቀር ሁሉም ለማለት ይቻላላ የኮንትሮባንዱ ትርፍ ተቋዳሽ ነበሩ፡፡ እናም በኮንትሮባንዱ የሚቸበቸበው የነዳጅ ረብጣ የጦር ሰበቃውን ደረቱን የነፋለት ባርዛኒም በአሸባሪነት የሰሜኑን ግዛት ማናጋት ጀመረ፡፡

የዋሽንግተን መንግስት ስለኮንትሮባንድ ንግዱ በደንብ እርጐ ቢያውቅም እውቆ እንዳላወቀ መሆንን መርጧል፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የቱርክ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ሆነ ቱርክ ያለው ኤምባሲያችን በአንድ የስልክ ጥሪ ብቻ የኮንትሮባንድ ንግዱን እንቅስቃሴ ማቋረጥ ሲቻላቸው እነሱ ግን ይሄንን ዕርምጃ ከመውሰድ ታቅበዋል፡፡ ቱርኮች የባህረ ሰላጤው ጦርነት በአካባቢው የሚፈጥረው ትርምስ ያሳስደሰታቸው መሆኑ ሌላው የችግሩ አካል ነበር፡፡ በእኛ በኩል ጦርነቱ ፈጣንና ውጤቱም የማያዳግም መሆኑን ለቱርኮቹ ቃል ብንገባላቸውም ስለገደብ የለሹ ማዕቀብ እና በቱርኮች ምጣኔ ሀብት ላይ ስለሚያደርሰው የተራዘመ ጥፋት የተናገርነው ነገር አልነበረም፡፡ ማዕቀቡ እንዲፀና የሚያደርግ ቢሮክራሲያዊ ጋሬጣም ነበር፡፡ ይኸውም የቱርኩ ኢምባሲያችን በአውሮፓው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ቢሮ ስር መሆኑ ነበር፡፡ በኮንትሮባንድ የሚቸበቸበው ነዳጅ፣ ሳዳም፣ የኢራቅ ተቀዋሚዎች፣ ፀበኞቹ ኩርዶች፣ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ በጥቅሉ ራስ ምታቶች ነበሩ፡፡ የቱርኩ ኢምባሲያችን ስራዬ ብሎ የያዘውም ቱርኮቹን ማስደሰት በመሆኑ ቱርኮቹ በማጣሪያዎቻቸው የሚጣራ ርካሽ ነደጅ ከፈለጉ የራሳቸው ጉዳይ መሆኑን አምኖበታል፡፡

የማይገባኝ ነገር ቢኖር ስለምን የኃይት ሃውስ ገገርዎች በጉዳዩ ጣልቃ እንደማይገቡ ነው፡፡ ገቺዎቹ ሳዑዲ አረቢያ ለቱርክ ነዳጅ በቅናሽ እንድታቀርብ ማግባባት ብቻ በቂ ነበር፡፡ ቱርክ ነዳጁን ከሌላ ወገን በትክክለኛ ዋጋው ብታገኝ ኮንትሮባንዱን ማስቆሟ አያጠራጥርም፡፡ ነገሩ ሁሉ የኃይት ሃውስ ገገርዎች ሳዳም ትንሽ መንቀሳቀሻ ገንዘብ እንዲያጡ ያሰቡ ያስመስላል፡፡

ይህ የአሜሪካ አካሄድ ደግሞ ለኢራቃውያን ትርጉም ያስጠዋል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ የኮንትሮባንድ ነዳጅ ንግዱን አይቶ እንዳላየ መሆን የኩርዱ አማጺ ቡድን እርስ



t.me/OLDBOOKSPDF

በርሱ እንዲናጭ ሳዳምም የመንግስታቸው ጠባቂ የሆነውን የክብር ዘብ በገንዘብ መደጐም እንዲችሉ መንገድ ከፍቷል፡፡ ይህም በአካባቢው ላለ አንድ ምባገነን መሪ ምስጢራዊ ድጋፍ ከሚያደርግ አንድ ብልጥ ልዕለ ሃያል አገር የሚጠበቅ አካሄድ ነው፡፡ እናም ግዳጄን ዕሳት መሀል ሆኜ እየተወጣሁ መሆኔን ጥያቄ ባይኖረውም እኔ በኩርዶቹ ግዛት በመንቀሳቀስ የሳዳም ባላንጣዎች ሳዳምን ለማስወገድ በሚያደርጉት ጥረት እርዳታዬን ለመለገስ ስሯሯጥ ዋሽንግተን ያሉት ቱባ ቱባ ባለስልጣን አለቆቼን ግን ስለሳዳም በስልጣን መቆየት አለመቆየት ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው የመርሳታቸው ምክንያት በእጅጉ እንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፲፩

## መጋቢት 3/1995 ፤ ሳሳህ ሽል-ዲን፣ ኢራቅ

ቻላባይ ከቶኒ ሌክ የደረሰውን መልዕክት አንብቦ እንደጨረሰ ከሶፋው ላይ በቁሙ ተዘረፈጠ፡፡

«ሁሉንም አቁሙ ማለቱ ይሆን እንዴ?» ሲልም በለሆሳሳ ጠየቀኝ፡፡

«አህመድ! ልክ እንደኔው እንግሊዘኛ የሚገባህ ይመስለኛል፡፡ ይሁንና በእቅዱ መግፋት አለመግፋቱ ያንተ ጉዳይ መሆኑን አሳውቆሃል» አልኩት፡፡

«ለማሱድ አሳይተኸዋል?»

ቻላባይ ሊለኝ የፈለገው ገብቶኛል ደግሞም ግምቱ ትክክል ነበር፡፡ ከኢራቅ ሰራዊት የከዳው ሜጀር ጄኔራል መንግስት ለመገልበጥ ያቀረበውን ሃሳብ ቀሽንግተን በማጣጣሏ እቅዱን ከቻላባይ እቅድ ጋር ለማስማማት ተገዷል፡፡ ምንም እንኳ የቻላባይ ሃሳብ ከጄኔራሉ እቅድ ጋር ሙሉ ለሙሉ ባይስማማም ሁለቱን የሚያስማማ ነጥብ ነበር፡፡ ባርዛኒ በበኩሉም ቻላባይ መጋቢት 4 ለመክፈት ያቀደውን የጥቃት እቅድ ያጤነው በታላቅ ቁጣ ነበር፡፡ በቻላባይ በእቅዱ እንዲሳተፍ ያቀረበለትን ሃሳብ ግን በቀላሉ ወደጎን መግፋት አልቻለም፡፡ ያን ባለመቀበሉ ኩርዶቹ ኪሳራ ውስጥ ሊከቱት እንደሚችሉ አልጠፋውም፡፡ ቢሆንም እኔ ቻላባይን ከግስጋሴው መግታት እንደሚቻለኝ ገምቷል እኔም አሜሪካ በኢራቅ የሳዳም ሀልውና ማብቃቱን እንደምትሻ በገለፅኩለት ጊዜ የጎሪጥ አየኝ፡፡ የባግዳድን መንግስት ማስወገድ አላማቸው ላደረጉ የኢራቅ ተቃዋሚ ወገኖች አሜሪካ ድጋፏን እንደምትቸር መናገሬ አናዶታል፡፡ እኔም ሆንኩ ቻላባይ ባርዛኒ በእቅዱ እንዲሳተፍ የሚያዘው የሌክ መልዕክት ዱብዕዳ እንደሆነበት አውቀናል፡፡

«ስለ ፒግስ ባህረ ሰላጤ ሚ/ር ሌክ የሚያውቀው ነገር ይኖር ይሆን? ሲል ቻላባይ በፈገግታ ጠየቀኝ፡፡

«መቼስ ይህንን መልዕክት ማሱድ እንዳገኘው ለሁሉም እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ፡፡» አለና ከሌክ የደረሰውን መልዕክት በንዴት ወደ አንደኛዉ ጥግ አሽቀንጥሮ ወረወረው «ደደቡ ሌክ ማሱድን እንጂ እኔን ማስፈራራት አይችልም፡፡ እስከመጨረሻው በሃሳቤ እፀናለሁ፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

ቻላባይ ወደመኪናዬ በመሸኘት በጓደኝነት መንፈስ የመኪናውን በር ከፈተልኝ «ሌክ ትክክለኛ የማፈግፈጊያ ሰዓት አልመረጠለኝም» ሲልም በቁዘማ ተናገረ፡፡ እናም «የእዚህ እቅድ ፍፃሜ በሳዳም ፈንታ የኛ መስዋት ይሆናል፡፡» አለኝ፡፡

ቻላባይ እንዳለውም የሌክን መልዕክት ሳላደርስው በፊት ባርዛኒ ከእቅዱ ማፈግፈግ ጀመረ፡፡ ባለፈው ወር በተደጋጋሚ ከባርዛኒ ጋር ግንኙነት እናረግበት ከነበረው ከሳላ አልዲን በላይ ያለ መኖሪያ ቤቱ ስደርስ ያለወትሮው ግቢው ጭር ብሎ አገኘሁት የቤቱ መስኮቶች ተከርችመዋል፡፡ የግቢው መኪኖች ሁሉም የሉም፡፡ ይህ ሁሉም ባርዛኒ ቤቱን ስለመልቀቁ ፍንጭ ሰጥቶኛል፡፡ ግቢው ውስጥ የቀሩት ሁለቱ ዘበኞችም የት እንደሚገኝ መናገር ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡

እኔም የሌክን መልዕክት ለማድረስ የጦሩ ምክትል አዛዥና የማሱድ ወንድም ልጅ ከሆነው ኒቸርዋ ጋር በመሆን ባርዛኒን ፍለጋ ተሰማራን፡፡ ኒቸርዋን ፊት ጋብዞኝ ስለነበር ቤቱን በሚገባ የማየት እድል ገጥሞኝ ነበር፡፡ ጣሊያን ሰራሽ ቁሳቁሶቹን፣ ፐርሺያ ሰራሽ ምንጣፎቹንና ሌሎች ውድ አልባሳቶቹን አይቼለታለሁ፡፡ ከህገ ወጡ ነዳጅ ንግድ የሚገኘውን ገቢ ሙሉ ለሙሉ ኬዲፒ ለሚያረጋቸው ጦርነቶች በትክክል እንደማይውልም ተረድቼአለሁ፡፡ ስር መሠረታቸው ድሃ የሆኑት ባርዛኒዎች ኒቸርዋን እና አጎቱ ማሱድ መኖሪያቸውን በሰሜናዊ አገሪቱ በተገነቡት የሳሪ አይ አፓርትመንቶች አርገዋል ምንም እንኳ የነዳጅ ንግዱ አስተማማኝ ቢሆንም አሁንም በመጨረሻ ከንግድ ሸሪካቸው ሳዳም ጋር የሚያደርጉትን ፀብ አጫሪነትን ሽተውታል፡፡

«ማሱድ እኮ አስቀድሞ ይህ እንደሚሆን አውቋል ሲል ኒቸርዋን ቅሬታ ባዘለ ድምፅ ጥልፍልፉን በር አሻግሮ እየተመለከተ ተናገረ፡፡

አጎቱ መጋቢት 4 ሊፈፀም ስለአቀደው እመፅ ያሰበውን ስነግረው ትከሻውን ከመስበቅ ባለፈ የተናገረው ነገር አልነበረም፡፡ እኔ ግን ከሁኔታው ችግር ውስጥ መነከሬችን ታውቆኛል፡፡ እናም ታዲያ ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ጥርጣሬዬ እርግጥ መሆኑን ቻላባይ ነገረኝ፡፡ ባርዛኒ ሁኔታዎች ከከፋ በግለት ድንበር ተሻግሮ ቱርኮችን ጥገኝነት ለመጠየቅ መዘጋጀቱን አሳወቀኝ፡፡ እኔም ኮሎኔሉ ለጊዜው እፈግፍጐ ነገሩን ሌላ ጊዜ ሊሞክረው ይችላል ከሚል ድምዳሜ ደረስኩኝ፡፡

☼☼☼

ያንዕለት ሌሊት ቻላባይ ሃሳቡን አልለወጠም፡፡ ሁሉ ነገር እንደታቀደው መጋቢት 4 ተጀመረ እናም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ቀድሞ በትምህርት ቤትነት ያገለገለው የኢራቅ ብሄራዊ ሸንጐ ዕዝ በመብራት ተንቦገቦገ እናም እኔ ቻላባይ ከሆነ ቦታ ላገቢው የሚሆን ጀኔሬተር ስለማግኘቱ አልተጠራጠርኩም ነበር፡፡ መኪና መቆሚያው ላይ የተገሸሩት ከባባድ ካሚዮኖቹ ወደ ኢራቅ ጦር ግንባር የሚተሙ የ አይ.ኤን.ሲ ምልምል ወታደሮችን ለመጫን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ፡፡ ለወትሮው በግቢው ውስጥ የሚርመሰመሱት ሳንድኪሩዘሮችም የሚያደርሱአቸውን መልዕክቶች ተቀብለው በፍጥነት ግቢውን ለቀዋል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሆንፃው ውስጥም የሰርከስ ጨዋታ የመሰለ ነገር ይታያል፡፡ ስልኮችም ይንጫረራሉ እርዳታ የሚሹ ሰዎች በእጃቸው ያያዙዋቸውን ወረቀቶች ያራግባሉ፡፡ አዎን! ሰወቹ አንድ ነገር የሚሹ ይመስላሉ፡፡ ያም የዩናይትድ ስቴትስ እገዛን ነው፡፡

ወደቢሮው ስዘልቅ ጄኔራሉን ከባዶው ክፍል ተቀምጦ አገኘሁት ጄኔራሉ አዲስ የጄኔራል ደንብ ልብስ ለብሷል፡፡ አንፀባራቂውን በትረ-መንግስቱንም ጠረጴዛው ላይ አኑሯል፡፡ እንዳየኝም ከቅምጡ በመነሳት በድካም መንፈስ ጨበጠኝ፡፡ ለጥቆም ወደኢራቅ ግንባር የሚወስደው መልዕክተኛ ዝግጁ መሆኑን ነገረኝ፡፡ መልዕክተኛውም ከተቀሩት በቲክሪት ግንባር ከተሰለፉ ጓዶቹ እንደሚቀላቀለውም አወጋኝ፡፡ የጄኔራሉ ቲክሪት መሄድም የመፈንቅለ መንግስቱን እይቀሬነት አሳወቀኝ፡፡

ጄኔራሉ ከአንድ ቀን በፊት ስለሰጠሁት የሌክ መልዕክት ትንፍሽ ያለው ነገር አልነበረም፡፡ እንደቻላባይ ሁሉ ለማፈግፈግ ጊዜው ረፍዷል ከሚል ድምዳሜ ሳይደርስ አልቀረም፡፡ ከታንክ ትምህርት ቤት የተመረቀው ኮሎኔልም ታንኮቹን የተሰረቀ የታንክ አረር አጉርሷቸዋል፡፡ ኮሎኔሉ ከዚህ ሁሉ በኋላ ታንኮቹን ከጥቃቱ እንዲያፈገፍጉና ከእይታ እንዲሰወሩ ማድረግ እንደማይቻለው አውቋል፡፡ እኔም መለገስ የምችለው እርዳታ ስላልነበረ፡፡ ጄኔራሉ ከፊቱ የተጋረጠውን ጦር ጠርምሶ ያልፋል ወይስ አያልፍም ኩዴታው ይሳካል ወይስ አይሳካም ዳግም የማላገኘው መሆኔን በሚገልፅ መልኩ ጨብጬው ወደቤቴ አቀናሁኝ፡፡ እናም ወደቤቴ የመልስ ጉዞዬን በማረግበት ቅፅበትም ከርቀት የተተኮሰች አብሪ ጥይት ሰማዩን በብርሃን ስታደምቀው አየሁኝ፡፡

✲✲✲

ቻላባይ የደረሰው ወሬ ካለ ከፅንቅልፌ ቢሆን እንኳ ቀስቅሶ እንደሚያጋራኝ በማመን ወደመኝታዬ ብሄድም ሌቱ ያለፈው ከእርሱ አንዲት ቃል ሳልሰማ ነበር፡፡ በማግስቱ ማለትም መጋቢት 5 ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ወደ አይ.ኤን.ሲ ጠቅላይ መምሪያ አመራሁ፡፡ እናም የውጊያ መንፈስ ዝር ያለበት እንኳን አይመስልም ነበር፡፡ በእርግጥ መምሪያው ስራ በዝቶበት እንደሰነበተ ገምቼአለሁ፡፡ ግምቴ ግን ልክ አልነበረም ከመምሪያው ሆንፃ የሚታይ የሰው ዘር የሌለ ከመሆኑም በላይ ጄኔሬተሩ ተወስዷል፡፡ አንድም መኪና በአካባቢው አይታይም፡፡ ሌላው ቀርቶ ሰው ወዴት እንደሄደ የሚናገር ዘበኛ እንኳ የለም፡፡ የሆንፃው የፊት በር በንፋስ እየተላጋ ይከፈትና ይዘጋ ነበር፡፡ ከሆንፃው ውስጥ ያሉት ቢሮዎችም ተራቁተዋል-ኮምፒተሮቻቸው የፋይል ማስቀመጫዎቻቸውና እቃዎቻቸው ተጠራርገው ተወስደዋል፡፡ የቢሮዎቹ ማሞቂያዎች በጡሎን ከታሰሩባቸው ግድግዳዎች ተፈንቅለው አለመወሰዳቸውም በግማሽ አስገርሞኝ እንደነበር ዛሬ ላይ ቆሜ እስተውላለሁ፡፡

ወደ ሲ.አይ.ኤ ማረፊያ ቤታችን በዝግታ የመልስ ጉዞዬን ሳደርግ ወደ ዋሽንግተን ጠቅላይ መምሪያ የምልከውን መልዕክት ይዘት ማሰላሰል ይዣለሁ፡፡ «ውድ ላንግሌይ ትላንት ማታ የኢራቅ ተቃዋሚ ኃይል ከነበረበት ስፍራ ያጣሁት መሆኔን የምገልፅልህ በታላቅ ሃዘን ነው» የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ወሰኜአለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እናም እንደተመለስኩ ከቻላባይ ረዳቶች አንዱ ቤት ውስጥ ሲጠብቀኝ አገኘሁት፡፡ ረዳቱ ጄነራሉ ግንባሩን አቋርጦ ወደ ቲክሪት ለማቋረጥ ሲሞክር ባርዛኒ በቁጥጥሩ ስር እንዳረገው ነገረኝ፡፡ ባርዛኒ ጄኔራሉን ከ6 ሰዓታት ዕገታ በኋላ ቢለቀውም የኢራቅ ጦር ይዞታውን ለማጥበቅ ተጠቅሞባቸዋል፡፡ ባርዛኒ ጄነራሉን በቁጥጥር ስር አድርጎ በነበረበት ጊዜ ለቻላባይ ደውሎ ወታደሮቹ በአመፁ እንደማይሳተፉ ብቻ ሳይሆን ቢያንስ በርሱ ይዞታ ስር ካለው የኩርዶች ግዛት ያለ ሰው ሁሉ በአመፁ መሣተፉን እንደማይፈቅደው ጭምር ነግሮታል፡፡ የባርዛኒ መልዕክትም በይዞታው ስር ወዳሉ ክልሎች በመስራጨቱ ወታደሮቹ በኒቸርዋን አዛዥነት በመመራት እያንዳንዱን ታጣቂ የአይ ኤን.ሲ አባል ትጥቅ በማስፈታት በቁጥጥር ስር አውለዋል፡፡ የሲክ መልዕክትም ግልፅ ነበር፡፡ ሌክ ቻላባይም ሆነ ጄነራሉ ከጉዞቸው እንዲገቱ ፈልጓል፡፡ ይሁንና ይህ ታላቅ ክህደት የተፈፀመበት ቻላባይ አፈግፍጎና ጓዙን ጠቅሎ ወደ አርቢል ተጉዟል፡፡ ከተማዋን በቁጥጥሩ ስር ያደረገው ታላባኒ ደግሞ መጋቢት 4 አመፁን ለማፈንዳት ባይንቀሳቀስም ቀኑን ሙሉ ቅስቀሳ በማድረግ እንደተሳተፉ የሚታወስ ነው፡፡

በማግስቱ ማለትም መጋቢት 6 ቀን ከእንቅልፌ እንደነቃሁ የጀኔራሉ መኪና ከቤታችን ፊት ለፊት ስትቆም አየሁ፡፡ ጄኔራሉ ከሜጀር ጄኔራል መለዮው ይልቅ ርካሽ የስፓርት ቱታ ለብሶ ሪዙንም እንኳርጎአለ፡፡

«ጌታው» ሲል ሶፋው ላይ እየተቀመጠ ዝግ ባለ ድምፅ «አሁን ከዚህ መሄድ ይኖርብኛል፡፡ ወደ ደማስቆ ሂጄ ልጆቼን ትምህርት ቤት ማስገባት ይገባኛል፡፡» አለኝ፡፡

ለምንድን ነው የማይገባው ስልም ራሴን ጠይቄያለሁ፡፡ መልዕክተኞቹ፣ የሚስጥር ኮሚቴው እና ኮሎኔሉ በፖሊስ ተይዘዋል፡፡ ሳዳም ሰዎቹን ከእስር ፈተው ይለቋቸዋል ብሎ ማሰብም የዋህነት ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ጄነራሉ ከሰሜኑ ግዛት ከአሁን አሁን የጥይት እራት እሆንን? በሚል ስጋት ተጠፍሮ መኖሩን አልፈለገውም፡፡

እናም ብዙ መናገር የሚፈልገው ነገር እንዳለው ገብቶኛል፡፡ ሃገሩን፣ ቤተሰቡን፣ ህይወቱንና፡፡ ያለውን ሁሉ ከጦር ግንባሩ አስልፏል እምነቱንም በኛ ላይ ጥሏል፡፡ የዋሽንግተን መንግስት ያለምንም ማብራሪያ እጁን መሰብሰቡን እስከገለፀበት ጊዜ ድረስ በመፈንቅለ መንግስት እቅዱ እንዲገፋበት ፈቅደንለታል፡፡ እናም እኔ እና አማካሪው የቀረበልንን ሻይ እስክንጨርስ በትዕግስት ጠበቀን፡፡ እንደዕውነቱ ከሆነ ምን ልለው እንደምችል የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ በመጨረሻም ዋሽንግተን በነገሩ መግፋት ሳትፈልግ ቀርታ ነውን? አለቆቼ ስለሁኔታው ሙሉ መረጃ እንዲያገኙ ባደርጋቸውም ሲያመነቱ ቆይተው በመጨረሻ ሁኔታው በኢራቅ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ የሚያናጋ መስሎ ታይቷቸው ይሆንን? ያም የዋሽንግተን መንግስት ያለው አማራጭ ነገሩን ማድረግ ወይም መተው እንደሆነ አድርጎ አይቶና ሁለተኛውን አማራጭ ተጠቅሞ መልካሞቹን እና ጀግኖቹን በውቅያኖስ ንፋስ እያግለበለበ እንዲወስዳቸው ፈቅዶ ይሆንን? በትክክል ይኼ ነው ብሎ መግለፅ የሚቻል ነገር አልነበረም፡፡ ስለዚህ ጄነራሉን ወደደጅ ሸኘሁት፡፡ ጨብጨውም መኪናው ኩርባውን ጨርሶ ከዕይታ እስኪሰወር በአይኔ ሸኘሁት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ተመልሼም ወደቤት እንደገባሁ ቶም ቨርጂኒያ ከሚገኘው የCIA መልዕክት ማስራጫ ጣቢያ ጋር እንዲያገናኘኝ አዘዝኩት፡፡ ሽንፈታችን ይበልጥ ግልፅ እየሆነ ቢሄድም በቀላሉ ተስፋ ለመቁረጥ እሁንም ቢሆን ዝግጁ አይደለሁም፡፡ እናም ሳተላይቶቹ ቦታውን ለቆ ያዩት ክፍለ ጦር፣ ሻምበል ጦር ወይንም አንድም ታንክ ቢሆን መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ፈልጌያለሁ፡፡

እንደጠበቅነው የደረሰን ዜና መጥፎ ነበር፡፡ ተቃዋሚው ጎራ የሞት ሽረት ፍልሚያ ያደርግበታል ተብሎ ይጠበቅበት በነበረበት የመጋቢት 5 ከሰዓት በኃላ የኢራቅ ጦር ሰራዊት በከፍተኛ ተጠንቀቅ ላይ ነበር፡፡ ከየካቲት 28 ጀምሮ በሞዋሲል እና ኪርኩክ ጎዳዎች ላይ ሲጓጓዝ ይታይ የነበረው ጦር መግሪያ የት እንደደረሰ ባይታወቅም፡፡ መንግስት ግልበጣውን እውን ለማድረግ ጥምረት በፈጠሩት በ76 ኛው ብርጌድ፣ በ15 ኛው ክፍለ ጦር እና በ5 ኛው ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር ሰፈሮች ውስጥም የሚታይ እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡ ከሁሉም የሳበኝ ግን ቲክሪት አቅራቢያ የሚገኘው የኮሎኔሉ ጦር ሰፈር ነበር፡፡ እዛም ከስፍራው የተነቃነቀ ታንክ አልነበረም፡፡ ታንኮቹ መጋቢት 4 ከመጠለያቸው ወጥተው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ግዳጃቸውን ፈፅመው የሚመለሱት ቀን በሆነም ነበር፡፡

☼☼☼

የዚያን ዕለት ማታ 4፡22 ሲሆን ለደህንነት አገልግሎት የሚሰጠው ስልኬ አንጫረረች፡፡ ደዋዩም ደግሞ ዋሽንግተን ውስጥ የሚገኘው አለቃዬ ቦብ ነበር፡፡ ቦብ ሰሜናዊ ኢራቅ ከገባሁ አንዴ ብቻ እንደደወለልኝ እስታውሳለሁ፡፡

«እዛ እየሆነ ያለው ምንድነው?» ሲል ጠየቀኝ፡፡

«ምንም ቀዝቃዛ መጠጣችንን እየተጎነጨን ቁጭ ብለናል፡፡»

«ቶሻሻውን ጠርገህ ማስወገድ ይኖርብሃል የምነግርህን ማንም እንዲሰማው ማድረግ የለብህም ገብቶሃል?» አለኝ በሻካራ ድምፅ፡፡

የገባኝ መሆኑን ከአረጋገጥኩለት በኃላ «በቡድንህ ውስጥ ሮበርት ፓፕ የሚለውን የሃሰት ስም የሚጠቀም ሰው አለ?» ሲል ጠየቀኝ፡፡

«የሚባል ሰው አላውቅም» ከኔ በቀር

በቡድኔ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ የሀሰት ስሞች እሏቸው ሮበርት ፓፕ የሚለውን መጠሪያ የሚጠቀም ሰው ግን አልነበረም፡፡

«እርግጠኛ መሆን ይኖርብሃል፡፡ ምክንያቱም ሽርትቱ እየተጫወትክ ያለኸው ስስ በረዶ ላይ በመሆኑ ነው፡፡ እየሆነ ያለውን ነገር ልነግርህ አልችልም ሌላው ቀርቶ ስለ ፓፕ ልጠይቅህ አይገባኝም፡፡ ስለዚህ ይህ ከኔና ከአንተ መውጣት የለበትም ገባህ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

ቦብ ስለምን እያወራ እንደሆነ መጠየቅ የለብኝም ሊነግረኝ የሚችለው ነገር ቢሆን ኖሮ አይደብቀኝም የባህር ሃይል ባልደረባ የነበረውና በጡረታ ከተገለለ በኋላ እድሜው ከ40 ዎቹ መጨረሻ ሲደርስ CIA ውስጥ የተቀጠረው ቦብ አለቆቹ ያዘዙትን ይፈፅማል፡፡ ትዕዛዞቹን ወደዳቸውም ጠላቸው ከአለቆቹ ተቀብሎ ተፈፃሚ ያደርጋቸዋል፡፡ አንድን ነገር ሊነገረኝ እንደማይችል ከተናገረ እንደማይነግረኝም አውቃለሁ፡፡

«በተቻለ ፍጥነት ወደዋሽንግተን መመለስ ይኖርብሃል በአንካራ በኩል ስታልፍ ስለዚህ ጉዳይ ለማንም መናገር የለብህም፡፡ የምትነግራቸው ሰዎች በአንተ ላይ ሊመሰክሩብህ ይችላሉ፡፡ አገር ቤት ከተመለስክ በኋላም ለማንም አትደውል፡፡ እነዚህም በአንተ ላይ ሊመሰክሩብህ ይችላሉ፡፡»

ምስክሮች!? ቃሉን የተጠቀመበት በመጥፎ ጐኑ ነበር ሆኖም ከ6/192 ማይል ርቀት ላይ ሆኜ ልፈፅመው ከማልችለው ነገር ጋር በተያያዘ የተጠቀመበት ቃል ስለመሆኑ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡

«ቦብ አሁን መመለስ አልችልም፡፡ ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ ቢሆንም ተቃዋሚው ኃይል በማጥ አረንቋ ውስጥ ተዘፍቋል፡፡ ሁለት ሳምንት ብትሰጠኝ ሁሉንም ነገር ወደነበረበት ልመልሰው እችላለሁ፡፡»

«ያልኩህን አልሰማህም እንድትወጣ ታዟኻል በቃ!! ይኸው ነው፡፡»

«ሰዎቼኮ በሰሜኑ ግዛት ውስጥ ተበታትነው ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ አሁን በምትለኝ መልኩ አሰባስቤአቸው ከዚህ መውጣት አልችልም፡፡»

«ደህና ይሁን ለማድረግ የሚያስፈልግህ ከሆነ አራት ቀናት ይሰጡሃል፡፡ ነገር ግን ከዛ የበለጠ አንዲት ቀን ብትሆንም መቆየት አትችልም፡፡»

ቦብ ስልኩን ከዘጋው በኋላ በተቃዋሚዎች ስለተጠነሰሰው አመፅም ሆነ ስለመንግስት ግልበጣው ቃል ትንፋሽ አለማለቱን ተገነዘብኩ፡፡ በዋሽንግተን እይታ ሁለቱም እንቃስቅሴዎች እንደ ማጭበርበር ድርጊት ሆነው ተወስደዋል፡፡ የዋሽንግተን መንግስት ከመልዕክተኞቹ የሚቀበላቸው መልዕክቶች መረጃ ሆነው ካልታዩት የመልዕክተኞቹን ዋጋ ያራክሳል፡፡ በዚህ ሁኔታ እንደመልዕክተኛ ተቆጥረው የነበሩት የቻላባይ እና ጀኔራሉ እጣ ፈንታም ይኸው ነበር፡፡ እናም ዋሽንግተን ውስጥ የሚገኘው የመረጃ ቢሮ መጋቢት 4 ቀን ኢራቅ ውስጥ የተካሄደ ምንም አይነት እንቅስቃሴ አለመኖሩን አረጋግጧል፡፡ በዚህ በኩል በግልፅ ለመናገር የዋሽንግተን መንግስት ትክክል ባይሆን ኖሮ ይገርመኝ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፮

## መጋቢት 6/1995 ፤ ሳላህ አል-ዲን ኢራቅ

ቶም ከቤታችን ጣራ ላይ ሆኖ የኢራቅ ሰራዊት ወደ መሸገበት የደቡብ አቅጣጫ በአቅርቦ ማሳያ መነፅሩ ሲመለከት አገኘሁት፡፡ ስለ ሮበርት ፓፕ እና ትውስታችን ሳወጋው ያዳመጠኝ በዝምታ ነበር፡፡ እያወጋሁት ባለበት ቅፅበትም ሰሜናዊው ኢራቅን ለቀን ለመውጣት ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ከማሰብ አልቦዘንኩም፡፡

«አንድ ነገር ሊሆን እንደሚችል እረዳለሁ» ሲል ንግግሬን እንደጨረስኩ ተናገረ፡፡ «ታላባኒ ዛሬ ማታ ጥቃቱን ይከፍታል፡፡ የዋሽንግተን መንግስትም ፓፕ ከተባለው ሰው በበለጠ የሚያስጨንቅ ሃሳብ ይኖረዋል፡፡»

ቶም አቅርቦ ማሳያ መነፅሩን አቀበለኝ ወዲያውም ማየት የቻልኩት ነገር ቢኖር ከሳላዲን በታች ከተንጣለለው መስክ ላይ የሚያብረቀርቅ ብርሃንን ብቻ ነበር፡፡ ለጥቆም በስተደቡብ አቅጣጫ አንዲት አብሪ ጥይት ሰማዩ ላይ የሰራችውን ደካማ የብርሃን ጅረት እና ጥይቷ ፈንድታ ስትከስም የፈጠረችውን ወገግታ ተመለከትኩኝ፡፡ ካለሁበት እርቀት አንፃር እርግጠኛ አልሁን እንጂ የመድፍ ሳይሆን አይቀርም ያልኩትን አንድ ብሩህ ብልጭታ አየሁኝ፡፡ ደቂቃ ወይንም ከዛ የበለጠ ጊዜ እንዳለፈ ከባድ መሳርያዎች ላንቃቸውን ከፈቱ፡፡ ፍንዳታዎቹም ሳላ አልዲን ዙሪያ ባሉ ኮረብቶች ላይ አጓሩ፡፡ የሌቱ ሰማይም በጥይቶች ወገግታና ቅሪቶች ተሞላ፡፡

ሁኔታውን እንዳየሁት መጀመሪያ የመጣልኝ የተረገሙት የኩርዶች ግጭት ዳግም አገርሽቷል የሚል ሐሳብ ነበር፡፡ ሆኖም ፍንዳታዎቹ ይከሰቱ የነበሩት በታላባኒ ወይም ባርዛኒ ጦሮች ይዞታ ስር ካሉ ክልሎች ሳይሆን ከኢብሪል በስተደቡብ አቅጣጫ ካለ ክልል ሆኖ አገኘሁት፡፡ እናም የቶም ግምት ትክክል ነበር፡፡ ታላባኒ በሺ. ወታደሮች ላይ ጥቃት ተፍቷል ማለት ነው፡፡ ደረጃዎቹ ሁለት ሁለቱን በአንዴ እየዘለልኩ ወርጄ ኢብሪል በሚገኘው የታላባኒ እዝ ፅሕፈት ቤት ላስቀመጥኩትና የቀድሞ ወታደራዊ አዛዥ ለነበረው ፖል ደወልኩለት ፖል የታላባኒ ደፈጣ ተዋጊዎች የ 38ኛው ምድብ ጦር አካል የሆነን አንድ ብርጌድ የፈጠረበትን መገረምና ተዋጊዎቹ ብርጌዱን ለመማረክ መቃረባቸውን እየተደነቀ በጩኸት ነገረኝ፡፡

ፖወል ስለሁኔታቸው ዘገባ ለማቅረብ ሌቱን ሲደውልልኝ ነበር ያደረው የታላባኒ ፔከ መርጋ ተዋጊዎች ከማኃላቸው 22 ግዳይ ቢያጋጥማቸውም የ 38ኛው ክፍለ ጦር በ 848 ኛውን ብርጌዱን በመደምሰስ የብርጌዱን ጦር አዛገች ማርከዋል፡፡ የብርጌዱ አካል የሆነውን 601 ኛውን የከባድ መሳርያ ምድብም በቁጥጥራቸው ስር አውለውታል፡፡ በዚሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውጊያም የብርጌዱ አዛዥ የሆነውን ኮሎኔል አብደላዚዝ ናሙሪን ጨምሮ 80 የኢራቅ ወታደሮች ምርኮኞች ሆነዋል፡፡ የታላባኒ ተዋጊዎች የባታሊዮንን የመሬት ውስጥ ምሽጎች በድማሚት በማንጎድ ባለ 152 ሚ.ሜ እና 130 ሚ.ሜ የሆኑ ከባድ መሳርያዎችን ከጥቅም ውጪ አድርገዋል፡፡ በያዝዋቸው ላንድከሩዘር አውቶሞቢሎቻቸውም በመውሰድ የቻሉትን ያህል የጥይትና ቀላል መሳርያ ምርኮ ወስደዋል፡፡ ለጥቆም ጥቃታቸውን በሪፐብሊካን ዘብ በተሰኘው ክፍለ ጦር ላይ በመክፈት ክፍለጦሩ ለከባድ መሣሪያና ለወታደር ማጓጓዣነት የሚጠቀምባቸውን ካሚዮኖችን ደምስሰዋል የኩርዶቹ ጥቃት አስፈሪነት ያስደነገጠው የሪፐብሊካን ዘብ ክፍለ ጦር አዛዥ ወታደሮቹ የ848 ተኛውን ብርጌድ ለመታደግ እንዳይንቀሳቀሱ ከማዘዙም በላይ ወታደሮቹ እራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከል እንዲያዘጋጁ ነግረዋቸዋል ጥቃቱም ኩርዶች ከመጋቢት 1991 ህዝባዊ መነሳሳት በኃላ በኢራቅ ጦር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ታላቅ ጥፋት ያደረሱበት ድል እንዲጎናፀፉ አድርጓቸዋል፡፡ ኢራቅ ውስጥ ስለተካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ ለማሳወቅ የደወልኩት ዋሽንግተን ውስጥ ስለጉዳዩ ከታወቀ በኃላ ነበር፡፡

«አዋን! ዘገባህ አንብበነዋል» ምላሹን የሰጠችኝ እኔን እንደአንድ እረኛ የምትቆጥረኝ አንድ ጠሚጋ ባለስልጣን ነበረች ከዋሽንግተን ሳልወጣ በፊት ኢራቅ ውስጥ አንድ ህዋስ የማስቀመጥ ሐሳብ ከCIA የሞኝ አስተሳሰብ የመነጨ ሐሳብ ነው ስትል አጣጥላኝ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

«ከአጋር መረጃ ድርጅቶቻችን የተወሰነ መረጃ አሰባስበናል፡፡» ስትልም ንግግሯን ቀጠለች፡፡

«የተወሰነ ስትይ»?

«ነገሩ ምን መሰለህ ትላንት ሌቱን የሺ ክፍለ ጦሮች ከሰፈሩበት አካባቢ የተካሄደ ውጊያ ነበር፡፡ በውጊያውም ሮኬቶች ተወንጭፈዋል፣ የእጅ ቦንቦችና ጠመንጃዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ውጊያው የቆመው በእናንተ አቆጣጠር ዛሬ ጠዋት ስድስት መቶ ሰዓት ላይ ነበር፡፡ ሰላሳ የሚሆኑ ተማራኪዎች ወደ ኢርቢል መጓጓዛቸውን የሚገልፅ ዘገባ በደረሰንም ስለ እርግጠኝነቱም ያወቅነው ነገር የለም»፡፡

«ስለ እርግጠኝነቱ ያወቅነው ነገር የለም ስትይ ምን ማለትሽ ነው? ሌቱን ሙሉ የከባድ መሳሪያ ልውውጥ ስናይ ነው ያደርነው፡፡»

«ጠንካራ መሠረት ያለው መረጃ አልነበረም»

«አዋን! እርግጥ ነው ጥቃቱ የተፈፀመው ሌቱን ሙሉ ነው፡፡»

«እየነገርኩህ ያለሁት እኮ እዚህ ያሉት ሰዎች የደረሳቸውን መረጃ መሰለኝ፡፡»

«እንዲያ ስትይ ታላባኒ ያን ሁሉ ተኩስ ያካሂድ የነበረው እኛን ግራ ለማጋባት ነው ማለት የፈለግሽ መሰለኝ፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

ስልኩን ከጠረቀምኩት በኃላ ከጠቅላይ መምሪያው ባለስልጣናት ጋር ያለውን ሁኔታና እየተካሄደ ያለውን ነገር ለማጣራት ወደድኩ ግን ምን ያደርጋል የትም መሄድ አልችልም፡፡ ሁኔታውን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ እለቶቹ በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርተው ከድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ነው፡፡ የዋሽንግተን መንግስት አንድ ነገር መሆኑን ለማመን የግድ ሰማይ ላይ ባለው ትልቅ አይኑ (በሳተላይት) ማየት ይኖርበታል፡፡ እሊያ ግን ድምዳሜው አልሆነም የሚል ይሆናል፡፡

እናም እኔ ነገሩን በዓይኔ ማረጋገጥ ስለፈለግኩ «ወደ ግንባር ሄደን ታላባኒን ማግኘት ይኖርብናል ስለዚህ ጓዝህን ሸክፍ ስል ቶምን አዘዝኩት፡፡»

ባለ ሁለት በሩ አሮጌ ኒሳን ፓትሮል መኪናችን ሊይዝልን የቻለውን አንድ ደርዘን ነዳጅና ውሃ የተሞሉ ጀሪካኖች፣ የምግብ ራሽን የያዙ ጥንድ ሳጥኖች፣ አንድ ኮምፓስ፣ አንድ የመሬት ከፍታ ጠቋሚ መሣሪያ፣ አንድ የኢራቅ ጉዞ ካርታ እና ኤል. ኤስ. ቲ-5 የተሰኘ መገናኛ መሳሪያን ነበር፡፡

በሳላህ አል ዲን እና ኢርቢል መሃል በተጓዝንባቸው ቅዕበቶች ያየነው ካሚዮን አልነበረም ለወትሮው ዘር የሚዘሩ ብሩህ ቀለማት ያላቸው ቀሚሶችን ያጠለቁ የኩርድ ሴቶች የሚታዩባቸው ማሳዎች ሰው አልባ ነበሩ፡፡ የኢርቢል ግዛትን እንዳለፍን የታላባኒን የተጠመደ ከባድ መሳሪያዎች፣ የመሣሪያ መጋዘኖችንና ጥብቅ ምሽጎቻቸውን ማየት ችለናል፡፡ ኢርቢል ባርዛኒ ከደፈረ ለዉጊያ ዝግጁ ሆናለታለች፡፡

ኢርቢል እንደደረስን አንድ የኛ የሆነን ሰው ኢራን ድንበር አቅራቢያ በሰሜን ምስራቅ ኢራቅ ወደምትገኘው ሱላማኒያን ወደተሰኘችው የኩርዶች ከተማ እንዲወስደን በማለት ጫንነው፡፡ ዱኻህ ከተማ እንደደረስንም ሃይቁ አቅራቢያ ምሳችንን ተመገብን፡፡ እዚያም የሚከራዩ ጀልባዎች መኖራቸውን የሚገልፅ ማስታወቂያ ከአንድ በመዛግ ላይ ካለ ቆርቆሮ ላይ ተፅፎ ተመለከትን፡፡ ለእፍታ ያህልም ጀልባዎቹ አሁን የት ደርሰው ይሆን? ሐይቁ ላይ የጀልባ ጉዞ ከተደረገሰ ስንት አመታት አልፈዋል? በሚል ሃሳብ ተዋጥኩ፡፡ አሁን ከ36 ኛው ሃሳባዊ መስመር በታች በመሆናችን ለሳዳም ጦር መርከቦች ልንጋለጥ እንደምንችልም አሰብኩ፡፡

ሱላማኒያህ የገባነው ለአይን ያዝ ሲያደርግ ነበር፡፡ የከተማዋ መንገዶች ጭር ብለዋል ከታላባኒ ማዘጋጃ ፅህፈት ቤት በቀር የብርሃን ጭላንጭል አልነበረም፡፡ ብዙ ወጣትና አዛውንት ወንዶችም ፅህፈት ቤቱን ከበው ወደውስጥ ለመግባት ይገፋፋሉ፡፡

«ወዶ ዘማቾች ናቸው፡፡» ሲል ዘቡ እያንሾካሾከልኝ መንገዱን አስለቀቀልን፡፡

የሱላማኒያህ ጦር አዛዥም ወደ ቢሮው ወስዶ ሻይ ከጋበዘን በኃላ ከጠረጴዛው ጀርባ ወዳለው ካርታ እየጠቆመም በግንባር ስላለው ሁኔታ ትንታኔ ይሰጠን ገባ፡፡ ይሁንና አዛዡ የሚያውቀው የኢራቅ ጦር ያለበትን ቦታ ብቻ ይመስል ነበር፡፡ በመጨረሻ ላይ ግን ገለፃውን አቁሞና ትከሻውን ሰብቆ ወደታላባኒ ጦር ሰፈር እንድንሄድ ሃሳብ አቀረበልን፡፡ እኛም ታላባኒ የላከልንን የመንገድ መሪ እዛው ሆኖ እኛን ሲጠባበቅ ስለነበር ወደዚያው አቀናን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁልል የቆሻሻ ክምር ያለበትን መስመር ተከትሎ የተሰራውን ምንም ዓይነት ምልክት የሌለውን መንገድ ይዘንና የመኪናችንን ፊት መብራቶች አጥፍተን ከሱላማኒያህ በስተደቡብ ወደሚገኙት ተራሮች አመራን እናም ውድቅት ሌሊቱ ጥቂት እንዳለፈ የመንገዱን ጥሻ ጥሰን ወደ አንድ የተመነጠረ መስክ ቁልቁል መውረድ ጀመርን፡፡ ከመስኩ መሃል ሰው የሌለበት መስሎ የታየንን ባለ አንድ ፎቅ ህንፃ ብናየውም ከህንፃው ፊት ለፊት ደርሰን የመኪናችንን መብራት እንዳጠፋን ደርዘን የሚሞሉ የፔክ መርጋ ተዋጊዎች ከእይታችን ገቡ፡፡ በፀጥታም ወደ መኪናችን ቀርበውም ጓዛችንን ማውረድ ጀመሩ፡፡ ይህን ያደረጉትም መኪናው ከህንፃው በፍጥነት እንዲርቅ በመፈለጋቸው ነበር፡፡

ታላባኒ ከዋሻው እንደሚወጣ ድብ ሁሉ ከህንፃው እያደባ በመውጣት ወደ እኔ በመቅረብ ወገቤን በእጁ ለቀም አድርጐ ይዞም ከመሬት ወደ ላይ አነሳኝ «በጉዞ ላይ ሳለህ ብዙ ነገር እምልጠሃል፡፡» ሲል አንሾካሾከልኝ፡፡ «ለክብራችሁ ስንል ሌቱን የምናሳልፈው መስኩ ላይ ሳይሆን ቤተመንግስቱ ውስጥ ይሆናል፡፡

በክንዱ ክንዴን ቆልፎ ይዞ እየመራ በ1988 በኩርድና በመንግስት መሃል በተፈጠረ ግጭት መደበኛ አገልግሎቱን መስጠቱን ወደ አቋረጠውና ቀደም ሲል በትምህርት ቤትነት ወዳገለገለ ጥቁር ህንፃ ይዞኝ ሄደ፡፡ እናም ህንፃው ውስጥ የምናድረው እኔ ቶምና ታላባኒ ብቻ ነበርን፡፡ የታላባኒ ተዋጊዎች ግን የሳዳም ሄሊኮፕተሮች እነሱን ማግኘቱ አዳጋች ከሚሆንባቸው በህንፃው ዙሪያ ካሉ ኮረብቶችና ዋሻዎች ተበታትነዋል፡፡ ከህንፃው መተላለፊያ ጠርዝ የሚገኘው የታላባኒ ክፍል ደግሞ ወረቀቶችና መፅሃፍት ከተሞሉ ግማሽ ደርዘን ሳጥኖች እና ጥቂት ወለሉ ላይ ካሉ ብርድልብሶች ሌላ ምንም ነገር አልነበረውም፡፡ ክፍሉም ብቸኛ ብርሃኑን የሚያገኘው በአንድ በባትሪ ከሚሰራ ፋኖስ ነበር፡፡ እኛም ወደ ውስጥ እንደዘለቅን ከክፍሉ ሲሚንቶ ወለል ላይ ከተነጠፈው ምንጣፍ ላይ እግራችንን አጣጥፈን ተቀመጥን፡፡

«ዛሬ ማታ ዳግም እንዘምታለን» ሲል ታላባኒ ከአንድ የሲጋራ ፓኮ ስሪታቸው የኩባ የሆኑ ሶስት ሲጋራዎችን እያወጣ ተናገረ፡፡ ካርባላክን እንደበድባታለን፡፡ አሁን እያወራን ባለንበት ቅፅበት እንኳን ሰዎቻችን ግንባሩን ጥሰው ማለፍ ይኖርባቸዋል፡፡» እኔም ካርባላክን የማላውቃት በመሆኔ ታላባኒ ካርታ ፈልጎ ከተማዋ ያለችበትን ቦታ አሳየኝ፡፡

ታላባኒ ስለኢራቅ ጦር ድክመት የኩርዶች ህጋዊ ይዞታ መሆኗን አስረግጦ የሚናገርላትንና ወናዋ የኢራቅ ነዳጅ ዘይት አምራች የሆነችውን ኪርኩክ ከተማ ለመግረክ ስላለው እቅድ እንዲሁም ስለመፃኢዋ ዴሞራሲያዊት ኢራቅ አውርቶ የሚጠግብ አይመስልም፡፡ አይኖቹ ማሸለብ ባይጀምሩ ኖሮ ሌሊቱን ሙሉ ከማውራት ወደኋላ አይልም ነበር፡፡

«በሉ ተኙ» ሲልም ተናገረ መዳከማችንን ሲያስተውል ጊዜ፡፡

«ያለማንም እገዛ ሁሉንም ዘመቻ በራስህ እየተወጣህ ያለህ መስሎኛል፡፡»

«ያሉኝን ጦር መሪዎች እየጨረስኩ ነኝ፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጆላል በዚህ በኩል ስጋት አይግባህ፡፡ የዋሽንግተን መንግስት እያደረግከ ያለኸውን ነገር በንቃት በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡ ደግሞም እቅድህ እንደላከኝ መንግስት እቅድ ሁሉ ሳዳምን ማስወገድ መሆኑን መርሳት የለብህም፡፡» ቢያንስ ያን ያህል የተናገርኩት እውነት መሆኑን አውቃለሁ፡፡ ይሁንና የቶኒ ሌክ መልዕክት ታላባኒም ሆነ ሌሎቹ ሳዳምን የመገልበጥ እቅዳቸው ይሰርዙ የሚል ይዘት አልነበረውም፡፡ መልዕክቱ የሚለው «ከዚህ በኋላ ለመግፋት ከወሰናችሁ በራሳችሁ ተወጡት» የሚል ምክር አዝሏል፡፡ ታላባኒም ምክሩን ተረድቶታል፡፡ እንደኔው ሁሉ ኢራቃውያን ሳዳም ከስልጣን መንበራቸው ላይ እስካሉ የሰላም አየር መተንፈስ እንደማይችሉ ያውቃል፡፡

ታላባኒ ሁለት ተጨማሪ ሲጋራዎችን ከፓኮው አወጣ፡፡ «ይህን ያዝ ከዚህ እንደሄድክ ወደ ዋሽንግተን ደውል፡፡» አለኝ፡፡

«ጆላል ያላወቅከው ነገር አለ፡፡» በአትኩሮት ተመለከተኝ፡፡

«እኛ አካባቢውን ለቀን መሄዳችን ነው፡፡ ሆኖም በእኛ እግርም አዲስ ቡድን ይተካል፡፡» አልኩት

ታላባኒ መልስ ሳይሰጠኝ ሲጋራውን አቀበለኝ፡፡

«በመጨረሻም ወደመኝታችሁ ሂዱ ሁላችንም ደክሞናል፡፡» አለ፡፡

አስር ያህል ደቂቃዎች እንዳለፉ ተመልሶ መጥቶና ያለሁበትን መኝታ ቤት በር ቆርቁሮ ወደ ውስጥ ከዘለቀ በኋላ ከካርባላክ የደረሰውን የፋክስ መልዕክት አቀበለኝ፡፡ መልዕክቱም ወታደሮቹ እዛ በሚገኝ አንድ የኢራቅ ባታሊዮን ጦር ላይ ወረራ መፈፀማቸውን ይገልፃል፡፡

«አየህ» አለ ታላባኒ በደስታ ተውጦ «የኢራቅ ጦር እየተፍረከረከ ነው፡፡»

እናም እኔ የኢራቅ ዘመቻዎች ምክትል ኃላፊ የሆነው ቦብን በመገናኛ መሳሪያ ደውዬ ካገኘሁት በኋላ በካርባላክ የተፈፀመውን ነገርኩት ቦብም በመልዕክቱ ይዘት ሳይመሰጥና በተሰላቸ ድምፅ «አሁን ያለኸው የት ነው?» ሲል ጠየቀኝ፡፡

«ሲንጋው፡፡» አልኩት

«እሱ ማለት የት ነው ያለው?» አለኝ፡፡

«ከ 36 ኛዉ የሀንድ ግዛት በስተደቡብ ይገኛል፡፡ አሁን ያለሁት ከታላባኒ ጋር ነው፡፡»

የምክትል ሃላፊው ትንፋሽ ሲቆራረጥ ተሰማኝ፡፡ «አቅልህን ስተሃለ እንዴ!? አለቆችህም እንደተመለስክ ገመድ በአንገትህ ሊሸመቅቁ ተዘጋጅተውልሃል፡፡» አለኝ በቁጣ መንፈስ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የተናገረውን ያልሰማሁ በማስመሰል ስልኩን ልዘጋው ስል የታላባኒ ፔክ መርጋዎች ኪርኩክ ላይ በሚከፍቱት ጥቃት ለማነፍነፍ ዱካ ዱካቸውን እየተከታተልኩነኝ፡፡

ታሊባን ደግሞ በሬን ሲያንኳኳ ዕንቅልፍ እያንጎላጀኝ ነበር፡፡

«ሳዳም በፍርሃት ርዷል፡፡ በይዞታችን ስር ያሉ ግንባሮችን ሁሉ በከባድ መሳሪያ መደብደብ ጀምሯል፡፡» በሩን በቀስታ ዘግቶ ወደከፍሉ ሲያመራም እየተንከተከተ ሲስቅ ይሰማኝ ነበር፡፡

ታላባኒ ከግንባር የሚደርሱትን ዘገባዎች በማንበብ ቁጭ ብሎ እንደሚያነጋ ግልፅ ነበር፡፡ እኔ ግን ድካም እደቋቁሶኝ ዕንቅልፍ ተጫጭኖኛል እናም ለብሼው ስለተኛሁት ስስ ብርድልብስም ሆነ ሌቱን በሙሉ እኛን በማደን ስለሚያሳልፉት የሳዳም ተዋጊ ሄሊኮፕተሮች ማሰቡ ግድ አልሰጥህ ብሎኛል፡፡

እናም በሚቀጥለው ጥዋት 12 ሰዓት ሲሆን ታላባኒ ቀሰቀሰን ወታደሮቹን አስነበኘን፡፡ ወታደሮቹ ትምህርት ቤቱ አካባቢ ካለው መስክ ላይ ተከማችተው መሣሪያዎቻቸውን እየወለወሉና መኪናዎቻቸው ላይ እየጫኑ ማታ ላይ ለሚከፍቱት ጥቃት ሲዘጋጁ ተመለከትን፡፡ ታላባኒ በመሃላቸው ሲያልፍም ከአክብሮታቸው የተነሳም ይከቡት፣ እጅ ይነሱት እና እጁን ይስሙት ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለም እንደኛው የታላባኒ ረዳትም በጉብኝት ላይ ሳለን ጣፋጭ ሻይ በትሪ አድርጐ አቀረበልን፡፡

ታላባኒ ከእርሱ ጋር እንድቆይ ቢማፀነኝም የተሰጠን ጊዜ ወደማለቁ ተቃርቦ ስለነበር አንድ ቀን ከግማሽ ያህል ተጉዘን እንካራ መድረስ ስለሚኖርብን ባለችን ቀሪ ጊዜ ቶም እና እኔ በፍጥነት መጓዝ ይኖርብናል ብዬ ቁርጡን አሳወኩት፡፡

ታላባኒ አቅፎ ሲሰናበተን እኛም በቶሎ እንደምንገናኝ ተስፋ ማድረጋችንን ገለፅንለት፡፡

«ምናልባት የምንገናኘው ባግዳድ ይሆናል» ሲል ታላባኒ ተሳለቀ፡፡

ከኪርኩክ በስተምስራቅ ጥቂት ማይሎች ርቀት ላይ ወደምትገኘው ቻማቻማል ከተማ የሚወስደው መንገድ በጥሩ ይዞታ ላይ ይገኛል፡፡ በዛ ላይ በመንገዱ ላይ የሚመላለስ መኪና አልነበረም፡፡ ቀኑም ብራ ስለነበር ከአንድ ሰዓት በሚያንስ ጊዜ ውስጥ ቻማቻማል እንደምንደርስ ገምተን ዕንቅስቃሴ ጀምረናል፡፡ ይሁንና ጥቂት እንደተጓዝን ኤም.አይ 24 ተዋጊ ሄሊኮፕተር ስታንዣብብ ተመለከትን ተዋጊ ሄሊኮፕተሯ ወደፊት ወደኋላ ሳትል ሰማዩ ላይ እንደቆመች ቅንኝቷን መሬቱ ላይ አነጣጥራለች፡፡ በአካባቢያችንም እኛን እስከመኪናችን ሊሸሽገን የሚችል ሸለቆ ነገርም ሆነ ዛፎች ወይም አለት ቢኖር ኖሮ ብለንም ከመቅፅበት በፍራቻ ከመራዳችን የተነሳ ባልታየናቸው ስንል ተመኝተን እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ እናም የአንድ የታላባኒ ፔክ መርጋ ቡድን አባል ኒሳኑ መኪናችንን ከአካባቢው ጋር እንዲመሳሰል በሚል ጭቃ ባይቀባት ኖሮ ከአንድ ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሄሊኮፕተሯ ወዳለንበት ዝቅ ብላ በመብረር እኛንም ሆነ



t.me/OLDBOOKSPDF

መኪናችንን በማጋየት እንዳልነበረ ማድረግ ባልተሳናትም ነበር፡፡ ይሁንና ከአንድ ደቂቃ በኃላ ሄሊኮፕተር ከሽንተረሮቹ ጀርባ በራ እንደተሰወረች መኪናችንን በሚቻለን ፍጥነት ወደፊት እንዲፈተለክ አደረግነው፡፡

ቻማቻማል አለወትሮዋ በፀጥታ ተውጣለች ሰዎቿም ሜዳ ላይ ከተዘረጋው ገበያ ይገበያያሉ፡፡ ልክ የመኪናችንን ሞተር እንዳጠፋን ከተማይቱን ያናወጠ የከባድ መሣሪያ ድምፅ ሰማን፡፡ ለጥቆም ነጭና ግራጫ ጢስ ከቻማቻማል በስተምስራቅ ካሉት ኮረብቶች ግርጌ ሲነሳ ተመለከትን፡፡

እኛም በቀጥታ ኩርድን ከኢራቅ ወደሚለየው ጦር ግምባር ስናመራ የታላባኒ ተዋጊዎች ከጊዜያዊ የድንበር ኬላ ሰብሰብ ብለው አገኘናቸው፡፡ ተዋጊዎቹም በተቃራኒው ወገን በኩል እየሆነ ስላለው የሚያውቁ እየመሰሉም የሚያውቁት ነገር ቢኖር ከነባሩ ኬላ የኢራቅ ፖሊስ እንዳስለቀቃቸውና ድንበሩም ክፍት መሆኑን ነበር፡፡

ወደሳላህ አል-ዲን የመልስ ጉዞ ስናረግ ለመጨረሻ ጊዜ እረፍት የወሰድነው ኢብሪል ውስጥ ነበር፡፡ ለጥቆም ከታላባኒ ዋና ጦር ሰፈር እንደገባን በቀጥታ ያመራነው የኢራቅ ምርኮኞች ወዳሉበት ቦታ ነበር፡፡ ምርኮኞቹም እራት የእግር ኳስ ሜዳዎችን በሚያህል ስፍራ ላይ ፈሰዋል፡፡ አንዳዶቹ ቆመዋል ሌሎቹም ተቀምጠዋል አሊያም መሬቱ ላይ ተንጋለዋል፡፡ ከግቢው ውጭ ባለው የመንገድ ጥግ ላይም የፔክ መርጋ ተዋጊዎች የማረኳቸውን ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎች፣ ካማዝ የተሰኙ ከባድ ካሚዮኖች፣ ሮኬት ማስወንጨፊያዎች፣ የኤኬ 47 ቀለሀ የያዙ ሣጥኖችና ተዋጊዎቹ ከጦርነቱ መማረክ የቻሉት ነገር ሁሉ ተቆልሎ ክምር ሰርቷል፡፡

ጉዳዩን የሚመለከተው የ.ፒ.ዩ.ኬ ባለስልጣን የመጣነው ለምርኮኞቹ ቃለመጠይቅ ለማቅረብ እንደሆነ በማመን ከቢሮው አስገባን፡፡ ለጥቆም ደርዘን የሚሞሉ የኢራቅ ጦር አዛገሮች ወዳሉበትና ግድግዳው ተደግፎ በተቀመጠላቸው አግዳሚ ወንበር ላይ ወደተቀመጡበት አንድ ክፍል ይዞኝ ገባ፡፡ እኔም በዘፈቀደ አንድ ሻምበልን ማናገር መረጥኩ፡፡ ሻምበሉም እድሜው ወደ ሰላሳ የሚጠጋ ሲሆን ድካም ይነበብበታል፡፡ ያን ዕለት ጠዋት ሰዓቱ ሁለት ከመሙላቱ በፊት የሚመራውን ሻምበል ጦር ቃኚ ወታደሮችን ለማየት ሲዘዋወር የመጀመሪያውን የቃኚ ቡድን ይዞታ ባዶ ሆኖ ማግኘቱ እንዳስገረመውና በሻምበል ጦሩ ጎንና ጎን ያሉ የቅኝት ክልሎችም እንዲሁ ሆነው ማግኘቱን ገለፀልን፡፡ እናም የቅኝት ወታደሮቹ የደረሱበትን ለማጣራት ወደ ሻምበል ጦሩ ዕዝ በመመለስ ላይ እንዳለ ዙሪያውን የፈነዳው የአውቶማቲክ ጠመንጃ ተኩስ ከጉዞው እንደገታው፡፡ ወታደሮቹም የአፀፋ ተኩስ ያደርጋሉ ብሎ ቢጠብቅም የተተኮሰች አንዲት ጥይት እንዳልነበረ ከዚያ ይልቅ የታላባኒ ፔክ መርጋዎች ያለማቋረጥ ከያሉበት ብቅ ብቅ ማለት እንደጀመሩ፡፡ ሁኔታው ዋሻ ቆፍረው መጥተው ከመሬቱ ውስጥ ድንገት የፈለቁ ያህል ሆኖ እንዲሰማው እንዳደረገውና እጅ ከመስጠት ውጭ አማራጭ እንዳልነበረው ሳይሸሽግ ገለፀልኝ፡፡ እኔም ሻምበሉን አመስግኜ እጄ ላይ የቀረውን የመጨረሻ የቆርቆሮ ሬሽን ሰጠሁት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እናም እኔ አካባቢውን ለቅቄ ከመሄዴ በፊት የኢርቢሉን አዛዥ አገኘሁት፡፡ እሱም በመጨረሻ ስለተፈፀመው ጥቃት ማብራሪያ ቢጤ ሰጠኝ፡፡ ወታደሮቻቸውም 847 ኛውን ብርጌድ እንደደመሰሱትና አሁን ኩርኩክ ለጥቃት የተመቻቸች እንደሆነች፡፡ ታላባኒም በቂ የጦር መሣሪያ ካገኘ ከተማዋን በቁጥጥሩ ስር ሊያደርጋት እንደሚችል ደሰኮረልኝ፡፡

እኛም ወደ ሳላህ አል ዲን የመልስ ጉዟችንን እያደረግን ሳለን ቶመ ስለመረመራቸው የኢራቅ ጦር መሣሪያዎች ገለፀልኝ፡፡ ማለትም ጦር መሳሪያዎቹ ሰሞኑን መማረካቸው እንዳጠራጠረው ነገረኝ፡፡ ካለው የረዥም ጊዜ ልምድ በመነሳት ጠመንጃዎቹ ሊሆኑ የሚችሉት የኢራቅ ጦር ንብረት መሆናቸውን አጫወተኝ፡፡

እናም ወደ ቤት እንደተመለስን ወደጠቅላይ መምሪያው 847 ኛውን ብርጌድ በተመለከተ መልዕክት አስተላለፍኩ፡፡ ያስተላለፍኩትን መልእክት ተከትሎም ከዛው ተደወለልኝ፡፡

«አሁንም ተፈፀመ ያልካቸውን ጥቃት የተመለከቱ ምስሎች ከሀዋ ላይ አልደረሱንም፡፡» አሁንም ያቺው ጠሟጋ ሴት ነበረች ሹክክ ያለችኝ፡፡

«ላምናችሁ አልችልም፡፡ እዚህ ውጊያ በመካሄድ ላይ እንዳለ የምናስመስል ይመስላችኋልን??? ባይገርምሽ አሁን ገና ከኢርቢል መመለሴ ነው፡፡ እዛ በሺህ የሚቆጠሩ የኢራቅ ምርኮኞችን በአይን በብረቱ አይተናል፡፡ የተማረኩ የጦር መሣሪያዎችንም ተመልክተናል፡፡

የምርኮኞቹ ነገር ቶም መሣሪያዎቹ በእርግጠኝነት የኢራቅ መሆናቸውን መናገሩ እና እኔም እንደ አንድ ቡድን ሃላፊ ጦርነቱ ጨዋታ ሳይሆን የምር እንደነበር አስረግጬ መናገሬ ሴትየዋን ሊያሳምኗት አልቻሉም፡፡

«ጥሩ» ስትል ተናገረች «እኔ አምናችኋለሁ የተቀረው ማህበረሰብ በተለይም ፔንታጎን ሊያምናችሁ ግን አይችልም፡፡»

የተናገረችው ስለ CIA እንደሆነ አውቄአለሁ፡፡ ፔንታጎንን የጠቀሰችውም ቁጣዬን ለማብረድ ነበር፡፡ ቢሆንም ስሜቴ አልተቀየረም፡፡

«ጥሩ ለነዚያ ለማይረቡ ሰዎችሽ የፖለቲካ ጨዋታቸውን አቁመው በየውስኪ ቤቱ ከሚቀርብላቸው ማርቲኒ ባሻገር ማየት እንዲጀምሩ ንገሪያቸው፡፡»

«የነገርኩህ እኮ ያሉኝን ነው፡፡»

«እኮ አሁን እኮ ተረዳሁሽ፡፡ አንድ ዜና በዋሽንግተን ፖስት ወይም ኒውዮርክ ታይምስ መፅሔቶች ላይ ካልወጣ እውነት አይደለም ማለት ነው፡፡ አንድ የመፅሄት ዝነኛ ዘጋቢ የተሳሳተ አውሮፕላን ተሳፍሮ ኩርድ ግዛት በወረደና ጦር ግንባሮቹ ያሉበትን ስፍራ በጠቆምኩት ነበር፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

ከወዲያኛው ጫፍ ፀጥታ ነገሰ፡፡

«እባክሽ ከቦብ ጋር አገናኚኝ፡፡» አልኳት

አገናኘችኝ ቢሆንም ቦብ በሁኔታው የተሳበ አይመስልም፡፡

«እርግፍ አርገሀ ተወው» ሲል ልክ እንደቀረበ አንባረቀብኝ፡፡

«ቦብ ለአንድ ሰከንድ አድምጠኝ፡፡ እዚህ እውነተኛ ጦርነት እየተካሄደ ነው፡፡ በሌላ ሳምንት የሺ ክፍለ ጦር ሀልውና ያከትምለታል፡፡»

እዚህ ኩርዶችን በተመለከተ መረጃ ያደረሰን የመረጃ ምንጭ የለም፡፡ ገብቶሃል? እናም እኔ አሁን ከአንተ መስማት የምፈልገው የቱርክ ድንበርን መሻገርህን ብቻ ነው፡፡»

«ሁኔታውን ቢያንስ በኢራቅ ተቃዋሚ ጎራ ቦታ ላይ ሆንህ ልታየው ይገባል እኔ በግሌ የሺ ክፍለጦርን ለማከሰም በሚደረገው ዘመቻ እያንፍንፍኩ በመከታተል ላይ ነኝ፡፡ እኔን ከኩርድ እንድወጣ ካደረግከኝ ምንም አይነት መረጃ አይኖረንም፡፡»

ጌታው! ቶኒ ሌክ ያደረከውን አስተዋፅኦ ማወቅ እንደሚፈልግ መረዳት ይኖርብሃል፡፡ መጋቢት 15 ዘጠኝ መቶ ሰዓት ከፍሬድ ቱርኮ ጋር እንድትገናኝ ቀጠሮ ተይዞልሃል የሚበጅህም ወደቀጠሮው ስፍራ መሄድ ነው፡፡ ትሰማኛለህ?!፡፡»

☆☆☆

እንደተገመተው የታላባኒ ጥቃት የሺ ክፍለ ጦርን አላከሰመውም፡፡ ታላባኒ ራሱንና ተዋጊዎቹን አትርፎ ማብቂያ ያለው የማይመስለውን የኩርዶቹን የእርስ በርስ ግጭት ከባርዛኒ ጋር ጀምሯል፡፡ ቻላባይ በበኩሉም በአካባቢው ቅኝቱን ከአደረገ በኃላ ወደ ሳላሀ አልዲን ተመልሷል፡፡ ባርዛኒ ምናልባትም በሳዳም ትዕዛዝ ቻላባይ በይዞታው ስር ካለው መሬት እንዲወጣ ሲያደርገው ይችላል፡፡ በኩዴታ ጥንስስ ወደ ሰሜናዊ ኢራቅ የመጣው ጀነራልም ወደደማስቆ ተሰዷል፡፡ ከእዛም ወደ ለንደን አምርቷል፡፡ ይህ ሁሉ ሳዳም ሁሴንን መጠነኛ ምቾት የነሳ ነገር ሆኖ አልፋል፡፡

ብዙም ሳይቆይ ሳዳም ነዳጅ ዘይት በምግብ መገበያየት ጀምረዋል ይህም ኢራቅ ውስጥ ያለውን የምግብ እጥረት እንደሚያቃልልላቸው እና ሰራዊታቸው ውስጥ የሚፈጠረውን ኩብለላና ክደት እንደሚያስቆምላቸው አምነዋል፡፡ እናም አሁን እሳቸውን ከስልጣን ማስወገድ ከፈለግን ማድረግ ያለብን ነገር ቢኖር ጦርነት መክፈት እንጂ መንግስት ግልበጣ ማካሄድ አይደለም፡፡ እኔ እንደሆንኩ በበኩሌ መጋቢት 15 ዘጠኝ መቶ ሰዓት ላይ ላንግሌይ ቨርጂኒያ ለሚገኘው ቢሮ ሪፖርት አድርግ በተባልኩት መሰረት ሪፖርቱን ለማቅረብ ወደዚያው አቅንቼያለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፯

## መጋቢት 1995፣ ዋሽንግተን-ዲ.ሲ.

ፍሬድ ቱርክ ወደ CIA ካውንስል ዋና አለቃ ቢሮ ሲወስደኝ ምንም ፍርሃት አልተሠማኝም፡፡ ሁለቱ የFBI ሰዎች የወንጀሉ ዋነኛ ተዋናይ እኔ መሆኔን ሲነግሩኝ እንኳን አልደነገጥኩም፡፡ ሳዳም ሁሴንን ያህል ሰው ለመግደል ሙከራ በማድረግ ወንጀል መጠርጠር እንኳን ሲያስቡት በራሱ አስፈሪ ቢሆንም ለእኔ ግን ምንም ማለት አልነበረም ምክንያቱም ከደሙ ንፁህ ነኝና፡፡

ቶኒ ሌክም ሆነ ሌላው የብሄራዊ ደህንነት ካውንስል አባል የፈለገውን ነገር ሊያምን ቢችልም በሰሜናዊ ኢራቅ ተፈጠረ የተባለውን ነገር እንደሌለሁበት አውቀዋለሁ፡፡ ቅንብሩም የቻላቢ የተወሳሰበ ቀመር መሆኑ ይገባኛል፤ ቻላቢ በመረቡ ውስጥ እንዳስገባኝም ተረድቻለሁ፡፡ የግድያ ሙከራን የሚከለክለውን አንቀፅ 12333 እንዳልጣስኩም አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንፃር እውነት በራሷ ጊዜ እንደምትወጣ አገነዘብ ስለነበር በራሴ መተማመኔ እንዳለ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡

በማርች 22/1995 ዓ.ም የአካል ምርመራዬን ካደረኩ በኃላ ለተጨማሪ ምርመራ ወደቶኒ ሌክ ቢሮ ማቅናት ነበረብኝ፡፡

የ CIA ቅጥረኞች ከእኔ ጉዳይ ጋር የተያያዙ የድርጅቱን ፋይሎችና ዶክመንቶች ቢያገላብጡም አንድም መረጃ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም በሚያዚያ 4/1996 የአሜሪካ የፍትህ ሚኒስቴር እኔን ሊያሣስር አሊያም ሊያስቀል የሚያስችል መረጃ እንደሌለና ፋይሉም በዚሁ እንዲዘጋ ሲል ለ CIA ደብዳቤ ፃፉ፡፡

CIA'ም በሁኔታው በመፀፀት ከይቅርታ ባልተናነስ አኳኋን ለእኔ በጎ ትኩረትን የሰጠበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡

የሆነው ሆኖ የCIA'ም ሆነ የፍትህ ሚኒስቴር ድጋፍ የእስር ቤት መውጫ ካርድ ሊሆን አልተቻለውም ነበር፡፡ ጉዳዩ በተለይም በብሄራዊው ደህንነት መስሪያ ቤት ስር ሰዶ የነበረ ሲሆን ውጥረቱም ኳሷ በፍፁም ቅጣት ክልል ውስጥ በመገኘቷ አጥቂዎችና ተከላካዮች ከሚረባረቡባት አጋጣሚ ጋር የሚመሣሰል ነበር፡፡ ቢያንስ 2-3 ዓመታት ያህል የሰነበተው ይህ መሣዩ ጨዋታ እስከሚበርድ ድረስ እንደ CIA ቅጥረኛ ከውጭ የተያያዙ ጉዳዮችን ከመስራት አግዶኝ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ እንዲህ ዓይነት ዕድሎችን መልሼ የማገኛቸው አልመሰለኝም ነበር፡፡ ምክንያቱም ከራዲዮ ታንክና ሄሊኮፕተር እንዲሁም



t.me/OLDBOOKSPDF

ከራሺያ ባለስልጣናት ጋር የነበረኝን የጠበቀ ቁርኝትና ወዳጅነት በርካቶች ያውቁ ነበርና ነው፡፡ ቢሆንም CIA ሌላ ችግር ይፈጥራል ብሎ እስካልገመተኝ ድረስ ብቻዬን ሊተወኝ ወይንም በፈለኩት ስፍራ ሊመድበኝ እንደማይገደው ይሰማኝ ነበር፡፡

በመካከለኛው ዮሮሲያ የCIA ምክትል ባለስልጣን ሆኜ መሾሜ የፈጠረልኝ ነገር ቢኖር መተኛትና ማንቀላፋት ብቻ ነበር፡፡ ስራዬ ከCIA ቅጥረኞች ጋር እንድገናኝ የማይፈቅድ ስለነበር ስራዬ ሁሉ ወረቀቶችን ስርዓት ማስያዝና የኢሜይል መልዕክቶችን መቀበልና መላክ ብቻ ነበር፡፡ እናም በእኔ ስር 25 የሚሆኑ ሰዎች ስላሉ ስራ የሚባለው ነገር በእነርሱ ውስጥ ስለሚያልፍና ስለሚከናወን በእኔ ደረጃ ያሉ ባለስልጣናት የስራ ጫና እንዲቀንስ ያደረገ ነበር፡፡

በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ስኖር የከተማዋን አጠቃላይ ገፅታ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም፡፡ ለነገሩ ዋሽንግተንን በፊትም አውቃት ስለነበር የከተማዋ ኑሮ መወደድ በተለይም የቤት ኪራይና የሬስቶራንት ምግቦች ዋጋ እንዲህ መናሩ በጣም አስገርሞኛል፡፡ የእኔን ሁኔታ ከ ዲሲ ለውጥ ጋር ሳነፃፅረው ደግሞ እደነግጣለሁ፡፡ ምክንያቱም ከከተማዋ መለወጥ ጋር ተያይዞ የመጣው የኑሮ ውድነት አይጣል ነው እኔማ መጥኔ ለመጪዎቹ ብያለሁ፡፡ ከሁሉም ነገር በላይ ደግሞ ለእኔም ለአሜሪካም አስደንጋጭ የነበረው ነገር ቢኖር ስለ ሃገሬ ከማውቀው ይልቅ ስለ ፍልስጤም የነፃነት ትግል፣ ስለ አሜሪካ ሴኔት ከማውቀው ይልቅ ስለ ሳኡዲው የዋሃቢ ቡድን የማውቀው ነገር መበርከቱ ነበር፡፡

ለበርካታ አመታት ሻንጣዬን በጀርባዬ አዝዬ በታጂኪስታንና ሱዳን አስቸጋሪ ስፍራዎች ከመዞሬ አንፃር በእነዚህ ሃገራት ውስጥ የሚገቡና የሚወጡ በተለይም ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ጉዳዮች የማወቅ ዕድሉ የነበረው ከእኔ ጋር ነበር፡፡ አሁንም የምሰራው ይህንን ጉዳይ ነው ማለት እችላለሁ፡፡

ከምንም ነገር በላይ ለመማር ያለኝ ፍላጎት ከፍተኛ ነበር፡፡ ይህንን ዕድል የሚሠጠኝ አካል ግን አልነበረም፣ ስለዚህ ያለኝ አማራጭ ራሴ ለራሴ በራሴ ውስጥ ኮሌጅ መክፈት ነበር፡፡ እናም የአሜሪካንን ፓለቲካ ከሁሉም አቅጣጫ ወደ ውስጤ ማስገባት ቀጠልኩ፡፡ ይህንን ነገር ለማግኘትም ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ማወቅና መረዳት ያስፈልገኝ ነበር፡፡ እናም ሃይማኖት፣ ዘርና የፓለቲካ ልዩነት ሳልመረጥ የዋሽንግተን ፖለቲካ እንዴት እንደሚሰራ ከተለያዩ ሰዎች መስማቴን ስራዬ ብዬ ተያያዝኩት፡፡ እያንዳንዱ የዓለም ማህበረሰብ ስለ አሜሪካ ፖለቲካ ማውራት የሚፈልግ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ የተለያዩ አቋም ያለው በመሆኑ የፈለኩትን ነገር ሁሉ ለመስማት የሚያዳግተኝ አልነበረም፡፡ ሁኔታው በመጀመሪያ ግርምታን ፈጠረብኝ፣ በተለይም ፓለቲካዊ ይዘት ያላቸውን የኮሚቴ ስብሰባዎችን የምስጢር ብክነቶች ከአጥፍቶ ጠፊዎች ባልተናነሰ እኳን ጥሩ የፓለቲካ ሚናን እንደሚጫወቱ መረዳቴ ደንቆኛል፡፡ ሁኔታው ያበሳጨኝ ደግሞ ከዚህ በፊት የማላውቀውን ፓለቲካዊ ምስጢር ምናልባትም በዕንፍ ከሚገኙት የዓለም ጳርቻዎች ተነስተው ኃይት ሃውስ ቤተመንግስት የሚደርሱ ቁምነገሮችን መረዳቴ ነበር፡፡ ከብስጭት አልፌ ወደ ቁጣ አመራ ዘንድ ደግሞ ከሰው ህይወት ይልቅ ገንዘብ እኔ ለምገኝበት አይነቱ የፓለቲካ ሰንሰለት እጅግ የላቀ ሚና የነበረው ነገር መሆኑ ነበር፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች በተጨማሪ በእንዲህ ዓይነቱ የፓለቲካ መረብ ውስጥ ላለን ሰዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

ሌላው ገለልተኛ ማህበረሰብ የሚሰጠን ትኩረትና ፍቅር በዜሮ የተባዛ መሆኑ ነበር፡፡ ብቻ ሁሉም ነገር የኦዲሲይን ተረቶች ይመስል ነበር፡፡ በዚያ የፓለቲካ አየር ውስጥ የነበርን ሰዎች የሚሠማን ማጣታችን በርግጥም ሆድ የሚያስብስ ነገር ነበር፡፡ እኔም የዚህ ቡድን እንደ አካል ስለነበርኩኝ ቅሬታ እንደሚሰማኝ ጥርጥር የለውም፡፡ ያም ሆነ ይህ ለማንኛውም ታሪኬን ለማውራት ወደ ኃላ አልልም፡፡

☼☼☼

በዋሽንግተን ፖለቲካ ተማትሮዬ ውስጥ የመጀመሪያውንና እጅግ እንድማርበት የሆንኩትን ትምህርት ያገኘሁት በአንድ አጋጣሚ ነበር፡፡ ጊዜውም ግንቦት 17/1995 ዓ.ም. ነበር፡፡ ሼላ ሔልሲን በCIA የደቡብ ቀጠና ተብሎ በሚጠራው ሕዋስ ውስጥ ኦፊሰር ስትሆን በዚህ በተጠቀሰው ዕለት ይዛው ወደ እኔ የመጣችው ሪፓርትም የሚያስደነግጥና ከኦፊሰሯ ፊጣን ምላስና ጥንቅላት ጋር ተዳምሮ ዕረፍት የሚነሣ አይነት ነበር፡፡

ሔስሊን ወደ እኔ ይዛው የመጣችው ወረቀት የሚያስረዳው ወይንም ደግሞ እርሷ ማወቅ የምትፈልገው ሶስት አሜሪካውያን ከCIA ጋር ስላላቸው ግንኙነት ነበር፡፡ የመጀመሪያው ግለሰብ ሮብ ሰብሃኒ ሲሰኙ የጆርጅታውን ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰርና የሚረላንድ ሪፐብሊካን ፓርቲ አባል ናቸው፡፡ ሁለተኛው ግለሰብ ሳሃግ ባግዴ ሳሪያን ሲሰኙ በካሊፎርኒያ የሚኖሩ ዶክተር ናቸው፡፡ ሶስተኛው ግለሰብ ደግሞ ሮገር ታምህዝ ይሠኛል፡፡

ስለ መጀመሪያዎቹ ሁለት ግለሰቦች የማውቀው እንዳችም ነገር ባይኖርም ሶስተኛውን አሜሪካዊ ማለትም ሮገር ታምራንዝን በተመለከተ ግን ሊባኖስ ውስጥ በነበርኩበት ወቅት ስለ እርሱ እሰማ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ታምራዝ በ1983 ዓ.ም ቤሩት የሚገኘውን የአሜሪካ ኤምባሲ ያፈነዱትን ተጠርጣሪዎች ከእስር ያስለቀቁት የሊባኖስ ፕሬዚዳንት አሚን ጄማይል የቢዝነስ አጋር የነበረ ሲሆን ፕሬዚዳንቱ ስልጣን ከለቀቁ በኃላ በቤሩት የሚገኘው ባንኩ ከፍተኛ ክስረትን በማስተናገዱ በተለይ ከሶሪያ መንግስት ጋር እሰጣ ገባ ገብቶ ነበር፡፡ ታምራዝ እንደሚለው ባንኩ ለኪሳራ እንዲዳረግ ያደረጋቸው ሶሪያ ስትሆን ምክንያቱ ደግሞ ሶሪያ የእስራኤል መልዕክተኛ ናቸው ብላ ከምትፈርጃቸው ጄማይል ጋር ታምራዝ ወግኗል በሚል ነበር፡፡

እውነታው የትኛውም ይሁን ሁኔታው ታምራዝን ከአካባቢው ፖለቲካና ቢዝነስ ጋር በተያያዘ አለማቀፋዊ ዝና እንዲኖረው አድርጎ ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ ከሶሪያ ጋር የገጠመው እሰጠ ገባ ከመካከለኛው ምስራቅ ሃገራት ጋር የሚያደርገው የንግድ እንቅስቃሴ አስተጓጉሎበት ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ከስተቱ ታምራዝን ወደ ካስፒያን ባህር ፊቱንና ስሜቱን ያዞር ዘንድ አላገደውም፡፡ እናም ቱርክሜኒስተን ነፃነቷን ካገኘች በኃላ በሃገሪቱ የመጀመሪያው ነዳጅ ነጋዴ በመሆን ብቅ አለ፡፡ እናም በአካባቢው ከሚገኙ ሁለት የነዳጅ ዘይት ማምረቻ ግዙፍ ካምፓኒዎች ጋር እጅግ የጠበቀ የንግድ ግንኙነትን መሠረተ፡፡ በ1994 ዓ.ም ደግሞ ከካስፒያን ወደ ሜዲትራኒያን ከዚያም ወደ አርሜኒያ የሚሄድ የነዳጅ ዘይደት መስመር መርኃቱ ታወቀ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሼላ ሑስሊን ጉዳያቸውን በእንክሮ የያዙችባቸው ሶስቱ ሰዎች አሜሪካውያን በመሆናቸው ሁኔታው አለመግባባት እንደሚፈጥር ግልፅ ነበር፡፡ ምክንያቱም በፕሬዚዳንት ኒክሰን ዘመን እንደተደነገገው በአሜሪካውያን ላይ ስለላ ማካሄድ አይቻልም ነበር፡፡ እንደዕውነቱ ከሆነም በCIA መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ይሄ ነገር መኖሩንም አውቃለሁ፡፡ የሆነው ሆኖ በኃይት ሀውስ ዙሪያ የሚሽከረከረው ለጋው የፖለቲካ አዙሪት የኒክሰንን ዘመን ድንጋጌ የማስታወስ አቅምና አስተዋይ አዕምሮ ይኖረዋል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

«ሑስሊን እነዚህን ሶስት ሰዎች ጥላሸት ለመቀባት የምትፈልገው ለምንድን ነው?» ብዬ ጠየኩኝ፡፡ ጥያቄውን ያቀረብኩለት ግን ለሴትዮዋ ረዳት ነበር፡፡

«እንዴት ላውቅ እችላለሁ?... ምናልባት ቀን የጣላት እፍቃሪ ልትሆን ትችላለች» ብሎ መለሠ፡፡

«ስለዚህ ምንድንነው ማድረግ ያለብን?» አልኩኝ በማስከተል፡፡ የሑስሊን ረዳት ለእኛ ማለትም ለዳይሬክቶሬት ኢንተለጀንስ ሳይሆን ለዳይሬክቶሬት ኦፕሬሽን የተመደበ በመሆኑ ጥያቄዬን ከምን አቅላጣጫ ሊመልሰው እንደሚችል አውጠነጠንኩ፡፡ እሱ ግን ትንሽ ቆይቶ «ሑስሊን ታምራዝ የCIA ቅጥረኛ ወይም አባል ነው ብላ ታስባለች» አለኝ፡፡ አሁን ነገሮች በመጠኑም ቢሆን ተገለጡልኝ፡፡

በአሜሪካ መንግስትና በCIA ዳይሬክተር መካከል በ1977 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት መሠረት የዳይሬክቶሬት ኦፕሬሽን ከእዳዲስ ቅጥረኞች ጋር ግንኙነት ሲደረግ ፖሊስ አውጭዎች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡ የብሔራዊ ደህንነት ካውንስል አባላት እንደፖሊስ አውጭ ስለሚቆጠሩ የዚህ አካል የሆነችው ሑስሊን ታምራዝን በሰኔ 2 ሲገናኙ ታምራዝ ከCIA ጋር ያለውን ግንኙነት ልንነግራት የግድ ነበር ይሁንና ይህ ግን አልሆነም፡፡

በዚህ ስሌት መሠረትም የሑስሊን ጥያቄ ትክክል ነበር፡፡ ከምስራቅ ሀዋስ በደረሰው ሪፖርት መሠረትም ሮገር ታምራዝ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ከCIA ጋር ግንኙነት ነበረው፡፡ የሆነው ሆኖ የታምራዝና የCIA ግንኙነት በጥቅም ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ ምክንያቱም ታምራዝ በምንም መልኩ የCIA እውነተኛ ቅጥረኛ የሚሆን ሰው አይደለም ታምራዝ CIA'ን የሚጠጋው ከራሱ ጥቅም አነፃር ስለነበር ለCIA እንደማይሆን ወትሮም ግልፅ ነበር፡፡ የCIA ባለስልጣናት በተለያዩ አጋጣሚዎች በገንዘብ መርዳቱ የCIA ተቆርቋሪ ሳይሆን CIA'ን መጠቀም የሚፈልግ ሰው መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ሑስሊን ስህተት የሰራችው ግን እዚህ ላይ የነበረ ሲሆን እሱም ታምራዝን የCIA ዋና አባል አድርጋ እምና መቀበሏ ነበር፡፡

ሑስሊን በጠየቀችው መሠረት የዴስክ ኦፊሰራችን የታምራዝን ፋይል ወደ እኔ ሲያመጣልኝ ምንም ሳልመለከተው «ለሴን ሰጠውና ይፈርምበት» አልኩት፡፡» ሴን ማለት ደግሞ የደቡብ ቀጠና ሕዋስ አለቃ ነው፡፡

ሁኔታው በጣም ከንክኖኛል፡፡ ታምራዝ ከሑስሊን ጋር እንዴት እንደተገናኘ፣ ሑስሊን ስለ CIA እና ታምራዝ ግንኙነት እንዴት እንዳወቀች በተለይ ደግሞ የብሄራዊው



t.me/OLDBOOKSPDF

ደህንነት ካውንስል አባላት ታምራዝን ለማግኘት ለምን እንደጓጉና የመሣሠሉት ሁኔታዎች ቀልብ ያሳጡኝ ነበሩ፡፡ በግንቦት 19 ቀን ልክ ከሌሊቱ 7፡02 ሰዓት ላይ የደቡብ ሕዋስ ታምራዝ ከ CIA ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚገልፅና ሌሎች መረጃዎችን ለሑስሊን በፋክስ ላክላት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በባኩ የሚገኘው ህዋሳችን አሊቃ ከነበረው ጋር ግንኙነት የነበራቸውና የእሞኮ የነዳጅ ዘይት አማካሪ የነበሩት የፕሮፍሰር ሮብ ሶብሃኒ ፋይልም ለሑስሊን ፋክስ ተደረገ፡፡ ምንም እንኳን ፕሮፌሰሩ ከ CIA ጋር ስላላቸው ግንኙነት የማያውቁ ሊሆኑ ቢችልም ሁኔታውን ለሑስሊን ማሣወቃችን አልቀረም ነበር፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ከታምራዝ ጋር የተያያዘ ሌላ መረጃ ለሑስሊን ልኩላት ነበር፡፡

ከአንድ ሳምንት በኋላም የሪፓርት አፊሠራችን ቢሮ ድረስ መጥታ «ሑስሊን ታምራዝን ከማንኛውም አደጋ እንደምንጠብቀው ማመኗን ነገረችኝ፡፡

በዚህን ግዜ ከበፊቱ በበለጠ የታምራዝን ፋይሎች እንደገና እመረምራቸው ገባሁ፡፡ ፋይሉም ታምራዝን ከራሱ ባንክ ጋር በተያያዙና በሌሎች ወንጀሎች በሊባኖስ እንደሚፈለግ ያስረዳል፡፡

«ስለዚህ ይህ ጉዳይ ከምን ጋር ይያያዛል? አልኳት የሪፓርት ኦፊሠሯን፡፡

«ሑስሊን ታምራዝ ታንቆ እንዲገደል ፅኑ ፍላጎት አላት፤ ለዚህ ደግሞ የእኛን ትብብር ትፈልጋለች» አለችኝ፡፡

ሑስሊን እዚህ ውሳኔ ላይ ልትደርስ የቻለችበት ምክንያት ከኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት (DO) እና ከኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት (DI) ያገኘቻቸው ታምራዝን የተመለከቱ መረጃዎች የተለያዩ በመሆናቸውና በእኛ በኩል የተሠጣት መረጃ ታምራዝን የሚሸፋፍን መስሎ ስለተሠማት ነበር፡፡ ሁኔታውን በእንክሮ ከመረመርኩ በኃላ የዳይሬክቶሬት ኦፕሬሽን የቅጥረኞችንም ሆነ ከCIA ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች መረጃዎች የሚይዘው ከኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ጋር ተመሳሳይ ባልሆነ ሁኔታ እንደሆነ ለሑስለኒን ማስረዳት እንዳለብኝ ተረዳሁ፡፡ ሑስሊንን ወደ ቢሮዬ በማስጠራትም እነዚህን ሁኔታዎች በዝርዝር ለሑስሊን አስረዳኃት፡፡ ሑስሊንም በሁኔታው ምንም ዓይነት አግራሞትም ሆነ ትዝብትን ሳታሳየኝ ንግግሬን እንደጨረስኩ ያደረገችው ነገር ቢኖር ስልክ አንስታ ለመደወል ቁጥሮችን መነካካት ነበር፡፡ ለማን እንደምትደውል ግን እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡

☼☼☼

ቀኑ ግንቦት 30 ይመስለኛል፡፡ ቢል በድርጅታችን ውስጥ የኒዎርክሲቲ ምክትል ሹም ነው፡፡ እናም መጥቶ ፊቴ ላይ በመቆም እና እኔን እኔን እያየ «እናንተ በካስፒያን የነዳጅ ዘይት ቢዝነስ ውስጥ አንድ ነጋዴ እንዲንቀሣቀስ የምትፈልጉትናችሁ» በማለት በጥያቄ መልክ ይሁን በእርግጠኝነት ግልፅ ባልሆነ መንገድ ተናገረ፡፡ ለጥቆም «ኒውዮርክ ውስጥ ከዚህ ሰውዬ ጋር ለመስራት ጊዜ ያለው ሰው አይመስለኝም፡፡ ለእኛ ካስፒያንም ውስብስብ ይመስለኛል» አለ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

«ለመሆኑ ግን ሰውዬው ማን ነው?» አልኩት ቢልን

«ሮገር ታምራዝ» አለኝ፡፡

ሁኔታውም አስደነቀኝ ምክንያቱም በፋይሉ ውስጥ ታምራዝ ከኒውዮርክ ጋር እንደሚገናኝ የሚገልፅ ምንም አይነት ነገር የለምና፡፡

እዚህ ላይ ግን ግልፅ መናገር እንዳለብኝ ሳይሰማኝ አልቀረም ምክንያቱም በእኔ ቦታ ያለ የዳይሬክቶሬት ኦፍ ኦፕሬሽን ኦፊሠር እንዲህ ዓይነት ስራ ሊሠራ የሚችለው በሌላ መንገድ ነው፡፡ በዙሪያችን ቀይ ባንዲራ እየተወለበለበ ያለ ይመስለኛል፡፡ በሊባኖስ ስለሚፈለገው ሰው፤ የካስፒያን የነዳጅ ዘይት ድርድርና የብሄራዊ ደህንነቱ ጉዳይ በነበሩበት እንዳሉ ናቸው፡፡ ከኔ ጉዳይ ጋር የሚያያዘው የቶኔ ሌክና የእኔን ፍጥጫ ሳይጨምር መሆኑ ነው፡፡ ለማንናቸውም ዳይሬክቶሬት ኦፍ ኦፕሬሽንን (DO) የታምራዝ ጉዳይ የሚያሳስበው አልነበረም፡፡ የብሄራዊው ደህንነት ሰዎች ታምራዝን የመጥላታቸው ነገር ግን ሰውዬውን እንዳገኘው ሳይገፋፋኝ አልቀረም፡፡ የCIA ምስጢራዊ የስልክ ቁጥሬን ወረቀት ላይ ከፃፍኩኝ በኃላ «እንዲደውልልኝ ንገረው» ብዬ ለቢል ሰጠሁት፡፡

☆☆☆

ታምራዝ የሆቴሉን በር ከፍቶ እንደገባ ገፅታውን ከፋይሉ ፎቶግራፍ ጋር ከመቅፅበት አነፃፀርኩት፡፡ ከለበሳቸው ልብሶቹ በስተቀር የተለወጠ ነገር የለም ራሱ ነው፡፡ ቀንዳም መነፅር፣ በነጭ ሸሚዝ ላይ ከራቫትና ቀለል ያለ ጃኬት አይሉት ኮት ነገር ደርቧል፡፡ አሽዋማ ፀጉሩ ለየት የሚያረገው አንዱ ምልክቱ ነው፡፡ እብሮት ያለው ግለሰብ ኬድ ፒቾስ ቀደም ሲል CIA ውስጥ የሰራ ሲሆን ከድርጅቱ ከለቀቀ በኃላም ከታምራዝ ጋር እንደሚሰራ ደርሰንበታል እናም እንደ አዲስ ከተዋወቅን በኃላ ታምራዝ ፒቾስን የሆነ ነገር ሹክ ሲለው ፒቾስም የታምራዝን አታሼ ቦርሳ ይዞ እኛን ለብቻችን ትቶን ወጣ፡፡ ታምራዝና እኔ ከሠላምታው ምዕራፍ በኃላ ከጉዳያችን ጋር የማይገናኝ የባጥ የቆጡን ስናወራ ቆየን፡፡ አስተናጋጁም ቡናችንን ይዞልን ከመጣ በኃላ ግን ወደ ዋናው ጉዳያችን ገባን፡፡

«ከሼላ ሔስሊን ጋር የነበረህ ውይይት እንዴት ተጠናቀቀ?» አልኩት፡፡

«እጅግ ቆንጆ ነበር ወደ አርሜኒያ የሚዘረጋውን የነዳጅ መስመር ሃሳብ ወደዋለች» አለኝ፡፡ (በኃላ ቆይቶ እንደሰማሁት ግን ሔስሊን ታምራዝን ከቢሮዋ ገፈታትራ እንዳስወጣችዉ ነበር)፡፡

ታምራዝ የካውካስና ቱርክን አካባቢ የሚያሳይ ካርታ አውጥቶ እንድመለከተው ጠረጴዛ ላይ ዘረጋጋው፡፡

«ካስፒያንንና ሜዲትራንያንን በነዳጅ ዘይት መስመር ማገናኘት እፈልጋለሁ» አለኝ፡፡ በሌባ ጣቱ አዘርባጃን፣ ናሳርኖ ካራባክ፣ አርሜኒያንና ቱርክ የሚገኙበትን አቅጣጫ በመስመር እያመላከተ ለቀጣዮቹ ሰላሳ ደቂቃዎች ውይይታችን ያተኮረው ታምራዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሰላም ቀጠና» ብሎ በሚጠራው የነዳጅ ዘይት ቱቦ ማለፊያ መስመር ላይ ነበር፡፡ ታምራዝ አርሜኒያንና አዘርባጃንን በነዳጅ ቱቦ ማገናኘት ሰላምን በመፍጠር ሂደት አይነተኛ ሚና እንዳለው እንዳምንለት ይፈልጋል፡፡ የፖለቲካ ሽኩቻዎች በተፈጠሩ ቁጥር መጀመሪያ የሚፈነዳው የነዳጅ መተላለፊያ ቱቦ ስለመሆኑ ግን ትኩረት ያለው አይመስልም ነበር፡፡

«ይህ ነገር እጅግ በርካታ ገንዘብ የሚያስወጣ ይመስለኛል» አልኩት ታምራዝን ውይይታችን መቋጫ እንዲኖረው በማሰብና ወደ ሌላ አጭር ጉዳይ ልወስደው በመፈለግ፡፡ አስከተልኩናም «ለመሆኑ ለሚዘረጋው መስመር ወጭውን የሚሸፍነው ማነው?» አልኩት፡፡

«ቻይናዎች ናቸው!» አለና አንድ ፎቶግራፍ አወጣ ፎቶግራፉም የታምራዝ ነዳጅ ዘይት ካምፓኒ ፕሬዚዳንት የሆነው ማት ስቴከል የነዳጅ መስመር ስራውን ለማከናወን ከቻይናዎች ጋር ስምምነት ሲፈራረም የሚያሳይ ነው፡፡ መግለጫ ፅሁፉም በቻይንኛ ስለተፃፉ ምን እንደሚል ስለማላውቅ ታምራዝ ያለውን መቀበል ግዴታዬ ነበር፡፡

«ሮገር፤ በዕውነቱ ይሄ ሃሳብህ ጥሩ ነው፡፡ ለመሆኑ ግን እኔ ልረዳህ የምችለው በምን መልኩ ነው?» አልኩት፡፡

ሮገር ትንሽ አሠብ ካደረገ በኃላ «ፕሬዚዳንቱ ፕሮፖዛሌን እንዲያዩልኝ እፈልጋለሁ» አለ፡፡

እንደገባኝ ከሆነ ታምራዝ ቀጣሪ ድረጅቱ ማለትም CIA በኃይት ሃውስ ቤተመንግስት ያሉ ምስጢራዊ ቢሮችን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው የሚመስለው፡፡ ቢል ክሊንተን ስልጣን በያዙበት ወቅት ከCIA የመረጃ ምንጮቻቸው ጋር የነበራቸውን የግንኙነት መሰመር በራሳቸው መንገድ ጠፍጥፈው እንደሰሩት የአንድ ወቅት የሚዲያ ማድመቂያ የነበረውን ወሬም ታምራዝ የዘነጋ ይመስለኛል፡፡

«ታምራዝ በኃይት ሃውስ መንግስት ውስጥ በፊት የነበረንን ዓይነት ነፃነት ዛሬ የለንም፡፡ እውነት እልሃለው ሌላው ቀርቶ ከብሄራዊ ደህንነት ካውንስሉ (NSC) ጋር ስብሰባ ማድረግ እንኳን አንችልም» አልኩት፡፡

«ታዲያ ምን ይሻለኛል» አለኝ ታምራዝ

«እንዳንተ ያሉ ሠዎች ይህን ስራ የሚሠራላቸው አንድ ጥሩ ቅጥረኛ የሚያስፈልጋቸው ይመስለኛ» አልኩት፡፡

ታምራዝም አተኩሮ እየተመለከተኝ ዝም አለ፡፡ ምናልባትም የሠው ስም እንደጠራለት ፈልጎም ይሆናል፡፡ እኔም ታዲያ ይህ ሁኔታ ወዲያውኑ ተገለጠልኝና የክሊንተን የቀድሞ አማካሪ የነበረው ሎይድ ክአለር ትዝ አለኝ፡፡ ሎይድ በዋሽንግተን ፓስት የሚሰራ ሲሆን የክሊንተን ጥሩ አማካሪ እንደነበረም ሰምቻለሁ፡፡ ለሮገር ታምራዝ የሚስማማ ሰው መሆኑም ገብቶኛል፡፡ እናም ለታምራዝ ሹክ ስለው በአድናቆትና በፍቅር



t.me/OLDBOOKSPDF

ስሜት እየተመለከተኝ «ግንኙነታችን ተጠናከሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡» አለኝና ለቀጣይ ስብሰባ ቶሎ መድረስ እንዳለበት ባለስልጣን ተሰናብቶኝ በችኮላ እፌስ-እፌስ ብሎ ወጣ፡፡

☼☼☼

ቆይቼ እንደተረዳሁት ከሆነ ታምራዝ ከክሊንተን አስተዳደር ጋር የሚገናኝበት መንገድ መፍጠር መቻሉን ሲሆን ለዚህም ይረዳው ዘንድ አረኔልና ሃስቲ ከተሰኙ ግዙፍ ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት እንደጀመረና የካምፓኒው ፈላጭ ቆራጭ የንግድ ሚኒስትሩ ሮን ብራውን ስለነበረም ታምራዝ በእርሱ በኩል የዋሽንግተንን አየር መሳብ ይቻለው ነበር፡፡

በዚህም የተነሣ ታምራዝ በሮን ብራውን አውሮፕላን ከአሜሪካ ወደ ራሺያ የሚደረግን የንግድ ልምድ ልውውጥን እንዲፈፅምለት ፈለገ፡፡ ይሁንና ሮን ብራውን ሊስማማበት ባለመቻሉ የተነሳ የታምራዝ ካምፓኒ ለአውሮፕላኑ ትኬት የተከፈለውን ጨምሮ ከሌሎች ወጭዎች ጋር 130 ሺህ ዶላር ኪሳራን ተከናነበ፡፡

ሮገር ታምራዝ ወደሌላ አቅጣጫ በመዞርም ለአሜሪካን መንግስት አዲስ ራስምታታ ሆነ ምክንያቱ ደግሞ ቱርክንና አርሜኒያን እየጎበኘ በነበረበት ወቅት የሁለቱ ሃገራት የአሜሪካ አምባሳደሮች እንዲጣሉና እንዲናቆሩ ምንም አይነት ግንኙነት እንዳይኖራቸውም እስከማድረግ ደርሶ ነበር፡፡

☼☼☼

ስለ ሮገር ታምራዝና ፔትሮሊየም ኢንዳስትሪው እሉ የተባሉትን ፕሮጠቢዎቹን ስጠይቅ የአብዛኛዎቹ ስሜት እንዴት CIA ስለ ራሱ ነገር ይጠይቀናል?' የሚል ዓይነት ነበር፡፡ እናም እኔም በሂደት እንደተረዳሁት ከሆነ ደግሞ ሼላ ሔስሊን ሮገር ታምራዝ ከእኛ ጋር ግንኙነት እንዳለውና ምናልባትም የሚያውቀውን ሁሉንም ነገር የሚነግራትም ራሱ ታምራዝ ሊሆን እንደሚችል ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ታዲያ ከነዳጅ ዘይት ዝውውር ጋር በተያያዘ ከታምራዝ የተሻለ ዕውቀት አለው ወደ ሚባል አንድ ግለሰብ ዘንድ ሄድኩ፡፡ ሰውየውንም መጀመሪያ እንዳገኘሁት አቀባበሉ ግራ አጋብቶኝ ነበር፡፡

«ይሂውልህ ወንድም እኔ ሚሬያ አይደለሁም፡፡ ሚሬያዎችን ከፈለክ ሂደህ በቀጥታ እነሡን አናግራቸው» ነበር ያለኝ፡፡ እኔም ሁዱን ለማረጋጋት ሞከርኩ፡፡

ከቆይታ በኃላም «ለመሆኑ ታምራዝ ይሄንን የነዳጅ ዘይት መስመር መዘርጋት ቢዝነስ እንዴት እንደጀመረ ታውቃለህ?» አለኝ በፍፁም እንደማላውቅ ስነግረው ሊነግረኝ ጉሮሮውን ጠራረገ፡፡ ከመናገሩ በፊት ግን በእርማኛክ ጅን ጠርሙሱን መሙላትና ሲጋራውንም መለኮስ ነበረበት፡፡ እናም ቀጠለ፡፡

«ሮገር ታምራዝ የሚኖረው ቤሩት ነበር፡፡ እዚያም በአንድ የሃገር ውስጥ ባንክ ውስጥ ይሠራ ነበር እናም አንድ ጊዜ ከዚህ ስራው ጋር በተያያዘ ዶክመንት ሲያገላብጥ ስለቀድሞው የሳዑዲአረቢያ ኢንተሊጀንስ ከማል አደም አንድ መረጃ አገኘ፡፡ ታምራዝ በጊዜው አደምን መተዋወቅ ብቻ ነበር የፈለገው እናም እንደምንም ብሎ ከተዋወቀው



t.me/OLDBOOKSPDF

በኃላም ግንኙነታቸው ባጥሩ ጓደኝነት መንፈስ ቀጠለ፡፡ ከጥቂት ጊዜያት በኃላ ግን አደም ለታምራዝ ግብፅ ውስጥ አንድ ስምምነት አለ ብሎ ደወለለት፡፡ እንደውም የዚህ አካል ቢሆን ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያገኝ ነገረው፡፡ ስምምነቱም ከቀይ ባህር እስከሜዲትራኒያን የሚዘልቅ የነዳጅ ቱቦ የመዘርጋት ስራ ሲሆን ከታምራዝ የሚጠበቀው ደግሞ በስምምነቱ ፊርማውን እንዲያኖርና ችግር ቢፈጠር አደምን ነፃ እንዲወጣ ማድረግ ነበር፡፡ ታምራዝም በውሉ በመስማማቱ መስመሩም ተዘረጋ፡፡ በዚህም ታምራዝ ከጠበቀው በላይ ገንዘብና ዝና አገኘ፡፡ ከዚህ በመቀጠልም ታምራዝ ሌላ ስምምነት በግብፅ ሲያፈላልግ በለስቀንቶት ተመሳሳይ ስምምነት ከወደ ጣሊያን መጣለት፡፡»

ሰውየው የእለቀውን ሲጋራ በመተርኮሻ ተርኩሶ ጅኑን በብርጭቆው ከቀዳ በኃላ ፊቱን ወደ እኔ በማዞር «ጣሊያን ውስጥ ስለነበረው የአሞኮ ችግር የምታስታውሰው ነገር አለህ?» አለኝ፡፡ እኔም አለማወቄን ከገለፅኩለት በኃላ እንዲነግረኝ መወትወቴን ቀጠልኩ፡፡

«. . . ከሠራተኛ እጥረት ጋር በተያያዘ የአሞኮ ነዳጅ ማጣሪያ ሊዘጋ ተቃርቦ ነበር፡፡ እናም ይህ ችግር ሌላ ጣጣ ከመፍጠሩ በፊት ግን ታምራዝ ደረሠ፡፡ ታምራዝ ከሊቢያው ፕሬዘዳንት ሙሀመር ጋዳፊ ጋር ግንኙነት ስለነበረው ፕሬዚዳንቱ የኩባንያውን ድርሻ ጠቅለው እንዲገዙት ከሲሲሊ የመረጣቸውን ደላሎች በመጠቀም አግባባቸው፡፡ ስምምነቱም ተከናወነ፡፡ ታምራዝም የአምስት ፐርሠንት ኮሚሽንና ጠቀም ያለ ጉርሻ አገኘ፡፡ የሆነው ሆኖ አሮጌው የአሞኮ የነዳጅ ማጣሪያ የተፈለገውን ያህል አትራፊ ሊሆን ባለመቻሉና በዚህ የተነሣ ሊቢያውያኑ ስማቸው ከአሞኮ ጋር እንዳይነሳ ስለፈለጉ ለመዝጋት ተገደዱ በዚህ ጊዜ ታምራዝ የራሱን የነዳጅ ካምፓኒ እንዲጠቀሙ ማድረግ ነበረበትና በዚህ የተነሣ የታምራዝ ንብረት የሆነው 'ታምኦይልነ ኩባንያ እጅግ ተጠናከረ እናም ዛሬ ታምኦይል የማይገኝበት የአውሮፓ ሃገር የለም፡፡»

እኔም ከግለሰቡ ጋር ከተለያየን በኃላ ደግሞ ስለታምራዝ ሊያውቅ ይችላል ብዬ ያሰብኩትን ሌላ ግለሰብ አስጠራሁ፡፡

«. . . የቱርኳ ጠቅላይ ሚኒስቴር ታንሱ ሲለር ባለቤት የሆኑት አዜር ሲለርና ታምራዝ የንግድ አጋሮች መሆናቸውን ታውቃለህ አለኝ፡፡

ምንም እንኳን ታምራዝ ቱርክ በነበረበት ወቅት ወደአርሜኒያ የሚዘረጋውን የነዳጅ መስመር ለማስተዋወቅ በሄደበት ወቅት ከጠቅላይ ሚኒስትሯ ባለቤት ጋር የጠበቀ ግንኙነት መመስረቱን ባውቅም ለሰውየው ግን እንደማላውቅ ነገርኩት፡፡ እንካራ የሚገኘው ኢምባሲያችን የሁለቱን ሰዎች የንግድ አጋርነት እንዲመሠረት ያደረገው «እረንጓዴ ተኩላዎች» የተሠኘው የቱርክ ናሽናሊስት ቡድን እንደሆነም ደረሰበት ስለነበር መረጃው አለኝ፡፡ የማዳም ሲለር ባለቤት የሆኑት አዜር ከታምራዝ ጋር ብቻ ሳይሆን እ.ኤ.አ. በ1996 ዓ.ም አሜሪካ በሊለበት የእስራት ፍርድ ወስናበት ከነበረው አደገኛ ዕፅ አዘዋዋሪው እማራ ሉፍቲ ቶፓል ጋርም ጥብቅ የቢዝነስ ጓደኝነት እንደነበራቸው እናውቅ ነበር አለኝ፡፡

«ለመሆኑ ሮገርና አዜር ምን አይነት ቢዝነስ ነበር የሚሠሩት?» በማለት ሰውየውን ጠየኩት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«ነዳጅ ዘይት፡፡ ታምራዝ ለሚገጥመው የትኛውም አይነት እንቅፋት አዜር ተከላካይ ነበሩ፡፡ ለዚህም ጠቀም ያለ ገንዘብ ይከፍላቸዋል» አለኝ፡፡ ወዲያውኑ ከታምራዝ ፋይል ጋር የተያያዘውን ታሪክ ገልበጥ ገልበጥ አድርጌ ስመለከት ግለሰቡ ካለኝ ነገር ጋር የሚገጣጠም እውነታ አገኘሁ፡፡ ለዚህም በናርኮቲክ ድራግ አዘዋዋሪው ኦማር ሉፍቲ ቶፓል ስም የተመዘገበው «ኢምፔሪያል» የተሰኘው በቱር ከሜኒስታን ውስጥ ዋንኛው የካሲኖስ ማከማቻና በቱርክ የሚገኘው 'ነቦታስነ የተባለው የነዳጅ ዘይት ካምፓኒ ጥሩ ምስክር ነበሩ፡፡

ከአንድ ሳምንት በኃላ ግለሰቡ ደወለልኝና ሌላ አንድ ትልቅ መረጃ ነገረኝ፡፡ ሰውዬውም ያገኘሁት መረጃ ቱርክሜኒስተን ከሚገኙ ጓደኞቼ በመሆኑ እርግጠኛ መሆን አልችልም፡፡ ቢሆንም ግን እነግርሃለሁ፡፡» በማለት ጀመረ፡፡

«አዜርና ታምራዝ የብሎክ I ምስጢራዊ አጋሮች ወይንም ባለቤቶች ናቸው አለኝ፡፡ ይህ ነገር እውነት ከሆነ በርግጥም የሚደንቅ ነው፡፡ ብሎክ I ማለት ደግሞ ቱርክሜኒስታን ውስጥ የሚገኝ የሮገር እጅግ ግዙፍ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ድረጅት ነው፡፡ ኩባንያው 358 ሚሊዮን በርሜል ዘይትና 3.7 ትሪሊዬን ኪዮቢክፊት የጋዝ ክምችት እንዳለው የሚነገርለት ነው፡፡ የCIA አናሊስቶች በጣም ከሚያስደንቃቸው ነገር አንዱ የሆነው ታምራዝ ይህንን የሚያክል ግዙፍ ኩባንያ ለመግዛት ገንዘብ ከየት እንዳገኘ ነው፡፡

«አዜር ለምንድን ነው የቱርክሜኒስታን የነዳጅ ቢዝነስ ውስጥ እጁን ሊያስገባ የቻለው? ይህ ነገር በትክክል ሊዋጥልኝ አልቻለም፡፡» አልኩት

«የነዳጅ ዘይት ቢዝነስ ካልገባህ ልክ ነህ፡፡ ነገር ግን ብሎክ I የተመሠረተበት ገንዘብ የአዜር አይደለም፡፡ ላፒስ የተሠኘው ሌላ ኩባንያ ነው ገንዘቡን በሙሉ የሸፈነው፡፡ ላፒስ ለብሎክ I መስራች ከሠጠው ገንዘብ በተጨማሪ በቱርክሜኒስተን ፕሬዚዳንት ሳፓርሙራት ኒያዞቭ ኪስ የሚገባ የ30 ሚሊዮን ዶላር ስምምነት ፈርሟል በማለት ነገረኝ፡፡

ጉጉቴም እየጨመረ መጣ አይኔም ተበለጠጠ፡፡ «ለመሆኑ ላፒስ ይሄንን የሚሠራው ለምንድን ነው?» ስል ጥያቄዬን አስከተልኩ፡፡

«ገንዘቡ የላፒስ አይደለም፡፡ ገንዘቡን 'TYT' የተሠኘው የቱርክ የቱሪዝምና ኢንቨስትመንት ባንክ ነው ለላፒስ ሆልዲንግስ ያበደረው፡፡ በዚህ ሁኔታ አዜርና ላፒስ ባንኩ ባዶውን እንዲቀር ካደረጉት በኃላ በኪሣራ ምክንያት ይነሣ ወደቀ፡፡ የብድር ስምምነቱም በላፒስና በአዜር እጅ ስለነበር የ 'TYT' ባንክ ከስነዱ ተሰረዘ ስለዚህ ጥያቄህን ለመመለስ ያህል ገንዘቡ የታምራዝም፣ የላፒስም ሆነ የአዜር ሳይሆን የቱርክ የቱሪዝምና ኢንቨስትመነት ባንክ ነው» አለኝ፡፡

«እርግጠኛ ነህ?» አልኩት

«መጀመሪያም እንደነገርኩህ የሰማሁትን ነው እየነገርኩህ ያለሁት፤ ስለዚህ እረግጠኛ ልሆን አልችልም» አለኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«ስለዚህ ማን ማንን በገንዘብ ደገፌ ብለህ ታስባለህ?» በማለት ቀጠልኩ፡፡

«ሰላሣ ሚሊዮን ዶላሩን ለፕሬዚዳንት ኒያዞቭ የሠጠው ታምራዝ ይመስለኛል፡፡ አይመስልህም?» በማለት ገለፀልኝ፡፡

እናም ይህ በጣም ጥሩ መረጃ እንደሆነ ተገንዘብኩኝ፡፡ ብቻዬንም ከማብሠለስለው ሌላ ሰው መስማት እንዳለበት ተሰማኝ፡፡ እናም ለሼላ ሔስሊን ደወልኩላት፡፡ ስልኩን እንስታም እኔ የምናገረውን ብቻ አዳመጠችኝ ይሁንና ምንም አስተያየት አልሰጠችም፡፡ በኃላ ላይ ግን በአዕምሮዬ የመጣልኝ ነገር ቢኖር ሮገር ታምራዝ ለኦዜር ሲለር ጉቦ ሰጥቷል . . . መስከረም 28 . . . ትዕዛዝ ቦብ ቢ.ር፡፡ የሚለው ሔስሊን በማስታወሻዋ ወይንም በጭንቅላቷ የምታሰፍረው ሃረግ ነው፡፡ ይህ ነገር በርግጥም እውነት ከሆነ እኔም የጉዳዩ አንድ ተዋናይ እንደምሆን ግልፅ ነበር፡፡ ታምራዝ በርግጥም ለሌሎች ሐገራት ባለስልጣናት ጉቦ የሚሰጥ ከሆነ የአሜሪካንን ህግ እንደመጣስ ይቆጠራል፡፡ ታምራዝ ያለ አሜሪካ መንግስት እርዳታ ከካስፒያን የነዳጅ ዘይት ቢዝነስ ጋር አንድ እርምጃ እንደማይሄድ ግልፅ ነበር፡፡

ሔስሊን ሮገር ታምራዝ እጄን የሰደደበትን ምስጢራት ሁሉ አንድ በአንድ ሳትረዳ የምትመለስ አልሆነም፡፡ ሁኔታው ደግሞ ለታምራዝ ብቻ ሳይሆን ለእኔም የሚበጅ አይሆንም፣ ምናልባትም ጉዳዩ የእኔን አንገት ለታምራዝ አንገት በተዘጋጀው ገመድ ውስጥ ሊያስገባኝ የሚችልበት አጋጣሚም ነበረውና፡፡

☼☼☼

ከነታምራዝ ጋር የተገናኘ ሌላ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ተገኘ፡፡ ይኼውም ሮገር ታምራዝ ከኦዜር ሲለርና ኦማር ቀፖል ጋር በመሆን በአዘርባጃን መፈንቅለ መንግስት ተሳትፏል የሚል ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ መረጃውን ሙሉ በሙሉ ላምነው ግን አልቻልኩም፡፡

☼☼☼

ሮገር ታምራዝን የተመለከቱ ጉዳዮችን እያውጠነጠንኩ በነበረበት ጊዜ ከራሱ ከታምራዝ የፋክስ መልዕክት ደረሠኝ፡፡ መልዕክቱም የሚልከው ማንሃታን ከሚገኘው ኩባንያው ሆኖ ሲሆን አቪስ የተሠኘችው ከተማም ለነዳጅ መስመር ዝርጋታው እርዳታ እንደምታደርግለትና ኒዎርከሲቲ የሚገኝ አንድ ጓደኛው ካምፓኒውን በመቆጣጠር እንደሚሠራ ይገልፃል፡፡ በእርግጥ ታምራዝ በመልዕክቱ ያስቀመጠው አድራሻ ትክክል ቢሆንም ስለ አቪስ ከተማ ግን እኔም ሆንኩ ሌሎች የጠየኳቸው ሠዎች እንግዳ ሆንን፡፡ የታምራዝ ፋክስ በውሸትና በእውነት የታጀለ መልዕክት መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ ይህ ደግሞ እንደታምራዝ ያለ አንድ ነጋዴ ከኃይት ሃውስ መንግስት ጋር የሚያደርገው ድብብቆሽ አንድ ገፅታ ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ያጋጠመኝ ተመሣሣይ ሁኔታዎች አስተምረውኛል፡፡

☼☼☼



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ በእንዲህ እንዳለ CIA የስራ ድርቀት የተመለከተባቸውን ክፍተቶቹን በጥልቀት መመርመሩን ቀጥሏል፡፡

የካቲት 21/1994 FBI ራክ አሜሰንን በቁጥጥር ስር ሲያደርገው እኔ ደግሞ ዱሻንቤ ውስጥ ነበርኩ፡፡ በCNN ከአዲሱ XJ-6 ጃጓር ጋር በመሆን አሜሰንን ስመለከተው በአዕምሮዬ የመጣው ነገር ቢኖር በCIA ውስጥ ይሠራ የነበረ አንድም ሰው አውሮፕላን የሌለው መሆኑን ነበር፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ተማትሮ የነበራቸውና CIA'ን (እ.ኤ.አ. 1947 ዓ.ም) የመሠረቱት የታላላቅ ባለስልጣናት የግል አውሮፕላኖች በሙሉ አሁን ግን የሉም፡፡ የአሜስን ጃጓር ከየት ሊመጣ እንደቻለ ግን ሊገባኝ አልቻለም፡፡

የአሜስን በቁጥጥር ስር መዋል እንደተመለከትኩ ታዲያ በመጀመሪያ በአዕምሮዬ የመጣው ነገር ቢኖር የእንግሊዙ የስለላ ድርጅት MI-6 ባልደረባ የነበረው ፊልቢ ነበር ምንአልባትም ሁለቱም በሚሰሩበት ድርጅት ተከሰው ለፍርድ የቀረቡ መሆናቸው ያመሳስላቸው ይሆናል፡፡ ልዩነቱ ግን ፊልቢ ከMI-6 ጋር ሆድና ጀርባ የሆነው በሃሳብ ባለመግባባቱ ስበብ በፈጠረው ችግር ሲሆን አሜስ ደግሞ CIA'ን በገንዘብ አሳልፎ በመሸጡ የተነሳ ነው፡፡ ለማንኛውም በCIA ውስጥ እንዲህ አይነት ነገሮችን መመልከት በተለይ እንደኔ ላለ ነባር አባል አዲስ አይሆንም፡፡ እንደ CIA ባለ ግዙፍና ውስብስብ የፖለቲካ አየር ውስጥ ፈልገውም ሆነ ሳይፈልጉ መንሳፈፍን መቀበልም ገና ከጅምሩ ቃል የሚገቡለት ነገር ነው፡፡

CIA ሮድ ስሚዝን የካወንተር ኢንተለጀንስ ሃላፊ አድርጎ ሲሾምና ኩራንም በእርሱ ስር እንዲሠራ ሲደረግ ኩራን የመጨረሻ ነፃነትን ተቀዳጀ፡፡ ጠበቃው ስሚዝ ሃላፊነቱን ከያዘ ጀምሮ በድርጅቱ ውስጥ የሚንፀባረቀውን የቢሮክራሲውን መሠላል ለመነቅነቅት ጊዜ አላስፈለገውም፤ የሆነው ሆኖ እንደ አዲስነቱ ነገሮች ቀለል ባለ አኳኃን ይሄዱለታል ተብሎ አይታውብም ነበርና ችግሮች በነበሩበት መቀጠላቸው ግድ ነበር፡፡ በተለይም ኩራን ከስሚዝ ቁጥጥር ውጭ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች ስለነበሩ ችግሮች መንፀባረቃቸው አልቀረም ነበር፡፡ ቀላል የተባሉ ችግሮች ስራ እየሠደዱ ባልታሠበ ሁኔታ በዚያ አካባቢ የምንገኝን ሠዎች በሙሉ ሊያነካካና እንደ ማዕበል ወጀብ ሊጠራርገን የሚችል ወንጀል መፈፀሙ በመስማቱ የFBI ቅጥረኞች ጠንከር ያሉ ምርመራዎችን ያደርጉ ጀመር፡፡ ሁኔታውንም ላስተዋለው እጅግ የሚያስፈራም ነበር፡፡ ዛሬ በቢሮህ እገር እማን ነው ብለህ በሰላም ስትሰራ ውለህ ነገ ወይ ተንገወዲያ ራስህን ዘብጥያ ልታገኘው ትችላለህ፡፡ በቃ! ነገር ሁሉ የሚሸከክ ነበር ሁኔታውም ሁሉ የባንቹ ጨዋታ እለ እይደለ ቀይዋን ያየ ነገር... ሁሉም የCIA ሰራተኛ የሚሰማውና የሚያወራው ስለ አዲሱ ወንጀልና ምርመራ ሆነ፡፡ ሌላው ቀርቶ ከደሙ ንፁህ የሆኑ ሁሉ ጠንከር ያለ ምርመራ ይደረግባቸው ገባ፡፡ የኋላ ኋላ ታዲያ በ1995 መጨረሻ ግድም ከ መቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በጉዳዩ ዙሪያ ተጠርጥረው ዘብጥያ ወረዱ፤ ከእነዚህም ውስጥም አብዛኞቹ የCIA ቅጥረኞች ነበሩ፡፡

የ FBI'ው ዳይሬክተር ሊዊስ ፍሪች ከፊቱ ላይ የሚነበበው የምፀት ፈገግታው ነገርን የሚያመነዥክ አስመስሎታል፡፡ የCIA 'ን እያንዳንዱን መረጃ መመርመሩን



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀጥሎበታል፡፡ ፍሪች ይህንን ሲያደርግ ታዲያ ከአሜሪካ ኮንግረስ ጠቀም ያለ ገንዘብ እየተሠጠው ስለመሆኑ ሌላው ጭምጭምታ ነበር፡፡ በውጭ ሀገራት የFBI ቅርንጫፎችን በመመስረት CIA 'ን የማጻከም ስራም ጎን ለጎን መስራቱ ቀድሞውኑ የታቀደለትም ይመስላል፡፡ በመሆኑም እጅግ በርካታ ቅጥረኞችን በማቀፍ FBI'ን በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ የማደራጀትና የማጠናከር እንቅስቃሴን ገፋበት፡፡ በኃላ ላይ ግን የእያንዳንዱ የጀርባ ማህደር ሲፈተሽ ሊዊስፍሪች ራሱ FBI ቀጥሮት ከነበሩት አዲስ ቅጥረኞች መካከል ቀደም ሲል ከCIA የተባረረ ግለሰብ ሆኖ ተገኘ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለም ታዲያ FBI በCIA ላይ የሚያደርገውን ምርመራ እያጠናከረ ባለበት ሁኔታ ሮበርት ሀንሰን የFBI ምስጢራዊ መረጃዎችን እሳልፎ መስጠቱ ተደረሰበት፡፡

☼☼☼

ከዕለታት አንድ ቀን የጠዋቱን የትራፊክ ዘገባ የተመለከተ ሪፓርት ቢሮዬ ሆኜ እያነበብኩ ሳለሁ ካውንተር ኢስፓኔጅ ከተባለው ክፍላችን አንድ የደህንነት ኦፊሰርና አንድ ቅልጥማም ወጣት አቢሮዬ ዘው አሉ፡፡ እኔም ገና ስመለከታቸው አመጣጣቸው የሰላም እንዳልሆነ ተርድቻለሁና የወጉን ሰላመታም ሳንለዋወጥም ኦፊሰሩ በነገር ይለበልበኝ ጀመረ፡፡

«ዱሻንቤ ከነበረችው ራሺያዊ ወዳጅህ ጋር አሁንም ወዳጅነትህን የመቀጠልህ ምስጢር ምንድን ነው?» አለኝ፡፡

ኦፊሰሩንም በአትኩሮት ለትንሽ ሴኮንዶች ስመለከተው ቆየሁና እርስ በእርሳችን በአይኖቻችን ተፈታተሽን፡፡ ከመቅፅበትም ከትውስታዬ ማህደር ዱሻንቤ የማውቃትና ከራሽያውያኑ የበረዶ ሸርተቴ ተጫዋቾች ጋር ያስተዋወቀችኝ ሴት ትዝ አለችኝ፡፡ እውነት ለመናገር ከሆነ ከዚህች ሴት ጋር ይህንን ያህል የጠነከረ ትውውቅ አልነበረንም፡፡ ከራሺያውያኑ ጋር ካስተዋወቀችኝ በኃላም ግንኙነታችን ተቋርጧል፡፡

ከኦፊሰሩ ጋር ያለው ቅልጥማም ወጣት «አስፈላጊውን ፓሊሳዊ ምርመራ ልናደርግብህ መጥተናል፤ አንተም ዝግጁ ሁን» አለኝ፡፡

የፋሺስትነት ቀልብ ያለው የሚመስለው ይህ ሰው አለባበሱም ቅጥ ያጣ ነበር ማለትም በረጅም ቅልጥሙ ልክ የሆነ የእረኛ ቡትስ የተጫመ ሲሆን የታጠቀውም ቀበቶ የተንዘላዘለ ነበር፡፡

በስድስት ወር ውስጥ ሁለት ጊዜ የህክምና እንዲሁም የእሻራ ምርመራዎችን ማድረግ ግድ ይለኝ ነበር፡፡ ይሀን ካላደረኩም ከCIA ጋር የሚኖረኝ ግንኙነት ያከትማል ማለት ስለሆነ ይሄንኑ ጊዜውን ጠብቄ ፈፅሜያለሁ፡፡

ቅልጥማሙ ወታደርና የደህንነት ኦፊሰሩ ስለዱሻንቤዋ ሴት ከጠየቁኝ ከሠዓታት በኃላ ወደ ኦፊሡሩ ቢሮ አምርቼ በግልምጫ በአይኔ ቂጥ አነሳሁት ምክንያቱም ከዚህ በፊት አውቀው ስለነበር እንዴት በሰላማዊ መንገድ አያናግረኝም በሚል ሙድ ነበር እናም እሱም ታሪኩን ነገረኝ፡- «ታሽኬንት ውስጥ የሚገኝ ባልደረባችን የካውንተር ኢስፓናጁን



t.me/OLDBOOKSPDF

ዲፓርትመንት ለፕሮግሽን ስራ ሊጠቀምበት መፈለጉን ገለፀልኝ፡፡ ስለዚህም ሲል እንተንና የራሺያዋን ሴት ያላችሁን ግንኙነት እንደ ቅመም ጨምሮ ወደ አሉባልታነት በማዞር ጉዳዩን ልክ እንደፔንዱለም ኳስ መወዝወዝ አስፈላጊ ነበር» አለኝ፡፡

ከዚህ በፊት በወንጀል ተጠርጥሬ በአሻራ ህክምና ምርመራ ያደረኩበት ጊዜ ይኖር ይሆን?' ብዬ ራሴንም ጠየኩት፡፡ መልሱንም ወዲያውኑ ነበር ያገኘሁት፡፡ በግድያ ወንጀል በFBI ተጠርጥሬ ጠንከር ያሉ ምርመራዎችን ካስተናገድኩኝ ብዙ ጊዜ አልሆነኝም ነበር፡፡

ኢድ ኩራን በCIA ውስጥ የፈጠረጠው ነውጥ CIA'ን ከውጭ ሲመለከቱት አስፈሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በCIA ምክንያትም የውጭ ሃገር ሰዎች መፍራት ብቻ ሳይሆን ከውጭ ሀገር ሰዎችን ጋር መስራት የCIA ቅርንጫፎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች በሙሉ ማለት የቻላል የማይታሰቡ ነበሩ፡፡

እናም የዚህን እውድ በተለይም በማዕከላዊ እስያና ካውከስ አካባቢ መመልከት የተለመደ ክስተት ሆኗል፡፡ በእነዚህ ቦታዎችና በዩሮኤሺያ የሚገኙት ስምንቱ የCIA ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች በጠቅላላ ከህዝብ ጋር የሚያገናኙ የስራ እንቅስቃሴዎች ቆመው ነበር፡፡ ማንም ማንንም ማግኘትም ሆነ ማየት አይፈልግም፡፡ የመረጃ ምንጮችና ፍንጮችም በከፊል ዝግ ሆነው ነበር፡፡ በደቡብ ዕዝ የተገኘ አንድ አዲስ የመረጃ ምንጭ እንደ ብርቅ መታየት ሲጀምር CIA የቆመለት ሁነኛው ስራው እየተዘነጋ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ማሰብ አይጠይቅም ነበር፡፡ በሁሉም የCIA ቅርንጫፎች መደበኛ ስራ የነበሩት የባጀትና ፕሮጀክት ዕቅዶች፣ የሰው ኃይል ለውጥና አዳዲስ ኦፊሰሮችን በመቅጠር ላይ ያተኮሩ ጉዳዮች ብቻ ነበሩ፡፡ በአረቡ ዓለም ግን አዳዲስ የፀር ሽብር እንቅስቃሴ ሃይሎች እየተፈጠሩ ከመሆኑ አንፃር እውነተኛውን የመረጃ ምንጭ ለማግኘት የጦርነት ያህል ይከብድ ነበር፡፡ በርግጥም አዳዲሶቹን የሽብር ህዋሶችን መቋቋም ቀላል አልነበረም፡፡ የዴቭ ኮሎን በCIA የዳይሬክቶሬት ኦፕሬሽን ኃላፊ ሆኖ መመረጥም ነገሮችን የሚያቀል ሆኖም አልተገኘም፡፡ ዴቭ ኮሄን ለስፍራው ብቁ ሰውም አይመስልም፤ ምክንያቱም ካሁን በፊት በኦፕሬሽን እንቅስቃሴዎች ላይ የነበረው ልምድ አነስተኛ በመሆኑ ነበር፡፡ ሃላፊ ሆኖ እንደተቀጠረመ የወሰደው የመጀመሪያ ዕርምጃው ነባሮቹን ቅጥረኞች ማባረርና በምትካቸውም አንድም የመረጃ ሰው ሊቀጥር አለመቻሉ የሰውየውን የብቃት ደረጃ ማነስ የሚያሳይ ነበር፡፡ ሲላው ቀርቶ ከህንድ ወታደራዊ ሃይል ጋር ከአረቡ ኦፊሰር ሳሚ ጋር ያስተዋወቀኝ ጠቃሚ ግለሠብና በቤሩት የሙግሀኒያህን መረብ አብጠርጥረው የሚያውቁት የእኔ የመረጃ ሰዎች እንኳ በኮሄን አይን ዋጋ ያላገኙ ነበሩ፡፡

በሪያድ፣ ቱላቪቭና ናይሮቢ አዳዲስና ምንም ዓይነት የኦፕሬሽን ልምድ የሌላቸው ግለሠቦች ኃላፊ ሆነው ተሾሙ፡፡ ምናልባት በሪያድ የተሠየመው ግለሠብ ቴኔት በነበረበት ወቅት በብሄራዊ ደህንነት መስሪያ ቤት ውስጥ ጥሩ ስራ ሠርቶ ያለፈ ስለነበር መልካም ምርጫ ነው ሊባል ይችል ይኖናል፡፡ ድሻንቢ የነበርኩት እኔ ደግሞ የኬዝ ኦፊሰርነት ልምድ በሌለው ሌላ ኦፊሰር ተተካ፡፡ በእኔ ስር የሪፓርት ኦፊሰር ሆና ትሠራ የነበረችው ረዳቴ ደግሞ የካስፒያን ሃላፊ ሆና ተሾመች፡፡ ሴትዮዋ ጥሩ ምላስ ያላት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቢሆንም ከዚህ በፊት አንድም አዲስ ቅጥረኛ ወደ CIA እንደሚመጣ እድርጋ የማታውቅ በመሆኑ ነገሩ ሁሉ ግራ እንደሚያጋባት መረዳት አያዳግትም ነበር፡፡

አዲሱ መዋቅር እጅግ አደገኛ አካሄድ እንዳለው ለማረጋገጥ በCIA ውስጥ እሠራ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሁኔታዎች ላይ የራሴን ምርመራ ማድረግ ጀመርኩ፡፡ በ1986 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ለዳይሬክቶሬት ኦፕሬሽን የሚደርሱትን ሁሉንም መረጃዎች በአንድ የኮምፒዮተር ሰርቨር ውስጥ እንዲገቡ በማድረጌ ከሁሉም የድርጅቱ ሀዋሶች የሚኖሩ መረጃዎችንና ምስጢራትን ማግኘት ይቻል ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ በኢራን የሚንቀሳቀሰውን የፓስዳራን ፓርቲ ሕዋሶችና ጠቃሚ ምስጢራት በዝርዝር የማግኘቱ ዕድል ነበር፡፡ ይሁንና በ1980 ዓ.ም አካባቢ እንዲህ አይነት መረጃዎችን ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡ በ1995 ዓ.ም ደግሞ በ1980 ዓ.ም ወደ ነበረው ሁኔታ ተመለሰ፡፡ ከፓስዳራንም ሆነ በአረቡ ሃገራት ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ የሽብር ህዋሶች የሚገኝ መረጃ አልነበረም በአጭሩ CIA መረጃ የሚያነፈንፍ ጆሮዎቹን በሙሉ በገዛ ፍቃዱ ዘግቶ የገዴለሽነት ስራ እየሰራ ይመስል ነበር፡፡

በኢራቅ የነበረው የCIA እንቅስቃሴ ደግሞ የባሰበት ነበር፡፡ በኢራቅ ከተመደቡት 35 የCIA ኦፊሰሮች ውስጥ ቢያንስ አስሩ የአልኮል ሱሰኞች ሲሆኑ ሌሎቹ አስሩ ደግሞ ደካማ የስራ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ነበሩ፡፡ ከአምስቱ ሁለት የሚሆኑት ደግሞ ጡረታ የወጡና በኮንትራት ስምምነት የሚሠሩ ነበሩ፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ CIA በኢራቅ ውስጥ ለሚያከናውነው ስራ ደንታ ቢሶች ነበሩ፡፡ የአሜሪካ ኮንግረስ በኢራቅ ለሚገኘው የCIA ሀይል በየጊዜው ሚሊዮን ዶላሮችን የሚመድብ ቢሆንም ይህንን ከቁብ ቆጥሮ ስራውን የሚሠራ አንድም ሰው አልነበረም፡፡

ለንደን ውስጥ የምትሰራ እንዲት አሜሪካዊት አማካሪ የCIA ዳይሬክተርና የአሜሪካ ፕሬዚደንት በአንድነት የማያገኙት ደሞዝ ይከፈላታል፡፡ ከለንደን ወደ አሜሪካ የምታደርገው የአውሮፕላን ጉዞም በፈለገችው መጠንና ደረጃ ይከፈልላታል፡፡ በለንደን የተከራየችው ቢሮም እጅግ ውድ የሚባለውን ሲሆን የCIA ሰዎች ቢሮዋን ለመጎብኘት ሲሄዱም በሌላ ድክም ባለ ቢሮ እንደምትሰራ በማስመሰል ታሳያቸዋለች፡፡ ሁኔታውም ተጨማሪ ገንዘብን ያስገኝላታል፡፡ ግለሰቧ ከCIA አማካሪነቷ በተጨማሪ ከሕግ ውጭ በለንደን በሚገኝ አንድ ድርጅትም ውስጥ ትሰራለች፡፡ ድርጊቱ ህገወጥ ቢሆንም ሴትዮዋን ለመቆጣጠር የሚያስችል ዕድል ከCIA ባለመኖሩ እሁን ድረስ ግለሠቧ ከአሜሪካ ኮንግረስና ከCIA ከፍተኛ ገንዘብ ታጋብስበታለች፡፡

እናም CIA ገንዘቡን ብቻ አልነበረም መቆጣጠር የተሳነው፡፡ በ1997 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የኢራቁ የቀድሞ ጓደኛዬ መሃመድ ቻላቢ ለንደን የሚገኘውን ስቱዲዮውን ለሳውዲ አረቢያው ስደተኛ ዶክተር ሰይድ አልፋኪ ሲያከራየው የብሪታንያ ባለስልጣናት ደንግጠው እንደነበረ አስታውሳለሁ ምክንያቱም ዶክተር አልፋኪ የኦሳማ ቢላደን ዋንኛ ወዳጅ የነበሩና በሳውዲ አረቢያ የአልሳውድን ዘውዳዊ ቤተሠብ ለመገርሰስ ከሚታገሉት ሳውዲዎች አንዱ በመሆናቸው እንዲሁም ብሪታንያና አሜሪካ በመካከለኛው ምስራቅ ፖለቲካ ያላቸውን ጣልቃ ገብነት ለማስቆም የሚታገሉ ግለሠብ በመሆናቸው ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቻላቢ ከዶክተሩ ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ለCIA ያለውን ጥላቻ መግለፁንም የሚያሳይ ነበር፡፡ በርግጥም ቻላቢ ምክንያታዊ ነበር፡፡ CIA በሚገባ ከተጠቀመበት በኃላ የእርሱ ፍላጎት ሲደርስ ከዶታል፡፡ በመሆኑም ቻላቢንን የCIA ወዳጅ ለማድረግ ያስቸግራል፡፡ እናም የCIA ንክኪ ከመካከለኛው ምስራቅ ብቻ አልነበረም፡፡ ወደ ማዕከላዊ ኤሽያ ተጉዞ ከቻይና ጋር የኒውክሌር ጦር መሣሪያዎችን በተመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ፖለቲካዊ ጨዋታ ነበረው፡፡ እ.ኤ.አ. በ1996 ዓ.ም CIA 'ሎፕ ኖር' በተባለው የቻይና የኒውክለር ጦር መሣሪያዎች መሞከሪያ ላይ ምስጢራዊ ምርመራ ማድረግ ጀምሮ ነበር፡፡ ነገር ግን የኒውክሌር መፈተሻ ጣቢያው የተሠራበት ሸለቋማና ገደላ ገደሉ ስፍራ ለCIA የመፈተሻ መሳሪያዎች የሚመች ካለመሆኑም በተጨማሪ ከማብላያው የሚወጡት ቅንጣቶች ከመፈተሻ መሳሪያዎቹ ቁጥጥር ውጭ ነበሩ፡፡

ከብሔራዊው ደህንነት ባለስልጣናት ጋር በተደረገው ምክክርም የኒውክሌር ፍላፃዎችንና ቅንጣቶችን የሚያነፈንፉ መሣሪያ በአሜሪካ ኢምባሲ አቅራቢያ ተተከለ፡፡ ሆኖም ኢምባሲው 'ሎፕ ኖር' ከሚገኝበት በመቶዎች ማይልስ የራቀ ስለነበር ውጤታማ ሳይሆን ቀርቶአል፡፡ እናም ታዲያ ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ የቻይና ባለስልጣን ቻይና ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የተፈራረመችውን ውል እንደማታፈርስ በኢሜል ላከልን፡፡ የሆነው ሆኖ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች ካልተገኙ በስተቀር የቻይናዊውን ባለስልጣን የኢሜል መልዕክት በማመን ብቻ እንቅስቃሴውን ማቆም አስቸጋሪ ነበር፡፡

የሆነው ሆኖ CIA የራሱን ሁነኛ ሰዎች መጠበቁን በማቆሙ ምክንያት ነገሮች ሁሉ መጥፎ አቅጣጫን ይዘው ሲሄዱ ተገደው ነበር፡፡ ለCIA ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ ግለሰቦች ዋጋ ሲያጡ መመልከትም የሚያስደነግጥ ነበር፡፡ በተለይም በ1996 የፀደይ ወቅት የዋሽንግተን ህይወቴ እጅ እጅ እያለኝ በመምጣቱ በቦሲኒያ ሰርገው የገቡትን የኢራን ሽብርተኞች እንቅስቃሴ በሚከታተለው ቡድን ውስጥ እንድካተትና ወደ ሳሪያቮ እንድጓዝ ጠየኩኝ እናም ከግማሽ ደርዘን በላይ ከሚሆኑ ረዳቶቼና ከባልና ሚስት የክትትል ቡድን አባላት ጋር በመሆን ወደ ስፍራው ተጓዝኩ፡፡

በጊዜው ሰርቪያ ውስጥ በተለይም የውጭ ዜጋ ሆኖ መኖር አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ሁሉም የውጭ ዜጎች ከተማዋ ውጭ ነበር የሚኖሩት፡፡

አንድ ዕለት ባልና ሚስቱ የክትትል ቡድናችን ተቆጣጣሪዎች ለስራ እንቅስቃሴ በከተማው ውስጥ መኪናቸውን ሲያሽከረክሩ የጦር መሣሪያ በታጠቁ የተደራጁ ሃይሎች መኪናቸው ድንገት ተከበበች፡፡ በመኪናው ውስጥ የሚገኙት ሰዎቹም ጦር ማሣሪያቸውን ደገኑባቸው፤ ይህንን ሁኔታም ቀድማ ያየችው ሴቷ ስትጮህ መሪውን ጨብጦ የነበረው ባሏ ከበባውን ሰንጥቆት አፈተለከ፡፡ ከኃላም ባወረዱባቸው የጥይት ዝናብ ሴቷ ጀርባዋ ላይ የመቁሰል አደጋ ሲያጋጥማት የሞት አደጋ ሳይደርስባቸው ቀረ፡፡ የቡድናችን አባላት ከእንዲህ ዓይነቱ አደጋ ለጊዜው ቢተርፍም የሁኔታውን ዳግም እንዲከሰት ምክንያት ከሚሆነው ብሮክራሲ ግን እንደማያመልጡ ግልፅ ነበር፡፡

ከአደጋው በኃላ በቦሲኒያ ከተሾመችው የCIA ኦፊሰር ጋር ውይይት አድርገናል፡፡ እናም ከግለሰቧ የተረዳሁት ነገር ቢኖር CIA'ን በተመለከተ በአካባቢው ስላለው ሁኔታ



t.me/OLDBOOKSPDF

የነበራት እውቀት እምብዛም መሆኑንና በጥቂቱም እንኳ የአካባቢውን ቋንቋ የማትችል መሆኗ ነበር፡፡ ለነገሩ «እሷ ብቻ ሳትሆን በሁሉም ህዋሶቻችን የሚገኙ ሃላፊዎች እንደዚሁ ናቸው» ብሎ መደምደም ሳይሻል ይቀር ይሆን??



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፰

## ጥቅምት 3/1995 ፤ ዋሽንግተን - ዲ.ሲ

... ከወራት በኃላ CIA ከሮገር ታምራዝ ጋር ለዓመታት የጠበቀ ቁርኝነት እንዲኖረው ያደረገበትን ምክንያት ግልፅ እየሆነልኝ መጣ፡፡ ሮገር በፈለገው ሰዓት ማንኛውንም ሰው ማግኘት የሚችል ግለሰብ ነበር፡፡ አንድ ቀን ጧት ላይ ታዲያ ቢሮዬ ገብቼ እንደተቀመጥኩ ስልኩ እንጫረረና አነሳሁት፡፡ ሮገር ታምራዝ ነበር፡፡ ከዚህ ቀን በፊት ማታ ከምክትል ፕሬዚደንት አልጎር ጋር ቨርጂኒያ ውስጥ በሚገኘው የቴድ ኬኔዲ ቤት ራት መብላታቸውን አውቅ ነበር፡፡

«ለምክትል ፕሬዚዳንቱ የነዳጅ መስመሩን የተወሰነ ድርሻ ሸጥኩላቸው፡፡ የካትሊርም ጉርሻ ተከፍሏል» አለኝ፡፡

ሮገር ያልነገረኝ ነገር ቢኖር ከሊዮድ ካትሊር በተጨማሪ የሴናተር ኬኔዲ ባለቤት ቪክቶሪያም ከጉርሻው የተቋደሱ መሆናቸውን ነበር፡፡ ሚስ ቪክቶሪያ ታምራዝ ሊባኖስ በነበረበት ወቅት ያጣውን ገንዘብ እንዲያገኝ የረዱት ሲሆን ከቅምሻው ቢቋደሱም አያስደንቅም ነበር፡፡ እንግዲህ ታምራዝና አልጎር በሴናተር ኬኔዲ ቤት ያደረጉት የራት ግብዣ የቅምሻው አካል መሆኑ ነው፡፡ ታምራዝ በራት ግብዣው ብቻ ሳይሆን በሌላም ነገር ደስ መሰኘቱ አልቀረም ለምሳሌ ከ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ጋር በመተዋወቁ፡፡ ታምራዝ እንደነገረኝ ከሆነም ክሊንተን የአዘርባጃን ፕሬዚዳንት የሆኑትን አሊዮቭን በርካታ የነዳጅ መስመሮች እንዲዘረጋ ጥሪ አቅርበውላቸዋል፡፡ ምናልባትም ፕሬዘዳንቱ የቱርኩ 'ባኩ ጌያን' መስመር እንዲዘረጋ ወይንም የአርሜኒያው መስመር እንዲስፋፋ ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ግራም ነፈሰ ቀኝ አሞኮና በካስፒያ የአሞኮ አጋር የሆነው ብሪቲሽ ፔትሮሊዩም የኃይት ሃውስ ባለስልጣናት የቱርኩ የነዳጅ ዘይት መስመር እንዲዘረጋ እንዲስማሙ ባለስለጣናቱን ለሚያሳምኑ ቅጥረኞቻቸው ከፍተኛ ገንዘብ እያፈሰሱ ነበር፡፡ ሊዩድ ካትለርን እንደመሰሉት ውስጥ አዋቂዎች ከሆነም የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ 'ባኩ ጌያ' የተሰኘው በቱርክ የሚገኝ መስመር ተግባራዊ መሆን እንደሚቻል ነው ግምታቸውን የሰነዘሩት፡፡ ይሁን እንጅ ታምራዝ ለ እንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ የሚተኛ አይሆንም ሁሉንም ነገር እሱ ከፍተኛ ጥቅምን በሚያገኝበት አቅጣጫ ይወስደዋል፡፡ ቆይቼ እንደተረዳሁት ከሆነ ፕሬዚዳንት ክሊንተንም ለአዘርባጃኑ ፕሬዚደንት የደወሉላቸው ሲሆን የውይይታቸውን ዋንኛ ነጥብ የምታውቀውም ሼላ ሔስሊን እንደሆነች ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያረጋገጥኩት ጉዳይ ሔስሊን ከክሊንተን ጋር በነበራት የስልክ ውይይት የታምራዝን ፍላጎቶች በሙሉ ያልጠበቀ ስምምነቶችን ማድረጓን ነበር፡፡ እናም ይህን ሁኔታ ለማረጋገጥም ወደ አዘርባጃን መሄድ የግድ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

✡✡✡

አዘርባጃን የደረስነው እመሻሹ ላይ ሲሆን በወቅቱ በበረዶ ተሸፍኖ የነበረው የባሕር ዳርቻ አካባቢ ሰፍራው ደስ የሚል ሕብረ ቀለማትን ያንፀባርቅ ነበር፡፡ ከአውሮፕላን ማረፊያው ከደረስን በኋላ በመኪና ሆነን ወደቤተ መንግስቱ አቅጣጫ ተጓዝን፡፡ ከቤተመንግስቱ የእንግዳ ማረፊያም ራት ከበላን በኋላ ወደ ሚጠብቀን ስብሰባ አመራን፡፡ እኩለ ሌሊት ሲሆንም ፕሬዚዳንት ሔይደር አሊዮቭ በመምጣታቸው ወደ መሰብሰቢያ አዳራሹ መሄድ ግድ ነበረብን፡፡ ሔይዳር አሊዮቭ ሶቪዮት ህብረት ከተፈረካከሰች በኋላ ስልጣናቸውን ይዘው መቆየት ከቻሉ ጥቂት የሶቪዮት መሪዎች አንዱ ናቸው፡፡ በቀድሞዋ ሶቪዮት የኮሚኒስት ፓርቲ ፖሊት ቢሮ አባልና የKGB ሊቀመንበር የነበሩ ትልቅ ሰው ሲሆኑ ሶቪዮት ህብረት ባትፈራርስ ኖሮም ሃገሪቱን የመምራት ዕድል ነበራቸው፡፡ ሶቪዮት መፈረካከስ በኋላ እጅግ ኃላ ቀር ነገር ግን በነዳጅ ዘይት ሃብቷ የውጭ ኢንቨስተሮችን የምታጓጓውን አዘርባጃንን በፕሬዚዳንትነት ይዘው መቀጠል ነበረባቸው፡፡ አሊዮቭ በሁሉም የፖለቲካ አቅጣጫ ተሞክሮአቸው የትዮለሌ ቁምነገሮችን የሚያውቁ ሲሆኑ የአዘርባጃን ተስፋ የሆነውን የነዳጅ ክምችት ለውጭ በተለይም ለአሜሪካ ኢንቨስተሮች ክፍት ማድረግ ሃገሪቱን የማሣደግ ትልቁ የቤት ስራ ብለው በማሰብ የመጀመሪያውን ስምምነት የተፈራረሙት በመስከረም 20/1994 ሲሆን ካምፓኒዎቹም አሞኮ፣ ፔንዞይል፣ ቱኖካል፣ ራምኮ፣ ስታቶይል፣ ዴልታና ብሪቲሽ ፔትሮሊዮም ሲሆኑ እነዚህም ካምፓኒዎች ከአዘርባጃኑ አለም አቀፍ የኦፕሬቲንግ ኮንሰርቲዮም (AIOC) ጋር በሚኖር የስራ ስምምነትና ተግባር የነዳጅ ቁፋሮ ስራቸውን ይከውናሉ፡፡ በዚህ መሰረትም ሁለቱ አካላት የ4.4 ቢሊዮን በርሜል ነዳጅ የማውጣት ስምምነት ሲያደርጉ ኩባንያዎቹም እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ 700 ሺህ በርሜል ነዳጅ ድፍድፍ እንደሚያወጡም ይጠበቃል፡፡ የመገናኛ ብዙሃንም ይህን ስምምነት «የክፍል ዘመኑ ትልቅ ስምምነት» በማለት ሊያሞካሹት በሳውድ አረቢያ የሚገኙትን ኩባንያዎችን ከገበያውጭ ያደርጋል ተብሎ የተፈራ ስምምነት ነበር፡፡ ለፕሬዚዳንት አሊዮቭ ይህ ስምምነት ከገንዘብም በላይ ነው፡፡ ምክንያቱም አሊዮቭ በሰሜን ከራሺያ ጋር በደቡብ ደግሞ ከኢራን ጋር መልካም ግንኙነት የሌላቸው ሲሆን ከአሜሪካ ብሪታንያ ጋር ያደረጉት ስምምነት ከታላላቆች ሃገራት የፖለቲካ ድጋፍ እንደሚያስገኝላቸውም ያስባሉ፡፡

እናም ስብሰባውን ከተሰበሰብን ከጥቂት ቆይታዎች በኋላ ፕሬዚዳንት አሊዮቭ ወሳለንበት ዘለቁ፡፡ ምንም እንኳ ፕሬዚዳንቱ ወደ 70ኛ ዓመታቸው እየተጠጉ ቢሆንም አሁንም ግን ቅልጥፍናና ንቁት የሚያንፀባርቅ ገፅታ አላቸው፡፡ ግርማ ሞገስ በተሞላበት አኳኋንም ወደተቀመጥንበት እየተጠጉ አንድ በአንድ የእጅ ሠላምታ ሠጡን፡፡ እናም አሊዮቭ ውይይታቸውን የጀመሩት በመጋቢት 1995 ዓ.ም በተደረገባቸው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ነበር፡፡ በሙከራውም CIA የሚጠረጥረው ሲለር ተሳትፎ ያደረጉ ሲሆን እንደ አሊዮቭ አባባል ከሆነ ደግሞ ከራሺያ እስከቱርክ ድረስ ያሉ ግለሰቦች በግልበጣው በቀጥታ ተሳትፈዋል ባይ ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ በአሜሪካ የሚኖሩ የአዘርባጃን ዜጎችን ሳይቀር በመጥራት በግልበጣው መሣተፋቸውን ገልፀውልን ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ እጅግ ሆድ የባሳቸው የሚመስሉት አሊዮቭ ወሬያቸው ወደ ሌላ አቅጣጫ አልሄድ በማለቱ ሰልቸትም ብሎኝ ነበር፡፡ ኧረ! እንደውም ሰንቅልፍም እያንጉላጀኝ ነበር፡፡ ቆይቶ ግን ፕሬዚዳንቱ ስለ ሳሰጋና አራን ማውራት ሲጀምሩ ነቃ ማለት ጀመርኩ፡፡ አሊዮቭ ስለነዚህ ነገሮች



t.me/OLDBOOKSPDF

በሚያወሩበት ወቅት ቁጣቸው መጨመሩንም ተገነዘብኩ:: ፕሬዚደንት ኦሊዮብ «የተከበራችሁ ወዳጆቼ አሜሪካንና የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎቿን ለመርዳት ዝግጁ መሆኔን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ» ብለው ከተናገሩ በኃላ ዙሪያ ገባውን ዞር ዞር ብለው ተመለከቱ፡፡ ከእኛ በስተቀር የሚናገሩትን የሚሰማ ሌላ እንግዳ አካል አለመኖሩ ግልፅ ነበር፡፡ በ1995 ዓ.ም ኦሊዮብ ከአሜሪካ መንግስት የኢኮኖሚ ጉዳዮች ባለስልጣናት ከሆነችው ጃዋን ስፒሮ ጋር የስልክ ውይይት አድርገው እንደነበር የሚታወስ ነበር፡፡ በዋና ፀሃፊው ዋረን ክርስቶፈር ስም ሆና ያናገረቻቸው ስፒሮ አዘርባጀን ከአሜሪካ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራት ከፈለገች የኢክሶንን የ5 በመቶ ድርሻ መስጠት ይኖርባታል» በማለት ለፕሬዚዳንት ኦሊዮብ ነግራቸው ነበር፡፡ በዚህ ወቅትም ኦሊዮብ የመለሱት መልስ ሳይሆን ጥያቄ ነበር «የኢራንን ግፊት እንዴት እችለዋለሁ?» የሚል፡፡ ስፒሮ የመለሰከላቸውም መለስም «ለዚህ አይጨነቁ አሜሪካ እርዳታ ታደርግልዎታለች» የሚል ነበር፡፡

አሊዮብ ከኢኮኖሚ ጉዳይ ባለስልጣኑ ጋር ከተወያዩ በኃላ ያስተናገዱት ስልክ ምክትል የኢነርጂ ሴክሬተሪ የሆኑትን ቦብ ዋይትን ነበር፡፡ ቦብ ለአሊዮብ ያነሡት ሃሳብም የኢክሶንን 5 በመቶ ድርሻ የተመለከተውን ሲሆን በዚህ ሳቢያ አዘርባጃንም ሆነ አሊዮብ ከኢራን ለሚደርስባቸው ዛቻም ሆነ ችግር አሜሪካ ሃላፊነቱን በሙሉ እንደምትወስድ ቦብ ዋይት ለፕሬዝዳንት አሊዮብ ገልፀውላቸዋል፡፡

አሊዮብ «... አሁን የኢክሶንን 5 በመቶ ድርሻ ተቀብያለሁ፤ ኢራንን በተመለከተ ምን እየሰራችሁ ነው?» በማለት ሁላችንንም በጥያቄ አይን ቃኙን፡፡ «ከኢራን ጋር በረጅምና ከፍት ድንበር እዋሰናለሁ፤ ይህ ምን ያህል ጥንቃቄ የሚፈልግ ጉዳይ መሆኑን መረዳት አያቅታችሁም ብዬ አስባለሁ» ሲሉም አከሉ፡፡ ኦሊዮብ ይህንን እያወሩ ባሉበት ቅፅበት በአዕምሮዬ የመጣው ነገር ቢኖር የክሊንተን አስተዳደር ለኢክሶን 5 በመቶ ድርሻ ብሎ አዘርባጃንን ከኢራን የመጠበቅ ያለ መጠበቁ ጉዳይ ነው፡፡ ሳስበው ነገሩ አልዋጥልህ አለኝ ምክንያቱም የአሜሪካ ዓላማ በሁሉም የቢዝነስ አቅጣጫዎች ዕድገትን ማፋጠን ሆኖ ሳለ ለአንድ ኩባንያ ጥቅም ስትል ኦሊዮብ የሚፈልጉትን ዓይነት ትጫወታለች ብዬ ማሰብ ስላልቻልኩ ነው፡፡ በፕሬስ ኮንፈረንሱ ወቅት ቶኒ ሌክ የብሄራዊ ደህንነት አካሪ ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ከሚስቱ ጋር በመሆን የ 304 ሺህ ዶላር ድርሻን አግኝቷል የሚለውን ነገር ስሰማ ምናልባት ኦሊዮብ ከጄዋን ስፒሮና ከቦብ ዋይት ጋር ያደረጉትን የስልክ ልውውጥ ያቀናበረው ራሱ ቶኒ ሌክ ሊሆን ይችላላ ብዬ አሰብኩ፡፡ ይህ ከሆነም ውጥረቱን በቀላሉ ለመበጠስ አስቸጋሪ ይሆናል ማለት ነው፤ ምክንያቱም በአሁኑ ሰዓት ቶኒሌክ ኢክሶንን በባለቤትነት የያዘ ሲሆን ባለቤቱ ደግሞ ሞቢልን ትቆጣጠራለች፡፡ የሆነው ሆኖ ከገንዘብና ግንዘብነክ ጉደዮች ጋር የተያያዘው አጀንዳ ወደ ሌላ ትልቅ ጉዳይ በመለጠጡ የሁሉም ትኩረት ወደ አዲሱ ጉዳይ ሆነና በርካታ ነገሮች ተረሱ፡፡ በጊዜው ሱዳን ኦሳማ ቢላደንን አሳልፋ ለመስጠት ቃል መግባቷን ተከትሎ ኃይት ሀውስና የብሄራዊ ደህንነት መሳሪያ ቤቱ ስለ እሞኮ፣ ሞቢልና ኢክሶን የሚያስቡበት ሽርፍራፊ ጊዜም አልነበራቸውም፡፡ ከአሜሪካ ፖለቲካዊ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሰው በሙሉ ማለት ይቻላል ትኩረቱን ያደረገው ከኦሳማ ቢላደን ጋር ከተያያዘው ጉዳይ ጋር ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

✡✡✡

ጂም ጅፋን ማለት የካዚኪስታን የነዳጅ ዘይት ቢዝነስ የተቆጣጠረ ግለሠብ ነው፡፡ ከቢዝነሱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ የአካባቢው ከንቲባ እርሱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የጂፋን ስራ ከቢዝነሱም በላይ ነው፡፡ በካዛኪስታን የዋሽንግተን አምባሳደርም ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአንድ ወቅት የካዛኪስታን ፕሬዚዳንት ናዛርባየቭ ዋሽንግተንን ለመጎብኘት ሲዘጋጁ አልም እታ ለምትገኘው አምባሳደር ለያ ቤት ጃንስ ሳይሆን ለጅፋን ነበር የደወሉለት፡፡ ከዚህ አንፃር ታዲያ የጅፋርና የካዛኪስታን ፕሬዚዳንት ናዛርባየቭ ግንኙነት እስከምን ሊደርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ናዛርባዮቭ ለጅፋን ኩባንያ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚያበረክቱም አያጠራጥርም፡፡

ዋሽንግተን ውስጥ የጂፋን ተቀዳሚ ግንኙነት የተመሰረተው በኃይት ሀውስ መንግስት የኢንተሊጀንስ እና ሪሰርች ቢሮ ሃላፊ ከሆኑት ቶቢ ትሪስተር ጋቲ ጋር ነው፡፡ ሀላፊው ከCIA ወይም ከሌላ አካል ከሚያገኙት መረጃ ይልቅ ጂፋን የሚሠጣቸው መረጃ ጠቃሚ ነው፡፡ በተለይም ከካዛኪስታንና ከፕሬዚዳንቱ ጋር ለሚያያዙ ጉዳዮች ጋቲ መረጃ የሚያገኙት ከጂፋን ነው፡፡ ካዛኪስታን ለሰሜን ኮሪያና ኢራን የጦር መሣሪያዎችን በድብቅ እንደምትሸጥ የደረሱበት ጋቲ መረጃውን ያገኙት የናዛርባዮቭ ወዳጅ ከሆነው ጂፈን ነበር፡፡ በካዛኪስታን የተከሰተን አንድ የሙስና ወንጀል ጋቲ ያገኙት ከጂፈን ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ሁኔታ አምባሳደር ያቤት ጆንስንን ያስቆጣ ነበር፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ጂፋን አንድ ሰው እንጅ ድርጅት ባለመሆኑ ከ CIA እና ከሌሎች የአሜሪካ ቀኝ እጅ ድርጅቶች ይልቅ ጂፈን ሊታመንና ሊከበር አይገባውም የሚል እምነት ስለነበራቸው ነው፡፡ የሆነው ሆኖ የያቤት ጆንሰን ንትርክም ሆነ ቁጣ ጋቲም ሆኑ ኋይት ሀውስ የሚያዳምጡት አልሆነም፡፡

በታህሳስ 1995 ዓ.ም ለአንድ አስቸኳይ ስብሰባ በጆርጅያ ስገኝ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ጋቲ ምን ያህል በነዳጅ ዘይት ቢዝነስ መረብ ውስጥ በጥልቀት እንደገባ ነው፡፡ በብሄራዊ ደህንነት ካውንስሉ መሰብሰቢያ አዳራሽ ሰገባ የሼላ ሔስሊን አሊታን ጨምሮ የጆርጅ ታውን ዩኒቨርስቲ ዲን ባለቤትንና ሌሎች ለፕሮቶኮል የመጡ የሚመስሉ ሰዎችን ነበር ያገኘሁት፡፡

ስብሰባው እንደተጀመረም የመጀመሪያ ተናጋሪዋ የነበሩት የጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ዲን ባለቤት ጄኒፈር ሲምስ ነበሩ፡፡ ሲምስ «ለጆርጅያ ፕሬዘዳንት ኤድዋርድ ሸቨርድና ድዚ አውሮፕላኖቻቸውንና ሄሊኮፕተሮቻቸውን ከጥቃት የሚከላከሉበት ማታዶር ሊንሰጣቸው ይገባል አሉ፡፡ እስቲ የታያችሁ «ማታዶር» ማለት ደግሞ ልክ እንደ ራዶር ሄሊኮፕተርንና አውሮፕላንን ለመምታት የሚተኮሱ ሚሳኤሎችን የሚቆጣጠር የረቀቀ መሳሪያ ነው፡፡ ሸቨርድና ድዚ አሜሪካ ከአካባቢው የነዳጅ ዘይት ኤክስፖርት መስመር እንዲዘረጋለት መስዋዕትነት የከፈሉ ግለሰብ ናቸው፡፡ ስለሆነም አሜሪካ እኚህን ሰው ማጣት የለባትም፡፡» በማለት ተናገሩ እናም ታዲያ ሲምስ ይህንን በሚናገሩበት ቅፅበት «ሰውዬው ይህንን ያህል ጠቃሚ ከሆኑ ለምን የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች ከለላ አያደርጉላቸውም?» በማለት አሰብ ነበር፡፡ ይሁንና ሀሳቡን ለራሴ በማስቀረት ማዳም ሲምስ የሚናገሩትን ከመስማት ውጭ አማራጭ አልነበረኝም፡፡ ሲምስም ንግግራቸውን



t.me/OLDBOOKSPDF

በመቀጠል ያልጠበኩትን ጉድ ዘከዘኩት «ለማታዶር መግገር የሚውለው ገንዘብም ከ CIA ሊገኝ ይችላል፡፡» ሲሉ አይኔ በድንጋጤ ሲፈጥ ታወቀኝ፡፡ መጀመሪያ ላይ ሀልም እያለምኩ መስሎኝ ነበር፡፡ አለመሆኑን ስገነዘብ ግን በጣም አዘንኩ፡፡ ከሁሉ ከሁሉ በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ የኃይት ሀውስ መንግስትና ባለስልጣናት የ CIA ባልደረባ የነበረው ፍሬድ ውድሩፍ በጆርጂያ ሲገደል ፕሬዚዳንት ሼቫርድናድዚ የመረጃ ምንጮችን በመዝጋት ጉዳዮ ተድበስብሶ እንዲቀር ማድረጋቸውን መዘጋታቸው ነበር፡፡ ይባስ ብለውም ለማታዶር መግገር ሁለት ሚሊዮን ዶላር ከCIA ኪስ እንዲወጣና ፕሬዚዳንቱ ከለላ እንዲደረግላቸው ይወተውታሉ፡፡ እኔም ታዲያ ንዴቴን መቆጣር ሲያቅተኝ የግለሰቧን ንግግር በማቋረጥ «ይህ ሊሆን የማይችል ነገር ነው!» ስል አምባረቅኩ፡፡ በዚህን ግዜ ሁሉም ሰው ወደ እኔ በአግራሞት ተመለከተ፡፡

የሼላ ሑስሊን አለቃ የሆኑት ራንድ ቢርስ በተረጋጋ ስሜት ወደኔ በመዞር «ቦብ፣ ምን ችግር አለው ትላለህ?» አሉኝ፡፡

«ሚስ ሲምስ የማታዶር ሲስተም እንዲዘጋጅላቸው ሃሳብ የሚያቀርቡላቸው ግለሰብ ነፍስ ገዳይ ናቸው!» አልኩኝ፡፡

ዶክተር ብላከር ግን አፋቸውን ከፍተው ቀሩ፡፡ የኮንፈረሱን አዳራሽ ሰንጥቀው ወደ እኔ በመምጣት ካልገደልኩህ የሚሉኝም መሠለኝ፡፡ «ይቅርታ ቦብ አንተ ስለምታወራው ነገር እዚህ ቤት ያለን ሰዎች በጠቅላላ እንግዳ ሳንሆን አንቀርም» ሲሉ ቢር ተናገሩ፡፡

«የጆርጂያ KGB ሃላፊ፣ የሸቫርድናድዚ ደህንነት ሃላፊና ግለሰብ ነፍስ ገዳዮች ናቸው፡፡ በተለይም የደህንነት ሃላፊው ስድስት ጭምብል ያጠለቁ እስረኞችን ጭንቅላ. ጭንቅላታቸውን በመትረየስ ሲረሽኗቸው የሚያሳይ የቪዲዮ ምስል አለን፡፡ ከፈለጋችሁ አሁኑኑ ወደላንግሌይ ሄጄ ቪዲዮውን አምጥቼ ላሣያችሁ እችላለሁ፡፡ ወደዳችሁም ጠላችሁም እነዚህ ሰዎች ሰብዓዊ መብትን የጣሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ በየትኛውም ስሌት CIA ለእነዚህ ሰዎች እርዳታ ሊያደርግ አይችልም፡፡» አልኩኝ ፈርጠም ብዬ፡፡

የቪዲዮ ፊልሙን ለማምጣት ፈቃደኝነቴን በመመልከት ይህንን እንዳደረግ ፍላጎት የነበረው ማንም አልነበረም፡፡ እኔም ስለ ማታዶር ከዚያን ቀን ስብሰባ በኃላም ስምቼ አላውቅም፡፡

☆☆☆

እንደነዚህ አይነት አስገራሚ ውይይት የሚደረግባቸው ስብሰባዎች እያንዳንዱን ሰው በአንክሮ እንዲመለከቱት የሚያስገድዱ ናቸው፡፡ የሼላ ሑስሊን አለቃ ራንድ ቢር በውይይታችን ወቅት ከነበረው ተሣትፎ አንፃርም ዋሽንግተን የምትገኘው ሼላ ሑስሊን ምን እንደምትሠራ መከታተል ግድ ይሆናል፡፡ የሑስሊን መደበኛ ስራም ከውጭ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን በተለይም በካስፒያን አካባቢ ለሚንቀሳቀሱት ግዙፎቹ ነዳጅ አምራች ድረጅቶች ወይንም 'ነጋዴዎች' የተቀላጠፈ እርዳታ እንዲያገኙ በሚያደርገው ዲፓርትመንት ውስጥ ከፍተኛ ተሣትፎ ታደርጋለች፡፡ ይሄ የነጋዴዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

ቡድን ደግሞ ለሮገር ታምራዝ መልካም አመለካከት የሌለው ነበር፡፡ ምክንያቱም ሁሉንም ነገር ከትርፍ አንፃር የሚመለከተው ታምራዝ ከእነሱ ጋር የመግባባት ወኔ ይኖረዋል ተብሎ አይጠበቅምና፤ በዚያ ላይ ታምራዝ በርካታ ሰዎችን ስለሚያውቅ በአካባቢው ባለው የነዳጅ ዘይት ግንድ እንቅስቃሴ ከሁሉም ሰዎች ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆነው እርሱ ነውና ነው፡፡

እንግዲህ ቪላ ሔስሊን ለሮገር ታምራዝ ያላት ጥላቻ ከዚህ ይመነጫል ብሎ ማሡብ ይቻላል፡፡ በዚያ ላይ የሔስሊን ሌላኛው አለቃዋ በብሄራዊ ደህንነቱ ምክትል አማካሪ በመሆን የሚሠራው ሳንዲ በርገርም ከካስፒያን የነዳጅ ዘይት የቢዝነስ እንቅስቃሴ እጁ ያለበት መሆኑና ይህም ለታምራዝ አስፈሪ ከሚሆኑበት ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑ ነው፡፡ ሌላው የሮገር ታምራዝ የነዳጅ ቢዝነስ ባላንጣ ደግሞ በቼቭሮን የሚመራው ቡድን ነው፡፡ እናም እኔ በጉዳዩ ዙሪያ በጥልቀት በገባሁ ቁጥር የካስፒያን ነዳጅ ቢዝነስ የገንዘብ ምንጭ ከወደ ኃይትሃውስ እንደሚፈልቅ እየተረዳሁ መጣሁ፡፡ ሁሉም የአካባቢው የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች ባለአክሲዮኖችን ከኃይት ሀውስ ጋር ጥብቅ ግንኙት በመፍጠር ድርሻቸውን መሸጥ የሚፈልጉ ወይም ደግሞ በፖለቲካ ሽፋን ማደግ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ በዚህ ዓይነቱ የቢዝነስ አየር ውስጥ ንቁ ተሣትፎ ከሚያደርጉት ካምፓኒዎች ውስጥ የበርገር «Hogan & Hartson» የተሰኘው ኩባንያ የሚገኝበት ሲሆን ኩባንያው በኃይት ሀውስ እና በካስፒያን አካባቢ ባለው እንቅስቃሴ በመሆን የቢዝነሱን ሁነኛ የፖለቲካ ጨዋታ ይጫወታል። ከኃይት ሀውስ ጋር ግንኙነትን መፍጠር ለሚችሉ ሃገራትም ሆነ አካላት ዋስትናን በመስጠት ሁኔታውን የማፋጠን አቅም አለው። ከዚህ አነፃርም ታዲያ ቱርክሜኒስታን ሁኔታውን በመጠቀም 'ሜርሄቭ' በተባለ ድርጅት አማካኝነት ከአሜሪካ እስከ እስራኤል የህዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ ጋር ግንኙነትን መፍጠር ችላለች። በጥቅሉ እንመልከተው ብንል አንድ ነገር ይገለፅልናል፦ የነዳጅ ዘይት ካምፓኒም ሆነ ነዳጅ ዘይት አምራች ሃገር በዋሽንግተን ውስጥ አንድ ነገር ለመስራት ቢፈልግ አስቀድሞ የሚከፍለው ዋጋ እንዳለ መኖሩን መረዳት አለበት።

☼☼☼

ከሁለት ቀናት በፊት ከሮገር ታምራዝ ጋር የስልክ ግንኙት አድርገን ነበር ታምራዝ አሁንም የግዙፍን የነዳጅ ዘይት ፖለቲካዊ የቢዝነስ ስትራቴጅ በኃይት ሃውስ መንግስትና በካስቢያን አካባቢ በመሆን እያጠናከረው እንዳለ ነው ያጫወተኝ፡፡ ተቀናቃኞቹንም እንዴት መምታት እንዳለበትም ያውቃል፡፡ ታዲያ ለዚህ ተግባሩ የCIA ሰዎችና የኃይት ሀውስ ቤተመንግስት ጆሮ ጠቢዎች ያስፈልጉታል፡፡

«ስልክ ቁጥርህንና ስምህን ለዶን ፎውለር ሰጥቼዋለሁ» አለኝ ታምራዝ በመካለብ፡፡ በመለጠቅም ፕሮጀክታችን በተመለከተ አንተን ደውሎ እንዲያናግርህ ነግሬዋለሁ» አለ፡፡

«ዶን ፎውለር?!» አልኩ በድንጋጤ፡፡

«አዎ!፤ የብሄራዊ ዴሞክራሲው ሊቀመንበር ከእኛ ጎን ነው» ሲል ታምራዝ የሰውዬውን ማንነት ይበልጥ አረጋገጠልኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«ቁጥሬን ለብሄራዊ ዲሞክራሲው ሊቀመንበር ሰጠኸው??» አልኩት ግራ ተጋብቼ፡፡

ሮገር ታምራዝ የሚያስበው አንድ ነገር ብቻ ይመስላል፡፡ በCIA ውስጥ ስላሉት ውጥንቅጥ ጉዳዮች ቁብ የለውም፡፡ ለታምራዝ የሰጠሁት ስልክ ቁጥሬ በCIA የምጠቀምበትን ምስጢራዊ ቁጥሬን ስለነበር ይህ ለእኔ አደገኛ ነበር፡፡ ከሮገር ጋር በስልኩ ተነጋግረን ከተለያየን በኃላ ወዲያውኑ ለፎውለር ደወልኩለት፡፡ ላገኘው ባለመቻሌ ሌላ የስልክ አድራሻ ትቼለት በዚሁ እንዲደውልልኝ መልዕክት አስቀምጬ ስልኩን ዘጋሁት፡፡

ሁለት ሰዓት ከምናምን ላይ በCIA'ው ሚስጢራዊ ስልኬ ላይ መልሰው ደወሉልኝ፡፡

«ዶን ፎውለር ነኝ፡፡» ከድምፃቸው ጥግ ያለው ድምፅ የተጠቀሙበት ስልክ የህዝብ ስልክ መሆኑን ሰብቆኛል፡፡ እናም ፎውለር የደወሉልኝ ከአየር ማረፊያው ነበር፡፡ የሮጀር ወዳጅ ነኝ፡፡ እርሱን በተመለከተ ስኃይት ሃውስ የምታስተላልፈው አንድ ፅሁፍ እያዘጋጀህ መሆኑን ሮጀር ነግሮኛል፡፡» አሉኝ፡፡

እንደእውነቱ ከሆነ ሮጀርን በተመለከተ የያዝናቸውን ማስታወሻዎች በሙሉ በሺይላ ጥያቄ ወደ N.S.C ልከናቸዋል፡፡ C.I.A ምስጢር አድርጐ ያቆየውንና ከታማራዝ ጋር ያለውን ግንኙነት የተመለከቱ ወረቀቶችን በዋሽንግተን አካባቢ እያሰራጩ ቢሆን ኖሮ እያናገሩኝ ያሉት የራሱ የፐሬዝዳንቱ ሰው በመሆናቸው ቢያንስ እውነታውን ልነግራቸው እችል ነበር፡፡

የኔ ልጅ ለፐሬዝዳንቱ የማሳየው አንድ የወረቀቱ ቅጂ እንዲኖረኝ እሻለሁ ፕሬዝዳንቱ ሮጀር ለዚህች አገር የዋለውን ውለታ ማወቅ ይፈልጋል፡፡ የት አግኝቼህ እንደምትሰጠኝ ንገረኝ፡፡»

እናም ይህ አባባላቸው ፈጥኖ ማሰብን የሚጠይቅ ሆኖ አገኘቼዋለሁ፡፡ ሮጀርን ማወቁን ማስተባበል ብችልም ለፕሬዝዳንቱ ቅርብ ለሆነ ሰው መዋሸት ማምለጫ መንገድ ሊሆን ይችላልን? ወይስ ሮጀርን እንደማውቀው አምኜ በእርሱ ዙሪያ የተፃፈ ወረቀት መኖሩን ሸምጥጬ ልካድ፡፡ ያን ማድረጉ ግን በመጠኑ ሊያስነቃ እንደሚችል በማወቁ ሶስተኛ መላ ዘየድኩ፡፡

«ጌታዬ» ስል ተናገርኩ፡፡ ሮጀር ለዚህች አገር ስለሰራውም ሆነ ስላልሰራው ነገር መናገር አልችልም፡፡ ሮጀር እንደነገርዎት በእርሱ ላይ የተፃፈ ወረቀት ካለ ኃይት ሃውስ ውስጥ ያገኙታል፡፡» አልኳቸው

በራሴ ኮራሁ፡፡ ለፎውለር የሰጠሁዋቸው ምላሽ ቢሮክራሲያዊ አሰራርን የተከተለ ነበር፡፡ ከአሁን በኃላም ማስታወሻውን በተመለከተ ሂስሊን ሊያገኙት እንደማይችሉ እንድትነግራቸው አድርጌአለሁ፡፡

ፎውለር ያሰቡትን ከኔ ማግኘት ባለመቻላቸው ደንፍተው ስልኩን ጠረቀሙት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ከDNC ሊቀመንበር ለአንድ ለመሀከለኛ የስልጣን እርከን ላይ ለሚገኝ የCIA ዘመቻ መምሪያ ባለስልጣን የሚደረግ የለዘበ የስልክ ጥሪ ያለውን አደጋ በመገንዘቤ ወዳጄ ለሆነ አንድ የFBI ሰራተኛ ደውዬ ምክሩን ጠየቅኩት፡፡

የFBI ጓደኛዬም በአግራሞት ዕይታ ምክሩን ለገሰኝ።

«አሁን ማድረግ ያለብህ ጉዳዮን በሳግሴይ አካባቢ እንደፍግ ማዳረስ ነው፡፡» ሲል መከረኝ፡፡ ልትነግራቸው ለምትችለው ሰዎች ሁሉ ጉዳዩን ተናገር፡፡ በየቦታው እርሱን የተመለከተ መዝገብ አስቀምጥ፡፡ ይህን ካደረግክ እያነፈነፍክ ያለኸው ምን ሆነ ምን ማንም ዞር ብሎ ከአንተ ጋር የተነጋገረውን ማስታወስ አይፈልግም፡፡»

ምክሩንም በማዕከላዊ አውሮ-ኤስያ ምድብ ስራ አስኪያጅ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ጀመርኩ፡፡ ታሪኬንም ስነግረው የስራ አስኪያጁ ፊት እንዳች አስፈሪ ገፅታ መላበሱን አስተዋልኩ፡፡ ለምድቤ የሚሰራውን ጠበቃ ላገኘው ባለመቻሌ ለቅርብ ምስራቁ ምድብ ወደሚሰራው ጠበቃ ቢሮ አመራሁ፡፡ ጠበቃውም ቢሮውን ለቅቄ እንደወጣሁ የተነጋገርንበትን ጉዳይ ጠቅለል ባለ መልኩ የማዕከላዊ አውሮፓ ምድብ ጠበቃ ለሆነው ቦብ ካውዴል፣ የCIA ዘመቻ መምሪያ ቢሮ ጠበቃ ለሆነው ጆን ሪዞ እና የኢራቁ ጉዳይ ምርመራን ማካሄዱ እንደሚጠቅመኝ ለነገረኝ ብልሁ ሮብ ዳቪስ በኢሜይል በማስተላለፍ ረገድ በአድሜዬ ሁሉ የማልዘነጋው ውለታ ውሎልኛል ኋላ ላይ ግን ጉዳዩ መፈንዳት ሲጀመር መሰራጨት ህይወቱን እንደሚያተርፍልኝ ገብቶኛል።

በጉዳይ እንድገፋበት እንደምትነግረኝ ተስፋ በማድረጌ ሄስሲንን ደውዬ እስካገኛት መታገስ አልቻልኩም፡፡ አሁን አሁን ሁኔታዎችን በመመዝገብ ሁነቶችን እና ጊዜያትን እያነፃፀርኩ ያላቸውን አድምታ መመርመሩን ልምዱ አድርጌዋለሁ፡፡ የስልክ ጥሪውን ያደረግኩላት ጥቅምት 23 የነበር ሲሆን በማስታወሻዬ ያሰፈርኩት ንግግራችን የሚከተለው ነበር፡፡

እኔ፡- «ሮጀር ኃይት ሃውስ ሲገባ መሆኑን የምታውቂ ይመስለኛል፡፡ ከክሊንተን ጋር ቀጠሮ ይዟል መሰለኝ፡፡»

እሷ፡- «ሰምቼ የማላውቀው መሆን የማይገባው ነገር ነው፡፡ ሮጀር በምስጢር ድርጅቱ ጥቁር መዝገብ የሰፈር ሰው ሲሆን፡፡ ስሙ እዚያ ዝርዝር ውስጥ እንዲሰፍር ያደረግኩትም እኔው ነኝ ኃይት ሃውስ ውስጥ መግባት አይችልም እራት ነጥብ፡፡»

እኔ፡- «እዚያ የሚደርሰው በፎውለር በኩል ነው ይባላል፡፡»

እሷ፡- «የለም የሚደርስ አይመስለኝም፡፡ እዛ ላሉት ሰዎች የምታበጁላቸው መላ ምንድነው?»

ስልኩ ከወዲያኛው ጫፍ በሀይል ሲጠረቀም ተሰማኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እናም በወርሃ ጥቅምት 25 ቡድኑ በሮጀር ታምራዝ ላይ የሚያደርገውን ክትትል ፈፀመ፡፡ ከክረምቱ የሰራተኞች የስራ ዝውውርና እረፍት ጐን ለጐን ከመዝገብ ቤት የሮጀር ፋይል እንዲመጣልኝ አድርጌ ፋይሉ ከሰኔ ጀምሮ ቢሮዬ እንዲቀመጥ አድርጌአለሁ፡፡ ማስታወሻው ከማንኛዉም ተፅእኖ እንዲጠበቅ ለማድረግ ፎውለር ከመደወላቸው በፊት ቢላክ ምርጫዬ ነበር፡፡ ምክንያቱም ራሱን በራሱ የሚገልፅ ማስታወሻ እንደሆነ እውቃለሁና፡፡ ግንቦት 19 ለሂስሊን የላክንላትን ክብር የሚነካ መረጃን ብቻ ሳይሆን BCCI'ን የተመለከተ ዝርዝር መረጃ ጭምር ነበር፡፡ ይሁንና ሮጀርን ለማስከሰስ የሚበቃ የተጠናከረ ማስታወሻ ግን አልነበረም፡፡ ከዛ ይልቅ እርሱን በተመለከተ የCIA'ው ዘመቻ መምሪያ (D.O) የሚያውቀውን ትክክለኛና ተዓማኒ መረጃ ሁሉ ማስታወሻው ይዟል፡፡

የጥቅምቱ ማስታወሻ ከደቡባዊ ቡድኑ ከተላከ በኃላ ያስከተላቸው ችግሮች መታየት ጀመሩ. ታማራዝ ብዙ ሰዎችን ማስፈራራት ጀምሯል፡፡ ማስታወሻው ዲ.ዲ.ኦ 953136 የሚል መለያ ተሰጥቶት ከዴብ ኮህን እጅ ቢገባም ዴብ ነገሮች ጥሩ ሳይሸቱት ቀርተዋል፡፡ የታምራዝ ከዲ.ኤን.ሲ እና ኃይት ሃውስ ሰዎች ጋር ሽርክና መፍጠር በማስታወሻው ተገልፆል፡፡ ስለዚህ ራሱን ለመከላከል ፖለቲካዊ ደመነፍስ የሚነድለው በመሆኑ የዘመቻዎች ኃላፊ ያልተደረገው ኮህን ከማስታወሻው ህዳግ በረዳቱ «ታማራዝን የተመከተውን መረጃ ወደ ኤን. ኤስ. ሲ አስተላልፈናል፡፡ በመሆኑም ኤፍ ዋይ ኢ! ሰውየው የአሜሪካ ዜጋ መሆኑን እየገለፅኩ ዲ.ኦ/ኤል.ጂ.ኤል ፋይሉ ወደ ኤን.ኤስ.ሲ እንዲተላለፍ እንዲፈቅድ እጠይቃለሁ፡፡» የሚል ፅሁፍ እንዲሰፍር አድርጎ ማስታወሻውን ለጠቅላላ ካውንስሉ ቢሮ መራው፡፡

ራሱን ለመከላከል የሚሮጠው ሰው ኮህን ብቻ አልነበረም፡፡ ታህሳስ 13/1995 የፀረ ስለላ ተቋሙ ምክትል ኃላፊ የሆነው ፓውል ሬድሞንድ የጥቅምቱን ማስታወሻ የተቋሙ ኃላፊ ለመሆን ለታጨው እና በተከታይ ምክትል ኃላፊነት ቦታ ለሚሰራው ጆርጅ ቴኔት አስተላልፎታል ማስታወሻው ከልባሱ ላይ በጥቁር እና ነጭ ቀለማት ታማራዝ ከፎውለር፣ ከሄስሊን እና ከሌሎችም ፖለቲከኞች ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚገልፅ ፅሁፍ ቢኖረውም ቴኔት ህዳጉ ላይ «ሙሉ በሙሉ ያልተነበበ በመሆኑ እዚህ ላይ ትኩረት ይደረግበት» የሚል ማሳሰቢያ አስፍሮበታል፡፡ ቴኔት ሁለት ገፅ ሙሉ በዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝዳንት እና ተከሳሽ በሆነው መካከለኛ ኑሮ ባለው ሰው መሃል ያለውን የገንዘብ ትስስር በተመለከተ የሰፈረውን ማስታወሻ የሚያነብበት ጊዜ አልነበረውም፡፡ እኔ ግን በቴኔት ቦታ ብሆን ኖሮ ያንኑ እለት ማስታወሻውን አይቼ እንዳላየሁ አስመስል ነበር እንጂ በዛ መልኩ የማገኘው ትርፍ እንደሌለ እውቃለሁ፡፡

የጠቅላላ ካውንስሉ ቢሮ ሰባተኛ ደርብ ላይ የሚገኘውን ውሳኔ ሰጭ አካል መሸበር መዘንጋቱ ግልፅ ነው፡፡ በጠባቡ የአለም ህጋዊ እይታ ታማራዝ ከቢንላደንም ሆነ ከእየሱስ ክርስቶስ ያለው ግንኙነት የሚፈጥረው ልዩነት የለም በ CIA'ው ሕግ ግን ቀላልና ለሌሎች ተቀናቃኝ ግኝቶች ቦታ የማይሰጥ ነው ሕጉ CIA የአሜሪካን ዜጎችን ክብር የሚያጎድፍ መረጃ ኃይት ሀውስን ጨምሮ ለሌሎች የመንግስት ተቋማት አሳልፎ እንዳይሰጥ ያግዳል፡፡ ከዚህ አኳያ የጠቅላላ ካውንስሉ ቢሮ ታማራዝን በተመለከተ የቀረቡ አሉታዊ አስተያየቶችን በማውጣት ማስታወሻውን ለኮህን መልሶ ልኮታል ራሱን ከተጠያቂነት ያወጣው ኮህንም ማስታወሻውን በፋክስ ለሄስሊን ታህሳስ 26, 1995 አስተላልፎታል፡፡ ሰኔ ውስጥ ተጠይቆና ከሰባት ወራት መዘግየት በኃላ የደረሰው የማስታወሻው ተከታይ ክፍልም ስለ ሮጀር



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚነቅሰው ነገር አልነበረውም። ሄስሲንም ለCIA በነበራት ቸልታ ተደነቃቅፋ ከሙሰኛው የCIA የሴራ መረብ መውደቋን አውቃለች፡፡

☼☼☼

ነገሩ በዚያ ቢያበቃ ጥሩ ነበር፡፡ ታህሳስ 6 ሮጀር ታማራዝ ምሳ ሊጋብዘኝ ጥያቄ አቀረበልኝ ነበር ተገናኘን ከዚያም ፎር ሲዝንስ ሬስቶራንት ውስጥ የ ሲ እና ኦ ጅረትን እዘቅዝቀን ማየት ከሚያስችለን አንድ የግማሽ ቅርፅ ያለው ቤት ገብተን ተቀመጥን፡፡ ቤቱ ነጋዴዎች ብዙ ጊዜ ራሳቸቸውን ወደፊት አስግገው ሰው ሳይሰማቸው ለማውጋት የሚመርጡት ዓይነት የሚመች ቤት ነው፡፡

«ፕሬዚዳንቱን አግኝቼዋለሁ፡፡» አለኝ ሮጀር በኩራት መንፈስ

«እንዴት አድርገህ ሮጀር?» ስል ጠየቅኩት ቃላቱ ከአፌ እንደወጣ ስቀጠጠኝ መውጣት እንዳልነበረበት አውቄአለሁ፡፡

«ቀላል ነበር ፎውለር ለዘመቻው መዋጮ ማቅረብ የምችለውን የዋጋ ዝርዝር ሰጠኝ እኔም ከፕሬዝዳንቱ ጋር በጉዳዮ ላይ ለመምከር አንድ ሌሊት በሊንከን መኝታ ቤት ከማሳለፍ አንስቶ ከፕሬዝዳንቱ እንቁላላማ ቅርፅ ቢሮ እስከመዝለቅ ደርሼአለሁ፡፡»

ለጠቀና «ግብዣዬን በትንሹ ልጀምርልህ ቡና ጠጣ» ሲል ታማራዝ በገንዘብ ቆጣቢነቱ እየተኩራራ ተናገረ፡፡ «ቢልን ለማግኘት ወይ አርሜንያ መጓዜን ልነግርህ ይገባል ቢልም የሴራው ተካፋይ ስለነበር የበለጠ ስለሱ እንድነግረው ፈልጓል፡፡»

«ይህ ነገር ሄስሲንን ያስደስታታል» ስል ጮክ ብዬ አጉተመተምኩ፡፡ እኔም ብሆን በእውነቱ ፕሬዝዳንቱ ለሮጀር ፍፁም አባውንቱን' ቢልን' መስሎ እንደሚታየው አውቄአለሁ፡፡ ታማራዝ ታላቅ እምነት የሚጣልበት ሰው አይደለም፡፡

«የለም የለም» ሲል ንግግሩን ቀጠለ ነገሩ ከዛም አልፎ ሄዷል፡፡ ነገ እንቁላልማው ቢሮ ውስጥ ቢል እና እኔ እንገናኛለን፡፡ ሁለታችንም ለአካባቢው ጠቃሚ የሆነ የጦር ስልት እንነድፋለን፡፡ ለዚሁ ስል ከሩሲያ ጋር የሚያገናኝ የግንኙነት መስመር እንዲከፍት አድርጌአለሁ፡፡»

«ከሩሲያ ጋር የሚያገናኝ የግንኙነት መስመር?» ታማራዝ ለመጨረሻ ጊዜ ያደረገው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያተረፈለት ኪሳራን ነበር፡፡

«በእውነቱ ወዲህ የተመለስኩት ሚላን ውስጥ ከሩሲያውያኑ ጋር ካደረግኩት ስብሰባ በኃላ ነው ስብሰባው ላይ አሌክሳንደር ኮርዛኮቭ እና ፓቬል ቦሮዲን ተገኝተዋል፡፡»

ኮርዛኮቭ እና ፓቬል ቦሪስ የልሲን የአስቸኳይ መልዕክት ማስተላለፊያውን የስልክ መስመር ለማግኘት ይደክሙባቸው በነበሩባቸው ሌቶችና ቀናት ሩሲያን እንዳሻቸው ያሽከረከሩ የነበሩ ሰዎች መሆናቸው በግልፅ የሚታወቅ ሲሆን በድብቅ የየልሲንን ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ቦሮዲን ጆርጅ ቡሽ በሚፈፅሙት



t.me/OLDBOOKSPDF

ፕሬዝዳንታዊ ቃለ መሃላ ላይ ለመገኘት በመጓዝ ላይ እንዳለ በስዊስ ባንክ በወንጀል የተገኘ ገንዘብን በማስቀመጥ ወንጀል ተከሶ ኒውዮርክ ውስጥ በፖሊስ ተይዟል፡፡

«ለክሊንተን ጻግም ምረጡኝ ዘመቻ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ነግረውኛል፡፡ ... ድጋፋቸውም በገንዘብ በኩል የሚደረግ ነው፡፡» ይገባሀል አለኝ፡፡

አሁን ከመቀመጫዬ ልነሳ ምንም ያህል አልቀረኝም ሮጀር በትክክል አቅሉን ስቷል፡፡

«የፕሮጀክታችን ዋናው ክፍልም ይኸው ነው፡፡»

«ፕሮጀክታችን እያለ ማውራቱን ቢያቆም ምኞቴ ነበር፡፡

«የልሲን ስራቸውን ጥለው ወደ አሜሪካ ይጓዛሉ፡፡ ለዘመቻቸውም የተወሰነ ገንዘብ ይዘው ይሄዳሉ ገንዘቡም በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር እንደሚሆን ተነጋግረናል፡፡ እኔም የሚያስፈልገኝንም ገንዘብ ሊያሟላልኝ ቻይናዊው ቃል ገብቶልኛል፡፡ የልሲንም ለቢል ዘመቻ ጥቂት ገንዘብ ፌሰስ ለማድረግ ተስማምተዋል፡፡ እናም ፕሬዝዳንቱን አግኝቼ ስለሁኔታው ለመናገር ቸኩያለሁ፡፡

ከሮጀር ጋር እንደተለያየን ወደ ሞገደኛውና ግልፍተኛው የእውሮ ኤስያው ምድብ ኃላፊው ቢል ሎፍግረን በማምራት ሮጀር የነገረኝን ወሬ ነገርኩት፡፡

«ዕመነኝ የማይታመን ወሬ ነው፡፡» ሲል ቢል ምላሽ ሰጠኝ፡፡

እርግጠኛ ለመሆን ስልኩን አንስቶ እና ወደ ፀሃፊው ደውሎ ከሮም ጋር እንድታገናኘው ጠየቃት። ታማራዝ እንዳለው ታህሳስ አንድና ሁለት ቦሮዲን እና ኮርዢብሽ ሚላን ውስጥ እንደነበሩ ለማረጋገጥ ፈልጓል። ሁሌም መጀመር ያለበት ተጨባጭ ከሆኑ መረጃዎች እንደሆነ ያውቃል።

በቀጣዩ ቀን ሁለቱ ሩሲያውያን ሮጀር ነበሩ ካላቸው ስፍራ መገኘታቸውን ካረጋገጥን በኋላ ሎፍግረንን ታማራዝ የተናገረውን ከራሱ አንደበት እንዲሰማው በማለት ወደታማራዝ ወሰድኩት። እዛም ታማራዝ ያልኩትን ቃል በቃል ደገመለት። አሁንም ያን ዕለት ከሰዓት ክሊንተንን ለማግኘት የያዘውን ቀጠሮው እንዳልሰረዘው ለሎፍግረን አረጋገጠለት። አዲስ የጨመረልን ነገርም ኃይት ሃውስ ውስጥ ከክሊንተን ፊት ተቀምጦ ቡና እየጠጣ የተነሳውን ፎቶ ግራፍ ያሳየን መሆኑን ነው።

እኛም ወደጠቅላይ መምሪያው እንደተመለስን ሎፍግረን ለምክትል ሃላፊው ጆን ደች ደውሎ ወሬውን ነገረው። ያንዕለቱኑ ከሰዓት በኋላ የደች ረዳት ደወለልን ፕሬዝዳንቱ ለአጭር ቆይታ ወደፓሪስ መሄዳቸውንና ከታማራዝ ጋር ቀጠሮ እንደሌላቸው ነገረን። «የመረጃ ምንጭህ ችግር አለበት። ቀጣፊ መሆኑም ግልፅ ሆኖልናል።» ሲል ረዳቱ ለሎፍግረን ነገረው።

☆☆☆



t.me/OLDBOOKSPDF

ከአራት ቀናት በኋላም ፎውለር ደወሉልኝ። «የኔ ልጅ አሁንስ ስለዛ ማስታወሻ ያለህን ሃሳብ አልለወጥክም?»

የጥቅምቱ ማስታወሻ በዘመቻ መምሪያው ምክትል ኃላፊ እና በጠቅላላው ካውንስል ቢሮ መስረዝና መደለዙን ባለማወቁ ታማራዝን የተመለከተ CIA ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ወረቀት በሺይላ ሄስሊን እጅ እንደሚገኝ ለፎውለር ነገርኳቸው ወረቀቱም ከእርሷ ሊያገኙት እንደሚችሉ ጠቆምኳቸው።

«ያች የተረገመች ሴት ለኔ የምትሰጠኝ ነገር የለም» ሲሉ ፎውለር እየተጉተመተሙ ተናገሩ።

እኔም የማስጠንቀቂያ መልዕክት ማስራጪት እንዳለብኝ ታወቀኝ። ታላላቆቹ ነዳጅ አምራች ኩባንያዎች ከኢን.ኤስ.ሲ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው የሚያውቁ ብቸኛ ሰው ደግሞ ፎውለር ናቸው።

«ሚስተር ፎውለር ከታላላቆቹ ጋር ችግር ውስጥ ገብተዋል። ትልቁ ችግርም የአሞኮ ጉዳይ ይመስለኛል።»

ሆኖም ጉዳዩ እንደ ሮጀር ያለ ባልተፈቀደለት ክልል የሚያድን ሰርጎ ገብ አያሻውም። ከኃይት ሀውስ ቀዝቃዛ ምላሽ ይዞ የወጣውም ለዚያ ይመስለኛል።»

«በእርግጠኝነት ልክ ነህ። አሞኮ ውስጥ እየተደረገ ያለውን ደግሞም ኢን.ኤስ.ሲ. ውስጥ የአሞኮ ጉዳይ ተጠሪ የሆነችውን ሄስሊን ማንነቷን አሳምሬ አውቃለሁ።»

«ጥሩ እርሷ ደህና አድርጋ የረታችዎት ይመስለኛል።»

«እስቲ እናያለን።» ብለው የስልኩን እጀታ ጠረቀሙት።

✡✡✡

ነገሩ ከገንዘብ ወይም ፖለቲካዊ ሙስና ጋር ንክኪ ቢኖረውኗ ኖሮ ስለታላቁ የነዳጅ ዘይት ጉዳይ፣ ስለኃይት ሃውስ እና ስለ ኢን.ኤስ.ሲ ያለኝን መረጃ እረግፍ አድርጌ በተውኩትም ነበር። ተመራጭ ፖለቲከኞች ሁሌም ቢሆን አስጠሊ ገፅታ አላቸው አሁን የገጠመኝ እድልም እንደወትሮዬ ሁሉ አዲስ ድንጋይ ፈንቅዬ ከስሩ ተመሳሳይ ድንጋይ ማግኘትን ነው። አዲሱን ድንጋይ በፈነቀልኩ ቁጥር ከስር መውጣቱን ወይም መተውን የሚጠባበቅ የመጨረሻውን አስጠሊ ድንጋይ አገኛለሁ። ያን የማደርገው ግን ሁሌም ቢሆን ስበሳጭ ነው።

የታሪኩ መሰረት ኢራን በ1991 ያገተቻቸውን አሜሪካውያንን መልቀቋን ተከትሎ ኃይት ሃውስ ከሽብርተኝነት መዝገብ የሰረዛት መሆኑ ነው። በወርሃ ታህሳስ ግን ኢራን የወሰደችው እርምጃ ጠር ሜዳ የመቀየር ያህል የሚወሰድ መሆኑ ግልፅ ሆኗል። CIA በርካታ የሳውዲ ሂዝቦላህ መሪዎች ቴህራን መግባታቸውን የተመለከተ መረጃ ደርሶታል። ከመረጃው በመነሳትም ቴህራን ውስጥ የሆነ ሴራ እየተጎነጎነ መሆኑን መደምደም ይቻላል። የቴህራኑ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስብሰባ ውጤትም የኢራኑ ፓሳድራን ለሳውዲ የሂዝቦላ አሸባሪ ካድሬዎች ማሰልጠኛ ካምፕ ቢካ ውስጥ መከፈቱ ሆኗል። አሸባሪዎቹ የሃሰተኛ መታወቂያ ተሰርቶላቸዋል። የሚያስፈልጋቸውን ሙሉ የገንዘብ ድጋፍም ተደርጉላቸዋል። በወርሃ ሐምሌ 1995 በኢራን የሰለጠነው የአሸባሪዎቹ ቡድን ጅዳ ውስጥ ያለውን የቆንስላ ቢሮ ጨምሮ በሳውዲ ውስጥ ያሉትን የአሜሪካ ተቋማት በዓይነ ቁራኛ መከታተል ጀምሯል። ነዋሪነቱን ከኢራን ከተሞች ሁሉ ቅዱስ በሆነችው ኮም ያደረገው አንድ የሃይማኖት መሪ በሳውዲ አረብያ ላይ ጥቃት እንዲከፈት ማወጁም ኃይት ሃውስ መዓኢውን የከፋ አደጋ ለመጋፈጥ ራሱን እንዲያዘጋጅ አድርጉታል። የመጀመሪያው ጥቃት የተከፈተው በህዳር ወር 1995 ሪያድ በሚገኘው የብሄራዊ ዘብ ጦር ሰፈር ላይ ሲሆን በጥቃቱም አምስት አሜሪካውያን ተገድለዋል። ሰኔ 25,1996 በከባር ጦር ሰፈሮች ላይ የተከፈተው ጥቃትም 19 አሜሪካውያንን ለሞት ደርጓል።

ቢንላደን ከኢራን ጋር የፈፀማቸው ቀጥተኛ ያልሆኑ የመጀመሪያ ግንኙነቶች CIA ውስጥ መደናገጥን ፈጥረዋል፡፡ በግብፅ ከሚገኙ የቢንላደን አጋሮች አንደኛው በወርሃ ታህሳስ 1995 ቴህራንን በመጎብኘት ከአያሌ የሃገሪቱ መረጃና ደህንነት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ባለስልጣናት ጋር ተገናኝቷል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ ቢንላደን ከኢራን መንግስት ጋር የጦር ስምምነት ስለመፈፀሙ እረግጠኛ ባትሆንም በመረጃው ማህበረሰብ ውስጥ የምንገኝ ሰራተኞች ያን በተመለከተ እርግጠኞች ሆነናል፡፡ ቢንላደን ኢራን ያላትን የካበተ የአሸባሪነት ችሎታ ጥገኛ መሆንን አጥብቆ ሽቶታል በወርሃ ሐምሌ 1996 አፍጋኒስታን ውስጥ አንድን የኢራን የመረጃ ባለስልጣን አግኝቶ በጦር ስምምነቱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ መወያየቱ ፍራቻችንን የበለጠ አጠናከሮታል፡፡ ሁኔታው አሜሪካንን ኢላማው ያደረገ የአሸባሪዎች ሽርክና ማንሰራራት ስለመጀመሩ ግልፅ ስላደረገልን ችላ የምንለው ነገር አልነበረም፡፡

እኔም በጊዜው የቡድን መሪ የነበርኩ በመሆኔ ቡድኔን የፈለግኩትን እንደፈፅም የማዘዝ ስልጣኑ ነበረኝ፡፡ ከዚህ እንፃርም በካስፒይንና ማዕከላዊ እስያ የሚገኙትን ቢሮዎችን የኢራንን ኢላማ በትኩረት እንዲከታተሉ አድርጌአለሁኝ፡፡ በ1996 መግቢያ ከፓሳድራን ጦር ሰፈር አንደኛዉ ውስጥ በድብቅ የድምፅ መቅጃ መሳሪያ ለማስቀመጥ አሰበን ነበር ምክንያቱም በወቅቱ ፓሳድራን ካስፒይን ውስጥ ለመስራት ስለወጠነው ውጥን ባናውቅም ከሳኡድ አረቢያ በተጨማሪ ሶስተኛ ግንባር የመክፈት እቅድ ሊኖረው እንደሚችል ገምተናልና፡፡ በመሆኑም ከስፍራው የምናገኘው ማንኛውም መረጃ ጠቃሚ እንደሚሆን አምነንበታል፡፡

የተለመደውን አሰራር ዘዴ በመከተል እና በእቅዳችን መግፋት የሚያስችለንን ፍቃድ ለማግኘት በሚል ለሼይላ ሄስሲን ደወልኩላት፡፡ ለሼይላ ያቀድነውን የእቅዳችንን ውጤት እና ውጤቱ በአካባቢው የዩናይትድ ስቴትስን ጥቅም እንደምን ማስከበር እንደሚችል አብራራሁላት፡፡ ይሁንና ወዲያውኑ በቴሌፎኑ የወዲያኛው ጫፍ ቀዝቀዝ ያለ አየር ሲነፍስ ተሰማኝ፡፡

ከሃያ ያነሱ ደቂቃዎች እንዳለፉ ጥብቅ መረጃዎችን የምንለዋወጥበት አረንጓዴ ስልኬ አቃጨለ፡፡ ስልኩንም እንዳነሳሁት ከወዲያኛው የስልኩ ጫፍ የራንድ ቢያርስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ድምፅ ተሰማኝ፡፡ «ይኼ ፓስድራንና ያቀድኩት የድምፅ መቅዳት ዘመቻ የምትለን ነገር ምንድነው?» ሲልም ቢየርስ ጠየቀኝ፡፡

«እናስ ምን ችግር አለው?»

«ሂስሲንን የመልስ ምቱ አስጨንቋታል፡፡»

«ስጋቷ ኢራኖቹ አዘርባጃን ውስጥ ባሉት የአሞኮ ብሄር አባላት ላይ የብቀላ እርምጃ ይወስዳሉ የሚል ነበር፡፡»

ቢየርስ ሊነግረኝ የሞከረው የኤን.ኤስ.ሲን አሰራር ቢሆንም ሁኔታው አስቆጥቶኛል፡፡ «የአምኮውን የሂሳብ መዝገባችሁን ከኪሳራ ለመጠበቅ በአንድ ምናልባትም በሳኡድ አረቢያ ውስጥ ለተገደሉት አምስት አሜሪካውያን ተጠያቂ በሆነ አሸባሪ ቡድን ላይ ለመከፈት ያሰብነውን ዘመቻ እንድናቆመው እየነገርከን ይሆን!?»

«ደህና እኔ እንኳ ያንን የተናገርኩት በዛ መልኩ አልነበረም፡፡»

«መልካም ለምክር ቤቱ ደውዬ በአሞኮ ጉዳይ የኤን.ኤስ.ሲ. ተጠሪ የሆነችውን ሼይላ የአሞኮውን ትርፍን በማስሳት የኢራትን ፓሳድራን ኢላማ ያደረገ ዘመቻ እንዳናደርግ መከልከሏን እናገራለሁ፡፡»

እንደአንድ ጥሩ ቢሮክራት የዘመቻ ጉዳዮች ምክትል ኃላፊ ለሆኑት ዴቭ ኮህን ከቢየርስ ጋር የተነጋገርንበትን ጉዳይ ሪፖርት አደረግኩ፡፡ ለሪፖርቴ የተሰጠኝ ምላሽ ግን አልነበረም፡፡ ቢየርስ ግን በዛው እለት ደውሎ ኤን.ኤስ.ሲ. ሃሳቡን በመቀየር የደቡብ ቡድን ፓስድራንን ኢላማ ያደረገ ዘመቻ እንዲያካሂድ መፍቀዱን ነገረኝ በሌላ በኩል ግን ከአሜሪካ ምክር ቤት የተወከሉ አባላት ከኢራን ልዑክ ጋር በአንዳች ጉዳይ ላይ ኃይት ሃውስ ውስጥ በመምከር ላይ ነበሩ፡፡

ወቅቱ በስራው አለም ቆይታዬ ታላቅ ስፍራ የሚቸረው ወቅት እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ከኒያ ሁሉ ውስጣዊ የቢሮክራሲ ሹክቻዎችና በመረጃው ማህበረሰብ ውስጥ በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ ካደረግኳቸው ተጋድሎዎች በኃላ አንድ ድልን መጨበጥ ችዬአለሁ፡፡ ለጊዜውም ቢሆን በሽብርተኞች ላይ የተከፈተው ጦርነት የነዳጅ ዘይት ገንዘብን ለማካበት በተከፈተው ጦርነት ላይ ድልን ተጎናፅፏል፡፡ ሁሉም ነገር አታክቶኛል ቅድሚያ የምንሰጠው ለሰው ልጅ ደህንነት ቢሆን ኖሮ የፀረ ሽብር ዘመቻው እጅግ ባልከበደንም ነበር፡፡

«የአለም ፍፃሜ ሲል» ቲ.ኤስ ኢሊየት «ዘ ሆለው ሜን» በተሰኘ መፅሃፉ ውስጥ ፅፏል «በሆታ ሳይሆን በዋይታ ይሆናል፡፡»

✡✡✡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሮጀር ታማራዝ ድንገት እንዳገኘሁት ሁሉ ድንገት ተሰወረብኝ ታህሳስ 7 ቢል ሎፍግረንን አግኝቶ ጉዳዩን ከነገረው በኋላ ደውሎልኝ አያውቅም ለበርካታ ጊዜያት አግኝቼው በነበረበት 1996 ዓ.ም ከእርሱ ጋር ግትርነት የተንፀባረቀባቸው ግን ስርዓትን የጠበቁ ውይይቶችን አድርጌያሁ ስለዘመቻው መዋጮ ጉዳይም ሆነ ሮጀር የየልሲንን ዘመቻ ለመደጎም ስላለው እቅድ የተነጋገርነው ነገር አልነበረም፡፡ ኋላ ላይ ግን እርሱን እያሳደድኩት መሆኔን መስማቱ ግልፅ ሆኖልኛል፡፡ በሃሳቡም ሌላ ራዕይ የሌለው ቢሮክራት ሊለኝ እንደሚችልም ገብቶኛል፡፡

ሎፍግረን ሮጀርን ለመጀመሪያ ጊዜ ካገኘሁበት ግንቦት ወር እስከ ታህሳስ 7 ሮጀር የነገረኝን ነገሮች በዝርዝር በወረቀት ላይ እንዳሰፍራቸው አዘዘኝ ከኃይት ሃውሱ የዋጋ ዝርዝር እስከ ፎውለር የስልክ ጥሪ የተነገረኝን አንድ በአንድ ወረቀት ላይ አሰፈርኩት፡፡ ታማራዝ ያደረገውን የሚላኑን ስብሰባ እና በ1996 ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ላይ የሩሲያን ገንዘብ ፈሰስ ለማድረግ መተላለፊያ ሆኖ አገልግሏል በሚል ስላለው ጥርጣሬ በመፃፍ አንድ ገፅ ሙሉ ወረቀት ፈጀሁ፡፡ ይሁንና የፃፍኩት ማስታወሻ የደቡብ ቡድን ታህሳስ 8/1995 ያደረገውን የስራ ክንውን ያካተተ አልነበረም፡፡ ክንውኑን የተመለከተ ማስታወሻ ግን በቡድኑ ቅደም ተከተል ምስጢራዊ መዝገብ ውስጥ ተቀምጦ ስለነበርና እኔም ከሁለት አመት በሁዋላ ክንውኑን የዳሰሰ ሪፓርት በአንድ የአሪሜካ ጋዜጣ እስካነበብኩት ዕለት ድረስ ጳግም ስለርሱ አልሰማሁም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፱

## መጋቢት 1997 ፤ ዋሽንግተን - ዲሲ

በ1997 ወርሃ መጋቢት አሁን በጡረታ ከስራው ለተገለለው ቢል ሎፍግረን ደውዬ ኃይት ሃውስ ውስጥ እየተካሄደ ስላለው ነገር በቂ መረጃ እንዳለኝና የማንቂያ ደውል ለማስማት በመዘጋጀት ላይ መሆኔን ገለፅኩለት፡፡ ይሁንና ቢል ወዲያውኑ ምላሽ አልሰጠኝም፡፡ በፀጥታ ተውጦ ያልኩትን ባደርገው የሚያስከትለውን መዘዝ እያሰበ እንደሆነ ገምቼአለሁ፡፡

በመጨሻም «አድርገው» ሲል ጥርጣሬ ባልቀላቀለ ድምፀት ተናገረ፡፡ ቢል ነገሩን የተናገረው አቅልሎ አልነበረም፡፡ እንደኔው ሁሉ ተመሳሳይ በሆኑ ሁለት ወይም ሶስት የመረጃ ምንጮች ላይ እምነቱን የሚጥል ነዋሪ ባላት ዋሽንግተን ውስጥ የማንቂያ ደውል ማሰማት የሚጀምር ሰው ተወዳጅነት እንደማያተርፍ ያውቃል፡፡ ለምንስ ሰው ቀልቡ ወደ እውነታው እንዲሳብ በማድረግ ራስን ለአደጋ የጋልጣል፡፡

በእርግጥ ቢል ደውሉን ከማስማት እንድቆጠብ የሚፈልግበት ግላዊ ምክንያት ነበረው፡፡ ከCIA በጡረታ ከተገለለ በኋላ ባህር ማዶ የቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ጉዳዮች አማካሪ ሆኖ ተሹሟል። በጊዜው ለመጀመሪያ ጊዜ ደውሶ ያገኘው ባለጉዳይ ሮጀር ታምራዝን የነበር ሲሆን የደወለውም አዘርባጃን ውስጥ ለገጠመው ችግር የቢልን መፍትሄ በመሻት ነበር። ቢል ከሮጀር ጋር የፈፀመው አነስተኛ ውል ቢያንስ ከጅምሩ የስልክ ወጪውን መሸፈን አስችሎታል። በእኛ ተፈላጊ ከሆነ አንድ ግለሰብ ጋር እንዲሰራ ጥያቄ ስናቀርብለትም የገባበት ጥልፍልፍ የቅኝት መረብ መኖሩን ነግሮናል። የሴናተር ኬኔዲ ሚስት ለታማራዝ የሚሰሩ ከሁኑ ለእርሱ እንዲያ ማድረጉ ለምን አይቻለውም? ኒውዮርክ ውስጥ የተከበረውን የክሊንተን 50ኛ አመት የልደት በዓል አብዛኛው ወጪ የሸፈነው ኃይት ሃውስ ውስጥ ከተከፈተው የነፃነት ቀን አውደ ርዕይ ላይ የተገኘው ታማራዝ አልነበረምን? የሚሉ ጥያቄዎችን አቅርቦልናል። ሮጀር ዳግም የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝደንት ወዳጅ የመሆን ሃሳቡን በበቂ መልኩ እስከገፋበት ድረስ ሎፍግረን ለእርሱ ጥቂት የማይታመንበት ምክንያት መኖሩ አልታየውም።

የማንቂያ ደውሉን ለማሰማት መወሰኑን የሚከ፡ድ ነገር ሆኖ አግኝቼዋለሁ ደውሉን የሚያስማ ሰው ማግኘቱ ከነጭራሹ የማይቻል ሲሆን እንደሚችል ተረድቼአለሁ ቀጥሎም አሳባማ ውስጥ ራሳቸውን ከዴሞክራትነት ወደሪፐብሊካንነት ወደቀየሩት ሴናተር ሪቻርድ ሼልቢ ቢሮ ደወልኩ በመረጃ ጉዳዮች ላይ የሚሰራውና ከሴኔቱ የተመረጠው ኮሚቴ (ኤስ.ኤስ.ሲ.አይ) አባል የሆኑት ሼልቢ ብሄራዊው የደህንነት ሸንጐን (ኤን.ኤስ.ሲ) ለክሊንተን



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘመቻ የገንዘብ መዋጮ የፈፀሙ ሰዎችን ዝርዝር እንዲሰጣቸው በመጠየቅ በጉዳዩ ላይ ጥይት የተኮሱ የመጀመሪያው ሰው ሆነዋል። ለዚሁ ጉዳይ ሼልቢ ማግኘት የሚችሉትን ዕርዳታ ሁሉ የሚቀበሉ ቢመስለኝም ግምቴ ትክክል አልነበረም።

ወደ ሼልቢ ቢሮ ያደረኩትም የስልክ ጥሪ ምላሽ ሲያገኝ ባለመቻሉ የመረጃ ኮሚቴ ምክር ቤት ሰብሳቢ ለሆኑት ጆን ሚሊስ ደውዬ ለሼልቢ መልዕክቴን ልተውላቸው ወሰንኩ። ሚሊስ ቀደም ሲል CIA ውስጥ በመረጃ መርማሪነት ካገለገሉ በኋላ ወደምክር ቤቱ ተዛውረው በመስራት ላይ የሚገኙ ሲሆን ሰውየው ምንም እንኳን ከፍተኛ የፓለቲካ ሃላፊነት ቢኖርባቸውም ጥንቁቅ እና በፅናት ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ሰው ሆነው አግኝቼአቸዋለሁ። ያ ባይሆን ኖሮ ወደ CIA የገባሁበትን በር ክፍት ባላረጉልኝም ነበር፡፡

ሚሊስ ታሪኩን ነግሬአቸው እንደጨረስኩ ከትብለው ሳቁና እያደረግክ ያለው ምን እንደሆነ ይታወቅሃል?» አሉኝ፡፡

ስለተጠርጣሪዎቹ እና ታማራዝ ከፕሬዝዳንቱ ጋር ስለፈጠረው ግንኙነት ነገርኳቸው፡፡

«ጎመን በጤና ብለህ እርፋህ አትቀመጥም ዋ! ሰዎቹ ያሳድድሁና መጨረሻህም እዚህ ከተማ ውስጥ መገለል ይሆናል፡፡ የሆኖ ሆኖ መልዕክትህን ለሼልቢ አደርስልሃለሁ፡፡» ብለው በመናገር ሚልስ ስልኩን ዘጉት፡፡

ሚሊስ መልዕክቱን ያድርሱልኝ አያድርሱልኝ ባላውቅም ከሼልቢ ያገኘሁት ምላሽ ግን አልነበረም፡፡ ስለዚህ የዘመቻውን መዋጮ ጉዳይ በመመርመር ላይ ወዳለው ፍትህ ሚኒስቴር ደውዬ መስሪያ ቤቱም ድረስ በመሄድ በጉዳዩ ዙሪያ ያለኝን መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ መሆኔን ገለፅኩ፡፡ ያደረኩትንም ለእስቃዬ ማሳወቄም የሳንግሌይ ቢሮ የሚገኝበት ሰባተኛ ፎቅ ሁሉ ያስተጋባ የማስጠንቀቂያ ደውል የደወለ ክስተት ሆነ፡፡ የካውንስሉ ቢሮም ለፍትህ ሚኒስቴር ደውሎ የያዝኩትን ቀጠሮ እንዲሰርዙብኝ ማሳሰቢያ አስተላለፈ፡፡ ለፍትሕ ሚኒስቴር የተነገረው ምክንያትም «እናዝናለን ሰውየው (ቢየር) ገደቡን አልፎአል፡፡ የሚል ነበር፡፡ ለኔም ጉዳዩን በተመለከተ CIA የራሱን ማጣራት እንደሚያደርግና መረጃዎች ተጠናክረው እንዳበቁ ፍርድ ቤት እንዲያየው እንደሚደረግ ተነግሮኛል።

በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ሃሳቡ ጥሩ ይመስላል። ከምክር ቤቱ እና የህትመት ሚዲያው አስቀድሞ ያአጠያያቂውን የዘመቻ መዋጮ የተመለከተ መረጃ CIA ደርሶታል CIA የመዋጮ ስረ መሰረትን በመመርመር በሃገሪቷ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት የተመለከቱ መረጃዎች ሊያጠናክር ቢሰነብትም መረጃዎቹ ደብዛቸው እየጠፋ ተቸግሯል።

ሌላው ደግሞ የላሪ ዋላስ ጉዳይም ከዚሁ ጋር ተያያዥ የሚነሳ ሲሆን ይህ ሰው የቀድሞው ኃይት ሃውስ ኃላፊ ማክ ማክላርቲ የቆየ የንግድ ሸሪክ የሆነው ዋላስ ቀን ላይ ወደኃይት ሃውስ መግባት የሚያስችለውና የፕሬዚዳንቱ የውጭ ጉዳዮች ተወካይ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ያለው ሰው ነበር። ፡ ለማክላርቲ ምስጋና ይግባውና ሰውየው ባሻው ጊዜ ወደኃይት ሃውስ ይገባል ይወጣል። ዋላስ ደብዳቤውን ያሲን አረፋትን ጨምሮ ከሌሎች ባህር



t.me/OLDBOOKSPDF

ማዶ ካሉ እውቅ ግለሰቦች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ተጠቅሞበታል። ቤልግሬድ ውስጥ ለስሎቦዳን ሚሎሶቪች የደብዳቤውን ቅጂ በመስጠቱ ግን ትልቅ ስህተት ፈፅሟል ወዲያውኑ ግን እዚያው የሚገኘው ቢሮአችን ቅጂውን እጁ በማስገባቱና ወደ ጠቅላይ መምሪያውም በፋክስ በማስተላለፉ ምክንያት ጠቅላይ መምሪያው በመሃከለኛው አውሮፓ የሚገኘውን ምድብ መስሪያ ቤታችንን በዋላስ ላይ ፋይል እንዲከፍት አዞታል።

CIA አሜሪካውያን ሰላዮች መሆናቸውን ወይም ከጠላት ጋር መወገናቸውን የሚገልፅ ጠንካራ መረጃ ከደረሰው እነሱን የተመለከቱ መረጃዎች ማሳባሰብ ይችላል። ይሁንና የሚገርመው ነገር ቢኖር የዋላስ ፋይል ለምክር ቤቱ እና ለፍትሕ ሚኒስቴር መርማሪዎች ከመድረሱ በፊት ተሰውሯል።

የቻይና ወታደራዊ መረጃ መስሪያ ቤት አባል የሆነው ኮሎኔል ሊዮ ቻኦ ዩንግ ጉዳይም መነሳት ያለበት ነገር ነው።

ጆኒ ቻንግ ለክሊንተን ዘመቻ መዋጮ ያዋለውንና ብዙ የተባለለትን 300,000 ዶላር ሊዩ ሰጥታዋለች። ቻንግ ሌላ ነገር እስቦ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ የተጠረጠረበትን ከተሰጠው ውስጥ 20,000 ዶላሩን ብቻ ለዲ.ኤን.ሲ ሰጥቷል። ይህ እየተካሄደ ባለበት ጊዜ አንድ የመረጃ ሰራተኞችን ከሊዮ ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ግን ሳይታወቅ ቀርቷል CIA ስለሴትየዋ ለፍትህ ሚኒስቴር ሳያሳውቅ መቅረቱም ድረጅቱን አሳፋሪ አድርጉታል።

በእውነቱ የመረጃው ሰራተኞችን በጠቅላይ መምሪያው አነስተኛ የስልጣን እርከን ላይ ያሉ ሰራተኞች ስለሊዩ ከኃላፊዎቹ የተሻለ እንደሚያውቁ ደርሰበታል። ሴትየዋ ቻንግ ኃይት ሃውስ እንዲገባ ያደረገውን ጉዳይ ከሚገልፀው ደብዳቤ ላይ የፕሬዚዳንቱ ማህተም አርፎበት በማየቷ ስውየው ኃይት ሀውስ ውስጥ ቀጠሮ እንደነበረው የሚጠይቅ ቴሌግራም ለጠቅላይ መምሪያው ብታስተላልፍም ኃላፊዎቹ የሰጧት ምላሽ አልነበረም። ጠቅላይ መመሪያው ሊዩ ከኢራን ጋር በአብዛኛው አሜሪካ ሰራሽ የሆኑ ጦር መሣሪያዎችን በነዳጅ ዘይት ለመገበያየት በሚስጥር ይደራደር ከነበረውና የቻይና ብሄራዊ የአውሮፕላን መሳሪያዎች አስመጪና ላኪ ከተሰኘው ኩባንያ ጋር ስላላት ግንኙነት አልተጨነቀበትም።

CIA የታማራዝን መረጃ በሂደት ፍትህ ሚኒስቴር ላዋቀረው መርማሪ ኮሚቴ ቢያስተላልፍም ኮሚቴው የጉዳዩን ምስጢርነት ለመጠበቅ አጥብቆ ይሻ ነበር። ይሁንና የሆነ ሰው የሮጀር ታማራዝ ጉዳይን የዎል ስትሪት መፅሔት ዘጋቢ የሆነው ሚካኤል ፍሪስቢይ እንዲሰማው አድርጉታል።

ቬልቢ.ታዲያ የፍሪስቢይን ዘገባ ካነበቡ በኃላ እኔን ለማግኘት ቀጠሮ ያዙ። CIA'ም በአንድ ሽፍን የጭነት ካሚዮን የኤሰ.ኤስ.ሲ.አይ ቢሮዎች ወደሚገኙበትና ከታችኛው ከተማ ወዳለው የሃርት ኦፊስ ህንፃ ላከኝ። እናም ታዲያ በስብሰባው ላይ የተገኘነው ስድስት ሰዎች ነበርን። በስተግራዬ ሼልቢ. እና ረዳታቸው ተቀምጠዋል። የCIA'ው ጀነራል ካውንስል የሆኑት ማይክ አኔይል እና የምክር ቤት ጉዳዮች ሃላፊው ጆን ሞስማን ከጠረጴዛው ባሻገር ያሉትን ወንበሮች ይዘዋል፡፡ እንደጠረጠርኩትም ሴናተን ቦብ ኬሪ በስብሰባው ላይ አልተገኙም፡፡ በቬየትናም ጦርነት የተሳተፉት የቀድሞ ወታደር ኬሪ ወኔያም ብቻ ሳይሆን በዋሽንግተን ያሉ የፓለቲካ ቅንጣቶች እነደምን እንደሚቀያየሩ በቂ መረዳት ያላቸው ብስል ሰው



t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው፡፡ ይሁንና በእርሳቸው ፋንታ የኤስ.ኤስ.ሲ.አይ ባልደረባ የሆነውን ክሪስ ስትራውብን ማየቱ አስደስቶኛል፡፡ ስትራውብ እኔና ሌላ የምክር ቤቱ ባልደረባ ለሦስት ቀናት ሰሜናዊ ኢራቅን ተዘዋውረ በመጎብኘት CIA በስፍራው ለመስራት እየሞከረው ስለነበረው ነገር ከዚህ በፊት ተነጋግረን እንደነበር አስታውሳለሁ። ሰውየውን እወደዋለሁ። እርሱም እምነቱን ሊጥልብኝ እንደሚችል እገምታለሁ።

ስለብሰባው የነበረኝ ተስፋ ምንይሁን ምን ስሌላ አላማ የታቀደ መሆኑን እንደተረዳሁ የነበረኝ ተስፋ በአንዴ ሲመክን ችሏል። CIA እንደፍትህ ሚኒስቴሩ ኮሚቴ ሁሉ ሼልቢ ማየት አለባቸው ያለውን መረጃ አሳይቷቸዋል። ሼልቢ ግን ሌላው ቀርቶ ታማራዝ የሩሲያን ገንዘብ ወደ ዲ.ኤን.ሲ አራግፎ ይሆናል የሚለውን ወሬ አልሰሙም ወይንም ቢሰሙም የጉዳዩ አሳሳቢነት ሊያስጨንቃቸው እንደሚችል እርግጠኛ አይደለሁም። ስብሰባውን ሊጠቀሙበት የፈለጉት የቶኒ ሌክን የ CIA ዳይሬክተር ሆኖ መሾም ለመቃወም ነበር ለተቃውሟቸውም ሌክ ኢራን በቦስኒያ ውስጥ እጇን እንድታስገባ ፍንጭ መስጠቱን በምክንያትነት አልጠቀሱም።

ሴናተሩ ያመጣሁትን መረጃ መስማት ፈለጉም አልፈለጉ ማውራት ነበረብኝና ውይይቱ ቆም ብሎበት በነበረበት አፍታም ሼልቢይን «ሴናተር ሮጀር ኃይት ሃውስ እንዴት ይገባ እንደነበር ያውቃሉ? እዚያ ይገባ የነበረው በሴናተር ኬኔዲ በኩል ነበር፡፡»

«ጌታው እዚህ የተገኘነው ስለተከበረው ወዳጄ ለማውራት አይደለም፡፡» ሲሉ ሼልቢ ከጋመትኩት በላይ ፈጥነው ምላሽ በመስጠት አቋረጡኝ።

በቁጣም ስብሰባው መቋጨቱን ተናገሩ። ሌክን በመቃወም ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን በቂ መረጃዎች በማግኘታቸው የእኔውን ታላቁን የነዳጅ ዘይት ለዘመቻ መዋጮ እና የወንዳጆቻቸውን ግብረገባዊነት የተመለከቱ መረጃዎች የሚያደምጡበት ጆሮ አልነበራቸውም።

ወደ ደጅ ስንወጣና ያሉኝን ተጨማሪ መረጃዎች መናገሬን ለማቆም ስዘጋጅ ስትራውብ ወደአንድ ጉኑ ጐተት አድርጉኝ «ችግሩ ምንድነው?» ሲል ጠየቀኝ፡፡

ብዙ ችግር አለ ከሚያደምጠኝ ኮሚቴ ፊት ካቆምከኝ ሁሉንም ዘርዝሬ እናገረዋለሁ፡፡»

ስለአሞኮ እና ለኢራት ፓስድራን ብስጭት መንስኤ ስለሆነው የሂስሊን ቅዋሜ አጫወትኩት፡፡

«ጉዳዩ ያን ያህል የከፋ ነውን»

«አዎን ክሪስ የከፋ ይመስለኛል፡፡»



t.me/OLDBOOKSPDF

ያንዕለት ከሰዓት በኋላ ስትራውብ ከኬሪ ጋር በጉዳዩ ዙሪያ መከረበት፡፡ ቀጥሎ በመጣው ቅዳሜም ኬሪ ለፕሬዝዳንት ክሊንተን ደውለው የሌክን የ CIA ዳይሬክተር ሆኖ መሾም ከዛንጊዜ አንስቶ እንደማይደግፉት አሳወቁ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ሌክ ስልጣኑን በራሱ ፈቃድ ለቀቀ ያ ድል የተጐናፀፍኩበት ጊዜ ቢሆንም ድሉን የማከብርበት ጊዜ አልነበረኝም፡፡

☆☆☆

መልዕክታቸው በCIA ተቀባይነት ያላገኘ የመረጃ ሰራተኞች የሚጣልባቸውን ቅጣት ለማሳየት ኬጂቢን የከዳው ዩሪ ኖሴንኮ የደረሰበትን መጥቀሱ በቂ ነው፡፡ ኖሴንኮ በሊ ሃርቬይ ጉዳይ እና በኬኔዲ ግድያ ላይ ያቀረበው መረጃ ድርጅቱ ከነበረው መረጃ ጋር የሚጣረስ ሆኖ በመገኘቱ በትልቁ እርሻ ውስጥ ለሶስት አመታት ተገሎ እንዲኖር ተፈርዶበታል፡፡ እናም ለኔ የተለየ አስተያየት የሚደረግበት ምንም ምክንያት ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡

እንደታዘዝኩት መጋቢት 18/1997 ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ከ CIA ምርመራ ቢሮ ቀረብኩ ወዲያውም አንደ መስኮት የለሽ ክፍል ውስጥ እንደገባ ተደረግኩ፡፡ እዚያም ሁለቱ ሰዎች ፊት ካለው ጥቁር ቡኒ የውይይት ጠረጴዛ ባሻገር ቆምኩ ሰዎቹም ቅጭም ያለ የገረጣ ፊት ያላቸው ሲሆን አንድ አይነት ሙሉ ልብስ ለብሰው መንትዮች መስለዋል፡፡ ደግሞም ሁለቱም ስማቸውን ሳያስተዋውቁኝ ፊታቸው እንደ ጅብራ ተገተርኩ፡፡

ከመቀመጤ በፊትም ከሁለቱ አንዱ አስቀያሚ ገፅታን የተላበሰው የመጀመሪያዋን ጥይት ተኮሰ፡፡ «ያወደምከውን ሰነድ ግልባጭ አስቀምጠሃል?» አለኝ፡፡

የጣውላው ወንበር ላይ እየተቀመጥኩ ሳለ ምላሽ አልሰጠሁትም፡፡ የታወቀ ሰነድን ማውደም ከወንጀልም የከፋ ወንጀል ነው፡፡ ብዙም ሳይቆይ ሰዎቹ ለቢል ሎፍግሪን ጥያቄ ያዘጋጀሁትንና ከሮጀር ታማራዝ ጋር ያሳለፍኳትን እያንዳንዷን ጊዜ የሚዳስሰውን የታህሳስ 28 ቱ ማስታወሻዬን የተመለከቱ ጥያቄዎች አጎረፉልኝ፡፡

በመጨረሻም እስቲ ልብ በሉት» ስል ምላሽ ሰጠሁ፡፡ «ራሴ ያዘጋጀሁትን የአንድን ሰው ወንጀል የሚዘረዝር ሃተታ በፋይል አድርጌ አለም ሁሉ እንዲያየው በየአቅጣጫው ከላኩት በኋላ ማውደሜ የሚያስኬድ ነገር ነው ትላላችሁን?? የሆነ ሆኖ ፓውል ሬድሞንድን ፋይሉ በመጨረሻ እንደምን ካቢኔቱ ውስጥ እንደገባ ልትጠይቁት ትችላላችሁ፡፡ ፋይሉን እንዳላወደምኩት ማስረጃው ያ ነው፡፡»

እንደእውነቱ ከሆነ ፋይሉ ከፀረ-ስለላ ተቋሙ ምክትል ሃላፊ ካቢኔት እንዴት እንደገባ ባላውቅም እዛ መኖሩን ማወቁ ብቻ የCIA ውሳኔ ሰጭ ሰዎችን ከለላ ማግኘት



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚያስችለኝ ተረድቼአለሁ። መርማሪዎቹ የነገርኳቸውን ከቁብ የቆጠሩት አይመስሉም። እናም ከመንትዮቹ አንዱ «የታህሳስ 28ቱን ማስታወሻ ለምን እንዳወደምከው ብቻ ንገረን» ሲል ተናገረ። ቀስል አድርገህ ልትጀምርልን ትችላለህ።»

ከአንድ ሰዓት በኃላ ጠያቂዎቹ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ደጋግመው መጠየቃቸው ታክቷቸዋል። «የጥቅምቱን ማስታወሻ እንድታስወግድለት ታማራዝ ምን ያህል ከፈለህ?» ሲል አንደኛው ሰውዬ ጠየቀኝ።

ማስታወሻውን ያስወገደው የጠቅላላ ካውንስሉ ቢሮ እንጂ እኔ አለመሆኔን ብነግራቸውም ሊሰሙኝ አልቻሉም።

ለጥቆም ጥያቄው ሌላ አቅጣጫ ያዘ። «ሺይላ ሄስሊን የታማራዝን ስም ከምስጢር ድርጅቱ ጥቁር መዝገብ እንድትፍቀው ለምን አሳመንካት?»

ጥያቄው አናደደኝ «ያልከው ሃሰት ነው። በኔ ቦታ ያለ ሰራተኛ ድንበሩን ጥሶ እንዴት የኤን.ኤስ.ሲ ባለስልጣን ማድረግ ያለባትን ሊነግራት አይችልም።» በሃሳቤም ሄስሊን እንዲያ ብላ ነግራቸው ከሆነ አሳልፋ ሰጥታኛለች ማለት ነው።

«እንደዛ አላለችም።» ሲል አንደኛው ሰውዬ መልሶ ተናገረ። «ያለችው የታማራዝን ስም ከኃይት ሃውስ ጥቁር መዝገብ እንድፍቅለት ጫና አሳድሮብኛል ነው። ጉዳዩን በተመለከተ በደርዘን የሚቆጠሩ የስልክ ጥሪዎችን በማድረግ አስፈራርተሃታል።»

ከ6 ወራት በፊት ለአንድ አዞ መልዕክተኛ ጆርጅታውን ከሚገኘው የላ ሻውሚየር ሬስቶራንት ያደረግኩትን የራት ግብዣ ልነግራቸው አሰቤ ነበር በግብዣው ላይ ሄስሊንን ጨምሮ በርካታ የመንግስት ባለስልጣናት ተገኝተው ነበር። እናም ግብዣውን እንዳደርግ ጉትጉታ ያሳመነችኝ ራሷ ሄስሊን ስትሆን በመጨረሻም በጥያቄዋ መሰረት ወደ ቤቷ በመኪናዬ ሸኘቼአታለሁ። እርሷን ማስፈራራት ካለብኝ ላስፈራራት የምችለው ያኔ ነበር። ይህን ለመናገር ባስብም አዲሶቹ ወዳጆቼ ነገሩ ላይስባቸው እንደሚችል አውቄአለሁ። ስለዚህም ድል እንደሚያጉናፅፈኝ ያመንኩበትን የመጨረሻ ካርታ ሳብኩ የሄስሊን የኃይት ሃውስ ውስጥ ለውስጥ ኢ-ሜይሎችን ጉዳይ ሄስሊን ሃቁን መሳቷን ለማወቅ ከኢሜይሎቹ ጥቂቱን ማንበብ ይበቃል አልኩ።

«የሄስሊንን ኢ-ሜይሎች ተመልከቷቸው» በማለት የኢሜይሎቹን ቅጂዎች ሰጠኃቸው። «CIA እስምን መርታት ግቡ ካደረገው ሴራ ጀርባ ያለ ድርጅት መሆኑ ታምናለች።»



t.me/OLDBOOKSPDF

እነርሱ ግን ኢ-ሜይሎቹን የማየት ፍላጎት አልነበራቸውም እናም አንደኛው መርማሪዬ «እየመረመርን ያለነው አንተን እንጂ ሄስሲንን አይደለም» ሲል አንባረቀ።

«የሆነ ሆኖ» ስል ጥያቄዬን አቀረብኩላቸው። «ለCIA መስራት ከጀመራችሁ ምን ያህል ጊዜ ሆናችሁ?» የCIA ሰራተኝነታቸውን የሚገልፅ ሰማያዊ ባጅ ደረታቸው ላይ ቢያንጠለጥሉም የሆነ ነገራቸው ትክክል መስሎ አልታየኝምና።

ሰዎቹ ተያይተው ራሶቻቸውን ከፍ ዝቅ አደረጉ። የመጡበትን ከመናገር ውጪ ምርጫ አልነበራቸውምና። «የመጣነው ከምስጢር ድርጅቱ ነው።» አሉኝ።

ይገርማል ስል በሃሳቤ ተናገርኩ። ሁለት የውጭ ሰዎች የCIA'ን የውስጥ ምርመራን የመመርመር ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል ይገርማል! CIA የውስጥ አደረጃጀቱ ምን ያህል እንደወረደና ቅጥ እንዳጣ ለመገንዘብ ጊዜ አልፈጀብኝም።

☼☼☼

በማግስቱም ስድስት ወንዶች እና እስከአንገቱ ድረስ የተቆለፈ ቀሚስ ያጠለቀች አንዲት ሴት ሮምን እንደወረሯት ኦስትሮጎቶች ሁሉ ከደቡባዊ ቡድኑ ቢሮ ተሰገሰጉ። ማንም ሰው ከቢሮው እንዳይወጣ ካደረጉ በኋላ ካቢኔቶቹን መበርበር ፋይሎቹን መገነጣጠል እና ወለሉ ላይ መበታተን ጀመሩ። ቢሮውንም በአውሎንፋስ የተመታ አስመሰሉት።

ብዙም ሳይቆይ በሩን ቆልፋው ለሰራተኞቹ ጥያቄዎችን ያቀርቡላቸው ጀመር ለሁሉም ሰራተኞች የቀረበላቸው የመጀመሪያ ጥያቄ «ጠበቃ አላችሁ?» ከሌላቹህ ልትገዙ ይገባችኃል የሚል ነበር። ነገሩ ለማስፈራራት ተብሎ የተደረገ መሆኑ ግልፅ ነበር። ከመካከላቸውም በ1995 ከታማራዝ ጋር እንገናኝ በነበረበት ጊዜ አብረውኝ የሰሩት ሁለቱ ብቻ ናቸው። ሆኖም መልዕክታቸው ግልፅ ላይሆንላቸው ይችላል በማለት መርማሪዎቹ የዛንዕለት ከሰዓት በኋላ የሠራተኞቹን ኮምፒውተሮች ምርመራ አካሂደውባቸዋል። ይህ ግን ተራ ማስፈራሪያ አይደለም ይኸውም CIA ውስጥ አንድን ኮምፒውተር አላግባብ መጠቀም እንደሚየስረሽን የታወቀ ስለሆነ ነው። ብዙም ሳይቆይ ደቡባዊ ቡድኑ ውስጥ ብቻዬን ቀርቻለሁ። ሁሉም ሠራተኞቹ ሌላ ቦታ እንዲሰሩ ተመድበዋል።

በወርሃ ግንቦት አጋማሽ ደግሞ ተደጋጋሚ የህክምና ፈተና እንደወስድ ተደረግኩ። በመጨረሻም ግንቦት 30 ፈተናውን ማለፌን የሚገልፅ በኮምፒውተር የተጻፈ ወረቀት ቢሮ ጠረጴዛዬ ላይ ተቀምጦ ባገኘም ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደአውሮፓ ለመጓዝ ስሰናዳ አካላዊ «ችግር» እንዳለብኝ የሚገልፅ ማስታወሻ ደረሰኝ ማስታወሻውም የህክምና ባለሙያው ፎርማ ያላረፈበት ከመሆኑ ሌላ የህክምና ፈተና እንድወስድ ተነገረኝ። ችግር አለብህ የተባለው ተራ ቅጥፈት ሆኖ እያለ ደግም ተደጋጋሚ አካላዊ ምርመራ እንዳደርግ ታዘዝኩኝ። ያም ዳግሞ ሌላ ቅጥፈት የሚሆነው አንድም CIA አንድ ሰራተኛውን አካላዊ ምርመራ እንዲያደርግ የሚያደርገው ሰራተኛው ከባድ አደጋ ባለባቸው እንደሞስኮ እና ፔኪንግ ባሉ ቦታዎች ተመድቦ የሚሰራ ከሆነ በመሆኑ ነው። ከዚህ አንፃር አለቃዬ ሊያስተላልፍ የፈለገው ነገር እፌን ካልዘጋሁ መጨረሻዬ ከእብዶች መታጕሪያ መግባት እንደሚሆን የሚገልፅ መልዕክት መሆኑ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግልፅ ነበር። የሆነ ስባተኛው ፎቅ ላይ ያለ ሰውም ዩሪ ኖሴንኮ የታሰረባት ክፍል ስለመሰቀቁ በማሰብ ላይ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ።

✡✡✡

የክሊንተን የዘመቻ መዋጮ አሉባልታ ነፍስ ዘርቶ በችሎት እና በምክር ቤቱ ፊት ሊታይ ባለበት ሁኔታ ፍትህ ሚኒስቴር ያቋቋመው መርማሪ ቡድን እንደ CIA ሁሉ...

✡✡✡

ላውራ ኢንግሮስል የፍትህ ዲፓርትመንቱ ሀላፊ ስትሆን እኔ ከታምራዝ ጋር ስለነበረኝ ግንኙነት ነግሬያት ነበር። በዚህ መሠረትም ከታምራዝ ጋር የተያያዙ ዶክመንቶችንና ስለሠውዬው የሚታወቁ ነገሮችን መመርመሯን ቀጥላለች። ሆኖም ታምራዝን ወንጀለኛ ሊያስደርጉ የሚችሉ በሰው የተመዘገቡ የገንዘብ ደረሠኞች ሊገኙ አልቻሉም። ይህን የተረዳችው ኢንግሮስል የታምራዝ የገንዘብ ምንጭ የት ሊሆን ይችላል? ምናልባት ከራሺያው የስለላ ድርጅት KGB ይሆን? በሚል ከጠየቀች በኃላ ለጥያቄዋ መልስ ስትፈልግ የእርግጠኝነት ምልክት አሳየች፡፡

በዚህ ሁኔታ ከቀጠልን በኃላ ለኢንግሮስል የታምራዝ የገንዘብ ምንጭን ሊጠቁም የሚችል ሀሳብ ሳቀርብላት ልታዳምጠኝ አልፈለገችም፡፡ የታምራዝ መሠረት በKGB ዙሪያ ያጠነጥናል የሚለውን ሃሳቧን የምትተውም አትመስልም፡፡ ስለሁኔታው በዝርዝር ልነግራትና እውነቱን እንድታውቅ ለማድረግ ያደረኩት ጥረትም ዋጋ ሳይኖረው ቀረ፡፡ ታምራዝ ከኃይት ሃውስ ቤተመንግስት ጋር ስላለው የጠበቀ የመረጃና የሌሎች ጥቅማጥቅሞች ምንጭ የምታውቀው ነገር እንደሌላትም መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም ታምራዝ ከቴድ ኬኔዲ ባለቤትና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዋረን ክርስቶፈር ልጅ ስላለው የጠበቀ ወዳጅነት ያላት እውቀት አነስተኛ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ከአዮዋው ሴናተር ቶም ሃርኪን ጋር ስላላቸው የጥቅም ትስስር ኢንግሮስል እንግዳ ነበረች ብዬ ለማሠብ የምመለከታቸው ምልክቶች አስገድደውኝ ነበር፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ኢንግሮስል አንድ ያልተጠበቀ ጥያቄ ጠየቀችኝ፡፡ ጥያቄዋም «ታምራዝ አንድ ስራ አልሠጠህም ወይ?» የሚል ሲሆን የጥያቄዋን ምስጢራዊነት በሚያሳብቅ መልኩ ሁሉንም በክፍሉ ያሉትን ተሰብሳቢዎች ተመለከተቻቸው። ጥያቄውንም ሲመለከቱት ቀለል ያለ ቢመስልም ታምራዝ ፍላጎቱን ለሚያስፈፅምበት ሠዎች ጥሩ የገንዘብና የስራ ዕድል እንደሚሠጥ ስለሚታወቅ ጥያቄው ብዙ ነገሮችን ሊጠቁም የሚችል ነበር፡፡ ታምራዝ ሼላ ሂስሊንን ጨምሮ ለበርካታ ከኃይት ሃውስ መንግስት ጋር ቀጥተኛ የስራ ግንኙነት አላቸው ከሚባሉ ጠቃሚ ሰዎች የገንዘብና የስራ ድጎማ ይሠጣል የሚል ጭምጭምታም ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ኢንግሮስል ምንም እንኳን በታምራዝ የገንዘብ መቀበያና መስጫ ሰነድ ላይ እነማን እንዳሉ ልታውቅ ወይም ልትገምት ብትችልም እኔን ለማሳጣት ስለተናገረችው ነገር በዙሪያዋ ባሉት ሰዎች ዘንድ ከቁብ የተቆጠረ አይመስልም ነበር፡፡ ይህ ሁኔታም ነገሩን ዋጋቢስ እንዲሆን አደረገው፡፡ ይህም ማለት እንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ሲድበሰበስ ለታምራዝ እንደድል ሊቆጠር የሚችል ይሆናል ማለት ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በሮጀር ታምራዝ የገንዘብ ምንጭ ዙሪያ የሴናተር ኬኔዲ ሃርኪን አስተዳደር በቴሌቪዥን ያስተላለፈው የገንዘብ ቁጥጥር የተመለከተ አጀንዳም ምንም ዓይነት ፍንጭ የማይሠጥ ደካማ ነበር፡፡ የሃገሪቱ ሪፐብሊካኖችም ሆኑ ዲሞክራት መሪዎች ስለዚህ ጉዳይ የጠነከረ እንቅስቃሴም ሆነ በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ወሬ የማነፍነፍ ነገር አይታይባቸውም ነበር፡፡ ምንም እንኳን የሮጀር ታምራዝ የገንዘብ ምንጭ ከKGB እና ሌሎች የራሺያ የፓለቲካ ተቋማት ጋር በተገናኘ አሜሪካንን ሊጠቅም አሊያም ሊጎዳ የሚችል ፓለቲካዊ ይዘት ሊኖረው ቢችልም ትኩረት ሊሠጠው የሚፈልግ ያለ አይመስልም ነበር፡፡

በአንድ ወቅት የኢሊኒዮው ዲሞክራቲክ ሴናተር እኔን በተመለከተ ያሉት ነገር ነበር፡፡ «ይህ ሰው የሚተዳደረው በምንድን ነው?» የሚለውና እኔ ላይ ያነጣጠረው «አንተ የምትሰራው በንግድ ምክር ቤት ውስጥ ነው!» የሚል መልዕክት ጥያቄያቸው ግልፅ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ሴናተር ዲክሩቢን የነበረው ሲሆን ሰውየው መናገር የፈለጉትም ግልፅ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ሴናተር ዲክሩቢን የነበረው ሲሆን ሰውየው መናገር የፈለጉትም በአሜሪካ ፓለቲካ ውስጥ ስለሚጠዘው የውጭ ገንዘብ የእኔ ዕውቀት CIA ይህን የተናገሩት በአሜሪካ ፓለቲካ ውስጥ ስለሚጠዘው የውጭ ገንዘብ የእኔ ዕውቀት CIA ከሚያቀርበው የውጭ ፋይናንስ ሪፓርት የሚልቅ መሆኑን ከመረዳታቸው በፊት ብቻ ነበር፡፡ ከዚያ በኃላ አፋቸውን መዝጋታቸውም ግልፅ ነበር፡፡ ወደ ጨለማና አዘቅት የሚወስድን ኑሮና የስራ ሁኔታ ምን ብለን ልንጠራው እንደምንችል አይገባኝም፡፡ የእኔ ሁኔታ እንደዛው ነው፡፡ ምናልባትም በፕላኔታችን ውስጥ በሚገኝ እጅግ አደገኛ የስራ ቦታዎችና ሁኔታዎች የምገኝ ነኝ፡፡ ኢራን ስፓንሰር የምታደርገው የሽብርተኝነት መረብ ውስጥ ልጠለፍ እችላለሁ፤ በአሜሪካ ኢምባሲዎች ላይ በሚያነጣጥሩ የቦምብ አደጋዎች የመገኘት ዕድልም ይኖረኛል፡፡ ታጂኪስታን ነበርኩ፤ በቤሩት የአሜሪካ ኢንባሲ ሲጋይም ተዓምር በሚመስል ሁኔታ በስፍራው ላልገኝ ተርፌያለሁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ህይወት ቢያንስ በሩብ ዓመታት ማግለፍ የቻልኩ እስገራሚ ሰው ነኝ ልባል እችላለሁ፡፡ አሁንም በዚሁ ስራ ውስጥ መገኘቴ ይበልጥ አስገራሚ መሆኑ አይቀርም፡፡

የአሜሪካም ሆነ የእኔ ዓላማ ተመሣሣይ ነው፡፡ ሀገራዊ ሀላፊነትን እወጣ ዘንድ ይጠበቅብኛል፡፡ በCIA ለሃገር መስዋዕት መሆን እንደግዴታ ነው፡፡ በCIA ምርመራ አንድ ውጤት ላይ መድረስ አለመቻልም ትልቅ ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ የቤሩቱን የአሜሪካ ኤምባሲ በቦምብ መጋየት እንውሰድ፡፡ ቦምቡን ማን ቀበረው? ምን ዓይነት ፈንጅዎች ነበሩ? የሚሉና ሌሎች ወንጀል ነክ ጥያቄዎችን መመለስ አለመቻል በCIA ውስጥ እንደሸንፈት የሚቆጠርበት ዘመን ነበር፡፡ ምክንያቱም CIA'ን የሚያክል ድርጅት እነኝህን ጥያቄዎች መመለስ ካልቻለ በቤሩት ከተከሰተው አደጋ በበለጠ በሌሎች ሃገራት የአሜሪካ ኢምባሲዎች ላይ ጥቃቱ ከፍ ባለ ደረጃ መከናወኑ የማይቀር ነው፡፡ ለሩብ ዓመታት ያህል በእንዲህ ዓይነት ውስብስብ ህይወት ውስጥ መቆየቴ ብዙ ነገር አስተምሮኛል፡፡ ምናልባትም ሳታውቀው ከሚጠልፍህ ወንጀል ራሴን ለማዳንም ጭምር የተማረኩት ትምህርት ይኖራል፡፡ አሁን CIA እንደ በፊቱ ጠንካራ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ በቀላሉ መልስ የሚገኝለት አይመስልም፡፡

በCIA ያሉ ሰዎች ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ከሆነ ነገሮች ሁሉ ሌላ አቅጣጫ ይይዛሉ፡፡ አሁን የሚታየውም ይኼው ነገር ይመስላል፡፡ ምናልባትም CIA ጤነኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

አቅጣጫ ሊያሲዝ በሚችል አቅጣጫ ለመጓተፍ ብቃቱ ይኖረኛል፡፡ ድርጅቱ በአደጋ ጊዜ ውስጥ ከገባም ራሴን የማድንበት መንገዶችን መማሬም እንደሚጠቅመኝ ግልፅ ነው፡፡

የኢራንን የአሸባሪነት ተግባር ለመግታት ጥሩ የሚባሉ ዕድሎች መኖራቸው ግልፅ ነው፡፡ ኢራን በአሸባሪነት ተግባሯ የምትታወቅና በአሜሪካ ዓይን ክትትል የሚደረግባት መሆንዋ ብቻ ሳይሆን የአሜሪካ ፖለቲከኞች ለራሳቸው ደህንነትና ጥቅም ሲሉ በኢራን ላይ ጥብቅ ክትትል ያደርጋሉ ከሚለው እምነት እንፃር ነው፡፡ ሼላ ሑሰሊን በኢራን የፓስዳራን ፓርቲ ላይ የተንጣጠረ ጥቃት መከላከሏን የኃይት ሃውስ መንግስት በከባር በደረሰው የቦምብ አደጋ የምርመራ ተግባር እጁን አስገብቷል የሚሉ መረጃዎች ደግሞ ከህሳቡ ጋር የማይጣጣሙ ነበሩ፡፡

ኮምፒዩተሯን በመከፈት ሊባኖስ ስለሚገኙት ታጋቾች ጉዳይ መረጃ ይኖረዋል ብዬ የማስበውን አንድ ሰው መፈለግ ጀመርኩ፡፡ በመጀመሪያ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ኢራን ታጋቾቹ በ1991 ዓ.ም እንዲለቀቁ ሲደረግ ለታጋቾቹ መፈታት አስተዋፅኦ የነበራት መሆኑን ሲሆን ሁለት የፓስድራን ፓርቲ ከፍተኛ ባለስልጣናት ማለትም ፈሪደም መኸዲነዛድና ሆሴን ሞስሌህ ታጋቾቹን ጎብኝተዋቸው የነበረ መሆኑን ነበር፡፡ ከዚያ በኃላ ባሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ደግሞ ሁለቱ ባለስልጣናት ኢማድ ሙግኒያህን ለመጎብኘት ወደ ዳማስቆ ሄደው የነበረ ሲሆን የጉዟቸው አላማም ኢሪን በታጋቾች ላይ እጇን ያነሣች መሆኑንና የእስላሚክ ጅሃድም እንዲሁም በጉዳዩ ዙሪያ ጣልቃ መግባት ማቆሙን ለማሣየት ነበር፡፡ ሁለቱ ባለስልጣናት ከሙግኒያህ ጋር ከተገናኙ በኃላ በኢራቱ መንፈሳዊ መሪ አያቶላህ ካሜኒ አዛዥነት ከሙግሀኒያህ ጋር እንደገና በቤሩት እንዲገኙ አድርገው የነበረ ሲሆን የግንኙነታቸው ተቀዳሚ አላማም ኢራን ሙሉ በሙሉ ከሽብርተኝነት ተግባሯ አለመውጣቷን ለማሳመንና እንዲያውም እንቅስቃሴውን አጠናክረው በሚቀጥሉበት ሁኔታ ዙሪያ ለመምከር ነበር፡፡

ይህንን ጉዳይ ከተረዳሁ በኃላ ለንፅፅር እንዲመቸኝ በ1987 ዓ.ም ታግተው የነበሩ ፈረንሳውያን የተለቀቁበትን ሁኔታ መመርመር ጀመርኩ፡፡ ፈረንሣውያኑ የተፈቱት ሊባኖሳውያኑ በተፈቱበት አኳኃን የነበረ ከመሆኑ በተጨማሪ በጉዳዩ ዙሪያ ሁለቱ የኢራን ባለስልጣናት እጃቸውን አስገብተው የነበረና የፈረንሳዩን ፕሬዚዳንት ዣክ ሺራክንና በፓስድራን ፓርቲ ውስጥ የሚገኙ ባለስልጣናትን እንዲገናኙና ጉዳዩን በምስጢር እንዲፈቱት ያስቻሉ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ነገሮችን ስመረምር የተረዳሁት ትልቅ ነገር ቢኖር ሙኸዲነዛድና ሞስሌህ በፓስድራን ፓርቲ ውስጥ ዋንኛ የሽብር ሞተሮች መሆናቸውን ነበር፡፡ የእነኚህ ኢራናውያን የሽብር ስራም ከ80 ዎቹ ጀምሮ የነበረና በተለይም ከእስራኤል ወረራ በኃላ በባላባክ ተመድበው መስራት ከጀመሩበት ጊዜ በኃላ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ የአሜሪካ ዜጎች በታገቱበት ወቅትም ሙኸዲና ሞስሌህ የተሣተፉ ሲሆን በተለይም «TWA flight 877» የተሰኘው አውሮፕላን በተጠለፈበት ወቅት ሙግኒያህን ሙኸዲ ነዛድ በቤሩት አለማቀፍ ኤርፖርት አብረው ታይተው ነበር፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

ሙኸዲ ነዛድ ከጓደኛው ሞስሌህ በበለጠ ሁኔታ በብዙ የሽብር ተግባራት ላይ የሚንቀሣቀስ ሲሆን የሎከርቢ አውሮፕላን እንዲጋይ ለሙሃመድ ሃፌዝ ዳልቃሙኒ ትዕዛዝ የሠጠ እርሱ እንደሆነም ይታመናል። ቪዬና ውስጥ የኩርዶች መሪ የነበሩት ሰው እንዲገደሉ ያደረገ እርሱ ነበር። በሳዑዲ አረቢያ «ኮባር ባራክስ» ላይ በደረሰው አደጋ በጦክስ አደረሱ ጥቃት እንዲሁም በፍራንክፈርቱ የአውሮፕላን ጠለፋና በሎከርቢው ፍንዳታ እጁ እንዳለበት በእጅጉ የሚጠረጠር አደገኛ የሽብር አቀናባሪ ነበር።

✡✡✡

«ሀዐ» የኢስላሚክ ጅሃድ ድርጅት ምህፃረ ቃላዊ መጠሪያ ነው። ድርጅቱ ከፓስዳራን ፓርቲ ባልተናነሰ ሁኔታ በመላው ዓለም ያሉ ሽብርተኞችንና የሽብር ጥቃቶችን የሚቆጣጠርና የሚያስፈፅም እጅግ አደገኛ ድርጅት ነው። በተለይ ደግሞ ስለዚህ ድርጅት የሰው ሃይል አደረጃጀት፣መሠረትና እንቅስቃሴ በትክክል መረዳት ስለማይቻል የድርጅቱን ውስብስብነትና አደገኛነት ያጎላዋል። እስላሚክ ጅሃድ የሽብር ጥቃቶች በደረሱበት አካባቢ ሁሉ የማይጠፋ ከሠመ የሚመስል አዘናጊ ድርጅት ነው። ድርጅቱ የከሰመ ነገሮች ሲብሱ ደግሞ አብሮ የከሠመ የሚመስል አዘናጊ ድርጅት ነው። ድርጅቱ የከሰመ ነገሮች ሲብሱ ደግሞ አብሮ የከሠመ በሚመስልበት ወቅት እኔም አሁን አሜሪካ አሊያም CIA የምናስበው እስላሚክ ጅሃድ በሚመስልበት ወቅት እኔም አሁን አሜሪካ አሊያም CIA የምናስበው እስላሚክ ጅሃድ የፓስድራን ፓርቲ የፈጠረው አደናጋሪ ስም ወይንም በጥቃት ጊዜ የመጨረሻ ርምጃዎችን የሚወስድ ጥላ ድርጅት መሆኑን ነው። ሌላው ቀርቶ CIA መንፈሳዊው መሪ አያቶላህ ናሆሚና ፕሬዚዳንት ራፍሳንጃኒ የሽብር ጥቃቶች መነሻም ሆነ መድረሻ ኢራቅ እንድትሆን ማድረጋቸውን የደረሠበት ቢሆንም የኢስላሚክ ጅሃድን ምንነት ግን በትክክል የደረሰበት አይመስልም ነገሮችን በጥልቀት ስመረምር የማገኛቸው መረጃዎችም ቢጠኗቸውም ሊጋፈጧቸው የሚያስገድዱ ናቸው። በተለይ ኢራን በአሜሪካ ላይ ምስጢራዊ ጦርነትን ማወጃንና አሜሪካም ይህንን ሁኔታ የምታውቀው የመሆኑን እውነት ማወቅም ቢሸሹትም የሚከተል እውነት ነው።

ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ የኢራን ጉዳይን የሚከተታተል አንድ የፓለቲካ አናሊስት አውቅ ነበር። ግለሰቡ ጂሞ ይሠኛል። ትዝ እንዳለኝ ጊዜ ሳላጠፋ አገኘሁት። በብዙ ጉዳዮች ላይ አወራን። በተለይም ስለ ኢራናውያኑ ሙኽዲ ነዘድና ጓደኛው ሞስሌህ ተጨዋወትን። ሁለቱን ግለሰቦች በተመለከተ የሠበሰብኳቸውን ፋይሎችም አሣየሁት። በመቀጠልም ሁለቱ ሰዎች የሚሠሩት ለማን እንደሆነ ጠየኩት። አንድ ዶክመንት ወደፊቴ እየገፋልኝ በአፉ ደግሞ መናገሩን ቀጠለ «ከሞስሌህ ጋር የተዋወቅነው በ1983 ዓ.ም ሲሆን። በጊዜው በሌላ ስም ነበር የተዋወቀኝ። ቀጥሎ ሞስሌህ የሚሠኘውን ሌላ ስሙን ለማወቅ ችያለሁ። እውነት ለመናገር ግን ሙሉ ስሙን አላውቀውም። ዞሮ ዞሮ ግን በጊዜው ሞስሌህ ትኩረት የሚደረግበት ስላልነበር ብዙም አላጠናሁትም ነበር። በተለይም ከኢራን መንግስት የተሠጠው ምንም ዓይነት የስልጣን ደረጃ እንደሌለው ነበር የማውቀው። ቆይቶ ሲገባኝ ግን ኢስላሚክ ጅሃድን የመሠረተው ሞስሌህ ነው። ምክንያቱም ምስሌህ ከሙግኒያህ ጋር ግንኙነት ያለው ከመሆኑም በላይ ከፋታህ ንቅናቄ ሰዎች ጋርም ከፍተኛ ግንኙነት ነበረው። ነገር ግን ኢስላሚክ ጅሃድን ሞስሌህ መሠረተው ቢባልም ድርጅቱ ሲመሠረት ምንም ዓይነት የስልጣን ምልክቶች የድርጅቱ አርማዎች ያልነበሩት በመሆኑ ነገሮች ግልፅ አይደሉም ነበር። ስለሆነም አንተ እንዳልከው ኢስላሚክ ጅሃድ ኢራን የምትጠቀምበት ልበሰድ ድርጅት ነበር ማለት ይቻላል።» አለኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እሱን እኔም ገምቻለሁ» አልኩትና «ለመሆኑ ግን CIA ይህንን ጉዳይ ያወቀው መቼ ነበር?» ብዬ ጠየኩት፡፡

ጂም ከቦርሳው ውስጥ የተወሠኑ ፋይሎችና እያወጣ «ከመጀመሪያ ጀምሮ ያሉትን ነገሮች ባሳይህ ይሻላል ብዬ ነው» በማለት ፋይሎቹን አወጣ «ግን ለምንድን ነው ... ይህን ነገር ቤሩት እያለሁ ማወቅ ይገባኝ ነበርኮ?» የሚል ጥያቄ ሳነሳለት ጂም «ሁሉም ሰው በወቅቱ ታግተው በነበሩት ሠዎች ጉዳይ ተወጥሮ ስለነበር ይህንን ነገር በጊዜው ማሠብ ይቸግር ነበር» ብሉ መለሰልኝ፡፡

«በ 1983 በተፈፀመው የኢምባሲ የቦምብ አደጋና ስለ ኢራን ምን እናውቅ ነበር?» በማለት የመጨረሻ ጥያቄዬ ነው ብዬ ያሠብኩትን ጥያቄ ለጂሞ ስነዘርኩለት፡፡ ጂሞ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ይበልጥ እየተስጠጠ አየር ከሳበ በኋላ ቦርሣ ውስጥ ባለሶስት ገፅ ፋይል አውጥቶ ሠጠኝ፡፡

ፋይሉ ከአንደኛ ደረጃ ምንጭ ተገኘ የሚባልና በቤሩቱ የቦምብ አደጋ የኢራን እጅ በትክክል እንዳለበት የሚናገር ነበር፡፡ አሜሪካ ከኢራን ጋር መልካም ግንኙነትን ለመመስረት ባሠበችበት ወቅት ሙኽዲ ነዛድ በዩናይትድ ስቴትስና በፕሬዚዳንት ሙሃመድ ካታሚ መካከል ሆኖ ይሠራ እንደነበርም መረዳት የቻልኩት ነገር ነበር፡፡ ይህ የሆነው ጀርመን ሃገር ሜንዝ ከተማ ውስጥ ኦክቶበር 29/1986 ዓ.ም በተደረገ ስብሠባ ሲሆን በስብሰባው ያየሁት ሰውና ራሡን ኢዮብ ሞዛፋሪ ብሉ የሚጠራው በኃላ ደግሞ እውነተኛ ሰሙ መኽዲ ነዛድ መሆኑ የተረጋገጠው አሜሪካና ካታሚ በአንድ ጉዳይ ላይ እየተወያዩ ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነበር፡፡ ኢራናዊው ካታሚ ለአሜሪካ ይሠራል ተብሉ ሊጠበቅ ባይችልም ሃገሪቱ ከኢራን ጋር ለሚኖራት ግንኙነት የሆነ ሚና ይጫወታል የሚል ስሜት ያለው ስሌት እየተጫወተች ያለች ትመስል ነበር ... ሌላም ማየትና ማወቅ የፈለኩት ጉዳይ ነበር፡፡ ስለሙግኒያህና ኦሳማ ቢንላደን ግንኙነት፡፡ ቢንላደን ፓኪስታን ኢስለማባድ በሚገኘው የግብፅ ኢምባሲ ላደረሰው የቦምብ ጥቃት እጁ ነበረበት፡፡ ስድስት ወራት በኃላ ደግሞ የኦሳማ ቢንላደን አደገኛ ሰውና የሙግኒያህ ሌላው ተወካይ በቤሩት ተገናኝተው መወያየታቸው ታውቆ ነበር፡፡ በርግጥ ይሄ ነገር ቀላል ይመስላል፤ ሽብርተኝነት እንዴት እንደሚከናወን ለሚያውቅ ሰው ግን የሁለቱን ሰዎች ግንኙነት በዋዛ የሚያየው አይሆንም፡፡

እንደኔ እምነት እንደዚህ የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ሁሉ አሜሪካንን የሚያስጉና በአሜሪካ ላይ የሚያነጣጥሩ ናቸው፡፡ ቢንላደንም ይሁን ሳዳም፤ ያሲር አራፋትም ሆኑ ሌላ የኢራን ሽብርተኛ ቡድን ወይም ደግሞ ሌሎች ሽብርተኞች በክሊንተን አስተዳደር ሲጠፉ የሚገባቸው ለአሜሪካ መቼም ቢሆን ጤና ሊሠጡ የማይችሉ ናቸው፡፡ ከክሊንተን በፊት የነበሩት ቡሽና ሬገን በዚህ በኩል ጠንካራ ነበሩ ማለት አይቻልም፤ በዚህ ጉዳይ CIA'ና በፔንሱሉቬንያ ምክር ቤት ጠንካራ ናቸው የሚል አቋሜን ባንፀባርቅ ይሻላል፡፡ ነገር ግን የእነሱም ክፍተቶች ቀላላ አይባሉምና ሁኔታው እሁንም ከማስጨነቅ አያልፍም፡፡

☆☆☆

በህዳር 1997 መጨረሻ አካባቢ ስራዬን ለመልቀቅ ከራሴ ጋር ሙግት ገጠምኩኝ፡፡ የFBI እና CIA ኢንስፔክተር ጀኔራል ስለ ኤጀንሲያችን ማወቅ የምፈልገውን ነገር ለመንገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ዝግጁ መሆናቸውን ነገሩኝ። በቃ የፖለቲካ ነገር እንደዚሁ ነው? ብዬ ራሴንም ጠይቄያለሁ። CIA'ን የተቀላቀልኩት ለማንም ያልተገለጠ እውነትን አገኛለሁ ብዬ ነበር። በተወሠነ ደረጃ ስኬታማ ነበርኩ ማለት እችላለሁ። ባለፉት የመጨረሻ ወሮች የቤሩቱን የቦምብ ጥቃት ጉዳይ ለመፈልፈል ችያለሁ። አደጋውን ኢራን እንዳቀናበረችውና ፋታህ ተግባራዊ እንዳደረገውም ለደርስበት ችያለሁ። የትኛውም የልቦለድ ደራሲ ሊገምተው በማይቻለውና የሚሆን በማይመስለው ተዓምራዊ ትዕይንት ሁሉ አልፌያለሁ። እነኚህ ሁሉ ነገሮች ቀላል አይደሉም። ከዚህም አንፃር ለ21 ዓመታት ያገለገልኩትን CIA'ን በሚገባ እንደጠቀምኩት ቢያንስ ለራሴ እርግጠኛ መሆን እችላለሁ። አሁን CIA ከ21 ዓመታት በፊት እንደነበረው ነው ብዬ አላስብም። በፍጥነት እየተሰወጠ ያለ ይመስለኛል። ለውጡ አሉታዊም አዎንታዊም ሊሆን ይችላል! የሆነ ሆኖ ለውጠ ከእኔ ጋር የማጣጣም አይደለምና የመሄጃዬ ጊዜ አሁን መሆኑ ተሰምቶኛል።

አንድ አርብ ዕለት ከሠዓት በኃላ ወደ ዳይሬክቶሬት ኦፐሬሽን ዋና ዳይሬክተር ጃክ ዳውኒንግ ቢሮ አመራሁ። ለጊዜው ያገኘሁት ረዳቱን ነበር። የሆነው ሆኖ ያዘጋጀሁትን የስራ መልቀቂያ ወረቀት አስረክቤው መወጣቴ ግድ ነበር። ይህን ካደረኩ ከጥቂት ሰዓታት በኃላ ጃክ ዳውኒንግ ሊያገኘኝ እንደሚፈልግ ተናገረኝና ዳውኒንግን አገኘሁት። ሊያባብለኝ ሞከረ CIA ወደቀድሞ ሁኔታው እንደሚመለስና ለእኔም ሁሉም ነገር ምቹ እንደሚሆንልኝ አስረዳኝ። በአይኖቹ ውስጥ ግን የማባበያ እንጅ እውነትን የሚያሣዩ ነገሮችን መመልከት ስላልቻልኩ ልቀበለው አልቻልኩም። CIA እንደገና ወደ ቀድሞ ጥንካሬው ለመመለስ አሰርት አመታት እንደሚያስፈልጉት እየተሠማኝ ከመጣ ቆይቷል። ዳውኒንግ «በመልቀቅህ እጅግ አዝኛለሁ። ለረጅም ዘመናት CIA'ን በቀናነት አገልግልሃል! ለዚህ ስራህ የሜዳሊያ ሽልማት የሚገባህ ሰው ነህ» ብሎኝ ተሰያየን። ዳውኒግም ቃሉን ጠብቆ ያሰውን ነገር አደረገው።

በመጋቢት 11/1998 ዓ.ም የCIA'ን የሜዳሊያ ሽልማት ተበረከተልኝ። በሜዳሊያው ላይ የተፃፉት ነገሮች በርግጥም CIA'ን ለረጅም ዘመናት ማገልገሌን ብቻ ሳይሆን ለድርጅቱ የስራኃቸውን እጅግ ጠቃሚ ነገሮችን የሚናገሩ ስለነበሩ በየጊዜው አነባቸውና በስራዬ ከማገኘው እርካታ በበለጠ ደስታን ያጎናፅፈኝ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዝክረ - ታሪክ

የአለም ግዙፍ አጀንዳ የነበረው የመስከረም 11ዱ የሺብርተኞች ጥቃት ሲደርስ ዋሽንግተን ዲ.ሲ.በሚገኘው ቤቴ ውስጥ ነበርኩ። አደጋው ለምን ዋሽንግተን ላይ እንዳላነጣጠረ ለአብዛኞቻችን ሊገርመን ይችላል። ምናልባትም CIA አሊያም ደግሞ FBI ዋሽንግተንን ከዚህ አይነቱ አደጋ አተረፉት ተብሎም ሊታሰብ ይችል ይሆናል። ነገር ግን አይደለም። ዋሽንግተን ከመስከረም አስራ አንዱ የሽብር ጥቃት የተረፈችው እፍኝ በማይሞሉ አሜሪካውያን ዜጎች ጥረትና ቆራጥነት ነበር።

በኒውዮርኩ አደጋ የተከሰተውን ሞትና የንብረት መውደም ስመለከት ደግሞ የዋሽንግተን ከጥቃቱ መትረፍ የኒውዮርኩን ጥቃት እጅግ ዘግናኝ እንዲሆን ያስገደደው መሆኑ ሰማኝ።

በመስከረም 11/2001 የደረሠው አደጋ በአሜሪካ ታሪክ እጅግ ዘግናኙ ነበር። በተለይ ደግሞ ከአደጋው እስከፊነት ባሻገር ያለው የሽብርተኞቹ የጥቃት ቅንብርና መረብ እጅግ ውስብስብና ተግባሩ ለበጎ ቢሆን ኖሮ አቀናባሪዎቹን እጅግ እንድናደንቃቸው የሚያደርግ ነበር። የአሜሪካ ጠላቶች አሜሪካንን በሚገባ የተበቀሉበት ድርጊት ነበር ሊባልም ይችላል። ምናልባት በአሜሪካ ላይ ቀስታቸውን ያነጣጠሩ ሽብርተኞቹ ከኒውዮርኩ አስከፊ ውድመት በኋላ ድምጥማጣቸው ቢጠፋ! ቀንደኛ መሪያቸው ኦሳማ ቢንላደን ቢያዝና ቢገደል ወይንም ደግሞ መደበቂያቸው የሆነው አፍጋኒስታን ዋሻና ጉድባ እንደጥንቱ ወደ ድንጋይ ዘመን እንድትሰወጥ ቢደረግ እንኳን የሚቆጫቸው አይሆንም ነበር። በርግጥም መስከረም 11/2001 ዓ.ም አሜሪካ የማትዘነጋው ታሪካዊ ሽንፈት የቀመሠችበትና ሽብርተኞች በበኩላቸው ትልቅ የሚሉትን ድል የተጎናፀፉበት ታሪካዊ ቀን ነበር ማለት ይቻላል።

✡✡✡

የኒውዮርክ ህንፃዎች ውድመትና እልቂት የአሜሪካንን ህልውና ያናጋ የኦሳማ ቢላንደንን ጥንካሬ ደግሞ ያሳየ ነበር። በተለይም ደግሞ ቢንላደን በአረቡ አገራት እጅግ በርካታ ተከታዮች ያሉትና ቢሞትም እንኳ ያቀዳቸው ነገሮች ሁሉ እንደሚከናወኑ የታየበት አጋጣሚም ነበር።

አልቃይዳ ሲነሣ ሁሉም ሰው የሚያስታውሰው ቢንላደንን ሲሆን ይችላል። ነገር ግን የአልቃይዳ ጥንካሬ በቢንላደን ብቻ የተመሠረተ አይደለም። ቢያንስ በቢንላደን መንፈስ የሽብር መረቡን የሚቀላቀሉ የዓረቡ ዓለም ወጣቶች የትየለሌ ናቸው። ከዚህም ሌላ ኢራንና አልቃይዳ መልካም ግንኙነት አላቸው። ቢንላደን በቤሩት ያደረሰውን የአሜሪካ ኢምባሲ ፍንዳታ በዋነኝነት ካቀናበረው ኢማድ ሙግኒያህ ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ያደርግ እንደነበረ ግልፅ የነበረ ሲሆን CIA'ን ከመልቀቁ በፊት ደግሞ ቢን ላደን ለወጭው መጠንሰሬ የሽብር ጥቃት



t.me/OLDBOOKSPDF

(ምናልባትም እንደ መስከረም አስራ አንዱ የኒውዮርክ አደጋ) ከኢራን ጋር ግንኙነት በመፍጠር ዝግጅት ያደርግ እንደነበረ ደርሰንበት ነበር። ነገር ግን ቢንላደን ያሰበውን ወይንም ሲፈፅም ያቀደውን ነገር የማክሸፍ ብቃቱ አልነበረንም። ቢንላደን አንድ አደጋ ሲጥል ካሰበ ምናልባት መቼ፣ እንዴት፣ የትና በምን መጠን የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ አይቻል እንጂ አደጋው መከሰቱ የማይቀር እንደሚሆን ይታመን ነበር።

☼☼☼

ከCIA ከለቀኩኝ በኃላ ወደ ቤሩት ተመልሼ ከአንድ የቀድሞ የCIA'ን ኦፊሰር ጋር በመሆን የኮምፒዮተር መደብር ከፈትኩኝ። ይህ ሁኔታም ቀድሞ ቤሩት እያለሁ የማላውቃቸውን ሰዎች እንዳውቅ ረዳኝ። አንድ ቀን ግን የኢማድ ሙግኒያህ የቅርብ አማካሪ የነበረ ሰው ከእኔ ጋር የኮምፒዩተር ካምፓኒ መክፈት እንደሚፈልግ ሃሳብ አቀረበልኝ። የሆነው ሆኖ ግን ከዚህ ሰውዬ ይልቅ የእኔ ቅርበት የላቀ የነበረው በጊዜው ደማስቆ ይኖር የነበረው የባህረ ሰላጤ ንጉሳዊ ቤተሰብ አባል የነበረ ሰው ነበር። የህ ሰው የአጎቱን ልጅ ለመገልበጥ የሞከረ ያልተሳካ መፈንቅለ መንግስት ያካሄደ በዚህም ምክንያት በደማስቆስ በስደት እንዲኖር የተገደደ ሰው ነበር። ከዚህ ሰው ጋርም እኔና አማካሪዬ በእርሱ ቤትና በእኛ ቢሮ መካከል በሚገኝ አንድ ስፍራ እየተገናኘን እንጫወት ነበር። በታህሳስ ወር 1997 ዓ.ም ይህ ሰው ለእኔና ለቀድሞው የCIA ኦፊሰር አማካሪዬ አንድ ታሪክ ነገረን።

እርሱ በሃገሩ መንግስት የፓሊስ አዛዥ ሆኖ ይሠራ በነበረበት ወቅት የሀገሩ መንግስት ኦሳማ ቢንላደን የሽብር ተግባር የሚሳተፉ ሁለት ሰዎችን መመደቡን ደረሰበት። የእነኚህ ሁለት ሰዎች ስምም ሻወኪ ኢስላምቡሊ እና ካሊድ ሻይክ መሀመድ ይሰኝ ነበር። ኢስላምቡሊ በ1981 አንዋር ሳዳትን የገደለው ግለሰብ ወንድም ሲሆን ካሊድ ሻይክ ደግሞ የስለጠነበት ሙያ የአውሮፕላን ጠለፋ ብቻ የሆነ ሰው ነበር። የሆነው ሆኖ የእነኝህን ሰዎች እንቅስቃሴ የደረሰበት FBI ግለሰቦቹን በቁጥጥር ስራ ሲያውላቸው ሲፈልጋቸው አደጋ ቢገጥማቸው ከለላ እንደሚሰጣቸው ቃል የገባላቸው መንግስት በፍጥነት ካገር እንዲወጡ በማድረግ በፕራግ ውስጥ እንዲኖሩ አደረገ። የቀድሞ የፖሊስ ባልደረባ የሚነግረን ታሪክ በርግጥም የሚደንቅና በርካታ ነገሮችን እንደገና ወደኃላ ተመልሰን እንድናውጠነጥናቸው የሚያደርግ አይነት ነበር። የነገረን ነገር ውስብስብና ማንም ሊገምተው የማይቻለውም ነበር።

ይህ ከሆነ ከሶስት ዓመት በኃላ ማለትም በ2001 ዓ.ም አንድ ሌላ የፖሊስ ባልደረባ ወዳጄ ስለቀድሞው የፖሊስ ባልደረባና የመንፈንቅለ መንግስቱ ተዋናይ ምስጢር ነገረኝ። ሰውየው ኦሳማ ቢንላደንን በተመለከተ እጅግ በርካታ መረጃዎች እንዳሉትና በተለይ ደግሞ በየመንና ሳዑዲ አረቢያ እንዲሁም በባህረሰላጤው አካባቢ ስላሉት የቢንላደን ህዋሶች በርካታ መረጃ የያዘ ሰው መሆኑን አስረዳኝ።

በነሀሴ 2001 ዓ.ም ላይ በዚሁ የሚሊታሪ ኦፊሰር ወዳጄ አጋዥነት ከሳዑዲ አረቢያው መከላከያ ሚኒስቴር ልዑል ሱልጣን ቢን አብዱላዚዝ ጋር ተገናኘሁ። የሆነው ሆኖ ከልዑሉ ጋር ያወራንበት ዋንኛ ጉዳይ ሳዑዲ አረቢያ የምትከተለው ሹብርተኝነት ፖሊሲ CIA ከሚከተለው ጋር ያልራቀ መሆኑን ከመግለፅ ያልዘለለ ሆነ።

☼☼☼



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ሁሉንም ሰው የምናዳምጥበት ጊዜ ይመስለኛል። መልዕክቱ የቱንም ያህል ሹካራና የመረረ ይሁን መረጃዎችን መሰብሰብ ግድ ነው።

CIA ግለሰቦችን በማነፍነፍ መረጃ ከማግኘት የተሻለ ምርጫ የለውም። ከ20 ዓመታት በፊት የተቀላቀልኩት CIA ያልተሰማ የሚሰማ፤ ያልታየ የሚያይ ነበር። ለዚያውም እንዳሁኑ የሳይንስና ቴክኖሎጅ ድጋፍ ሳይኖረው። የአሁኑ ግን የተለየ CIA ነው። እንዲህ ሆኖ ብዙ መንገዶችን መራመድ ይቸግረዋል። በዚህ ሁኔታ በCIA ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ድርጅቱ ነፃነትን ያጎናፅፋቸዋል ተብሎም አይጠበቅም።

አሜሪካና ምዕራባውያን በሙሉ ጦርነት ላይ ናቸው። ጦርነት የገጠሙትም ታንክና አውሮፕላን እንዲሁም የጦር መርከብ ካላቸው ሳይሆን ምንም ዓይነት የጦር ማዛሪያ ካልታጠቁ አካላት ጋር ነው። እንዲህን ያለ ጠላት ማሸነፍ የሚቻለው ደግሞ ጦር በመታጠቅ ሳይሆን በስለላ ነው። በስለላ ጠላትን ማወቅ፤ በስለላ ዕቅዳቸውን ቀድሞ መረዳት፤ በስለላ አደጋ ሊጥሉ ሲዘጋጁ ማገድ፤ በስለላ ሊጥሉ ያቀዱትን አደጋ ማክሸፍ CIA'ም ሆነ አሜሪካ ጠላቶቻቸውን የሚያሸንፉበት አስተማማኝ መንገድ ነው። ይህ ይሆን ዘንድም ለአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለበርካታ ጊዜያት ምናልባት ለዘመናት ስመኝ ኖሬያለሁ።

## ተፈጸመ



t.me/OLDBOOKSPDF



ራሲን በማጋለጥ ታሪኩን ይፋ ያረግኩበት ምክንያት ለሩብ ምዕተ ዓመት ያገለገልኩትን CIA ምን ነካው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሆናል በማለት ነው፡፡ ተቋሙን ከውድቀት ለማንሳት ምን መደረግ ይኖርበታል ለሚለውም ጥያቄ ምላሽ ለማፈላለግም ሞክሬአለሁ፡፡ የመስከረም አስራ አንዱን ጥቃት የአንድ ስህተት ብቻ ሳይሆን እንደሰንሰለት የተያያዙ የብዙ ስህተቶች ድምር ውጤት እንደሆነ እስገነዝባለሁ፡፡

ጀርመኖች እንደብሪታንያውያን፣ ፈረንሳዩችና፣ ሳውዲ አረቢያ ሁሉ ጉድ አርገውናል፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው የምንፈልገውን መረጃ አሊያም እንደተቋምነታቸው የመረጃውን ፍሰት አልለቀቁልንምና፡፡ ስህተቶቻችንን አርመን በሽብርተኝነት ላይ ደግሞ የበላይነት መቀዳጃ ቀላል እንዳልሆነ እናውቀዋለን፡፡ ግን ሊደረግ የሚችል ነው፡፡ እናም ታዲያ ሁሉም ነገር መጀመር ያለበት የ CIA ባለስልጣናትን ወደ ትክክለኛው መስመር በማስገባት ሰራተኞቻቸውን በጥራትና በብቃት እንዲመለምሉ በማድረግ የመረጃ ምንጮችን በመስኪዶችና በሌሎችም የሽብርተኞቹ መጠለያ ባሉባቸው ስፍራዎች እንዲያነፈንፉ በማድረግ ይሆናል፡፡ ይህም የሽብርተኞችን የጥፋት ጥንስስ ወደ አስፈሪና አስደንጋጭ ሰበር-ዜና ከመቀየርና የአሳዛኝ ፊልም ድራ ከመሆን ይታደገናል፡፡

[illegible] ወደ [illegible] ያቋቋሙ ጠረው በአጋጣሚ አለመሆኑን ሲያጤኑት [illegible] ሙ ዘግናኝ ጋሻ አጃግሬዎቹ፣ በዋጋቢሶቹ [illegible] መሃል በነበረው ሽኩቻ እና በሌሎችም [illegible] ጥቃትና ፍራቻ በሚያጥቡት ወቅት [illegible] መጠር የነበረበት ሩሲ እንጋፋ ተቋም የራሱን [illegible]

[illegible] KGB [illegible] የለሽ ድርጅት ምክጢር ምን ይመስላል?

[illegible] የሰለሳ ድርጅት በዛሰምዶ አጠራር CIA [illegible] ማጠና መጠን ድርጅቱ በዚህ ዕድሜው [illegible] ያልተሰያፔዉን ታሪኮቹን አስተናግዷል፡፡ [illegible] በደች ለበላኒ ተግባራት እየመደበች በአብዛኛው [illegible] የሰለላ ተቋም ማለትም CIA'ን [illegible] ድርጅቱ አውነተኛው ዓላማውና ሚስጢሩ ምንድነው?

Cover Design- Lesie Manayea Tel 0912437173

95 ብር

t.me/OLDBOOKSPDF